# የኢትዮጵያ ታሪክ

## ከንግሥተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል



ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# የኢትዮጵያ ታሪክ

## ከንግሥተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል

ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ

በ፲፱፻፳፫ ዓ ም ተጻፈ

የልጅ ልጃቸው ወይዘሮ ሡናይትተክለማርያም ለመጀመሪያ ጊዜ
በ፲፱፻፺፱ ዓ ም አሳተሞት

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ



አባቶች ሆይ! ከመጀመሪያው የነበረውን አውቃችኋልና እጽፍላችኋለሁ።

ጐበዞች ሆይ! ክፉውን አሸንፋችኋልና እጽፍላችኋለሁ።

ልጆች ሆይ! አብን አውቃችኋልና እጽፍላችኋለሁ።

የመጀመሪይቱ የሐዋርያው ዮሐንስ መልዕክት ምዕ ፪ ቁ ፲፫

የመጽሐፉ ደራሲ ብላታን ጌታ ኅሩይ

# ማውጫ

መቅድም ........................................................................ 13
ምዕራፍ ፩ ...................................................................... 41
ከንግሥተ ሳባ እስከ ባዜን ድረስ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ፩ሺ ፲፫ እስከ ፰ ዓመተ ምሕረት ................................................................ 41
ምዕራፍ ፪ ...................................................................... 50
ከባዚን ጀምሮ የቀዳማዊ ምኒልክ መንግሥት ወደ ነገደ ዛጉዌ እስከፈለሰበት እስከ ድልነዓድ ድረስ። ...................................................... 50
ምዕራፍ ፫ ...................................................................... 62
የኢትጵያ መንግስት ከቀዳማዊ ምኒልክ ዘር ወደ ዛጉዌ ዘር ካለፈበት ከ፱፻፲፪ ጀምሮ ከዛጉዌ ወደ ቀዳማዊ ምኒልክ ዘር እስከ ተመለሰበት እስከ ሺ፪፻፵፫ ዓመተ ምሕረት ስለ ዛጉዌ መንግሥት ማስረጃ በአጭሩ እንጽፋለን። ............................... 62
ምዕራፍ ፬ ...................................................................... 68
የኢትዮጵያ መንግሥት በኃይል ወደ ዛጉዌ ዘር ካለፈ ከ፫፻፴፫ ዓመት በኋላ እንደ ገና ወደ ቀዳማዊ ምኒልክ ዘር ወደ ይኩኖ አምላክ ከተመለሰበት ከሺ፪፻፶፫ /ሺ፪፻፶፫/ ጀምሮ ልብነድንግል እስከ ነገሠበት እስከ ሺ፬፻፸፪ /ሺ፭፻/ ዓመተ ምሕረት። .... 68
ምዕራፍ ፭ ...................................................................... 75
ስለ አቤቶ ያዕቆብ ............................................................ 75
ምዕራፍ ፮ ...................................................................... 76
ስለ አቤቶ ነጋሢ ............................................................. 76
ምዕራፍ ፯ ...................................................................... 79
ስለ ስብስቴ /ስብስትያኖስ/...................................................... 79
ምዕራፍ ፰ ...................................................................... 85
ስለ መርድ አዝማች አብዬ .................................................... 85
የክርስትና ስሙ ቀዳሜ - ቃል ................................................. 85
ምዕራፍ ፱ ...................................................................... 87
ስለ መርድ አዝማች አምኃ ኢየሱስ። ......................................... 87
ምዕራፍ ፲ ...................................................................... 90
ስለ መርድ አዝማች አስፋ ወሰን .............................................. 90
የክርስትና ስሙ ቴዎድሮስ ..................................................... 90

ምዕራፍ ፲፩ ........ 95
ስለ መርድ አዝማች ወሰን ሰገድ። ........ 95
የክርስትና ስሙ ወልደ ጊዮርጊስ ........ 95
ምዕራፍ ፲፪ ........ 98
ስለ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ........ 98
ምዕራፍ ፲፫ ........ 101
አቶ መተኰ ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ስለ መከዳቱ ........ 101
ምዕራፍ ፲፬ ........ 108
በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘመን የውጭ አገር ........ 108
ሰዎች ወደ ሸዋ ስለ መምጣታቸው ........ 108
ምዕራፍ ፲፭ ........ 116
ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ቅብዓ መንግሥት ተቀብተው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለመሆን ስለ ማሰባቸው ........ 116
ምዕራፍ ፲፮ ........ 118
ስለ አቤቶ ኃይለ መለኮት ........ 118
ምዕራፍ ፲፯ ........ 122
ስለ አቤቶ ምኒልክ ........ 122
ምዕራፍ ፲፰ ........ 123
ስለ አጼ ቴዎድሮስና ስለ አቤቶ ምኒልክ ........ 123
ምዕራፍ ፲፱ ........ 127
አቤቶ ዳርጌ ወደ አጼ ቴዎድሮስ ስለ መሄዳቸውና ስለ መታሠራቸው ........ 127
ምዕራፍ ፳ ........ 130
አቤቶ ምኒልክ ከመቅደላ አምልጠው ወደ ሸዋ ስለ መመለሳቸው። ........ 130
ምዕራፍ ፳፩ ........ 131
ስለ አቤቶ ምኒልክና ስለ አቶ በዛብህ ጦርነት ........ 131
ምዕራፍ ፳፪ ........ 133
ስለ አቶ በዛብ የሞት ፍርድ ........ 133
ምዕራፍ ፳፫ ........ 136
ስለ አጼ ቴዎድሮስ ዕረፍት ........ 136

ምዕራፍ ፳፬ ............................................................ 139
ንጉሥ ነገሥት ምኒልክ የሸዋን መንግሥት አደላድለው ስለ መያዛቸው.......... 139
ምዕራፍ ፳፭ ............................................................ 142
ስለ ወይዘሮ ባፈና መከዳት ............................................ 142
ምዕራፍ ፳፮ ............................................................ 148
አጼ ዮሐንስ ወደ ሸዋ ስለ መምጣታቸው .............................. 148
ምዕራፍ ፳፯ ............................................................ 152
ስለ ሃይማኖት ክርክር ነገር............................................ 152
ምዕራፍ ፳፰............................................................ 156
አጼ ዮሐንስ ለራስ አዳል ዘውድ ሰጥተው ሲያነግሡ ንጉሥ ምኒልክን ስለ መጥራታቸው። ............................................................ 156
ምዕራፍ ፳፱ ............................................................ 159
ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጠብ ስለ መጀመራቸው .............. 159
ምዕራፍ ፴............................................................ 159
ስለ እምባቦ ጦርነት............................................ 159
ምዕራፍ ፴፩ ............................................................ 165
ስለ ንጉሥ ምኒልክና ስለ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ዕርቅ......................... 165
ምዕራፍ ፴፪ ............................................................ 169
ስለ ልዑል ራስ አርአያና ስለ ልዕልት ወይዘሮ ዘውዲቱ ጋብቻ .................. 169
ምዕራፍ ፴፫ ............................................................ 173
ስለ ወይዘሮ ጣይቱ ትውልድና ንጉሥ ምኒልክ ወይዘሮ ጣይቱን ስለ ማግባታቸው ............................................................ 173
ምዕራፍ ፴፬ ............................................................ 176
የንጉሥ ምኒልክና የኢጣሊያኖች ወዳጅነት አጀማመር .......................... 176
ምዕራፍ ፴፭............................................................ 181
ስለ አፄ ዮሐንስና ስለ ምስሮች /ስለ ግብፆች/ ጦርነት። .......................... 181
ምዕራፍ ፴፮ ............................................................ 183
በአፄ ዮሐንስና በእስላሞች መካከል ስለ ተነሣው ሁከት። ...................... 183
ምዕራፍ ፴፯............................................................ 186
ንጉሥ ምኒልክ እንደ ገና ወደ ወሎ ስለመሄዳቸው። ............................ 186

ምዕራፍ ፴፰ ........................................................................ 189
አጼ ዮሐንስ ወደ ወሎ ስለ መምጣታቸውና ንጉሥ ምኒልክም ለመገናኘት ወደ ወሎ ስለ መሄዳቸው።......................................................................... 189
ምዕራፍ ፴፱.......................................................................... 190
በአጼ ዮሐንስና በኢጣልያኖች መካከል ጠብ ስለ መጀመሩ ..................... 190
ምዕራፍ ፵............................................................................. 192
ንጉሥ ምኒልክ ወደ ሐረርጌ ስለ መዘመታቸው.................................. 192
ምዕራፍ ፵፩ .......................................................................... 194
ራስ አሉላ ከኢጣልያኖች ጋራ ተዋግተው ድል ስለ ማድረጋቸው ............... 194
ምዕራፍ ፵፪ .......................................................................... 197
የእንግሊዝ መላክተኛ ሰር ፖርታል የሚባለው ወደ አጼ ዮሐንስ ስለ መምጣቱ 197
ምዕራፍ ፵፫ .......................................................................... 203
ንጉሥ ምኒልክ በአጼ ዮሐንስ ፈቃድ ወደ ወሎ ስለ መሔዳቸው። ............. 203
ምዕራፍ ፵፬ .......................................................................... 204
አጼ ዮሐንስ ከኢጣሊያኖች ጋራ ለመዋጋት ወደ ሰሐጢ ስለ መውረዳቸው .... 204
ምዕራፍ ፵፭.......................................................................... 206
ንጉሥ ምኒልክ ከወሎ ቤጌምድር ሄደው በጐጃም አድርገው ወደ ሸዋ ስለ መመለሳቸው ................................................................................ 206
ምዕራፍ ፵፮ .......................................................................... 208
አጼ ዮሐንስ ጐጃምን ስለ ማጥፋታችው ........................................ 208
ምዕራፍ ፵፯ .......................................................................... 210
አጼ ዮሐንስ በንጉሥ ምኒልክ ስለ መቀየማቸውና ወደ ልዑል ራስ ዳርጌ የወቀሳ ቃል ስለ መላካቸው።......................................................................... 210
ምዕራፍ ፵፰.......................................................................... 219
ስለ አጼ ዮሐንስ ዕረፍት .......................................................... 219
ምዕራፍ ፵፱ .......................................................................... 225
ንጉሥ ምኒልክ ወደ ወሎ ሲሄዱ የአጼ ዮሐንስን ዕረፍት ስለ መስማታቸው.... 225
ምዕራፍ ፶ ............................................................................ 227
በአጼ ምኒልክና በኢጣሊያ መንግሥት መካከል በውጫሌ ሥፈር ስለ ተደረገው ውል። ................................................................................. 227

ምዕራፍ ፶፩ ........................................................................ 235
ልዑል ደጃዝማች መኮንን በአጼ ምኒልክ ተልከው ወደ ኢጣሊያ አገር ስለ መሄዳቸው ........................................................................ 235
ምዕራፍ ፶፪ ........................................................................ 238
አጼ ምኒልክ የንጉሡ ነተሥት ዘውድ ስለ መጫናቸው። ........................... 238
ምዕራፍ ፶፫ ........................................................................ 240
ስለ እቴጌ ጣይቱ ዘውድ መጫን። ................................................ 240
ምዕራፍ ፶፬ ........................................................................ 244
አጼ ምኒልክ ወደ ትግሬ /ትግራይ/ ስለ መሄዳቸው። ............................ 244
ምዕራፍ ፶፭ ........................................................................ 246
በውጫሌ በተደረገው ውል በ፲፯ኛው ክፍል በተጻፈው ቃል በአጼ ምኒልክና በኢጣሊያ መንግሥት መካከል ክርክር ስለ መነሳቱ። ............................ 246
ምዕራፍ ፶፮ ........................................................................ 250
ስለ ራስ መንገሻና ስለ ኢጣሊያኖች የወዳጅነት ውል። ........................... 250
ምዕራፍ ፶፯ ........................................................................ 253
ራስ መንገሻ ባለፈው ሥራቸው ተጸጽተው ከአጼ ምኒልክ ጋራ ስለ መታረቃቸው ........................................................................ 253
ምዕራፍ ፶፰ ........................................................................ 256
አጼ ምኒልክ በኢትዮጵያ ያሉት ኢጣሊያኖች እየወጡ ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ስለ ማዘዛቸው። ........................................................................ 256
ምዕራፍ ፶፱ ........................................................................ 258
ጄነራል ባራቴሪ አድዋ መጥቶ በወታደር ከተከበበ በኋላ በእጨጌ ቴዎፍሎስ ስለ ማምለጡ ........................................................................ 258
ምዕራፍ ፷ ........................................................................ 260
ስለ ራስ መንገሻና ስለ ኢጣሊያኖች ጦርነት ........................................ 260
ምዕራፍ ፷፩ ........................................................................ 261
አጼ ምኒልክ ኢጣሊያኖች የውጫሌን ውል ፲፯ኛውን ክፍል አንፍቅም ካሏቸው በኋላ ውሉን ለማፍረስ ቁርጥ አሳብ ስለ ማድረጋቸው። ................................ 262
ምዕራፍ ፷፪ ........................................................................ 265
ኢጣሊያኖች ወሰን አልፈው ወደ አጋሜ ስለ መግባታቸው። ..................... 265

ምዕራፍ ፳፫ ........ 266
የመስኮብ መላክተኞች ወደ ኢትዮጵያ ስለ መምጣታቸውና የኢትዮጵያም መላክተኞች ወደ መስኮብ ስለ መሔዳቸው ........ 266
ምዕራፍ ፳፬ ........ 267
ራስ መንገሻ መቀሌን ለቀው ወደ ሕንጣሎና ወደ ደብረ ኃይላ ስለ መሄዳቸው 268
ምዕራፍ ፳፭ ........ 269
አጼ ምኒልክ ከኢጣሊያኖች ጋራ ለመዋጋት ቁርጥ አሳብ ካደረጉ በኋላ አዋጅ ስለ መንገራቸው። ........ 269
ምዕራፍ ፳፮ ........ 274
ልዑል ራስ መኮንን በጦር አበጋዝነታቸው አላጌ ላይ ከኢጣሊያኖች ጋር ስለ መዋጋታቸው ........ 274
ምዕራፍ ፳፯ ........ 278
ስለ መቀሌ ጦርነት ........ 278
ምዕራፍ ፳፰ ........ 285
ራስ ስብሐትና ደጃች ሐጐስ ተፈሪ ከኢጣሊያኖች እየከዱ ወደ አጼ ምኒልክ ስለ መግባታቸው ........ 285
ምዕራፍ ፳፱ ........ 288
ስለ አድዋ ጦርነት ........ 288
የጎኑይ ጉብኝት ውጤቶች ........ 317
የሰውና የሥፍራ ስሞች ማገናዘቢያ - INDEX ........ 0

# ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የጻፏቸው መጻሕፍትና የታተመባቸውም ዘመናት

1. የኢትዮጵያና መተማ /የአጼ ዮሐንስ ታሪክ ባጭሩ/ በኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት በ፲፱፻፲ /1910/ ዓ.ም ታተመ
2. ወዳጄ ልቤ በ፲፱፻፲፭ /1915/ ዓ.ም ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ፤
3. ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በግምት በ፲፱፻፲፭ /1915/ ዓ.ም ታተመ፤
4. የልዕልት ወይዘሮ መነን መንገድ በኢየሩሳሌምና በምስር። በልዑል አልጋ ወራሽ ማተሚያ ቤት በ፲፱፻፲፭ /1915/ ዓ.ም ታተመ፤
5. ደስታና ክብር፣ የኢትዮጵያ መንግስት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ልዑል ራስ ተፈሪ ወደ አውሮፓ ሲሄዱ እና ሲመለሱ የመንገዳቸውን አኳኋን የሚገልጽ በ፲፱፻፲፭ /1915/ ዓ.ም ታተመ፤
6. የሕይወት ታሪኢክ /በኋላ ዘመን ለሚነሱ ልጆች ማስታወቂያ/ በልዑል አልጋወራሽ ማተሚያ ቤት በ፲፱፻፲፭ /1915/ ዓ.ም ታተመ፤
7. ስለ አውሮፓ መንገድ የምክር ቃል፤ በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን ማተሚያ ቤት በ፲፱፻፲፭ /1915/ ዓ.ም ታተመ፤
8. መጽሐፈ ቅኔ ዘቀደምት ወደኃርያት ሊቃውንቲሃ ወማዕምራኒሃ ለኢትዮጵያ ዘአስተጋብኡ ወጸሐፎ ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በእንተ ዘአስተናሥኦ ወአትግሆ ንቡረዕድ ገብረ ሥላሴ ዘውእቱ ጸሐፌ ትእዛዙ ለዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት በ፯ወ፱፻ወ፩ ዓመት እምድኅረ ልደቱ ለክርስቶስ ወተኅትመ በማኅተመ መጻሕፍቲሁ ለልዑል መኮንን ወራሴ መንበረ መንግሥት ዘኢትዮጵያ በ፯ወ፱ወ፻ወ፰ /1918/፤
9. ጐኅጽባ /በጐኅጽባሕ ማተሚያ ቤት በ፲፱፻፲፱ /1919/ ዓ.ም ታተመ
10. በኢትዮጵያ የሚገኙ በግዕዝና በአማርኛ ቋንቋዎች የተፃፉ መጻሕፍት ካታሎግ። በልዑል ራስ ተፈሪ መኮንን ማተሚያ ቤት ፲፱፻፳ /1920/ ዓ.ም ታተመ
11. ዋዜማ በጐኅጽባሕ ማተሚያ ቤት በ፲፱፻፳፮ /1926/ ዓ.ም ታተመ
12. የግ.ን.ቀ.ኃ.ሥ. የሕይወት ታሪክ በ፲፱፻፳፪ /1922/ ዓ.ም ታተመ።
13. ሱካርና ወተት የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ትርጉም ለሕፃናት ማስተማሪያ የሚሆን በ፲፱፻፳፪ /1922/ ዓ.ም ታተመ።
14. ለልጅ ምክር ለአባት መታሰቢያ በ፲፱፻፳፫ /1923/ ዓ.ም ታተመ።
15. የልብ አሳብ /የብርሃኔና የጽዮን ሞገሳ ጋብቻ/ በጐኅ ጽባሕ ማተሚኢያ ቤት በ፲፱፻፳፫ /1923/ ዓ.ም ታተመ።
16. ጥሩ ምንጭ በጐኅጽባሕ ማተሚዒያ ቤት በ፲፱፻፳፫ /1923/፤ ዓ.ም ታተመ።
17. ማኅደረ ብርሃን /ሀገረ ጃፓን/ በ፲፱፻፳፬ /1924/ ዓ.ም ታተመ።
18. አዲስ አለም በ፲፱፻፳፭ /1925/ ዓ.ም ታተመ።

19. በዕድሜ መሰንበት፤ ሁሉንም ማየት። በጐሳ ጽባሕ ማተሚያ ቤት በ፲፱፻፳፮ /1926/ ዓ.ም ታተመ።
20. እኔና ወዳጄ በ፲፱፻፳፯ /1927/ ዓ.ም ታተመ።
21. የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግሥት ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል ድረስ፣ በግምት በ፲፱፻፳፯ - ፳፰ ዓ.ም /1927 - 28/ ዓ.ም ተዘጋጅቶ በ፲፱፻፺፱ /1999/ ዓ.ም የታተመው ይህ የመጨረው መጽሐፍ ነው።



አጼ ኃይለሥላሴ በስደት ለንደን በነበሩበት ጊዜ

## የንጉሠ ነገሥቱ ምስክርነት

## "ታላቅ ነህ ሳልልህ ብቀር ሥራዎችህ ቀድመውኝ ይናገራሉ።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት
መስከረም ፲ቀን ፲፱፻8 ዓ.ም.

"አሁን የአዳምን ልጆች ወግ ሲቀብል የምታዩት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ በአገራችን ሥርዓት በመልካም አያያዝ ያደገ ከኢትዮጵያም ከፍ ካሉት ሊቃውንት የሚቆጠር ነው። ብልሃቱንና ትጋቱንም ለመልካም ሥራ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ስለአደረጋቸው በመንግሥታችን ሥራ ለመመረጥና ወደ ታላቁ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ለመድረስ በቃ። በየጊዜውም የጻፉቸው ከፍተኛ ባህርዩን የሚገልጡ መጻሕፍት ይልቁንም በቤተክህነትና በታሪክ ዕውቀት በዓለም ሊቃውንት ዘንድ የታወቀና የተከበረ አደረጉት። ለምታውቁት ሰው ከታሪኩ ከዚህ የበለጠ ልነግራችሁ የሚያስፈልግ አልመሰለኝም።

በአጭሩ ከጠባዩ ትልቅነት የሚሰማኝን ለመናገር ሳስብ ጊዜውን ሁሉ ቁም ነገር በመሥራት ማሳለፉ፤ ከራሱ ይልቅ የተቸገሩትን ለመርዳት መጣሩ፤ ዕውነትን ፍርድንም ማክበሩና በአገር ፍቅር መቃጠሉ ትዝ ይሉኛል።

አገልጋዬና ወዳጄ ኅሩይ!

በተቻለህ ስለአገርህ ሥራህን በሚገባ ፈጽመህ በምትሰናበት ጊዜ ታላቅ ነህ ሳልልህ ብቀር ሥራዎችህ ቀድመውኝ ይናገራሉ።

በክፉ አድራጊዎች የሚገፋ የዓለምን ፀጥታ የሚያናውጥ ነፋስ ምንም ቢያንገላታህና በታላቅ ፈተና ላይ ቢጥልህም ሊያሸንፍህ አልቻለም። ታላቅና ቸር በሆነው ጌታ ለተመደበው ሕግ ግን መታዘዝ ግድ ሆነብህ።

ይህም ለእያንዳንዳችን በተራ የሚደርሰን ዕድል ነው አንተም እስከ መጨረሻ ከታገልክ በኋላ ዛሬ ደከመህ፤ አንቀላፋህም በሥጋ ብትለየን ስምህና ሥራህ በመካከላችን ይኖራሉ።

ኅሩይ! እግዚአብሔር ሲያስበን አጥንቶችህ መንፈስህ የሚሰፉበትን ቦታ እስኪያዩና ከአባቶችህ እስኪቀላቀሉ ድረስ በእንግድነት በመጣህበት በዚህ ሥፍራ በሰላም ዕረፍ።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት
ለንደን መስከረም ፲ ቀን ፲፱፻፴፩

# መቅድም

የተለያዩ ምርጥ መጻሕፍትን ለአገራችን ያበረከቱት ስመ ጥሩው ደራሲ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. “ዋዜማ” የተሰኘውን ድርሰት ጽፈው ሲያሳትሙ ማግስቱ የኢትዮጵያን ነገሥታት የታሪክ በዓል ለማክበር መሆኑን ከአርዕስቱ ግርጌ ገልጸው፣ በዚሁ መጽሐፍ ገጽ 45 ላይ “ዋናውን የኢትዮጵያን ነገሥታት ታሪክ በሙሉ በምንጽፍበት ጊዜ» በማለት ተከታይና የተሟላ ታሪክ ለመጻፍ ያቀዱ መሆናቸውን ጠቁመው ነበር።

ደራሲው ይህን ያቀዱትን የኢትዮጵያን ነገሥታት ታሪክ መጻፍ ጀምረው ከዚህ ከጻፉት ውስጥ 113 ገጾች ለኅትመት በቅተው ሌሎች 13 ገጾች በእጅ ጽሑፍ ላይ እንዳሉ በ1928 ዓ.ም በኢትዮጵያ ላይ በደረሰው የኢጣሊያ ፋሽስት ወረራ ምክንያት ደራሲው ሥራቸውን በማቋረጥ ተገደው ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ወደ ውጭ አገር ይሰደዳሉ።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ፣ በዚህ በጀመሩትና አሁን ሊታተም በቻለው የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ከንግሥተ ሳባ እስከ ድልነዓድ፣ ቀጥሎ የዛጉዌን ዘመን፣ ከዚያም ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል የነበረውን ክፍል በመጠኑ ከዳሰሱ በኋላ፣ ከነጋሢ እስከ ኃይለ መለኮት ድረስ ያለውን የሸዋን ታሪክ በዝርዝር አቅርበውታል።

አያይዘውም፣ ዘመነ መሳፍንት የሚባል ምዕራፍ በታሪካችን ውስጥ እንደነበር አውስተው ወደ አጼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ይገባሉ፡፡

ስለ አጼ ቴዎድሮስ ዘመን የጻፉት፣ አጼ ቴዎድሮስ በመሳፍንት ሽኩቻና ውጊያ በእነርሱም ሥራ የተከፋፈለችውን ኢትዮጵያን በአንድ ንጉሠ ነገሥት ሥልጣን ሥር የምትተዳደር አንዲት አገር ለማድረግ ከአደረጉት ጥረት ይልቅ በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን በተፈጸመው ጭካኔ ላይ ይበልጥ ያተኩራል።

በስፋት የሚተርኩት ስለ አፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግስት ነው። ንጉሠ ነገሥቱ ከእንግሊዞች ጋር የነበራቸውን የቅርብ ግንኙነት ከግብጽና ከኢጣሊያ ጋር ያደረጓቸውን ጦርነቶች በቅደም ተከተል አገባብ በደንብ ጽፈውታል።

በአገር ውስጥም ከሸዋው ንጉሥ ምኒልክና ከጐጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር የነበሯቸውን ግንኙነቶች የተለያዩ ባህሪዎቻቸውን በየመልክ በየመልኩ በሥርዓት አስቀምጠውታል።

አጼ ዮሐንስ በዘመናቸው ፍጻሜ ላይ መተማ ከመዝመታቸው በፊት በእርሳቸውና በንጉሥ ምኒልክ መኻከል የተፈጠረውን ቅራኔ መሠረት አድርገው ለንጉሡ አጐት ለራስ

ዳርጌ መጻፋቸውን፣ ራስ ዳርጌም ከንጉሠ ነገሥቱ የመጡላችውን መልዕክቶች ለንጉሡ ማድረሳቸውን፣ ንጉሡም በተራቸው ለአጼ ዮሐንስ የላኳቸውን የመልስ ደብዳቤዎችን በቅደም ተከተል ሥርዓት አቅርበዋል።

ደራሲው በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኢትዮጵያ መድረክ ላይ በተለየ ደረጃ ገንነው በነአብሩት በሁለቱ ታላላቅ ሰዎች መኻከል የተፈጠረውን የሻከረ ስውር ሁኔታ ከነምክንያቱ በጥልቀት ለማወቅ የሚረዱትን መረጃዎችና ሰነዶች ከታሪኩ ሂደት ጋር አያይዘው በመጽሐፋቸው ውስጥ ለትውልድ በማስተላለፍ በአጠቃላይ ለአንባብያንና በተለይም ለታሪክ ተማሪዎችና ተመራማሪዎች በዓይነቱም ሆነ በይዘቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ግምቱ እጅግ ከፍ ያለ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ታላቅ የታሪክ ጽሑፍ አበርክተዋል።

ይህ ጽሑፍ የሚቆመው ከአጼ ዮሐንስ ዕረፍት በኋላ ንጉሠ ነገሥት የሆኑት የዳግማዊ ምኒልክን ዘመነ መንግሥት የመጀመሪያውን ክፍል ከውጫሌ ውል እስከ የአድዋው ጦርነትና ታላቅ ድል ድረስ ያለውን ከ፲፰፻፹፩ - ፲፰፻፹፰ /1881 – 1888/ ታሪክ በመተርክ ነው።

ይህ አሁን ለኅትመት የበቃው ታሪክ በዋዜማ መጽሐፋቸው ላይ ያወሱት የትልቁ ሥራቸው አንዱ ክፍል መሆኑ አያጠራጥርም። በፋሽስት ወረራ ምክንያት ንጉሠ ነገሥቱና ደራሲው ወደ ውጭ አገር ለመሰደድ ሲገደዱ ደራሲው የወጠኑት ታላቅ እቅድ ይሰነካከላል። ለኅትመት የበቃውም ሥራቸው በሚገባ ተጠርዞ ገበያ ላይ ሳይውል ድካማቸው ከንቱ ሆኖ ቀርቶ ነበር።

በየቦታው ተበታትኖ የነበረው ይህ እጅግ የደከሙበት ታሪካዊ ሥራ በእግዚአብሔር ፈቃድ፣ ከያለበት ተሰብስቦ የተገኘው ቅጅ ዘግይቶም ቢሆን በልጅ ልጃቸው በወይዘሮ ሠናይት ተክለ ማርያም ትጋት ይሁን ታትሞ መቅረቡና ለንባብ መብቃቱ የሚያስደስት ነው።

ታላቁ ደራሲ ብላቴ ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በሰፊው አቅደው መጻፍ የጀመሩትን የኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ በኢጣሊያ ወረራ በአገራችን ላይ በደረሰው ታላቅ ጥፋት ምክንያት ከፍጻሜ ለመድረስ አለመቻላቸው ቢያሳዝነንም፤ የማናውቃቸውን የአገራችንን የሩቅና የቅርብ ዘመናት ታሪክ በመጠኑም ቢሆን ገልጠን ለማየት የሚረዳንን ይህን መጽሐፋቸውን ስናነብ፣ ወደ ኋላ መለስ ብለን ምን ዓይነት ሰው እንደ ነበሩ ጥቂት ለመመራመርና ሕይወታቸውን ለመቃኘት ዕድል ይሰጠናል።

በጊዜው በእንጦጦ ራጉኤል ደብር እጅግ ከታወቁት የአገራችን ሊቃውንት ዘንድ በገበዩት ትምህርትና ዕውቀት እጅግ ልቀው የነበሩት እኝህ ታላቅ ሰው የመንግስት ሥራ የጀመሩት በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት በወጣትነት ዕድሜያቸው ነበር።

በተከታዮቹ ዓመታት በአቤቶ ኢያሱና በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ እንዲሁም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በተለያየ የመልዕክት ሥራ ወደ አውሮፓ፣ አሜሪካና ጃፓን በመሄድ የዕውቀት አድማሳቸውን ለማስፋትና ስለ ሄዱበትም መልዕክትና ስላዩዋቸውም አገሮች ዕድገት እና ሥልጣኔ ለአገራቸው ሕዝብ ግንዛቤ የሚሰጡ መጻሕፍትን ለማበርከት የቻሉ ሰው ነበሩ።

ለድርሰት ሙያ ልዩ ስጦታና ዝንባሌ ስለ ነበራቸው በ፲፱፻፫ ዓ.ም ካሳተሙት «ወዳጄ ልቤ» ከተባለው በይዘቱ እጅግ የጠለቀ መንፈሳዊ ትምህርት ከሚገኝበት መጽሐፍ ጀምሮ በሕየት ዘማንቸው ከ፳ /20/ የሚበልጡ የተለያዩ መጻሕፍት ጽፈዋል በአገር ውስጥ ታዋቂነትን ለማግኘት የበቁትም በእነዚህ መጻሕፍት ነው።

በመንግሥት ሥራም ከጠላት ወረራ በፊት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ለከፍተኛው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ሹመትና ደረጃ በቅተዋል። በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም በኢትዮጵያ ላይ በወረደው መከራ ምክንያት ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ተሰደው፣ የአገራቸው ጥፋት ያሳደደረባቸው ጽኑ ምሬትና የሱም ጠንቅ ያስከተለው ሕመም አንድ ላይ ተዳምሮ ለሕይወታቸው ማለፍ ምክናይት ሆኗል።

በስድት ዓለም በእንግሊዝ አገር አርፎ የነበረው አስከሬናቸው ኢትዮጵያ ነፃነቷን እንደ ገና መልሳ ከተጐናፀፈች በኋላ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ስላሴ ካቴድራል እንዲያርፍ ተደርጓል። ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩም የስድሳ ዘመን አዛውንት ነበሩ።

ተከታዩ የኢትዮጵያ ትውልድ ሊያውቃቸውና ሊያስታውሳቸው የሚገባ ታላቅ ኢትዮጵያዊና ስመ - ጥሩ ደራሲ እንደ ነበሩ ሥራቸው ይመሰክራል።

ዘውዴ ገብረ ሥላሴ

ዶክተር ደጃዝማች

# የአሳታሚዋ መልእክት

የመጽሐፉ አሳታሚ መልዕክት በሚለው ጽሑፍ ውስጥ

ሀ. መጽሐፉ እንዲታተም ስለ አስፈለገበት ዓላማ፤

ለ. በደራሲው ሞት የቀብር ሥርዓት ላይ የንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስሜት ገላጭ ንግግር ግዚኤን፤ ሥፍራንና ሁኔታን ያጣመረ ስለ መሆኑ ባጭር የሚያስረዳ፤ መሆኑ፤

ብላቴ ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ማን እንደ ነበሩ ለማስታወስም ያህል

ሐ. ልደት ዕድገትና ትምህርት፥

መ. ስለ ደራሲው ሀገራዊ አገልግሎት፣

ሠ. በቤተሰብአዊ ኑሮና አባትነት፣

ረ. ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በደራሲነት፣

ሰ. የባላቴን ጌታ ኅሩይ አፅማቸው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ የማረፊያ ፍጻሜውን ስለ ማግኘቱ፣

ተካትተው ይገኙበታል።



ብላቴን ጌታ ኅሩይ ከቤተሰቦቻቸው ጋር

# መጽሐፉ እንዲታተም ያስፈለገበት ዓላማ፡-

1. ደራሲው ጽፈው ያዘጋጁትንና ሳይታተም የቆየውን ይህን የኢትዮጵያን ታሪክ ሥራቸውን ለማሳተምና ለሕዝብ እንዲቀርብ ማድረ፣
2. የኢትዮጵያን የብዙ ሺህ አመታት ረዥምና ያልተቋረጠ ሀገረ መንግሥትነት ታሪክ ለማጥፋትና የኢትዮጵያን ህልውና ለመበታተን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተነሱ አፍራሽ ኃይላት የኢትዮጵያን ታሪክ የ፩፻ /100/ ዓመት ዕድሜኤ ብቻ ያለው ነው በማለት ሀሰተኞች ለሚነዙት ውሸት ኢትዮጵያ ከ፫ ሺህ /3000/ ዘመናት የበለጠ ያልተቋረጠ መንግሥትነትና ታሪክ ያላት ሀገር ለመሆኗ እውነተኛ ታሪካዊ የሰነድ ማስረጃ መኖሩን በተረጋገጠ መልክ ለማሳየት፤
3. የኢትዮጵያ አዲስና ቀጣይ ትውልድ ሁሉ በየጊዜው የሀገሩን እውነተኛ ታሪክ እያበበ የቀደምት አባቶቹን እና እናቶቹን ታሪክ በአዕምሮው እንዲመዘግበውና ታሪኩና መጽሐፉንም ጠብቆ እርሱም በፋንታው ለሚቀጥለው ትውልዱ ትውልዱ እንዲያወርሰው ለማድረግ ነው።

## የአሳታሚዋ መልዕክት



የመጽሐፉ አሳታሚ የወይዘሮ ሠናይት ተክለማርያም መልዕክት

“ዝክረ ጻድቅ ለዓለም ይሄሉ።

/ የጻድት መታሰቢያው ለዘለዓለም ይኖራል፣ /

መዝ ፻፲፩ ቁ.፮

የተከበራችሁ አንባቢያን፡-

በዚህ መጽሐፍ ከመቅድሙ አስቀድሞ በሚገኘው ገጽ ላይ የንጉሠ ነገሥቱ ምስክርነት በሚል ርእስ የታተመው የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንግግር ንጉሠ ነገሥቱ ስለዚህ መጽሐፍ ደራሲ እና በወቀቱም የኢትዮጵያ መንግስት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስለ ነበሩ አያቴ ስለ ክቡር ብላቴ ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ሞት በሥርዓተ - ቀብራቸው ላይ ያደረጉት ንግግር ነው። ቀብሩም የተፈጸመው መስከረም ፲ቀን ፲፱፻፴፩ ዓ.ም በእንግሊዝ አገር ለንደን ከተማ አጠገብ ባዝ በተባለ ሥፍራ ነበር።

ይህ ጊዜን፤ ሥፍራንና ሁኔታን አጣምሮ እጅግ ጥልቅ ከሆነ የግል ውስጣዊ ስሜት ፈንቅሎ የወጣው የእውነተኛ ስሜትን ገላጭ ንግግር ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ ቦታውን ጊዜ ከንጉሠ ነገሥቱ አፍ ሴንገር ያልተሰማ ዓይነት ነው። ምክንያቱም ስለ ሁሉም ነገር «እኛ» በሚል የፕሮቶኮል ሥርዓት እንጂ፣ «እኔ» በሚል ግላዊና ስሜታዊ ቃል መናገራቸው ያልተለመደ በመሆኑ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በዚያን ጊዜ የኢትዮያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና ታላቅም ደራሲ ስለ ነበሩ ስለ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ሞት በቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ያደረጉት የመሪር ኀዘንና የመጨረሻው መሰናበቻ ንግግር ነው።

ወቅቱ ሀገራችን ኢትዮጵያ በጣሊያን ፋሽስቶች ተወርራ ነፃነቷን በመገፈፍዋ ንጉሠ ነገሥቱና ሟች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ፤ ሌሎችም ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ሁሉ በእንግሊዝና በሌሎች አገሮች ተሰድደው በኀዘን፣ በመከራ፣ በችግር በሥጋና በመንፈስ ስቃይ ውስጥ የተገኙበት ጊዜ ስለ ነበር ኀዘናቸውን እጥፍ ድርብ አድርጎታል። የሁላቸውም እምነትና ተስፋ ሁሉን ማድረግ በማይሳነው በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ነበር እንጂ በምድራዊ የመንግሥታትና የሰዎች ቃል ለመተማመን አንዳችም የተስፋ ጭላንጭል የማይታያቸው የነበረበት ሁኔታ ነው።

የማቴሪያል ዓለም በሆነውና ግዙፉን ነገር ብቻ በሚያደንቀው አካባቢ ውስጥ መገኘት፤ ነገር ግን በማይጨበጥና በማይዳሰስ በዓይን በማይታይና በማይለይ በእግዚአብሔር አምላክ ላይ ብቻ መተማመንና በክፉ አድራጊዎች የሚፈፀመውን የግፍ ሥራ መመልከቱ፤ ተጠቂ የሆነ ሰውን አዕምሮ ማክተሚያ በሌለው የሀሳብ ማዕበል ሲያንገላታው ከመዋሉና ከማደር አልፎ መፍትሔውን በቶሎ ስለማይሰጠው ምንኛ ብርቱ ፈተናና ጭንቀት መሆኑ ግልጽ ጉዳይ ነው። በመሆኑ ከግ.ቀ. ኃይለ ሥላሴ ስለ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የተነገረው የኀዘን ንግግር የተነገረላቸው ሟች በሕይወት በነበሩ ጊዜ የጻፉትና ከሰባ ዓመታት በኋላ አሁን በታተመው በዚይ የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፍ ውስጥ ለአንባቢያን መቅረቡ ስለ ደራሲው ሥራዎችና ታላቅነትትም ከንጉሠ ነገሥት የበለጠ ምስክር የማይገኝለት አድርጐታል።

# ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ማን ነበሩ?

የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የእናቴ የክብርት ወይዘሮ ገነት ኅሩይ አባት ናቸው። ይህን መጽሐፋቸውን ለአሳተምሁት ለኔም ደግሞ ያሳደጉኝ አያቴ ናቸው።

## ልደት፣ ዕድገትና ትምህርት

ስለ ሕይወት ታሪካቸው ከተመዘገቡ ጽሑፎችና ቤተሰብም በመሆን ማወዓቅ እንደ ተቻለው ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በኢትዮጵያ መኻል አገር በሰሜን ሸዋ በመርሐቤቴ አውራጃ በታች ቤት ወረዳ ረመሽት ቀበሌ ደን አቦ ገዳም በተባለ ሥፍራ ከአባታቸው ከአቶ ወልደ ሥላሴ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ወለተማርያም በ፲፰፻፸፩ ዓ.ም ተወለዱ። ሲወልዱም የተሰጣቸው ስም ገብረ መስቀል ነው። የደን አቦ ገዳም ቤተ ክርስቲያን የዳግማዊ አፄ ምኒልክ የቀድሞዋ ሚስታቸው ወይዘሮ ባፈና ያሠሩት ገዳም ስለ ነበር አቶ ወልደ ሥላሴም የወይዘኦ ባፈና ቤተ - ርስት ሹም ነበሩ። ከዕለታት አንድ ቀን አቶ ወልደ ሥላሴ የገዳሙን ካህናትና ዲያቆናት ግብር ለማብላት ዝጅግት ባስደረጉ ጊዜ የገዳሙ አለቃ ለጊዜው በሥፍራው ባለመገኘታቸው ካህናቱ በረሀብ ከሚሰቃዩ ለገዳሙ አለቃ የድርሻቸው ምግብ ተቀምጦላቸው ካህናቱ እንዲመገብ ያደርጋሉ። የደብሩም አለቃ ብዙ ቆይተው በመጡ ጊዜ ካህናቱና ዲያቆናቱ በመመገብ ላይ መሆናቸውንን በመመልከታቸው በቁታ ንግግር «የገዳሙ ባህል ፈረሰ! እንዴትስ እኔ ሳልመጣ ሌሎች ግብር ይገባሉ? ይህን የሚያደርጉ እሜይቴ ወይዘሮ ባፈና ናቸው፣ ወልደ ሥላሴ የሚባል ያልተማረ ጨዋ ሾመው ይኸውና ይጫወትብናል? » በማለት ከተናገሩ በኋላ ካህናቱንም «እንዴትስ በሌለሁበት ግብር ትበላላችሁ? » ብለው ገሰፁዋቸው። አቶ ወልደ ሥልሳሴም ጠቡንና ጭቅጭቁን ያበረዱ መስሏቸው «ካህናቱ በደጅ ሆነው በፀሐዩ ሙቀት ስለተጐዱ ገብረው ግብር እንዲበሉ ያደረግሁ እኔ ነው! » የእርስዎም ፋንታ በክብር ተቀምጧል። እባክዎን ይቀመጡ።» በማለት በትህትና ለመኑአቸው። የደብሩ አለቃ ግን «ካልተማረ መሃይም ምን ይጠበቅና! ቆይ ለወይዘሮ ባፈና ነግሬ ከሹመትህ ባላሽርህ እኔ ሰው አይደለሁም! » ሲሉ ከዛቱ በኋላ ፊታቸውን ወደ ተደገሰው ምግብ አዙረው ይኮመኩሙት ጀመር።

አቶ ወልደ ሥላሴም በደብሩ አለቃ ንግግር ተበሳጭተው ነበርና «መቼም እኔ ከእንግዲህ ተምሬ አልደርስም። ልጄ እንደ እኔ እንዳይሰደብ እርሱን ማስተማር አለብኝ» በማለት ወሰኑ። ልጃቸውን ገብረ መስቀልን ደን አቦ ገዳም ትምህርት በማስገባታቸው ወታቱ በዚያ ፊደል ቆጥረው ንባብ አውቀው ከፍተኛውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለመከታተል እንዲችሉ አባታቸው ከመርሐቤቴ እስከ ሥላሴ ከዚያም እስከ ሸሬ

መድኃኒዓለም ድረስ ወስደዋቸው ከነስንቃቸው ጭምር ለመምህራኑ አስረከቧቸው። ከዚያም የቤተ ክህነቱን ልዩ ልዩ ከፍተኛ ትምህርት ሲማሩ ቆይተው በዜማ ትምህርት እስከ መምህርትነት ደረጃ አጠናቀቁ። ቀጥሎም ወደ አዲስ አበባ እንጦጦ ራጉኤል ደብር መጥተው የመጻሕፍትን ትርጓሜ በዘመኑ ከነበሩት የደብሩ ሊቃውንት ዘንድ በመማር አጠናቀቁ። በእንጦጦ የነበሩ አንድ አስተማሪያቸው የሆኑ ሊቅ ስማቸውን በጠየቋቸው ጊዜ ገብረ መስቀል መሆኑ ነገሯቸው። ሊቁም «ጐንደር በነበርሁ ጊዜ አስተማሪዬ ስለ ወደዱኝ ኅሩይ እያሉ ይጠሩኝ ነበር። ወደ አዲስ አበባ ስመለስ ግን በቀድሞ ስሜ እየተጠራሁ ነኝ። ስለዚህም አንተ የቀለም ቀንድ ስለሆንህ በምግባርህም የተመሰገንህ ነህና ኅሩይ የተባለውን ስሜን ሸልሜሃለሁ፤ ከእንግዲህ ኅሩይ እየተባልክ ተጠራ! አሏቸው» ኅሩይ ማለትም በግዕዝ ቋንቋ «ምርጥ» ማለት ሲሆን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኅሩይ ስማቸው ሆነ።

በ፲፱፻፮ ዓ.ም ራጉኤል የደብር የዳግማዊ አጼ ምኒልክ የጽሕፈት ሚኒስትር ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ ከደብሩ ሊቃውንት ስለ ኅሩይ ዝና ስለ ሰሙ ኅሩይን በጣም አቀረቧቸው። ኅሩይንና ጓደኞቻቸውን ስለ ብሩህ ምሁርነታቸው እንዲሁም አስተማሪያቸውንም ጭምር ስለ ትጋትና ታማኝነታቸው ከዳግማዊ አጼ ምኒልክ ፊት አቅርበው አሸለሟቸው። አጼ ምኒልክም የኅሩይን ገና ልጅ መሆን አይተው «እንዲያአው ለቁትር ማበራከቻ አቅርበኸው ከሊቃውንቱ ጋር እንዲሸለም አደረግኸው እንጂ፤ ገና ልጅ በመሆኑ ምን ሊያውቅ ይችላል? » ብሏቸው ጸሐፊ ትእዛዝም «ጃንሆይ! እድሜው ነው እንጂ ዕውቀቱ ትልቅና ዘሊቅ ነው» ብለው በመመስከር ንጉሡ ነገሥቱን አሳመኑአቸው። ከዚያን ጊዜ አንስቶ ኅሩይ በቤተ ክህነትና በቤተ መንግሥት እየታወቁና እየገነኑ ስለ መጡ ተወዳጅነታቸው በሁሉም ሰው ዘንድ የዘለቄታ ሆነላቸው።

## ሀገራዊ አገልግሎት

ክቡር ባላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የሚወዷትን አገራቸውን ኢትዮጵያን በልዩ ልዩ ፍፁም በሆነ ቅንነትና ልባዊነት አገልግለዋታል። ከነዚህም አገልግሎታቸው ከብዙ በጥቂት በ፲፱፻፲፫ ዓ.ም ግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ ጆርጅ በንጉሥነት ዘውድ ሲጭኑ ከደጃዝማች /በኋላም ልዑል ራስ/ ካሣ ጋር የኢትዮጵያ መንግሥት መልዕክተኛ በመሆን በሥርዓተ ንጉሡ ላይ ተገኝተዋል። ከ፲፱፻፲፪ እስከ ፲፱፻፲፬ ዓ.ም ድረስ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ዲሬክተር ሆነው በኢትዮጵያ ለከተማ አስተዳደር ሥርዓት ማዘጋጃ ቤት የሚል ስም በመጀመሪያ ያወጡላት እርሳቸው ነበሩ። በ፲፱፻፲፬ ዓ.ም ብላታ ተብለው እስከ ፲፱፻፲፪ ጥቅምት በልዩ የቆመ ፍርድ ቤት ዳኛ። ከ፲፱፻፲፰ ትቅምት እስከ ፲፱፻፲፱ መጋቢት ፯ ድረስ የመንግሥት አማካሪ፣ በዚያን ጊዜም በ፲፱፻፲፰ ከአልጋ ወራሽና


የኢትዮጵያ መንግስት ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ከልዑል ራስ መኮንን ጋር አውሮፓን ጐበኙ። በ፲፱፻፲፱ መጋቢኢት ብላቴን ጌታ ተብለው እስከ ፲፱፻፳፪ ሚያዝያ ፲፪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዲሬክተር። ከ፲፱፻፳፪ ሚያዝያ ፲፪ ጀምሮ እስከ አረፉበት መስከረም ፱ ቀን ፲፱፻ወ፩ ዓ.ም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ነበሩ። በነዚህም ሁሉ ጊዜያት በጃፓን የኢትዮጵያ መንግስት ልዩ መልዕክተኛና ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር /አምባሳደር/ ሆነው የተሾሙበትም ወቅት ነበር። ስለ መንግስት ሥራም ብዙ ጊዜ ወደ አውሮፓና አሜሪካ አገሮች እየተላኩ በመሄድ የተላኩባቸውን ጉዳዮች በሚገባ ፈጽመዋል። በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም የተቋቋመው የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር የመጀመሪያው ሊቀ መንበር ሆነው የጣሊያን ፋሽስቶች ወረራ ከመጀመሩ በፊት በጥድፊያ ብዙ ዝግጅት እንዲደረግና በየጦር ግንባሩም የቀይ መስቀል እንዲሠርማራ ብዙ ደከመውበታል። ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሲኤ በጀኔቫ የዓለም መንግሥታት ማኅበር የኢትዮጵያን በግፍ መወረር ሲገልፁ ብላቴን ጌታም ከንጉሠ ነገሥቱ ሳይለዩ አብረው በመከራውና በስደቱ ተካፋይ ሆነዋል።



ኅሩይ ወልደሥላሴ በብላታነት ማዕረግ

# በቤተሰብአዊ ኑሮና አባትነት

ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የስድስት ልጆቻቸው አባት እንዲሁም የበርካታ የልጅ ልጆቻችው አያት ከመሆናቸውም በላይ ቤተሰባቸውን በእግዚአብሔር ሕግና ፍቅር ይመሩና ያስተዳድሩ ነበር። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሕግ በሥርዓተ ቁርባን /በክርስቶስ ሥጋና ደም/ በመወሰን ባለቤታቸውን ክብርት ወይዘሮ ሐመረ እሸቴን በማግባታቸው ከአብራካቸው ስድስት ወንዶችና ሴቶች ልጆችን አፍርተዋል። በጠቅላላው ለቤተሰባቸው በተለይም ለልጆቻቸውና ለልጅ ልጆቻቸው የይነበራቸው ፍቅር ይህ ነበር ተብሎ በቃላት ሊገለፅ የማይችል ነው። በመሆኑም ዘወትር በማዕድ ቤት ጊዜ ስንኳ ሳይቀር በገበታ ዙሪያ ልጆቻቸውንና የልጅ ልጆቻቸውን ሰብስበው አብረው ስለሚመገቡ በዚህ አድራጎታቸው ልባዊ ደስታና እርካታ ይሰማቸው ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን በማዕርግና በዕድሜ ታላቅ ይሆነ ሰው ምሳ ተጋብዘው በክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ቤት እንደተገኙ የብላቴን ጌታ ልጆችና የልጅ ልጆች በማዕድ ገበታ ዙሪያ አብረን ለመሳተፍ በተሰባሰብን ጊዜ እንግዳው ሰው «ምነው! ከልጆች ጋር የምትመገበው ለምድነው? » በማለት ቢጠይቋቸው ብላቴን ጌታም «ከልጆቼ የተለየ ምን ነገር ይኖረኛል? እኔ ሀብት የለኝም። ሀብቶቼ ልጆቼ ናቸው። ስለዚህ ልጆቼ ከኔ አባባላቸውም ትክክለኛ ነበር። ምክንያቱም ሀብት መሬትና የተትረፈረፈ ገንዘብ አልነበራቸውም። በዘመነ ሕይወታቸው ሁሉ ሀብት ገንዘብና ከንቱ ዝና ያልማረካቸው ቅድሚያውን ለኢትዮጵያ ህልውናና ለነፃነቷ በመስጠት አቅማቸው እስከ ፈቀደ በመጣርና በመሥራት ልከኛ ኑሮን በመኖርና ሕይወታቸውን ሳይቀር በስደት ለሀገራቸው መስዋዕት እንዲሆን ያደርጉ እጅግ ታላቅ ሰው ታላቅ ሊቅና ፈተናም ያልበገራቸው በእምነታችወ የፀኑ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ነበሩ።



ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ ከቤተሰቦቻቸው ጋር

(በቀኝ ሦስተኛው)

## ብላቴን ጌታ ኅሩይ በደራሲነት

ክቡር ብላቴ ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በሀገራቸው ኢትዮጵያ በኖሩበት ጊዜ ከሀያ በላይ ልዩ ልዩ የተደነቁ መጻሕፍትን ጽፈዋል። ጽሑፎቻቸው ሁሉ ትህትናን፤ ትክክለኛነትን፤ ምግባረ ሠናይንና ሞራሊቲን ከፍ አድርገው የሚያሳዩ እንደ መሆናቸው ሰው በዕለታዊ ኑሮው ሥጋዊ ጥቅሙን ብቻ ከመመልከት መንፈሳዊ ሕይወቱንም እየመረመረ ሚዛናዊ የሆነ መንገድ እንዲይዝ የሚያሳስቡ አስተያየቶችን የሚያስገነዝቡ ናቸው። ይልቁንም ደግሞ ሰው በሕይወቱ በሚኖርበት መዋዕለት ዘመኑ የሥራ ክቡርነትን ተገንዝቦ በውነት፤ በታማኝነት፣ በትዕግሥትና በተስፋም በመጽናት ዘወትር ታታሪ እንዲሆን የሚመከሩና የሚያበረታቱ ሀሳቦች ከዚያ የሚበልጡ ሰዎች መካከል እንደ ውይይት ወይም እንደ ጭውውት በሚመስል ዓይነት የቀረቡ ስለሆነ ከደረቅ ትረካና ችክ ካለ ሐተታዊ አቀራረብ የተለየና ከእርሳቸው ጽሑፍ በፊት በኢትዮጵያ

ሀገራችን ሥነ ጹሑፍ ውስጥ እምብዛም ያልታየ ወይም ያልተለመደ አዲስ አቀራረብ ነው። አንዳንዱም እንደ ቴአትር አጻጻፍ ሆኖ በልዩ ልዩ ሀሳብና ዓላማ አራማጆች መካከል የሚካሄድ ውይይት ክርክር ወይም ዲያሎግ የመሰለ ነው። በዚህም ከአሮጌው ባህልና አጉል ልማድ ሕዝቡ እየተላቀቀ ወደ ዘመናዊ አስተሳሰብ እንዲሸጋገር በዘዴ የሚመከር ዓይነትም ነው።

ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ /70/ ዓመታት በፊት ያዘጋጁት ይህ የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፋቸው ከንግሥት ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል ድረስ ብቻ የሚተርክ ቢሆንም ቀጣዩን ታሪክ ለመጻፍና ለማዘጋጀት እያሰቡ ሳሉ የኢጣሊያ ፋሽስቶች ኢትዮጵያን ለመያዝ የከፈቱት ዳግም የወረራ ጦርነት ለታሪኩ ዝግጅት መቀጠል እንቅፋት ስለሆነባቸው ታሪኩን በሚገባ እንዲደመድሙት አላስቻላቸውም። ከፋሽስቶች ወረራ በፊትና በወረራውም ጊዜ በስደትም ሆነው የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስለ ነበሩት ወረራውን ለመከላከልና ለመቋቋም በፖለቲካውና በዲፕሎማሲው መስክ የወደቀባቸው ቀንበር ቀላል ስለልነበረ ምንም ዓይነት ፋታ እንዳልሰጣቸው ግልጽ ነው። ቢሆንም የገጠማቸውን ፈተና በትዕግሥት በሃይማኖታዊ እምነትና በዓላማ ጽናት በመቋቋም ተስፋ ባለመቁረጥ የበኩላቸውን ግዴታ በመፈፀም ለእናት ሀገራቸው ኢትዮጵያ በታማኝነት እስከ መጨረሻው በመቆም ከዚህ ዓለም አልፈዋል።

መጽሐፉ ከሰባ ዓመታት በኋላ በመታተሙ እስከ ታላቁ አድዋ ጦርነት ድል ድረስ በነበረችው ኢትዮጵያ በተለይም ከዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ጊዜ አንስቶ በአጼ ዮሐንስና በኋላም በአጼ ምኒልክ ዘመናት መንግሥት የነበረውን ውስጣዊ የሥልጣን ትግል፤ የባዕዳን ኃይሎችንና የውጭ ወራሪዎችን እቅድም በየጊዜያቱ የነበሩት መሪዎች ነገሥታትና መሳፍንቱ መኳንንቱና ሕዝቡ የሀገርን አንድነትም ከምንም በላይ በማስቀደም ያደረጓቸውን ተጋድሎዎች ከነውስጣዊ ገጽታዎቻቸው ጭምር ጥሩ አድርጎ ስለሚያሳይ አንባቢያን ዛሬ ካለንበት ጊዜና ሁኔታ ጋር እያነፃፀሩ ብዙ ዕውቀትና ሀቅ ሊያገኙበት ይችላሉ። በመሆኑም ይህን የታሪክ መጽሐፍ አሳትሚ ለተወደዳችሁ ትጉሃን አንባብያን አቅርቤአለሁ።



ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የኢትዮጵያዊነት ባህል እንዲዳብር ብዙ የጣሩ ነበሩ እዚህ በሀገር ባህል አለባበስ ይታያሉ



ብላቴን ጌታ ኅሩይ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋር በአውሮፓ



ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ ከንጉሥ ተፈሪ ጋር ሆነው ለቀ.ኃ.ሥ የንግሥ በዓል የመጡትን የፈረንሣይ መንግሥት ዋና መልእክተኛ ማርሻል ፍራንሼ ደስፕሬይን ሲቀበሉ



ብላቴን ጌታ ኅሩይ በዚያን ዘመን በኢትዮጵያ አዲስ በገባው የስልክ አገልግሎት ሲነጋገሩ

# የብላቴ ጌታ ኅሩይ ሞትና ቀብር፣ አፅማቸው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ የማረፊያውን ፍጻሜ ስለማግኘቱ።

ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በስደት በእንግሊዝ አገር በነበሩበት ጊዜ ኢትዮጵያ በዚያን ወቅት በኢጣሊያ ፋሽስት ወራሪዎች ተይዛ ስለ ነበር የሀገራቸው ኢትዮጵያ ሁኔታ እጅግ የሚጨንቅቸው ስለ ነበር የአካልም ሆነ የመንፈስ ዕረፍት ሊሰጣቸው አልቻለም። ስለዚህም በስደት ኑሮአቸው ዘወትር በኀዘን ውስጥ በመሆናቸው ለወራሪዎችና ለግፈኞች ድርጊት በጊዜው የፍትሕና የርትዕ ማረሚያ መልስ ስላልተሰጣቸው በዓለም መንግሥታት ማኅበርና በአንዳንድ ኃያላን አገሮች ቸልተኝነት የኢትዮጵያ መበደል ብላቴን ጌታን ከፋኛ ይሰማቸው ነበር።

ይህም ጭንቀትና ብስጭት ከስደተኛነትና ከመከፋት ከኀዘንም ጋር ተዳምሮ የጤና መታወክን ሕመም በማስከተሉ ከሥጋ ሕመም ይልቅ የመንፈስ ኀዘን ከፋኛ ስለሚጐዳ ክቡር ብላቴ ጌታ ኅሩይ ሕመማቸው ፋታ ሳይሰጣቸው በተወለዱ በስድሳ ዓመት እድሜአቸው መስከረ ፱ ቀን ፲፱፻፴፩ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። በማግሥቱም መስከረም ፲ ቀን ፲፱፻፴፩ ዓ.ም እንግሊዝ ሀገር ከሎንዶን ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኘው በባዝ ከተማ ሉክሰንበርግ በተባለ የመቃብር ሥፍራ ተቀበሩ። ብላቴን ጌታ ኅሩይም የደከሙለትንና መስዋዕትም የሆኑለትን የኢትዮጵያን የነፃነት ትንሣኤ ለማየት ባይታደሉም ከኅልፈተ - ሕይወታቸው ሁለት ዓመት ከሰባት ወር ጊዜ በኋላ በሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ኢትዮጵያ በጀግኖች አርበኞች ልጆቿ ተጋድሎና በታላቋ ብሪታንያ የጦር ቃል ኪዳን ድጋፍ የኢጣሊያን ፋሽስት ይዞታ ሰባብራ እንደ ገና ነፃነቷን ተጐናጸፈች።

ይህም ሆኖ ከኅልፈተ - ሕይወታቸው ከዘተኝ ዓመታት በኋላ መስከረም ፲፩ ቀን ፲፱፻፵ ዓ.ም የክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ አፅም በአውሮፕላን አዲስ አበባ ገባ። ከዚያም በዕለቱ ወዲያውኑ ወደ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተወስዶ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ግርማዊ እቴጌ መነን ከልዑላን ልጆቻቸውና ንጉሣውያን ቤተሰብ ጋር፣ እንዲሁም ልዑላን መሳፍንትና ክቡራን መኳንንት፣ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ዐርበኞችና የአዲስ አበባ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞ አፅማቸው በደከሙላትና በሞቱላት ሀገራቸው የመጨረሻ ማረፊያውን የክብር ሥፍራ አገኘ። በዚህም ሥነ ሥርዓት በወቅቱ ተጠባባቂ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ታላቅ ዐርበኛ ክቡር ራስ አበበ አረጋይ ከተናገሯቸው ታላቅ ውስጥ የሚከተለው ይገኝበት ነበር።

# ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ!


«ገናና ታሪክን ያተረፈ የሰውነትም መቋቋሚያ የነበረው አፅምዎ በእንግድነት አርፎ ከቆየበት አገር ዛሬ መጥቶ ለተወዳጅ አገርዎ መሬት አደራ የሚሰጥበትን ይህን የዛሬውን ቀን ለማክበር ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ግርማዊት እቴጌ፤ ከንጉሣውያን ቤተ ዘመድ ጋር እዚህ ይገኛሉ። ቤተ ዘመድዎ፤ ልዑላን መሣፍንት ክቡራን መኳንንትና የመጻሕፍቶችዎ ወዳጆች በዚህ ተሰብስበዋል። ሥራዎን ጨርሰው በሞት ባንቀላፉ ጊዜ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በተነገረው የሰውነትዎን ከፍተኛ ጠባይና ታማኝ አገልጋይነትዎን በሚገልጠው ንግግር የተሰጠው የተስፋ ቃል /አፅማቸው ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ እንዲመለስ የሚደረግ መሆኑ/ እነሆ! ዛሬ ተፈፀመ።

«ለሰው ልጅ በዚህ ዓለም ከመልካም ሥራ ላይ ማሳለፍም ስምዎን ለዘለዓለማዊነት ባለው ታሪክ አስጊጦታል። ሞት ምንጊዜም የማይቀር የሰው ልጅ ዕዳ ነው። ደምሳሽ ለሆነው ለዚህ ሕግ ከመታዘዝዎ በፊት በዚያ በታደሉት

የሕይወት ዘመን የፈፀሙዋቸው ሥራዎች ዕድሜዎን በብዙ እጥፍ አዝብተው የሚያሳዩ ናቸው። በየጊዜው በእምነት በተሰጠ ሥራ ንጉሠ ነገሥትዎን በቅንነትና በሙሉ ልብ ከማገልገል በላይ ዕረፍት አጥተው ሌት ከቀን የጻፉዋቸው መጻሕፍት ይህንኑ ለማስረዳት ምስክሮች ናቸው።

«በቤት መጻሕፍት ወመዘክር የብላቴን ጌታ ኅሩይ አዳራሽ» ተብሎ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የተሰየመው የአንባቢዎች መሰብሰቢያ የስምዎ ታላቁ መታሰቢያ ነው። ለተወደደች አገርዎ እስከ መጨረሻ ትንፋሽዎ በትጋት ከማገልገል አላቋረጡም።» «ዘወትር እያደገ ከሚሄደው ታሪክዎ ዛሬ እኔ በአጭሩ ብጠቅስለትም መጭው ትውልድ ከዚህ ይበልጥ ከፍ ከፍ እንደሚያደርገው አምናለሁ።

«ለሚወዷት አገር መሬት በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መልካም ፈቃድ ስለ በቁ በተዘጋጀልዎ በዚህ በተከበረው ሥፍራ አፅምዎ በሰላም ይረፍ! » የሚሉ ነበሩ።



በእንግሊዝ አገር በስደት ሆነው የሚታዩት

በመካከል ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ፣ በስተግራ አቶ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ /በኋላም ጸሐፌ ትእዛዝ ተብለው የጽሕፈት ሚኒስትርነት የተሾሙትና/ በስተቀኝ ብላቴን ጌታ ሎሬንሶ ታእዛዝ

/በኋላም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቀጥሎም በሞስኮ የኢትዮጵያ መንግሥት ሚኒስትር

# የተወደዳችሁ አንባቢያን

አንደኛ መጻሕፍትን ማንበብ፥ ሁለተኛም ለሰው ዘር ሁሉ ጠቃሚ የሚሆን የነፍስም ሆነ የሥጋን የተቃና መንገድ የሚያመለክት ቀጥተኛ ሕይወትን ለመልካም ዓላማ የሚያንፅ ሀሳብ ማፍለቅ፣ ሦስተኛም ጠቃሚ ምርምርን ማድረግ ከሰው ልጆች የላቁ ተግባራት መካከል የሚገኙ ናቸው።

ክቡር ብላቴ ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴም በሕይወት በነበሩበት ዘመን እነዚህን ፈጽመው በማለፋቸው ምንም እንኳ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሞትና ስለ ትንሣኤ ሕይወት የተነገረው ስለ ነፍስ ሁኔታ ቢሆንም የሚሞተው አካል የማይሞተውንና የማይበሰብሰውን በሚለብስበት ጊዜ በታላቅ ክብር ይነሳል (የጳውሎስ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ም. ፲፭ ቍ ፶፫ - ፶፩) እንደ ተባለው ሁሉ፣ የክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ሥራዎቻቸው ሁሉ እነዚህም ማለት ብርቱ የሀገር ፍቅር ስሜት፣ ምን ጊዜም ፍትሕና ርትዕ እንዲነግሡ ያደረጉት ጥረት፣ እውነቱን ለማስተማር የመመራመርና የደራሲነት ሊቅነታቸው፣ እስካሁን በአገራችን ወደር ያልተገኘላቸው በመሆናቸው የሚቺ ሥጋቸው የማይሞቱትን ሥራዎቻችውን ለብሶ እነሆ የክብር ትንሣኤውን አገኘ በማለት በሰማያዊ ሳይሆን በምድራዊ አባባል ብንናገር አልተሳሳትንም። ስለዚህም ይህን የኢትዮጵያ ታሪክና ሌሎችም እንረዳለን። ከእንግዲህም በማንበብ ለአገራችን የተሰውትን የታላቁን ሊቅ ማንነት ይበልጥ እንረዳለን። ከእንግዲህም አንባብያን ሁሉ መልካም ንባብና ጥሩ ግንዛቤ እንዲሁም ጠቃሚ ትምህርት እንድታገኙበት እመኘላቿለሁ።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ! አሜን።

ሠናይት ተክለማርያም

# ማስገንዘቢያ

በዚህ የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፍና በሌሎችም የጥንት ጽሑፎችን «ግባት» ወይም «ግብአት» የሚል ቃል ተደጋግሞ ተጽፎ ይገኛል። ይህ ቃል በቀድሞ ጊዜ የአማርኛ ቋንቋ የወታደርና የጦር ሠራዊት ትርኢት፣ ሠልፍ፣ የተኩስና የእርችት ተግባር መግለጫ ነው። ይኸውም በእንግሊዝኛ ቋንቋ MILITARY SHOW, MILITARY DEMONSTRATION OR MANOUEVER እንደ ማለት ሲሆን ይኸውም ለመሪዎችና ታላላቅ ሰዎች ለመንግሥታት መልዕክተኞች የ«እንኳን» ደህና መጡ! ወይም የእንኳን ደህና ገቡ! የአቀባበል ደግሞም የእንኳን ደህና ተመለሱ የአሸኛኘትም መግለጫ ተኩስ ነው።

በዛሬው ዘመን ግን «ግብአት ወይም /ግባት/ የሚለው ቃል በተለይም በግብርናና በእርሻ ሥራ እንደ መሬት ማዳበሪያ፣ እንደ ምርጥ ዘር፣ እንደ ፀረ አረምና ፀረ ተባይ የሆኑ ልዩ ልዩ ዓይነት ውጤቶችን በጥቅል አጠራር ለመግለጽ የሚጠቀቡበት ቃል ሲሆን፣ በሌላውም የሳይንስና የቴክኖሎጂ ሥራዎች ውስጥ አባልና አካል እየሆኑ ለሚገቡ ዕቃዎች፣ መሣሪያዎችና ሀሳቦች ሁሉ ግብአት /ግባት/ (INPUT) የመገለጫቸው ቃል ሆኖአል።

ታጥቀው ገቡ የሚለው አገላለጽም «ራስ እከሌ ወይም ደጃዝማች እከሌ ለንጉሡ ወይም ለንጉሠ ነገሥቱ ታጥቀው ገቡላቸው እየተባለ በብዙ ሥፍራ ተጽፎ ይገኛል። ይህም ማለት በዚያ ዘመን አነጋገር የንጉሡን ወይ የንጉሠ ነገሥቱን ሥልጣንና የበላይነት አሜን ብለው በመቀበልና በማመን ታጥቀው ወይም አደግድገው ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ አመንኩ! ገበርኩ! ከእርስዎ በታች ሆኜአለሁ ወይም ተገዢዎ ነኝ በማለት ታማኝነታቸውን ገለፁላቸው ማለት ነው እንጂ፣ እንደ ዛሬው ጊዜ አባባል ታጥቀው ማለትም የቶር መሣሪያ ታጥቀው ገቡ ማለት አይደለም።

ስለሆነም አንባቢያን የቃሉ አገባብና አጠቃቀም እንደየዘመኑ አገላለጽና ሁኔታ ተዛማጅነት እንዳለው መገንዘብ ይኖርባቸዋል ፡

በዚህ የታሪክ መጽሐፍ ውስጥ በኢትዮጵያ የሚገኙ አንዳንድ ብሔረሰብና ሕዝብ በጥንት /በቀድሞ/ መጠሪያቸው እየተጻፉ ስለሚገኙ የመጽሐፉን የዚያን ዘመን አጻጻፍ ባለመለወጥ የአሁኑ ስማቸውንም በቅንፍ አብሮ እንዲታተም በማድረግ ለታሪክ ተመራማሪዎች ልዩ ልይ ጥናቶችን ለሚያደርጉ ሁሉ የባለታሪኮችን ማንነትና ምንነት ለመግለጽ ቅን ሙከራ ተደርጓል። ለምሳሌም ያህል፡-

- ትግሬ ትግራይ

- ጋላ ኦሮሞ

- ወላሞ ወላይታ

- ከፋ ከፊቾ

- አዳል ወይም ደንከል ወይም አውሳ አፋር እየተባለ ስለ ተጻፈ የማንኛውንም ብሔረሰብና ሕዝብ ታሪኩን ባህሉንና ማንነቱን ለመንቀፍ ወይም ለማንኳሰስ አሳታሚዋ ምንም ዓይነት ፍላጐት፥ እቅድ ወይም ዓላማ እንደሌለኝ አንባቢያን እንዲያውቁልኝ በትህትና እጠይቃለሁ። በዚህም አጋጣሚ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን እኩልነት የማንነታቸውን መገለጫ ባህሎቻቸውንና መልካም ልማዶቻቸውን ሁሉ የማከብር መሆኔንም በተጨማሪ እገልጻለሁ።

ሪም፡- ታናሽ የመሬት ክፍል። ታላቅ ከሆነ ርስት ተከፍሎ ላገለገለ አሽከር፣ ለሎሌ፣ ለወዳጅ፤ ለካህን የተሰጠ ማሳ ነው።

ወቦ ደጀን ተከታይ ማለት ሲሆን ወበበ ተከተለ በስተኋላ ሆነ ማለት ነው። ወበብ ወበብ፣ ተረታዊ የድመት ዘፈን «ከተልከተል ወበብ ወበብ ዳርዳሩን ከበብ» ይላል።

የሤራው ጋላ፣ /ኦሮሞ/ የሚባለው አነጋገር ሰላምና ፀጥታ በሰፈነበት መልክ ለመኖር ተስማምቶና ተረጋግቶ የሚገኘው የኦሮሞ ሕዝብ እንደ ማለት ነው። በሸዋ ቀደም ባለው ጊዜ በገዥዎች መሳፍንት በኋላ ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ጀምሮ በነገሡት በሸዋ ነገሥታት መንግሥት ክልልና በዙሪያውም ሁሉ የነበሩት ኦሮሞዎች የመንግሥትን ሥልጣን አወቀውና ተቀብለው በኖሩበት ጊዜ ወደ መንግሥት የገቡ የሤራ ጋላ /ኦሮሞ/ በሚል አጠራር ይታወቁ እንደ ነበር የተሰጠ ስያሜ ነው። ለአንባቢም ይህን አጠራር እንደ ቃሉ አገባብና እንደዚያ ዘመን ነባራዊነት ሁኔታ እንዲረዳው ያስፈልጋል።

## የምስጋና ወሮታ

ክብር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የጻፉት የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፍ ከብዙ ዓመታት ቆይታ በኋላ በዚህ መልኩ ታትሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ለአንባብያን እንዲቀርብ ላቻሉት፡-

፩ኛ. የመጽሐፉን ረቂቅ ጽሑፍ ከኢጣሊያ ዳግም ወረራ ዋዜማ ላይ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ለክቡር ቄስ ባድማ ያለው በአደራ መልክ እንዲያስቀምጡላቸው ሰጥተዋቸው ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ጋር ወደ አውሮፓ በስደት በመሄዳቸው፣ ቄስ ባድማም የመጽሐፉን ረቂቅ ጽሑፍ በጥንቃቄ አቆይተው ከመሞታቸው በፊት ለክቡር

ዶክተር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ በመስጠታቸው የክቡር ቄስ ባድማ ያለውን ታማኝነት አሳቢነትና ለአገራቸው ኢትዮጵያና ለውገናቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያላቸውን ፍቅር እዚህ ላይ ለመግለጽ አሳታሚዋ የጎሊና ግዴታዬ ነው። በዚህም አጋጣሚ ተገቢውን ምስጋና ለወራሾቻቸው አቀርባለሁ።

2ኛ. ክቡር ዶክተር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴም የክብር ቄስ ባድማን ቃልና አደራ ተቀብለውና ጠብቀው ከልብ አስበውበትም የመጽሐፉን ረቂቅ ጽሑፍ ለአሳታሚዋ በማስረከባቸው የሀገር ታሪና ቅርስ ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር ስላደረጉት በጎ ተግባር ከልብ አመሰግናችዋለሁ።

3ኛ. የዚህ መጽሐፍ ጽሑፍ አብዛኛው ክፍል በማጎተም ፊደላት ተለቅሞ የቀሩት ጥቂት ገጾቹም በእጅ ጽሑፍ ተጽፈው ይገኙ ስለ ነበር በጽሑፉ ውስጥ አልፎ አልፎ በርካታ ገጾች ላይ የነበሩትን የቃላት ግድፈትና መደምሰስ በሌሎች ሥፍራዎች ካሉት ኮፒዎች ለማመሳከርና ትክክለኛውን አባባል ፈር ለመያዝ በተደረገው ጥረት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ማዕከል ላደረገው ወደር የለለው እርዳታና ትብብር አሳታሚዋ በጣም አመሰግናለሁ።

4ኛ. በመጽሐፉ ኅትመት ውስጥ ተጨማሪ ሆነው ለገቡት የሰዎችና የሥፍራዎች መግለጫ ፎቶ ግራፎችና ሥዕሎች ኢትዮጵያ ኤንግሬቭድና ኢትዮጵያ ፎቶግራፍድ ከተባሉ መጻሕፍቶቻቸው ወስደን እንድናሳትም ለፈቀዱልን ለፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክኸርስት አሳታሚዋ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ።

5ኛ. ፕሮፌሰር ባርሕሩ ዘውዴ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ ክፍልና እንዲሁም ዶክተር ያሬድ አማረ ስለ መጽሐፉ ዝግጅትና አቀራረብ ለሰጡት የሙያ አስተያየት ደራሲዋ ከልብ እያመሰገንኩ፤

6ኛ. ስማቸው ቀጥሎ የተገለፀው ቤተ ዘመዶቼ፡-

ሀ. ዶክተር ዳዊት ዘውዴ ገብረ ሕይወት የአባታቸውን የክብር ቢትወደድ ዘውዴ ገብረሕይወትን የቤተሰባዊነት ፍቅርና መልካም አርአያቸውንም የወረሱ በመሆናቸው ለዚህ መጽሐፍ መታተም ያደረጉት ጥረትና ሁለገብ ድጋፍ ከፍ ያለ ስለ ሆነ ምስጋናዬ ወሰን የለውም።

ለ. ልጄ አቶ ቢያለው ጌታቸው አባተ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የታተሙትን ፎቶ ግራፎችና የእጅ ሥዕሎች በጥንቃቄና በጥራት በሲዲ ፊልም አስነስቶና አዘጋጅቶ ለኅትመት በማብቃቱ ከልብ አመሰግነዋለሁ።

ሐ. በእናቴ ስም ተሰማይ የምትጠራዋና የታናሽ ወንድሜ የአቶ ኀሩይ ተክለ ማርያም ልጅ የሆነችው ወይዘሮ ገነት ኀሩይ ለመጽሐፉ መታተም የተቃና መንገድ እንዲይዝ ስላደረገችው ስኬታማ ጥረቷና ድካሟ ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርብላታላሁ።

7ኛ. አቶ ቀፀላ መንግሥቱ አላምነህ የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ የቃላት ግድፈቶችንና ድምሳሴዎችን ከሌሎች ከፒዎች ጋር በማመሳከር መጽሐፉ ትክክለኛና የተሟላ ሆኖ እንዲታተም በማዘጋጀታቸው ከልብ አመሰግናቸዋለሁ።

8ኛ. አቶ ዳርፈታ ሸዋ ከኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ስለአደረጉት ቅን ትብብርና፣

9ኛ. ይህ መጽሐፍ ለታተመበት የሴንትራል ማተሚያ ቤት ኃላፊ ለወዘሮ አስተኢር ዘሙይ ተክሉና ለማተሚያ ቤቱ ሠራተኞች ምስጋናዬን እያቀርብኩ፣

10ኛ. በጠቅላላው በዚህ የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፍ ዝግጅትና ኅትመት ከልብ የተባበሩትን ሁሉ ሳታሚዋ በግሌ አመሰግናሁ።

ወ/ሮ ሡናይት ተክለ ማርያም

የመጽሐፉ አሳታሚ

## <u>ልዩ ማሳሰቢያ</u>

የኢጣሊያ ፋሽስቶች ወረራ በድል ከተወገደና ኢትዮጵያ ነፃነትዋን ካስመለሰችበት ፲፱፻፴፫ ዓ.ም በኋላ በልዩ ልዩ ደራስያን የተጻፉት የኢትዮጵያ ታሪክ መጻሕፍት ሁሉ መሠረታቸውንና ዋቢም እያደረጉ የጠቀሱት ይህን አሁን የታተመውን የክቡር ብላቴ ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴን የኢትዮጵያ ታሪኪ የረቂቅ ዝግጅቱን ጽሐፍ መሆኑን ለተከበራችሁ አንባብያን ሁሉ በትህትና እንገልጻለን።

# ምዕራፍ ፩

## ከንግሥተ ሳባ እስከ ባዜን ድረስ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ፩ሺ ፲፫ እስከ ፰ ዓመተ ምሕረት

የንግሥ ሳባ ዓብት አጋቦስ ይባላል። ከክርስቶስ ልደት አስቀድሞ በኢትዮጵያ ከነገሡት ነገሥታት ሁሉ ንግሥተ ሳባ እጅግ ስመ ጥሩ ነበረች። ንግሥተ ሳባ የተባለችው በመጽሐፈ ነገሥት ነው። ይኸውም በትግሬ አውራጃ ከአክሱም አጠገብ ያለ አገር ነው። በወንጌል ግን ንግሥተ አዜብ ትባላለች። ይኸውም እርሷ በዚያ ዘመን ከዓረብ የመን የሚባለውን ጨምራ ትገዛ ነበርና የመን ለኢየሩሳሌም አዜብ ስለሆነ ነው። አዜብ ማለትም በምዕራብና በደቡብ መካከል ያለ ማዕዘነ ዓለም ነው።

በክብረ ነገሥት ግን ማክዳ ይላታል። ይኸውም መንገደኛ ማለት ነውና ወደ ኢየሩሳሌም ወርዳ ከተመለሰች በኋላ የተጠራችበት ስም ነው ይባላል። ስለዚህ በአገሩዋና በግብሯ ስም ትጠራ ነበር ከማለት አባትና እናቷ ያወጡላት ስም ነው ለማለት ያስቸግራል።

ግዛቱዋም እጅግ ሰፊ ነበር። በስተ ምሥራቅ እስከ ማዳጋስጋካር በስተ ሰሜንና በስተ ምዕራብ እስከ ኖብ ዳርቻ፤ በስተ ደብቡብ ዛሬ የቪክቶሪያ ባሕር እስከ ተባለው እስከ ኒያንዛ ባሕር ነበር። ኒያንዛ ከሚባለው ባሕር ነጭ ዓባይ ወጥቶ ከጣና ከሚወጣው ከጥቁር ዓባይ ጋር በካርቱም ላይ ተገናኝቶ የሱዳንንና የምስርን አገሮች ያጠጣል።

በንግሥተ ሳባ ዘመን ከኢየሩሳሌምና ከዓረብ ከምስርና ከህንድም አገሮች ብዙ ነጋዴዎች ወደ ኢትዮጵያ ይመላለሱ ነበርና እነርሱ ከኢትዮጵያ የሚገኘውን ልዩ ልዩ ዕንቁና አልማዝ ወርቅና ሽቱም እየገዙ በየሀገራቸው ስለ ወሰዱ በዚህ ሁሉ ምክንያት የኢትዮጵያና የንግሥተ ሳባ ዝና በዓለም ሁሉ ተሰማ።

በንግሥተ ሳባም ዘመን የዳዊት ልጅ ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ነግሦ ነበር። በዚያም ዘመን ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም የሚመላለስ ታምሪን የሚባል ነጋዴ ነበርና እርሱ በኢየሩሳሌም ያየውን የሰሎሞንን ሥራ ሁሉ ስለ ነገራት በጆሮ ከመስማት በዓይን ማየት ይበልታል ከአክሱም ተነሥታ ወደ ኢየሩሳሌም ወረደች።

በዓረቦች ታሪክ ግን ሰሎሞን መፍቀሬ - እንስት ስለሆነ ለዚሁ ጉዳይ በምስጢር ደብዳቤ እየጻፈ ይልክባት ነበርና ወደ ኢየሩሳሌም የወረደችበት ምክንያቱ ስለዚህ ነው



ንግሥተ ሳባና ንጉሥ ሰሎሞን ተገናኝተው ሲነጋገሩ

(በቀድሞው የኢትዮጵያ ፓርላማ ከነበረው እና የዓለም ሎሪየት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ከሣሉት የተወሰደ)

የሚል ተጽፎ ይገኛል። ስትሔድም ብዙ ወርቅና ዕንቁ ዋጋው የበዛና ልዩ ልዩ የሆነ ሽቱ ይዛ ነበር።

በዚያን ዘመን የመን የሚባለው የዓረብ አገር የእርስዋ ግዛት ነበርና ባሕረ ኤትራን ተሻግራ የመን አገር ስትደርስ ያገሩ ባላባቶች ብዙ ስንቅ በግመሎች ጭነው ሲጠብቋት አገኘች።

ከየመንም ተነስታ በብዙ ታጅባ ኢየሩሳሌም በደረሰች ጊዜ ንጉሡ ሰሎሞን በታላቅ ደስታና ክብር ተቀብሎ የማረፊያ ሥፍራ ሰጣት።

ንግሥተ ሳባም ብዙ እንቆቅልሽ ጠየቀችውና አንዱንም ሳይሰውር ተረጐመላት። ሰሎሞንም ጥበቡን ሁሉ የሠራውንም ቤተ መንግሥትና ቤተ መቅደስ ወደ ቤተ መቅደስም የሚገባበትና የሚወጣበትን መንገድ ካሳያት በኋላ ባዳራሽ ተቀምጦ መሳፍንቱንና መኳንንቱን በማዕድ ግብር ሲያበላ ሊያሳያት አሰበ። ስለዚህ ለሌሎች ሰዎች በማትታይበት እርሷ ግን ሁሉን በምታይበት በመስትዋትና ባይነ ርግብ በተሠራ በልዩ ሥፍራ አስቀምጦ ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ላገርም ባላባቶችና ለሠራዊቱ ትልቅ ግብር

አድርጐ ዋለ። ንግሥተ ሳባም የመሳፍንቱንና የመኳንንቱን የባላባቶችንና የሠራዊቱንም አቀማመጥ ያገልጋዮቹንና የፀጅ አሳላፊዎቹን አለባበስና ቅልጥፍናቸውን በማየትና በማድነቅ አእምሮዋ በደስታ ፈዘዘ።

የማዕዱም ግብር ከተጨረሰ በኋላ፣ ሰሎሞን ባየችው ሁሉ ደስ እንዳላት ሊጠይቃትና ሊያነጋግራት ከዙፋኑ ተነስቶ እርስዋ ወዳለችበት ቤት ገባ። ንግሥተ ሳባም በብሩህ ገጽና እንደ ማግኔት በሚስብ ንግግር እንደዚህ እያለች ታመሰግነው ጀመረ። «ንጉሥ ሆይ። ባገሬ በኢትዮጵያ ሳለውሁ የሥራህንና የጥበብህን ነገር ሁሉ ቢነግሩኝ እኔ መጥቼ በዓይኔ እስካይ ድረስ የነገሩኝን ሁሉ አላመንሁም ነበር። አሁን ግን ሁሉንም ነገር ባይኔ ስላየሁ ባገሬ ሳለሁ ከሰማሁት ይልቅ በልጦ አገኘሁት። በዘመንህ ሁሉ በፊትህ የሚቆሙት ሰዎችና አገልጋዮችህ ሁሉ የታደሉ ናቸው። ለወደዳቸው ለእስራኤል ፍርድንና ቅንን ታደርግ ዘንድ በዙፋኑ ያነገሠህ እግዚአብሔር አምላክህ የተባረከ ይሁን! » አለችው።

ከዚህም በኋላ ከሀገርዋ የወሰደችለትን ገጸ በረከት ዕንቁና ብዙ ሽቶ ከመቶ ሃያ ቅንጣር ወርቅ ጋር ሰጠችው። ከንግሥተ ሳባ አስቀድሞ ይህን የመሰለ ሽታው የጣፈጠና ዋጋ የበዛ ሽቱ ለሰሎሞን አልመጣለትም ነበርና አሁን ግን ይህን የመሰለ ገጸ በረከት ስላመጣችለት እጅግ ደስ አለው።

ይህም ሁሉ ከተደረገ በኋላ ንግሥተ ሳባ ወደ ሀገርዋ ለመመለስ ማሰቧን ነገረችው። ነገር ግን በዓለም የታወቀችና የከእብረች እንኳን ንግሥተ ሳባን አይቶና እንዲያውም ቢሆን ሰሎሞን መፍቀሬ - እንስት መሆኑ የታወቀ ነውና በፈቃደ ሥጋ ተገናኛት። እስዋም በድንግልናና በንጽሕና ተጠብቃ የምትኖር ነበረችና በቶሎ ፀነሰች። የፅንዋንም ነገር ባወቀች ጊዜ ተሰናብታ ወደ ሀገርዋ ተመለሰች። በቶሎም የተመለሰችበት ምክንያቱ በሀገርዋ በድንግልና ተጠብቃ ስትኖር ወደ ኢየሩሳሌም መጥታ የዝሙት ሥራ ሠርታ ልጅ ወለደች ተብላ እንዳትነወር ስለፈራች ይመስላል።

የኤርትራንም ባሕር ተሻግራ በሐማሴን አውራጃ ማይበላ በሚባል አገር ስትደርስ ወንድ ልጅ ወለደች። ስሙንም ኢብነ - መለክ ባላ አወጣችለት። ትርጓሜውም የንጉሥ ልጅ ማለት ነው በዘመን ብዛት ግን ንግግሩ እየተለዋወጠ ምኒልክ ተባለ። ኢብነ - ሐኪምም ተብሏል። የዚህም ትርጓሜ የብልህ ልጅ ማለት ነው።

ምኒልክ ተወልዶ ካደገ በኋላ «አባቴ ማነው? » ብሎ እናቱን ንግሥተ ሳባን ቢይጠይቃት «አባትህ የኢየሩሳሌም ንጉሥ ሰሎሞን ነው» ብላ ነገረችውና እጅግ ደስ አለው። በዚሁም ምክንያት በተወለደ በ፳ ዓመቱ አባቱን ሰሎሞንን ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም ወርዶ ነበርና በታላቅ ደስታና ክብር ተቀበለው።

በኢየሩሳሌምም ፫ ዓመት ያህል ተቀምጦ ወደ እናቱ አገር ወደ ኢትዮጵያ በተመለሰ ጊዜ ንግሥተ ሳባ ልጅዋ በደህና ወደ ሀገሩ ስለ ተመለሰ እጅግ ደስ አላት።

ከዚህም በኋላ የኢትዮጵያን መሳንቱንና መኳንንቱን ባላባቶችንም ሁሉ ሰብስባ በሕይወቴ ዓይኔ እያየ ልጄን ምኒልክን ባነግሠው ይሻለኛል ብላ ነገረቻቸውና አሳቧን ከተቀበላት በኋላ አነገሠችው። እርሱም የእናቱን መንግሥት ወርሶ ፳፫ ዓመት በኢትዮጵያ ከነገሠ በኋላ በተውለደ ፵፱ ዓመቱ አረፈና አክሱም ከእናቱ መቃብር አጠገብ ተቀበረ።

በአንዳንድ ታሪክ ሰሎሞን ልጁን ምኒልክ በኢትዮጵያ አነገሠው ተብሎ ተጽፎ ይገኛል። እንደዚህም ተብሎ መጻፉ ምናልባት ኢትዮጵያ ከብዙ ዘመን አስቀድሞ ስምዋ የታወቀ ገናና መንግሥት መሆንዋ ባይታወቅ ይሆናል።

ሁለተኛም፤ የኢትዮጵያ ነገሥታትና ሕዝብ ኃይለኞችና የጦር ሰዎች መሆናቸው ባይታወቅ ይሆናል።

ሦስተኛም፣ ንጉሥ ሰሎሞን ከንግሥተ ሳባ የሚበልጥ፤ ኢየሩሳሌምም ከኢትዮጵያ የምትበልጥ ስለ መሰለ ለቀዳማዊ ምኒልክ ክብር እንዲሆን ታስቦ ይሆናል።

ይኸውም የታሪኩ አኳኋን ከሥሩ እስከ ጫፉ ባይመረመር ነው እንጂ ተመርምሮ ቢሆን ሰሎሞን ልጁን ምኒልክን በኢትዮጵያ አነገሠው ተብሎ ባልተጻፈም ነበር።

የታሪኩም አኳኋን ባይመረመር መሆኑን ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው እናስረዳለን። ኢትዮጵያ ከብዙ ዘመን አስቀድሞ ስምዋ የታወቀ ገናና መንግሥት መሆንዋ ባይታወቅ ይሆናል የተባለው ነገር እውነት መሆኑን ለማስረዳት ኢየሩሳሌም ገና በመሳፍንቱ በነ ኢያሱ በነ ጌዴዎን በነ ባርቅ በነ ሳምሶን በካህናቱም በነፊንሐስ በነ ዔሊ በነ ሳሙኤል ስትገዛ ኢትዮጵያ በነገሥታት ትገዛ ነበር።

ሁለተኛም የኢትዮጵያ ነገሥታትና ሕዝብ ኃይለኞችና የጦር ሰዎች መሆናቸው ባይታወቅም ይሆናል የተባለው ነገር እውነት መሆኑን ለማስረዳት የሰሎሞን አባቶች እነ ያዕቆብና እነ ይሁዳ በምድረ ግብፅ በባርነት ቤት ሳሉ የኢትዮጵያ ነገሥታት የተደላደለ መንግሥት ይዘው በነፃነት ይኖሩ ነበር።

ሦስተኛም፣ ከንግሥተ ሳባ ንጉሥ ሰሎሞን ከኢትዮጵያ ኢየሩሳሌም የሚበልጡ ስለ መሰለ ለቀዳማዊ ምኒልክ ክብር እንዲሆን አስበው ይሆናል የተባለው ነገር እውነት መሆኑ ለማስረዳት ሰሎሞን ለኢየሩሳሌም በንጉሥነት ሦስተኛ ነበር። እነዚህም ፩ኛ ሳኦል። ፪ኛ ዳዊት። ፫ኛ ሰሎሞን ናቸው። በትውልድም ፪ኛ ነበር። ፩ኛ ዳዊት። ፪ኛ ሰሎሞን ነው። ንግሥተ ሳባ ግን ለኢትዮጵያ በንጉሥነት ፶፪ኛ ነበረች።

ደግሞ በመሬት መልካምነት ወይም በለምነት ወይም በስፋትም ቢሆን ኢየሩሳሌም ከኢትዮጵያ የምትበልጥበት ነገር የለም።

የኢየሩሳሌም ወሰንዋ ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ነበር። የኢትዮጵያ ወሰን ግን በምሥራቅ እስከ ማዳጋስካር በሰሜን እስከ ምስርና እስከ ኖብያ ድርቻ። በደቡብም እስከ ኒያንዛ ባሕር ነበር። በዚያ ዘመን ኢየሩሳሌም ከኢትዮጵያ ትበልጥ ነበር ቢባል ያገር ጅዎግራፊያ የሚያውቁ ሰዎች ሊያምኑትና ሊቀበሉት አይችሉም።

ደግሞ በማንም ነገር ቢሆን ንጉሡ ሳለ ባገሩ ላይ የሌላው አገር ንጉሥ ሊነግሥበት አይችልምና ኢትዮጵያን ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ የምትገዛ ንግሥት ሳባ ሳለች ሰሎሞን ምኒልክን በኢትዮጵያ ላይ አነገሠው ቢባል መርማሪና አስተዋይ ልብ ያለው ሰው እውነት ነው ብሎ ሊቀበለው አይችልም።

ነገር ግን ምኒልክ ምንም እንኳ የገናናይቱ የንግሥተ ሳባ ልጅ ቢሆንም ካንድ መስፍን ወይም ካንድ ባላባት ከመወለድ ይልቅ በጥበቡና በእውቀቱ በባለጠግነቱም ስሙ በዓለም ሁሉ ከታወቀው ከኢየሩሳሌም ንጉሥ ከሰሎሞን መወለዱ ትልቅ ክብር መሆኑ አይጠረጠርም። እንዲህም ማለት በክብር ላይ ክብር ተጨመረለት ማለት ነው እንጂ፤ የንጉሥነቱን ማዕረግና ክብር መንግሥቱንም መጀመሪያ ከሰሎሞን አገኘው ማለት አይደለም። ስለዚህ በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ቀዳማዊ ምኒልክ የንግሥተ ሳባ ልጅ ስለ ሆነ እናቱ ከመሳንቶቹዋና ከመኩዋንንቶቹዋ ጋራ ተማክራ በሀገርዋ በኢትዮጵያ አነገሥችው ቢባል፤ እውነት ይመስላ እንጂ ሰሎሞን ሊያዝበት በማይቻለው በኢትዮጵያ ምኒልክን አነገሠው ማለት ያስቸግራል።

ነገር ግን የሰሎሞን አገር ኢየሩሳሌም ምንም እንኳ ሩቅ ቢሆንም ንግሥተ ሳባ መንግሥቷን በሕይወትዋ ለልጅዋ ለምኒልክ ለመስጠት ባሰበች ጊዜ አስቀድማ ወደ ሰሎሞን መላክተኛ ልካ ነገሩን ሁሉ አስታውቃው ነብር ቢባል እንኳ እውነት ነገር ሳይሆን አይቀርም። እንግዲህ የዚህን ነገር አቆይቶን የነገሥታቱን ስምና ቁጥር እንጽፋለን።



ቀዳማዊ ምኒልክ

(ሠዓሊ አገኘሁ እንግዳ የተወሰደ)

| ስማቸውና ቁጥራቸው | የነገሡበት ዘመን | ከክርስቶስ ልደት በፊት |
|---|---|---|
| ፩ ንግሥተ ሳባ | ፴፩ | በ፩ሺ ፲፫ |
| ፪ ምኒልክ ፩ኛ /ዳዊት/ | ፳፭ | ፱፻፹፪ |
| ፫ ሐንድዩን | ፩ | ፱፻፶፯ |
| ፬ ሲራህ ፩ኛ /ቶማይ/ | ፳፮ | ፱፻፶፮ |
| ፭ አሜንሆቴፕ ዘግዱር | ፵፩ | ፱፻፴ |
| ፮ አክሱማይ ራሚሱ | ፳ | ፰፻፹፱ |
| ፯ ሲራህ ፪ኛ /አውስዩ/ | ፴፰ | ፰፻፷፱ |
| ፰ ተዋስያ ፪ኛ | ፳፩ | ፰፻፴፩ |
| ፱ አብራልዩስ ፒያንያኪያ ፪ኛ | ፴፪ | ፰፻፲ |
| ፲ አክሱማይ ወረደ ፀሐይ | ፳፫ | ፯፻፸፰ |
| ፲፩ ካስሕታ ሐንድዮን | ፲፫ | ፯፻፶፭ |
| ፲፪ ሳባካ ፪ኛ | ፲፪ | ፯፻፵፪ |
| ፲፫ ኒካንታ ቅንዳኬ ፪ኛ | ፲ | ፯፻፴ |
| ፲፬ ዳውዕ ቲርሐቅ /ወርደ ነጋሽ/ | ፵፱ | ፯፻፳ |
| ፲፭ አርድአሜን አውስያ | ፮ | ፮፻፸፩ |
| ፲፮ ገስዮ | ፮ ሰዓት | |
| ፲፯ ኑአትሚአሙን | ፬ | ፮፻፷፭ |
| ፲፰ ቶማድዮን ፒያንኪያ ፫ኛ | ፲፪ | ፮፻፷፩ |
| ፲፱ አሚነአስሮ ፪ኛ | ፲፮ | ፮፻፵፱ |
| ፳ ቢያንኪ ፬ኛ /አውጥዮ/ | ፴፬ | ፯፻፴፫ |
| ፳፪ ሰይፋይ እሕርሲአተው | ፲፪ | ፭፻፶፰ |
| ፳፫ ረምኃይ ናስቶሶናን | ፲፬ | ፭፻፵፮ |
| ፳፬ ሐንዲው አብራ | ፲፩ | ፭፻፴፪ |
| ፳፭ ሶፌልያ ኒኪቦን | ፴፩ | ፭፻፳፩ |
| ፳፮ አግልቡል ስዌኮስ | ፳፩ | ፬፻፺ |
| ፳፯ ጽስመረት /ወረደ ነጋሽ/ | ፳፩ | ፬፻፷፱ |
| ፳፰ አውስያ ቡራኮስ | ፲፪ | ፬፻፵፰ |
| ፳፱ ቀኒዝ ጽስሜስ | ፲፫ | ፬፻፴፮ |
| ፴ አጽራሶ | ፲ | ፬፻፳፫ |
| ፴፩ ካስህታ ወልደ እኊሁ | ፳ | ፬፻፲፫ |
| ፴፪ ኤልሳዮን ተአኒኪ | ፲ | ፫፻፺፫ |
| ፴፫ አትሲርክአሚን ፫ኛ | ፲ | ፫፻፹፫ |
| ፴፬ አትሲርክአሚን ፬ኛ | ፲ | ፫፻፸፫ |
| ፴፭ ሐዲና | ፲ | ፫፻፷፫ |

| | | |
|---|---|---|
| ፴፮ አትሲክአሚን ፭ኛ | ፲ | ፫፻፶፫ |
| ፴፯ አትሲርክአሚን ፮ኛ | ፲ | ፫፻፵፫ |
| ፴፰ ኒካውላ ቅንዳኬ ፫ኛ | ፲ | ፫፻፴፫ |
| ፴፱ ባስዑ | ፲ | ፫፻፳፫ |
| ፵ ኒካውሊስ ቅንዳኬ ፬ኛ | ፲ | ፫፻፲፮ |
| ፵፩ አውጥጥ አራውራ | ፲ | ፫፻፮ |
| ፵፪ አርካሜን ፪ኛ | ፲ | ፪፻፺፮ |
| ፵፫ ከልዓስ ፪ኛ /ኪሊትሮ/ | ፲ | ፪፻፹፮ |
| ፵፬ ዙዋሬንብረት | ፲፮ | ፪፻፸፮ |
| ፵፭ ሶትዮ | ፲፬ | ፪፻፷ |
| ፵፮ ሰይፉይ | ፲፫ | ፪፻፵፮ |
| ፵፯ ኒኮሲስ ቅንዳኬ ፭ኛ | ፲ | ፪፻፴፫ |
| ፵፰ ረምኃይ አርሚን ፬ኛ | ፲ | ፪፻፳፫ |
| ፵፱ ፈልያ ሑርኔክሀት | ፲፭ | ፪፻፲፫ |
| ፶ ሀንዲ አውኪራራ | ፪ | ፻፺፮ |
| ፶፩ አግሀቡ ብሴሀራን | ፲ | ፻፸፮ |
| ፶፪ ሱላይ ከዋውሚኑን | ፳፪ | ፻፷፮ |
| ፶፫ መስልኒ ቁራርሜር | ፰ | ፻፵፮ |
| ፶፬ ነግሣይ ብሲኒት | ፲ | ፻፴፰ |
| ፶፭ ኤትቢኑካዊር | ፲ | ፻፳፰ |
| ፶፮ ሰፌልያ አብራሚን | ፳ | ፻፲፰ |
| ፶፯ ሠናይ | ፲ | ፺፰ |
| ፶፰ አወሲና መንግሥት | ፲፩ | ፹፰ |
| ፶፱ ዳዊት ፪ኛ | ፲ | ፸፱ |
| ፷ አግልቡልስ | ፰ | ፷፱ |
| ፷፩ በዋውል | ፲ | ፶፱ |
| ፷፪ በረዋስ | ፲ | ፵፱ |
| ፷፫ ዳኒዳይ | ፲ | ፴፱ |
| ፷፬ አሞይ መሐሲ | ፭ | ፳፱ |
| ፷፭ ኒኮትሪስ ሀንደኬ ንግሥት ፮ኛ | ፲ | ፳፬ |
| ፷፮ ኖልኪ | ፬ | ፲፬ |
| ፷፯ ሉዛይ | ፪ | ፲ |
| ፷፰ ባዚን | ፰ | ፰ |

ባዚን በነገሠ በ፰ኛው ዓመት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔ ተወለደ።

ከንግሥተ ሳባ እስከ ባዚን በኢትዮጵያ የነገሡት ነገሥታት ፷፰ ናቸው። ዘመኑም ሺ ፲፫ ዓመት ይሆናል። ነገር ግን ከክርስቶስም ልደት በኋላ ፱ ዓመት ነግሦዋልና ይህ ሲጨመር ከ፳፪ ዓመት ይሆናል።

# ምዕራፍ ፪

## ከባዚን ጀምሮ የቀዳማዊ ምኒልክ መንግሥት ወደ ነገደ ዛጉዌ እስከፈለሰበት እስከ ድልነዓድ ድረስ።

ከ፩ - ፱፻፪ ዓ.ም።

| ስማቸውና ቁጥራቸው | የነገሡበት ዘመን | ከክርስቶስ ልደት በኋላ |
|---|---|---|
| ፷፱ ባዚን | ፱ | ከ፩ |
| ፸ ሰርጡ /ጽፈን አሰግድ/ | ፳፩ | ፱ |
| ፸፩ አካጥታህ /ጽንፈ አርአድ/ | ፪ | ፴ |
| ፸፪ ሆርኤምትኩ ፪ኛ | ፪ | ፴፪ |
| ፸፫ ገርሳሞት /ህንደኬ/ ፺ኛ | ፰ | ፴፬ |

ንግሥት ህንደኬ በፐለስቲና አውራጃ በጋዛ ቦታዋ የሚኖር አንድ ኢትዮጵያዊ ሾማ ነበር። እርሱም ከጋዛ ለበዓል ወደ ኢየሩሳሌም ወጥቶ ሲመለስ በፊልጶስ እጅ ተጠምቆ ነበርና እርሱ የጥምቀትን ነገር በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ አስታወቀ። የሐዋ ሥራ. ፰ ፳፮ - ፵።

ይህም በጋዛ የሚኖር ኢትዮጵያዊ የንግሥት ህንደኬ የግምጃ ቤት ሹም ነበር። እርሱንም ያጠመቀው ለኢየሩሳሊኤም ማኅበር አገልግሎት ከተመረጡት ከሰባቱ ዲያቆናት አንደኛው ፊልጶስ ነው እንጂ፣ ሐዋርያት ፊልጶስ አይደለም። ይህንም ለመረዳት የፈለገ ሰው ቢኖር በሐዋርያት ሥራ መስሐፍ በ፰ኛው ምዕራፍ የተጻፈውን ቃል ከ፩ ቁጥር እስከ ፱ ቁጥር ቢመለከት ከኢየሩሳሌም ወደ ሰማርያ የወረደው ዲያቆኑ ፊልጶስ መሆኑን ያገኘዋል። ሐዋርያት ግን በዚያን ወራት ከኢየሩሳሌም ወደ ውጭ አገር አልወጡም ነበር።



## የኢትዮጵያ ንግሥት ሕንደኬ በጅሮንድ ጋዛ ላይ ፊሊጶስን እንዳገኘው

(በቀድሞው የኢትዮጵያ ፓርላማ ከነበረውና የዓለም ሎሪየት ሜትር አርቲስት
አፈወርቅ ተክሌ ከሣሉት የተወሰደ)

| ስማቸውና ቁጥራቸው | የነገሡበት ዘመን | ከክርስቶስ ልደት በኋላ |
|---|---|---|
| ፸፬ ሐተዘ /ባሕረ አስገድ/ | ፳፫ | ፵፪ |
| ፸፭ ምሴንህ ግርማሶር | ፯ | ፭ |
| ፸፮ ሰጥዋ /ግርማ አስፈር/ | ፱ | ፸፯ |
| ፸፯ አድገለ ፪ኛ | ፲ዓ፮ ወር | ፹፮ |
| ፸፯ አግባ | ፮ወር | ፺፮ |
| ፸፱ ሰርዓዳ | ፲፮ | ፺፯ |
| ፹ መሊስ አላሜዳ | ፬ | ፻፲፫ |
| ፹፩ ሐቀቤ ኩሉ ጽዮን | ፮ | ፻፲፯ |
| ፹፪ ሐቅሌ ሠርጓይ | ፲፪ | ፻፳፫ |
| ፹፫ ድድሜ ዘርዓይ | ፲ | ፻፴፭ |
| ፹፬ አውጥፖ | ፪ | ፻፵፭ |
| ፹፭ አልዓዶ በጋማይ | ፯ | ፻፵፯ |
| ፹፮ አውዱ ዣን አስገድ | ፴ | ፻፶፬ |
| ፹፯ ዛግን ጽዮን ሕግዛ | ፭ | ፻፹፬ |

| | | |
|---|---|---|
| ፹፰ ራማ ጽዮን ሕግዛ | ፫ | ፻፹፱ |
| ፹፱ አዚጋን መዓልባጋድ | ፯ | ፻፺፪ |
| ፺ ፈለገ ሰብአ አስገድ | ፩ | ፻፺፱ |
| ፺፩ ድጋዮ ብእሲ ሠረቅ | ፬ | ፪፻ |
| ፺፪ ጋዛ አግዱር | ፱ | ፪፻፬ |
| ፺፫ አግዱር አስጓጓ | ፰ | ፪፻፲፫ |
| ፺፬ ደዊዛ | ፩ | ፪፻፳፩ |
| ፺፭ ዋካና | ፪ ቀን | |
| ፺፮ ሐዳውስ | ፬ ወር | ፪፻፳፪ |
| ፺፯ አዕላል ሳን ሰገል | ፫ | ፪፻፳፭ |
| ፺፰ አስፍህ | ፲፬ | ፪፻፴፱ |
| ፺፱ አድገበ | ፮ | ፪፻፴፭ |
| ፻ አይላ | ፲፯ | ፪፻፷፯ |
| ፻፩ ጸሐመ ላክዱን | ፱ | ፪፻፷፫ |
| ፻፪ ጽጋብ | ፲ | ፲፪፻፸፩ |
| ፻፫ ታዜን | ፲ | ፪፻፹፩ |
| ፻፬ አሕይዋ /ሶፍያ/ | ፯ | ፪፻፺፩ |
| ፻፭ አብርሃ ወአጽብሐ በአንድነት | ፳፮ | ፪፻፺፫ |

በኢትዮጵያ የጥምቀትና የክርስትና ሥርዓት የገባው በአብርሃና በአጽብሐ ዘመን ነው። ምክንያቱን ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን።

ከቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን አስቀድሞ የነበሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕገ ኦሪትን ተቀብለው እውነተኛውን አምላክ እስቲያመልኩ ድረስ በፀሐይና በጨረቃ በከዋክብትም በእንስሳትና በአራዊትም በዛርና በክፉ መናፍስትም ያመልኩ ነበር እንጂ፣ እንደ ሌሎች አሕዛብ እንጨት ጠርበው ደንጊያ አለዝበው ጣዖት ቀርጸው ወይም ወርቅና ብር አፍስሰው ብር አፍስሰው ምስል መስለው አያመልኩ ነበር።

ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ኢየሩሳሌም ወርዶ የኦሪትን ካህናት ይዞላቸው ከመጣ በኋላ ግን እየተማሩ በእውነተኛው አምላክ ብቻ አምነው ይኖሩ ነበር።

ከክርስቶስም ልደት በኋላ በ፴፬ ዓ.ም የኢትዮጵያ ንግሥት የህንደግኬ ጃንደረባ ኢየሩሳሌም ደርሶ ወደ ጋዛ ሲመለስ በፊልጶስ እጅ በተጠመቀ ጊዜ እርሱ የጥምቀትን ዜና ወደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ አመጣ ጥምቀትን የሚቀበሉበት ጊዜ ሲጠብቁና ሲናፍቁ ይኖሩ ነበር።

እንደዚህም ጥምቀትንና ክርስትናን እየጠበቁ ሲኖሩ በፍሬምናጦስ ምክንያት ክርስትና መጣላቸ። የፍሬምናጦስ ታሪክ ባጭሩ እንደዚህ ነው። መሮፔዎስ የተባለ አገሩ ግሪክ መኖሪያው በጢሮስ አገር ነጋዴ የሆነ ነጋዴ በአፍሪቃ ዳር በአልጀርያና በቱኒዝያ በትሪፖሊና በእስክንድርያ እየዞረ ይነግድ ነበር። እነዚሁም የአፍሪቃ ክፍል አገሮች በዚያን ዘመን በዓለም ሁሉ እጅግ የታወቁ ስለ ነበሩ ከሮምና ከኢየሩሳሌም ከግሪክም አገር ወደ መምሕራን እየሄዱ ወንጌልን ይሰብኩላቸው ነበር።

ያም የጢሮስ አገር ነጋዴ ሁለቱንም ልጆቹን ፍሬምናጦስንና ሲድራኮስን አስከትሎ በአፍሪቃ ጠረፍ እየዞረ ሲነግድ የኢትዮጵያ ጠረፍ በምትሆን በምጥዋ ሲደርስ እርሱ ስለ ሞተ ሁለቱን ልጆች የምጥዋ ልጆች አግኝተው ለሐማሴኑ ገዥ ሰጡት። የሐማሴኑም ገዥ ወደ አክሱም ወስዶ ለንግሥት አሕየዋ /ሶፍያ/ ሰጣ። እርስዋም ባልዋ ስለ ሞተ ልጆችዋም ብርሃና አጽብሐ ገና ልጆች ስለ ነበሩ የኢትዮጵያ መንግሥት ትገዛ ነበርና ፍሬምናጦስን ለልጆቿ ለአብርሃና ለአጽብሐ ሞግዚትና ጸሐፊ፣ ሲድራኮስን ግን ጠጅ አሳላፊ አድርጋ ታኖራቸው ጀመረች።

ፍሬምናጦስም ከሕፃንነቱ ጀምሮ ወንጌልን እየተማረ ያደገ ክርስቲያን ስለ ነበረ የኢትዮጵያ ሕዝብ እኩለ በአረመኔነት እኩሉም በሕገ ኦሪት በመኖራቸው ያዝን ነበር። ቢሆንም ወደ ባላገር እየሔደ አላስተማረም እንጂ፣ በዚኢያው በቤተ መንግሥቱ ግቢ ለንግሥቱንና ለልጆችዋ ለመኳንንቱም የክርስቶስን መንግሥት የወንጌልን ትምህርት ጥቂት በጥቂት እያለ መስበኩ አልቀረም ነበር።

ነገር ግን በቅስና ሹመት አልነበረውምና ማንንም ለማጥመቅ አለመቻሉን አስታውቆ ከእስክንድርያ አንድ ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ ማስመጣት የተሻለ ነገር መሆኑን ለንግሥቲቱና ለልጆችዋ እያስረዳ ይነግር ነበር። ንግሥቲቱና ልጆቿም እርሱን ለመላክ አስበው ከአክሱም ቤተ መንግሥት የመልዕክቱን ደብዳቤ ከሰጡት በኋላ ለመንገዱ የሚያስፈልገውን ሁሉ አዘጋጅቶ ለመሄድ አስቀሞም ለንግድ ሥራ ከአባቱ ከመሮፔዎስ ጋራ የአፍሪቃን አገሮች ሲዞር እስክንድርያን ያውቅ ነበረና ከአክሱም ተነስቶ ወደ እስክንድርያ ሄደ።



አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን (ፍሬምናጦስ)

(በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ጳጳስና የክርስትናን እምነት ያመጣ)
ከፕሮፌሰር ፓንክኸረስት ኢትዮጵያ ፎቶግራፍድ መጽሐፍ የተወሰደ፡

ከዚያም አስቀድሞ አርዮስ የተባለ አንድ የግብጽ ቄስ ወልድ በመለኮቱ ፍጡር ነው የሚል የኑፋቄ ባህል ስለ አወጣ ሊቃውንቱ ሁሉ በገላትያ አገር በኒቅያ ጉባኤ አድርገው እንዲከራከሩ ትልቁ ቆስጠንጢኖስ አዋጅ አድርጎ ነበርና ፫፻፲፰ (318) ሊቃውንት በኒቅያ ጉባኤ አደረጉ። የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት እለእስክንድሮስ አፈ ጉባኤ ነበርና ጉባዔው ከተፈጸመ በኋላ ወደ እስክንድርያ ተመልሶ በ፫፻፳፯ ዓ.ም አረፈ።

ከእርሱም ቀጥሎ ትልቁ አትናቴዎስ በቅዱስ ማርቆስ ወንበር ተቀምጦ ሳለ ፍሬምናጦስ እስክንድርያ ደረሰ። አትናቴዎስም በታላቅ ደስታና ክብር ተቀበለው። ወዲያውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥምቀትና ክርስትና ፈላጊዎች መሆናቸውን አስረድቶ አንድ ጳጳስ ሾሞ እንዲሰድላቸው ለመነው።

ቅዱስ አትናቴዎስም የፍሬምናጦስን ነገር ከሰማን በኋላ ያገሩን ልማድና ቋንቋ ከምታውቀው ካንተ የሚሻል ሰው አይገኝምና አንተኑ እሾምሃለሁ አለው።

ከዚህም በኋላ ፍሬምናጦስ የኢትዮጵያ ጳጳስ ሆኖ ተሾሞ በ፫፻፴ ዓ.ም ያህል ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ። ወደ አክሱም በገባ ጊዜ በታላቅ ደስታና ክብር ተቀበሉት።

አንባቢ ሆይ! የኢትዮጵያ ሕዝብ የክርስቲያንነትን ዜና ስለ ሰሙ ጥምቀትንና ቁርባንን የሚሰጣቸው ጳጳስ ራሳቸው ፈልገው አስመጡ እንጂ ላጥምቃችሁ ላቁርባችሁ የሚል ጳጳስ ራሱ ፈልጐ አልመጣላቸውምና በዚሁም ብቻ ብፁዓን መባል እንዲገባቸው አስተውል።

ፍሬምናጦስም የኢትዮጵያ ጳጳስ ሆኖ ከመጣ በኋላ ስሙ ከሣቴ ብርሃን ሰላማ ተባለ። ሰላማ መባሉ በአምልኮ ባዕድ ከእግዚአብሔር ጋራ ተጣልተው የነበሩትን የኢትዮጵያንሕዝብ አስተምሮና አጥምቆ ከእግዚአብሔር ጋር ስለ አስታረቃቸው ነው።

ከሣቴ ብርሃንም መባሉ የጨለማ ሥራ የሚሆን በኃጢአት ኑሮ ለሚኖሩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የወንጌልን ብርሃን ስለ አበራላቸው ነው።

በዚያም ዘመን እንደ ሕገ ኦሪት ሊቀ ካህናት የነበረው አንበረም ይባል ነበርና አንበረምንም በክርስቲያን ሕግ በወንጌል አስተምሮ በክርስቶስ አሳመነው። አባ ሰላማ በመጀመሪያ አንበረምን በማስተማሩና በማሳመኑ ትልቅ የብልሃት ሥራ መሥራቱን ያስረዳል።

አንበረም በመጀመሪያ ወደ ክርስቲያን ሃይማኖት ባይመለስና ባይጠመቅ ለጊዜ በከተማ የነበሩትን በሕገ ኦሪት የሚኖሩ ሰዎች የሃይማኖት ጠብ አስነስተውና ወገን ለይተው ሳያስቸግሩት አይቀሩም ነበር።

ይልቁንም አባ ሰላማ ትልቅ የብልሃት ስራ ሊሠራ አንበረምን አሳምኖና አጥምቆ ብቻ አልቀረም። ነገር ግን ማዕረግህ ከእኔ በታች ኤጲስ ቆጶስ ይሁን ብሎ ስለ ሾመው ሥራው እየተቃናለት ሄደ።

አንባቢ ሆይ! አባ ሰላማ አንበረምን አስተምሮና አጥምቆ ስሙንም ሕዝብ - ቀድስ ብሎ ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ መሾሙ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ በመቺኤውም ቢሆን በበታቹ ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሾም የሚገባው መሆኑን እንዲያስረዳ አስተውል።

| ስማቸውና ቁጥራቸው | የነገሡበት ዘመን | ከክርስቶስ ልደት በኋላ |
|---|---|---|
| የ፮ አጽብሐ ለብቻው | ፲፪ | ፫፻፳፬ |
| የ፯ አስፍሀ ደልዝ | ፯ | ፫፻፴፮ |
| የ፰ ሣህል | ፲፬ | ፫፻፵፫ |
| የ፱ አርድ /ገብረ መስቀል/ | ፬ | ፫፻፶፯ |
| የ፲ አድኃና | ፭ | ፫፻፷፩ |
| የ፲፩ ርትዕ | ፩ | ፫፻፷፮ |
| የ፲፪ አስፍሐ ፪ኛ | ፩ | ፫፻፷፯ |
| የ፲፫ አጽብሐ ፪ኛ | ፭ | ፫፻፷፰ |
| የ፲፬ አሜዳ ፩ኛ | ፲፭ | ፫፻፸፫ |
| የ፲፭ አብርሃ ፪ኛ | ፯ ወር | ....... |
| የ፲፮ እለሣህል | ፪ ወር | ...... |
| የ፲፯ እለገበዝ | ፪ | ፫፻፹፰ |
| የ፲፰ ሱሕል | ፬ | ፫፻፺ |
| የ፲፱ አብርሃ ፫ኛ | ፲ | ፫፻፺፬ |
| የ፳ ኢድኃና ንግሥት ፪ኛ | ፮ | ፬፻፬ |
| የ፳፩ ኢዮአብ | ፲ | ፬፻፲ |
| የ፳፪ ጸሐም ፩ኛ | ፪ | ፬፻፳ |
| የ፳፫ አሜዳ ፪ኛ | ፩ | ፬፻፳፪ |
| የ፳፬ ሣህለ አሕዛብ | ፪ | ፬፻፳፫ |
| የ፳፭ ጽባሕ /መሀረነ ክርስቶስ/ | ፫ | ፬፻፳፭ |
| የ፳፮ ጽሐም ፪ኛ | ፪ | ፬፻፳፰ |
| የ፳፯ እለገበዝ ፪ኛ | ፮ | ፬፻፴ |
| የ፳፰ ዓጋሌ /አጋቤ/ | ፩ | ፬፻፴፮ |
| የ፳፱ ሌዊ | ፪ | ፬፻፴፯ |
| የ፴ አሜዳ ፫ኛ /ያዕቆብ/ | ፫ | ፬፻፴፱ |
| የ፴፩ አርማህ ዳዊት | ፲፬ | ፬፻፵፪ |

| | | |
|---|---|---|
| ፻፵፪ አምሲ | ፭ | ፬፻፶፮ |
| ፻፵፫ ሶልዓዶባ | ፱ | ፬፻፷፩ |
| ፻፵፬ እልአሜዳ | ፰ | ፬፻፸ |
| ፻፵፭ ዜና | ፯ | ፬፻፹፰ |
| ፻፵፮ ካሌብ | ፴ | ፬፻፹፭ |
| ፻፵፯ ዘእስራኤል | ፩ ወር | |
| ፻፵፰ ገብረ መስቀል | ፲ | ፭፻፲፭ |

እልዓሚዳ በነገሠ በ፰ኛው ዓመት ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ዘጠኙ ቅዱሳን ወደ አክሱም መጡ።

| ስማቸውና ቁጥራቸው | አገራቸው |
|---|---|
| ዘሚካኤል /አረጋዊ/ | ሮም |
| ሊቃኖስ | ቁስጥንጥንያ |
| ይምዓታ | እስያ |
| ጽሕማ | አንጾኪያ |
| ጉባ | ቂልቅያ |
| አፍጺ | እስያ |
| ጴንጠሊዮን | ሮም |
| አሌፍ | ቂሣርያ |
| ገሪማ | ሮም |

ሮም የተባለው ግሪክ ሮም /አዲስ ሮም/ ነው እንጂ፣ የኢጣልያን ከተማ ሮም አይደለም።

እነዚህ ዘጠኙ ቅዱሳን በአክሱምና በቀሩትም የትግሬ (የትግራይ) አውራጃዎች እየዞሩ በማስተማራቸውና መጻሕፍትን ወደ ግዕዝ ቋንቋ በመመለሳቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ከድንቁርና ጨለማ ወደ ዕውቀት ብርሃን እየመሩ አድርሰዋልና በሙሉ ኢትዮጵያ ሲመሰገኑ ይኖራሉ።

በአጼ ካሌብም ዘመን ዛሬ ሔጃዝ በሚባለው በዓረብ አገር የሚኖሩትን ክርስቲያኖች አይሁድ ልዩ ልዩ መከራ እያመጡ ስለ አስጨነቋቸው በቁስጥንጥንያ ንጉሥ ዩስቲያኖስ /ጁስቲኒያን/ የሚባለው ወደ አጼ ካሌብ እርዳታ ለምኖ ነበርና አጼ ካሌብ በኤርትራ ባሕር ላይ ብዙ መርከቦች ስለ ነበሩት ወደ ዓረብ አገር ተሻግሮ አይሁድን

ወግቶና ድል አድርጐ በዚያው አብርሃ የተባለውን የጦር አበጋዝ ትቶ ስለ ተመለሰ ከተማም ቤተ ክርስቲያንም ተሰርቶ መቶ ዓመት ያህል በኢትዮጵያ ነገሥታት እጅ ሆኖ ቆይቶ ነበር። እስከ ዛሬም የከተማውና የቤተ ክርስቲያኑ ፍራሽ እንደ ኣንቲካ /አንቲክ/ ሲታይ ይኖራል።




ኢትዮጵያዊው ሊቅ ማኅሌታይ ቅዱስ ያሬድ

አጼ ካሌብ ዓለምን ንቆ መንግሥቱን ትቶ ወደ ኢየሩሳሌም መንኖ ስለ ሞተ ቅዱስ ተብሏል።


አጼ ገብረ መስቀልም በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት ወደ ደብረ ዳሞ ወጥቶ ከአቡነ ጋራ ተገናኝቶ ከተባረከ በኋላ በተራራው ላይ ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት አስፈቅዶ እጅግ የተዋበ ቤተ ክርስቲያን ሠርቶበታል።

ቤተ ክርስቲያኑም ተሠርቶ ከተጨረሰ በኋላ ማኅሌታይ ያሬድ ቤተ ክርስቲያኑን ለማየት ወደ ተራራው ወጥቶ ነበርና የሥራውን ማማር አይቶ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ዜማ ዘመረ። **/ይሔጽዋ መላእክት እለ በሰማያት። እስመ ማኅደረ መለኮት ይእቲ። ፆድከዋ! ፆድከዋ! ፆድከዋ! ወርኢኩ ስነ ሕንፃሃ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን።/**

አጼ ገብረ መስቀል በደብረ ዳሞ የሠራው ቤተ ክርስቲያን ምንም አንዳንድ ጊዜ ቢጠገን እንኳ እስካሁን ድረስ መሠረቱና ሕንፃው በጭራሽ አልፈረሰም።

| ስማቸውና ቁጥራቸው | የነገሡበት ዘመን | ከክርስቶስ ልደት በኋላ |
|---|---|---|
| የ፻፴፱ ቆስጠንጢኖስ /ሣህል/ | ፳፰ | ፭፻፳፱ |
| የ፻፵ ወሰን ሰገድ | ፲፭ | ፭፻፶፯ |
| የ፻፵፩ ፍሬ ሠናይ | ፳፫ | ፭፻፸፪ |
| የ፻፵፪ አድርዓዝ | ፳ | ፮፻፺፭ |
| የ፻፵፫ አካለወድም | ፰ | ፮፻፲፭ |
| የ፻፵፬ ግራም አስፈር | ፲-፭ | ፮፻፳፫ |
| የ፻፵፭ ዝርጋዝ | ፲ | ፮፻፴፰ |
| የ፻፵፮ ድግና ሚካኤል | ፳፮ | ፮፻፵፰ |
| የ፻፵፮ ባሕረ ኤከላ | ፲፱ | ፮፻፸፬ |
| የ፻፵፰ ጉም | ፳፬ | ፮፻፺፫ |
| የ፻፵፱ አስጎምጉም | ፭ | ፮፻፲፯ |
| የ፶ ለትም | ፲፮ | ፮፻፳፪ |
| የ፶፩ ተላተም | ፳፩ | ፯፻፵፰ |
| የ፶፪ ፆደጎሽ | ፲፫ | ፯፻፵፱ |
| የ፶፫ አይዞር | ፩ | ..... |
| የ፶፬ ድድም | ፭ | ፯፻፸፪ |
| የ፶፭ ድድም | ፭ | ፯፻፸፪ |
| የ፶፮ ውድድም | ፲ | ፯፻፸፯ |
| የ፶፮ ውድም አስፈሬ | ፵ | ፯፻፹፯ |
| የ፶፯ አርማህ | ፭ | ፰፻፲፯ |


| | | |
|---|---|---|
| ፻፶፫ ድግናዥን | ፲፱ ከ፫ ወር | ፫፻፳፪ |
| ፻፶፬ ግዳዜን | ፲ | ፫፻፵፩ |
| ፻፷ ዮዲት | ፴ | ፫፻፵፪ |
| ፻፷፩ አንበሳ ውድም | ፳ | ፫፻፹፪ |
| ፻፷፪ ድልነዓድ | ፲ | ፬፻፪ |



**አጼ ገብረመስቀል በደብረዳሞ ገዳም**
**ያሠራው ሕንፃ ቤተክርስቲያን**



ቅዱስ ያሬድ ለንጉሡ ለአጼ ገብረመስቅል ስለደብረዳሞ ገዳም
ቤተክርስቲያን ቅኔ ሲቀኝለት



አቡነ አረጋዊ ዘደብረዳሞ

# ምዕራፍ ፫

## የኢትጵያ መንግስት ከቀዳማዊ ምኒልክ ዘር ወደ ዛጉዌ ዘር ካለፈበት ከ፱፻፲፪ ጀምሮ ከዛጉዌ ወደ ቀዳማዊ ምኒልክ ዘር እስከ ተመለሰበት እስከ ሺ፪፻፵፫ ዓመተ ምሕረት ስለ ዛጉዌ መንግሥት ማስረጃ በአጭሩ እንጽፋለን።

በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ብዙ እስራኤላውያን ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ በመጡ ጊዜ ከካህናቱም ወገን ሕጉ ኦሪትን ለማስተማር የመጡ ብዙ ነበሩና እነዚያ ሕዝቡን እያስተማሩ ከአረማዊነት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ስለ መለሱ ብዙ የሃይማኖት ወገኖችን አግኝተው ነበር። ደግሞ እነዚሁ ከኢየሩሳሌም የመጡ እስራኤላውያን ከኢትዮጵያ ሴቶች ጋር እየተጋቡና እየተዋለዱ ተራብተው ነበር።

በኋላ ግን በአብርሃምና በአጽብሐ ዘመን ከሣቴ ብርሃን ሰላማ የተባለ ፍሬምናጦስ በኢትዮጵያ ወንጌልን በሰበከ ጊዜ ነገሥታቱ አብርሃና አጽብሐ ሊቀ ካህናቱ አንበረም መኳንንቱም ሁሉ በክርስቶስ አምነው ክርስቲያኖች ሲሆኑ ከነዚህ ከእስራኤል ወገን በትውልድ የተቀላቀሉ በሃይማኖትም የመሰሉ አንዳንድ የኢትዮጵያ ሰዎች ክርስቲያንነትን አንቀበልም ብለው ኦሪት ሕግ ጸንተውና ወገን ለይተው ይኖሩ ጀመር።

በዚህም ምክንያት በየጊዜው የሃይማኖት ሁከት የሚነሳባቸው ስለሆነ የመንግሥቱን ዋና ከተማ አክሱምን እየለቀቁ በሰሜንና በወገራ በወልቃይ በላስታም ዙሪያ ባሉት አገሮች ተበትነው ይኖሩ ጀመር። ስለዚህም ፈላሾች ተባሉ ይባላል።

የሰሜን አውራጃ ተራራማ ስለ ሆነ ከየስፍራው የተሰበሰቡ ፈላሾች ያለ ሥጋት በደህና ይኖሩ ነበር። ጦርም በመጣባቸው ጊዜ የተራራው የፍጥረቱ ምሽግነት ይጠብቃቸው ነበር።

እንደዚህም እየሆኑ ቁጥራቸው እየበዛና ኃይላቸውም እየበረታ በሄደ ጊዜ ከመካከላቸው ጌዴዎን የተባለ ሰው መርጠው በላያቸው እንደ ንጉሥ አደረጉት።

ጌዲዎንም ሴት ልጅ በወለደ ጊዜ ዮዲት ብሎ አወጣላት። አስቴርም ትባል ነበር። ዮዲኢትም እጅግ የተዋበጅ ቆንጆ ነበረችና በላስታ አጠገብ ያለውን ቡግና የሚባለውን አገር የሚገዛ ዘርዓ ጽዮን የተባለ ፈላሽነቷን ሳያስብ የመልኳ ውበትና ቁንጅናዋን ብቻ አይቶ አገባት። እርስዋም በውበቷና በፍቅሯ እየሳበች ወደ አይሁድ ሃይማኖት አስገባች። ስሙንም ሰሎሞን አሰኘችው።

በዚያንም ዘመን የኢትዮጵያ ድግናዥን የሚባለው ስለ ሞተ ልጁ ግዳዥን ነገሠና በ፲ ወሩ ሞተ። ለርሱም አንበሳ ውድም የተባለ ገና ሕፃን ልጅ ነበረውና እርሱን ቢያነግሡት መንግሥቱን ለመጠበቅና ለመግዛት የማይችል ሆነ።

ዮዲትም የአንበሳ ውድምን ሕፃንነት አይታ በሰሜንና በላስታ አውራጃ የሚኖሩት በትውልድና በሃይማኖት የሚመስሏትን ፈላሾችንና ማንዘራሾችን ሁሉ መሰብሰብ ጀመረች።

ሠራዊትም እንደ በዛላትና ኃይልዋ እንደ በረታ ባወቀች ጊዜ በ፰፻፵፪ /፰፻፵፱/ ዓ.ም በኃይል ነገሠች። መኳንንቱም ንጉሣቸው ሕፃን ስለ ሆነ ለመዋጋት የማይችሉ መሆናቸውን አውቀው ሕፃኑን ንጉሥ አንበሳ ውድምን ይዘው ከትግሬ ወደ ሸዋ ተሰደዱ።

ዮዲትም የክርስቲያንን ሃይማኖት አጥፍታ የፈላሻን ሃይማኖት ለማቆም ስለ አሰበች በትግሬ /ትግራይ/ አውራጃ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ማቃጠልና ካህናቱን መግደል ጀመረች። የአክሱምንም ቤተ ክርስቲያን አቃጠለች። በዙሪያውም ያሉትን ሐውልቶች አሁን ዛሬ ካሉት ከጥቂቶቹ በቀር ሁሉንም ሰባበረች።

ደግሞ ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ የመንግሥት ልጆች የሆኑትን ሁሉ እንዳይሸፍቱና ባገር ላይ ሁከትን እንዳያስነሱ እየተባለ ወደ ደብረ ዳሞ ተራራ እያወጡና እያኖሩ ንጉሥ በሞተ ጊዜ መኳንንቱ ወደ ደብረ ዳሞ ተራራ እየወጡ ከመንግሥት ልጆች የመረጡትን አንዱን እያወረዱ ያንግሡት ነበር። ዮዲትም ይህን ነገር ታውቅ ነበርና ምናልባት ሳትሞትም ቢሆን ወይም ከሞተች በኋላም ቢሆን የኢትዮጵያ መኳንንት በደብረ ዳሞ አንዱን የመንግሥት ዘር አውርደውና አንግሠው ለጊዜው እርስዋን በኋላም የርስዋን ዘር እንዳያጠፉ ስለ ፈራች በደብረ ዳሞ የሚኖሩትን የመንግሥት ልጆች ሁሉ ቅጥራቸው እስከ ፬፻ የሚሆነውን አሳረደቻቸው ይባላል። በዚህም በሥራዋ ክፋት ዮዲት የተባለውን ስሟን ለወጠው ጉዲት አሏት። ጉደኛ ማለት ነው። አስርቴርም የተባለውን ስሟን ለውጠው እሳቶ አሏት። የምታቃጥል እሳት ማለት ነው።

አንበሳ ውድምም ከዮዲት ሸሽቶ ወደ ሸዋ በመጣ ግዚኤ የሸዋ ሕዝብ በደስታ ተቀበሉት። ዮዲትም የሸዋ ሕዝብ አንበሳ ውድምን በደስታ እንደ ተቀበሉት በሰማች ጊዜ በነገሠች በ፳፫ ዓመት ብዙ ሠራዊት ሰብስባ ባንድ የጦር አበጋዝ አድርጋ ወደ ሸዋ እንዲዘዝምቱና ከአንበሳ ውድም ጋር እንዲዋጉ አዘዘች። አንበሳ ውድምም የመንዝን ባላገሮች ሰብስቦ ተዋግቶ ድል አድርጎ መለሳቸው።

ዮዲትም ሠራዊቷ ድል መሆናቸውን በሰማች ጊዜ የቀሩትን ሠራዊቷን ሰብስባ እርስዋ ራስዋ ወደ ሸዋ መጣች። አንበሳ ውድም የዮዲትን መምጣት በሰማ ጊዜ መንዝን ለቆ ወደ መርሐ ቤቴ ወረደ። እርስዋም ተከታትላ ወደ መርሐ ቤቴ ለመውረድ አስባ ሳለች የአህያ ፈጅና የዶባ መንገድ እጅግ አስቸጋሪ ስለ ሆነባትና የመንዝንም ባላገሮች እየተከታተሉ ሌሊት ሠፈር ላይ አደጋ እየታሉ ስለ አስጨነቋት በዚህ ሁሉ አደጋ ምክንያት በድንጋጤ ተመልሳ ወደ አክሱም ሄደች። እርስዋም ከሸዋ በተመለሰች በ፲፯ በነገሠች በ፵ ዓመት በ፰፻፹፪ /፰፻፹፱/ ዓመተ ምሕረት ሞተች።

አንበሳ ውድምም የዮዲትን ሞት በሰማ ጊዜ ገስግሶ ወደ አክሱም ሄደ። የአክሱም ሕዝብ በደስታ ተቀበለው ባባቶቹ አልጋ አስቀመጡት። የአክሱምንም ቤተ ክርስቲያን መልሶ ሠራ። ከፈላሾችም ወገን እስከሚቻለው ድረስ ብዙ ሰዎች ገደለ። ነገር ግን ኃይላቸው በርትቶ ነበርና በጭራሽ ሊያጠፋቸው አልቻለም። ሃያ ዓመት ያህል ከነገሠ በኋላ በ፱፻፪ /፱፻፱/ ዓ.ም አረፈና ልጁ ድልነአድ ነገሠ። በዮዲትም ዘመን በሰሜንና በላስታ የሚኖሩ ሰዎች ኃይላቸው ስለ በረታ ዮዲትም ካለፈች በኋላም ቢሆን ኃይላቸው አልደከመም ነበርና በየጊዜው ሁከት ማስነሳታቸው አልቀረም ነበር። በዚህም ምክንያት ድልነዓድ በአክሱም ተቀምጦ ኢትዮጵያን ለመግዛትና በሰላም ለመኖር አልተቻለውም። ፲ ዓመትም ያህል እንደ ነገሠ መራ ተክለ ሃይማኖት የተባለ ሰው ትርዳእ ጐበዝ በምትባል ሴት ረዳትነት በላስታ አውራጃ ስለተነሣበት ለመዋጋት አለመቻሉን አውቆ እንደ አባቱ እንደ አነብሳ ውድም አክሱምን ትቶ ወደ ሸዋ ስለ መጣ መራ ተክለ ሃይማኖት የድልነዓድን መንግሥት በኃይል ወስዶ በኢትዮጵያ ነገሠ። ስመ መንግሥቱም ዛጉዌ ተባለ። ዛጉዌ ማለት አንዳንድ ሰዎች እንደተረጐሙት «ዘአገዌ» ከአገው ማለት ነው ደግሞ ሌሎቹ እንደ ተረጐሙት በግዕዝ ቋንቋ ሸሸ ማለት ነውና ድልነዓድን ስለ አባረረ ዘአጉየየ ያባረረው ወይም ያሸሸው ማለት ነው ይላሉ።

ዛጉዌ /መራ ተክለ ሃይማኖት ማለቱ ይመስላል/ ከሞተ በኋላ ከርሱ ወገን አሥር ነገሥታት ነግሠው ኢትዮጵያን በኃይል ገዝተዋል። ስማቸውና ቁጥራቸውን ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን።

| ስማቸውና ቁጥራቸው | የነገሱበት ዘመን | ከክርስቶስ ልደት በኋላ |
|---|---|---|
| ፩ መራ ተክለ ሃይማኖት መንግሥቱ ዛጉዌ | ፲፫ | በ፱፻፲፪ |
| ፪ ጠጠውድም | ፵ | ፱፻፳፭ |
| ፫ ጃን ስዩም | ፵ | ፱፻፷፭ |
| ፬ ግርማ ስዩም | ፵ | ፲፻፭ |

| | | |
|---|---|---|
| ፭ መይራሪ | ፲፭ | ሺ፵፭ |
| ፮ ሀርበይ | ፲፯ | ሺ፰ |
| ፯ ይምርሐነ ክርስቶስ | ፵ | ሺ፸፯ |
| ፰ ቅዱስ ሀርቤ /ገብረ ማርያም/ | ፵ | ሺ፻፯ |
| ፱ ላሊበላ | ፵ | ሺ፻፶፯ |
| ፲ ነአኩቶ ለአብ | ፵ | ሺ፻፷፯ |
| ፲፩ ይትባረክ | ፰ | ሺ፪፻፴፯ |

ደግሞ ባንዳንድ ታሪክ ውስጥ መሪ ተክለ ሃይማኖት የድልነዓድን ልጅ መሶበ ወርቅ የምትባለውን አግብቶ ሸፈተ። ድልነዓድም ሠራዊት ሰብስቦ ጦርነት ቢገጥመው ድል ሆነና ሸሸ፣ መራ ተክለ ሃይማኖትም መንግሥቱን ወሰደ እየተባለ ተጽፎ ይገኛል።

እንደዚህ የተባለ እንደ ሆነ ግን መሶበ ወርቅ የድልነዓድ ልጅ ከሆነች መራ ተክለ ሃይማኖትም መሶበ ወርቅን አግብቶ ልጆች ወልዶ ልጆች በላስታ ከነገሡ መንግሥት ከቤተ እስራሌል /ቀዳማዊ ምኒልክ/ ወጥቶ ወደ ቤተ ዛጉዌ አለፈ ያሰኝም።

በማናቸውም ቢሆን ከድልነዓድ በኋላ ከነገሠው ከዛጉዌ ጀምሮ እስከ ይትባረክ በኢትዮጵያ በኃይል የነገሱ ፲፩ ነገሥታት ናቸው። ዘመኑም ፫፻፴፫ ዓመት ይሆናል።

ከነዚህም ከአሥራ አንዱ ነገሥታት መካከል ላሊበላ የተባለው ንጉሥ እጅግ ስመ ጥሩ ነበር። ምክንያቱም ከዚህ ቀጥለውን እንጽፋለን።

ቅዱስ ሀርቤ የተባለው ገብረ ማርያምና ላሊበላ ወንድማማች ናቸው። ከላሊበላም አስቀድሞ ታላቅ ወንድሙ ገብረ ማርያም ነግሶ ነበር። ገብረ ማርያምም ሲሞት ታናሽ ወንድሙ ላሊበላ ነገሠ።

በዛጉዌ ወገኖች ዝመእን እስላሞች ከዓረብ አገር ወደ ምድረ ግብፅ በጦርነት ገብተው አገሩን በያዙት ጊዜ በምድረ ግብጽ የሚኖሩትን ክርስቲያኖች ሁሉ ከሊቀ ጳጳሳቱ ጀምሮ እጅግ አስጨንቀዋቸው ነበር። ይልቁንም የእጅ ሥራ የሚያውቁትን ገንቢዎችንና አናጢዎችን ድንጋይ ጠራቢዎችን ሁሉ እንደ ርኩስ እያዩና እየተጠየፉ እንደ ባሮች አስጨንቀው ይገዟቸው ነበርና መከራውና ችግሩ ስለ በረባታቸው ወደ ሌላ አገር መሰደዳቸውን ትተው የሃይማኖት ወንድሞቻቸውን ሲፈልጉ ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው የዛጉዌ ወገኖች ዋና ከተማ ወደ ነበረው ወደ ላስታ ገቡ።

ላሊበላም ከምድረ ግብጽ ተሰደው ለመጡት ለሃይማኖት ወንድሞቼ የሚጠጉበትንና የሚያርፉበትን ሥፍራ ሰጣቸው።

ከጥቂት ወራት በኋላም ከነዚሁ መካከል የእጅ ሥራ ግንብ መገንባት እንጨት መጥረብ ደንጊያ መውቀር የሚያውቁ መኖራቸውን በሰማ ጊዜ እያስጠራ ቢጠይቃቸው እርግጥ መሆኑን አስረዱት።

ከዚህም በኋላ በተወለደበትና በነገሠበት በላስታ አገር ውስጥ ጭንጫና ደንጋማ የሆነ ሥፍራ ፈልጎ ውስጡን እያስቆፈረ የደንጊያ አዕማድ እያስጠረበና እያስፈለፈለ (እያስቦረቦረ) አሥራ አንድ አብያተ ክርስቲያናትን በመሬት ውስጥ አሳነፀ።

የነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው።

፩ ቤተ ደናግል

፪ ቤተ ማርያም

፫ ቤተ መድኃኔ ዓለም

፬ ቤተ መስቀል

፭ ቤተ ጐልጐታ

፮ ቤተ ቅዱስ ሚካኤል

፯ ቤተ ገብርኤል

፰ ቤተ አባ ሊባኖስ

፱ ቤተ መርቆሬዎስ

፲ ቤተ አማኑኤል

፲፩ ቤተ ጊዮርጊስ

ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት በላስታ ዙሪያ ያሳነፃቸው ፳፬ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው ይባላል።

እነዚህም ከምድረ ግብጽ እየተሰደዱ የመጡ ክርስቲያኖች የዓረብ እስላሞች አገራቸውን ስለ ወሰዱባቸውና ስለ አሳደዱዋቸው እነርሱም ብድር ለመመለስ ሲሉ ወደ አጼ ላሊበላ ገብተው በምድረ ግብጽ የሚኖሩ ሰዎች የዓባይን ውኃ ከመንገዱ አውጥተህ ወደ በረሃ የሰደኸው እንደሆነ አገራችንን ግብጽን የወሰዱ ባራካን የተባሉ እስላሞች ችግር ሲጸናባቸው እየለቀቁ ይሄዳሉ ብለው መከሩት።



ላሊበላ (ሮሀ) ገዳም



የቤተጊዮርጊስ ሕንፃ ቤተክርስቲያን

አጼ ላሊበላ የአባይን ውኃ ከመገዱ አውጥቶ ወደ በረሃ ለመስደድ እጅግ የሚያቸግርና የማይቻል መሆኑን አውቆ ለዓባይ ውኃ ኃይልና ብዛት የሚሰጡትን በዝናብ ጊዜ ብዙ ጐርፍ እያየዙ ወደ ዓባይ የሚገቡትንና ከየተራራው የሚወርዱትን ወንዞች ሁሉ ወደ ዓባይ እንዳይገቡ እየቆረጠ ወደ ሌላ ሥፍራ መስደድ ጀመረ። ከዚህም ሁሉ ምክንያት የላሊበላ ስሙ በሙሉ ኢትዮጵያ በውጭም አገር ሁሉ የታወቀ ሆነ። እነሆ ዛሬ እንኳ በመሬት ውስጥ የታነፁትን አብያተ ክርስቲያናት ሕንፃዎችን ለማየት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከየአውራጃው እየተሰበሰቡ በያመቱ እየሄዱ እንደ ኢየሩሳሌም ይሳለሙታል። ሥፍራውም ገዳመ ሮሐ ወይም ደብረ ሮሐ ተብሏል።

እነዚህም በመሬት ውስጥ የታነፁት አብያተ ክርስቲያን ሕንፃዎች እስከ ዛሬ ጸንቶ ይኖራልና ከውጭ አገርም የሚመጡ ብዙ እንግዶች ወደዚያ እየሄዱ ውስጡንና ውጭውን ፎቶግራፍ እያነሱ በታሪካቸውም እየጻፉት ይገኛሉ።

# ምዕራፍ ፬

## የኢትዮጵያ መንግሥት በኃይል ወደ ዛጉዌ ዘር ካለፈ ከ፫፻፵፫ ዓመት በኋላ እንደ ገና ወደ ቀዳማዊ ምኒልክ ዘር ወደ ይኩኖ አምላክ ከተመለሰበት ከሺ፪፻፶፫ /ሺ፪፻፶፫/ ጀምሮ ልብነድንግል እስከ ነገሠበት እስከ ሺ፬፻፴፪ /ሺ፭፻/ ዓመተ ምሕረት።

የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ዛጉዌ ዘር ካለፈ በኋላ ወደ ቀዳማዊ ዘር እንደ ገና የተመለሰበት ምክንያት ባጭሩ እንጽፋለን።

በዛጉዌ ወገኖች ነገሥታት ዘመን እየተያዙ እንዳይታሠሩና እንዳይሞቱ እየፈሩ በዱርና በዋሻ እየተደበቁ ዘራቸው ሳይጠፋ የቆዩ የቀዳማዊ ምኒልክ ወገኖች ፱ ናቸው። እነዚሁም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፉት ናቸው።

ድልነዓድ

አግብአ ጽዮን

ጽንፈ አርእድ

ነጋሽ ዞሬ

አሰፍሐ

ያዕቆብ

ባሕር ሰገድ

እድም አሰገድ /አድማስ ሰገድ/

ይኩኖ አምላክ

ነገር ግን ከትግሬ /ከትግራይ/ ተሰዶ ወደ ሸዋ ሳይመጣ አሥር ዓመት፣ ይኩኖ አምላክም የዛጉዌ መንግሥት ካለፈ በኋላ ፲፫ ዓመት ነግሠው ነበርና ሳይነግሡ ዕድሜአቸውን በስደትና በመከራ የጨረሱ ሰባቱ ናቸው።

ይኩኖ አምላክ የክርስትና ስሙ ተስፋ ኢየሱስ ነው። ብዙ ጊዜዜም በክርስትና ስሙ ይጠራ ነበር። ኋላ ግን ከቀዳማዊ ምኒልክ ዘር የተረፈ እርሱ ብቻ መሆኑን የሚያውቁ ሰዎች ይኩኖ አምላክ እያሉ ስለ ጠሩት ስሙ ሁኖ ቀረ። ትርጓሜውም «አምላክ ጠባቂ ረዳት ይሁነው» ማለት ነው። ለምሳሌ፡- በሀገራችን በኢትዮጵያ አንድ የታሰረ ሰው በታየ ጊዜ የሚያየው ሰው ሁሉ አሳሪው እንኳ ሳይቀር እግዚአብሔር ያወጣህ እንደሚለው ነው። ይኸውም የኢትዮጵያ ሰዎች በችግርና በመከራ ለሚኖር ሰው ርኅሩኅ መሆናቸውን ያስረዳል።

እድም አስገድ ልጅ ይኩኖ አምላክ ካደገ በኋላ ተይዞ እንዳይሞትበት ስለ ፈራ ወደ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም ወደ ሐይቅ ወስዶ ለገዳሙ መምሕር ለአባ ኢየሱስ ሞዓ አደራ ብሎ ሰጥቶት ነበርና ለክርስቲያን ልጆች የሚገባቸውን ትምህርት እየተማረ በሐይቅ ደሴት ይኖር ጀመር። ከብዙ ዘመንም በኋላ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከአባ ኢየሱስ ሞዓ ጋራ ለመገናኘት ወደ ሐይቅ ደሴት ገብተ ሳሉ ይኩኖ አምላክን በገዳሙ ውስጥ አይተው «ይህ ብላቴን የማን ልጅ ነው?» ብለው ቢጠይቁት የቀዳማዊ ምኒልክ ዘር የእድም አሰገድ ልጅ ነው ብለው ወደ ሐይቅ ደሴት የገባበትን ምክንያት ሁሉ ከስር እስከ ጫፍ ነገሯቸው።

በዚያ ዘመን አባ ተክለ ሃይማኖት በደብረ ሊባኖስ፣ አባ ኢየሱስ ሞዓ በሐይቅ ደሴት፣ አባ ዮሐኒ በደብረ ዳሞ ሆነው የቀዳማዊ ምኒልክ መንግሥት ትውልዱ ልዩ ወደ ሆነው ወደ ዛጉዌ በማለፉ እያዘኑ ወደ እግዚአብሔርም እየጸለዩ ይኖሩ ነበሩና አባ ተክለ ሃይማኖት የቀዳማዊ ምኒልክን ዘር ይኩኖ አምላክን በሐይቅ ደሴት በማግኘታቸውና በማየታቸው እጅግ ደስ አላቸው።

ከሐይቅም ወጥተው በሚሄዱበት ጊዜ ወደ አባ ኢየሱስ ሞዓ ቀርበው የቀዳማዊ ምኒልክ ዘር ይኩኖ አምላክ አሁን ያለበት ይህ ሥፍራ ለላስታ ቀርብ ነውና ተይዞ እንዳይታሰር ሸዋ ልውሰደው ብለው አማከሩዋቸው። አባ ኢየሱስ ሞዓም የአባ ተክለ

ሃይማኖት አሳብ መልካም መሆኑን ስለ ተረዱት ይዘውት ወደ ሸዋ እንዲመለሱ ፈቀዱላቸው።

በሸዋም አውራጃ በይፋት በመንዝ በተጉለት በመርሐቤቴ እነዚህን በመሰሉት አገሮች ሁሉ እየዞሩ በየባላባቶቹ ጋር አስተዋወቁት። ዋና መኖሪያው ግን በተጉለት እንዲሆን አደረጉ።

ይኩኖ አምልካ በጥበብና በዕውቀት በቁመትም እያደገ ስለ ሄደ ኃይለኛ ሆነ። አንዳንድ ጊዜም ይኩኖ አምላክ መሆኑ ሳይገለጥ ከሸዋ ወደ ላስታ እየሔደ እንግዳ እየመሰለ ለንጉሥም ሎሌነት እያደረገ ሥርዓተ መንግሥት እያየ ወደ ሸዋ ይመለስ ነበር ይባላል።

አቡነ ተክለ ሃይማኖትም የሸዋን ባላባቶች ልብ ሁሉ ወደ ይኩኖ አምላክ በመመለሳቸው ይኩኖ አምላክ እጅግ ደስ ስላለው «አባቴ ሆይ! እግዚአብሔር ያባቶችን መንግሥት እንዲመልስልኝ እንደሆነ ለእርስዎም ያባትዎን የአዛርያስን ሊቀ ካህናትነት እመልስልዎታለሁ» ብሎ የልቡን አሳብ ገልጦ ነገራቸው። ከዚህም በኋላ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከሸዋ ተነሥተው ወደ አማራ አገር ሄዱ። በዚያም በቤጌምድርና በላስታ አውራጆች እየተዘዋወሩ ወንጌልን ሲያስተምሩ ወዲያውም የዛጉዌ ወገኖች በኢትዮጵያ መንገሣቸው የማይገባ መሆኑን ለየባላባቶች ለየትልልቁ ስዎች እያስረዱ ይሰብኩ ጀመር። /ፕሮፓጋንዳ አደረጉ ማለት ነው/

ወደ አጼ ነአኩቶ ለአብም ገብተው የኢትዮጵያን መንግሥት የወሰዳችሁት በማይገባ በኃይል ነውና ለሚገባው መልሱ እያሉ ሳይፈሩ በግልጥና በድፍረት ነገሩት።

ነአኩቶም ለአብም እግዚአብሔርን የፈራ ደግ ንጉሥ ነበርና ባንድ ወገን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሐዋርያ መሆናቸውን ስለ አወቀ በሁለተኛውም ወገን ዛጉዌዎች ትውልዳቸው ከቀዳማዊ ምኒልክ ወገን ሳይሆን መንግሥቱን የወሰዱት በኃይል መሆኑን ስለ ተረዳው በ፫ኛውም ወገን የሕዝቡ ልብ ወደ ቀዳማዊ ምኒልክ ዘር እንደ ተመለሰ ስለሰማ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የነገሩትን የምክር ቃል በፍጥነት ተቀበለ። ነገር ግን ምክራቸው ከፈጸሙ አስቀድሞ ሁለቱንም ትልልቆቹን አሳቦቹን ገልጦ ነገራቸው።

፩ኛው አሳቡ። ከቀዳማዊ ምኒልክ ወገን መንግሥት የሚገባው ሰው ከተገኘ መንግሥቱን እንመልሳለን። ነገር ግን የእኔ ዘመነ መንግሥት ካለፈ በኋላ ነው እንጂ፣ በእኔ ዘመን አይሆንም የሚል ነው።

፪ኛው አሳቡ ግን መንግሥቱ የሚመለስበት ንጉሥ ስለ ዛጉዌ ወገኖች ኑሮ ቃል ኪዳን ይግባልን የሚል ነው። የቃል ኪዳኑም አሳብ ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው።

፭ኛ የዛጉዌ ወገኖች በማይገባ በኃይል የወሰዱትን መንግሥት ለሚነግሠው ለቀዳማዊ ምኒልክ ዘር ለይኩኖ አምላክ እንዲመልሱ ነው።

፪ተኛ ይኩኖ አምላክ መንግሥቱን ከተቀበለ በኋላ ከዛጉዌ ዘር አንድ መስፍን እየመረጠ በላስታ አልጋ እንዲሾም፤ የላታም ግዛት ከዛጉዌ ወገኖች እንዳይወጣ ነው።

፫ኛ ላስታን በሚገዛ መስፍን የንጉሡ የዛጉዌ ዘር ለመሆኑ ምልክቱ ሁለት የብር ነጋሪት እንዲያስጭን፣ የዘበኞቹም ጦር ባለ ብር ሽቦ እንዲሆን የዓላማአውም መያዣ የሰንደቁ ጫፍ የብር እንዲሆን ነው።

፬ኛ የቀዳማዊ ምኒልክ ዘር የሆነው ንጉሥ በወርቅ ዙፋን ሲቀመጥ የላስታው መስፍን በትንሽ የብር ወንበር እንዲቀመጥ ከንግሡም ጋራ በሚገናኝበት ጊዜ ወንድም ከወንድሙ ጋር እንዲገናኝ እንጂ፣ እንደ ሌሎች መሳፍንቶች ምድር እንዳይስም ነው።

፭ኛ በርስቱ ማናቸውም ዓይነት ግብር እንዳይገብርና ሌሎች መሳፍንቶች በግድ ሊያደርጉ የሚታዘዙትን ሁሉ ለማድረግ በግድ እንዳይታዘዝ ነው።

፮ኛ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ላስታና ወደ ሸዋ እየተመላለሱ ይህን የወዳጅነት ውል አዋውለው በቃል ስለ አስታወቁ በኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት በየገጠሩም አብያተ ክርስቲያናት ለሚኖሩ ለሊቃውንቱና ለመነኰሳቱ ለቀሳውስቱና ለዲያቆናቱ ለመምሕራኑና ለተማሪዎቹ ሁሉ ለልብሳቸውና ለምግባቸው ለሌላውም ችግራቸው ሁሉ እንዲሆን የመንግሥቱን ሲሶ እንዲወስዱ ነው።

ሥርዋጽ። በዮዲት መንግሥት ፵ ዓመት በዛጉዌ ወገኖች መንግሥት ፫፻፴፫ ዓመት በድምሩ ፫፻፸፫ ዓመት የቤተ ክርስቲያናት ርስትና ጉልት ሁሉ በመንግሥት እጅ ሆኖ ነበርና ነአኩቶ ለአብ መንግሥትን ለሚገባው ለቀዳማዊ ምኒልክ ዘር ለይኩኖ አምላክ ሲመልስ የቤተ ክርስቲያንም ርስት ጉልት ለሚገባው ለሊቀ ካህናቱ ለአዛርያስ ዘር ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት መመለሱ ነው። የሲሶ መንግሥትም ትርጓሜው ይህ ነው እንጂ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሦስት ተከፍሎ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አንድ እጅ አገር ግዛቱን ወሰዱ ማለት አይደለም።



አቡነ ተክለ ሃይማኖት

አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ነአኩቶ ለአብ ያቀረበውን የቃል ኪዳን አሳብ ለይኩኖ አምላክ አስታወቀ በግዝትና በመሃላ አስታረቋቸው። ዕርቁ ግን በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ማካይነት ተላልከው ነው እንጅ፣ ይኩኖ አምላክ ወደ ላስታ ሄዶ ወደ ነአኩቶ ለአብ ወደ ሸዋ መጥቶ ዓይን ለዓይን ተያይተው ቃል ለቃል ተነጋግረው አይደለም።

ከዚህም በኋላ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በጳጳስነታቸው ቅብዓ መንግሥቱን አሰናድተው ይኩኖ አምላክን ስለቀቡት ለጊዜው በሸዋ፣ ነአኩቶ ለአብ ከሞተ በኋላ ግን በሙሉ ኢትዮጵያ ነገሡ። እንደ ቃል ኪዳናቸውም የዛጉዌ ዘር የሚሆን ይትባረክ የተባለው የላሊበላ ልጅ እልመክኑን ብቻ በላስታ አልጋ ተቀመተ።

አንባቢዎች ሆይ! በላስታ ቤተ መንግሥት አንድ አውራ ድሮ የእኔን ራስ የበላ ይነግሣል እያለ ሲጮህ ንጉሡ እልመክኑን ሰምቶ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት ነገራቸው። አቡነ ተክለ ሃይማኖትም አሳርደው ብለው ስለ መከሩት ወጥ ሠርተሽ አቅርቢልኝ ብሎ ከነገራት በኋላ የዶሮውን ራስ ንጉሡ የማይበላ መስሏት ጣለችውና ይኩኖ አምላክ አግኝቶ በልቶ ነገሠ ተብሎ እንደ ተረት የተጻፈውን ታሪክ ሳልጽፍላችሁ በመቅረቴ እንዳታዝኑ እለምናችኋለሁ። አለመጻፌም እውነትን ፈላጊዎች ከሆናችሁ የተረት ነገር አያስፈልጋችሁም ብዬ ነው።

ይኩኖ አምላክ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጸሎትና እርዳታ ያባቶቹ መንግሥት በተመለሰለት ጊዜ አንዳንድ የዮዲት የዛጉዌ ወገኖች /በትግራይና/ በአማራ አገር እንዲገኙ ከማወቁ የተነሣ ሁለተኛ በመንግሥቱ ላይ ሁከት እንዳይነሳ ስለ ፈራ ወደ አክሱምና አማራ አገር መሄዱን ትቶ ዋና ከተማውን በሸዋ ውስጥ በተጉለት አውራጃ አደረገ።

| ስማቸውና ቁጥራቸው | የነገሡበት ዘመን | ከክርስቶስ ልደት በኋላ |
|---|---|---|
| ፻፳፫ ይኩኖ አምላክ | ፲፭ | ሺ፪፻፵፭ |
| ፻፳፬ አግብአ ጽዮን | ፱ | ሺ፪፻፳ |
| ፻፳፭ ጽንፈ አርአድ | ፩ | ሺ፪፻፳፱ |
| ፻፳፮ ሕዝብ አስገድ | ፩ | ሺ፪፻፴፩ |
| ፻፳፯ ቅድመ አስገድ | ፩ | ሺ፪፻፴፪ |
| ፻፳፰ ጃን አስገድ | ፩ | ሺ፪፻፴፩ |
| ፻፳፱ ሰብአ አስገድ | ፩ | ሺ፪፻፴፫ |
| ፻፴ ውድም አርዕድ | ፲፭ | ሺ፪፻፴፬ |
| ፻፴፩ ዓምድ ጽዮን | ፴ | ሺ፪፻፹፱ |
| ፻፴፪ ሰይፈ አርእድ | ፳፰ | ሺ፫፻፲፱ |
| ፻፴፫ ውድም አስፈሬ | ፲ | ሺ፫፻፵፯ |
| ፻፴፬ ዳዊት | ፳፫ | ሺ፫፻፶፯ |

| | | |
|---|---|---|
| ፻፸፫ ቴዎድሮስ | ፲፩ | ሺ፫፻፶፰ |
| ፻፸፬ ይስሐቅ | ፲፫ | ሺ፫፻፺፩ |
| ፻፸፯ እስክንድር | ፯ወር | ..... |
| ፻፸፰ ሕዝበ ናኝ | ፬ | ሺ፬፻፯ |
| ፻፸፱ በድል ናኝ | ፩ | ሺ፬፻፲ |
| ፻፹ ዓምደ ጽዮን | ፮ | ሺ፬፻፲፩ |
| ፻፹፩ ዘርዐ ያዕቆብ | ፴፬ | ሺ፬፻፲፰ |

በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ካቶሊክ ቤተ ክርሲያንና በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መካከል ትልቅ ክርክር ተነስቶ ነበር። ምክንያቱም የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ይሥርፃል ስትል የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከአብ ብቻ ይሥርፃርል ስለ ማለቷ ነው።

ቢሆንም በዚህ ዘመን የሃይማኖት መለያየት ገና ስላልተጀመረ የዓለም አብያተ ክርስቲያን ሁሉ አለቃ የሮም ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ስለሆነ አዛዡ እርሱ ነበርና ጉባዔው በሮማ አጠገብ ፍሎርንጻ /ፍሎሬንስ/ በሚባል ከተማ እንዲሆን አድርጐ ነበር።

ይልቁንም አጼ ዘርዐ ያዕቆብ የመንፈሳዊ መጻሕፍትን የተማረ በመሆኑና በዘመኑም ለመንፈሳዊ ሥራው ረዳት የሆኑትን የጋስጫውን አባ ጊዮርጊስን በማግኘቱ ድርሰት እየደረሰ ይጽፍ ነበር። በዚህም ላይ በዓለ ወልድና፣ በዓለ ማርያም በዓለ ሚካኤልም በየወሩ እንዲከበሩ ቀዳሚት ሰንበትም እንዳትሻር አዋጅ ነግሮ ይህን በመሰለ ሥራው ሁሉ ስሙ በጣም የታወቀና የተከበረ ሆኖ ነበር።

አጼ ልብነ ድግንል ስመ መንግሥቱ ወናግ ሰገ ነው። ወናግ ማለት በውጋዴን ቋንቋ አንበሳ ማለት ነው። ልብን ማለትም በግዕዝ ቋንቋ ዕጣን ማለት ነው።

| ስማቸውና ቁጥራቸው | የነገሱበት ዘመን | ከክርስቶስ ልደት በኋላ |
|---|---|---|
| ፻፹፪ በእደ ማርያም | ፲ | ሺ፬፻፶፪ |
| ፻፹፫ እስክንድር | ፲፯ | ሺ፬፻፷፪ |
| ፻፹፬ ዓምደ ጽዮን | ...፩ | ሺ፬፻፸፰ |
| ፻፹፭ ናዖድ | ፲፫ | ሺ፬፻፸፱ |
| ፻፹፮ ልብነ ድንግል | ፴ | ሺ፭፻፺፪ |

ልብነ ድንግል በነገሠ ፲፭ኛው ዓመት በክርስቲያኖችና በአዳል (በአፋር) እስላሞች መካከል ጦርነት ተጀምሮ ነበርና አንድ ጊዜ የክርስቲያን ወገን ድል እያደረገ አንድ ጊዜም የአዳል (የአፋር) ወገን ድል እያደረገ አምስት ዓመት የህል ብርቱ ጦርነት ሆኖ ነበር።

አዳሎችም (አፋሮችም) የቱርኩን መንግሥት ሹም የዘይላውን ገዥ መሐመድ ግራኝን ረዳት አድርገው ስለ ተነሱ ኃያላቸው እየበረታ ሄዶ ነበርና በይፋት በማፉድ መጥተው አጼ ልብነ ድንግል በሄደበት ሥፍራ እየተከታተሉ ይወጉት ጀመር። ልብነ ድንግል ጦርነቱ ዘወትር በመሆኑ ስለ ደከመ ሸዋን ትቶ ወደ አማራው አገር ለመሄድ አሰበና አያቱን እቴጌ እሌኒን ሚስቱንም እቴጌ ሰብለ ወንጌልን ወንዶችና ሴቶች ልጆች ሁሉ ይዞ ተነሣ።

የወንዶች ልጆች ስም ፈቅጦር፣ ሚናስ፣ ያዕቆብ፣ ገላውዴዎስ ነው፣ መንዝ ላይ ገሆር የሚባለው አገር ሲደርስ ለልጁ ለአቤቶ ያዕቆብ ልብሰ መንግሥቱን ሰጥቶ ባላገሮቹን አደራ ብሎ ከሴቶቹ ጋር ትቶት ሔደ።

እንደዚህም ማድረጉ የመንዝ አገር ገደልና ዋሻ የሞላበት ለጠላት የማይመች መሆኑን ያውቃልና ምናልባት የመሐመድ ግራኝ ጦርነት እየበረታ የሄደ እንደሆነ ዘር እንዳይጠፋ ብሎ ነው።

እንግዲህ የአጼ ልብነ ድንግልና የመሐመድ ግራኝን መጨረሻ በተከታዩ በኋለኛው ታሪክ እጽፈዋለሁ። አሁን የተመራሁበትን የሸዋ ባላባቶች ግንድ የሚሆን አቤቶ ያዕቆብን መሠረት አድርጌ ወደ ፊት ያሉትን የሸዋን ባላባቶች ታሪክ እጀምራለሁ።

# ምዕራፍ ፫

## <u>ስለ አቤቶ ያዕቆብ</u>

አቤቶ ያዕቆብ የግራኝ መሐመድ ጦርነት እስቲጨረስ የአጼ ልብነ ድንግል ልጅ መሆኑ እንዲታወቅበት በመንዝ አውራጃ ካንዱ ሥፍራ ወደ ሌላው ሥፍራ እየተዘዋወረ ሲኖር በኋላ ንግሥተ አዜብ የምትባል ከጐንደር የመጣች ሴት አግብቶ ሦስት ልጆችና አንዲት ሴት ልጅ ወለደ። የወንዶቹ ልጆች ስም ፋሲል፣ ሥግው ቃል ተዝካረ - ድንግል ነው። የሴቲቱ ልጅ ስም ወለተ ማርያም ነው።

ፋሲል ደግና ልበ ቅን ሰው ስለ ነበረ ገራም ፋሲኢል ተባለ ይባላል። እርሱም ከጐጃም ባላባት ወገን ወይዘሮ ሐመልማል የምትባለዋን አግብቶ አቤቶ ሱስንዮስን ወለደ። አበቶ ሱስንዮስም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆኖ በጐንደር ይኖር ነበርና የእርሱ ትውልድ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እየተባሉ እስከ ተፍጻሜተ መንግሥት ተክለ ጊዮርጊስ ፲፱ ነገሥታት ነግሠው ኢትዮጵያን ገዝተዋል።

የአቤቶ ያዕቆብ ሴቲቱ ልጁ ወይዘሮ ወለተ ማርያምም መርድ አዝማች ከፍሉን አግብታ ደጃዝማች ወልደ ክርስቶስን ወይዘሮ ሮማነ ወርቅን ወይዘሮ ሕልቀተ ድንግልን ወለደች። ከዚህም በኋላ ደጃዝማች ወልደ ክርስቶስ ፺ ልጆች ወይዘሮ ሮማነ ወርቅ ፺ ልጆች ወለዱና እነዚህ ፻፹ቱ የከምከም ዙፋን ወይዛዝሮች እየተባሉ ኖሩ።

ሦስተኛው ልጁ አቤቶ ሥግወ - ቃል ወይዘሮ ሰንበልትን ወለደና ወይዘሮ ሰንበልት አቤቶ ነጋሢን ወለደች። የክርስትና ስሙ ነጋሢ - ክርስቶስ ነው። ወይዘሮ ሕልቀተ ድንግል ግን መካን ስለ ነበረች ልጅ ሳትወልድ ሞተች።

እንዲህ በጐንደርም፣ በሸዋ፣ በጐጃምም አልጋውን የያዙ ባላባቶች የአቤቶ ያዕቆብ ልጆች መሆናቸውን ይህ ብቻ ያስረዳል።

# ምዕራፍ ፺

## <u>ስለ አቤቶ ነጋሢ</u>

አጼ ልብነ ድንግል በመሐመድ ግራኝ ጦርነት ከሸዋ እስከ ትግሬ /ትግራይ/ እየሸሸ ሄዶ ትግሬ /ትግራይ/ ላይ ስለ ሞተ ልጁ ገላውዴዎስ ያባቱን ዙፋን ወረሰና በፖርቱጊዝ ወታደሮች እርዳታ ከመሐመድ ግራኝ ጋራ ተዋግቶ ግራኝን ድል አድርጎ ገደለው።

ከዚህም በኋላ መንግሥቱን አደላድሎ ሲኖር በነገሠ በ፲፯ኛው ዓመት የወንድሙን የአቤቶ ያዕቆብን ሞት ስለ ሰማ እናታቸው እቴጌ ሰብለ ወንጌልም በዚያው ነበረችና በአፄ ገላውዴዎስ ከተማ ትልቅ ኀዘን ተደረገ።

ከዚያም ወዲህ በሸዋ አንድ አጠቃላይ ገዥ ስላልተገኘ በያውራጃው ባላባቶች ተነስተው አገሩን ተካፍለው በርስት እየተዋጉ ይኖሩ ጀመር።

እነዚህ ከነጋሢ ፊትና ከነጋሢ በኋላም በሸዋ የተነሱ ባላባቶች ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

ከአንጾኪያ መርድ ደጃዝማች ዘሜ ወይም ዘሚካኤል።
በኤፍራታ ወልደ ገብርኤል።
በግድም ለታ።
በመንዝ ማማ።
ደግሞ ባንድ ወገን መንዝ ባላምባራስ ላሎ።
በግሼ አውሳብዮስ።

በዶባ ጌታቸው።
በደቡብ ጸጋ።
በምሁይ አዛዥ መሄዲ።
በመርሐቤቴ በኲራ ወልዱ።
በሞረት ጥዱ።
በተጉለት ይገባዋል።
በወግዳ ሕርያቆስ።

የነዚህ ሁሉ አገር የማይመች ገደልና ዋሻ ፍርኩታና ኮረብታ ባይሆን ኖሮ ጋልው /ኦሮሞው/ ብዙ ነበርና ለዘር እንኳ ሰው አይተርፍም ነበር። ዳሩ ግን ሀገሩ አስቸጋሪ ስለ መሆኑ በርሳቸው ከመዋጋት በቀር ጋላ /ኦሮሞ/ አላጠቃቸውም ነበር።

ደግሞ ሁሉ በየበኩላቸው በጐንደር ለሚቀመጠው ንጉሠ ነገሥት ግብር እየገበሩ በወሰን ሲጣሉና የባሰ ችግር ሲያገኛቸው ሁሉም በየበኩላቸው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ መላከተኞች ይልኩ ነበር።

በዚያንም ዘመን በጐንደር የነበረው አጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ በነገሠ በ፲፩ኛው ዓመት ለመላከተኞቹ ሁሉ አንድ ደብዳቤ ሰጣቸውና ደብዳቤውን ተቀብለው ከጐንደር ተመልሰው ደብረ ሊባኖስ መግባታቸው በተሰማ ጊዜ የሸዋ ባላባቶችና የቀሩትም መኳንንቶች ወደ ደብረ ሊባኖስ ወረዱ። የቡልጋና የጠራ ሰዎች ብቻ መንገዳቸውን ጋላ /ኦሮሞ/ ስለ አቋረጣቸው ወደ ደብረ ሊባኖስ ለመውረድ አልቻሉም ነበር። ወደ ደብረ ሊባኖስ መውረዳቸው ለሁሉም አማካይ ሥፍራ እንዲሆን አጼ ስለ አዘዙ ይመስላል።

የደብዳቤውም ቃል በግዕዝ ቋንቋ የተጻፈው «ዛቲ ጦርማ ዘተፍነወት እምኀበ ንጉሠ ነገሥት እያሱ ዘተሰየመ አድያም ሰገድ። ትብጻሕ ኀበ መኳንንተ ሸዋ። ሰላም ለክሙ። እስመ እመጽእ ኀቤክሙ በቅሩብ መዋዕል፤ ተዓገሡ ኀዳጠ እስከ እመጽእ ወአሃውደክሙ። ተጽሕፈ በጐንደር በ፲፻ወ፮፻ወ፪ ዓመተ ምሕረት» የሚል ነበር።

አቤቶ ነጋሢ ግን ኃይለኛና ብርቱ ስለ ሆነ ጋላው /ኦሮሞው/ ወደ መንዝ እየወርደ ለመዋጋት በሚመጣበት ጊዜ እርሱ እየወጣና እየተዋጋ ይመልሰው ነበር።

ደግሞ በዚያን ዘመን እንደ ነበረው እንደ አገሩ ልማድ የመንዝ ሰዎች ወደ አዳባይ ወንዝ እየወረዱ እርስ በርሳቸው ይዋጉ ነበርና አቤቶ ነጋሢ ባለበት በኲል ዘወትር ያሸንፍ ነበር። በዚህም ሁሉ ምክንያት ስሙ በየሥፍራው የታወቀ ሆነ።

ከዚያም በኋላ ዋና ቤቱን በአንጋች አድርጐ ሲኖር አከዋን፣ ዳኛን ስብስትያኖስን፣ ሻንቆን፣ ዮናኤልን ወርቂትን ወለደ።

ደግሞ በጉብዝናው ላይ ሥራ ወዳድ ነበርና ጅጌ የሚባል ድግስ እያስደገሰ ያገሩን ሰው በልመና እየሰበሰበ መሬቱን ያስቆፍር ነበር።

እንደዚህም እያደረገ መሬቱን ሲያስቆፍር በመሬት ውስጥ በማሰሮ የተቀበረ ወርቅ አገኙና ብዙ ሎሌ አሳደረ። ኃይልም ስለ ተሰማው ወደ ጌስ እየወጣ ደገኛውን እየዘረፈ ገንዘብና ጉልበት ባገኘ ጊዜ ከጌራ ጋር ውጊያ ጀመረ።

ሽማግሌዎቹም ተሰብስበው «ከሞፈር ውሃ ወዲያ በጌራ አትድረስበት፣ እርሱም ከሞፈር ውሃ ወዲህ አይድረስብህ» ቢሉት ለጊዜው እሺ ብሎ ታረቀና እንደ ገና እርቅ አፍርሶ ሞፈር ውሃን አልፎ ጌራን ይወጋ ጀመር።

ከዚህም በኋላ አጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ በነገሠ በ፲፬ ዓመት በ፲፯፻፹፬ ዓ.ም ከጐንደር ተነስቶ በማኅደረ ማርያም አድርጐ ወደ ሽዋ በገዛ ጊዜ የሽዋ ባላባቶችና መኳንንቶች ሁሉ በደስታ ተቀበሉት። ከነዚሁም መካከል መርድ አዝማች ዘሚካኤል ቅኔ አዋቂ ነበርና ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቅኔ አበረከተ።

በአስተናስኦ ማኅሌት ወበይባቤ፤

ኢያሱ ንጉሥ ተቀበልናከ።

እመሰ ይደሉ እግዚኦ እምወሀብናከ ሰጊደ፣

ወእምረሰይናከ አምላከ ዋህደ፣

ባሕሩ አምላክ ዘእምቤትከ ተወልደ፣

ውስተ ደብረ ሲና አመ ወረደ፣

በቅድመ ሙሴ ወአሮን ይቤ ገሃደ፣

እንቤሌየ ኢታምልኩ ባዕደ።

## ትርጓሜ

ንጉሡ ኢያሱ ሆይ! በዘፈንና በእልልታ ተቀበልንህ፣

ጌታ ሆይ! የሚገባ ቢሆንስ በሰገድልንህ ነበር፣

አንድ አምላክም ባደረግንህ ነበር፣

ነገር ግን ከወገንህ የተወለደው አምላክ፣

ወደ ደብረ ሲና በወረደ ጊዜ

በሙስና በአሮን ፊት በግልጥ ተናግሮዋልና

ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልኩ ብሎአል።

## አጭር ትርጓሜ

ከወገንህ የተወለደው አምላክ በደብረ ሲና በወረደ ጊዜ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልኩ ብሎ ባልተናገረ ኑሮ አንተን አድያም ሰገድ ኢያሱን አምላክ አድርገን በሰገድንልህም ነበር ማለት ነው።

የሸዋም ባላባቶች አስቀድሞ እርስ በራሳቸው ሲጣሉ ነበርና አድያም ሰገድ ኢያሱ በምክርም በማስፈራራትም ሁሉንም አስማምቶ አስታረቃቸው።

አቤቶ ነጋሢም ወደ አጼ ኢያሱ ቀርቦ የአጼ ልብነ ድንግል ዘር መሆኑን ስለ ተናገረ ወዲያውም ኃይለኛ ጐበዝ መሆኑ ስለ ተመሰከረለት ከጋላው /ከኦሮሞው/ አገር ግዛት ጨምሮለት ሹመትና ሽልማት ሰጥቶት ወደ ጐንደር ተመለሰ።

ከዚህም በኋላ ዓይኔ በሚባል አገር ከተማውን ቀርቍሮ የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሠራ። እስከ ቆቦ እከ መንግሥት እስከ ሮቢኢ ከጣርማ በር በታች እስከ አዋዲ አቅንቶ መሬቱን ለዘመዶቹ ለመንዞች መራቸው።

እንደዚህም እያደረገ ማኻል ሸዋን ሰባት ዓመት ያህል ከገዛ በኋላ ማኅተምና የማዕርግ ስም ለማስፈቀድ ወደ ጐንደር ሄዶ ነበርና አገርሁ ሁሉ በጋላ /በኦሮሞ/ ስለ ታጠረ መመለሻ መንገድ ቸግሮት በዝያው በጐንደር ብዙ ዘመን ኖረ። በኋላም በድንገት ቢታመም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የኑዛዜ ቃል ተናገረ። አልጋዬን ለአካዋ፣ ጦሬንና የብር ካራዬን ለስብስቴ፣ ገንዘቤንና ርስቴን ለቀሩት ልጆቼ ሰጥቻለሁ አለ።

ከዚህም በኋላ በሽታው እየጠነከረ ስለ ሄደ አረፈና በዚያው በጐንደር ፊት አቦ በሚባለው ደብረ ተቀበረ።

# ምዕራፍ ፺

## ስለ ስብስቴ /ስብስትያኖስ/

አቤቶ ነጋሢ በኑዛዜው አልጋዬን ለአካዋ ብሎ ስለተናዘዘ ባንጋች በአባቱ አልጋ አካዋን አስቀምጠውት ነበር። ነገር ግን ያልተማረ ሕዝብ ድርቅም ቢሆን ረሀብም ቢሆን

በገዥውና በንጉሡ ያመካኛልና አካዋ በአልጋው በተቀመጠበት ዘመን ዝናም ጠፍቶ ድርቅ ስለሆነ እርሱን ሽረው ወንድሙን ዳኛን በአባቱ አልጋ አስቀመጡት።

አቤቶ ስብስቴ ግን ይህን የአልጋውን መዘዋወር ባየ ጊዜ እዚህ ከወንድሞቹ ጋራ ከመጣላትና ከመጋደል ወደ ሩቅ አገር ሄጄ ላንድ ጌታ ሎሌ ሆኜ ብኖር ይሻለኛል ብሎ ወደ መርሐቤቴ ወረደ።

መሐመድ ግራኝ ሸዋን ካጠፋው በኋላ ቤተ መንግሥቱ በጐንደር ስለሆነ ሸዋን ባላባቶች እየተካፈሉ እንደ ንግሥ እየሆኑ ይገዙት ነበር። በዚያም ዘመን በመርሐ ቤቴ እንደ ንጉሥ ሆኖ የሚገዛው ባላባት መዘምር ይባል ነበርና ስብስቴ ለመዘምር ሎሌነት ገብቶ ተቀመጠ።

ዘመዘምር ስብስቴ የአቤቶ ነጋሢ ልጅ መሆኑ ስለ አወቀ ለጊዜው አክብሮ ያኖረው ጀመር። በኋላ ግን መነኩሴ ነኝ የሚል አንድ ሰው ወደ መዘምር ገብቶ «የዚህ ሰው የልጅ ልጅ ያንተን የልጅ ልጅ ከምድር ጋራ ረግጦ መሬት አስልሶ ይገዛዋል» ብሎ እንደ ትንቢት ያለ ነገረው ከዚያ ቀን ጀምሮ ስብቴን በመልካም ዓይን የማያየው ሆነ። ከብዙ ቀንም በኋላ የመርሐቤቴ ባላባት መዘምር ጐሽ ለማደን ወጥቶ ሳለ በደለማ ወረዳ በልበልቲ በሚባል አገር ብዙ ደን ያለበት ሥፍራ ነበርና ከአሽከሮቹ ጋር እየተነጋገረ ሲያልፍ አንድ ጐሽ ወገሽና ብቅ አለ። ከዚያንም ጊዜ አሽከሮቹ ሁሉ ትተውት ሲበተኑ ስብስቴ ቀርቶ ነበርና ጦሩን ነጠል አድርጐ «ኮርማው ስብስቴ! » ብሎ ቢወረውር ሽንጡን ወግቶ ባንድ አወጋግ ገደለው። ስለሆነም አደኑ በመዘምር ስም ነውና የመዘምር ግዳይ ተባለ።

መዘምርም ስብስቴ የሠራውን ሥራና መነኩሴው የነገረውን ነገር አመዛዝኖ ልቡ ስለ ፈራ መኳንንቱን ሰብስቦ «ከዚህ ቀደም የስብስቴን ነገር መነኩሴ ነግሮኝ ነበር። አሁን ያደረገውን ነገር አይታችኋል። ባንድ ጊዜ ውርወራ ጐሽ ገደል ከእንግዲህ ምን ሰው ይተርፈዋል? አሁንም ሳይሰማ በደለማ እጁን ይዘን ብናስረው አይሻልም ወይ? » ብሎ ምክር ጠየቃቸው።

መኳንንቱ ግን «ለጌታችን ይህ ነገር የታየህ አይመስለንም። አሁን በዚህ እንያዝህ ብንለው ብርታቱና ጀግንነቱን ባንድ ጊዜ ውርወራ ጐሽ ሲገድል አይተኸዋል።

ይህን የመሰለው ሰው መያዝ ከቤት ገብቶ ግብር እንዲበላ ጠርቶ ትጥቁን አስፈቶ ነው እንጂ ከሜዳ ላይ እንያዝህ ቢሉት ሰው ይፈጃል እንጂ አይያዝም ብለው ስለ መከሩት መልካም ነው ብሎ ተወው።

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ለማዳን ለፈቀደው ምክንያት ይፈልግለታልና በደጋው በነጋሢ አልጋ የተቀመጠው ዳኛ የሚባል የጐረቤቱ ጋራ ጦርነት እየገጠመ ድል ስለሆነ

ወገኖች ለጦርነት ግምባር የለውም ብለው ሸረው ስብስቴን ባልጋው ለማስቀመጥ ፈልገው መርሐቤቴ ድረስ መልዕክተኞች ላኩበት።

ሲልኩ ግን «እንዲያው ና! ብንለው አይመጣምና እናቱን አጥብቆ የሚወድ ስለሆነ እናትህ በብርቱ በሽታ ታማ በነፍሴ ድረስልኝ ብላሃለች» ብላችሁ ንገሩት ብለው ለመላክተኞች አስጠንቅቀዋችው ነበር።

መላክተኞቹም መርሐቤቴ ወርደው ከመዘርም ደጅ ሆነው ስብስቴን ቢጠይቁ ከጌአው ጋራ አደን ሄዷል ብለው ስለ ነገራቸው በእድሞ ስር ተቀምጠው ሲጠብቁ መዘመር ስለ ጐሹ ግዳይ ሆ! እያሰኘና እያፈነጠዘ ሲመጣ አዩና ወደ አጀቡ ቀርበው በስብስቴ እግር ላይ ወድቀው ይስሙት ጀመር።

ስብስቴም መላክተኖቹን ባየ ጊዜ «እናቴ ደህና ባትሆን ይሆናል እንጂ፣ እነዚህ ሰዎች እንዲያው አልመጡም» ብሎ ደንገጠ። ወዲያውም «እናቴ ደህና አይደለችምን? » ብሎ ቢጠይቃቸው «በብርቱ ስለታመመች ምንም ደህነት የላምት ስለዚህ የልጄን ዓይን ሳላይ እንዳልሞት በነፍሴ ድረስ ብላችሁ ንገሩት ብላ ልካናለች» አሉት። ስብስቴም እንደ ቆመ ጥቂት አለቃቅሶ «ከጌታዬ ልሰናበትና ባንድነት እንወጣለን» አላቸው።

ነገር ግን በጌአው ቤት ስለ ጐሹ መገደል ትልቅ ዓለምና ደስታ ሆኖ ይዘፈን ይጨበጨብ ነበርና «አሁን በዚህ ዓለም ደስታ መካከል ማን ያሰናብትሃል? ይልቅስ እናትህን ዓይነህ ለማየት ጓጉታ ሳትደስላት ብትሞት ፀፀቱ አይወጣልህምና በቶሎ እንሂድ «ብለው ቢመክሩት» ይሁን ብሎ ጌታውን ሳይሰናበት ከመላክተኞቹ ጋራ ወደ አገሩ ለመሄድ ተነሣ።

መዘምርም ስብስቴን ይዞ ለማሠር ያሰበው በግብር ላይ ነበርና መኳንንቱ ሁሉ ለግብር ሲገቡ ስብስቴን ሳያየው በመቅረቱ አጋፋሪውን ጠርቶ «ስብስቴ ወዴት ሄደ? » ቢለው «ከገባን ጀምሮ በዚህ አላየሁትም የሄደበትንም አላወቅሁም» ብሎ ስለ መለሰ «በአደባባይ ሁሉ በቤቱም አስፈልገህ ጥራው! » አለው። አጋፋሪውም አስፈልጎ ባጣው ጊዜ ለመዘምር የተናገረና በያገሩ በር ሁሉ ጠብቁ አታሳልፉ ተብሎ ታዘዘ። ነገር ግን እግዚአብሔር ያዳነውን ሰው ሊያጠፋው አይችልምና የሄደበት መንገድ ስላልታወቀ ሳይገኝ ቀረ።

ስብስቴም ወደ ሀገሩ በደረሰ ጊዜ እናቱን ሳትታመም በደህና ቢያገኛት እጅግ ደስ አለው። በዚያም ወራት የጥሙጋ ጋላ /ኦሮሞ/ በወጋውማ እየወጣ ያብቹ ጋላ /ኦሮሞ/ በሰፌድ ሜዳ እየወረደ ያስቸግር ነበርና ስብስቴ የቆላውንም የደጋውንም ጋላ /ኦሮሞ/

እየወጋ ያጠፋው ጀመር። ከብቱንና ገንዘቡንም እየዘረፈ ሴቱንና ሕፃናቱን እየማረከ በብዙ ወሰደበት።

ለጊዜው በነጋሢ አልጋ የተቀመጠው ወንድሙ ዳኛ ነበርና የዳኛ ባለሟሎች ተሰብስበው «ስብስቴ እንደ ወርካ ሥር የተሰደደ በኋላ ሁላችንንም ፈነቃቅሎ ዋና ሆኖ ይቀራልና አሁን ብናስብበት ይሻላል። ስለዚህ ግዳዩን ቅቤው ይበቃሃልና የተማረከውን ከብትና ገንዘብ ወደኛ አግባ በለን እንላከበት» ብለው መከሩና ቢልኩበት «የፈሩት ይደርሳል! የጠሉት ይወርሳል» የሚባለው ተረት በእኔ ሊደርስ ነው ቀድሞም አገሬን ትቼ ወደ መርሐቤቴ መውረዴ እንደዚሁ ከወንድሞቼ ጋራ እንዳልጋደል ብዬ ነበር አሁን ግን ተከብሬ በደህና ከምኖርበት አገር እናትህ ታማላችና በነፍሷ ድረስ ብላችሁ አታላችሁኝ ካመጣችሁኝ በኋላ ያሰባችሁትን አድርጉ እንጂ ከጋላ /ከኦሮሞ/ ጋር የተሟሟትሁበትንና የማረክሁትን ከብት ወደ እናንተ አላገባም ብሎ» ላከባቸው።

አሳባቸውም እንዳልተፈጸመላቸው ባዩ ጊዜ ከጌታቸው ከዳኛ ጋር ተሰልፈው መጥተው ጦርነት ቢገጥሙት ሁሉንም ድል አደረጋቸው። የደውጋውም ጋላ /ኦሮሞ/ ሁሉ ይህን ወሬ በሰማ ጊዜ እየሸሸ በየበረሃው ገባ።

ከዚህም በኋላ አቤቶ ስብስቴ «አባቴ አንድ ማሳ መሬት እንኳ ሳይሰጡኝ ጦሩንና ብር ካራውን በኑዛዜ መስጠቱ አገር አቅንተህ ግዛ፣ አንተን አለቃ አድርጌሃለሁ ማለቱ አይደለም? » ብሎ አሰበና «ለአባቴ ለነጋሢ ውሎ አድርጌ አስለቅሳለሁና ዘመድ ወዳጁ የሆንሽ ሾላ ሜዳ ድረስ በዚህ ቀን እንድትመጣልኝ» እያለ በየሀገሩ ላከ።

ከዶባ ባላባት ወገት የሆነች ሚስት አግብቶ አብዬን ወልዶ ነበርና ድቦች መጡ። ልጁ አብዬም የማማን ልጅ ታጉንሥጢያን አግብቶ ነበርና አፍሮ አይገባ መጣ። የነጋሢ እናት ወይዘሮ ሰንበልት የአራድማው የደጃዝማች ፋሪስ ልጅ ነበረችና መላ አራድማ መጣ። ነጋሢም የአንጋቻ ነውና መላ የላሎ ምድር ሰው መጣ። የይፋት ወላስማ መሐመድም መጥቶ ነበርና ይህ ሁሉ ሰው ተሰብስቦ ውሎ ተደርጎ ስለ ነጋሢ ተለቀሰ።

አቤቶ ስብስቴም ለውሎው የተሰበሰብው ሰው ሳይበተን ከወላስማ መሐምድ ጋር ተማክሮ ከዚህ ቅጥሎ ያለውን አዋጅ አስነገረ።

«የመንዝ ሰው ተከተለኝ! ስሜም መርድ አዝማች ነውና ከእንግዲህ ወዲህ መርድ አዝማች ያላልኸኝ ብርቱ ቅጣት ትቀጣለህ! » አለው። የከረዩንም ጋላ /ኦሮሞ/ ከይፋት አስወጣው። ከተማውንም በዶቃቂት አደረገ ፡

ይህም ሁሉ ከሆነ በኋላ የቆላው ባላባት የመዘምር መኳንንቶች ወደ ጌታቸው ገብተው አቤቶ ስብስቴ የሠራውን ሥራና የኃይሉንም ብርታት በነጋሢም አልጋ

መቀመጡን ቢነግሩት «ስብስቴን ሳይለማ በደለማ አሥርን እናስቀምጠው ብላችሁ አይሆንም ብላችሁ ከእጄ አመለጠ። ከእንግዲህስ ወዲህ እንኳንስ ለደጋው አገር ይቅርና ለእኛው ለቆላውም አገር ሳያስፈራ አይቀርም። ይህም ሁሉ የሆነው በእናንተው ፍርሃትና ስንፍና ስለሆነ ሁለተኛ የስብስቴ ነገር አታንሱብኝ» አላቸው።

በዚያም ዘመን ለስብስቴ እንደዚህ ተብሎ ተገጠመለት ይባላል።

የነጋሢ ልጅ አልተስማሙም ከቶ።
አባታቸው ቢሞት ሰባት ልጆች ትቶ።
አንዱ አንዱ ጠላው ሁከት አስነስቶ።
ስብቴም ለቀቀ ሄደ ካገር ወጥቶ።
ከወንድሞቹ ጋር መጋደልን ጠልቶ።
ወደ ቆላው ወርዶ አደረ ለጌታው።
ጌታውም ወደደው ሰጠው ከበሬታ።
አደን ሂዶ ጌታው ሥራዊት ሲፈታ።
ባንድ ውርወራ አስቀረው ጐሹን በቱማታ።
የጐሽ ሰበንር /ጨጓራ/ በላ ቀኝ እጁም በረታ።
ለጌታው አንድ ሰው ትንቢት ቢነግረው።
በወደደው ፋንታ ፈጽሞ ጠላው።
ሊያስረውም ፈልገ ደግሞም ሊገድለው።
ጋላ /ኦሮሞ/ አስቸግሯቸው እጅግ ተጨንቀው።
ዘመዶቹ ላኩ ምክንያት አድርገው።
እናትህ ታመዋል ድረስ ና ብለው።
የቅንነት አምላክ ከሞት አዳነው።
ሊታሠር ተመክሮ ሲሉ ነገ ሠልስት።
እናትህ ታመዋል ብለው ነገሩት።

ደንግጦ ተነሣ በዚህ ምክንያት።

ፈጥኖ አገሩን ሄደ ሳይሰናበት።

ቢፈልግወ ቢያጣው ልኮ ወደ ቤት።

ያ ቆለኛ ጌታው ሆነበት ፀፀት።

እያለ ተከዘ ምነው በሞትኩት።

ምነው በደለማ በፊት በያዝሁት።

አመለጠኝ ብሎ ነደደ እንደ እሳት።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያስቀረ መስሎት።

አምላክ የፈቀደው ያሰበው ከጥንት።

ምን ቢሆን አይቀርም በሌላ ብልሃት፡

በከንቱ ነው እንጂ እንዲያው መታከት።

በትእዛዝ አይሆንም አልጋና መንግሥት።

ከላይ ካልፈቀደ አምላክ ፀባዖት።

ነጋሢም አዘዘ አልጋውን ለአካዋ።

ዝናም አልዘንብ አለ በግዛቱ ሸዋ።

አማልክ ባይፈቅድለት ሰው ሁሉ ጠላዋ።

ዳኛም ግንባር አጣ አላገኘም ግርማ።

በስብስቴ ጉልበት አልጋውን ተቀማ።

ስብስቴ ተመርጦ አምላክ ፈቅዶለት።

ለልጅ ልጁ ሆነ የሸዋ መንግሥት።

ከዚህም በኋላ ስብስቴ ቀረጥ አምባን ትቶ ዓይኔ በሚባል አገር ከተማ ሠርቶ ስለተቀመጠ አብዬ የሚባለው ልጁ በዶቃቂት ከተማ ለብቻው ተቀመጠ። ነገር ግን በዶቃቂት ታቦት ለመትከል ቢያስብ ግራኝ መሐመድ የሸዋን ታቦታት ሁሉ እያቃጠለ ስለ ጨረሳቸው ታቦት ለማግኘት ችግር ሆነበት። ስለዚህ ወደ ዓይኔ ሂዶ ያባቱን ታቦት ቅዱስ ሚካኤልን ሰርቆ ተመለሰ። ነገሩንም ያላወቁ ሰዎች ልጅህ ታቦትህን ይዞ ከዳ

ብለው ለስብስቴ ነገሩት። ስብስቴም ሰው ልኮ ምክንያቱን ሳያስጠይቅ በቁታ ተነስቶ ሽል ወንዝ ሠፈረ። አብዬም አባቱ ለጦርነት መምጣቱን በሰማ ጊዜ የቶርነት ለምዱን እንደለበሰ ይላላ ለማየት ወጥቶ ነበርና ስብስቴም ከሠፈሩ ዝቅ ብሎ ይላላ ሲመለከት ልጁ የጦርነት ልብሱን ለብሶ አየውና «እኔ ይህ ልጅ እንደዚህ የሚጨክን አልመሰለኝም ነበር። ለካ ከእኔ ጋራ ጠቡን ቁም ነገር አድርጐ ይዞታልና! » ብሎ በፍጥነት ገስግሶ ወደ አብዬ ቀረበ።

አብዬም ልቡ ለጠብ አላሰበም ነበርና ምንም ሳይንቀሳቀስ ዝም ብሎ ቆሞ ነበር ስብስቴ ግን እጅግ ኃይለኛ ስለ ነበር የአብዬን ለምዱን ጨምዶ ይዞ እየጐተተ ወደ ጉያው አቀረበው።

ይህም ሁሉ ሲሆን የስብስቴ አሽከሮች ምናልባት ልጁን በጡጫና በክርን መትቶ የሚተወው መስሏቸው ዝም ብለው ቆመው ያዩ ነበር። ነገር ግን ከአብዬ አሽከሮች አንዱ «ጌታዬን አባቱ ሲገድለው ዝም ብዬ አያለሁን? » ብሎ እየፎከረ ቀርቦ ስብስቴን ከሹልዳው ላይ ወግቶ ገደለው። አብዬም አሽከሩ አባቱን በመግደሉ እጅግ ስለ ተቆጣ «ቢሆን ትገላልግል ነበር እንጂ ባይሆን እንደ አባቴ አሽከሮች ዝም ብለህ ትቆም ነበር እንጂ ድነ ምን ደፍረህ አባቴን ገደልከው? » ብሎ ወዲያው አስገደለው።

በማናቸውም ቢሆን አብዬ ደግ ሥራ አልሠራም። በፊትም ያለ ፈቃድ ያባቱን ታቦት ወስዶ የቀሰቀሰ እርሱ ነው። በኋላ ደግሞ አሽከሩ በጌታዬ እጅ በልቼ ጠጥቼ ጌታዬ ሲሞት ዝም ብዬ አላይም ብሎ የሚገባውን ሥራ ቢሠራ አሽከሬ ሆነህ ስሞት ዝም ብለህ አታይም ነበር ወይ? ለምን ረዳኸኝ? ብሎ በማይገባ ፍርድ ንጹሑን ደም አፈሰሰ።

ስብስቴም ሸዋን ፲፫ ዓመት ከገዛ በኋላ በየካቲ፳፪ በ፲፪፻፲፱ ዓ.ም አረፈ።

# ምዕራፍ ፰

## ስለ መርድ አዝማች አብዬ

## የክርስትና ስሙ ቀዳሜ - ቃል

አብዬ ምንም እርሱ ራሱ ባይገድለውም አባቱ ስብስቴ የሞተው በእርሱ ምክንያት ስለሆነ በአባቱ ለመቀመጥ ትልቅ ሥጋትና ፍርሃት ሆኖበት ነበር። ነገር ግን በቶሎ ከይፋት ወላስማ መሐመድ ጋር ቃል ኪዳን ስለገባና መሃላውን ስለ አጠነከረ ባንድ ወገንም ሚስቱ ታትንስጥያ የማማ የሩፋኤል ልጅ ስለሆነች አፍሮ አይገባ የሚባለው

ጨዋና የእናቱ ዘመዶች ዶቦች ስለረዱት ሥጋቱና ፍርሃቱ ጠፋለትና በአባቱ አልጋ ተቀመጠ።

ለጊዜው በአባቱ ከተማ በዶቃቂት ቆይቶ በኋላ ሐር - አምባን ቆረቆረና ቅዱስ ሚካኤልንም ቤተ ክርስቲያን ሠራ።

ስብስቴ እስከ አዋሽ ወንዝ መሬቱን አልምቶት ነበር። አብዬ ግን እስከ አይራራ ወንዝ እያሳረሰ አለማው። በመሐመድ ግራኝ ምክንያት የጠፋው መሬት እየለማ በመሔዱ ክርስቲያኑ ሁሉ ደስ አለው።

መርድ አዝማች አብዬም በዘመኑ ለነበረው ለጐንደሩ ንጉሥ አገልድም ለተባለው ለዳግማዊ ኢያሱ ግብር ከልክሎ ነበርና ራስ ወልደ ልዑልና ራስ ወዳጆ አየሊ ወሰኑ የሚባሉ አብዬን ለመውጋት ታዘው ወደ ሸዋ መጡ።

ከነርሱ ጋር በአብዬ የተመቀኙ የግሼና የአንጾኪያ የኤፍራታና የግድም ከመንዝም አንዳንድ ሰዎች ተጨምረው በሚያስፈራ ግርማ መጡበት። አብዬም ከይፋት ወላስማ ከመሐመድ ጋራ ሆኖ በአቤቶ ነጋሴ ከተማ በዓይኔ ተሰልፎ ቆይቶ ነበርና ጦርነቱ በተጀመረ ጊዜ ባንዳፍታ ድል አደረጋቸው። ራስ ወዳጆ ብቻ በጭንቅ ሲያመልጥ ራስ ወልደ ልዑልና አየሊ ወሰኑ ከ፯፻ ባለመጣቀሻ ነፍጥ ጋራ ከነሠራዊታቸው ተማረኩ። ነጋሪት መቾው፣ መለከተኛው እምቢልተኛው፣ ሥራ ቤቱ ድንኳን ይህን የመሰለ የዘመቻ ዕቃ ሁሉ ተማረከ።

መርድ አዝማች አብዬም ከነዚህ ከተማረኩት መኳንንቶች የጐንደርን ሥርዓት መንግሥት እየተማረ የንጉሥነት ደንብ ሁሉ አወቀ። ራስ ወልደ ልዑልን በዕርቅ ወደ ጐንደር መለሰው፡ ለቀሩት ግን መልከኝነትና የግንደ - በል መሬት እየሰጠ በዚህ በሸዋ በደስታ እንዲኖሩ አደረገ። ለአየሊ ወሰኑም የካራ መገንን አበጋዝነት ሰጠው። በነዚህም በአማሮቹ ምርኮኞች ኃይል መንዞችን እያስፈራራ ዝም አሰኛቸው።

በጐንደርና በአማራውም አገር ከሚኖሩት ሰዎች ይበልጥ እነዚህ በሸዋ የቀሩት ምርኮኞች ትልቅ ክብር ማግኘታቸውን በሰሙ ጊዜ ብዙዎቹ ስለ መጡ በደስታ እየተቀበለ ሪም እየሰጠ አኖራቸው።

ደግሞ የእጅ ሥራ ከሚያውቁ ከፈሳሾች /ጠቢባን/ ወገን ብዙ ሰዎች መጥተው ነበርና ማረሻ ወገል ማጭድ ምሳር መጥረቢያ ስለ ሠሩለት የእርሻ ሥራው እየለማለት ሔደ።

ከዚህም በኋላ ወደ አንኮበር ወጥቶ ከተማ በቆረቆረ ጊዜ ብዚያ ትኖር የነበረችው አንኮ ላሞቿን ነድታ አገር ጥላ ወደ ከረዩ ገባች። እንደዚህም ታፍሮና ተፈርቶ ሸዋን ፳፫

ዓመት ከገዛ በኋላ በየካቲት ፲፪ ቀን ፲፯፻፴፯ ዓ.ም አረፈና እርሱ በሠራው በሐር - አምባ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ።

# ምዕራፍ ፱

## ስለ መርድ አዝማች አምኃ ኢየሱስ።

አብዬ ካረፉ በኋላ ልጁ አምኃ ኢየሱስ በአባቱ አልጋ ተቀመጠ። ወዲያውም ሐር - አምባን ትቶ አባቱ የቆረቆረውን የአንኮበር ከተማ በሦስት እርከን ከፍሎ ማለፊያ ከተማ አደረገው።

በዚያ ወራት ከዱይ ወረዳ የውልዬና አብርዬ የሚባሉ የጠራ ሰዎች ለአምኃ ኢየሱስ አንገዛም በማለት አይራራ ወንዝ ድረስ እየመጡ ካራ መገን ላይ ከአየሊ ወሰኑ ጋራ ይዋጉ ነበርና እነርሱን ባላገር ይዞ ለአምኃ ኢየሱስ ከሰጠ በኋላ ጠራና ቡልጋ ለአምኃ ኢየሱስ ተገዛ። ምንጃርም መታረስ የጀመረው ያን ጊዜ ነው።

አምኃ ኢየሱስ በደግነቱ አገሩ እየሰፋለት ስለ ሄደ ከቀወት እስከ ምንጃር የቸር አምኃ ኢየሱስ አገር ይባል ነበር።

የአብቹንም ጋላ /ኦሮሞ/ እስከ በሬሳ ያለውን ሰለ አስገበረው የተጉለትና የወግዳ ሰው መገናኛ ጀመረ። በሆንም አንዳንድ ጊዜ የሴራው ጋላ /ኦሮሞ/ እየከዳ ሰው መግደሉ አልቀረም ነበርና እርሱ በአንኮበር ሆኖ ጦሩን ሁሉ በአበጋዝ አድርጐ ወደ ጋላ /ኦሮሞ/ አዝምቶት ሳለ፣ ጦሩ በሬሳ ሲደርስ እንደ ልማዱ በጣኡት ተሰልፎ ቆመ። የጦር አበጋዞቹም ለየብቻቸው ሆነው ከየጋላው /ከየኦሮሞው/ ጐሣ እየከዳ የመጣለትን በቆይታ ይዘው በየት ክፍል ወሪሳ እንምታ? የማናቸውን በረት ላም እንማርክ? እያሉ ሲጠያይቁ የጐሜ ጐሹ የሚባል ወታደር ወታደር ወንድሙን የሴራው ጋላ /ኦሮሞ/ ከድቶ ስለ ገደለበት እየተናደደ ይኖር ነበርና ከሠራዊቱ መካከል የተጠራ መስሎ እየሮጠ ወደ አበጋዞቹ ቀረበና ትእዛዝ እንደሚሰማ ሰው አጐነበሰ። በመጨረሻም ትእዛዙን የተቀበለ መስሎ እጅ ነሣና ተመለሰ።

ሠራዊቱም አስቀድሞ እንደ ተጠራ ሰው አቤት! እያለ ወደ ቆይታው መሄዱን በኋላም አጐንብሶ ስመቶ እንደ ታዘዘ ሰው እጅ መንሳቱን ይያ ነበርና ጐሜ ጐሹ እየሮጠ ተመልሶ «የሴራው ጋላ /ኦሮሞ/ ከበሬሳ እስከ ዳሳ እረደው ብለውሃል! » ብሎ እየጮኸ ተናገረና ወዲያው በፈረስ ሆኖ ጋለበ።

ሠራዊቱም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ በእርግጥ ከአበጋዞች የመጣ ትእዛዝ መስሎት ፈረሰኛው በፈረስ እግረኛው በእግር ተከታትሎ ከበሬሳ እስከ ጠራ ደጋ እስከ ቁንዲ እክሰ ጣርማ በር ያለውን ጋላ /ኦሮሞ/ ባንድ ቀን አረደው።

ጐሜ ጐሹም የወንድሙን ገዳዮች በማጥፋቱ ደስ ብሎት ነበርና «ወይ ጐሜ ጐሹ! ወይም ጐሜ ጐሹ! በድፍን ይፋት ዕዳ ነስናሹ! » እያለና እየሸለለ ፎከረ ይባላል። ነገር ግን በዚህ ነገር አምኃ - ኢየሱስ ስለፈራ ወደ ጥሙጋ ገብቶ ሳይመልስስ በዚያው ሞቶ ቀረ።

መርድ አዝማች አምኃ ኢየሱስ ብዙ ልጆች ነበሩት። ነገር ግን አልጋዬን ይወርሳል ብሎ ተስፋ ያደረገው አስፋ ወሰንን ነበር።

በአምኃ ኢየሱስ ዘመን ቢዛነ ወልድ የተባለ ሊቅ ከጐንደር አዘዞ መጥቶ በመንዝ አውራጃ ኩራኩሬ በሚባል አገር ተቀምጦ ቅኔና የመጻሕፍትን ትርጓሜ ያስተምር ነበርና አምኃ ኢየሱስ የእርሱን ዝና ስለ ሰማ ልጁን አስፋ ወሰንን ቅኔ ተማር ብሎ ወደ ቢዛነ ወልድ ሰደደው። አስፋ ወሰንም ከአራት አሽከሮቹ ጋር ሄዶ በትጋት እየተማረ ቅኔ አዋቂ ሆነ። ትምህርቱንም ከጨረሰ በኋላ አባቴ ናፈቁኝ ብሎ አራቱን አሽከሮቹን አስከትሎ ወደ አንኮበር ሲመለስ ወደራ ላይ ጊዜ ስለመሸበት አሳድሩኝ ለማለት ወደ ወይዘሮ አትሞችሆኖ ቤት ሄደ።

ወይዘሮ አትሞችሆኖ የወይዘሮ ትሁን ልጅ ናቸው። ወይዘሮ ትሁንም ከዋያት በመለስ እስከ ተከዜ የሚወልዱ የብዙ ባላባቶች ልጅ ነበሩ። አምኃ ኢየሱስም ይወይዘሮ አትሞችሆኖን ማማርና ባላባትነት በሰማ ጊዜ ትወልድልኛለች ብሎ አምስጥቶ ወደራ ላይ አቀምጧቸው ነበር።

አስፋ ወሰንም በወይዘሮ አትሞችሆኖ በር ቆሞ አሳድሩኝ ብሎ በጠየቀ ጊዜ ገረድቲቱ ብቅ ብላ አይታ «እመቤት ሆይ! አምስት ተማሪዎች በደጅ ቆመው አሳድሩኝ ይላሉ። ከመካከላቸው አንደኛው የአጥቢያ ኮከብ ይመስላል። ከቶ ከተውለድሁ እንደዚህ የመሰለ መልከ መልካም አላየሁም» ብላ ተናገረች።

ወይዘሮ አትሞችሆኖም የአሰፋ ወሰንን መልከ መልካምነት ከገረዲቱ አፍ በሰሙ ጊዜ አራቱን ተማሪዎች የአስፋ ወሰንን ማደሪያ ቤት አስገቧቸውና እራት አብሏቸው። አምስተኛውን ግን ወደዚህ አምጪው አሏትና ይዛው ገባች። ባዩትም ጊዜ በመልኩ ማማር የተነሳ ደስ አላቸውና በፍጥነት አገር ወዴት ነው? አባትህስ ማነው? » ብለው ጠየቁት እርሱም የንጉሥ ልጅ መሆኑ እንዳይታወቅበት ስለ ፈራ «የአንድ ባላገር ልጅ ነኝ

ከባልንጀሮቼ ጋር ወደ ትምህርት ቤት ሄጄ ስኖር አሁን ትምህርቴን ጨርሼ ወደ ሀገሬ መመለሴ? ነው አላቸው።

«አባትህና እናትህ አንተን የመሰለ ልጅ አምነው ወደ ሰው አገር መስደዳቸው ምን ይጠኑ? አሁን ለባልንጀሮችህ እራታቸውን አዝጌላችዋለሁና አንተ እዚህ እደር» አሉት። ከዚህ በኋላ እንኳን የሴት አሳብ ተጨምሮበትና ባይጨመርበትም የጐልማሳ ሰውነት ትኩስ ስለሆነ ለመታገስ አይችልምና ተገናኝተው አደሩ። ይህም ሁሉ ሲሆን አስፋ ወሰን የአምኃ ኢየሱስ ልጅ መሆኑ፣ ወይዘሮ አትሞችሆኖ የአምኃ ኢየሱስ ቁባት መሆናቸውን አልተዋወቁም ነበር።

ወደ አንኮበር በደረሰ ጊዜ መርድ አዝማች አምኃ ኢየሱስ እጅግ ደስ አለው። ወደ ቤትም ሲገባ አንገቱን ይዞ ፊቱን ሁሉ ዓይኑን ሳይቀር እያገላበጠ ይስመው ጀመር።

ወዲያውም «ልጄ ሆይ ዘንድሮ እሞታለሁ ብዬ ሆዴ ስለ ፈራ ላስጠራህ አስቤ ነበር። አሁንም እንኳን መጣህልኝ ከእንግዲህ ወዲህ ከአንኮበር ወጥተህ አትሂድ። ምናልባት ወጥተህ የሄድህ እንደ ሆነ ወንድሞችህ ብዙ ናቸውና በአልጋዬ ላይ በምትቀመትበት ጊዜ ያውኩሃል አለው።» አስፋ ወሰንም ከአባቱ ቃል ይህን በሰማ ጊዜ እጅ እንስቶና ጉልበቱን ስሞ ተቀመጠ።

ነገር ግን መቼም ቢሆን በዚህ ዓለም የተሠራ ሥራ ሳይገለጥና ስያሰማ የሚቀር የለምና አስፋ ወሰን ከትምህርት ቤቱ ሲመለስ አትሞችሆኖ ቤት ማደሩ ምንም እንኳ ቢወራና ቢሰማ አባቱ መርድ አዝማች አምኃ ኢየሱስ ነገሩን እስቲመረምርና እርግጥ መሆኑን እስቲያውቅ ድረስ በልጁ ላይ ክፉ ነገር አልተናገረም ነበር። ነገር ግን ጊዜን ጊዜ ይወልደዋልና እንደ ሚባለው ጊዜው ሲደርስ ወይዘሮ አትሞችሆኖ ከአስፋ ወሰን ወንድ ልጅ መውለዳቸው ተሰማ።

አስፋ ወሰንም የሠራው ሥራ እንደ ተገለበጠ በሰማ ጊዜ አባቱን ስለፈራ ከአንኮበር ወጥቶ ካንዱ ሥፍራ ወደ ሌላ እየተዛወረ ጥቂት ቀን ከቆየ በኋላ ምናልባት በድንገት የተያዝሁ እንደ ሆነ አባቴ ያስገድለኛል በማለት ፈርቶ ዳባ /እጥፍ/ ለብሶ መነኩሴ መስሎ በፍርኩታ ገዳም ፫ ዓመት ሙሉ ተቀመጠ።

አምኃ ኢየሱስም በልጁ መታጣት እጅግ ስለ አዘነ «አትርሱኝ! እዘኑልኝ! » እያለ በየአድባራቱና በየገዳማቱ የምጽዋት ገንዘብ ይክል ነበርና አስፋ ወሰን በፍርኩታ ገዳም ሳለ አባቱ ስለ እርሱ መጨነቁን ቢሰማ «አባቴ ሊታረቀኝ አስበው ይሆናል» ብሎ ወደ ገዳሙ መምሕር ገብቶ «የአምኃ ኢየሱስ ልጅ አስፋ ወሰን ማለት እኔ ነኝ ወደዚህም የመጣሁበት ምክንያት እንደዚህ ነው» እያለ ነገሩን ከሥር እስከ ጫፉ ገልጦ ነገራቸው።

ከዚህም በኋላ የፍርኩታ መምሕር ወደ አምኃ ኢየሱስ መላክተኛ ልከው ልጅህ ከእኔ ዘንድ አለ ብለው፣ ባስታወቁት ጊዜ «ልጄ በፍርኩታ ገዳም መግባቱ በሠራው ሥራ ንስሐ ለመግባት ይሆናልና በቶሎ ይምጣልኝ እታረቀዋለሁ! » ብሎ ምላሹን ላከባቸው።

መምሕሩም ወደ አንኮበር ወስደው ከአባቱ ጋር በቆይታ አገናኝተው ሲያነጋግሩት «ጥንቱንም እኔ ወይዘሮ አትሞችሆኖን ቁባት አድርጌ ማቀመጤ የብዙ ባላባቶች ልጅ መሆኗን ስላወቅሁ ዘር ለማትረፍ ብዬ ነበር። አሁን ግን እኔ ባሰብሁት መንገድ ቀርቶ በሌላ መንገድ ዘር አትርፋልኛለችና ምንም የማዝንበትና የምቀየምበት ነእር የለም» ብሎ ታረቀው።

ከዚህም በኋላ ለመኳንንቱና ለባለሟሎች ግብር አድርገው ሲያበላ አስፋ ወሰን ዳባውን እንደ ለበሰ ቆቡን እንዳደረገ ከፍርኩታው መምሕር ጋር ባንድነት ተቀምቶ ይበላ ነበር መርድ አዝማች አምኃ ኢየሱስ ሰው የሚለውን ለመስማት ፊቱን ወደ መኳንንቱና ወደ ባለሟሎቹ አዙሮ የሚያፈላልገኝ አጥቼ እንደ ጠፋ ሊቀር ነውን? » እያለ ሲናገር ከመኳንንቱ አንዱ ተነስቶ «አኔ አሸክርዎ አይገቡ ገብቼ ልጅዎን አመጣልዎታለሁ! » ባለው ጊዜ «ተው! እንደዚህ አድርገህ አትናገር! እነ አባ ይታዘቡሃል! » አለው ይባላል።

በሦስተኛው ቀን ዳባውን /አጥፉን/ አስወልቆ ያማረ ልብሱን አልብሶ ባጠገቡ አስቀምጦ መኳንንቱና ባለሟሎቹን ወታደሮቹን ወታደሩንም ሁሉ አስጠርቶ ልጁን አስፋ ወሰንና ስለ አሳያቸው ታላቅ ደስታ ተደረገ።

አምኃ ኢየሱስም ከወይዘሮ አትሞችሆኖ የተወለውን የአስፋ ወሰንን ልጅ አስመጥቶ አይቶ ስሙን ወሰን ሰገድ ብሎ አወጣለት።

አምኃ ኢየሱስም በዘመኑ ተድላና ደስታ ስለ በዛ ሐር - አምባን እንደ እልፍኝ አንኮበርን እንደ አዳራሽ አድርጐ ፴ ዓመት ከገዛ በኋላ በጥር ፳፱ ቀን ፲፯፻፺፯ ዓ.ም አረፈና በአንኮበር በሠራው በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ።

# ምዕራፍ ፲

## ስለ መርድ አዝማች አስፋ ወሰን

## የክርስትና ስሙ ቴዎድሮስ

መርድ አዝማች አስፋ ወሰን በአባቱ በአምኃ ኢየሱስ አልጋ ከተቀመጠ በኋላ የአንኮበር ከተማ እያስፋፋ እያጠነከረ ይሄድ ጀመር።

በሀገራችን በኢትዮጵያ ብዙ ሰዎችን ከጥፋት የሚያደርስና መንግሥትን የሚጐዳ የሐሰተኞች መነኮሳት ነገር ነው። ይህንንም የሚያስረዳ ነገር አንድ መነኩሴ ወደ መርድ አዝማች አስፋ ወሰን ገብቶ ዕድሜህ አጭር ነው ብሎ ቢነግረው እውነት መስሎት ረጅም ዕድሜ ለማግኘት ሲል የቤተ መንግሥቱን ገንዘብ ለየገዳማቱና ለየአድባራቱ ካህናት በመስጠት ጨርሶ ግምጃ ቤቱ ባዶ ሆኖ ቀረ። ላገሩና ለጌታው አሳቢ የሆነ አንድ ባለ ሟል ሰው ግምጃ ቤቱ ባዶ መሆኑን ዓይቶ «ለምን እንደዚህ ታደርጋለህ? » ብሎ ቢመክረው «በአልጋው ከቆየሁ እንደ ገና እሞላዋለሁ። ባልጋው ካልቆየሁ ባልጋው የሚቀመጠው ያስበበት እንጂ፣ እኔ ምን ቸገረኝ» ብሎ የማይገባ ምላሽ መለሰለት።

በዓለም ላይ ለጊዜው እኔን ደስ ይበለኝ ብሎ ለራሱ ብቻ የሚያስብ ንጉሥ ሲረገም ይኖራል እንጂ፣ እውነተኛ የሕዝብ ንጉሥ ነው ለመባል አይገባውም። ስለዚህ ከሞተ በኋላ ስሙ የሚጠራበትን መንግሥቱ የሚጸናበትን ሥራ እየሠራ የሚኖር ንጉሥ ብቻ በሕዝቡ ዘንድ የተወደደ ሆኖ ሲመሰገን ይኖራል። ዘሩም የተባረከ ይሆናል።

መርድ አዝማች አስፋ ወሰንም በሥራው ሁሉ ብርቱ ስለ ነበረ ግዛቱን ሸዋን እያሰፋ ይሔድ ጀመር።

ደግሞ ልጁ ወሰን ሰገድ ዐርበኛ መሆኑን ያውቅ ነበርና የጦር አበጋዝ አደረገው። በልጁም ጉልበት ግድምንና ኤፍራታን አንጦኪያንና ግሼን ደግሞ ከጣርማ በርና ከቁንዲ ጀምሮ እስከ ጫጫ አንድ አድርጐ ይገዛ ጀመር።

ወሰን ሰገድም ለጊዜው አባቱን ደስ ለማሰኘት ለኋላውም ግዛቱን ለማስፋት ስለ አሰበ በሰላሌ በኩል እስከ ዓባይ አፋፍ በወዲኢህም እስከ ጨቦና እስከ ጉራጌም አገር ይዘምት ነበር።

ደግሞ ሸዋን መሐመድ ግራኝ ካጠፋው ወዲህ አገር ተከፋፍሎ በየባላባቶች ይገዛ ነበርና አስፋ ወሰን እነዚህን የተከፋፈሉትን አገሮች አንድ አድርጐ ጠቅልሎ ለመግዛት ስለ አሰበ ወደ ቆላ አገር ይዘምት ነበርና ስለዚህ የሞረት ጥዱ ለመርድ አዝማች አስፋ ወሰን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ግጥም ልኮበት ነበር።

አስፋ ወሰን ይፋት ጠንክረው ይረሱ።

ሞረት ጥዱል /ጥዱ አለ/ ብለው ከመመላለሱ።

አስፋ ወሰንም ሲመልስ፡-

«ለሞፈር ለቀንበር ለመቃን ለጉበን የሚሆነኝን

ሳልቆርጠው አልቀርም ዘንድሮ ጥዱን።»

ጥዱም ሲኢመልስ።

«ያባቴ አገር ሞረት ሴቱን ያሳምራል፣

ወንዱን ያደረጃል፣

ምንጩን የመነጫል.

ጠበሉን ያፈልቃል፣

ቢለመልም እንጂ ጥዱ መች ይደርቃል? » አለ።

በኋላ ግን በቆላው አገር የሚኖሩ ባላባቶች ኃይላቸው እየደከመ በሞትም እያነሱ ስለ ሔዱ አስፋ ወሰን ወደ ቆላ ወርዶ ድል አድርጐ አምባውንም ሰብሮ የታሠሩትንም ፈትቶ አገሩን እጅ አደረገው።

ልጁ ወሰን ሰገድም ለአባቱ የጦር አበጋዝ ሆኖ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ወደ ላይም ወደ ታችም እየተዘዋወረ እየተዋጋ አገሩን አሰፋለት። ነገር ግን አስፋ ወሰን ከመንዝ ባላባት ልጅ ኢዮአስን ወልዶ ነበርና ኢዮአስ የእናቱ ወንድሞች በጋብቻም በዝምድናም ቁጥራቸው ፲ መኳንንቶች ስለ ሆኑ ክፉ ሰዎች ወደ ወሰን ሰገድ ገብተው ባለ ብዙ ወገን ኢዮአስ ሳለ አንተን ማን ያነግሥሃል? » ብለው ቢነግሩት ከአባቴ ከድቶ ሲሂድ አባቱ ሰምቶ በግሥጋሴ አጥንት መስበሪያ ላይ ደረሰበት። ውዲያውም ጦርነት ገጥመው ሲዋጉ አሽከሮቹ ትተውት ስለ ተበተኑ ወሰን ሰገድ ተያዘ። ቢሆንም ወሰን ሰገድ በብረት ይሞታል የሚባል ንግር ነበርና በሠንሰለት እንዳያስረው ይሞትብኛል ብሎ ፈራ። እንዳይለቀውም የመንግሥት ነገር ሆነበት። ስለዚህ በሻሽ አስሮ ሶስት ቀን ካሳደረው በኋላ የከዳበትን ምክንያት ቢጠይቀው «የነጃልዬ ወገን ኢዮአስ ሳለ አንተን ማን ያነግሥሃል? » እያሉ ቢነግሩኝ እንደዚህ ከሆነ አንተ አባቴ ከሞትክ በኋላ በጉልበቴም ቢሆን አልጋውን ለማግኘት እሞክረዋለሁ ብዬ ነው የከዳሁት» ብሎ መለሰ።

አስፋወሰንም ይህን በሰማ ጊዜ እኔ ለሞቴ የቸኰልህ መስሎኝ ነበር እንጂ፣ ለዚህማ ከአትሞችሆኖ የወለድሁህ አንተ ሳለህ ማንን አነግሣለሁ ብሎ ወሰን ሰገድ አልጋውን ለሌላ ልጅ እንዳያወርስ ቃል ኪዳን ገባለት። እርሱም ለአባቱ ዕድሜ ከመለመን በቀር አባቱ እስካለ ድረስ መንግሥት እንዳያምረው ማለና ታረቁ።

ከዚህም በኋላ የግድምና የቀወትን አበጋዝነት ስለ ተሾመ ዋና ከተማውን በቀወት አውራጃ ጌስ ላይ አደረገ።

ከቀወትም ወደ እርቄ ዘምቶ ነበርና ጐንጂ የሚባል እስላም ስለ ማረኩ በኋላ ሊቀ ካህናት የሆነው አለቃ ወልደ ኪሮስ የእስላም ሼህ መስሎ መሐመድ ኪሮስ እየተባለ ሄዶ ብዙ ገንዘብ ሰጥቶ ወደ ቀወት መልሶ አመጣው።

መርድ አዝማች አስፋ ወሰንም ብዙ ምቀኞችና ጠላቶች ነበሩበት ኅዘን ተለይቶት አያውቅም።

ከነዚሁም ከምቀኞቹ ዋነኞች የሻቃ ንግዴና የሻቃ ማርዬ ነበሩ። ማርዬ ኃይለኛና ተኳሽ ነፍጠኛ ነበር። ንግዴ ግን ተንኮለኛ ጨካኝ ነበር እንጂ ኃይለኛ አልነበረም።

ካልጠገቡ አይዘሉ! ካልዘለሉ አይሰበሩ! እንደሚባል ማርዬና ንግዴ እጅግ ስለ ጠገቡ ጌታቸውን አስፋ ወሰንን ከድተው ወደ ጋላ ለመግባት አሰቡ። ማርዬም ኃይለኛነቱን ያውቃልና «ከአስፋ ወሰን ብንከዳ ምንም የሚቸግረን ነገር የለም። ነገር ግን ነፍኞች አሉትና እነዚያ የመጡብን እንደ ሆነ እንደምን እናደርጋለን? » ብሎ ንግዴን ጠየቀው።

ንግዴ ግን ተንኮለኛ ነበርና «ከድተን ሳንሔድ መጀመሪያ ከነፍጠኞቹ ጋር ብናጣላው ይሻላል» ብሎ ስለ ተናገረ በዚሁ ተስማምተው ወደ አስፋ ወሰን ገቡና ንግዴ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገረ። «እግዚአብሔር እንኳ አዳምን በፊትህ ወዝ ባላ ብሎታል። እነዚህ የርስዎ ነፍጠኞች ግን ምንም ሥራ ሳይሠሩ ተቀምተው እየዋሉ ቀለብና ልብስ አምጡ ይላሉ። ስለዚህ ለፈረሶችዎ እንኳ ቀለብ ቢሆን ወደ ደጋ እየወጡ አስታውን እየመነጠሩ እንዲቆፍሩ ይዘዟቸው» አለው።

አስፋ ወሰንም የንግዴን ተንኮ ሳያውቅ «ደግ ነው! እየወጡ ይቆፍሩ» ብሎ አዘዘ።

ጥቂትም ሰንብተው እንደ ገና ገቡና ማርዬ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገረ። «እነዚህ ነፍጠኞች አስታ መመንጠራቸውና መቆፈራቸው አልቀረም። ነገር ግን ሲቆፍሩ ውለ እየመጡ ባዶ እጃቸውን ከመመለስ የመነጠሩትን አስታ እየተሸከሙ እያመጡ ለአዛዡ ቢያስረክቡና ለእንጀራ መጋገሪያ ለእንኩሮ ማንኮሪያ ቢሆን ይሻላል» ብሎ ተናገረ።

አሁንም የተንኮል ምክር መሆኑን ሳያውቅ ደግ ነው! ይሁን» ብሎ አዘዘ።

ከዚህም በኋላ ነፍጠኞቹ ተሰብስበው ወደ ንግዴ ዘንድ ሄደው «እንደ ቋሚ እኛኝ እንጨት የሚያሸከሙን በጦርነት የማንታኮስ የማንዋጋ ሆነን ነውን? አንተስ በልሟል ሆነህ ይህን ሁሉ በደላችንን እያየህ ዝም ማለትህ ለምን ነው? ደግሞ ተኩሰው አይዋጉልኝም የሚሉ ከሆነ ነፍጣችንን ይቀበሉንና ይህንኑ ቋሚነታችንን ይዘን እንቀመጥ

እንጂ፣ ባንድ ወገን ነፍጠኛነት ደግሞ ባንድ ወገን ቋሚነት አንችልምና አንተ ገብተህ አመልክትልን» አሉት።

ንግዴም ወጥመዱ እንደያዘለት አይቶ «እስካሁንስ ቢሆን በደላችሁን ሳልመለከት ዝም ብዬ ቆየሁ ይመስላችኋል? ነገር ግን መርድ አዝማች አስፋ ወሰን የራሳቸውን እንጂ ሰው የመከራቸውን አይሰሙምና ነፍጠኛ ግምጃ ቤቱንና ጐተራዬን ባዶ ከማድረግ በቀር ምን ያደርግልኛል? እያሉ በቁጣ ቃል ቢናገሩኝ ፈርቼ ዝም አልሁ። የሻቃ ማርዬም በእኛ ቀን ይኸው ናቸው እኮ ብሎ ተናገረ ስለዚህ እሁን ያዘዙዋቸውን ሁሉ እሺ እያላችሁ እየሠራችሁ ከመቆየት በቀር ሌላ የሚሻል ነገር የለም።

«ምናልባት ወደ ፊት እናንተን የሚያስመኛቸው ቀን ይመጣላችሁ ይሆናል» እያለ ለክዳት የሚበረታታ ነገር ይነገራቸው ጀመር።

ንግዴና ማርዬም በዚህ በተንኮል ሥራቸው መርድ አዝማች አስፋ ወሰንን ከነፍጠኛ ጋር ከአጣሉት በኋላ ከድተው ወደ ጋላ /ኦሮሞ/ አገር ገቡ።

አስፋ ወሰንም በዚህ ነገር እጅግ አዝኖ ሳለ አንድ ቀን ለያድባራቱ ካሃንት ግብር በሚያበላበት ጊዜ አንድ ቧልተኛ ቄስ ተነስቶ ሲያሳርግ «ንግዴ ዳር ዳሩን ያነፅንፅ፣ አስፋ ወሰንም ከመንበሩ አይናወፅ፣ አትርሱኝ! እየተባልን እንድንወደድ» ብሎ ተናገረ ይባላል።

ከዚህም በኋላ ንግዴና ማርዬ አስፋ ወሰንን ከነፍጠኛ ጋር ማጣላታቸውን ያውቃሉና ወደ ነፍጠኛው ተላልከው አስፋ ወሰንን ሊወጉ ወደ አንኮበር ወጡ።

«እሳት ቢተኛ ገለባ ሰደድ ጉበኛ» የተባለው ተረት ያን ጊዜ ተፈጸመ። ባንድነትም ሲሄዱ በብዛታቸው እንዳይታወቁ ንግዴ ባንጋቻ ማርዬ በጐረቤላ ሔደው ሙቅ ምድር ተገናኙ።

ለጦርነትም መምጣታቸው በተሰማ ጊዜ የአስፋ ወሰን የግቢ አሽከሮች ወደ ጥግ ወርደው ይከላከሉ ጀመር። ማርዬም እነዚህ የግቢ አሽከሮች በርትተው ሲከላከሉ ባየ ጊዜ «ምነው አንኮበሮች! ለዚህም ደርሳችኋል እንዴ? » ብሎ በኃይል ለመግባት ገና በበቅሎው ላይ ሲቀመጥ ልደቱ የሚባለው ቆለኛ ድንጋይ አንስቶ ቢወረውር ማዬ ጥንቱም አንድ ዓይና ነበርና ደህናንው ዓይኑን አውልቆ ጣለለት። ከበቅሎው ላይ ሲወድቅ ገስግሶ ቀርቦ በሾተል ቆራርጦ ገደለው።

ንግዴ ግን ከነ ልጁ ተማርኮ በወህኒ ቤት ታስሮ ነበርና በዚያው በወህኒ ቤት ግደሏቸው ተብሎ ስለ ታዘዘ ሁለቱንም በጦር በሾተል እየቆራረጡ ገደሏቸው።

«አልጋ ያማረው ድሀ ከነ መደቡ ያጣል»

«ታላቅ ሥስጋ የሚፈልግ ውሻ ከነ ሳምባው ያጣል»

የተባለው ተረት በንግዴ እና በማርዪ ላይ ደረሰባቸው። ይልቁንም «ድሀ ቢያገለግል ለሹመት፤ ቢከዳ ግን ለሞት» የተባለውን ተረት ሳያስቡ መቅረታቸው ያስደንቃል!

መርድ አዝማች አስፋ ወሰንም ዕድሜ አጭር ነው ብሎ ሐሰተኛው መነኩሴ የነገረው ቀረና ሸአና ፴፫ ዓመት ሙሉ ገዝቶ በሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፫፻ ዓመተ ምሕረት አረፈና በአንኮበር እርሱ በሠራው በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ።

በአስፋ ወሰን ዘመን በጐንደር የነገሠው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ተፍጻሜተ መንግሥት ተክለ ጊዮርጊስ ነበር።

# ምዕራፍ ፲፭

## ስለ መርድ አዝማች ወሰን ሰገድ።

## የክርስትና ስሙ ወልደ ጊዮርጊስ

ወሰን ሰገድ ገና አባቱ አስፋ ወሰን እያለ ከተማውን በጌስ አድርጐ ተቀምጦ ነበርና የመንዝ ባላባት ያፍቀራ ጐሴል ልጅ ወይዘሮ ዘነበ ወርቅ ባላቸውን ሰው ገድሎባቸው የኀዘን ልብስ እንደ ለበሱ ለጩኸት መጥተው ነበርና የወሰን ሰገድ አሽከሮች አይተው በግዛትዎ እጅግ የተዋበች ቆንጆ አይተናል ብለው ቢነግሩት አምጡልኝ ብሎ በሩካቤ ሥጋ ስለ ተገናኛቸው ሣህለ ሥላሴ ተፀነሱ ፡

ሣህለ ሥላሴም ሲወልዱ የምሥራች ተብሎ ወደ አባቱ ወደ አስፋ ወሰን ቢላክ ስሙን ምኒልክ እንድትለው የሚል ማልሽ መጣለት። ምክንያቱም በዚያ ዘመን ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ የሚገዛ ምኒልክ የሚባል ንጉሥ ይነግሣል እየተባለ ንግር ነበርና ንግሩ የደረሰ ስለ መሰለው ነበር። ደግሞ ጣይቱ በምትባል ሴት ኢትዮጵያ ትቀናለች እየተባላ ንግር ነበርና ወሰን ሰገድ ጣይቱ የምትባል ሴት ፈልጐ አግብቶ ነበር።

ነገር ግን የምኒልክም የጣይቱም ንግር በ፫ኛው ትውልድ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ተፈጸመ እንጂ፣ ንግሩ አልቀረም።

አባቱ አስፋ ወሰንም ከሞተ በኋላ ወሰን ሰገድ ከጌስ መጥቶ በአባቱ አልጋ ተቀመጠ።

በመጀመሪያም ከአንኮበር ወዲህ ያለውን የሜዳውን ጋላ /ኦሮሞ/ ወግቶ ድል ካደረገ በኋላ ቁንዲ ላይ ከተማ ሠርቶ ተቀመጠ። ቤተ ክርስቲያንም ሠርቶ በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም ሰየመው።

ከጥቂት ውራት በኋላ ወደ ደብረ ብርሃን ወርዶ ያባቱን ያጼ ዘርዐ ያዕቆብን ከተማ አድሶ በዚያውም ቤተ ክርስቲያን ሠርቶ የሥላሴን ታቦት አገባበት። በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ግን የኢየሱስ ታቦት ነበረ።

ወደ ደብረ ሊባኖስም ወርዶ ከእርሱ አስቀድሞ የጋሎች /የኦሮሞዎች/ ኃይል ስለ ተፈራ የደብረ ሊባኖስ መስቀሉና ንዋየ ቅዱሳቱ ሁሉ ታቦቱም ለጋላ /ለኦሮሞ/ ፈረ በማይመች በዜጋመል ቆላ ነበርና መሐመድ ግራኝ ባቃጠለው በቀድሞው ቤተ ክርስቲያን ፍራሽ ላይ መርድ አዝማች ወሰን ሰገድ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ለማሰራት ጀመረ።

በደብረ ሊባኖስም ሆኖ የሸዋ ሰው ሁሉ አማራውም ጋላውም /ኦሮሞውም/ አንጐለላ ድረስ እንዲሰበሰብ አዋጅ አድርጐ ነበርና የተፈራ ስለ መሆኑ ሁሉ ተሰብስበው ቆዩት።

ከደብረ ሊባኖስም ወጥቶ ከመኳንንቱና ከሕዝቡ ጋር ከተገናኘ በኋላ ከእንግዲህ ወዲህ ራስ ወሰን ሰገድ በለኝ እንጂ፣ መርድ አዝማች ያልኸኝ ትቀጣለህ። የሚል አዋጅ አስነገረና ወደ ከተማው ወደ ቁንዲ ወጣ።

ራስም በለኝ ያለበት ምክንያት በዘመኑ የአማራውን አገር ሁሉ የሚገዛው መስፍኑ ራስ ጉግሣ ነበርና ከመርድ አዝማችነት ራስነት የሚልጥ ስለ መሰለው ነው።

ከዚህም በኋላ ጉልበት ስለ ተሰማው ወደ ጐንደር ለመዝመት አሰበና ወደ መስፍኑ ወደ ራስ ጉግሳ «አንተ ቆዱበላ ጋላ /ኦሮሞ/ ባባቶቼ አልጋ ማነው ያስቀመጠህ? አሁንም መምጣቴ ነውና የጠራ ሜዳ ይዘህ እንድትቆየኝ» ብሎ ላከበት። ራስ ጉግሣም ይህ መልዕክት በደረሰበት ጊዜ «ረቢ ቢሰጠው ይስጠው እንጂ እንደዚህ ምን ያኮራዋል አለ? » ይባላል።

ራስ ወሰን ሰገድም የሸዋን ግዛት ካደላደለና ሥርዓተ መንግሥቱን ካደሰ በኋላ ወደ ጐንደር ለመዝመት ቁርጥ አሳብ ስለ አደረገ ስንቅንና መጫኛህን አሰናዳ ብሎ አዋጅ ነግሮ ነበር። ነገር ግን ወደ ጐንደር መዝመትን የማይወዱ ብዙ ጠላቶች ነበሩትና ለዚህ ዓለም የሚባል ባሪያውን በገንዘብ ገዝተው ስለ አሰገደሉት ያሰበው ሳይፈጸምለት ቀረ።

ያሟሟም ነገር ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው። ቀላል በሽታ ታሞ ተኝቶ ነበርና ለዚህ ዓለም የሚባለው ባሪያው ማታ ገብቶ እግሩን ማሻሸት ከጀመረ በኋላ ወዲያው ጩቤውን መዞ ሽንጡን ወጋው።

እርሱም «እኔ አባ ዳማ! ይህ ውላጅ አበላሸኝና! ብሎ ፎክሮ ተነስቶ እየተናነቁ እስከ ደጅ ወጥተው ነበርና በእልፍኙ አጠገብ የሚተኛ አባይቱ ወልደ አረጋይ የሚባል ጃንደረባ የጌታውን የፉከራ ቃል ሰምቶ ሾተሉን እንደ መዘዘ እየሮጠ ቢሄድ ባሪያውን ማጅራቱን ይዞ ሲተናነቀው ደረሰ። ጌታውም የታመነ አሽከሩን ወልደ አረጋይን ሲመጣ ባየው ጊዜ «ይህ ውላጅ አበላሽቶኛል ግን ሳትገድል ያዝና ግደል ብሎ የላከውን አናግረው» አለው። ወልደ አረጋይም «ግደል ብሎ የላከህ ማነው? » ብሎ ቢጠይቀው «አልናገርም እምቢ! ስላለ በያዘው ሾተል ቆራርጦ በእሳት ውስጥ ጥሎ አቃጠለው። ወሰን ሰገድም ወዲያው ነፍሱ ወጣችና አረፈ።

ለዚህ ዓለም ለሚባለው ባሪያ ገንዘብ ሰጥተው ወሰን ሰገድን ያስገደሉ ሰዎች በእርግጥ አልታወቁም። እኩሉ አልጋውን የፈለጉ ዘመዶቹ ናቸው ይላሉ።

እኩሉም ሚስታቸው ወይዘሮ ጣይቱ በፈቃድዋ የምትኖ ሴሰኛ እበረችና እርስዋን በዝሙት ሥራ የለመዱ ሰዎች ናቸው ይላሉ።

እኩሉ ግን ራሱ ለዚህ ዓለም ከእመቤቱ ከወይዘሮ ጣይቱ ጋራ የዝሙት ልማድ ስለ ነበረው «ሳይቀድመኝ ልቅደመው ብሎ ገደለው! » ይላሉ። ይህ ሦስተኛው ምክንያት ግን እውነት አይመስልም። እውነትም አለመሆኑን የሚያስረዳ ነገር መከረውም ያስገደሉ መኳንንቶች ሴት ምንም ቢሆን ምሥጢር ለመወሰን አትችልምና የኋላ ኋላ ምሥጢራችንን ታወጣብናለች ብለው ስለ ፈሩ «ይህ ሥራ ከወይዘሮ ጣይቱ በቀር ደፍሮ የሚሠራ የለም» የማለት ወሬ አስወርተው ሳያስመሰክሩና ሳያስፈርዱባት የጧፍ ቀሚስ አልብሰው አቃጥለው መግደላቸው ነው። ራስ ወሰን ሰገድም በሞተ ጊዜ አልቃሽ እንዲህ ብላ ገጠመች።

ምን አበላው? ምን አለብሰው? ብሎ ለምን ይጨነቃል?\

ለዚህ ዓለም ጉልበት የሰጠ አምላክ ያውቃል።

ከምድር ዳር እምድር ዳር ሲገዛ በድምጡ፣

ካውራውና ባሪያው ምነው አልተቀጡ።

አያችሁለት ወይ ይህ ውላጅ ትቢቱ፣

ከቀድሞ አሁን ድረስ አብሮ መተኛቱ።

ለሌልው መዳኒት ሰጥቶ የሚያድን፣

ባሪያ ጣለው አሉ ወሰን ሰገድን።

ራስ ወሰን ሰገድ ሸዋን ፬ ዓመት ገዝቶ በሰኔ ፪ ቀን ፲፰፻፺ ዓመተ ምሕረት አረፈና እርሱ በቁንዲ በሠራው በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ።

በዘመኑም በጐንደር በስም ብቻ የነገሠው አጼ ኢዮአስ ሲሆን ያገሩ ገዥ ግን መስፍኑ ራስ ጉግሣ ነበር።

# ምዕራፍ ፲፪

## ስለ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ

የራስ ወሰን ሰገድ ሞት በያውራጃው በተሰማ ጊዜ ሴራ ሆኖ የነበረው ጋላ /ኦሮሞ/ እንደ ገና ተነሥቶ ደብረ ሊባኖስን ደብረ ብርሃንን ከዚያም እስከ ቁንዲ ያለውን አገር በእሳት አቃጠለው።

የራስ ወሰን ሰገድ የበኩር ልጅ አቤቶ በኩሩ የመርሐቤቴን አበጋዝነት ተሾመ ይኖር ነእብርና በአባቱ አልጋ እንዲቀመጥ ተጠርቶ ጅሩ ሲደርስ የጅሩ ጋላ /ኦሮሞ/ መንገዱን ዘግቶ ስምንት ቀን ሙሉ ስለ ተዋጋ ሳይመጣ ቢቆይ የወሰን ሰገድ መኳንንት ባልጋው ሰው ሳይቀመጥ ብዙ ቀን የቆየ እድነ ሆነ የጋላ /የኦሮሞ/ ኃይል በርትቶ ሸዋን በጭራሽ የሚያጠፋው ስለ መሰላቸው ታናሹን ልጁን አቤቶ ሣህለ ሥላሴን ከቁሮ ገደል /ከሰላ ድንጋይ/ አምጥተው በ፲፰ ዓመቱ በአባቱ አልጋ አስቀመጡት።

እንግዲህ ከሣህለ ሥላሴ ጀምረን ነገሥታቱን ሁሉ እርስዎ በማለት እንጽፋለን።

አቤቶ ሣህለ ሥላሲኤ በአባታቸው አልጋ ከተቀመጡ በኋላ ራስም፤ ንጉሥም ይባሉ ነበርና ደብዳቤ እየጻፉ ሲልኩ «መልእክት ዘራስ ሣህለ ሥላሴ ንጉሠ ሸዋ» ይሉ ነበር። መታሰቢያም ሆኖ በሚቆይ ዕቃ ላይ ሲያጽፉ «ዝወንጌል ዘራስ ሣህለ ሥላሴ ንጉሠ ሸዋ። » «ዝከበሮ ዘራስ ሣህለ ሥላሴ ንጉሠ ሸዋ ይባል ነበር።»

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ሥጋዊ ጥበብ የተሰጣቸው ነበሩና ለችግረኛው ሁሉ ገንዘብ፣ ላም ለሌለው ላም፣ ጥማድ ለሌለው ጥማድ፣ እየሰጡ እረስ ቆፍር እያሉ ሀብትና ብልጥግና የሚገኝበት ሥራ ለሕዝባቸው ያስተምሩት ነበር።

ደግሞ እገሌ ዕዳ አለበት ሲሉ የሰሙ እንደሆነ ዕዳውን ለመክፈል የማይችል ደሀ መሆኑ እያስመረመሩ ከግምጃ ቤታቸው ገንዘብ እያወጡ ዕዳውን ይከፍሉለት ነበር። በርስቱም ግብር ለመገበር የማይችለውን ድሀ ግብሩን ይምሩት ነበር እንጂ ካልገበረ

ርስቱን ይነቀል አይሉም ነበርና በዚህ መልካሙ ሥራቸውና በቸርነታቸው ሁሉ የሕዝቡን ልብ በፍቅር ማረኩት።

በዚህም ላይ ደግሞ በሸዋ ዙሪያ ካሉት ባላባቶች ካማራውም ከጋላውም /ከኦሮሞውም/ ከጉራጌውም ሴቶች ልጆች እያስመጡ ቁባት እያደረጉ በማስቀመጣቸውና የራሳቸውንም ልጆች ለየባላባቱ በመዳራቸው ይህንንም የመሰለ የፖለቲካ ሥራ በመሥራታቸው ኃይልንና ከሕዝቡ ጋር መስማማትን አገኙ።

አባቶቻቸውም ያቀዱትን በአንኮበር ዙሪያ ያለውን አገር መሠረት አድርገው ግሼን፣ ግድምን፣ ኤፍራታን፣ አንጾኪያን፣ ይፋትን፣ መንዝን፣ ተጉለትን፣ አፍቀራን፣ ወግዳን፣ ቀያን፥ ደብብን፣ ዶባን፣ መርሐቤቴን፣ ላምዋሻን፣ ሞረትን እንሳሮን፣ አህያ ፈጅን፣ ቀይ አፈርን፣ ቡልጋን፣ ምንጃርን፣ የአዳል (አፋርን) አገር ከጋላውም /ከኦሮሞውም/ አገር እስከ ሶዶ ድረስ አቅንተው አንድ መንግሥት አደረጉት።

ይህም ዛሬ አዲስ አበባ ተብሎ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ የሆነው አገር በዚያ ዘመን ፊንፊኔ ይባል ነበርና ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ አገሩን ስያቀኑ አሁን ዛሬ ቤተ መንግሥቱ በተሠራበት ሥፍራ ላይ ድንኳናቸውን ተክለው በዚህ ሥፍራ ላይ የልጅ ልጄ ከተማ ይሠራበታል ብለው እንደ ትንቢት ተናግረው ነበር ይባላል።



## ሣህለ ሥላሴ ንጉሥ ሸዋ

ቢሆንም በዙሪያቸው ያለው ጋላ /ኦሮሞ/ ሴራ ከሆነ በኋላ እንደ ገና እየከዳ ያስቸግራቸው ነበርና ባመት ሦስት ጊዜ ይዘምቱ ነበር።

በኋላ ግን የአብቹና የገላን ጋሎች /ኦሮሞች/ ተጣልተው ጦርነት በጀመሩ ጊዜ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ አብቹን ያቀፉና የወደዱ ውስጥ ውስጡንም ለእርሱ የረዱ እየመሰሉ እርስ በእርሳቸው ያዋጓቸው ጀመር።

ሁለቱም ጐሣዎች ሰባት ዓመት ሙሉ ሲዋጉ ዘወትር አሸናፊው ገላን ነበር። በኋላ ግን ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ አብቹን በእውነት ለመርዳት አስበው በተነሱ ጊዜ አብቹ አሸንፈና ገላን ድል ሆነ። የአብቹንም አበጋዝነት ለተወላጁ ላቶ መረጭ ሰጡት። ከዚህም በኋላ በአብቹ ጉልበት ገላንን፣ አዳን፣ ወበሪን፣ ጅሩን፣ ዋዩን፣ ሰላሌን፣ አድክመው ገባር አደረጉት።

የጋሎች /የኦሮሞዎች/ እርስ በርስ መዋጋት የአማራን ጉልበት አበርትቶ የራሳቸውን ጉልበት አደከመ። ያገርን ባላባቶች እርስ በርሳቸው እያዋጉ ኃይላቸው ሲደክም ጥልቅ ብሎ ገብቶ አገርን መውሰድ ዛሬ የሠለጠኑት ነገሥታት ብቻ የሚያደርጉት ይመስለን ነበር። ነገር ግን አሁን ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በአብቹና በገላን ባላባቶች መካከል የሠሩትን የብልሃት ሥራ ስንመለከት ሰሎሞን ያው የተደረገው እየተመለሰ ሲደረግ ይኖራል እንጂ፣ ከፀሐይ በታች አዲስ ነገር የለም ያለውንን ያሳስበናል።

# ምዕራፍ ፲፫

## አቶ መተኰ ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ስለ መከዳቱ

ለንጉሥ ሣህለ ሥላሴ አቶ መተኮ የሚባል ሎሌ ነበራቸው። እርሱም ኃይለኛና ጀግና ስለ መሆኑ የጦር አበጋዝ አድርገውት ነበርና እንደዚሁ አበጋዝ ሆኖ ዘምቶ ሳለ በጋሎች /በኦሮሞዎች/ መንደር አቅራቢያ ሲደርስ አብረው የዘመቱትን መኳንንቶች አቶ አሸብርንና አቶ ገብሩን ጠርቶ በፍጥነት ሄዳችሁ ያንን የሚታየውን የጋሎች /ኦሮሞዎች/ መንደር አቃጥሎ ብሎ ስላዘዛቸው ሄደው ገና አንድ ቤት መለኮስ ሲጀምሩ ጋሎች /ኦሮሞዎች/ ሁለት ጮሌ ፈረሶች ይዘውለት ቢመጡ ፈረሰኛ ልኮ የጋሎቹን መደር ማቃጠላችሁ ይቅርና ተመለሱ አላቸው። እነዚያ ግን «አይንቀዠቀዥብን! አንድ ጊዜ አቃጥሉ ብሎናል» ብለው መንደሩን ሁሉ አቃጠሉት።

አቶ መተኮም እንኳ ይህን ያህል ነገር አግኝቶና እንዲያውም ቁጡ ስለ ነበረ ከሁለቱ መኳንንቶች ጋራ ለመዋጋት አስቦ ሳለ በዚያው የነበሩት ሌልቾ መኳንንቶች በመካከል ገብተው ገደሏቸው።

ከዘመቻው ሲመለሱ ግን ቂሙን አልረሳም ነበረና ወደ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ገብቶ «ንጉሥ ሆይ! » የንጉሥ ሎሌ ና! ሲሉት የሚመጣ ሂድ! ሲሉት የሚሄድ ነው። እነዚህ ሎሌዎች አሸብርና ገብሩ ግን በኃይላቸውና በጉልበታቸው እየተመኩ አይታዘዙምና እኔ

በነርሱ ላይ አበጋዝ ለመሆን አልችልም። ስለዚህ ይህን ጉልበታቸውን በጋላ /ኦሮሞ/ እንዲያደርጉት በየዳር አገሩ ይሹሟቸው» ብሎ ተናገረ።

በዚያንም ዘመን የዳር አገር የሚባለው በሸዋ በደቡብ ምንጃር በሸዋ ሰሜን ግድም ነበርና ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በአቶ መተኮ ምክር ላቶ አሸብር ግድምን ላቶ ገብሩ ምንጃር ሾመው ሰድደዋቸው።

አቶ ገብሩም በዚህ ተናዶ ነበርና «የቦርጃ ልጅ ከንዱ በምን እንደዚህ ጠነከረለት ይሆን? እኔን ቢወረውር ምንጃር። አሸብርን ቢወረውር ግድም ጣለን» ብሎ ተናገረ ይባላል።

ነገር ግን በነገረ ሠሪነት ሌላውን ሰው ከንጉሥ ጋራ የሚያጣላ ሰው ጊዜው ሲደርስ በራሱ ሳይደርስበት አይቀርምና አቶ መተኮ በልጁ ጋብቻ ምክንያት ከንጉሥ ጋራ ስለ ተጣላ በእስላም ቤት አግብተው አስረውት ነበር።

ነገሩም እንደዚህ ነው። ጃራ የሚባል ልጅ ነበረውና ወደ ንጉሡ ገብቶ «ልጅዎን ወይዘሮ በለጥሻቸውን ለልጄ ለጃራ ይስጡልኝ» ብሎ እርሱ ራሱ ደፍሮ በቃሉ ነገራቸው።

ንጉሡም ይህን ያቶ መተኮን ቃል በሰሙ ጊዜ ለጊዜው እጅግ አዘኑ። ያዘኑበትም ምክንያቱ ለልማዱ ንጉሥ ሴት ልጁን ከመኳንንቱ መካከል በጉብዝናም ቢሆን፣ በባለጠግነትም ቢሆም በጨዋ ልጅነትም ቢሆን፣ ላንዱ መርጦ ልጄን ሰጥቸሃለሁ ብሎ ይድርለት ነበር እንጂ የነጋሢ ዘር ካልሆነ በቀር እርሱ ደፍሮ የንጉሥ ልጅ ለማግባት የሚለምን አልነበረም።

ሁለተኛም እንኳን የንጉሥ ልጅና የሌላም የተራ ሰው ልጅ ብትሆን ሽማግሎች መርጦ «የዕገሌን ልጅ ለዕገሌ ለማጋባት አስቤአለሁና ለአብቷ ንገሩልኝ።» ብሎ ሽማግሎች ይልካል እንጂ እርሱ ራሱ ደፍሮ ልጅህን ለልጄ ስጥልኝ ብሎ የሚናገር ከሺ አሥር አይገኝም ነበር። አቶ መተኮ ግን ሁለቱንም ያገር ልማድ ሳይጠብቅ ልጅዎን ወይዘሮ በለጥሻቸውን ለልጄ ለጃራ ይስጡልኝ ብሎ ራሱ ደፍሮ መናገሩ ነው።

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴም «ነገሩን አስቤና መክሬ ምላሹን ሌላ ጊዜ እነግርሃለሁ» ብለው ካሰናበቱት በኋላ፥ ከባለሚሎቻቸው ጋር መከረው «እሺ ልጄን በለጥሻቸውን ለልጅህ እሰጥሃለሁ» አሉት።

አቶ መተኮም ይህን ትልቅ የምሥራች ቃል ሰለ ሰማ እንደ አገሩ ልማድ ሰንጋውን፣ ፈረሱን፣ በቅሎውን፣ ወርቁን፣ ብሩን፣ ጋሻውን፣ ጐራዴውን፣ ይህን የመሰለውን ሁሉ በብዙ አሰናድቶ ማጫ ነው ብሎ ለንጉሡ አቅርቦ ተቀብለውት ነበር።

ነገር ግን እናቲቱ ወይዘሮ በዛብሽ ልጃቸውን ለአቶ መተኮ ልጅ ለጃራ ለመዳር ደስ አላላቸውም ነበርና ነገሩን የሚያፈርሱበት ምክንያት ይፈልጉ ጀመር።

ከጥቂትም ወራት በኋላ ከወደ ይፋት የመጡ ላሊበሎች በከተማ ሲጮሁና ሲለምኑ ነበርና ያቶ መተኮ ዘምዶች ናቸው ተብሎ እንዲወራ አድርገው «ልጄን ትውልዱ ንጹሕ ላልሆነ ሰው አልሰጥም» ብለው በግልጥ ተናገሩ። በዚህም መካከል ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ እምቢ አልሰጥም! እንዳይሉት እሰጣለሁ ብለው ማጫውን ሁሉ ተቀብለውታል። እንዳይሰጡትም ሚስታቸው ወይዘሮ በዛብሽ ይህን የመሰለ ወሬ አስወርተው ልጄን ለጃራ አልሰጥም በማለት ቁርጥ ነገር ነግረዋቸዋል። እንደዚህም ተጨንቀው ሳሉ ውሎ አድሮ ሴት ማሸንፍዋ አይቀርምና ሚስታቸውን ወይዘሮ በዛብሽን ደስ ለማሰኘት ሲሉ ቃላቸውን ለውጠው ልጄን ለልጅህ አልሰጥም ብለው ጋብቻው እንዲቀር አደረጉ።

ደግሞ እንኳን የተነገረና የታሰበም ቢሆን በወራቱ መታወቁ አይቀርምና ጋብቻው የቀረበት ምክንያት በዘሩ እድፍ አለበት ተብሎ መሆኑ አቶ መተኮ ስለ ሰማ እጅግ ተናደደ። ከዚያም ጀምሮ ከጌታው ለመከዳት ቁርጥ አሳብ አድርጎ ነበርና በንግግሩም በሥራው ሁሉ ስለ ተጠራጠሩት አስይዘው ጐንጅ በሚባል የእስላም ቤት አሠሩት።

ከጥቂት ቀን በኋላ ግን አንዲት ደንደሳም ባሪያ ነበረችና እርስዋ የቤቱን ጣሪያ በትከሻዋ ገፍታ አንሥታ አሾልካ ሰደደችው። በማግሥቱም በማለዳ ዘበኞች ከፍተው ገብተው ቢያዩ አቶ መተኮ ታጣ። ወደ ቀኝም ወደ ግራም ተመልክተው ግድግዳው አለ መቀደዱን መዝጊያውም አለ መከፈቱን አይተው ነገሩ ቢቸግራቸው ባሪይዋን ይዘው «የሄዱበትን አላየሽሞይ? » እያሉ ይጠይቋት ጀመር። እርሷም ጌታዬን ሲሄዱ ካየኋቸው አብሬ እሄድ ነበር እንጂ ለምን እለያቸው ነበር ብላ ብትመልስላቸው ለቀቋት።

አቶ መተኮ ግን ምንም ለመከዳት ለመሸፈት ቢያስብ ገና አልተሰናዳም ነበርና ወደ አለቃ አሥራት ሄዶ ስለ ወወለ አግልደው አስታረቁት። ከዚህም በኋላ እንደ ጥንቱ ባለሟል ሆኖ ጥቂት ወራት ከቆዩ በኋላ ክፉ አመል ሳያስቀብር አይለቅም እንደሚባለው «ንጉሥ እሰጥሃለሁ በለው በቃላችው የነገሩኝን አገር ለሌላ ሰው ሰጡብኝ« የሚል ምክንያት ፈልጎ እንደ ገና ከድቶ ጋላ /ኦሮሞ/ አገር ገባ። የጠቡ ምክንያት ግን ያው የፊተኛው የጋብቻው ነገር በመቅረቱ ነበር እንጂ፣ ያገሩ ነገር ማደነጋገሪያና ማሳሳቻ ነበር። ደግሞም የራሱ መከዳትና መሸፈት አንሶት «አንተም ሣህለ ሥላሴን ከድተህ ከእኔ ጋራ ሁን» እያለ ወደ አድአው ባላባት አቶ ቡኔ ይላላክ ጀመር። አቶ ቡኔ ግን ብልህ ሰው ነበርና «ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የበደሉኝ ነገር የለምና ካንተ ጋር ተደርቤ አልከዳም» የሚል ቃል መለሰለት።

ከዚህም በኋላ ለማስፈራራት ብሎ «እንግዲያው መምጣቴ ነውና ተጠንቅቀህ ቆየኝ ሳልሰማ በድንገት መጥቶ ወጋኝ እንዳትል» የሚል የጥጋብና የትዕቢት ቃል ቢልክበት «ብትመጣ ምን ቸገረኝ። ላንተ እኔ አለሁልህ። ለልጅህ ለጃራ ልጄ ሽምቡ አለው፣ ለወንምድህ ለኃይሉ ወንድሜ ጂሎ አለው፣ ለፈረስህ ለመጋል ፈረሴ ዳማ አለና መጥተህ ሞክረኝ» ብሎ የጉብዝና ቃል ቢመልስለት ያቶ ኑነኔ አኳኋን አይቶ «ጋሎች /ኦሮሞዎች/ የማያስጠኙኝ ከሆነ ሣህለ ሥላሴ አስፈልገው ሳይሲዙኝ አይቀሩም በዕርቅ ገብቼ አዘንግቼ ብገድላቸው ይሻለኛል እንጂ፣ ሌላ ማምለጫ የለኝም» በማለት አሳቡን ቆረጠና እንደ ገና ከንጉሡ ጋራ ታረቀ።

ንጉሡንም ለመግደል የተመቸ ጊዜና ሥፍራ ሲፈልግ ነበርና በዚያ ወራት ውደ አንጐለላ ከተማቸው ሄደው ሳሉ እርሱም ልጁን ጅራን አስከትሎ ወደ አንጐለላ ሄደ። ልጁ ጃራ ግን አባቱ ንጉሡን ለመግደል ማሰቡን ልቡ ያውቅበት ነበርና ወደ ንጉሡ አግፋሪ ወደ ሻቃ ግፋወሰን ገብቶ »ይህ የእኔ አመለኛ አባት አሳቡና አኳኋኑ ሁሉ አላማረኝምና ከንጉሡ ጋራ በቆይይታ አነጋግረኝ ብሎ የነገረህ እንደ ሆነ አይመችም ብለህ ከልክለው እንጂ፣ እንዳታስገባው» ብሎ ነገረው።

ከዚህም በኋላ አቶ መተኮ የተሳለ ጉንዶውን ታጥቆ መጥቶ ሻቃ ግፋወሰንን አስጠርቶ «ዛሬ ከንጉሡ ጋራ በቆይታ የምነጋገረው ጉዳይ አለኝና ንገርልኝ» አለው። እርሱም በመኳንንቱ ማረፊያ በተዘጋጀው ቤት እንሽ ድንክ አልጋ ላይ አሳርፎት ገብቶ «አቶ እምተኮ ከንጉሡ ጋራ አገናኝኝ ብሎ መጥቷል። ልጁ ጃራ ግን አባቴ በሽታው ተነሥቶበታልና እንዳታስገቡት ብሎ ነግሮኝ ነበር። እንደ ምን ይሁን?! ብሎ ቢነግራቸው «አሁን ለግዚኤው ለጓዝህ ማሣረፊያ ፍየል አንባን ሰጥቸሃለሁ ብለውሃል ብለህ ንገረው» አሉትና ወጥቶ ይህን ቢረግረው «አገናኝተህ አነጋግረኝ አልሁህ እንጂ፣ አገር አሰጠኝ ብዬ መቼ ላክሁህ!» ብሎ በቁታ ቃል ተናገረው። ግፋወሰንም እንደ ገና ተመልሶ ገብቶ «ንጉሥ ሆይ! አቶ መተኮ እጅግ ተብቷል። የንጉሡን ቃል ብነግረው «አገናኝኝ አልሁህ እንጂ አገር አሰጠኝ አልሁህ ወይ?» ብሎ ገላመጠኝ አሁን ወጥቼ እጁን ብይዘው ይሻላል» ቢላቸው «ተው! አይሆንም ኃይለኛ ነውና አትችለውም ይገድልሃል» አሉት። «መተኮን እንደዚህ ያኮሩት እርስዎ ነዎት እንጂ፣ አንድ የገባር ልጅ አይደለምን። አሁንም ሣህለ ሥላሴ ይሙት እጁን ሳይልዘው ይቀረሁ እንደሆነ» ብሎ ፎክሮ ወጥቶ « ተያዝ! ብለውሃል» ቢለው «ቶኪቻ ፈርዳ!» ብሎ ፎክሮ ከተቀመጠበት ተነስቶ በታጠቀው ጉዶ /ጩቤ/ ትከሻውን ወጋው።

ከዚህም በኋላ ገስግሶ ገብቶ ንጉሡን ለመግደል ሲሄድ ግፋወሰን ነፍሱ አልወጣችም ነበርና «አበላችሽቶኛል! አያምልጣችሁ!» ብሎ ስለ ጮኸ አቶ መተኮ መለስ ብሎ «አንተ ውላጅ ሞተሃል መስሎኝ ነበር እንጂ!» ብሎ እንደ ተመዘዘ በያዘው ስለታም

ጉዶ አንገቱን ቢለው ራሱ ለብቻው ተሽከርክሮ ወደቀ። ይህንም ካደረገ በኋላ በደም የተነከረ ጉንዶውን በእጁ እንደያዘ ወደ እልፍኝ በር ቢገሰግስ አቶ ጠንቀኛ የሚዒባለው አይቶ «ምነው የቦርጃ ልጅ ማበድህ ነወይ?» እያለ ካቡን ተጠግቶ ሁለቱንም ቋንጃውን በጐራዴ መታው።

ከተመታም በኋላ እንደ ፊታ በሬ ሸለል ሸለ እያለ ንጉሡ ወዳሉበት እልፍኝ ለመግባት ሲጣጣር በአደባባይ ያለ ሰው ሁሉ በበትርም በደንጋይም ቀጥቅጦ ገደለውና ወደቀ። ውሾች እንኳ ሳይቀሩ እየጮሁ መጥተው እጁን ገነጣጥለው ጣሉት ይባላል።

ንጉሡም የቤቱን መስኮት ከፍተው ሁለት አፍ ግንጥል ጠመንጃቸውን አነጣጥረው ሲጠባበቁት ነበርና መሞቱን ቢነግሯቸው ምንም እንኳ ባጋፋሪያቸው በግፋወሰን ሞት ቢያዝኑም በመተኮ ሞት እጅግ ደስ አላቸው።

ከዚህም በኋላ «አጋም ተጠግቶ የበቀለ ቁልቋል ሲያለቅስ ይኖራል» እንደሚባለው ባቶ መተኮ የከፋት ሥራ ወንድሙ አቶ ኃይሉ ስለ ፈራ ወደ አብቹ ሄዶ ወዳጅ ግርሜ የተባለ የጋላ /የኦሮሞ/ ባላባት ሎሌ ሆኖ ተቀመጠ። ወዳጅ ግርሜም አቶ ኃይሉን በማር ወልዶ የሞጋሳ ልጅ አደረገው። ነገር ግን ምንም ቢሆን ልክስክስነቱን አይተውምና የሞጋሳ ልጁን ያቶ ኃይሉን ሚስት ውሽማ አድርጎ ስለ ያዛት አቶ ኃይሉ በዚህ እንገር ተቀይሞ ወደ ቡልጋ ገዥ ወደ አቶ ብርቄ ዘንድ ሄዶ እባክህ ከንጉሡ ጋር አስታርቀኝ ብሎ ለመነው። አቶ ብርቄም ንጉሡ መተኮ እኔን እገድላለሁ ብሎ በገዛ ሥራው ሞተ እንጂኢ እኔ ምን አልሁት? ኃይሉስ ምን በድለኝ?» እያሉ ዘወትር ሲናገሩ ሰምቻለሁና ስታርቅሀለሁ» አለው።

አቶ ኃይሉም «ነገሩ እንደዚህ ከሆነ መልካም እመጣለሁ። ስመጣም ያ ጋላ /ኦሮሞ/ ሚስቴን ስለ ቀማኝ ገድየው እመጣለሁና በዚህ ቀን በዚህ ሥፍራ እንድትጠብቀኝ» አለው።

አቶ ብርቄም ይህን ነገር በሰማ ጊዜ «መግደሉንስ አዘንግተህ በድንገት ትገድለዋለህ። ነገር ግን ከገደልከው በኋላ ያብቹን ፈረስ እንደምን አምልጠህ ትመጣለህ?» ቢለው «በቀጠሮው ቀን ጠብቀኝ እንጂ ላገዳደሉና ለማምለጡ አታስብ» ብሎት ሄደ፡ ከድቶ ለመሄድም ባሰበበት ቀን ወዳጄ ግርሜ ብዙ ጥማድ አስጠምዶ ያስርስ ነበርና አሽከሮቹን «ፈረሶች ጫኑና ተከተሉኝ። እኔም ከወዳጄ ግርሜ ጋር ቆሜ ስነጋገር ያያችሁ እንደ ሆነ ፈረሶቹን አራግፋችሁ አንከባሏቸውና በቶሎ መልሳችሁ ጫኗቸው። ቅናቱም እንዳይላላ አጥብቁ ከሰውም ጋራ ስጣላ ብታዩ አትደንግጡ!» ብሎ ምክር ሰጥቶ እርሱ ቀድሞ ወደ እርሻው ሥፍራ ሄደ።

ወዳጄ ግርሜም በገበሬዎቹ መካከል ወዲያና ወዲህ እየተመላለሰ እርሻውን ሲያይ አቶ ኃይሉ ጠጋብ ብሎ ያነጋግረው ጀመር። ጋላውም /ኦሮሞውም/ ለክፉ ነገር ያስበኛል ብሎ አልጠረጠረም ነበርና ወደ «እኅትህ ባል ወደ አቶ ብርቄ ሄደህ ነበር አሉ፣ ለምን ሄደህ ኑርዋል? አለው። እርሱም ከሣህለ ሥላሴ ከድቼ ስመጣ ያደራ ፍየሎች አስቀምጬበት ነበርና ንጉሥ የሰሙ እንደ ሆነ ይጣሉኛልና ውሰድልኝ ብሎ ቢልክብኝ ነገሩን ለመነጋገር ሄጄ ነበር አለው።

ከዚህ በኋላ ገበሬዎቹ ጥማዳቸውን አከታትለው ፊታቸውን አንድ ወገን አዙረው ሲያርሱ አይቶ በያዘው ጦር መኻል ደረቱን ወግቶ ጣለው። መዳጅ ግርሜም ተጣጥሮ የኃይሉን ልብስ ቢይዝበት የሱን ለብስ ወርውሮ ጥሎበት የጋላውን /የኦሮሞውን/ ልብስ ነጥቆ የወርቅ ቀለበቱን ከጣቱ ላይ በጥርሱ አውልቆ በጉንጩ እንደ ያዘ ፈረሱን ጋልቦ ሄደ።

ነገር ግን ልብሱን ለወዳጅ ግርሜ ወርውሮ ጥሎ የወዳጅ ግርሜን ልብስ ለብሶ ነበርና ፈርሱ የጋላ /የኦሮሞ/ ልብስ ቢሸተው ጠረን ስለ ተለወጠበት አላስወጣ ብሎ እየዘለለ ካስቸገረው በኋላ በብዙ ማባበልና በማዘንጋት ተቀምጦ ሄደ። ገበሬዎችም ሁሉ የወዳጅ ግርሜን ሞት ያቶ ኃይሉን መሸሽ አይተው ይጮሁ ነበርና የየመደሩ ጋላ /ኦሮሞ/ ጩኸት እየሰማ ሲመጣ አቶ ኃይሉን በመንገድ እያእኘ ምንድነው? እያለ ሲጠይቀው ገበሬዎቹ ባንድ ምክንያት እርስ በርሳቸው ተጣልተው ይሆናል እያለ አለፈ።

አንዳንድ ጋሎች /ኦሮሞዎች/ ግን ከእርሻው ሥፍራ እየደረሱ ነገሩን ካወቁት በኋላ በፈረስ ተከታትለውት ነበርና ፈረሱን ዘወር አድርጐ «አብቹዎች! ዓይናችሁን አጥፍቼ እጃችሁን ቆርጬ ሸሽቻለሁ። እንግዲህ ሞቱን የወደደ ይቀረበኝ!» እያለ ድምጡን እያሰማ ስለ ተናገረ «በሚስትህ እንገር መበደልህን እናውቃለንና እግዚአብሔር ያውጣህ!» እያሉት ተመልሱ።

አቶ ኃይሉም ከአቶ ብርቄ ጋራ ወደ ተቃጠሩበት ሥፍራ ሄዶ «ያንን ጋላ /ኦሮሞ/ ገደልሁት!» ብሎ ፎከረለትና በጉብዝናው እጅግ ተደነቀ።

ከዚህም በኋላ አቶ ብርቄ ወደ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ገብቶ አቶ ኃይሉ ወዳጅ ግርሜን ገድሎት መጣ ብሎ ቢነግራቸው ወሰን ሰገድ ይሙት! የቁሮ ገደል ሥላሴን ይህን ነገር አይደረግም ውሸት ነው፣ መግደሉንስ ይግደለው ያብቹን ጋላና /ኦሮሞና/ ፈረስ እንደ ምን አምልጦ መጣ አሉት። አቶ ብርቄም መልሶ «ወሰን ሰገድ ይሙት! እመቤቴን ማርያምን ገድሎት ነው የመጣው» አላቸው።

ሁለቱም ወሰን ሰገድ ይሙት ማለታቸው ለንጉሡም አባታቸው ላቶ ብርቄም ጌታ ስለ ሆኑ ባታችን በኢትይዮጵያም ልጅ በአባቱ ሎሌ በጌታው ስም መማል ልማድ ስለ ሆነ ነው። ደግሞ ንጉሡ የቁሮ ገደል ሥላሴን ማለታቸው አቶ ብርቄም እመቤትን ማርያምን ማለቱ ባገራችን በኢትዮጵያ በሚወዱትና ባደጉበት አገር ታቦት መማል ልማድ ስለ ሆነ ነው።

ንጉሡም አቶ ብርቄ ምሎ ከነገራቸው በኋላ «የቦርጃ ሽንት /ዘር/ ምንድነው ትለኛለህ? መተኮ እኔን እገድላለሁ ብሎ ሞተ። ያንተም ሚስት ጠባቂዋን በፍልት ደብድባ ገደለች። ኃይሉ ደግሞ ወዳጅ ግርሜን የሚያህል ስመ ጥሩ ባላበት ጋላ /ኦሮሞ/ ገድሎ ካብቹ ጋላና /ኦሮሞና/ ፈረስ አምልጦ መምጣቱ እጅግ የሚያስደንቅ ነገር ነው። አሁንም አምጣው እታረቀዋለሁ።» አሉት።

በቀጠሮው ቀን አቶ ብርቄ አቶ ኃይሉን አመጣውና በንጉሥ ፊት እጅ በነሣ ጊዜ «ወንድምህ መተኮ እኔን ካልገደልሁ ብሎ በገዛ ሥራው ሞተ እንጂ፣ እኔ ግደሉት ብዬ አላዘዝሁም ነበር። ምናልባት ወዳጅ ግርሜ ባንተ እጅ እንዲጠፋ ከእግዚአብሔር የታዘዘ ነገር ቢኖር ሄደህ ይሆናል እንጂ፣ ምሬሀለሁና እንደ ቀድሞህ ሎሌዬ ሆነህ ኑር» ብለው ታረቁት።



ንጉሥ ሣህለሥላሴ በደብረብርሃን የጦር ትርኢት ሲመለከቱ



በንጉሥ ሣህለሥላሴ ዘመን የፈረሰኛ አለባበስ

# ምዕራፍ ፲፬

## በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘመን የውጭ አገር ሰዎች ወደ ሸዋ ስለ መምጣታቸው

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ባንድ ወገን ሥራቸውን ሁሉ በዕውቀትና በጥበብ በመሥራታቸው በሁለተኛም ወገን የቀዳማዊ ምኒልክ ዘር ተወላጅ በመሆናቸው ዝናቸው በውጭ አገር ተሰምቶ ነበርና ከጭ አገር ሰዎች እንደ አንዱ አገር ለማየትና የንግድ ሥራ ለመጀመር፣ አንዳንዶቹም የወንጌል መላክተኞች እየሆኑ፣ አንዳንዱም ከየመንግሥታቸው እየተላኩ ወደ ሸዋ መምጣት ጀመሩ፡

ከነዚሁም ዋነኞቹ በ፲፰፴፪ ዓ.ም ከእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ተልከው የመጡ ዶክተር ክረጵፍና ምስተር ኢዘምበርግ /አይዘምበርግ/ ነበሩ። ከነዚህም ቀጥሎ በ፲፰፻፴፬ ዓ.ም ከእንግሊዝ ንግሥት ከቪክቶሪያ ተልኮ መጥቶ የንግድና የወዳጅነት ውል ተዋውሎ

አንድ ዓመት ከ፯ ወር ያህክ ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ጋር በአማራውም በጋላውም /በኦሮሞውም/ አገር እየተዛወረ ቆይቶ ወደ ሀገሩ የተመለሰ ሀሪስ ነው። የተዋዋለውም የውሉ ቃል ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው፡

## የወዳጅነትና የመነገድ አንድነት።

*ሣህለ ሥላሴ የሸዋና የይፋት የጋሎችም /የኦሮሞዎችም/ ንጉሥ። ካፒቴን ሀሪስ እርሱም ከቦምቢ /ቦይቤይ/ መኰንን በታች የሚሆን የቪክቴሪያም በታላቅ ብሪታንያ በኢርላንድም በሕንደኬም ንግሥት ስም የሚናገር በዚህ ጦማር የመንገድና የወዳጅነት አንድት አደረጉ። እንዲሁም እርስ በርሳቸው ተጋጠሙ ተስማሙ።*

*መነገድ ለሕዝብ ሁሉ እርስ በርሱ በወዳጅነት በፍቅርም ለሚገጥም የታላቅ ባለጠግነትና ደህንነት ምንጭ ነውና በሸዋና በብሪታንያ መካከል ወትሮ የሚኖር ወዳጅነት፣ የመነገድም አንድነት እንዲሆን በቀደም ይጠቅመ ብለው ፈልገዋልና፣ ደግሞም የወዳጅነት የደህና ፈቃድም የፍቅርም ምልክት በቀደም ሸዋም ንጉሥ በብሪታንያም ንግሥት መካከል ተሰጣጥተዋልና አሁን በምን ነገር ስለ መነገድ አንድነት ሁለት ገዥዎች እንደ ተስማሙ ማወቅ ይፈለጋልና ስለዚህ በዚህ ጦማር ነገሩ ይታወቅ ዘንድ ይቆረጥም ይስማሙም ዘንድ ይወዳሉ። እንደዚህ ሲሉ።*

ንጉሥ ሣህለሥላሴ በበቅሎ ተምጠው ሲጓዙ





ንጉሥ ሣህለሥላሴ በፍርድ ችሎት ላይ ሆነው

(ሥዕሎቹ ኢትዮጵያ ኤንግሬቨድ ከተባለው የሪቻርድ ፓንክኸረስት መጽሐፍ የተወሰዱ)

፩ኛ ጽኑ፣ ቅንም፣ ወትሮም የሚኖር ወዳጅነት ይሁን። በኀህለ ሥላሴ በሸዋ ንጉሥና ከርሱ ዘር የሚመጡ ምትኮች። በቪክቶሪያም በብሪታኒያም ንግሥት ከርስዋም ዘር በሚመጡ ምትኮች መካከል።

፪ኛ ይህ እርስ በርሳቸው የተደረገ ወዳጅነት እንዲጠባበቅ እንዲጸናም የሸዋ ንጉሥ ምኮችም የብሪታንያ ወይስ የእንግልጣር ንግሥት ምትኮቿም የሚልኩትን እንደኔ /እንደራሴ/ ወይስ መላከተኛ በሚገባው መዓርጉ ክብሩ ይቀበላሉ። ይወዱታልም።

፫ኛ እንዲህም ደግሞ የብሪታኒያ ንግሥት ምትኮቿም የሸዋ ንጉሥ ምትኮቹም የሚልኩትን እንደኔ ወይስ መላከተኛ በሚገባው ክብሩና መዓርጉ በደህና ይቀበላሉ። ይወዱታልም።

፬ኛ የመነገድም አንድነት በሸዋና በብሪታንያ ማኻል እንዲህ ይሁን።

፭ኛ የሸዋ ንጉሥ ምትኮቹም የእግንሊዝ ነጋዴዎች ከብታቸውን ወደ ሸዋ የሚያመጡ፣ በሸዋም ከሚሸጡትም ነገር ሁሉ ከመቶው አምስት ቀረጥ ይወስዳሉ ይቀበላሉም።

፮ኛ ይህ ከመቶው የሚወጣ የአምስት ቀረጥ እንደ ከብቱ ዋጋ መጠን በልዩ አምባ ገበያ ይቀረጥ ይከፈልም። ወይስ በብር ወይስ በከብቱ ዓይነት ነጋዴ እንደሚወድ መጠን።

፯ኛ ነጋዴ ይህን የከብቱን በሥራት ከከፈለ በኋላ ከብቱን ወይስ በሸዋ ወዲያ ይዞ ይሸጥ ዘንድ ይችላል። ማንም ሳያስቸግረው ዕቃውንም የሚገዙትን ሳይከለክል።

፰ኛ የብሪታንያ ነጋዴዎች ወይስ በሸዋ ወይስ ከሸዋ ወዲያ የተገኘ ነገር ሁሉ ቢወዱት ይገዛ ዘንድ ያለ ቀረጥም ወደ ሀገራቸው ይወስዱት ዘንድ ይችላሉ።

፱ኛ እንዲህም ደግሞ የሸዋ ነጋዴዎች ወደ ብሪታንያ የሚመጡ ሌላ ቀረጥ አይከፍልሙ። የብሪታንያ ሰዎች በጊዜው የሚዒከፍሉት በቀር ይህ ነው።

፲ኛ አሁን በሸዋ በብሪታንያ መካከል የተደረገ የመነገድ አንድነት ያድግ ዘንድ ይባዛና ይጸና ዘንድ የሸዋ ንጉሥ ምትኮቹም ነጋዴዎቹን ሁሉ ያመልከታሉ። ልብንም ያደርጉላቸዋል። ካፍሪካ ውስጥ በሸዋ መንገድ አልፈው ከብታችውን ያመጡ ዘንድ ከሁሉም ይልቅ በእንግሊዝ ገበያ ነጋዴዎች ከሚሹትና ከሚወዱት ነገር ጋራ ይነግዱ ዘንድ እንዲወዱ።

፲፩ኛ እንዲሁም ደግሞ የብሪታንያ ንግሥት ለነጋዴዎቿ ልብ ያደርጋሉ እርሳቸው በሸዋ ገበያ የተወደደውን የተፈለገውንም ነገር ያመጡ ዘንድ።

፲፪ኛ ዳሩ ግን ነጋዴዎች መንገድ ያደርጉ ዘንድ እንዲችሉ ምንምን በመንገዳቸው እንዳይጐዳው የሸዋ ንጉሥና የብሪታንያ ንግሥት ምትኮቻቸውም ኃይላቸውን ሁሉ ይዘው በጣም ይጋደላሉ። ከባሕር ዳርቻ ወደ ኢትዮጵያም የሚወስደውን መንገድና መግባት ይከፍቱ ያበጁም ይጠብቁትም ዘንድ።

፲፫ኛ ከብሪታንያ ወደ ሸዋ የሚመጡ መንገደኞች በተግባራቸው በመንቀሳቀሳቸውም በሸዋ ወይም በሜዳቸው ከሸዋ ወዲያ ወደ ሌላ አገር አይከለከልም።

፲፬ኛ እነዚህ መንገደኞች ለመሸጥ ያላመጡትን ዕቃዎች ቀረጥ አይሰጡም። እንደ ነጋዴዎች አልተቆጠሩምና ዕቃቸው የራሳቸው ነው ማንም ሳይነካው።

፲፭ኛ እንደዚህ ደግሞ ሸዋዊ መንገደኛ ወደ ብሪታንያ ንግሥት ግዛት ቢመጣ እንደ ፈቃዱ ይቀመት። ወይስ ከብሪታንያም ንግሥት ምትኮቿም እርስ በርሳቸው በስማቸው በቃላቸውም ይዋሳሉ። ይህን የወዳጅነታቸውን አንድነት ወትሮ እንደ ችሎታቸው በጣም ይጠብቁት ዘንድ እንዲወዱ ለጽል ምክንያት ሳይሰጡ ለፍቅርና ለወዳጅነት እንጂ።

እንደዚህ ተደረገ፣ በዚህም ጦማር ተጻፈ። ተቆረጠም። ባንጐለላ ከተማ በወርኃ ኅዳር በ፲ ዕለት ፲ወ፰ወ፴ወ፬። ሣህለ ሥላሴ በነገሡ በ፳፱ ዓመት።

## በእጅና በማኅተም

ካፒቴን ሀሪስ ፊርማ። የሣህለ ሥላሴ የሸዋና የይፋት የጋሎችም /የኦሮሞዎችም/ ንጉሥ ማኅተም።

ይህ ውል በተጻፈበት ሰሌዳ በአርእስቱ ላይ የሦስቱ ሥላሴ ሥዕል ተስሎበታል። በስተቀኝ የአንበሳ በስተግራም የርግብ ሥዕል አለበት።

አማርኛው ቋንቋ እጅግ አልተጣራም። ምናልባት ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ቋንቋ የተረጐሙለት። ከእነርሱ አስቀድሞ መጥተው በሸዋ የሚኖሩ የወንጌል መላክተኞች ዶክተር ክራጵፍና ምስተር ኢዘንግበርግ /አይዘንበርግ/ ሳይሆኑ አይቀሩም።

ቢሆንም የአማርኛ ቋንቋ ለሚያውቅ ሰው አሳቡ የተሰወረ አይደለም።

ከዚህም ቀጥሎ ፲፰፴፯ ዓ.ም የፈረንሳዊ ንጉሥ የታላቁ ሉዊ ፊሊፕ መላክተኛ ሙሴ ሮሼ መጥቶ አንድ ዓመት ከ፰ ወር ያህል በሸዋ በሌሎቹም ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በሚዛወሩባቸው አገሮች ሁሉ አብሮ እየሄደ ከቆየ በኋላ የንግድና የወዳጅነት ውል ተዋዋለ። የውሉም ቃል ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

ደብዳቤውንም፣ ሥራውንም ንግዱንም ለታላቁ ሉዊ ፊሊፕ የፈረንሳይ ንጉሥ። ሣህለ ሥላሴ የሸዋ ንጉሥ የሀበሻ መንግሥት በልጅዎ በልጅ ልጅዎ ይረጋል።

ሣህለ ሥላሴ የሸዋ ንጉሥ ከታላቁ ሉዊ ፊሊፕ ጋር ፍቅር ጀምረዋል።

ባቶ ሮሼ ዲሬኩር በረከት ተላልከው አሁን ወዳጅነት እንዲበረታ በሸዋ ንጉሥና በፈራንሲስ ንጉሥ መካከል ንግድ እንዲጠና መሃላ ይፈልጋሉ። ይህን መልዕክት የነገሩትን አቶ ሮሼ ናቸው ንጉሥ እንደ ሻለቆች የአሸለሚቸው።

## ፩ኛ ክፍል።

የሸዋ ሰዎችና የፈረንሲስ ሰዎች በሃይማኖት አንድ ሊሆኑ ተቃርበዋል። በሸዋ ላይ ሌላ ጠላት ፈረንጅም ቢሆን እስላምም ቢሆን የተነሣበት እንደ ሆነ የፈረንሲስ ንጉሥ ይጣላቸዋል። የሸዋም ንጉሥ በዚያን ጊዜ ደስ ይለዋል።



ንጉሥ ሣህለሥላሴ በካፒቴን ሀሪስ የተመሩትን የእንግሊዝ መልእክተኞች ሲቀበሉ



ሣህለሥላሴ ንጉሠ ሸዋ ከፈረንሣዩ ንጉሥ ሉዊ ፊሊፐ የተበረከቱላቸውን የንጉሡን ምስልመድፍና ጠመንጃ ሲመለከቱ



የንጉሥ ሣህለሥላሴ ባለቤት ወይዘሮ በዛብሽ የፈረንሳዩ መልእክተኛ ሮሼ ደሐሪኩ የሰጡዋቸውን ጃንጥላ ዘርግተው ከደንገጡሮቻቸው ጋር ሆነው ሲመለከቱ

(ሥዕሎቹ ኢትዮጵያ ኤንግሬቭድ ከተባለው የሪቻርድ ፓንክኸረስት መጽሐፍ የተወሰዱ)

## ፪ኛ ክፍል።

ኢየሩሳሌም በፈረንሲስ ንጉሥ ጥላ ተጠብቃለችና የሸዋ ልጆች ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ ቢፈልጉ የፈረንሲስ ንጉሥ ሹሞች በያገሩ ሁሉ እንደ ፈረንሲስ ልጆች ይጠብቁቸዋል።

## ፫ኛ ክፍል።

የሸዋ ንጉሥ የፈረንሲስን ልጆች ከሌላ አገር እንግዳ በላይ ያደርጉዋቸዋል። ለሌላውም እንግዳ ፈቃድ የስጠ እንደ ሆነ ለእኛ ከፍ ያለ ፈቃድ ይሰጠናል።

## ፬ኛ ክፍል።

የፈረንሲስ ዕቃ ለንግድ የመጣ እንደ ሆነ በሸዋ ከመቶ ሦስት ሰጥቶ እድነ ልብሀ ሸጥ ብለው ሊጠብቁት ነው።

## ፭ኛ ክፍል።

የፈረንሲስ ነጋዴዎች በሸዋ ንጉሥ አገር ሁሉ እንደ ልባቸው እንዲነግዱ ይሁን።

## ፮ኛ ክፍል።

የፈረንሲስ ሰዎች በሸዋ ቤትም ምድርም ቢገዙ እንዳይበደሉ ንጉሥ ይጠብቋቸዋል። ቢሸጡም ቢለውጡም እንደ ፈቃዳቸው ያድርጉት።

## ፯ኛ ክፍል።

የተጻፈው ሁለት ነው። አንዱ እኔ ዘንድ ቀረ። አንዱን ለፈረንሲስ ንጉሥ ላክሁት። በግንቦት ፴ ቀን የዮሐንስ ዕለት በአንጐለላ ተጻፈ። ፲፰፻፴፫ /፲፰፻፵፩/ ዓ.ም ያሮ ሮሼ ፊርማ። የሣህለ ሥላሴ የሸዋ ንጉሥ ማኅተም።

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በዚህ ውል የተዋዋሉት በዛሬ ዘመን እንደሚደረገው የመተማመንና የመረዳዳት ውል ጭምር ነው እንጂ፣ የወዳጅነትና የንግድ ውል ብቻ አልነበረም። ደግሞ የኢትዮጵያ ነገሥታት መቸም ቢሆን ለክርስቲያን ለሃይማኖታቸው ቀናተኞች ናቸውና በሁለተኛው ክፍል ስለ ኢየሩሳሌም መንገደኞች የጻፉት ቃል ለኋላ ትውልድ እጅግ የሚጠቅም ስለ መሆኑ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴንም ከልብና ልናመሰግናቸው ይገባልና።

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ለጊዜው ለሸዋ ለኋላውም ለሙሉ ኢትዮጵያ ጥቅም የሚሆን ሥራ ለመሥራት በማሰባቸው በፊትም በውጭ አገር ነጋዴዎችና የወንጌል መላክተኞች

በከተማቸው እንዲኖሩ አድርገው ነበር። በኋላም የእንግሊዝ ንግሥት የቪክቶሪያ መልክተኛና ቀጥሎም የፈረንሳዊ ንጉሥ የትልቁ ሉዊ ፊሊፕ መላክተኛ እንዲመጡ ፈቀዱ። ከመጡም በኋላ በአንኮበርና በደብረ ብርሃን በአንጐለላም ከተሞቻቸው የጋላውን /የኦሮሞውን/ አገር ሲሄዱ እያስከተሏቸው ይሄዱ ነበር። ሠፈርም በሆነ ጊዜ እነዚህ የውጭ አገር ሰዎች እንደ ሀገራቸው ልማድ የማደኛ ጠመንጃቸውን እየያዙ ወደ ዱር እየገቡ ቆቅና ዳክዬ ዝይም እነዚህንም የመሳሰሉትን የባሕር አሞሮች ሁሉ እየገደሉ በግልጥ በሕዝቡ ፊት ይበሉ ነበርና በዚህ ዘመን የነበረች ግጥም አዋቂ ሴት እንደዚህ ብላ ገጠመችባቸው።

ኧረ አይገባም ነበር በነጋሢ ፊት

ኧረ አይገባም ነበር በወይዘሮ ፊት

የሚበላ ሰው ቁራና ጭልፊት

ምታተኛ ነው ጥበበኛ ነው ብለው ይሉታል።

ይህ ሲሰነብት ጥሉም ያቅታል።

የርስዎ ጋሻ አይድፈርም

እንዲህ ያለ ወዳጅ ለልጅ አይሆንም።

የሚበላ ሰው ቁራና ጭልፊት ማለቷ ግን በወሬ ሰምታ ነው እንጂ፣ ባይኗ አይታ አይደለምና ቁራና ጭልፊት መብላታቸው እርግጥ ነው ለማለት አይቻልም።

# ምዕራፍ ፲፫

## ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ቅብዓ መንግሥት ተቀብተው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለመሆን ስለ ማሰባቸው

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከላይ የንግሥተ ሳባና የቀዳማዊ ምኒልክ ከታችም የአጼ ልብነ ድንግልና የአቤቶ ያዕቆብ ዘር መሆናቸውን ስለ አወቁ አሳባችው ቅብዓ መንግሥት ተቀብተው ንጉሠ ነገሥት ለመባል ነበር እንጂ፣ የሸዋ ንጉሥ ብቻ ተብለው ለመቅረት አልነበረም።

ይህንንም የሚያስረዳ ነገር ከዚያ ዘመን አስቀድሞ የጳጳሳት መኖሪያ በጐንደርና በትግሬ /በትግራይ/ ስለ ነበረ ጳጳስ ለማግኘት ችግር ሆኖባቸው ነበር።

በመካከሉም ትግሬንና /ትግራይንና/ ሰሜንን አንድ አድርገው ሲገዙ የነበሩት ደጃዝማች ውቤ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለመሆን አስበው ወደ እስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ተላልከው አቡነ ሰላማን ማስመጣታቸው ተሰማና የሸዋ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴና የቤጌምድሩ መስፍን ራስ አሊም ባንድነት ገጥመው ከሌላ አገር ጳጳስ ለማስመጣት መላላክ ጀምረው ነበር።

ከሌላ አገርም ጳጳስ ለማስመጣት መላላክ የጀመሩት ምክንያቱ ከሸዋ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴና ከቤጌምድሩ መስፍን ከራስ አሊ በፊት የነበሩት ራስ ጉግሣ በዘመናቸው ከነበሩት ከእጨጌ ወልደዮና ጋር በሦስት ልደት ሃይማኖት ስለ ገጠሙ ወልደ ቅብዕ በሉ እያሉ የገዙትትን አቡነ ቄርሎስን ከጐንደር አስወጥተው ወደ ትግሬ /ትግራይ/ ሰደዋቸው ነበርና የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት በዚህ ነገር መቀየሙ አይቀርምና ጳጳስ አይልክልንም በማለት ፈርተው ይመስላል።

ነገር ግን በማናቸውም ቢሆን ከሌላ አገር ጳጳስ ለማስመጣት ያሰቡት አሳብ ስላልተፈጸመላቸው ቅብዓ መንግሥት ተቀብተው ንጉሠ ነገሥት ለመባል ያሰቡት አሳብ ሳይፈጸምላቸው ቀረ።

ከዚህም በኋላ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በደግነትና በጥበብ እየተመሰገኑ ሸዋን ፴፩ ዓመት ገዝተው በጥቅምት ፲፪ ቀን ፲፰፻፴፯ ዓ.ም በደብረ ብርሃን አረፉና በአንኮበር እርሳቸው በሰሩት በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ። በዚሁም ቀን ባለ ቅኔ እንደዚህ ብሎ ተቀኘ፡-

ደብረ ሚካኤል ብክይ በላዕለ አንብዕኪ ደመ።

ሣህለ ሥላሴ ተስፋኪ እስመ ተፈጸመ።

ወኃልቀ ለዝሉፉ ወይትመየጥ ዳግመ።

ወልበ ግፉዓን አስተሐመመ።

ፈታሒ በጽድቅ ልሳኑ አምጣነ በሞት ተኀትመ።

ከመ ሕልመ ሌሊት ሞትከ ይመስለኒ ንጉሠ መግቦ ዓለመ።

ሣህለ ሥላሴ ልብከ ሐላዊ ደብረ ሊባኖስ ዳግመ።

በደዌ ኃይልከ እምድኅረ ደከም።

እንዘ ትብልሂ አሐውር እምጌሠም ጌሠመ።

ከመ ዓውሎ ሞትከ ቀደመ።

በደጋም በቆላም ያለው የሸዋ ሰው ሁሉ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴን ሞት በሰማ ጊዜ እንደ አባትና እንደ ወንድም ያህል አለቀሰላቸው ይባላል።

# ምዕራፍ ፲፪

## ስለ አቤቶ ኃይለ መለኮት

የሸዋ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከቆላ ባላባቶች ከኮራ ወልዱና ከሞረት ጥዱ ወገን የሚወለዱ ወይዘሮ በዛብሽን አግብተው በ፲፰፻፳ ዓ.ም አቤቶ ኃይለ መለኮትንና አቤቶ ሰይፉን ወይዘሮ በለጥሻቸውን ወለዱ።

ከዚህም በኋላ በ፲፰፻ወ፫ ዓ.ም ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ደብረ ብርሃን ላይ ባረፉ ጊዜ አቤቶ ኃይለ መለኮት «የሞትንም እኛ ያለንም እኛ ነንና አይዞህ ባለህ እርጋ!» የሚል አዋጅ አስነግረው ባባታቸው አልጋ ተቀምጠው ንጉሠ ሸዋ ተባሉ።

ወዲያውም ያባታቸውን ሬሳ ከደብረ ብርሃን አንኮበር ወስደው በነጋሪት በመለከት አስለቅሰው በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አስቀበርዋቸው።

ንጉሥ ኃይለ መለኮት ሰውነታቸው ግዙፍ ጠንካራና ኃይለኛም ነበር። ይህንም የሚያስረዳ ነገር ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

፩ኛ ዒላማ ለመተኮስ ጠመንጃ አምጡ ብለው በእጃቸው ይዘው አነጣጥረው ቢተኩሱት የዚያን ጊዜው ጠመንጃ በባሩድና በጨርቅ እየተደቀደቀ የሚተኮስ ባለ ከምሱር ስለ ነበር ባሩዱ ከልክ አልፎ ተሞልቶ ኑሮ ከባሩዱ ኃይል የተነሳ ጠመንጃው ከሁለት ተጐርዶ ግማሹ በቀኝ እጃቸው ደግሞ ግማሹ በግራ እጃቸው ላይ ቀረ።

፪ኛ ሥጋ የሚበሉበትን ቢላዋ ለጨዋታ ብለው ቢጠመዝዙት እንደ ብር ሽቦ ተጠቀለለ ይባላል።

፫ኛ በዚያን ዘመን ፊጋ በሬ ሲታረድ በጐሽ ጠፍር እየተጠለፈ ነበርና ፊጋውን በሬ ቀንዱን ሲጠልፉት አይተው የጠፍሩን ጫፍ ስጡኝ ብለው ቢስቡት ከበሬውና ከርሳቸው ኃይል የተነሣ ጠፍሩ ተበጥሶ ግማሹ በእጃቸው ላይ ግማሹ በበሬው ቀንድ ላይ ቀረ።

ደግሞ ልበ ቅንና ርኅሩኅ ነበሩ። ይህንንም የሚያስረዳ ነገር ከእርሳቸው አስቀድሞ የነበሩ ባላባቶች ይልቁንም ኃይለ ሥላሴ ስለ አልጋቸው እየፈሩ ወንድሞቻቸውን እየያዙን እያሰሩ በየእስላሙ ቤት ያስቀምጧቸው ነበር።

ንጉሥ ኃይለ መለኮት ግን መኳንንቶቻቸው ቀርበው ወንድሞችዎ አቤቶ ሰይፉና አቤቶ ዳርጌ አያስገዙዎትምና እየያዙ ይሠሩዋቸው ብለው ብመከሩዋቸው እግዚአብሔርን ከመፍራታቸውና ከርኅሩኅነታቸው የተነሣ «ወንድሞቼን አሥሬ ከማን ጋር ደስ ሊለኝ ነው? ማናቸውም ነገር ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አይሆንምና እግዚአብሔር ሰጥቶኝ እንደ ሆነ እገዛለሁ ለነርሱም ሰጥቷቸው እንደ ሆነ ይግዙ እንጂ ምንም ቢሆን ወንድሞቼን አላስርም።» ብለው በፍቅርና በመማማት ያኖሩዋቸው ጀመር።

ከዚህም በኋላ የደጋው ጋላ /ኦሮሞ/ ሁሉ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ስለ ሞቱና ንጉሥ ኃይለ መለኮት ኃይል የሌላቸው ስለ መሰለው ሁሉም ሸፍቶ ነበርና እየተከታተሉና እየተዋጉ ድል አድረጉት። እስከ አሩሲም ድረስ ዘምተው ነበር።

ከሁሉም የሚያስደንቀው ነገር የጐንደር ነገሥታት አጼ ይባላሉ ሲሉ ቢሰሙ ሳይቀቡና ዘውድ ሳይችኑ እንዲያው አጼ አጼ ኃይለ መለኮት በሉኝ ብለው አጼ ኃይለ መለኮት መባላቸው ነው።

አሳባቸው ሸዋን ብቻ ለመግዛት አልነበረም ወደ ቤጌምድር ገዥ ወደ ራስ አሊ እየተላላኩ ወዳጅነት ጀምረው ነበር።

በኋላም ቋረኛው አጼ ቴዎድሮስ ስለ ተነሱ ራስ አሊ አጼ ቴዎድሮስን በመፍራት ወደ የጁና ወደ ጐጃም እየተዘዋወሩ ቆይተው ነበርና ደራ ላይ ሲደርሱ የደራ ባላባት ዋቄ ዲቦ ይዞ አሠራቸው። ንጉሥ ኃይለ መለኮትም የራስ አሊን መታሠር በሰሙ ጊዜ ስለ ወዳጅነታቸው ወደ ደራ ዘምተው ከዋቄ ዲቦ ጋራ ተዋግተውና ድል አድርገው እርሱን አሥረው ራስ አሊን ፈትተው በታላቅ ደስታ ወደ አንኮበር ተመለሱ።

በኋላ ግን ወደ ሀገሬ እንድመለስ አሳብ አለኝና ሸኝተው ይስደዱኝ ብለው ቢለምኗቸው የሚሸሹ ብዙ ወታደሮችና ስንቅ ጨምረው ሰጥተው ሰደዷቸው።

ከዚህም በኋላ ንጉሥ ኃይለ መለኮት በነገሡ በስምንተኛው ዓመት አጼ ቴዎድሮስ ከአምባ ጫራ ተነስተው ወሎን እየወጉ ወደ ሸዋ ሊመጡ ነው የማለት ወሬ ስለ ተሰማ ንጉሥ ኃይለ መለኮት ከወሎ ገዥ ከወይዘሮ ወርቂት ጋራ ለመመካከር የሸዋን ሰው ሁሉ ካህኑ ሳይቀር ስብሰባው ወንድሞቻቸውን አቶ ሰይፉንና አቶ ዳርጌን አስከትለው ወደ ወሎ ዘመቱ። ሣኮ ላይም ሠፍረው ሳሉ ወይዘሮ ወርቂት መጥታ ነበርና አጼ ቴዎድሮስ ሲመጡ እርስዋ ከወደ ኋላ ንጉሥ ኃይለ መለኮት ግንባር ለግንባር ገጥመው እንዲዋጓቸው ተመካከረው ተለያዩ።



# ንጉሥ ኃይለ መለኮት

አጼ ቴዎድሮሶም እየገፉ መጥተው ነበርና አቶ ሰይፉ አንድ ሰላይ ወደ አጼ ቴዎድሮስ ልከው ኑሮ ያያታቸው የወይዘሮ ዘነበ ወርቅና የባለ አደራው ያቶ በድሉ መላከተኞች ወደ አጼ ቴዎድሮስ ገብተው ሲወጡ አይቶ ተመልሶ በነገራቸው ጊዜ ምሥጢራቸው እንደ ተገለጠባቸው አወቁ። አጼ ቴዎድሮሶም ከነ አቶ በድሉ እንደተላከባቸው ወደ ኋላቸው አፈግፍገው አያታ በሚባል አገር ላይ ብርቱ ምሽግ የሆነ በር ይዘው ተቀመጡ።

ንጉሥ ኃይለ መለኮትም በወሎ ጦርነት ከማድረግ በሀገሬ በሸዋ ላይ ሆኜ ብዋጋ ይሻለኛል ብለው አጼ ቴዎድሮስን ወደ ኋላቸው ትተው ወደ ሸዋ ተመለሱ።

አጼ ቴዎድሮስም ወይዘሮ ወርቂትን ብቻዋን ስለ አገኙዋት ድል አድርገው ክርምቱንም በመቅደላ ከረሙ። ከከረምትም በኋላ ወደ ሸዋ በመጡ ጊዜ ከሸዋ መኳንንት ብዙዎቹ ገቡላቸው። ይልቁንም ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ጀምሮ ከብሮ የሚኖረው የኤፍራታው ገዢ አቶ በድሉና አያታቸው ወይዘሮ ዘነበ ወርቅ እየረዱን መንገድ እምጥተዋቸው ቁንዲ ላይ ሲደርሱ ጳጳሱን አቡነ ሰላማን ከጓዝ ጋራ ትተው ወደ ደብረ ብርሃን ገሰገሱ።

ንጉሥ ኃይለ መለኮትም ከወሎ እንደ ተመለሱ ታመው ነበርና በሽታቸው እንደጸናባቸው ስላወቁ ወንድሞቼን ሰይፉንና ዳርጌን ጥሩልኝ ብለው ወደ ቆላ መላከተኞች ቢልኩ በዚያ ወራት በደብረ ብርሃንና በቆላው አገር መካከል ያለው ያብቼ ጋላ /ኦሮሞ/ የኃይለ መለኮትን መታመምና የአጼ ቴዎድሮስንም መምጣት ስለ ሰማ ሸፍቶ ነበርና አቤቶ ሰይፉ በሽፍታው ጋላ /ኦሮሞ/ አገር አቋርጠው ለመሄድ የማይቻላቸው ቢሆን አንተ ተራ ሰው መስለህ አድን አሽከር ብቻ አስከትለህ ወንድማችንን ጠይቀኸው ተመለስ ብለው አቤቶ ዳርጌን እርሳቸው ቀሩ።

አቤቶ ዳርጌም ብቻቸውን በደረሱ ጊዜ «ወንድሜ ሰይፉም ከዳኝን?» ብለው በኀዘን ቃል ቢጠይቋቸው «የጋላውን /ኦሮሞውን/ አገር አቋርጦ ለመምጣት የማይቻል ስለ ሆነበት ነው እንጂ፣ የመክዳት አሳብ የለበትም» በማለት የልባቸውን ኀዘን አበረዱላቸው።

ከዚህም በኋላ የንጉሥ ኃይለ መለኮት ሠራዊት በደብረ ብርሃን አጠገብ አታክልት በሚባል ሥፍራ ተሰልፎ ነበረና ከአጼ ቴዎድሮስ ሠራዊት ጋራ ጦርነት ተጋጥመው ሲዋጉ ውለው ድሉ ላንዳቸው ሳይሆን ጊዜው ስለ መሸ ተለያይተው አደሩ።

ነገር ግን ንጉሥ ኃይለ መለኮት በብርቱ ታመው ነበርና ጦርነቱ በተደረገበት ሌሊት ማረፋቸው ስለ ተሰማ መኳንንቶቻቸው ሬሳቸውን ይዘው ሌሊቱን ሲሄዱ አድረው ደብረ በግዕ ላይ ቀበሩዋቸው።

ዘመነ መንግሥታቸው ስምንት ዓመት ነው። ያረፉትም በጥቅምት ፴ ቀን በሺ፰፻፵፯ ዓመተ ምሕረት ነው።

ንጉሥ ኃይለ መለኮትም ካረፉና ከተቀበሩ በኋላ የሸዋ መኳንንት ባንድነት ሆነው የንጉሡ ልጅ አቤቶ ምኒልክ ገና ሕፃን ስለ ሆኑ «እርስዎ ከኛ ጋራ ሆነው በጦርነቱም በሌላው ነገር እየረዱን የንጉሡን ልጅ እናሳድግ ለአቤቶ ዳርጌ ቢነግሩዋቸው «እኔ አባቴ ሣህለ ሥላሴ ያዘዙኝ ከወንድሜ ከሰይፉ ጋር እንድኖር ስለሆነ ያባቴን ቃል አፍርሼ ከወንድሜ ከሰይፉ ተለይቼ ከናንተ ጋር ለመኖር አይቻለኝም» ብለው በፈረሳቸው ጋልበው ወደ አቤቶ ሰይፉ ተመለሱ።

በዚያ ጊዜ የሸዋ መኳንንት አቤቶ ዳርጌ ከእናንተ ጋር አልኖርም ማለታቸው አቤቶ ሰይፉ እንዲነግሡ አስበው የኃይለ መለኮትን ሞት ለመንገር መሄዳቸው ነው ብለው አምተዋቸው ነበር ይባላል። ነገር ግን ያባታቸውን የሣህለ ሥላሴን ቃል ለመጠበቅ ይሁን ወይም ለአቤቶ ሰይፉ አድልተው ይሁን የዚህን ነገር የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እስከ ሥሩ ጠልቆ ለሚመረምረው ሰው ግን የአቤቶ ምኒልክ የኋለኛው ዕድላቸው ነው ለማለት ይቻላል።

# ምዕራፍ ፲፯

## ስለ አቤቶ ምኒልክ

የሸዋ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ወይዘሮ በዛብሽን አግብተው አቤቶ ኃይለ መለኮትንና አቤቶ ሰይፉን ከወለዱ በኋላ ሁለቱም ባባታቸው ቤት ባንድነት ያድጉ ነበር። ለወይዘሮ በዛብሽም ወይዘሮ እጅግአየሁ የሚባሉ ደንገጡር ነበሩዋቸው ይህም እንደ ዛሬው እንደ አውሮጳ ልማድ ዳም ደ ኦነር /የክብር እመቤት የምትባለዋ ነች። ወይዘሮ እጅግአየሁም በወይዘሮ በዛብሽ እልፍኝ ሲኖሩ ወዲያው እንደ ሞግዚትም ሆነው አቤቶ ኃይለ መለኮትንና አቤቶ ሰይፉን ይጠብቁ ነበረና አቤቶ ኃይለ መለኮት የጐልማሳነት ፈቃድ ስለ አሸነፋቸው ከወይዘሮ እጅግአየሁ ጋራ ተገናኝተው አቤቶ ምኒልክ ተፀነሱ።

ከዚህም በኋላ የተሠራ ሳይነገር የሞተ ሳይቀበር አይቀርምና ወይዘሮ እጅግአየሁ መፀነሳቸውን ወይዘሮ በዛብሽ በሰሙ ጊዜ በፊታቸው አቅርበው በብዙ ምርመራ መረመርዋቸው።

አንደኛው ምርመራ ይህ ፅንስ ምናልባት ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ እንደ ሆነ ብለው ባላቸውን በመጠርጠራቸው ነበር።

ሁለተኛው ምርመራ ፅንሱ ከአቤቶ ኃይለ መለኮትና ከአቤቶ ሰይፉ ከማናቸው መሆኑን ለይተው ለማወቅ ነበር።

ወይዘሮ እጅግአየሁ ግን ከአቤቶ ኃይለ መለኮት መሆኑን አስረድተው ስለነገሩዋቸው እየፈሩና እየተጠንቀጠጡ ገብተው ለንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ስለታውቋቸው። መፍራታቸውን መንቀጥቀጣቸው «በወግ በማዕርግ ሚስት አግብቶ እንዲወልድ ሳትጠብቂው ለምን ቀረሽ? ብለው ይቆጡኛል» በማለት ነበር።

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ግን በደስታ እግዚአብሔርን አመሰገኑ እንጂ በአናቲቱ ወይም በልጃቸው በአቤቶ ኃይለ መለኮት ላይ ምንም የቁጣ ቃል አልተናገሩም። ዘጠኝ ወርም

ከሆነ በኋላ «ወንድ ልጅ ተወለደ!» ብለው ለንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ቢነግሩዋቸው «ስሙን ምኒልክ ብየዋለሁ!» ብለው ተናገሩና በ፹ኛው ቀን በአንጐለላ በኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ክርስትና ተነስተው በሞግዚት እንዲያድጉ ጠምቄ ወደ ሚባል አገር ወሰድዋቸው።

# ምዕራፍ ፲፰

## ስለ አጼ ቴዎድሮስና ስለ አቤቶ ምኒልክ

አቤቶ ምኒልክ በተወለዱ በአሥር ዓመታቸው በጥቅምት ወር በ፲፰፻፵፰ ዓ.ም አጼ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ በመጡ ጊዜ አባታቸው ንጉሥ ኃይለ መለኮት በደብረ ብርሃን አጠገብ አታክልት በሚባል አገር ስለ ሞቱ «ያለንም እኛ! የሞትንም እኛ ነንና ባለህ እርጋ!» የሚል አዋጅ አስነግረው በአባታቸው በኃይለ መለኮት አልጋ ተቀመጡ። አጼ ቴዎድሮስ ግን የንጉሥ ኃይለ መለኮትን ማረፍ ገና አልሰሙም ነበርና በግስጋሴ ሲከታተሉ በመንገድ ላይ አርፈዋል ብለው ስለ ነገርዋችው ወደ ፊት እየገፉ ሲሄዱ ጋላው /ኦሮሞው/ የኃይለ መለኮትን ማረፍ ሰምቶ ኑሮ ከወደ ግንባር መጥጦ ከኃይለ መለኮት መኳንንት ጋር ጦርነት ገጥሞ ሲዋጋ በመነጽር ያዩ ነበር። የመኳንንቱንም አርበኝነት በፈረስ ሆነው ጦር አወራወራቸውን በማየት እጅግ አደነቁ። በመጨረሻውም «እኔ ቴዎድሮስ ለጋላ /ለኦሮሞ/ እርዳታ አልመጣሁም!» ብለው ድንኳን አስተክለው በመነጽር እያዩ ዝም ብለው ተቀመጡ።

መኳንንቱም ጌታችው ቢሞቱ ጋላ /ኦሮሞ/ አሸነፉችው ተብሎ እንዳይሳቅባቸው በርትተው ስለ ተዋጉ ጋላውን /ኦሮሞውን/ ድል አደረጉት።

አጼ ቴዎድሮስም አቶ በድሉን ጠርተው «ንጉሡ ሞተዋል ብለኸኝ አልነበረም? ጌታቸው ከሞቱ እነዚህ መኳንንቱ እንደ እሳት ነበልባል፣ እንደ አራስ ነብር፣ ላም እንዳየ አንበሳ ሆነው እንደ ምን ለመዋጋት ይችሉ ነበር?» ብለው ቢጠይቁት መቃብራቸው በደብረ በግዕ ነውና ላሳይ ብሎ ስለ ተናገረ እንደ ገና ወደ ደብረ በግዕ ሄደው መቃብሩን አስቆፍረው አይተው ሞታቸውን በእርግጥ ካወቁት በኋላ ወደ አንኮበር ተመለሱ።



ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ንጉሠነገሥት ዘኢትዮጵያ

የሸዋ መኳንንት ግን አቤቶ ምኒልክን ይዘው ወደ ምንጃር የሄዱ መስለው አረርቲ ሲደርሱ ወደ በረከት ወረዱ።

በዚያንም ጊዜ ከአቤቶ ምኒልክ ጋር የነበሩ የንጉሥ ኃይለ መለኮት መኳንንቶች ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

አቶ አንዳርጋቸው ከነልጆቹ

አቶ ሽሹ

አቶ በሀብቱ

ያቶ በሀብቱ ልጅ አባ ኢሬ

አቶ በዛብህ

አቶ አባ ውርጂ

አቶ አቦዬ

አቶ አንተን ይስጠኝ

ያንተን ይስጠኝ ልጅ ከተማ

አቶ ወልደ ገብርኤል

አቶ ገርማሚ

አቶ ወልደ ጻድቅ

አቶ ናደው

አቶ አባይይነህ

ሌሎችም ብዙ ነበሩ።

አጼ ቴዎድሮስም አንኮበር ሆነው ራስ እንግዳን የጦር አበጋዝ አድርገው አቤቶ ምኒልክን ለማስያዝ ሠራዊታቸውን ሰደው በኅዳር ፲ ቀን በብረከት ላይ ከአቤቶ ምኒልክ መኳንንት ጋር ጦርነት ገጥመው ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰዎች አለቁ። አቶ በዛብህም ቆስሎ ተማረከ። በዚያንም ጊዜ በመኳንንቱ እንደዚህ ተብሎ ተገጠመባቸው።

ቁርጡኡን አወቁና አለመኖርህን

በረከት አገቡት ጌታዬ ልጅህን

ከጦርነቱም በኋላ የሸዋ መኳንንት የጌታቸውን ልጅ ይዘው ወደ ምንጃር ተመለሱ። ስለሆነም የአጼ ቴዎድሮስን ሠራዊት ብዛት የጦርነቱንም ብርታት አይተው ነበርና እኩለ

ጌታችንን አቤቶ ምኒልክን ይዘን ወደ ጋላ /ኦሮሞ/ አገር እንሽሽ ብለው መከሩ። እኩሉ ግን ይህን ሕፃን ንጉሥ በጋላ /በኦሮሞ/ አገር ከማንከራተትና አጼ ቴዎድሮስ ተከታትለው ከሚወስዱብን በፈቃዳችን ብንሰጣቸው ይሻላል ብለው መከሩ። እኩሉ ግን ምንም ሕፃን ቢሆኑ የንጉሥ ልጅ ናቸውና አሳባቸውን እንጠይቃቸው ብለው «ወደ ጋላ /ኦሮሞ/ አገር ከመሄድና ወደ አጼ ቴዎድሮስ ከመግባት ማናቸውን ይመርጣሉ?» ብለው ቢጠይቋቸው «ወደ ጋላ /ኦሮሞ/ አገር ይዛችሁኝ ብትሸሹ ይሻለኛል» ብለው ተናገሩ።

በዚህ መካከል አጼ ቴዎድሮስ አንኮበር ላይ ሆነው «አባት ያለህ ያባትህን እሰጥሃለሁና አባትህን መርቅ። አባት የሌለህ ግን አባትህ እኔ ነኝና ደጅ ጥናኝ» የሚል አዋጅ ስለ ነገሩ ብዙ ሰዎች ያባታቸውን አገርና ሹመት እናገኛለን እየመሰላቸው መግባታቸው ተሰማ። አቶ አንዳርጋቸውም ወደ አቤቶ ምኒልክ ቀርበ «ይኸው እንደዚህ የመሰለ አዋጅ ተነገረ። ንጉሡም ቃል ኪዳናቸውን የማያፈርሱ ቆራቢ ናቸው አቡነ ሰላማም ደግ ጳጳስ ናቸው ይባላልና የአባትዎን አልጋ አይነሱዎትም። ያባትዎን አልጋ ካገኙ ሌላ የሚፈልጉት ነገር የለም።» እያለ ለአቤቶ ምኒልክና ለመኳንንቱም ካስረዳ በኋላ ወደ አጼ ቴዎድሮስ ይዘዋቸው ገቡ።

አጼ ቴዎድሮስም በደስታና በክብር ተቀበሏቸው። ነገር ግን የበረከት ጦርነት በተደረገበት ቀን ባንድ ወገን አምልጠው የሄዱት የሸዋ መኳንንት ደከሞም ታሞም ቁንዲ ላይ የቀረውን የአጼ ቴዎድሮስን ሠራዊት ፈጅተውት ነበርና ወደ አንኮበርም ገስግሰው መጥተው ነጥቀው ይወስዱብኛል በማለት ስለ ፈሩ በአቤቶ ምኒልክና በመኳንንቱም ሠንሠለት አግብተውባቸው አደሩ።

አቤቶ ምኒልክም መከራን ሳያዩ በጌትነት ያደጉ ገና የአሥር ዓመት ልጅ ነበሩና ሠንሠለት ስለገባባቸው ደንግጠው ሌሊቱን ሁሉ ሲያለቅሱ አድረው ነበር። በማግሥቱም የማልቀሳቸውን ነገር ለአጼ ቴዎድሮስ ቢነግራዋቸው ሠንሠለቱን አውልቁለት ብለው አዘዙ።

ከዚህም በኋላ የሸዋን አልጋ ላንደኛው ለሣህለ ሥላሴ ልጅ ለመርድ አዝማች ኃይለ ሚካኤል አበጋዝነቱን ላቶ አንዳርጋቸው ሰጠው አቤቶ ምኒልክንና ጥቂቶች የሸዋ መኳንንት ይዘው በሰላሌ ተጉዘው በጃርሶ በኩል ዓባይን ተሻግረው በጐጃም ዞረው ደብረ ታቦር ገቡ።

ቢሆንም በዚያ ዘመን ፈንግል የሚባል በሽታ ተነስቶ ነበርና ከባላገሩም ከዘመተውም ሠራዊት ብዙ ሰዎች ሞቱባቸው።

አቤቶ ምኒልክንም በወግ በማዕርግ አሳድገው ልጃቸውን ድረውላቸው በደብረ ታቦርና በመቅደላ አሥር ዓመት ያህል ተቀመጡ።

# ምዕራፍ ፲፱

## አቤቶ ዳርጌ ወደ አጼ ቴዎድሮስ ስለ መሄዳቸውና ስለ መታሠራቸው

አጼ ቴዎድሮስ አቤቶ ምኒልክን ይዘው ከሸዋ ወደ ቤጌምድር ከተመለሱ በኋላ አቤቶ ሰይፉ በጋላው /በኦሮሞው/ አገር እየተዘዋወሩ ቆይተው ነበርና በሸዋ የአጼ ቴዎድሮስ እንደራሴ ሆነው የተሾሙት መርድ አዝማች ኃይሌ ስለባላንጣ ቸው አስፈለገውና አሲዘው በእግር ብረት አስረው አስቀመጧቸው።

አቤቶ ሰይፉና አቤቶ ዳርጌ ከወንድማማችነታቸው በላይ እንደ ዳዊትና እንደ ዮናታን ጽኑ የሆነ ፍቅር ነበራቸውና አቤቶ ዳርጌ በወንድማቸው መታሰር አዝነው አቤቱታቸውን ለአጼ ቴዎድሮስ ለመንገር ወደ ቤጌምድር ሄዱ።

አጼ ቴዎድሮስም በፊታቸው አቅርበው «ወደዚህ የመጣህበትን ነገር ንገረኝ» ቢሏቸው፣ «የመጣሁበት ነገር መርድ አዝማች ኃይሌ ወንድሜን ሰይፉን ይዞ አስሮታልና በባላንጣው እጅ ታስሮ እንዳይሞት ይፍቱልኝ ለማለት ነው። ወንድሜ በጃንሆይ ላይ ምንም ክፉ ሥራ እንዳይሠራ እኔ እንደ ዋስና እንደ መያዣ ሆኜ እዚህ እቀመጣለሁ» ብለው ተናገሩ።

አጼ ቴዎድሮስም ከአቤቶ ዳርጌ አፍ ይህን ነገር በሰሙ ጊዜ «ወንድምህ እንዲፈታ አደርግልሃለሁ» የሚል የተስፋ ቃል ብቻ ነግረዋቸው ተስፋው እንዲፈጸምላቸው ደጅ እየጠኑ ተቀምጠው ሳሉ ለአቤቶ ሰይፉ ወይዘሮ ገበያነሽ የሚባሉ ሚስት ነበርዋቸውና በባላቸው መታሠር እጅግ ስላዘኑ በመካከሉ ካንድ ሠራተኛ ቤት ሞረድ አስፈልገው በርጥብ ሥጋ ውስጥ አግብተው ሰደውላቸው ነበርና አቤቶ ሰይፉ ሥጋውን እየቆረጡ ሲበሉ ሞረዱን በውስጡ ስላገኙት እግር ብረቱን እየሞረዱ ቆርጠው አመለጡ።

መርድ አዝማች ኃይሌም የአቤቶ ሰይፉን መታሰር ለአጼ ቴዎድሮስ አስቀድሞ እንዳስታወቁ እግር ብረትም ሰብረው ማምለጣቸውን ለማስታወቅ መላክተኛ ልከው ነበርና አጼ ቴዎድሮስ በሰሙ ጊዜ «ለካ ዳርጌ የመጣው ሊሰልልና ሊያታልለኝ ኖርዋል!» ብለው በቁጣ ቃል አሲዘው እንዲታሠሩ አደረገ።

በኋላ ግን ነገሩን ሁሉ መርምረው አቤቶ ዳርጌ ወደ ቤጌምድር የሄዱት አቤቶ ሰይፉ ገና ሳያመልጡ መሆኑን በተረዱ ጊዜ እስራቱን ፈትተው በቁም እስር አድርገው አስቀመጡአቸው።

ነገር ግን በሌላ ሰው ክፉ ሥራ የሚሠራ ሰው ቢውል ቢያድር እንጂ፣ ብድሩን መቀበሉ አይቀርምና መርድ አዝማች ኃይሌ ጊዜ አገኘሁ ብለው ወንድማቸውን አቤቶ ሰይፉን አስረው ሲያጉላሏቸው ነበር። በኋላ ግን ሸዋን ሦስት ዓመት ገዝተው የብድር መቀበያቸው በደረሰ ጊዜ ሊሸፍቱ ነው ተብሎ ተወራባቸውና አፄ ቴዎድሮስ ወደ ወሎ አስጠርተውና አስረው በኮላሽ አምባ አስቀመጧቸው።

ለሸዋም አበጋዝነት አቶ በዛብህን ለአፈ ንጉሥነት አቶ አቦዬን ሾመው ሰደዱ።

አቤቶ ሰይፉም እግር ብረት ሰብረው ከመርድ አዝማች ኃይሌ እጅ ካመለጡ በኋላ በየጋላው /በየኦሮሞው/ አገር እየተዘዋወሩ ቆይተው ነበርና አፄ ቴዎድሮስ መርድ አዝማች ኃይሌን አስረው የሸዋን አልጋ ላቶ በዛብህ እንደ ሰጡት በሰሙ ጊዜ «የወንድሜን የኃይለ መለኮትን ልጅ ምኒልክን መልሰው ባባቱ አልጋ ያስቀምጡታል መስሎኝ ነው እንጂ፣ ለባዕድ ለበዛብህማ ከሰጡት ለምን ዝም እላለሁ» ብለው ከምንጃር እስከ ኤፍራታ ያለውን ምሥራቅ ምሥራቁን አገር እያስገበሩና እያሳበሩ አንኮበር ውስጥ በአባታቸው በሣህለ ሥላሴ አልጋ ተቀመጡ።

አቶ በዛብህና አቶ አቦዬም ከአቤቶ ሰይፉ ጋር ለመዋጋት የማይችሉ መሆናቸውን አውቀው ይድረሱልን ብለው ወደ አፄ ቴዎድሮስ መላክተኞች ሰደዱ። አንኮበር ደርሰው ከአቤቶ ሰይፉ ጋር ጦርነት ገጠሙ። የአቤቶ ሰይፉም ሠራዊት እጅግ ብዙ ነበርና ከአፄ ቴዎድሮስ ወገን ሠራዊቱ አልቀባቸው።

አቤቶ ሰይፉ ግን ከአፄ ቴዎድሮስ ተልኮ የመጣ አንድ የጦር አበጋዝ መስሏቸው ነበር እንጂ፣ አፄ ቴዎድሮስ መምጣታቸውን አላወቁም ነበርና አንድ ምርኮኛ ተይዞ የጦር አበጋዙ ማነው? ብለው ቢጠይቁት «ራሳቸው ጃንሆይ ናቸው» ብሎ ቢነግራቸው ከአንኮበር ወጥተው እየሸሹ ወደ ይፋት /ጨርጨር/ ወረዱ።

ወደ ሐረርጌም ለመድረስ አስበው ሳሉ ገዢው አሚር እንደማይቀበላቸው ስለ አወቁ ወደ መርሐቤቴ ተመለሱ። ነገር ግን የገዛ እንደራሴአቸው አቶ ክብረት ስለሸፈተባቸው እርዳታ ለመለመን ወደ ቦረናው ገዢ ወደ ዒመሮ አሊ ሔዱና የተቻለውን ያህል ረዳት ጦር ሰጥቷቸው ሜዳ ላይ ከአቶ ክብረት ጋር ገጥመው ሲዋጉ በጦር ወግቶ ገደላቸውና በዚያው በሜዳ ተቀበሩ።

በአንኮበር ጦርነት ግን አቤቶ ሰይፉ ጠንክረው ሲዋጉ አጼ ቴዎድሮስ አይተው ነበርና «እነዚህስ ሰዎች አስቀድሞ ግሼ ላይ አግኝተውኝ በነበረ ወደ ሸዋ አያስገቡኝም ኖርዋል» እያሉ ጦርነቱን በማድነቅ ሲናአሩ ነበር ይባላል።

ቢሆንም የሸዋ መኳንንት አቤቶ ሰይፉን ምክንያት አድርገው ስለ መሸፈታቸው ተናደው ነበርና አቶ በዛብህን አስጠርተው «ከመኳንንቱም ከወታደሩም ወገን የከዳ የከዳኝን እየለየህ አሳየኝ» ብለው ስለ አዘዙት «እገሌም ከድቶናል! እገሌም ወግቶናል! እያለ እየተናገረ ከመኳንንቱም ከወታደሩም ከሊቃውንቱም አምስት መቶ የሚሆኑ ሰዎች እጅግና እግራቸውን ተቆረጠ። የአቤቶ ሰይፉ ሚስት የወይዘሮ ገበያነሽ አባት አቶ ስሙ ንጉሥ ግን እንደ ተቆረጡ ወዲያውኑ ሞቱ።

ከሊቃውንቱም እነ አለቃ አሥራት እነ አለቀ ወልደ ሥላሴ እየተቀጡ ሞቱ። ሊቃውንቱ የተቀጡበት ምክንያቱ በነዚያ ዘመን በሸዋ ከነበሩት ሊቃውንቶች ብዙዎቹ በሦስቱ ልደት ሃይማኖት ከነ አቤቶ ሰይፉ ጋር አንድነት ነበራቸውና ለአቤቶ ሰይፉ ረድተዋል ተብሎ ነው።

አጼ ቴዎድሮስ ወደ በጌምድርም በሚመላለሱበት ጊዜ የአንኮበርን ቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳትና መጻሕፍት ሁሉ እየዘረፉ ይዘውት ሄዱ። እጅና እግርም ስለ መቁረጣቸው እንደዚህ ተብሎ ተገጠመባቸው።

እነ አጼ ቴዎድሮስ ምነው ተዋረዱ?

የሸዋን ሰው ሁሉ እጅ ነስተውት ሄዱ።

ከዚህም በኋላ በደብረ ታቦርና በመቅደላ እየተመላለሱ ሦስት ዓመት ያህል ቆይተው እንደራሴውን አቶ አቦዬንና የሸዋ መኳንንት ሁሉ አስጠርተዋቸው ነበርና በ፲፰፻፵፮ ዓ.ም የተሾመውም እንዳይሻር ያልተሾመውም እሾማለሁ እያለ አንድም ሳይቀር ሄደ። አቶ በዛብህ ብቻ ሸዋን ጋላ /ኦሮሞ/ እንዳያተፋው ጠብቅ ተብሎ ቀርቶ ነበር።

የሸዋም መኳንንት በደረሱ ጊዜ አጼ ቴዎድሮስ ሙሉ ግብር አግብተውላቸው ሲበሉ ሲጠጡ አዛምሪ ቆሞ እንደዚህ ብሎ ገጠመ።

ጃንሆይ /ቴዎድሮስን/ ባል ብሎ ማን አምኖ ይቀርባል?

ሴሰኛውን ጒበዝ ያራቱን ማዕዘን ባል።

በዚህም ጊዜ «ፈረሴን አቅርብ!» ብለው በፈረስ ሆነው ስለ ፎከሩ ተቀምጦ የሚበላው ቆሞሞ የሚያየው ሁሉ በፍርሃት ተንቀጠቀጠ ይባላል።

አቶ በዛብህ ግን በሸዋ የነጋሢ ዘር አለ መኖሩን አይቶ ከአብቹ ጋላ /ኦሮሞ/ ካቶ ጐበና ዳጪ ጋር ተማክሮ ከአጼ ቴዎድሮስ ለመከዳት ቁርጥ አሳብ ስለ አደረገ አብደላ አማን በሚባል አገር አጠገብ አዙ ዋሻ የሚባለውን አስጠርጐ ዕቃውን ገንዘቡን የምግቡም ዓይነት ሁሉ ከሰልና እንጨት ሳይቀር ማግባት ጀመረ።

ከዚህም በኋላ በኅዳር ወር በ፲፰፻፵፯ ዓ.ም ወልደ ትንሣይ ከሚባለው ከተማው ተነስቶ ወደ ደብረ ብርሃን ወጥቶ «የሸዋ ሰው ከቴዎድሮስ መገዛት የማድንህ ገዥህ እኔ ነኝና ባለህ እርጋ ባትገዛልኝ ግን ብርቱ ቅጣት እቀጣሀለሁ» የሚል በዛብህ አስነግሮ ነገሥ። ደብዳቤም ሲጻፍ «ዛቲ ጦማር ዘተፈነወት እምኀበ አቶ በዛብህ ንጉሠ ሸዋ» ይባል ጀመር። በቅዳሴም ጊዜ «እግርር ፀሮ፣ ወዕቀብ ንግሦ ወሠራዊቶ ለንግሥነ ወልደ ኪሮስ» እየተባለ ስሙ ይጠራ ጀመር።

ነገር ግን የሸዋ ሰው ስለ ናቀው በያውራጃው እየሸፈተ የማይገዛለት ሆነ። ጋላውም /ኦሮሞውም/ ሁሉ ከዳ።

አቶ ጐበናም አዙ ዋሻ ገብቶ አቶ በዛብህ የሰበሰበውን ገንዘብ ሁሉ ይዞ ሸፈተ።

አጼ ቴዎድሮስም ገስግሰው በመጡ ጊዜ አፍቀራ አምባው ላይ ወጥቶ ስለ ተቀመተ ለጦርነት የማይመች ሆነባቸውና የመንዝን ሰው ፈጅተው ከብቱን ዘርፈው ተመለሱ።

አቶ በዛብህም ከአፍቀራ ወርዶ አልገዛልህም ያለውን አማራውንም ጋላውንም /ኦሮሞውንም/ እየፈጀ በንጉሥነት ዘጠኝ ወር ያህል ሸዋን ገዛ።

# ምዕራፍ ፳

## አቤቶ ምኒልክ ከመቅደላ አምልጠው ወደ ሸዋ ስለ መመለሳቸው።

አቤቶ ምኒልክ የአጼ ቴዎድሮስን ልጅ አግብተው ምንም ስንኳ በክብር ቢቀመጡም አሳባቸው ወደ ሸዋ ተመልሰው በአባታቸው አልጋ ተቀምጠው ንጉሥ ለመባል ነበርና፣ በመቅደላ ሳሉ ወደ ሸዋ መኳንንት በምሥሪር መላላክ ጀመሩ። ከአቶ በዛብህም በቀር መኳንንቱ ሁሉ ባንድ ቃል ሆነው «ጌታችን የኃይለ መለኮት ልጅ ከመጡልን በደስታ እንቀበልዎታለን» እያሉ አስታወቋቸው። ከዚህም በኋላ በሰኔ ፳፬ ቀን ፲፰፻፵፯ ዓ.ም ሌሊት ከመቅደላ ተነስተው በአሊ በር ወጥተው ወደወረሂመኑ ተጓዙ።

በዚያም ሌሊት አጼ ቴዎድሮስ አቢቶ ምኒልክ ማምለጣቸውን ገና ሳይሰሙ ልባቸው ስለ ፈራ ሦስት ጊዜ ያህል እየፎከሩ ወጥተው ዘበኞቹ «ጃንሆይ ምንም የለም

ደህና ነው!» ይሏቸው ነበር። ከነጋ በኋላ ግን አቤቶ ምኒልክ ማምለጣቸው ስለ ታወቀ በመቅደላ ትልቅ ሽብር ሆነ። አጼ ቴዎድሮስም በአቤቶ ምኒልክ ማምለጥ ስለ ተናደዱ በመቅደላ ወህኒ እያሉ ያስቀመጡትን የባላባት ልጅ ሁሉ ገደል ያስጥሉት ጀመር።

አቤቶ ምኒልክ የወርሂመኑ ገዥ ወደ ነበረችው ወደ ወይዘሮ ወርቂት መላክተኞች ልከው «ከዚህም ቀድሞ ያባቴ የኃይለ መለኮት ወዳጅ ነበርሽና ያባት ወዳጅ ለልጅ ስለሆነ መጣሁ ተቀበይኝ፣ ተቀባይም ስደጅልኝ» ብለው ስለ አስታወቋት ለጊዜው ብዙ ሠራዊት ልካ ተቀበለቻቸው። ዳሩ ግን አጼ ቴዎድሮስ ልጅዋን አስረው በመቅደላ አኑረውት ነበርና አቤቶ ምኒልክን ለውጥ ሰጥታ ልጅዋን ለማስፈታት ስለ አሰበች ከነመኳንንቶቻቸው በዘበኞች አስከብባ አስቀመጠቻቸው። ወዲያውም ከሐይቅ ገዳም መነኮሳት አስጠርታ የምኒልክን እጅ ይዤ ልስጥዎትና ልጄን ይፍቱልኝ ብላችሁ ንገሩልኝ ብላ አስጠንቅቃ ላከቻቸው። ነገር ግን የእግዚአብሔርና የሰው አሳብ እንደ ሰማይና ምድር የተራራቀ ነውና የተላኩት መነኮሳት አሊ በር ሲደርሱ አጼ ቴዎድሮስ በአቤት ምኒልክ ማምለጥ ተናደውና ተቆጥተው የባላባቱን ልጅ ሁሉ ገደል ሲጥሉ የወይዘሮ ወርቂትም ልጅ ገደል ጥለውታል የሚል ወሬ ስለ ሰሙ ተመልሰው መጥተው ለወይዘሮ ወርቂት ቢነግሩዋት ብርቱ ለቅሶ ካለቀሰች በኋላ «ምኒልክን እግዚአብሔር ወደ ሀገሩ ሊያገባው ቢፈቅድ ይሆናል» በማለት የሚሸኙ ወታደሮች ሰጥታ አሰናበተችው። ወዲያውም «የሸዋ ሰው ሆይ! የጌታህ የኃይለ መለኮት ልጅ ምኒልክ መጥቶልሃልና በደስታ ተቀብለው» የሚል አዋጅ አስነገረላቸውና ወደ ሸዋ ጉዞ ጀመሩ።

# ምዕራፍ ፳፩

## ስለ አቤቶ ምኒልክና ስለ አቶ በዛብህ ጦርነት

አቶ በዛብህ አበጋዝነቱን ትቶ በሸዋ አልጋ ተቀምጦ እንደ ንጉሥ ይገዛ ነበርና ወይዘሮ ወርቂት «የሸዋ ሰው የጌታህ ልጅ ምኒልክ መጥቶልሃልና በደስታ ተቀበለው!» ብላ አዋጅ ማስነገርዋን በሰማ ጊዜ እንደ ገና ይዘሽ እሠሪልኝ ብሎ ሁለት ሺህ ብርና ብዙ ፈረሶች በቅሎዎችም ጨምሮ ሰደደላት። ነገር ግን የአቤቶ ምኒልክ ወደ ሸዋ መግባትና መንገሥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ነበርና ያቶ በዛብህ መላክተኞች ወደ ወይዘሮ ወርቂት ሳይደርሱ አቤቶ ምኒልክ በግስጋሴ የወሎን ወሰን አልፈው ወደ ግሼ ገቡ። የግሼና እያንጾኪያም ገዥዎች በደስታ ተቀበሏት በወይዘሮ ወርቂትም ትእዛዝ ለመሸኘት የመጡት ወታደሮች ወደ ወረሂመኑ አንመለስም ብለው ከአቤቶ ምኒልክ ጋር ይጓዙ

ነበርና ላቶ በዛብህ ሥጋት አልነበረባቸውም። ከግሼም በኤፍራታ አድርገው በነሐሴ ፲፫ ቀን ግድም ደረሱ።

አቶ በዛምህም አቤቶ ምኒልክ እንደ መጡና የሸዋም መኳንንት እንደ ተቀበሏቸው በሰማ ጊዜ የሸዋ ሰው የሚአብርለት መስሎት «ምኒልክ መምጣቱ በአጼ ቴዎድሮስ ፈቃድ ስለ ሆነ እኛን እያሠረ ለቴዎድሮስ እያሳለፈ እጅና እግራችንን ለማስቆረጥ ነውና የሸዋ ሰው ለራስህ ስትል በርትተህ ተዋጋ!» የሚል አዋጅ አነግሮ ወደ ጋዲሎ ተጓዘ።

በዚያም ጊዜ ጋዲሎ የሚጓዘውን ያቶ በዛብህን ሠራዊት ያየች ሴት እንዲህ ብላ ገጠመች።

«ማነው ብላችሁ ነው ጋሻው መወልወሉ?

ማነው ብላችሁ ነው ጦራችሁ መሾሉ?

ማነው ብላችሁ ነው ካራችሁ መሳሉ?

የጌታችን ልጅ ነው ኧረ በስመ አብ በሉ።»

ከዚህም በኋላ በነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፰፻፶፯ ዓ.ም ጋዲሎ ላይ ጦርነት ገጥመው ሲዋጉ ከአቶ በዛብህ ጋር የተሰለፉት የሚበዙት የኃይለ መለኮት አሽከሮች ነበሩና «በጌታችን በኃይለ መለኮት ልጅ ላይ አንተኩስም» እያሉ ጠመንጃቸውን ወደ ሰማይ ከተኮሱ በኋላ በፍጥነት እየዞሩ ከአቤቶ ምኒልክ ጋር ተቀላቀሉ። አቶ በዛብህም ሠራዊቱ እንደከዳው ባየ ጊዜ ባንድያ ፈረሱ ሸሽቶ አመለጠና አፍቀራ ገባ።

አቤቶ ምኒልክም ከጋዲሎ ተነስተው ምሥራቅ ምሥራቁን ተጉዘው ወደ አባታቸው ከተማ ወደ አንኮበር ገብተው የሸዋ ንጉሥ ተብለው ነገሡ።

አቶ በዛብህም ከአሥር ዓመት አስቀድሞ አጼ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ በመጡ ጊዜ የጌታዬን የኃይለ መለኮትን ልጅ ምኒልክን አላስማርከም ብሎ ከቀሩት ከሸዋ መኳንንት ጋራ ወደ በረከት ይዞ ሄዶ በረከት ላይ ከአጼ ቴዎድሮስ ሠራዊት ጋራ ሲዋጋ ቆስሎ ተማርኮ ነበርና አሁን እርሱ ለጌታው ልጅ ጠላት ሆኖ ጋዲሎ ላይ መዋጋቱን ያየች ሴት እንደዚህ ብላ ገጠመች።

«የበረከት ለታ ከሸንጡ ተወግቶ፣

ከሻንቅላ ጋራ አብሮ ተቆራኝቶ፣

አገር ለምኒልክ እያለ ቆይቶ፣

ሊወጋቸው ሄደ የሰው ነገር ሰምቶ።

አንተም አደረግሽኝ የመነኩሴ ፈራጅ፣

የሙት ልጅ ሲቀበል እንዲህ ነወይ ወዳጅ?»

ንጉሥ ምኒልክም በአንኮበር ጥቂት ወራት ከተቀመጡ በኋላ ወደ ደብረ ብርሃን ወደ የልቼን ከተማ እየሠሩ ተቀመጡ።

# ምዕራፍ ፳፪

## ስለ አቶ በዛብ የሞት ፍርድ

አቶ በዛብህ ከጋዲሎ ጦርነት አምልጦ አፍቀራ አምባ ገብቶ ነበርና የሸዋ መኳንንትና ሠራዊት ንጉሥ ምኒልክን በደስታ መቀበሉን አገሩም መርጋቱን አይቶ ይማሩኝ ብሎ መላከተኛውን ወደ ንጉሥ ምኒልክ ላከ። ነገር ግን ለሰው ምንም ቢሆን አንዳንድ ጠላት አይጠፋለትምና በዚያው በአፍቀራ ከእርሱ ጋር የነበረ አንድ ሰው «አቶ በዛብህ ይማሩኝ ብሎ ሲልክ ሰምቶ ይማሩኝ ማለቱ በከተማዎ ሆኖ ሠራዊትዎን እያባበለና እያሴረ የረጋውን አልጋውን ሊያፈርስ ነው እንጂ፣ ለዕርቅ ብሎ አይደለምና እንዳይዘነጉለት» ይሁን ብሎ ልኮባቸው ነበር።

ንጉሥ ምኒልክ ግን በማናቸውም ቢሆን አቶ በዛብህን እጅ ካደረጉ በኋላ የሚያደርጉበትን ያውቁ ነበርና «ስለ እግዚአብሔር ብዬ ምሬሃለሁ!» ብለው አስመጥተው በልቼ ከተማ አጠገብ በአባ ሞቴ አገር አስቀመጡት።

ስለሆነም የሸዋ መኳንንት አቶ በዛብህ ካልሞተ በሰላም ለመኖር እንዳይችሉ ተረድተውት ነበርና በዛብህ ከአፍቀራ ቢወጣም በአባ ሞቴ አገር ቢቀመጥም በንጉሥ ላይ ማሴሩንና ሰው ማባበሉን አልተወም እያሉ አይስውሩኡበት ጀመሩ።

ደግሞ አምባውን አፍቀራን አስረክብ ተብሎ ስለ ታዘዘ አስረክቡ ብሎ ወደ አሽከሮቹ ቢልክ አሽከሮቹ የጌታችንን መጨረሻ ሳናይ አናስረክብም ብለው እምቢ ብለው ነበርና እርሱ አታስረክቡ ብሎ ቢልክባቸው ነው እየተባለ ይወራ ጀመር።

በዚያም ሆነ በዚህም ሆነ ለቅናት የለውም ጽናት እንደሚባል ጐልማሳ በሚስቱ፣ ንጉሥ በመንግሥቱ የሚሰማውን ክፉ ወሬ ሐሰት ነው ለማለት አይችልምና አቶ በዛብህ ይያዝ ተብሎ በሠንሠለት ታስሮ ወደ ወህኒ ገባ። በወህኒም ታስሮ ክፉ ሕክም አይቶ ኑሮ ባጠገቡ ላለው ሰው «ዛሬ ሌሊት ክፉ ህልም አይቻለሁና ፈርቻለሁ» ብሎ ቢነግረው «አይዞዎ ምንም የለብዎ! አይፍሩ!» እያለ ያጽናናው ጀመር።

አቶ በዛብህ ግን የሰውዬውን ነገር ሰምቶ «እንደምን አይዞህ ትለኛለህ ንጉሡ ተውት ምሬዋለሁ እንዳይሉ ልጅ ናቸውና የልባቸውን የሚይሠራቸው የለም። ባጠገባቸውም ያሉት መኳንንቶች ብንለቀው ምን ያደርገናል? የማይሉ ፈሪዎች ናቸው። ስለዚህ ይገድሉኛል እንጂ ምንም ቢሆን አልተርፍም» ብሎ መለሰለት።

ከዚህም በኋላ «የጠሉት ይወርሳል የፈሩስት ይደርሳል» የሚባል ተረት አለና አቶ በዛብህ እንደ ፈራው ሊቃውንቱና መኳንንቱ ይፍረዱበት ተብሎ በችሎት አቀረቡት። በችሎትም የተነበበው የማስፈረጃው ቃል ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነበር።


«መጀመሪያ። አቶ በዛብህ የማያገባውን በአባቴ አልጋ ተቀምጦ ከመቅደላ አምልጬ ብመጣ አላስገባም ብሎ ጋዲሎ ላይ ተዋጋኝ።

ሁለተኛም። ማረኝ ብሎ ከማርሁት በኋላ በከተማዬ ተቀምጦ እያመካኘ ሳያስረክበኝ ቀረ።

ሦስተኛም። ማረኝ ብሎ ከማርሁት በኋላ በከተማዬ ተቀምጦ ያሴርብኝ ጀመር። ስለዚህ ሊቃውንቱም መኳንንቱም ፍረዱ» የሚል ነው።

መኳንንቱንና ሊቃውንቱም አቶ በዛብህ ገና ምላሽ ሳይሰጥ እየተነሱ መፍረድ ጀመሩ። እንደ ሕጉ ቢሆን በትልቁ ሰው ባቶ በዛብህ ይቅርና በማንም ተራ ሰው እንኳ ቢሆን የሞት ፍርድ ሲፈረድ ለተከሰተበት ወንጀል ሁሉ ምላሽ ከሰጠና ካስረዳ በኋላ ነበር።

መጀመሪያ። በአሽከሮቹ እያመካኘ አፍቀራን አምባውን አላስረክብም ብሏል ለተባለው ነገር እርሱ አምባውን አትልቀቁ ብሎ አሽከሮቹን ለማዘዝ አንድም ማስረጃ አልቀረበም ነበር።



## ንጉሥ ምኒልክ ከመኳንንቶቻቸው ጋር

ሁለተኛም። በከተማ ተቀምጦ ያሴራል ስለ ተባለው ነገር ጠላቶቹ የሆኑ ሰዎች በመሰከሩበት ነው እንጂ፣ እርሱ ይህን ነገር በቃሉ አላመነም ነበር። ዳሩ ግን ማሩኝ ብሎ ምሕረት አግኝቶበታል ማለት ነው እንጂ ያቶ በዛብህ ዋናው ጥፋቱ ንጉሥ ምኒልክ ከመቅደላ አምልጠው ሲመጡ አላስገባም ብሎ መዋጋቱ ብቻ ነበር።

ከዚህም በኋላ ሊቃውንቱና መኳንንቱ በየተራ እየተነሱ ይሙት በቃ እያሉ ሲፈርዱ ከመኳንንቱ መካከል አንዱ አቶ ሠራዊቱ የሚባለው ተነስቶ የቆመበትን መሬት በእግሩ እየረገጠ «አንተ ያልሞትህ ማን ይሞት ኖርዋል?» ትሞታለህ ብሎ ፈርዶ ሲቀመጥ አቶ በዛብህ ሰውዬው በጦርነት ላይ ፈሪ ነው እየተባለ መጠርጠሩን ያውቅ ነበርና ዓይኑን ወደ አቶ ሠራዊት ቀና አድርጎ «እኔ ስሞት የአማራ የጋላ /የኦሮሞ/ የእስላም ጀግኖች ተጨምረው ፈርደው እሞታለሁ እንጂ እንደ አንተ ያለው ፈሪ ብቻ ፈርዶ እሞታለሁን? አንተ የመግደያው ጦር ማመሙንና አለማመሙን ወዴት ታውቀዋለሁ?» እያለ ሳቀበት።

ግራዝማች ባዩ የሚባለው ብቻ «አቶ በዛብህ እንደ እኔ አድርጎ ያጠቃውና ያዋረደው የለም፣ ቢሆንም በዛብህን የመሰለ ጀግና ለክፉ ቀን የሚሆን ነውና ይሙት በቃ ብዬ አልፈርድም» ብሎ ተናገረ።

ነገር ግን ከእግዚአብሔርና ከንጉሥ ቁጣ የሚያመልጥ የለምና እንደ ፍርዱ ቃል ግደሉት ተብሎ ታዘዘና ወደ መግደያው ሥፍራ ወስደው በጠመንጃ ገደሉት።

ከሁሉም ይልቅ የሚያሳዝነው በዚያ ዘመን የነበረው ጠመንጃ በባሩድና በጨርቅ እየተደቀደቀ በከምሱር የሚተኮስ ነበርና ከባሩዱ ኃይልና ብዛት የተነሳ የለበሰው ልብስ ተያይዞ ስለ ነደደ ሥጋውና አጥንቱ መቃጠሉ ነው። ትራፊውንም ባለ ወጒች አንስተው ወደ ደብረ ብርሃን ወስደው ቀበሩት። በዚያንም ጊዜ አንዲት አልቃሽ እንዲህ ብላ ገጠመች።

አንተም ጨካኝ ነበርህ ጨካኝ አዘዘብህ፣

እንደ ገና ዳቦ እሳት ነደደብህ።

ጋላም /ኦሮሞም/ አርፈህ ተኛ አውልቀህ ዳባህን፣

አማራውም ተንፍስ አራግፍ ኮርቻህን፣

በሳት አቃጠሉት የሚያባንንህን።

# ምዕራፍ ፳፫

## ስለ አጼ ቴዎድሮስ ዕረፍት

ከዚህም በኋላ አጼ ቴዎድሮስ ከእርሳቸው ጋራ ያለውን የእንግሊዝን መንግሥት ቆንሲልና ሌሎችንም የውጭ አገር ሰዎች እያሠሩ በመቅደላ ስለ አስቀመጧቸው፣ በ፲፰፻፷ ዓ.ም በሎርድ ናፒየር አበጋዝነት ከእንግሊዝ ንግሥት ከቪክቶሪያ የታዘዙ የሕንድ ወታደሮች ወደ ኢትዮጵያ መጡ። ከኤርትራም ባሕር ጠረፍ ጀምሮ ምንም ችግር እንዳያገኛቸው የዋጉ ደጃዝማች ጐበዜና የትግራይ /የትግራዩ/ ደጃዝማች ካሣ መሪና ረዳት ዕይሰጡ እስከ መቅደላ አደረሷቸው።

አጼ ቴዎድሮስም በዚሁ ዓመት በሚያዝያ ፯ ቀን መቅደላ ላይ ከእንግሊዝ ወታደሮች ጋራ ጦርነት ገጥመው ሲዋጉ ከመኳንንቶቻቸውና ከወታደሮቻቸው ብዙዎቹ እየከዱ በያገራቸው መሄዳቸውን ባዩ ጊዜ የታጠቅ ጌታ በነዚህ በነጮች እጅ ከመያዝና ከመማረክ ሞት ይሻለኛል ብለው፤ በገዛ እጃቸው ሽጉጣቸውን መጥተው ሞቱ። ስለዚህም እንዲህ ተብሎ ተገጠመላቸው።

አንበሳው መቅደላ ወድቆ አገኘሁት፣

ሰው እያየው መሸሽ ነውር ሆኖበት።

መቅደላ አፋፉ ላይ ጩኸት በረከተ፣

የሴቱን አናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ።

ከድሉም በኋላ የእግሊዝ ጦር አበጋዝ ሎርድ ናፒየር የጦር መሣሪያውንና መንግሥቱንም ይቀበሉኝ ብሎ ለደጃዝማች ጐበዜ ቢልክባቸው የላስታንና የዋግን ባላባቶች ሰብስበው «እንደዚህ ተብሎ ተላከብኝ ምን ማድረግ ይሻላል?» ብለው ምክር ቢጠይቋቸው «ምናልባት እጅዎን ይዞ የወሰደው እንደ ሆነ ኋላ ፀፀት ይሆናልና አይሂዱ ይቅሩ እግዚአብሔር ሰጥቶዎ እንደ ሆነ ይገዛሉ ባይሰጥዎትም ይቀራል ብለው ስለ መከሩዋቸው ሳሄዱ ቀሩ።

ሎርድ ናፒየርም ሁለት ሳምንት ያህል ከጠበቀ በኋላ ምላሽ ሳያገኝ ስለ ቀረ ጉዞውን ጀመረና ሰንዓፌ ሲደርስ የትግሬው /የትግራዩ/ ደጃዝማች ካሣ ብዙ መስተንግዶ አስደግሰው በታላቅ ደስታና ክብር ተቀበሉት። እርሱም አራት መቶ ያህል ጠመጃና ሦስት መድፎች ሰጥቷቸው ሄደ።

ከዚህም በኋላ ንጉሥ ምኒልክ በሸዋ፤ ደጃዝማች ጐበዜ በአማራው አገር፣ ደጃዝማች ካሣ በትግሬ /በትግራይ/ ሆነው እነዚህ ሦስቱ ትልልቅ ጌቶች የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ለማግኘት መሸቀዳደም ጀምረው ነበርና የአማራው ገዥ ደጃዝማች ጐበዜ ኃይልና ዕድል አግኝተው በ፲፰፻፷፩ ዓ.ም ጳጳስ ስለሌለ በእጨጌ እጅ ተቀብለው አጼ ተክለ ጊዮርጊስ ተብለው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆኑ። እርሳቸውም ሦስት ዓመት ያህል እንደ ነገሡ የትግሬው /የትግራዩ/ ደጃዝማች ካሣ ከእንግሊዞች በተቀበሉት የጦር መሣሪያ ኃይል አግኝተው ነበርና በአድዋ አጠገብ ከአጼ ተክለ ጊዮርጊስ ጋር ተዋግተው ድል አድርገው ከያዙዋቸው በኋላ በ፲፰፻፷፬ ዓ.ም ዮሐንስ ተብለው በአቡነ አትናቴዎስ እጅ ቅብዓ መንግሥት ተቀብተው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆኑ።



የደጃዝማች ካሣ ምርጫ (በኋላ አፄ ዮሐንስ ፬ኛ የሆኑት) መልእክተኞች አፄ ቴዎድሮስን ለመውጋት የመጣውን የእንግሊዝ ጦር በአዲግራት እንደተቀበሉት



የደጃዝማች ካሣ ምርጫ (በኋላ አፄ ዮሐንስ ፬ኛ) መልክተኛ መርሻ ወርቄ ከእንግሊዝ የጦር አዛዦች ጋር ሆኖ



የእንግሊዝ ጦር ወደ መቅደላ ለመገስገስ በዝግጅት ላይ እንዳለ

(ኢትዮጵያ ኤንግሬቭድ ከተባለው ከሪቻርድ ፓንክኸረስት መፍሐፍ የተወሰደ)

# ምዕራፍ ፳፬

## ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ የሸዋን መንግሥት አደላድለው ስለ መያዛቸው

መርዕድ አዝማች ኃይለ ሚካኤል ከአፄ ቴዎድሮስ ሲከዱ አፄ ቴዎድሮስ አሲዘው በመርሐቤቴ አምባ በኮላሽ አግብተው ጐንደሬ የሚባለውን የቁር ጦር በደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ውስጥ አድርገው ያስጠብቋቸው ነበርና ንጉሥ ምኒልክ በግንቦት ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ.ም ከልቼ ወርደው የመርሐቤቴን አምባ ኮላሽን ከበው ሰለ ያዙት በውስጡ ያለው ጐንደሬ የሚባለው ጭፍራ እስረኛውን መርድ አዝማች ኃይሌንና መድፉንም ሌላውንም የጦር መሣሪያ አውጥቶ ለንጉሥ ምኒልክ አስረከበ። ንጉሥ ምኒልክም ወደ ልቼ ተመልሰው ጥቂት ቀን ከቆዩ በኋላ ላጐታቸው ለመርድ አዝማች ኃይሌ የቡልጋን ግዛት ሰጧቸው።

ከዚህም በኋላ በሚያዝያ ፯ ቀን ፲፰፻፷፫ ዓ.ም አጼ ቴዎድሮስ ማረፋቸው ስለ ተሰማ ንጉሥ ምኒልክ ወደ ዘመተው ቀድሞ ከመቅደላ በወጡ ጊዜ የተቀበለቻቸውን ወይዘሮ ወርቂትን ከወረሂመኑ መለስዋት። ወይዘሮ መስታወት ግን ለንጉሥ ምኒልክ አልገዛም ብላ ነበርና እርሷን ድል አድርገው አምባውን መስቀላን እጅ አድረጉባት። የቅሩትንም የወሎ ባላባቶች ካስገበሩ በኋላ የወረይሉን ከተማ ቆርቁረው ወደ ሸዋ ተመለሱ።

እንደዚህም ወደ ወረይሉና ወደ ሸዋ እየተመላለሱ ቆይተው ሳሉ ለይማሙ አባ ዋጠው ወሎን ጠቅለው ሰጥተው ወደ ቤጌምድር ለመጓዝ አሰቡና መንገድ ሲጀምሩ አባ ዋጠው ከወደ ኋላ ከዳቸው።

ከሸዋም ፊታውራሪ ናደው የግሼን ጦር ሁለት ሰብስቦ ከአባ ዋጠው ጋር ይጓዝ ነበርና አባ ዋጠው እርሱን አሥሮ ሠራዊቱን ሁሉ ዘረፈው። ንጉሥ ምኒልክም ይህን ወሬ ሰምተው ከፊተኛው እሥራቱ ሰዎቹ ምክር በመፍታታቸው አዘኑ። ይፈታም ብለው የመከሩ መኳንንቶች አፈሩ።

በዚህም ምክንያት ወደ ቤጌምድር መዝመታቸውን ትተው ወደ ወረይሉ ተመለሱ። አንደኛውም የወሎ ባላባት መሐመድ አሊ ገባላቸውና በክብር ተቀበሉት። ወይዘሮ ባፈናን ልጅ ወይዘሮ ማናለብሽን ዳሩለት። ያልተጠመቀ እስላም የተጠመቀችይቱን ክርስቲያን ማግባር ያልተለመደ ነበርና ለጊዜው ሕዝቡ ሁሉ በጣም ገረመው።

አባ ዋጠውም ፈርቶ መቅደላ አምባ ገባ። ንጉሥ ምኒልክም ተከታትለው ስለደረሱበት በመቅደላ እግር ብርቱ ጦርነት ተደረገና ከኊልቱም ወገን ብዙ ሰዎች ሞቱ። ይልቁንም ግራዝማች ባቡ የሚባል በሸዋ አንድ ተብሎ የሚቆጠር ጀግና በውጊያው ሞቶ ነበርና በንጉሥ ሚኒልክ ሠፈር ተልቅ ኀዘን ሆኖ ነበር።

የትግሬው /የትግራዩ/ ደጃዝማች ካሣም በሐምሌ ፬ ቀን ፲፰፻፷፬ ዓ.ም ከአጼ ተክለ ጊዮርጊስ ጋር ተዋግተው ድል ስለ አደረጉ ዮሐንስ ተብለው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆነው ነበርና የቤጌምድሩ ገዥ ራስ ወልደ ማርያም ወደ ንጉሥ ምኒልክ መግባቱን ስለ ሰሙ ከትግሬ ተነስተው በሰሜን አድርገው ወደ ቤጌምድር ገቡ። ከዚያም ወደ ጐጃም ተሻግረው ራስ አዳልን አባረው ራስ ደስታ ተድላን ሾመው ወደ ቤጌምድር ተመልሰው ሳሉ ራስ አዳል ራስ ደስታን ገድለው ቤጌምድር ላይ ለአጼ ዮሐንስ ታጥቀው ገቡላቸው።

አጼ ዮሐንስም ወደ ሸዋ ለመምጣት ዘቢጥ ሲደርሱ አባ ዋጠው ከመቅደላ ወርዶ ታጥቆ ገባላቸው። ዳሩ ግን ከወደ ኋላ የቱርክ ጦር መታ የማይባል ወሬ ሰለ ተሰማ በየጁ አድርገው ወደ ትግሬ /ትግራይ/ ስለ ተመለሱ ለንጉሥ ምኒልክ ትልቅ ደስታ ሆነ። ከዚያም በኋላ የአጼ ዮሐንስና የንጉሥ ምኒልክ ብድር መመላለስ ተጀመረ።

ራስ ወልደ ማርያም ከአፄ ዮሐንስ ከድቶ ወደ ንጉሥ ምኒልክ ስለ ገባ አጼ ዮሐንስ ራስ አዳልን አዘው አስገደሉት።

ይማሙ አባ ዋጠውም ከንጉሥ ምኒልክ ከድቶ ወደ አጼ ዮሐንስ ስለ ገባ ንጉሥ ምኒልክ የጁ ቃሲም ላይ ደረሱበትና እጁን አሲዘው በእነዋሪ እንዲታሰር ወደ ሸዋ ሰደዱት። በየጁም ባላባቱን ደጃዝማች ወሌን ሾመው ወደ ወረይሉ ተመልሰው ክረምቱን በወረይሉ ከርመው ነበርና በመስከረም ለመስቀል በዓል ትልቅ ሰልፍ አድርገው የወሎን ሰው ግብር በማብላት ሽልማት በመስጠት ደስ አሰኝተውት ዋሉ። በዚሁም ቀን መሸሻ ሰይፉ ከድቶ ወደ ሸዋ መጥቶ በደጃዝማች ጐበና ቤት ገብቶ ነበርና ደጃዝማች ጐበና ተላልከው አስታረቁት።

ከዚህም በኋላ ወደ ሸዋ ተመልሰው በጥቅምት ፳፩ ፲፰፻፷፱ ዓ.ም ወደ ቸሀ ዘምተው ነበርና ከዘመቻው ተመልሰው እነዋሪ ሲደርሱ አቤቶ መሸሻ ሰይፉን እንደታሰረ ወደ ጐንች ሰደዱት።

ከጥቂት ወራት በኋላ ወደ በጌምድር ሊዘምቱ አስበው ነበርና «የሸዋን እንደራሴነት ለደጃዝማች ገርማሚ ሰጥቻለሁና ገብሬ እረስ! ነጋዴም ነግድ!» የሚል አዋጅ ተነገረው በዚሁ ዓመት በጥር ወር ወደ ወረይሉ ተጓዙ። በወረይሉም ሳሉ የጐጃሙ ራስ አዳል ወደ በጌምድር ተሻግረው ነጋሽ ወሬኛን ድል አድርገው ነፍጡን ወሰዱበት የሚል ወሬ ስለ ሰሙ በፍጥነት ተነስተው በግስጋሴ ደብረ ታቦር ገቡ።

ደጃዝማች ወሌም ከጌታው ጋራ ለመገናኘት ከየጁ ወደ ደብረ ታቦር ሲገሰግስ ዘመዶቹ የሆኑ ሰባት ደጃዝማች ከድተዋል የሚል ወሬ ቢሰማ እንደገና ተመልሶ የጁ ላይ ጦርነት ገጠማቸው። እንደ አንድ ወታደር ሆኖ ጠጣው በሚባል ፈረሱ ተቀምጦ ሲወጋና ሲያዋጋም ውሎ ነበርና የገደላቸውን ገድሎ የተረፉትን ማረካቸው። በዚያም ጊዜ አዝማሪ እንደዚኢህ ብሎ ገጠመለት ።

ሰባት ደጃዝማች አስር ፊታውራሪ የጠቀመውን፣

የወሌ ፈረስ ጠጣው ብቻውን።

ንጉሥ ምኒልክም በደብረ ታቦር ሳሉ አጼ ዮሐንስ በግሥጋሴ መምታታቸውን በሰሙ ጊዜ ከብዙ ፈረስ በቀር እንደ አጼ ዮሐንስ ብዙ ነፍጥ እንደሌላቸው ያውቃሉና በጌምድርን ለቀው ወደ ጐጃም ለመሻገር ጉዞ ጀመሩ።

ራስ አዳልም ንጉሥ ምኒልክ ወደ ጐጃም ለመሻገር መጀመራቸውን ሰምተው በዓባይ ዳር እግር በር በሚባለው ሥፍራ ሠራዊታችወን አሰልፈው ይጠባበቁ ነበር። ነገር ግን የንጉሥ ምኒልክን ሠራዊት ብዛት ሰላይ አይቶ ነግሮዋቸው ነበርና እግር በርን

ትተው ወደ ዳሞት ስለ ተመለሱ ንጉሥ ምኒልክ ዓባይን ተሻግረው ሞጣ ላይ ሠፈሩ። ባላገሩም ከንጉሥ ምኒልክ ጋራ ለመዋጋትና መንገድ ለመከልከል አስቦ ነበርና አንዲት ሴት እንደዚህ ብላ ገጠመች።

ሞጣ ላይ ተከለ ሸዌ ድንኳኑን።

ተራዳ ጐጃሜ ትችል እንደሆን።

ራስ አዳልም አገራቸው ነውና በቆላና በደጋ ዳሞት እየተውዘዋወሩ ስለ ተቀመጡ ንጉሥ ምኒልክ ለጦርነት የማይመች መሆኑን አውቀው ጐጃምን ትተው በሊበን ወርደው ዓባይን ተሻግረው ወደ ሸዋ ተመለሱ።

# ምዕራፍ ፳፫

## ስለ ወይዘሮ ባፈና መከዳት

የወይዘሮ ባፈና ትውልዳቸው በመርሐቤቴ ቆላ ከረመሽት ባላባት ከበርበሬ ወገን ነው። ከንጉሥ ምኒልክ አቀድሞ ሦስት ባሎች ፈትተዋል። ከነዚሁም ከፊተኞች ባሎቻቸው ሦስት ወንዶችና ሁለት ሴቶች ልጆች ነበሯቸው። የወንዶቹ ልጆች ስም አመንሸዋ፣ ኃይሌና ግዛው፣ የሴቶቹ ልጆቻችውም ማናለብሽና እርመጃቸው ይባል ነበር። የወይዘሮ ባፈና ዕድሜ ከንጉሥ ምኒልክ በብዙ ይበልጥ ነበር። ቢሆንም በንጉሥ ምኒልክ ዘንድ እጅግ የተከበሩና የተወደዱ በመሆናቸው ሰው ሁሉ ይፈራቸው ነበር።

ንጉሥ ምኒልክ ወደ በጌምድር ዘምተው በዚያው ወደ ጐጃም በተሻገሩ ጊዜ ወይዘሮ ባፈናም አብረው ዘምተው ነበር። ነገር ግን የቀድሞ ዘመን ወይዛዝርትና መኳንንት ፈንታጣ መከተብ እየፈሩ ባገር ውስጥ የፈንጣጣ በሽታ ገባ ሲባል ከሰው እየተለዩ ለብቻቸው ይቀመጡ ነበርና ንጉሥ ምኒልክ ጐጃም በደረሱ ጊዜ በሠፈራቸው የፈንጣጣ በሽታ ስለ ገባ ወይዘሮ ባፈና እንደ ልማዱ ሠፈራቸውን ለይተው ለብቻቸው ይጓዙ ጀመር። በኋላ ግን ወደ ሸዋ ቢመለሱ ይሻላል ተብሎ ተመከረና ወደ ሸዋ ተመለሱ።

ወደ ሸዋም ሲመለሱ ንጉሥ ምኒልክን ለመዳት ከአማቻቸው ከይማሙ መሐመድ አሊ ጋራ ተማምለው ነበርና ለሥራቸው ሁሉ እንዲመቻቸው ወደ ሸዋም በገባሁ ጊዜ ሹሞችዎ ይህን ስጡኝ ይህን አድርጉልኝ ስላቸው እምቢ እያሉ እንዳያስቸግሩ ደረቅ ማህተም ይስጡኝ እያሉ በማታለል ለመኗቸው። ደረቅ ማኅተም ማለትም ቃሉ ሳይጻፍ ማህተሙ ብቻ እየታተመ በእምነት የሚሰጥ ነው። ንጉሥ ምኒልክም በወይዘሮ ባፈናና

በይማሙ መሐመድ አሊ መካከል የተደረገውን ስምምነትና መሀላ አያውቁም ነበርና ሳይጠረጥሩ እያተሙ ሰጧቸው።

በዚያንም ዘመን በንጉሥ ምኒልክ ላይ ብዙ ጠላቶች ስለ ተነሱባቸው በየሥፍራው ከጂው በዝቶ ነበር። የወሎ ጋላ /ኦሮሞ/ እየወጣ ግድምንና ኤፍራታን ይወጋ ጀመር። ደግሞ ከሁሉ የባሰና የከፋ ነገር መርድ አዝማች ኃይሌ ሸፍተው አንኮበርን ይዘው ነበርና አዛዥ ወልደ ጻድቅ ከእርሳቸው ጋር ያለውን ወታደር ይዘው ጐረቤላ ከዳሳው ላይ ጦርነት ቢገጥሙአቸው አዛዥ ወልደ ጻድቅ ድል ሆነው እየሸሹ ፍቅሬ ግምቡ ገቡ። ሰልፍ ለማስተማር ተቀጥሮ የነበረው ፖቲ የሚባለውም ፈረንሳዊ ሰልፍ ያስተማራቸውን ሙቶ ወታደሮች ይዞ ከአዛዥ ወልደ ጻድቅ ጋራ ተሰልፎ ነበርና እርሱም በዚያው በጦርነቱ ውስጥ ሞተ።

እንደራሴው ደጃዝማች ገማሚና አፈ ንጉሥ በዳኔ ግን ወደ እንጦጦ ወርደው ነበርና ከእጦጦ ተመልሰው በድሉ ለት ልቼ ገቡ። በዚሁም ቀን ንጉሡ ከጐጃም በደህና መመለሳቸውን ወይዘሮ ባፈናም ቀድመው መምጣታቸውን የሚያወሩ መላክተኞች ልቼ ገብረው ነበር።

መርድ አዝማች ኃይሌም ድል ካደረጉ በኋላ አንኮበር ገብተው ሹም ሽር ሲያደርጉ እነ ደጃዝማች ገርማሚና የንጉሡ መላክተኞች ልቼ መግባታቸውን ሰሙና ምክራቸው ሁሉ ፈረሰባቸው።

ከዚህም በኋላ ከአንኮበር ተነስተው ወደ ጋላ /ኦሮሞ/ ለመግባት ሚጣቅ ሲደርሱ ደጃዝማች ገርማሚ አፈ ንጉሥ በዳኔና፣ አቶ አንተን ይስጠኝን፣ አቶ ቸርነትንና አቶ ይገዙን፣ አቶ ድልነሣሁን ረዳቶች አድርገው በሚያዝያ ፳፯ ቀን ከልቼ በግሥጋሴ ሄደው ሚጣቅ አፋፍ ላይ ጦረንት ገጠሟቸው። በጦርነቱም ውስጥ አፈ ንጉሥ በዳኔ ፎከረው ቀርበው በጦር ከጭናቸው ላይ ጠቆም አድርገው ያዙዋቸውና ድሉ ለነደጃዝማች ገርማሚ ሆነ።

ከዚህም በኋላ ደጃዝማ ገርማሚ አቤቶ መሸሻ ሰይፉን ከጉንች አውጥተው ከመርድ አዝማች ኃይሌ ጋራ በእነዋሪ አስረው አስቀመጧቸው። ምክንያቱም ሁለቱም የንጉሥ ምኒልክን አልጋ ፈላጊዎች ስለ መሆናቸው ነበር።

ወይዘሮ ባፈናም እነዋሪ ገብተው ነበርና ስለ ድሉ ነገር ካንገት በላይ ትልቅ ደስታ አደረጉ። በኋላ ግን ከአማታቸው ከይማሙ መሐመድ አሊ ጋራ የተማከሩበትንና የተማማሉበትን ነገር ለማድረግ ወደ አጼ ዮሐንስ መላላክ ጀምረው ነበርና ከእነዋሪ ወደ

ልቼ ወጥተው የንጉሡን ባሩዱና ከባሕር ማዶ ያስመጡትን ማለፊያ ዕቃ ብሩንና ሌላውንም ዕቃ ሁሉ ዘርፈው ወደ እነዋሪ ተመለሱ።

ከጥቂትም ቀን በኋላ አቤቶ መሸሻ ሰይፉንና ይማሙ አባ ዋጠውን ደጃዝማች ዘገየንም ከእስራታቸው ፈትተው ከእነዋሪ ወደ ታሞ ተጓዙ።

መሸሻ ሰይፉን ያስከተሉበት ምክንያት ባንድ ወገን መርሐቤቴ የአቤቶ ሰይፉ ግዛት ስለ ነበረ የመርሐቤቴ ሰው ለጌታው ለአቤቶ ሰይፉ ልጅ ሲል እንዲቀበላቸውና እንዲረዳቸው ነው። በሁለተኛውም ወገን የንጉሥ ምኒልክ ባላንጣ ንጉሥ ምኒልክ ከመሸሻ ሰይፉ ጋራ ሲዋጉ ወደ ይማሙ መሐመድ አሊ መዝመታቸው እንዲቀር ብለው ነው። ይማሙ አባ ዋጠውን ወደ ታሞ መውሰዳቸው አባ ዋጠው ለይማሙ መሐመድ አሊ ባላንጣ ነውና ምናልባት ንጉሥ ምኒልክ ከጐጃም ሲመለሱ ወደ ወሎ እንዳይሰዱትና መሐመድ አሊን እንዳይወጋ ሰለ ፈሩ ነው።

ወደ ታሞም ለመሄድ ገረን በሚባለው አገር ሲደርሱ ባላገሩ ተሰብስቦ ወይዘሮ ባፈና ከንጉሥ ምኒልክ ከድተው መጥተዋልና እንዳያምልጡህ እያለ ለፈፈና የያዙትን ዕቃና ገንዘብ ዘረፈባቸው። እርሳቸው ግን በጭንቀት አመልጡ። አቤቶ መሸሻም ባንድ ሥፍራ ተደብቆ ነበርና አንድ ባላገር አግኝቶ »አንተ ማነህ?» ቢለው «መሸሻ ሰይፉ ነኝ!» ብሎ ስለ ተናገረ «አንተስ የጌታዬ ልጅ ነህ» ብሎ ሸኝቶ ሰደደውና ከወይዘሮ ባፈና ጋር ተቀላቅሎ ወደ ታሞ ገባ። ከጥቂት ወራትም በኋላ ወይዘሮ ባፈና ይማሙ አባ ዋጠውንና ደጃዝማች ዘገየን አስረው አቤቶ መሸሻ ሰይፉን የኮላሽን አምባ ይዘህ ተጠባበቅ በለው ሰደዱት።

ንጉሥ ምኒልክም በሰኔ ወር ከጐጃም ተመልሰው ስላሴ ሲደርሱ ነገሩን ሁሉ አላወቁም ነበርና ይማሙ መሐመድ አሊን አሰናብተው ወደ ሀገሩ ሰደዱት። እርሱ ግን ከወይዘሮ ባፈና ጋራ የመከዳት ምክሩን ለማጽናት ሲል በመርሐቤቴ በኩል ወደ ታሞ ወጥቶ ከወይዘሮ ባፈና ጋራ ተነጋግሮ ባህያ ፈጅ በኩል ወረይሉ ገባ።



## ንጉሥ ምኒልክ

ንጉሥ ምኒልክም እነዋሪ በገቡ ጊዜ በወይዘሮ ባፈና ሥራ ሁሉ እጅግ አዘኑ። በኋላ ግን አስታራቂዎች ልከው መሸሻ ሰይፉን እጁን ይዘው ከሰጡ እርሳቸውን በቂም ላይገድሏቸውና ላይጣሏቸው ስለተዋዋሉ ተቀባይ ይምጣ ተባለና መርሸሻ ሰይፉን የሚቀበሉ አቲከም መንገሻ ከጐንደሬ ጦር ጋራ ፮፻ ነፍጠኛ ከባሻ ተንጐዳኳጅ ጋራ ደጃዝማች ወልዴ፥ አቶ ሀብተ ሥላሴ አፈ ንጉሥ በዳኔ ተልከው ወደ ታሞ ወረዱ።

ወይዘሮ ባፈናም መሸሻ ሰይፉን ከኮላሽ አስጠርተው ባጠገባቸው አኑረውት ነበርና አኳኋናችውን ባየው ጊዜ ስለ ፈራ በዚያ ያሉትን ወታደሮች በምስጢር አድርጐ ምክር

ቢጠይቋቸው «ወይዘሮ ባፈና በፊት ከጌታችን አስከዱት አሁን ደግሞ አንተንማ የሚይዙህ ከሆነ እኛንስ እየያዙ መታረቂያ ሊያደርጉን አይደለምን? ከእንግዲህ ወዲህ ምንም ቢሆን ለሴት አንገዛምና እርሳቸውን ይዘን ማሠር ይሻለናል፣» በማለት ምክራቸውን ስለ ቀረጡ ወይዘሮ ባፈና የቁም እስር ሆኑ። መሸሻ ሰይፉም በታሞ የተገኙትን ወታደሮች ይዞ ሊወስዱት ከመጡት መኳንንቶች ጋራ ጦርነት ቢገጥም ባንድ አፍታ ድል አደረጋቸው። ባሻ ተንጐዳጓጅና ሌሎችም ብዙ ሰዎች በጦርነቱ ውስጥ ሞቱ። የተቀሩትም እንደ ትቢያ ተበተኑ። ከዚህም በኋላ አምባውን ታሞን አጠንክሮ ያዘ። ይማሙ አባ ዋጠውንና ደጃዝማች ዘገየንም እየፈታ ለቀቀቻቸው።

ንጉሥ ምኒልክም የመሸሻ ሰይፉን መበርታትና የወይዘሮ ባፈናን መታሰር በሰሙ ጊዜ ከአምባው እየወጣ አገር እንዳያጠፋና ሠራዊት እንዳያበዛ ታቹን በቆላው በቆፍና በኩል አጐታቸውን ልዑል ደጃዝማች ዳርጌን ላዩን በዶባ በኩል ያክስታቸውን የልዕልት ተናኘ ወርቅን ባል ደጃዝማች ወልደ ሚካኤልን አስቀምጠው ያስጠብቁ ጀመር። የወይዘሮ ባፈና ልጆች ግን ንጉሥ ምኒልክን ይወዱ ነበርና ከመሸሻ ሰይፉ እየከዱ ወጡ።

ይማሙ መሐመድ አሊም ከወይዘሮ ባፈና ጋራ እንደ ተማከረው ምክር በወረይሉ ያለውን የንጉሡንና የመኳንንቱን ገንዘብ ሁሉ ዘርፎ ከተማ ጠባቂዎቹን ፈጅቶ ለማዳ አንበሶች ሳይቀሩ ገድሎ ከተማውን አቃጥሎ ወደ ቤቱ ሄደ።

ንጉሥ ምኒልክም ይህን ወሬ በሰሙ ጊዜ በግስጋሴ ተነስተው እየተከታተሉ የውል ላይ ደረሰበት።

እርሱም የነገሩን አኳኋን አይቶ ፊት ለፊት ጦርነት ለመጋጠም የማይችል መሆኑን ስለ አወቀ ባንደኛው ፈረሱ ሸሽቶ አመለጠ። ንግሱስ ግን ስለ ተናደደ ከተማውን ደሴን አቃጠሉት።

ከዚያም ተመልሰው በወረይሉ ከተማ ሳሉ የእናታቸውን የወይዘሮ እጅግአየሁን ሞት ተረዱና በኀዘን ሰነእብቱ። መዋዕለ ኀዘናቸውም ሲፈጸም መሐመድ አሊ ያቃጠለውን የወረይሉን ከተማ እንደ ገና ሠርተውና አድሰው ደጃዝማች ወልዴን ጠባቂ አድርገው ወደ ልቼ ከተማ ተመለሱ።

አጼ ዮሐንስም ደብረ ታቦር ላይ ነበሩና ከሸዋ በሦስት ወገን መላክተኛ ይመጣላቸው ነበር።

በአንደኛው ወገን። አቤቶ መሸሻ ሰይፉ እርስዎ ከመጡ ከሸዋ ሰው የሚበዛው የእኔ ወገን ነውና ለንጉሡ ምኒልክ ምንም የሚያሰጋዎ ነገር የለም እያለ የደጃዝማች ገማሚን ልጅ አቶ ሰሙ ንጉሥን ልኮ ነበር።

በ፪ኛው ወገን የሁለት ልደት ሃይማኖት ወገኖች እስርዎ መጥተው የማርቆስን ሃይማኖት ቢያቀኑልን ነው እንጂ ንጉሥ ምኒልክማ ባንድ ወገን አባ ማስያስ የሚባል ጳጳስ በአዳል አገር በኩል አስመጥተዋል። በሁለተኛውም ወገን ከሦስት ልደቶች ጋራ ተፋቅረዋል እያሉ ይልኩባቸው ነበር።

በ፫ኛው ወገን ከወይዘሮ ባፈናና ከመርድ አዝማች ኃይሌ ጋር የመከሩ ሰዎች ጃንሆይ በቶሎ ካልደረሱልን ንጉሥ ምኒልክ ያጠፉናል እያሉ ይልኩባቸው ነበርና፤ አጼ ዮሐንስ ወደ ሸዋ ለመምጣት ቁርጥ ሀሳብ ማድረጋቸው የታወቀ ሆነ። በዚያን ጊዜ ጠላት መጥቶ አክሱምን ከቧታል ብለው ቢነግርዋቸው ስንኳ ወደ ትግሬ /ትግራይ/ ለመመለስ አያስቡም ነበር ይባላል።

ንጉሥ ምኒልክ አጼ ዮሐንስ ወደ ሸዋ ለመምጣት ቁርጥ ሀሳብ ማድረጋቸውን በሰሙ ጊዜ በጥቅምት ወር ፲፰፻፸ ዓ.ም ወደ ወሎ ተሻግረው ጅሩ ላይ ሠፈሩ። መሐመድ አሊም ሸሽቶ ወደ አጼ ዮሐንስ ገባ። ይማሙ አባ ዋጠው ግን ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ታርቆ ስለ ገባ የወሎን ግዛት መልሰው ሾሙት። ወደ ወሎ የተሻገሩበት ግን መሐመድ አሊን ለማባረር አባ ዋጠውን ለመሾም አልነበረምና ጅሩ ላይ ሆነው ወደ አጼ ዮሐንስ መኳንንቶች በምስጢር እየተላላኩ የአጼ ዮሐንስን አሳብ ሁሉ እርግጡን አገኙት።

የመሸሻ ሰይፉም መላከተኛ አቶ ስሙ ንጉሥ አጼ ዮሐንስ ባቋራጭ መንገድ በሳይንት አድርገው ወደ ሸዋ እንዲመጡ ይመክር ነበር። ነገር ግን ንጉሥ ምኒልክ የላኩባቸው የአጼ ዮሐንስ መኳንንት በበሽሎ በረሀ በንዳድ የምናልቀው ስለምን ነው። ከላዩ በየጁ ዞረን እህልና ሣር ሳንቸገር ብንሄድ ይሻለናል ብለው ስለመከሩ አጼ ዮሐንስ ወደ ጨጨሆ አመሩ።

ንጉሥ ምኒልክም የአጼ ዮሐንስን መንገድ አረዛዘም አይተው በኀዳር ወር መጨረሻ ከጅሩ ተነስተው ወደ መርሐቤቴ ወርደው መሸሻ ሰይፉ ያለበትን ታሞን ከበው ይዋጉ ጀመር። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው አለቀ። ንጉሥ ምኒልክም የታሞን አምባ ጽናት የመሸሻ ሰይፉን ብርታት አይተው እዚህ ከመሸሻ ሰይፉ ጋር ስዋጋ አጼ ዮሐንስ መጥተው አገሬን ያጠፉታልና ዕርቅ ማድረግ ይሻለኛል ብለው የደብረ ሊባኖስ የጀር የአቡነ ዜና ማርቆስ ገዳማት መነኮሳት ገብተው የዕርቁን ነገር እንዲጠይቁት አደረጉ።

መነኮሳቱም ወደ መሸሻ ሰይፉ ገብተው አፄ ዮሐንስን ያህል ጠላት መጣ ሊባል እናንተ እርስ በእርሳችሁ ለምን ትጣላላችሁ? ያባትህን አገር ሸዋን የትግሬ /የትግራይ/ ሰው ከሚያጠፋው ወንድምህ ንጉሥ ምኒልክ ቢበድሉህ ይሻላል ብለው ቢመክሩት እጄን ላይዙኝ የማሉልኝ እንደሆነ ታርቄ እገባለሁ አላቸው።

ከዚህም በኋላ ከኮራ ታቦት ማርያምን አምጥተው በሥጋና በደሙ አማምለው መሸሻ ሰይፉን ወይዘሮ ባፌናንም አስታረቋቸውና ሁሉም ወደ ልቼ ገቡ። ወዲያውም መሸሻ ሰይፉን ዛሬ አዲስ አበባ በተባለው በጉለሌ ደጃዝማች ብለው ሾሙትና እርሱም ከተማውን የካ ላይ አደረገ።

# ምዕራፍ ፳፮

## አጼ ዮሐንስ ወደ ሸዋ ስለ መምጣታቸው

አጼ ዮሐንስ ከአጼ ተክለ ጊዮርጊስ ጋራ ተዋግተው ድል አድርገው ለጊዜው የያዙት ከበሽሎ ወዲያ ያለውን አገር ነበረና ንጉሥ ምኒልክ በጉልበት ወደ ቤጌምድርና ወደ ጐጃም በመዝመታቸው ምክንያት በሁለቱ ነገሥታት መካከል ጠብ ስለ ተጀመረ አጼ ዮሐንስ ባባቱ አገር በየጁ የተሾመውን ወሌን ለማባበል ድሲሉ «ከጨጨሆ በላይ ያለውን አገር እሰጥሃለሁና ከንጉሥ ምኒልክ ከድተህ ወደኔ ና» እያሉ ይልኩበት ጀመሩ። ደጃዝማች ወሌም ወራቱ ክራምት ሰለ ሆነ ወደ ሸዋ ለመገስገስ የማይመች ቢሆንበትም እምቢም እሺም ሳይል ወዝ እየሰጠ ከርሞ ክረምቱ ሲያልፍ የየጁን ባላባቶች ሁሉ ሰብስቦ ወደ ሸዋ መጣ።

ከዚህም በኋላ በአጼ ዮሐንስና በንጉሥ ምኒልክ መካከል ያለው ጠብ እየተገለጠና እየሰፋ ይሄድ ጀመር። የዚህም ወሬ በያውራጃው ሁሉ በተሰማ ጊዜ ላገራቸው የሚያስቡ አንዳንድ መነኮሳት የክርስቲያን ደም ለምን በከንቱ ይፈሳል? በማለት ወደ አጼ ዮሐንስና ወደ ንጉሥ ምኒኢልክ እየተመላለሱ የእርቁን ድርድር ከደረደሩ በኋላ የእርቅኡን ነገር የሚጨርሱ ከአጺኤ ዮሐንስ ወገን በጅሮን ለውጤ ከንጉሥ ምኒልክም ወገን ፊታውራሪ ናደው ተመረጡ።

የእርቁም ድርድር አጼ ዮሐንስ ከበሽሎ ወዲህ ያለውን አገር በጭራሽ ለንጉሥ ምኒልክ እንዲለቁ ነበርና «ከበሽሎ ወዲህ ያለውን ነገር እሺ እለቃለሁ። ነገር ግን ለማናቸውም ቢሆን ተገናኝተን ቃል በቃል ካልተነጋገርን ዕርቁ አይጸናምና ይህንኑ ንገሩት» ብለው በጅሮንድ ለውጤንና ፊታውራሪ ናደውን መልሰው ሰደዷቸው። ቢሆንም ንጉሥ ምኒልክ ለመገናኘት አይመጡም በማለት ይጠራጠሩ ነበርና እነ በእጅሮንድ ለውጤን ከሰደዱ በኋላ በየካቲት ወር በ፲፻፸፪ ዓ.ም ተከታትለው መጥተው መንዝ ደረሱ።



# አፄ ዮሐንስ ፬ኛ ንጉሠነገሥት ዘኢትዮጵያ

(ኢትዮጵያ ኤንግሬቭድ ፎቶግራፍድ)

አመጣጣቸውም ራስ አዳልንና መሐመድ አሊን ፊታውራሪ፣ ቤጌምድርንና ሰሜንን ላስታንና የሁን ወቦ /ደጀን/ ትግሬን /ትግራይን ጦር/ ከባቢ ዘበኛ አድርገው አገሩን እያጠፉ ቀኝና ግራ እየወረዱ ከብቱን እየማረኩ ነበር። ወደራ ላይ በሠፈሩበት ቀን የወይዘሮ አትሞችሆኖን ከተማ ሰላድንጋይን አቃጠሉት።

ንጉሥ ምኒልክም ዕርቅ ፈልገው ነበርና አፄ ዮሐንስ የዕርቅ ወዝ እያሳዩ ወደ ፊት እየገፉ በመምጣታቸው ተናደው በአንጐለላ ሠራዊታቸውን ሁሉ ሰብስበው ሰልፍና ግባት አሳዩ። በዚያንም ቀን የሸዋ መኳንንቶች ሲፎክሩ «ለአምስት ሲናድር እገሌ ተዋሰኝ!

ለአስር ሲናደር እገሌ ተዋሰኝ!» እያሉ ይናገሩ ነበር። እንደዚህም ማለታቸው ከዚያ አስቀድሞ በንጉሥ ምኒልክ ሠራዊት እጅ የነበረው ጠመንጃ በባሩድና በጨርቅ እየተደደቀ በከምሱር ወይም በቋያ የሚተኮስ ነበር እንጂ በአጼ ዮሐንስ ሠራዊት እጅ እንዳለው በዘመኑ ማለፊያ እንደሚባለው እንደ ሲናድር ያለ ጠመንጃ ስለ አለመኖሩ ከአጼ ዮሐንስ ጋር ተዋግተንና ድል አድርገን ሲናድር ጠመንጃ እየማረክን እናመጣለን ማለታቸው ነበር።

ንጉሥ ምኒልክ ግን ከጦርነቱ ይልቅ እርቁን ፈልገው ነበርና ከአንኮበር አለቃ ስነጊዮርጊስን፣ አለቃ ምላትን፣ አለቃ እሸቱን፣ ከሚጣቅ አለቃ ሐሤቱንና ሌሎችንም መነኮሳት ጨምረው ወደ አጼ ዮሐንስ ሰደዷቸው። እነዚህም ሊቃውንቶች ወደራ ላይ ከአፄ ዮሐንስ ጋራ ተገናኝተው የዕርቁን ውል ተነጋግረው ጨረሱ። ውሉም ስለ ሁለት ነገር ብቻ ነበር።

፩ኛው ነገር ንጉሥ ምኒልክ ወደ አጼ ዮሐንስ ሄደው ላይገቡና ላይገናኙ በአጼ ዮሐንስም ላይ ጠላት ቢነሳ ንጉሥ ምኒልክ የጦር አበጋዞቻቸውን እየላኩ ሊረዱ እንጂ፣ ራሳቸው ወደ ዘመቻ ላይሄዱ ነው።

፪ኛውም ነገር በሃይማኖት አንድ ሊሆኑና አባ ማስያስ የሚባሉትን የካቶሊክ ጳጳስ ካገራቸው አስወጥተው ሊሰዱ ነው። የቀረው ትንንሹ ነገር ግን የሚያስቸግር አልነበረም።

እነዚህም አስታራቂዎችም ወደ ንጉሥ ምኒልክ ተመልሰው የዕርቁን ድር ገና ሳይናገሩና ሳያስወድዱ የአጼ ዮሐንስ ሠራዊት ወራሪው ጦር የችሬደንን ወንዝ ተሻግሮ ብቅ ባለ ጊዜ የንጉሥ ምኒልክ ሠራዊት ይልቁንም የፈረስ ዘበኛው ፈንድቶ ወጥቶ ጦርነት ተጋጠሙና ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው ሞተ።

በዚያንም ጊዜ የንጉሥ ምኒልክ የአክስታቸው ልጅ አቤቶ በሻህ አቦዬ ብዙ ትግሮች /ትግራዋዮች/ ገድሎ ብዙ ሲናድር ማርኮ እየፎከረ ተመልሶ ነበረ ማታውን እንደዚህ ተብሎ ተገጠመለት።

ለአምስት ሲናድር ለአስር ሲናድር ዋስ የጠራችሁ፤

በሻህ አቦዬ ከፈለላችሁ።

ከዚህም በኋላ አጼ ዮሐንስ የዕርቁን ውል ለማጽናት ሲሉ «ከወንድሜ ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ታርቄአለሁና ከእንግዲህ ወዲህ አገር ያጠፋህ ከብት የዘረፍክ ወታደር ትቀጣለህ» የሚል አዋጅ ነገሩ። ወታደሩ ግን ያዋጁን ቃል እምቢ ብሎ ከብት እየዘረፈ ሲመጣ ባዩት ጊዜ እያስያዙ በጠመንጃ አስደበደቡት። አንዳንዱንም እጁን ቁረጡት ብለው ካዘዙ በኋላ ፊታውራሪ ናደው ለጊዜው በዚያው ነበርና «ጃንሆይ ወታደር

መብሉን እንጂ ሞቱን አያስብምና በግርፋት ይቀጣ እንጂ መቆረጡን ይማሩት» ብሎ ስለ አማለደ እየተገረፉ ተለቀቁ።

አጼ ዮሐንስም ምንም እንኳ የዕርቁ ነገር ቢጨርሱም ሸዋ ደርሰው ደብረ ሊባኖስን ሳይሳለሙ ለመመለስ አላሰቡምና ወደ ደብረ ሊባኖስ ተጓዙ። ስለሆነም የዕቅ ውል ከተነጋገሩ ከጨረሱ በኋላ ከንጉሥ ምኒልክ ጋራ ፊት ለፊት ሳይተያዩና ቃል ለቃል ሳይነጋገሩ በመቅረታቸው ስለ ተፀፀቱ «ተገናኝተን በፍቅርና ባንድነት ብንኖር መልካም ነው የሚል ቃል ጽፈው መስቀልና ሥዕል ጨምረው በደጃዝማች ዋህድና በመምህር ግርማ ሥላሴ እጅ ወደ ንጉሥ ምኒልክ ልከው ወደ ፊት ይጓዙ ጀመር።

መላከተኞቹም ደብዳቤውን ለንጉሥ ምኒልክ ባስረከቡ ጊዜ ከመኳንንቶቼ ጋር መክሬ ምላሹን እነግራችኋለሁ በለው አሳደርዋቸው።

በማግሥቱም ደጃዝማች ጐበና ደጃዝማች መንገሻ አቲከምና ሊቀ ካህናት ኪዳነ ወልድ እየተጠሩ ገብተው ከተመከረ በኋላ፣ አጼ ዮሐንስ በእኔ ላይ ክፉ ሥራ ላይሠሩ የማሉና የተገዘቱ እንደሆነ ምላሹን ስትልኩብኝ መጥቼ እገናኛለሁ ብለው ለአጼ ዮሐንስ ባለ ወርቅ አልጋና ባለ ወርቅ ወንበር ለእጨጌ ቴዎፍሎስም ባለ ወርቅ ወንበር ብቻ ገጸ በረከት ጨምረው ሰደዷቸው።

አጼ ዮሐንስም ጥንቱንም ቢሆን ወደ ሸዋ ሲመጡ ንጉሥ ምኒልክ ለእኔ አይታጠቅም ብለው ስለ ጠረጠሩ ነበር እንጂ ይህ ከሆነ በኋላ ክፉ ሥራ እሠራባቸዋለሁ የማለት አሳብ አልነበራቸውምና ንጉሥ ምኒልክ የጠየቁትን የመሃላ ቃል እሺ ብለው ተቀበሉ።

ንጉሥ ምኒልክም ምላሹ ከተላከላቸው በኋላ በመጋቢት ፲፪ ቀን ከልቼ ከተማ ተነስተው ወደ አጼ ዮሐንስ ጉዞ ጀመሩና ጅጅጋ ላይ ደረሱባቸው። መምጣታቸውም በተሰማ ጊዜ ዋግሹም ብሩና ደጃዝማች ማሩ ደጃዝማች ተሰማና ደጃዝማች ዋህድ ንጉሥ ምኒልክን ለመቀበልና እጅቦ ለመምጣት ተልከው ሄዱ። አጼ ዮሐንስም ልብሰ መንግሥት ለብሰው ዘውድ ጭነው በትረ መንግሥት ይዘው ወታደሩን ቀኝና ግራ አሠልፈው መድፍ እያስተኮሱ እምቢልታና መለከት እያስነፉ በታላቅ ክብር ተቀበሏቸው። ከዚህም በኋላ በባለ ወርቅ ዙፋን ተቀምጠው ቃል ለቃል እየተነጋገሩ ከቆዩ በኋላ ተሰናብተው ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ። በማግሥቱም ተመልሠው ሄደው ወደራ ላይ የተደረገውን የዕቁን ውል ቃል ለቃል ተነጋግረው ስለ ጨረሱ በሁለቱም መካከል ትልቅ ደስታ ተደረገ።

ከዚህም በኋላ አጼ ዮሐንስ ለንጉሥ ምኒልክ ዘውድና ሙሉ ልብስ መንግሥት ሸለሟቸው። እስከዚህም ቀን ድረስ አጼ ምኒልክ ይባሉ ነበር። በደብዳቤም ንጉሠ ነገሥት

ምኒልክ እያሉ ያትሙ ነበር። አጼ ምኒልክ ወደ ሸዋ መጥተው የንጉሥነት ዘውድ ከሸለሟቸው በኋላ ግን አጼ ምኒልክ መባላቸው ቀረና ንጉሥ ምኒልክ ይባሉ ጀመር።

በዚያን ጊዜ አዝማሪ እንዲህ ብሎ ገጠመ።

እንዴት ያለ ነው ጭንቅ ያለው መንገድ፣

አሻቅቦ ወጥቶ ወደ ታች መውረድ።

ይህም ሁሉ ከተደረገ በኋላ በወደራ በተደረገው የዕርቅ ውል እንዲፈጸም ስለታሰበ በደብረ ሊባኖስ የሚኖሩ ለክርስቶስ ሦስተኛ ልደት አለው የሚሉ ዋልድቤ እንግድና ዙራምቤ እንግዳ ተከለ አልፋም እጃቸው ተያዘ። አጼ ዮሐንስም በመጋቢት ፳፫ ቀን ከደብረ ሊባኖስ ተነስተው በፍቼ አድርገው በደራ በኩል ወደ ወሎ ለመሄድ ጉዞ ጀመሩ። ንጉሥ ምኒልክም እስከ ቃሮዳ ሸኝተው ተመለሱና በእነዋሪ በኩል ወደ ልቼ ከተማ ገቡ።

# ምዕራፍ ፳፺

## ስለ ሃይማኖት ክርክር ነገር

የሃይማኖት ክርክር የሚደረገው ቦሩ ሜዳ ላይ መሆኑን አጼ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ ተነጋግረውና ተስማምተውበት ነበርና ንጉሥ ምኒልክ በልቼ ከተማ አንድ ወር ያህል ከቆዩ በኋላ፣ የሸዋን ሊቃውንትና ካሃንት በአዋጅ አስከትተው በግንቦት ፰ ቀን ፲፰፻፸ ዓ.ም ከልቼ ተነስተው ወደ ወሎ ተጉዙ። ከአጼ ዮሐንስም ጋር ቦሩ ሜዳ ላይ ከተገናኙ በኋላ የሃይማኖት ክርክር እንዲጀመር ተፈቀደና ሁለቱም ነገሥታት ቀኝና ግራ በተዘረጋላቸው ዙፋን ተቀመጡ።

በጉባኤውም የነበሩ ትልልቅ ሰዎች እጨጌ ቴዎፍሎስና ራስ አዳል ገና ያልተጠመቁት ይማሙ አባ ዋጠውና ይማሙ መሐመድ አሊም ነበሩ። ከሸዋም ወገን እነ ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል እነ ፊታውራሪ ናደው ሌሎችም ብዙ መኳንንቶች ናቸው።

ከሁለት ልደት ወገን አፈ ጉባኤው መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ ከሦስት ልደት ወገን አለቃ ወልደሃና ነበሩ። የሁለት ልደት ወገን አፈ ጉባኤ የጥያቄ ቃል እየመጡ መላልሰው ከጠየቁ በኋላ የሦስት ልደት ወገን አፈ ጉባኤ እንደ ሁለት ልደት አፈ ጉባኤ የጥያቄ ቃል እያመጣ እየመላለሰ ለመጠየቅ ቢጀምር አጼ ዮሐንስም መኳንንቱም ለጠየቅከው ነገር አጉራህ ጠናኝ ወይም አገባ በል እንጂ ተጠየቅ ማለት አይገባህም አሉት።

በዚህም ጊዜ ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ተነስተው ጃንሆይ በእኛ በሸዋ ሥርዓት ከሳሹ ተጠየቅ እያለ ከተሟገተ ተከሳሹም በተራው ተጠየቅ እያእ ለመከራከር አይከለከልም ብለው ስለ ተናገሩ አለቃ ወልደሐናም ተጠየቅ እያለ እንዲከራከር ተፈቀደለት።

ቢሆንም ለክርስቶስ ሦስተኛ ልደት አለው የሚል ከቅዱሳት መጻሕፍት ምስክር ስላልተገኘ የሁለት ልደት ወገን ረታ። የሦስት ልደት ወገን ተረታ። ስለዚህ በጉባኤው የነበረው ሰው ሁሉ ሃይማኖቴ ሁለት ልደት ነው እያለ ተገዘተ። ከደብረ ሊባኖስ እየተያዙ የሄዱት ዋልድቤ እንግዳና ዙራምቤ እንግዳ ተክለ አልፋ የሚባሉት ግን ለክርስቶስ ሦስት ልደት አለው ማለታችንን አንተውም ስለ ማለታቸው በጉባኤው ከተቀመጡት አንዱ ተነስቶ አሁን ይህን የኑፋቄ ሃይማኖት ይዛችሁ መንግሥተ ሰማይ ልትገቡ ነውን? ብላቸው ዋልድቤ እንግዳ የሚባሉት የማይፈሩ ተናገሪ የነበሩና ምናልባት ያን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ አጼ ዮሐንስ ሊጋባው አሉላ ይከለክሉን ይሆን? ብለው በድፍረት ተናገሩ። በማናቸውም ቢሆን ምላሳቸውን ይቆረጡ ተብሎ ተፈረደና የሦስቱንም ምላሳቸውን እየቆረጡ ቀጧቸው። ዋልድቤ እንግዳ ያንጊዜውን ሞቱ። ዙራምቤ እንግዳ ተክለ አልፋ ግን ከቦሩ ሜዳ ጉባኤ በኋላ ብዙ ዘመን ኑረው ሞቱ። ከዚህም በኋላ ከዚህ ቀጥሎ ያለው የሃይማኖት አዋጅ ተነገረ።

ክርስቶስ እምቅድመ ዓለም ከአብ፤ ድህረ ዓለም ከንጽህት ማርያም ስለ ተወለደ ሁለት ብቻ ልደት ብቻ አለው። በሰውነት አምላክ ነው። በሰውነቱ እንደ አብ እንደ መንፈስ ቅዱስ ያውቃል ወልድ ቅብዕ ነው። ወለወልዳ ሰጊድ በአምልኮት ይባል እንጂ፣ ዘምስለ ወልዳ ሰጊድ ወአምልኮት አይባል የሚል ነው።

ይህም ስለ ሃይማኖት የተደረገው የአካል ቅጣት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአስተማረው ትምህርት ፈጽሞ የተለየ ስለሆነ ዛሬ ታሪክ አንባቢዎችን በጣም ሳያሳዝናቸው አይቀርም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር ወንድምህ ቢበድልህ በመጀመሪያ ብቻህን ሆነህ ምከረው። ባይሰማህም በሁለተኛው አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ጨምረህ ምከረው። እነዚህንም ባይሰማቸው በሦስተኛው ለቤተ ክርስቲያን ንገበርና ማኅበሩ ሁሉ ይምከሩት። የቤተ ክርስቲያን ማኅበር የመከሩትን ባይሰማቸው ግን እንደ አረማዊ እንደ መጸብሀዊ ይሁን ብሎ አስተማረ እንጂ አካሉን ቅጡት ገንዘቡን ውረሱት ርስቱን ንቀሉት ብሎ አላስተማረም።

በኋላም ዘመን የተነሱ ነገሥታትና ሊቃውንት እንደዚህ እንደ ጌታችን ቃል አድርገዋል። አርዮስ ወልድ ፍጡር ብሎ በተነሳ ጊዜዔ ሥለስቱ ምዕት አውግዘው ከቤተ ክርስቲያን ለዩት እንጂ ቆስጠንጢኖስ እጅና እግሩን ወይም መላሱን አልቆረጠውም።

ንስጥሮስም ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ብሎ በተነሣ ጊዜ ሊቃውንቱ አውግዘው ከቤተ ክርስቲያን ለዩት እንጂ ንጉሡ ቴዎድሮስ ከሹመቱ ከመሻር አልተቀታም።

በአውሮጳ ግን የመካከለኛው ዘመን በሚባልበት ጊዜ የካቶሊክ ሃይማኖት ጸንቶና ሰፍቶ ብዙ ዘመን ከኖረ በኋላ በጀርመን አገር ፕሮቴስታንት የሚባለው አዲስ ሃይማኖት ባህል ስለ ተጀመረና ስለ ሰፋ በእንግሊዝም በፈረንሳይም በጀርመንም በሌሎችም አገሮች ያሉት ነገሥታቱ ትምህርትና ዕውቀት ያልነበራቸው ስለሆኑ በሮማ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አሳብ እየተማሩ የአካል ቅጣት እየቀጡ የብዙ እልፍ አዕላፍ ሰዎችን ደም ካፈሰሱ በኋላ ቆይቶም በየነገሥታቱ ልብ የወንጌል ብርሃን ስለ በራ ጳጳሳቱም የሚጣሉበት ምክንያቱ ሃይማኖት መስሎ ውስጡ ሹመትና ክብር መሆኑ ስለ ታወቀ በመንግሥታቸው የሚኖር ሰው ሁሉ በየሃይማኖቱ በነጻነትና በሰላም እንዲኖር አደረጉ።

በኢትዮጵያም እስከ አጼ ሱስንዮስ ዘመን በሃይማኖት ነገር የአካል ቅጣት አልነበረም። በአጼ ሱስንዮስ ዘመን ግን ጄዝዊት /ኢየሱሳውያን/ የሚባሉ የፖቱጋልና የእስጳንያ ካቶሊካዊያን ከአባ አልፎንሶ ጋራ ወደ ኢትዮጵያ በመጡ ጊዜ አጼ ሱስንዮስን ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት መልሰውት ስለ ነበረ ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት ለመግባት ያልወደደውንና የካቶሊክም ሃይማኖት የሚቃወመውን ሰው ሁሉ የአካል ቅጣት እንዲቀጣው በአንዳንዱም የሞት ፍርድ እንዲፈርድበት ይመክሩት ነበርና በሃይማኖት ነገር ብዙዎቹን ሰዎች የአካል ቅጣት እንደ ቀጣ በታሪክ ተጽፎ ይገኛል።

በካቶሊክ ሃይማኖት ውስጥ ጄዝዊት /ኢየሱሳውያን/ ፈረንሲስካን፣ ካፑችካን አውጉስቲካን የሚባሉ ልዩ ልዩ ማኅበሮች አሉ። ከነዚህም መካከል ጄዝዊት የሚባሉት ማኅበር ለካቶሊክ ሃይማኖት ፋናቲኮች /ወይም አክራሪዎች/ ናችውና ስለ ካቶሊክ ሃይማኖት ሰውን በማናቸውም ዓይነት ቅጣት ቢቀጡት በእግዚአብሔር ዘንድ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠራል እያሉ የሚያስተምሩ ለሰው ርኅራኄ የሌላቸው ናቸው።

እነዚህም ጄዝዊት የሚባሉት ካቶሊካውያን ይህን የመስለ እሾህ በኢትዮጵያ ከዘሩ በኋላ አጼ ሱስንዮስ ሞተና ልጁ ፋሲል ሲነግሥ «በቆፈሩት ጉድጓድ ይወድቃሉ፣ በቆረጡት ጨንገር ይመታትሉ» የሚባል ተረት አለና አጼ ፋሲል ወደ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት አንመለስም ያሉትንና ለኦርቶዶክስ ሃይማኖቱ ተቃዋሚ የሆኑት ካቶሊካውያንን ሁሉ እየያዘ እነሱ እንዳደረጉት በአካል ቅጣትም በሞትም እየፈረደ አጠፋቸው።

ከአጼ ፋሲል በኋላ በትግሬ /በትግራይ/ እስከ ነገሡበት እስከ ፬ኛ አጼ ዮሐንስ ዘመን በሃይማኖት ነገር ስደትና እስራት ነበር እንጂ፣ የአካል ቅጣት የሞት ፍርድ አልነበረም። አጼ ዮሐንስ ግን ትምህርት የሌላቸውና ለሰው ነፍስ የማይራሩ መነኮሳትና

ካህናት እንደ ገና ተነሥተው የጭካኔና የከፋት ምክር ስለ መከሩዋቸው በካህናቱ ምክር ብቻ የአካል ቅጣት እስከ መቅጣት ደረሱ።

አጼ ዮሐንስም በቦሩ ሜዳ በተደረገው የሃይማኖት ክርክር ሦስት ልደት የሚሉትን ወገኖች ምላሳቸውን ስለ ማስቆረጣቸው ከብዙ ዘመን በኋላ የውጭ ሀገር ሰዎች ስማቸውን እያከፉ የክርስቲያን ሥራ አይደለም እያሉ ጽፈውባቸው ነበርና ያንን መጽሐፍ ያነበበ የትግሬ /የትግራይ/ ተወላጅ የሆነ ነጋድራ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ የሚባለው ካህናቱ መነኮሳቱ ሦስት ልደት የሚሉትንና እስላሞችን የአካል ቅጣት ቢቀጧቸው ይጸድቃሉ እንጂ አይኮነኑም እያሉ እየመከሩ አስጐመዱ፣ አስጐመዱና አሁን ከእነዚህያ ከካህናቱና ከመነኮሳቱ ያንደኛው እንኳ ስሙ በከፋ ሳይነሳ የደጉና የእውነተኛው ንጉሥ የዮሐንስ ስም በከፋ ሲነሣ መኖሩ ያሳዝነኛል እያለ በኀዘንና በቃል ሲናገር ሰምቼዋለሁ።

በቦሩ ሜዳም የሃይማኖት ክርክር ከተጨረሰ በኋላ አጼ ዮሐንስ የወሎን ባላባት ይማሙ መሐመድ አሊን ክርስትና አንሥተው ስሙ ሚካኤል ተባለ።

ንጉሥ ምኒልክም ወረይሉ ሲደርሱ ሁለተኛውን የወሎ ባላባት ይማሙ አባ ዋጠውን ክርስትና አንሥተው ስሙ ኃይለ ማርያም ተባለ። ስለዚህም የወሎን እስላም ለማስተማር ወደ ክርስትና ለመመለስ መምሕር አካለ ወልድን ሾመው በሰኔ ወር መጨረሻ ፲፰፻፸፪ ዓ.ም ወደ ሸዋ ተመለሱ።

አጼ ዮሐንስም እስላሙና ጋላውም /ኦሮሞውም/ ሁሉ በግድ እንዲጠመቅና እንዲቆርብ አዋጅ አስነግረው የቦሩ ሜዳ ቤተ ክስቲያን እያሠሩ አልጠመቅም ያለውንም እስላም እየቀጡ ወሎ ከረሙ።

ከእስላም ወገን በሃይማኖቱ የጸናውና ጉልበት ያለው ወደ መተማ እየተሰደደ ከደርቡሽ ጋር ተደባለቀ። እኩሉም ወደ ሐረርና ቀቤና እደ ጂማም ተሰደደ። በዚሁም ምክንያት በያውራጃው ሁሉ ሽፍታ ብቻ ሆነ በየጅረቱም ሁሉ መጋደልና የሰው ደም መፍሰስ ሆነ።

ንጉሥ ምኒልክም እስላሙንና ጋላውንም /ኦሮሞውንም/ በግድ ማጥመቅ ማቁረብ ሁከት የሚያስነሳ መሆኑን አይተው ይህን ነገር ለጊዜው ብናቆየው ይሻላል ብለው ወደ አሴ ዮሐንስ ቢልኩባቸው «ግራኝ መሐመድ የኢትዮጵያን ሕዝብ በግድ ለማስለም በሰይፍና በእሳት ፈጅቶአቸዋልና፣ እኔም ደማቸውን እበቀልላቸዋለሁ» የሚል ዕውቀትና ትምህርት የሌላቸውን ሰዎች ብቻ ደስ የሚያሰኝ ምላሽ መለሱላቸው።

ንጉሥ ምኒልክ ከወሎ ተመልሰው አንኮበር ከገቡ በኋላ፣ የአጼ ዮሐንስን ትእዛዝ ለመፈጸም ሲሉ የይፋትንና የአርጐባን እስላም የአብቹንና የገላንን ጋላ /ኦሮሞውን/ በግድ

እንዲጠመቅና እንዲቆርብ አደረጉ። ይልቁንም ካህናቱ ጋላውን /ኦሮሞውን/ ካልተገረዘ አናጠምቅም ይሉ ነበርና ጋላው /ኦሮሞው/ እንደ አባቶቹ ሕግ ገዳ የሚባለው የሚገረዝበት ዘመኑ ሳይደርስ በመገረዙ ትልቅ ጭንቀት ሆኖበት ነበር።

ራስ አዳልም በበኩላቸው ወደ ጐጃም ሄደው እንደ ንጉሥ ምኒልክ የአጼ ዮሐንስን ትእዛዝ ለመፈጸምና ደስ ለማሰኘት ቅብዓት የሚባለውንም ሃይማኖት የያዙትን ሰዎች ማስገዘት ጀመሩ። በዚያን ዘመን በኢትዮጵያ እስላምና አረማዊ በነበረው ሕዝብ ላይ የደረሰበትን መከራና ጭነት ባይናቸው ያዩ ሰዎች ሲነግሩን ሁሉ ኢትዮጵያውያን ስለ መሆናቸው ልባችን ያዝናል።

# ምዕራፍ ፳፫

## <u>አጼ ዮሐንስ ለራስ አዳል ዘውድ ሰጥተው ሲያነግሡ ንጉሥ ምኒልክን ስለ መጥራታቸው።</u>

አጼ ዮሐንስ አሳባቸው ሁሉ ኢትዮጵያ ኃይል አግኝታ በነፃነታኡአ ተጠብቃ እንድትኖር ነበርና የሸዋ መንግሥት ለንጉሥ ምኒልክ ከላይ ከቀዳማዊ ምኒልክ ከታችም ከአጼ ልብነ ድንልግ ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ ተያይዞ የመጣላቸው መሆኑ ምንም እንኳ የታወቀ ቢሆንም በዘመኑ ኃይል አግኝተው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የሆኑት አጼ ዮሐንስ ስለሆኑ ለሸዋ ባላባት ለንጉሥ ምኒልክ ዘውድ እንደ ሰጡ ለጐጃምም ባላባት ለራስ አዳል ዘውድ ለመስጠት ቁርጥ ሀሳብ አድርገው ይህንኑ አሳባቸውን ከዚህ ቀጥሎ ባለው ደብዳቤ ለንጉሥ ምኒልክ አስታወቋቸው።

«መልዕክት ዘሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን፣ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ይድረስ ከንጉሥ ምኒልክ በአማን እሥራኤላዊ ዘአልቦ ጽልሁት። ሰላም ለከ ወሰላመ እግዚአብሔር የሀሉ ምስሌከ እኔ በእግዚአብሔር ቸርነት በእምነት ጽዮን አማላጅነት አምላክ ቅዱሳን ይክበር ይመስገን ደህና ነኝ። ምህረቱ ለዘላለም ነውና።

«ራስ አዳልን በጥምቀት ዕለት የምሾመው የማነግሠው ነኝ። ሲሆን ቢሰላ አብረውን ሁነን መሾም ይገባነ ነበር። ቀኑ የሚያጥር የማያዳርስ እንደሆነ አንድ ደህና ሰው ሁኔታውን ሁሉ የሚያይ ገስግሶ ለጥምቀት እንዲገባ ይሁን። እኔ ይህን ማለቴ ንጉሠ ነገሥት ተብዬ እኮራለሁ ብዬ አይደለም። አንድ ጊዜ ስሙም ወጥቶልኛል። የእግዚአብሔር ሃይማኖቱ እንዲጸናና እንዲሰፋ አሕዛቦች እንዲጠፉ ብዬ ነው። ለኢትዮያ ምቀኛዋ ብዙ ነውና ጸላቶቻችን እንዲደክሙና እንዲያፍሩ ብዬ ነው።

ደግሞ ይህነን ጉዳይ ካደረግነ በኋላ ወደ አምናችን የምመጣ ነኛን መምጣቴ የሚቸግር እንደሆነ ከዚያው እንድንገናኝ ይሁን።

የኢጣልያ ንጉሥ አምና በረከት ሰዶልኝ ነበር። ዕቃውን አኑሮ ሰዎቹን መልሶ ወሰዳቸው። ፍቅር ጀምሮ ሰዎቹን መልሶ መውሰዱ ብልሃቱ ጠፍቶኛል። የዚህ ነገሩ ወደ እርስዎ ይገኛል ይሆንን?

ተጽሕፈ በአምባ ጫራ ከተማ። አመ ሰሙኑ ለታኅሣሥ በ፲ወ፰፻፸፫ ወ፫ ዓ.ም

ንጉሥ ምኒልክ ይህን ደብዳቤ ካዩ በኋላ «ይህማ ትልቅ ነገር አይደለምን? እንደምን አድርጌ እቀራለሁ ብለው» በግስጋሴ ተነሥተው ወደ ደብረ ታቦር ሄዱ።

አጼ ዮሐንስም ከአምባ ጫራ ወደ ደብረ ታቦር መጥተው በጥር ፲፩ ቀን ለራስ አዳል ዘውድ ሰጥተው በከፋ /በከፊቾ/ እና በጐጃም ላይ አነገሡዋቸው። ስመ መንግሥታቸውም ተክለ ሃይማኖት ተባለ።



የጐጃም ንጉሥ ተክለሃይማኖት (የቀድሞው ራስ አዳል)

(ኢትዮጵያ ፎቶግራፍድ ከሚለው ከሪቻርድ ፓንክኸርስት መጽሐፍ የተወሰደ)

# ምዕራፍ ፳፱

## ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጠብ ስለ መጀመራቸው

አጼ ዮሐንስ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን አንግሠው ንጉሥ ምኒልክን አስናብተው ወደ ትግሬ ከተመለሱ በኋላ ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ምዕራብ ያለውን የጋላውን /የኦሮሞውን/ አገር ለመያዝ ለማቅናት መሽቀዳደም ጀመሩ። የንጉሥ ምኒልክ የጦር አበጋዝ ራስ ጐበና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም የጦር አበጋዝ ራስ ደረሶ ነበሩ። እነዚህም ሁለቱ የጦር አበጋዞች እጅግ ስመ ጥሩ ጀግኖች ነበሩ። ስለሆነም ራስ ደርሶ ወደ ጋላ /ኦሮሞ/ አገር መዝመትና ማቅናት የጀመሩት ከራስ ጐበና በፊት ስለሆነ ወለጋን ነቀምትን ጉማን አሞሩን ሆሮን ጉዶርን ግንደብረትን ጅማን እጅ አድርገውት ቆይተው ነበር።

ንጉሥ ምኒልክም በ፲፰፻፸፩ ዓ.ም የተጀመረውን የእንጦጦን ከተማ ሲሠሩ የጐጃም ጦር አበጋዝ ራስ ደረሶ አባ ጆቢር ከሚባለው ከጉማ ባላባት ጋር ተዋግቶ ገደለው የሚል ወሬ ሲሰሙ ራስ ጐበናን በግሥጋሴ ልከው ልዑል ራስ ዳርጌን ከተማ ጠባቂ አድርገው እርሳቸው ወደ አሩሲ ዘመቱ።

የአሩሲንም ጋላ /ኦሮሞ/ ወግተው ድል አድርገው ከብቱን ማርከው ሲመለሱ አዋሽ ላይ የራስ ጐበና ደብዳቤ ደረሰላቸው። ቃሉም እንደዚህ የሚል ነበር።

«ከራስ ደረሶ ጋራ ጉማ ላይ ተገናኝተን ከባላገር በግብር የተቀበሉትን ከብት ሁሉ አስመለስናቸው። ወደ ፊትም ንጉሥ ምኒልክ በፈቃዳቸው ከሰጧችሁ አገር በቀር ወደ ሌላ እንዳታልፉ ይሁን ብለን አምለንና አስገዝተን ሰደናቸዋል። «እኔም ወደዚያው ወደ ንጉሥ መምጣቴ ነው» የሚል ነው» ንጉሥ ምኒልክም ምናልባት ሁለቱ ዐርበኞች /ራስ ጐበናና ራስ ደረሶ/ ጦርነት የተጋጠሙ እንደሆነ የብዙ ክርስቲያን ደም ሳይፈስ አይቀርም እያሉ ሲሠጉ ነበርና፣ ነገሩ ያለ ጦርነት በመጨረሱ ደስ ብሏቸው ወደ እንጦጦ ከተማ ተመለሱ።

# ምዕራፍ ፴

## ስለ እምባቦ ጦርነት

ንጉሥ ምኒልክ አጼ ዮሐንስ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ማድላታቸውን ስለ ተረዱ ይሠጉ ነበርና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በጋላው /በኦሮሞው/ አገር የሚሠሩትን ሥራ ሁሉ

እየጻፉ ተበዳይ እየመሰሉ አቤቱታቸውን ቢልኩባቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ምላሽ መጣላቸው።

«መልእክት ከሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን፣ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ይድረስ ከንጉሥ ምኒልክ በአማን እስራኤላዊ ዘአልቦ ጽልሁት። ሰላም ለከ ወሰላመ እግዚአብሔር የሀሉ ምስሌከ፣ እኔ በእግዚአብሔር ቸርነት በእምነ ጽዮን አማላጅነት አምላከ ቅዱሳን ይክበር ይመስገን ደህና ነኝ፣ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። ደብዳቤውም ደረሰኝ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከዚህ በፊትም ልኬአለሁ እንግዴህም እሺ እልካለሁ። ደግሞ ለእራሳችሁ አንዳንድ ሰው አለመስደዴም ወደ ሸዋ የሔደው ለሸዋ ወደ ጐጃም የሄደውም ለጐጃም ያደላልና ነገሩ አያምርም ብዬ ነው። ነገር ግን አንድ ጳጳስ ሶስት ኤጲስ ቆጶሳት አራት ሁነው ሲወጡ በኢትዮጵያ ተደርጐ የማያውቅ ሐዲስ ነገር ሲደረግ የረከሰ በሚቀደስበት የተጠላ በሚታረቅበት ጊዜ እናንተ ትጣላላችሁን? እኔም ለሠራዊቴ ስንቅ አስይዝብዬ ነው እንጂ ምን አደርጋለሁ? ይኸው መጣሁ ተነስቼአለሁ። ሲህን ወይ ከዋድላ ወይ ከቤጌምድር ላይ ከእኔ ስንገናኝ አለያያችኋለሁ። አትቸኩሉ እስከመጣ ድረስ ቆዩ። የቸኮላችሁ እንደሆነ ግን ካለሁበት ድረስ እየራሳችሁን የሚለያይ አንድ አንድ ሰው ስደዱ። የሚመጣው ሰው ግን በጥንተ ውሉ ተጋጥሞ የሚለያይ ነው። ተጽሕፈ በመቀሌ ከተማ አመ ፳ወ፰ ለኅዳር በ፲ወ፰፻ወ፸ ዓመተ ምሕረት።

ለዚህም ደብዳቤ ምላሽ ንጉሥ ምኒልክ የጻፉትን ቃሉን አላገኘነውም እንጂ ምላሽ መጻፋቸውን ከዚህ ቀጥሎ ያለው የአጼ ዮሐንስ ደብዳቤ ያስረዳል።

«መልዕክት ዘሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን፣ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ይድረስ ከንጉሥ ምኒልክ። በአማን እስራኤላዊ ዘአልቦቱ ጽልሁት። ሰላም ለከ ወሰላመ እግዚአብሔር የሀሉ ምስሌከ፣ እኔ በእግዚአብሔር ቸርነት በእምነ ጽዮን አማላጅነት አምላከ ቅዱሳን ይክበር ይመስገን ደህና ነኝ። ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና።

ደብዳቤውም ደረሰኝ ከዚህ በፊትም የሁለታችሁን መልዕክት በደብዳቤ አመላልሳለሁ። አትጣሉብኝ ተፋቀሩልኝ። እንደ ሽማግሌ እንደ እናት፣ እንደ አባት እመክራለሁ እገላግላለሁ እንጂ፣ እንደ ንጉሥ ይህ ይሁን ብዬ ያዘዝሁት ነገር የለኝም። አሁንም የአሕዛብና የሰይታን መሳቂኢያ እንዳንሆን ከባሕር ወዲህ ከባሕር ወዲያ ብዙ ጠላት ሳለን እርስ በርሳችን ስንዋጋ የክርስቲያን ደም በከንቱ ቢፈስ ለክርስቶስ ኀዘን ነው። አሁንም የሁለታችሁ ጦር አይገናኝ ከተገናኘ ዘንድ ከመዋጋት ይደርሳል። እኔ እስከመጣ ድረስ ታገሡኝ ጦራችሁ በያለበት ይቆይ። ደግሞ እኔ ፊቴን ወደ ትግሬ /ትግራይ/ ብመልስ በወረባቦ በአርጐባ በወሎ ብዙ ንገር ይደረጋል። ማኅተቡን ይቆርጣል ሲሉ


እሰማለሁ። ከቀድሞውም ያጠፉ ያባ ዋጠው ምክር ይሆንን ብዬ ነበር። አሁንም ቢመከርበት ይሻላል። ነገር ግን እኔ ባጠፋው ቸግሮኝ አይደለም ከወንድሜ ጋራ እንዳልከፋ ብዬ ነው እንጂ። ተጽሕፈ በጭኒ ሠፈር አመ ፳ ለጥር በ፲ወ፰፻ወ፬ ዓመተ ምሕረት።

ደግሞ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም በበኩላቸው የተጠቁና የተበደሉ እየመሰሉ ወደ አጼ ዮሐንስ ይልኩ ነበርና ከዚህ ቀጥሎ ያለው ቃል ተጽፎላቸው ነበር።

«መልዕክት ዘሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ይድረስ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በአማን እስራኤላዊ ዘአልቦ ጽልሁት ሰላም ለከ ወሰላመ እግዚአብሔር የሃሉ ምስሌከ፣ እኔ በእግዚአብሔር ቸርነት በእምነ ጽዮን አማላጅነት አምላክ ቅዱሳን ይክበር ይመስገን ደህና ነኝ ምህረቴ ለዘላለም ነውና።

ደብዳቤውም ደረሰኝ እኔም የሁለታችሁን ነገር እየሰማሁ መከራ እየተቀበልሁ ተቀምጫለሁ። ነገር ግን ኢትማኡ በእኩይ አላ በገቢረ ሠናይ ነው። እንኳን በቅርብ ያለውን ጠላቴን በሩቅ ያለውን ጠላቴን እንኳን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጎዳልኛል እንጂ የተገፉ ሰው ምን ተጐድቶ ያውቃል። ለሁሉም እኔ ወደዚያ መጣሁ ሁሉም ስንገናኝ ይሆናል። ተጽሕፈ በአድዋ ከተማ አመ ፳ወ፫ ለጥር በ፲ወ፰፻፬ ዓመተ ምሕረት።»

ንጉሥ ምኒልክ ግን በምዕራቡ ጋላ /ኦሮሞ/ አገርና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የተነሱበትን ካፋን /ከፊችን/ በሙሉ ስለ አሰቡ ራስ ጐበናን ወደዚያው ግፋ ብለዋቸው ነበርና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የጦር አበጋዝ ራስ ደረሶና ሌሎችም መኳንንቶች በአንድነት ሆነው ከራስ ጐበና ጋር ለመዋጋት አስበው ነበር። ነገር ግን ራስ ጐበና የንጉሥ ምኒልክን አገር ለቃችሁ ትሄዱ እንደ ሆነ ሂዱ ያለዚያ እናንተም ወደ ጌታችሁ ላኩ እኔም ወደ ጌታዬ እልካለሁ እንጂ፣ ከናንተም ጋር ጋር አልዋጋም ብለው የኩራት ቃል ሰለላኩባቸው ተመልሰው ወደ ጐጃም ሄዱ ነገሩንም ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ቢያስታውቋቸው ተቆጥተው ራስ ደረሶን ብዙ ሠራዊት ጨምረው መልሰው ከሰደዷቸው በኋላ እርሳቸውም «ምታ ነጋሪት! ይከተት ሠራዊት!» ብለው ለዘመቻ አዋጅ አስነገሩ።



ራስ ጐበና ዳጪ (አባ ጥጉ)

(በደብረ ሊባኖስ ከመቃብራቸው ሐውልት ላይ የተገኘ ምስል)

ንጉሥ ምኒልክም ንጉሥ ተክለ ኃይማኖት ለዘመቻው አዋጅ ማስነገራቸውን በሰሙ ጊዜ እርሳቸውም በበኩላቸው «ምታ ነጋሪት! ይከተት ሠራዊት!» ብለው አዋጅ አስነግረው ነበርና በመጋቢት ፲፫ ቀን ፲፰፻፸፬ ዓ.ም እንጦጦ ከተማ ተነሱ።

ራስ ጐበና በጋላው /በኦሮሞው/ አገር ወዲያና ወዲህ እየተዘዋወሩ አገሩን ሲያቀኑ ስለ መንገዱ ርቀት ወሬያቸው ጠፍቶ ነበርና፣ ንጉሥ ምኒልክ ጥቁር መሬት ሲደርሱ ከጅማ የመጣ አንድ ነጋዴ ተገኝቶ ወሬ ቢጠይቅ «ራስ ጐበና ወደ ንጉሥ ለመምጣት አገሩን ሁሉ ማጥፋት ከጐጃሞችም ጋራ ጦርነት አልገጠሙም እንጂ ጐጃሞቹ አገሩን ሁሉ ማጥፋት ጀምረዋል» ብሎ ተናገረ። ሆኖም ሲደርሱ ራስ ጐበና መጥተው ተገናኙና ታላቅ ደስታ ሆነ።

ወዲያውም በእርሳቸውና በራስ ደርሶ መካከል የሆነውን ነገር ሁሉ ያገሩንም አኳኋን እያስረዱ ከተናገሩ በኋላ በአንድነት ሆነው ወደ ፊት ጉዞ ጀመሩ።

የወሎ ባላባት ወይዘሮ መስታወትም የወሎን ሠራዊት ይዛ እንድትመጣ ታዛ ነበርና ንጉሥ ምኒልክ ሊቃ ላይ ሲደርሱ በሰልፍ ገብታ የወሎን ሠራዊት አሳየች።

እንደዚህም እየገሰሰገሱ ሱዳዙ ንጉሥ ምኒልክ ሴሴ በሚባል ወንዝ ዳር መስፈራቸውን ጐጃሞች ሳያስቡት በድንገት ስለ ሰሙ የጐጃም ሠራዊት ደንግጠው ወደ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መልዕክተኞች ላኩ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ገና ዓባይን አልተሻገሩም ነበርና ከመኳንንቱ ጋር ተማክረው ፊታውራሪ ይመር የሚባለውን አሽከራቸውን ጠርተው ወደ ንጉሥ ምኒልክ ሄደህ ይህ አሁን እርስዎ ያሉበት አገር በአጼ ዮሐንስ ፈቃድ ያቀናሁት የኔ ግዛት ስለሆነ የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ ትተው ይመለሱ በለህ ንገር ብለው ልከውት ነበርና ወደ ንጉሥ ምኒልክ ገብቶ ቢነግራቸው «ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከዓባይ ወዲህ ምን ግዛት አለው? እኔ ስለ ወዳጅነትና ስለ ፍቅር ብዬ አሞሩን፣ ሆሮን፣ ጉድሩን ግንደበረትን የቀዲዳን አገር እንዲያቀና ብሰጠው እያለፈ ሌላውን አገር ሁሉ ይይዝ ጀመር። አሁን ግን በፈቃዴ የሰጠሁትን አገር ወስጃለሁና ከዓባይ ወዲህ ያለው የእርሱ ሠራዊት እየተመለሰ እንዲሻገር ይሁን» የሚል ቃል ነግረውት ተመልሶ ሄደ።

ከዚህም በኋላ ንጉሥ ምኒልክ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሠራዊት ባቀናው በጋላው /በኦሮሞው/ አገር ሹም ሽር አድርገው ወደ እንጦጦ ለመመለስ ሆር ጀሬ ከሚባል ሥፍራ ሲደርሱ በግንቦት ፳፩ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መላክተኞች መጡ ተባለና ንጉሥ ምኒልክ አስጠርተው «ደብዳቤ ይሻችሁ እንደሆነ ስጡኝ የቃል መልዕክትም እንደ ሆነ ንገሩኝ» ቢሏቸው መኳንንቱ ሁሉ ካልተሰበሰቡ ለብቻዎ እንዳነግር ታዘናል አሉዋቸው። መኳንንቱም ሁሉ ሰብስበው «እንግዲህ ንገሩንኝ አሏቸው።

ጌታችን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ንገሩ ያሉን ቃል ይህ ነው። «ምነው እርስዎ እኔ ሁልጊዜ ያዋርዱኛል። ከዚህ ቀድሞ በኃይል መጥተው አገሬን ጐጃምን አጥፍተውት ሄዱ። አሁን ደግሞ ያቀናሁትን የጋላውን /የኦሮሞውን/ አገር ከጅማና ከጨለያ በወደዱት

አገር የጠራ ሜዳ ይዘው ይቆዩኝ። ይህንንም ቃል በደብዳቤ አለመላኬ ደብዳቤውን ብቻዎን አይተው ቀደው ጥለው ሰምተው እንዳልሰማ ሆነው ሸሽተው ይኼዳሉ። በቃል የሆነ ግን ይህን ሰምተው ቢሸሹ አሽከሮችዎ ይታዘቡዎታልና በቃል መላኬ ስለዚህ ነው ብለዋል» እያሉ ተናገሩ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት «ኢይትመካህ ኃያል በኃይሉ። ኢይድኅን ንጉሥ በብዝኃ ሠራዊቱ» ያለውን ሳያስቡ ይህን የትዕቢት ቃል በመናገራቸው እግዚአብሔር በንጉሥ ምኒልክ እጅ የጣላቸው ይመስላል።

ንጉሥ ምኒልክም ይህን ቃል በሰሙ ጊዜ «ምንም ቢሆን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ይህን የመሰለ ኃይለ ቃል አይልክብኝም። ቢልክብኝም በማኅተሙ ይልክብኝ ነበር እንጂ፣ በቃል አይልክም። ስለዚህ ሀሰተኞች ናችሁና ተይዛችሁ ቆዩ» ብለው አሲያዟቸው። እነዚያ ግን ይህ ቃል የጌታችን መልዕክት ያልሆነ እንደ ሆነ በአካላችን እንቀጣ እያሉ ከማሉና ከተገዘቱ በኋላ እንግዲያውስ ከእናንተ አንዱ ሄዶ «አዎን ልኬአቸዋለሁ የሚል ባለ ማኅተም ደብዳቤ ይዞ ይምጣ እናንተ ግን እንደ ተያዛችሁ ቆዩ» ብለው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የቃል መልዕክት ጨምረው አንዱን ሰደዱት።

«እኔ ለአንተ ጦርነት ሰግቼ ሸሽቼ አልሄድም። ነገር ግን ከኔ ጋራ ለመዋጋት ከአጼ ዮሐንስ አግኝተህ እንደሆነ ፈቃድ ማግኘትህን በደብዳቤ እንድትልክልኝ ብዬ ነው እንጂ፣ ለጦርነቱስ እዚያው አገርህ ደረቤ ሜዳ ላይም ቢሆን እመጣልሃለሁና አንተን መንገድ አይምታህ፣ ይህንም በደብዳቤ አለመላኬ አንተ ደብዳቤውን ስትጥለው ዓይቼ ነው ብለህ ንገር» ብለውት ሄደ።

ከዚህም በኋላ ደጃዝማች ወልዴን ጠርተው «ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ለጦርነት መምጣቱ እውነትም ሀሰምት እንደ ሆነ በግስገሳ ሄደህ ወደ ዓባይ አፋፍ ዘልቀህ ዓይተህ አስታውቀኝ።» ብለው ሰደዱትና በግስጋሴ ሄዶ በመነጽር ተመልክቶ ሲመለስ «ከዓባይ ወዲህ ብዙ የድንኳን ሠፈር አይቻለሁ» ብሎ ስለ ነገራቸው ከሠፈሩበት ተነሥተው ወደ ጉድሩ ተጓዙ። ይላሎም በደረሱ ጊዜ በግንቦት ፳፫ ቀን በጠራ ሜዳ ላይ ሠራዊታቸውን አሰልፈው ሰልፉን ሲያዩ ዋሉ።

በግንቦት ፴ ቀን በማለዳ ተነሥተው ተጉዘው እምባቦ ሜዳ ሲደርሱ የጐጃም ሠልፍ ፊታውራሪ ፊት ለፊት ታየና ንጉሥ ምኒልክ በፈረስ ሆነው ወዲያና ወዲህ እየተዘዋወሩ ወታደሩን በየአለቃው አሰልፈው ከቀኑ ፯ ቀን ሲሆን ጦረንት ገጠሙ። የሁለቱም ወገን ሠራዊት ክርስቲያን ስለሆነ በተቀላቀለ ጊዜ እርስ በርሱ እንይጋደል ከዚህ ቀጥሎ ያለው ርችት በየሠልፉ ተለፎ ነበር።

የማን ነህ?

የአባ ዳኘው።

ዳኘው ምን አለ?

ስለበው አለ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ስመ ጥሩ ጀግና ነበሩና «በደጀን ሆነው ያዋጉ» ቡሏቸው አይሆንም ብለው እንደ ተራ ወታደር በፈረስ ሆነው መኻል ለመኻል ገብተው ሁለት ሰዓት ያህል እንደ ተዋጉ ቆስለው ተያዙ።

ነገር ግን ከእምባቦ ጦርነት አስቀድሞ ከማኅበረ ሥላሴ መጥተው ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር የሚኖሩ በኋላ እጨጌነት የተሾሙ አባ ወልደ ጊዮርጊስ የሚባለው መነኩሴ ከንጉሡ ጋራ ወደ ዘመቻው መጥተው ነበርና ንጉሡ ተማርከው ማለትን ቢሰሙ ከራስ ደርሶ ጋራ ሆነው ሰይፋቸውን መዘው «የሸሽህ ገዝቼሃለሁ!» እያሉ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ጋራ ሆነው ሲያዋጉት ዋሉ እንጂ ንጉሡ እንደ ተያዙ ጐጃሞች ድል አልሆኑም ነበር። ቢሆንም የጦርነት ነገር አውራው ከተያዘ በኋላ ምንም ያህል ብርታት አይገኝምና ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ድል ሆነው የሞተው ሞቶ የሚበዛው ተማረከ።

በማግስቱም ንጉሥ ምኒልክ በጦርነቱ ላይ የሞተውን የሸዋንም የጐጃሙንም ዋና ዋናውን እያስፈለጉ አስቀብረው ቁስለኛውንም አስነስተው ለጊዜው በየመኳንንቱ ሠፈር አሳድረው በጅማ በፊታውራሪ ቀንዲዳ አገር እየተመራ እንዲታመምና እንዲድን አደረጉ። በሦስተኛውም ቀን ለምርኮኛው ሁሉ ባልደረባ ራስ ጐበናን ሰጥተው ዓባይ ድረስ ሸኝተዋቸው ተመለስ ብለው አዘዙላቸው።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በበቅሎ ለመጓዝ የማይችሉ ሆነው ነበርና በአልጋ ተኝተው ሰው በየተራ እየተሸከመ ያጉዛቸው ነበር። ቁስላቸውንም ንጉሥ ምኒልክ ራሳቸው በመድኃኒት እያጠቡ በሻሽ ያስሩላቸው ነበር። እንደዚህም በቀስታ ሲጓዙ ሰንብተው በሰኔ ፳፱ ቀን እንጦጦ ከተማ ገቡ።

# ምዕራፍ ፴፩

## <u>ስለ ንጉሥ ምኒልክና ስለ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ዕርቅ</u>

አጼ ዮሐንስ በማናቸውም ቢሆን ንጉሥ ምኒልክን የሚወዷቸው በመፍራትና በሥጋት በመጠራጠርም ነበር። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ግን ባለ መፍራትና ባለ መሥጋት በማመንና በማለት ይወዷቸው ነበር ይባላል።

ስለዚህ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ጦርነት ለማድረግ ባሰቡ ጊዜ «እኔ ወደ ደብረ ታቦር ሳልዘልቅና ተዋጋ ብዬ ላስታውቅህ ምንም ቢሆን ጦርነት እንዳትገጥም» የሚል ቁርጥ ቃል ጽፈው ልከውባቸው ነበርና ራስ ደረሶ ንጉሥ ከመልዕክተኛው ተቀብለው ባዩት ጊዜ አትዋጋ የሚል ሆኖ ስላገኙት ንጉሥ ደብዳቤውን ያዩ እንደ ሆነ ከጦርነቱ ይቀራሉ በማለት ሳያሳዩዋቸው አስቀርተውት ነበር።

ደግሞ በዚያው ዘመን አጼ ዮሐንስ አራት ጳጳሳት ከምድረ ግብፅ አስመጥተው ነበርና ሁለቱ ነገሥታት እንዳይዋጉና የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ የውግዝትና የርግማን ቃል ላኩባቸው ብለው ስለ አዘዙዋቸው ወደ ሁለቱም ነገሥታት የውግዝት ቃል ልከው ነበርና የጳጳሳቱ ደብዳቤ ዘግይቶ ከጦርነቱ በኋላ ደረሰላቸውና ንጉሥ ምኒልክ በእንጦጦ ከተማ ሆነው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ምላሽ ደብዳቤ ጽፈው ልከው ነበር።

«ትብጻህ ኀበ ልዑላን ወኀሩያን በኀበ እግዚአብሔር አቡነ ጴጥሮስ ወአቡነ ማቴዎስ አቡነ ማርቆስ ወአቡነ ሉቃስ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ብርሃናተ ዓለም ወሐዋርያቲሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወውሉዱ ለማርቆስ ወንጌላዊ።»

የተላከ ከንጉሥ ምኒልክ። እኄምኀክሙ በአምኃ መንፈሳዊት ወአኃሥሥ በረከተክሙ ዘትረድአ ለኲሉ ፍጥረት አነ ዳህን ወሰላም በጸጋሁ ለእግዚአነ ወመኃኒነ ወበስእለታ ለእግዝትነ ወላዲተ ሕይወት። ሰኔ ፬ ቀን የተጻፈ ደብዳቤያችሁ በተዋጋን በ፳ ቀን ደረሰልኝ። እኔም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ለመውጋት አልፈለግሁም ነበር፣ እርሱ ፎክሮ ከወደ ኋላዬ ገሥግሶ ቢመጣብኝ አልሞት ባይተጋዳይ እንደሚባለው ዞሬ፥ ተዋጋን። እኔ ግን ለመውጋት ፈልጌው እንደ ሆነ ያወገዛችሁትም የረገማችሁትም ይድረስብኝ። ደግሞ ክርስቲያን ለክርስቲያን በመዋጋታችን ጃንሆይን አስቀይመን ይሆናል። የጃንሆም ልቡና እንዳይለወጥብኝ ስለ ሥላሴ ብላችሁ አስምሩኝ እንጂ በደለኛውንስ እኔ በጥቢ ስመጣ እዚያው ከጃንሆይ ፊት ታገኙታላችሁ። ሐምሌ ፳ ቀን ፲፰፻፸፩ ተጻፈ።

አጼ ዮሐንምስ ደብረ ታቦር ሳሉ ሁለቱ ነገሥታት ተዋግተው ጐጃሞች ማለቃቸውን በሰሙ ጊዜ መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው «ከክረምት በኋላ ወደ ሸዋ እንዘምታለንና ከብታችሁን እያጠነከራችሁ ክረሙ» ብለው ቢነግሩዋቸው ከመኳንንቱ የሚበዙ «ንጉሥ ምኒልክ እንኳን የጐጃምን መሣሪያ ጨምረው እንዲያውም የሚያስፈሩ

ሆነዋልና አሁኑኑ ቁስለኛው ሳይሽር፣ እይይደከምው ሳይበረታ፣ ገመምተኛው ሳይነሳና ሳይጠነከር ብንደርስባቸው ይሻለና እንጂ ክረምት ውጭስ አንችላቸውም፣» ብለው ስለ መከርዋቸው ሰኔ ሲያልቅ ሐምሌ ሲገባ ከደብረ ታቦር ተነሥተው በአምሐራ ሳይንት በኩል ተጓዙ።

ሳይንት ሲደርሱ ንጉሥ ምኒልክ አስረው በአትሮንስ ማርያም ያስቀመጡትን ደጃች መሸሻ ሰይፉን ፈትተው አውርደው እርሱን መንገድ መሪ አድርገው ለጋምቦንና ወሎን እያጠፉ ወረይሉ ገቡ።

ደጃች መሸሻ ሰይፉን ከታሰረበት ፈትተው መምጣታቸው የንጉሥ ምኒልክ ባላንጣ መሆኑን ያውቃሉና ማስፈራሪያ እንዲሆናቸው ነበር።

ቢሆንም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ባንድ ወገን ንጉሥ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እንዲሆኑ በየሰው አፍ ንግር መነገሩን ያውቁ ስለ ነበረ በሁለተኛውም ወገን ጠብ ፈላጊው ራሳቸው እንጂ ንጉሥ ምኒልክ አለ መሆናቸውን ስለ ተረዱት ወደ አጼ ዮሐንስ ለመሄድ ገና ከእንጦጦ ሲነሡ ተራርቀው አንድ ልብ ሆኑ።

ስለ ታረቁም ንጉሥ ምኒልክ ያጼ ዮሐንስ ልብ ወደ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ማዘንበሉን ያውቃሉና አስቀድሞ ነገሩን ማስታወቅ ይሻለኛል ብለው በእርሳቸውና በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መካከል የሆነውን ነገር ሁሉ ለአጼ ዮሐንስ የሚያስረዱ መላክተኞች ልከው ምላሹን ሲጠብቁ አጼ ዮሐንስ ክረምት እስቲያልፍ ልቆይ ሳይሉ በውሀ ሙላት በበረዶና በጭቃ ሠራዊታቸው እያለቀ ወደ ወሎ መምጣታቸውን ሲሰሙ እጅግ አደነቁ።

ቢሆንም መላክተኞቻችወ እስቲመለሱ በትዕግሥት ይጠብቁ ነበረና ከጥቂት ቀን በኋላ መልክተኞች ከአጼ ዮሐንስ ደብዳቤ ይዘው ደረሱላቸው። የደብዳቤውም ቃል ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

«መልዕክት ዘሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ይድረስ ከንጉሥ ምኒልክ በአማን እስራኤላዊ ዘአልቦ ጽልሑት ሰላም ለከ ወሰላመ እግዚአብሔር የሀሉ ምስሌከ እኔ በእግዚአብሔር ቸርነት በእምነ ጽዮን አማላጅነት አምላከ ቅዱሳን ይክበር ይመስገን ደህና ነኝ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና።

ቤጌምድር ሳለሁ ሁለቱ ነገሥታት ተዋግተው ድሉ ለንጉሥ ምኒልክ ሆነ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትንም ይዘው ወደ ሸዋ ተጓዙ ሲሉ ብሰማ እግዚአብሔር የፈቀደውን ሥርቷል ብዬ የክርስቲያን ደም በማይረባ ነገር በመፍሰሱ የእናንተ ደብዳቤ ስጠብቅ ደብረ ታቦር ላይ ወር ሙሉ ተቀመጥሁ። ኋላ ግን ወሬያችሁ ቢጠፋብኝ ይህስ ነገር አለበት

ብዬ ስመጣ ሳይንትን ሳልፈው የንጉሥ ወረቀት ደረሰልኝ። ደብዳቤውንም አይቼ መዘግየቱ በመንገዱ እርዝመት እንጂ ሌላ ተንኮ አለመኖሩን ባውቅ ወደ ቤጌምድር ለመመለስ አሰብሁ። ነገር ግን ክረምቱ ተጭኗልና ሠራዊቱ የሚጐዳብኝ ሆነ። ስለዚህ በወሎ እንድከርም ፈቃድ ይደረግልኝ። እኔም አገር አልበድልም። በጥቢ ተገናኝተን ሁሉንም ነገር ተማረክን ወደ በጌምድር መመለስ ይሻላል ብዬ ነው እንጂ ሌላ ጉዳይ ኖሮኝ አይደለም። ደግሞ ይህ የሚያሳዝን ነገር ቢሆን ተመልሼ ሠራዊቱ በውሀ ሙላትና በጭቃ ያለቀው አልቆ የተረፈውን ይዤ መመለስ ይሻለኛል። ሐምሌ ፪ ቀን ፲፰፻፸፬ ዓመተ ምሕረት።»

በአጼ ዮሐንስ ደብዳቤ ከሥር እስከ ጫፉ የተጻፈው ቃል የዲፕሎማቲክ ንግግር ነው እንጂ በንጉሣዊ አነጋገር በእውነት የተጻፈ አይመስልም። ይልቁንም በውሎ እንድንከርም ይፈቀድልኝ የሚለው የሚያሳዝን ሲሆን ግን ሠራዊቱ በውሀ ሙላት ያለቀ አልቆ ወደ ቤጌምድር መመለስ ይሻለኛል የሚለው ቃል የአንበሳ ልመና ጋማ ይዞ እንደ ማለት ነው እንጂ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከመንግሥቱ አገር ባንዱ አውራጃ ለመከረም ማስታወቅ ብቻ ይበቃ ነበር እንጂ ፈቃድ መጠየቅና መሰመን አያስፈልግም።

ንጉሥ ምኒልክም ደብዳቤውን አይተው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ጽፈው በግሥጋሴ ላኩ።

«ጃንሆይ መጥተው ወደ ወሎ ከቀረቡ ሳንገናኝ አንከርምምና ወደዚያው እመጣለሁ። ከድንኳንም ቤት ይሻለኛልና ወረይሉ ከእኔ ቤት ገብተው ቢከርሙ ይሻላል ሐምሌ ፲ ቀን ፲፰፻፸፬ ዓመተ ምሕረት እንጦጦ ከተማ ተጻፈ።»

ከዚህም በኋላ ንጉሥ ምኒልክ በሐምሌ ፲፩ ቀን ከእንጦጦ ተነሥተው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ይዘው በደብረ ብርሃን አድርገው ደጋ ደጋውን ተጉዘው በነሐሴ ፯ ቀን ወረይሉ ደረሱና አጼ ዮሐንስ በታላቅ ሠልፍና ክብር ግባት እየተከኮሰ ተቀበሏቸው።

አጼ ዮሐንስም ከሁለቱ ነገሥታት አንደኛው ከሳሽ ሆኖ ነገሩ በፍርድ የሚፈጸም መስሏቸው ይጠብቁ ነበር። ነገር ግን ሁለቱ ነገሥታት ገና ከእንጦጦ ሲነሡ በምሥጢር ተራርቀው ነገራቸውን በመሃላና በግዝት ጨርሰው ነበርና የክስ ነገር የሚያቀርብ አልተገኘም። ስለዚህ በሁለቱም ላይ ተቆጥተው «ከንጉሥ ምኒልክ የወሎን ግዛት፣ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም የአገውን ግዛት ስለ መቀጫ ወስጃለሁ» ብለው ለሁለቱም ነገሥታት አስታወቋቸው።

አንዳንድ ጊዜም አጼ ዮሐንስ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የሚያደሉ ስለ መሆናቸው ንጉሥ ምኒልክ በጦርነቱ ላይ የማረኩትን መድፍና ሲአንድር ጠመንጃ ሁሉ ለራስ አሉላ

እንዲያስረክቡ አዘዟቸውና «የሞትሁበትን መሣሪያ ለምን ለራስ አሉላ አስረክብ ይሉኛል?» በማለት እጅግ አዘኑ። ቢሆንም የንጉሥ ቃል ረዘመ ብሎ አያሳጥሩት አጠረ ብሎ አያስረዝሙት የሚባል ነገር አለና መድፉንም ሲናድሩንም በሙሉ ለራስ አሉላ አስረከቡ።

ይልቁንም አጼ ዮሐንስ መድፉንና ሲናድሩን ሁሉ ራስ አሉላ እንዲረከቡ ማዘዛቸው በኋላ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሊመልሱላቸው ነው እየተባለ ይወራ ነበርና የሸዋ መኳንንት በሙሉ አዝነው ነበር።

# ምዕራፍ ፴፪

## ስለ ልዑል ራስ አርአያና ስለ ልዕልት ወይዘሮ ዘውዲቱ ጋብቻ

ከዚህ በኋላ አጼ ዮሐንስ መቼም ቢሆን ለኢትዮጵያ የሚያስቡት አሳብ ሁሉ መሠረት ያለው ነበረና ንጉሥ ምኒልክ ኃይላቸው እየበረታ ሥራዊታቸው እየበዛ መሄዱን አይተው «ከእንግዲህ ወዲህ ለእኔም ያለኝ አንድ ወንድ ልጅ ብቻ ነው። የምኒልክን ሴት ልጅ ያገባ እንደ ሆነ እኛም በሞት ብናልፍ የሁለታችንም ዘር በአልጋው እንዲቀመጥ ሴት ልጅዎን ለልጄ ይስጡኝ» ብለው ራስ አሉላን ራስ ገብረ ኪዳንን ቢትወደድ ገብረ መስቀልን ወደ ንጉሥ ምኒልክ ላኳቸው።

ንቡረ እድ ገብረ ሥላሴ በጻፉት ታሪክ ግን አጼ ዮሐንስ መሃላና ግዝት አፍርሰው ወደ ወሎ ስለ መጡ ኃፍረት ሆኖባቸው ቢቸግራቸው ልጅዎን ወይዘሮ ዘውዲቱን ለልጄ ይስጡልኝ ብለው ላኩ ተብሎ ተጽፎዋል።

አጼ ዮሐንስ ወደ ወሎ ለመግባት በሐምሌ ፪ ቀን በ፲፰፻፸፬ ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤያቸው ከንጉሥ ምኒልክ በደብዳቤ ጠይቀውና አስፈቅደው ነው እንጂ፣ በኃይል አልገቡምና ወደ ወሎ መግባታቸው ልጅ ለመኑ የተባለውን ዘመናአዊኢ ንግግር ይመስላል።



አፄ ዮሐንስና ልጃቸው ራስ አርአያ

(ኢትዮጵያ ፎቶግራፍድ ከሚለው ከሪቻርድ ፓንክኸረስት መጽሐፍ የተወሰደ)

ንጉሥ ምኒልክም ይህን የጋብቻውን ነገር በሰሙ ጊዜ የልጂቱ ዕድሜ ገና ፯ ዓመት ስለሆነ ሕፃን በመሆኗ ብቻ ነው እንጂ ጋብቻው እጅግ ያማረ ነውና ጃንሆይ ፈቃዳቸው ከሆነ የእኔም ፈቃዴ ነው ብለው ተናገሩ አጼ ዮሐንስ አሳባቸው በመፈጸሙ ደስ አላቸው። ወዲያውም ስለ እምባቦ ጦርነት መቀጫ ከንጉሥ ምኒልክ የተወሰደባቸው የወሎ ግዛት ለራስ አርአያ እንዲሆን ተማከሩና አዋጁ ተነገረላቸው።

ከዚህም በኋላ በመስከረም ፪ ቀን ፲፰፻፸፭ ዓመተ ምሕረት አጼ ዮሐንስ ከወረይሉ ተነሥተው ከሁለቱ ነገሥታት ጋራ ባንድነት ወደ ቦሩ ሜዳ ሄዱ።

ንጉሥ ምኒልክም በመስከረም ፯ ቀን ወደ ቦሩ ሜዳ ሄደው የሠርጉን ነገር ከአጼ ዮሐንስ ጋራ ተመካክረው ወደ ወረይሉ ተመለሱና የሠርጉ ድግስ ተጀመረ።

በጥቅምት ፲፫ ቀን ልዑል ራስ አርአያ ልዕልት ወይዘሮ ዘውዲቱን በተክሊልና በቁርባን አገቡ። የሠርጉ ማማርና የሽልማቱ ብዛት ሊነገር አይቻልም።

የሠርጉም ወራት ካለፈ በኋላ ንጉሥ ምኒልክ ከወረይሉ ተነሥተው ባንድ ቀን ግስጋሴ ቦሩ ሜዳ ገብተው ከአጼ ዮሐንስ ጋር ተገናኙ።

የትግሬ /የትግራይ/ መኳንንቶም የንጉሥ ምኒልክን አኳኋንና የሠራዊታቸውን ብዛት በማየታቸው ሥጋት ስለ አደረባቸው ክፉ ምክር ይመክሩባቸው ጀመር።

አጼ ዮሐንስም ንጉሥ ምኒልክን ለማስቀናት ሲሉ ባላንጣቸውን ደጃች መሸሻ ስይፉን እጅግ ያከብሩት ጀመር። በዚህም ምክንያት ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት «በቶሎ እየተሰናበትን በየሀገራችን ብንገባ ይሻላል» ብለው ተማከሩና በፊት ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወደ አጼ ዮሐንስ ገብተው «እባክዎ ጃንሆይ ወደ ሀገሬ እንድገባ ይፍቀዱልኝ ብለው ቢለምኗቸው» «ወደ ሀገሬ ልግባ የምትለኝ እምቼ ማርሁህና ነው?»

«አሁንም ስለ ጥፋትህ ሁሉ ምህረት እንዳደርግልህ ንጉሥ ምኒልክን አማላጅ ላክብኝና ከዚያ በኋላ አሰናብትሃለሁ» አሏቸው። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ወደ ንጉሥ ምኒልክ ሄደው ወደ ሀገሬ እንድገባ ከጃንሆይ ጋራ ከልብ ያስታርቁኝ ብለው ወደቁባቸው። ንጉሥ ምኒልክም በአጼ ዮሐንስ ልብ የታሰበውን ነገር ሳያውቁ «እባክዎ ጃንሆይ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ከልብዎ ይታረቁትና ወደ ሀገሩ ይግባ» ብለው ቢለምኗቸው፣ «እኔ ባነግሠው እርሱ በጥጋቡ ለቀለታልና መንግሥት አይገባውም ነበር። ነገር ግን ንጉሥን አማለጅ ከላከ ምን ይደረጋል። ትናንትና ንጉሥ አድርገን ዛሬ ብንሽረው ለእኛም አያምርልንምና ምሬዋለሁ። ዳሩ ግን ንጉሥ ሆኖ ያለ መሣሪያ በጀሌ ወታደር ታጅቦ ወደ ሀገሩ ቢገባ ውርደት ለእኛው ነው «የተማረኩበት መድፉም ነፍጡም እንዲመለስለት ይሁን» አሏቸውና ንጉሥ ምኒልክ በድንጋጤ አዘኑ። የሸዋ መኳንንትም

ይህን ወሬ በሰሙ ጊዜ «ጥንቱንም የፈራነው ይህንኑ ነበር። መቼስ አሁን ምን እናደርጋለን ይልቅስ የባሰ ነገር ሳያገኝ ተሰናብተን ብንመለስ ይሻለናል።» በማለት ምክራቸውን ጨረሱ።



ወይዘሮ ዘውዲቱ ምኒልክ

(በኋላ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ)

በማናቸውም ቢሆን ንጉሥ ምኒልክ መከፋታቸው እንዳይታወቅባቸው ሥራቸውን ሁሉ በፖለቲካ እየሠሩ ሦስት ወር ያህል ከአጼ ዮሐንስ ጋራ ቆይተው ጳጳሱን አቡነ ማቲዎስን ለሸዋ ጳጳሳት ተቀብለው በየካቲት ፪ ቀን ከብሩ ሜዳ ተነስተው በየካቲት ፳፬ ቀን ልቼ ከተማ ገቡ። ወዲያው ወደ ደብረ ብርሃን ወጥተው ልብሰ መንግሥት ለብሰው ዘውድ ጭነው ጳጳሱም የጵጵስናቸውን ልብስ ለብሰው ታላቅ የክብር በዓል ተደረገ።

# ምዕራፍ ፴፫

## ስለ ወይዘሮ ጣይቱ ትውልድና ንጉሥ ምኒልክ ወይዘሮ ጣይቱን ስለ ማግባታቸው

አጼ ሱስንዮስ ገና ሳይነግሥ ከአጼ ያዕቆብ ሸሽቶ በስደት ወደ ሸዋ መጥቶ ሳለ የሸዋና የጋላው /የኦሮሞው/ አገር ሕዝብ በጣም ረድቶት ነበረና እንደ ገና ተመልሶ ከአጼ ያዕቆብ ጋራ በጐጃም ደብረ ዘይት ላይ ተዋግቶ ከገደለውና በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ከነገሠ በኋላ በስደቱ ጊዜ የረዱትን የሸዋን ሰውዎች ለማክበርና ደስ ለማሰኘት ሲል ከወግዳ ተከትሎት ለሄደው ኤሎስ ለሚባለው የሰሜንን ግዛት ሰጥቶት ይገዛ ነበረ። ኤሎስም ቁርሎስም ወለደ፣ ቁርሎስ ኤራቅሊስን፣ ኤራቅሊስ ተስፉን፣ ተስፉ ማርትን /ማርታ/ ይወልዳሉ።

ማርት የአበርገሌውን ደጃች ወልደ ሩፋሌን አግብታ ገብሬን፥ ገብሬ ኃይለ አምርያምን ይወልዳል ኃይለ ማርያም የራስ ጉግሣን ልጅ ወይዘሮ ኂሩትን አግብቶ መርሶን፣ ብጡልን የውብዳንርን ይወልዳል። ብጡል ጣይቱንና ወሌን አሉላንና ደስታን ይወልዳል። ብጡልም ደጃዝማች ተብሎ ሲገዛ ኑሮ ከሞተ በኋላ ልጆቹ ልጅ ወሌና ልጅ አሉላ ለአጼ ቴዎድሮስ ሎሌዎች ሆነው መቅደላ ይኖሩ ነበርና ከአቤቶ ምኒልክ ጋራ ተዋውቀው ባንድነት አደጉ።

ልጅ ወሌና ልጅ አሉላም ጣይቱ የምትባል ቆንጆ እኅት አለችን እያሉ ለአቤቶ ምኒልክ ሎሌ ላቶ ናደው ይነግሩት ነበርና እርሱ ለአቤቶ ምኒልክ ለማጋባት አስቦ አሳቡን ቢገልጥላቸው አጼ ቴዎድሮስ አልጋውን የወሰዱት ከእኛ ወገኖች ከራስ አሊና ከደጃዝማች ውቤ ላይ ስለሆነ እኛን እንደ ባላንጣ ያዩናል ስለዚህ አሁን እኅታችንን ከአቤቶ ምኒልክ ጋራ ያጋባትና እንደሆነ በጥርጣሬ ሁላችንም ያጠፉናልና እግዚአብሔር የፈቀደ ጊዜ ይሁን እንጂ ለዛሬው አይሆንም ቢሏቸው ወይዘሮ ጣይቱን ትተው የአጼ ቴዎድሮስን ልጅ አጋብተው አስቀመጧቸው።



እቴጌ ጣይቱ



# አጼ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ

ከዚህም በኋላ አቤቶ ምኒልክ ከመቅደላ አምልጠው ወደ ሸዋ በገቡ በሁለተኛው ዓመት ልጅ ወሌና ልጅ አሉላም ከአጼ ቴዎድሮስ እየከዱ ወደ ሸዋ መጥተው ለንጉሥ ምኒልክ ሎሌዎች ሆነው ልጅ ወሌ ደጃዝማች ልጅ አሉላም ፊታውራሪ ተብለው በክብር ይኖሩ ነበረና ወይዘሮ ጣይቱ የቀድሞ ባላቸውን ፈትተው ወንድሞቼን እያለሁ ብለው ወደ ሸዋ መጥተው በወንድማቸው በደጃዝማች ወሌ ቤት ተቀመጡ።

ንጉሥ ምኒልክም ወይዘሮ ባፈና አቤቶ መሸሻ ሰይፉን ይዘው ታሞ ገብተው በመሸፈታቸው አዝነው ለመፍታት ያስቡ ነበር። ነገር ግን ባንድ ወገን የሚወድዋቸው ስለ መሆናቸው በሁለተኛውም ወገን አጼ ዮሐንስ ይታረቁልኝ ብለው ስለ ለመኗቸው ታርቀው ሲኖሩ በኋላ ደግሞ አጼ ዮሐንስ ከሚስትዎ ከወይዘሮ ባፈና ጋር ቢቆርቡ መልካም ነው ብለው ስለ መከሩውቸው እንቁረብ ብለው ፈቃድ ቢጠይቋቸው እምቢ አልቆርብም አሉ። ወይዘሮ ባፈና ከንጉሥ ምኒልክ ጋራ አልቆርብም ያሉበት ምክንያቴ አልታወቀም። ከዚህም በቀር ወይዘሮ ባፈና ታሞ ገብተው ከሸፈቱና ከወጡ ወዲህ በመካከላቸው እውነተኛ ፍቅርና አንድነት አልተገኘም ነበርና ንጉሥ ምኒልክ ወይዘሮ ባፈናን ፈትተው በሺ፰፻፸፫ ዓመተ ምሕረት ጣይቱን አግብተው ሥጋ ወደሙ ተቀበሉ።

# ምዕራፍ ፴፬

## የንጉሥ ምኒልክና የኢጣሊያኖች ወዳጅነት አጀማመር

ከዚህ ቀድሞ በ፩፻፫ ገጽ እንዳስረዳነው አጼ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ ደጃዝማች ካሣ በትግሬ /በትግራይ/ ደጃዝማች ጐበዜ በዋግ ንጉሥ ምኒልክ በሸዋ ሆነው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትን ለማግኘት ይሽቀዳደሙ ነበርና እንደየዕድላቸው መጀመሪያ የዋጉ ደጃዝማች ጐበዜ ተክለ ጊዮርጊስ ተብለው የኢትዮጵያ ንጉሠ እንገሥት ሆኑ። የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ግን የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት ገና አላገኙም ነበረና ይህንኑ ለማግኘት ሲሉ በኋላ በኢትዮጵያ ላይ የሚመጣውን አደጋና ችግር ሳያስቡ አጼ ዮሐንስ ብቻ ጐድተው የሚቀሩ መስሏቸው ከኢጣሊያኖች ጋራ ወዳጅነት ለመጀመር አስበው በ፲፰፻፸፭ ዓመተ ምሕረት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ለኢጣሊያ ንጉሥ ጻፉላቸው።

«ይድረስ ከኢጣልያ ንጉሥ ከልዑል ዑምቤርቶ ፩ኛ። ዑምቤርቶ ሆይ በእግዚብሔር ቸርነት ሰላምታዬን እልክለታለሁና ልዑል ግርማዎ የወዳጅነቴን ሰላምታ ይቀበሉኝ። ጤናዎን እንደምን ነዎት? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ።»

«ልዑል ሆይ! ከዚህ በፊት ያልጻፍኩልዎት መንገዱ በእስላሞች ተዘግቶብን ስለ ነበረ ነው። አሁን ይህን የተዘጋውን መንገድ ከፍቻለሁና ወደ ልዕልናዎ መጻፌ እጅግ ደስ አለኝ። ወደዚህ የመጡት አንዳንድ የኢጣልያ መኳንንት ወደ ልዑል ግርማዎ ለመጻፍ መልካም ምክር ይመክሩኛል። ልዑል ሆይ ከልዑል ግርማዎ የምነጋገረው ብዙ ነገር አለኝ። ነገር ግን በፊት ወዳጅነትዎን ለማግኘት በትጋት እመኛለሁ። ወዳጅነቴን ለመጀመር ብዬ ከዚሁ ደብዳቤ ቀጥሎ መልእክተኛዬን ጨምሬ እልክልዎታለሁ። ሁለት አንበሶች ወንድና ሴት ለግርማዎ እጅ መንሻ አቀርባለሁ። ወዳጅዎ የሸዋ ንጉሥ ምኒልክ ሰኔ ፲፩ ቀን ፲፰፻፸፭ ዓመተ ምሕረት አንኮበር።»

በኢጣልያ አገር ሩባቲኖ የሚባለው ኰምፓንያ በእስላሞች አማካይነት ወደ አሰብ ገዥ ተላልኮ በ፲፰፻፷፪ ዓመተ ምሕረት አገሩን ስለ ገዛው ሌላም መሬት እየቸማመረ አሥራ ሰባት ዓመት ያህል ከያዘው በኋላ በሺ፰፻፸፬ ዓመተ ምሕረት ለኢጣሊያ መንግሥት አሳልፎ ሸጠላትና የኢጣሊያ ባንዲራ ተተከለበት። ንጉሥ ምኒልክም ለንጉሥ ዑምቤርቶ ደብዳቤ የላኩት በዚሁ መንገድ ነበረ።

በዚያንም ዘመን የነበረው የኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በንግድ አስመስሎ አንድ ውል ተዋውሎ ከአሰብ ወደ ኢትዮጵያ ደጋ ለመውጋት ሰለ አሰበ መቼም የኢትዮጵያ ነገሥታት በካህናት በኩል እንዲታለሉ ያውቃልና አባ ማስያስን መካከለኛ አድርጎ ወደ አጼ ዮሐንስ ልኳቸው ነበር። አባ ማስያስም ይህ ነገር የኢጣልያ ጥቅም

መሆኑን ስለ ተረዱት የመጡበትን የክርስቶስን መንግሥት ማስፋት ትተው በመንግሥት ፖለቲካ ውስጥ ገብተው የምድራዊ ንጉሥ መንግሥት እንዲሰፋ ይትሩ ነበርና፣ ስለዚህ ነገር አንድ እይፍቅርና የወዳጅነት ውል ረቂቅ ጽፈው ለአጼ ዮሐንስ ቢያቀርቡላቸው «በዚህ ውል ሀገሬ ኢትዮጵያ ጥቅም አታገኝምና ምንም ቢሆን ማኅተሜን አላትምም» ብለው እምቢ አሏቸው። ኢጣሊያኖችም በአጼ ዮሐንስ በኩል ለማግኘት ያሰቡት ነገር አለመፈጸሙን ባወቁት ጊዜ ከዚያው በትንሹ በረሃ በአሰብ በኩል ወደ ፊት ጊዜውን መጠበቅ ይሻለናል በማለት ምክራቸውን ቆረጡ።

ከዚህም በኋላ በ፲፰፻፸፱ ዓመተ ምሕረት ኮንት ጴጥሮስ አንቶኔሊ የሚባል ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ለመነጋገር በአጼ ዮሐንስ ላይ ክፉ ስብከት /ፕሮፓጋንዳ/ ለማድረግ ወደ ሸዋ ተልኮ በአሰብ በኩል ወደ አንኮበር መጣና ንጉሥ ምኒልክ በታላቅ ክብር ተቀበሉት። ወዲያውም አጼ ዮሐንስ ከኢጣሊያ መንግሥት ጋር የንግድ ውል ለመዋዋል እምቢ ማለታቸውን እያስረዳ በነገራቸው ጊዜ ከጣሊያን መንግሥት ጋራ ተፋቅረው አጼ ዮሐንስ እንዲቀኑና እንዲያዝኑ ለማድረግ ሲሉ እርሳቸው በሸዋ በኩል መንግሥትና በራሳቸው ስም ሆነው ኮንት አንቶኔሊ በጣሊያን መንግሥት ስም ሆኖ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የንግድና የወዳጅነት ውል ተዋዋሉ።

፩ኛ። በሸዋ መንግሥትና በኢጣሊያን መንግሥት መካከል በመኳንንቶቻቸውና በተከታዮቻቸው በሕዝቦቻውም መካክከል የማይነቀል ዘላለማዊ ፍቅርና ሰላም ይሆናል።

፪ኛ። ከሸዋ መንግሥትና ከኢጣሊያን መንግሥት ታምኖ የተላከ ሰው በሁለቱም መንግሥት መዝገብ የተጻፈ ቆንሲል ተብሎ ይጠራል። ሁለቱም መንግሥቶች በተዋዋሉበት ውል ሁሉ ሊያስማማቸው ይችላል። እርሱም በየተቀመጡበት ሥፍራ ቆንሲል ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

ስለ ንግድ ዋነኝነትም ደግሞ ወደ ሁለቱ አገር እየተመላለሱ በየተቀመጡበት ቦታ የንግድ ተጠባባቂ ወይም ቆንሲል ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ። በመኳንንትና በሕዝብ ደግሞ እንደ ሀገር ሥርዓት ሊከበሩ ይገባቸዋል። ከርሳቸው ጋር የሚኖሩ ሰዎች ደግሞ አንድ ወንጀል ቢሠሩ እንደ ሀገር ሥርዓትና ልማድ ይቀጣሉ።

፫ኛ። የሸዋ ሰዎችና የኢጣሊያ ሰዎች ሁለቱም በትክክል በነፃነት ወደ ሸዋና ወደ ኢጣሊያ አገር ሊመላለሱ ይችላሉ። እየተመላለሱም የንግድ ሥራ ሲሠሩ በሁለቱም ሀገር ወዲህና ወዲያ ገንዘባቸውን ሊያመላልሱ ይችላሉ። በየብስም በባሕርም ቢሆን ደግሞ ለመንግሥት የሚጠቅም የንግድ ሥራ ስለ ሠሩ በሆነው ነገር ሁሉ እርሱ በመግንሥት ሥልጣን ይጠበቃሉ።

፬ኛ። የሸዋ ሰዎች ወደ ኢጣሊያ፣ የኢጣሊያም ሰዎች ወደ ሸዋ በነፃነት እየተመላለሱ ትክክል እንደ ባላገሮች በሥርዓት በሁለቱም አገር የንግድና የእርሻ ሥራ ሲሠሩ የጥበብም ሁሉ ትምህርት ሲማሩ ሕግ አይከለክላቸውም።

፭ኛ። በሸዋ አገር ከዚህ በፊት ከመንግሥት ሃይማኖት በቀር ሌላ ሃይማኖት እንዲያስተምሩ ክልክል ነበር። ከእንግዲህ ወዲህ ግን በሁለቱም አገር የሃይማኖት ትምህርት በነፃነት ያለ ፍርሃት እንዲማሩ በትልቁ በመንግሥት ሥልጣን በግልጥ ተፈቅዶአል።

፮ኛ። የኢጣሊያ ሰው በሸዋ አገር ቢሞት የሀገሩ ገዥ እንደ ኢጣሊያ ቆንሲል አሳብና ፈቃድ ገንዘቡን ሁሉ በጥንቃቄና በፍጥነት ይጠብቀዋል። ገንዘቡንም በኢጣሊያ መንግሥት ታምኖ የተላከ ሰው ተቀብሎ ሊወስደው ይችላል። እንደዚሁም ደግሞ የሸዋ ሰው በኢጣሊያ አገር በድንገት የሞተ እንደ ሆነ ያገሩ ገዥ በትክክል በፊት እንደተባለው ገንዘቡን ይጠብቃል።

፯ኛ። እስካሁን ድረስ ከኢጣሊያ ወደ ሸዋ መመላለስ ችግር እንደ ነበረ የታወቀ ነውና ከእንግዲህ ወዲህ ንጉሥ ምኒልክ ውል ገብተው ከኢጣሊያ ሰው በትክክል እንዲመላለስ ፈቅደዋል። የሚመላለሰውም የንግድ ሥራ ለመሥራት ነው። ደግሞ ለዚሁ ያንድነት ንግድ ግድነት የሚሆን መሣሪያና የነጋዴዎችን ደመወዝ ዋና ሆኖ የሚያስብ የኢጣሊያ ሰው ይሆናል።

፰ኛ። የኢጣሊያ ነጋዴዎች በሸዋ በር ሲወጡና ሲገቡ አንድ ጊዜ እንደሚዛኑ ሂሳብ በመቶው አምስት ብር ይከፍላሉ። የሸዋ ነጋዴዎች ግን በኢጣልያ በር ሲወጡና ሲገቡ በአስበ ቢሆን ምንም አይከፍሉም።

፱ኛ። በሁለቱም መንግሥቶች ወገን የተዋዋሉበትን ነገር ሁሉ በየጊዜው ከንግድ የሚገኘው ትርፍ ምን ያህክ እንደሆነ የገንዘቡን ድምር ያስታውቃል። /ትርጓሜውም የሸዋ መንግሥት የብሩን ትርፍ ገልቶ እንዲያስታውቅ ተስማምተዋል ማለት ነው/።

ደግሞ የኢጣሊያ መንግሥት በዚሁ ኮሎኒያና በባሕር ውስጥ አንድ ሰው እንዳይጐዳ በጥንቃቄ ይጠብቃቸዋል። የሸዋ መንግሥት ደግሞ በወገኑ ነጋዴዎችን እስከ ባሕር ጠረፍ ድረስ እየላከ ኪራያቸውንም እየከፈለ በሀገር ዋና መንገድ በመሥሪያው ይጠብቃቸዋል።

፲ኛ። የሸዋ መንግሥት ኢጣሊያኖች በሸዋ አገር ለጉዳያቸው ካንዱ መንደር ወደ አንዱ መንደር ሊመላለሱ ማንም ባላገር እንዳይበድላቸው ይጠብቃቸዋል። በድንገትም ቢበደሉ በሚገባ ሥርዓት አነገሩን መርምሮ ይፈርድላቸዋል። ደግሞ እስከ አውሳ

ሡልጣን መሐመድ አንፋሪ አገር እስከሚወርደው ወንዝ ይጠብቃል። ከዚህም አገር አንዳንድ በጥቅም ትርፍ በዓመት እንዳገኘው ነገሩን ገልጦ አንድ ደንብ አድርጐ በደንከሌዎችና በሱማሌ ያለ ትርፍ በዓመት እንዳገኘው ነገሩን ገልጦ አንድ ደንብ አድርጐ በደንከሌዎችና በሱማሌ ያለ መካከለኛ መንገድ እየጠበቀ ለሁለቱም አገር አላፊ ሆኖ እንዳይጐዳ ደኅንነትን ያደርጋል።

፲፩ኛ። የኢጣሊያ መንግሥት ደግሞ የሸዋ ሰው ከሀገሩ ተነሥቶ ወደ አሰብ በመጣ ጊዜ ለማለፊያ ቤትም ቢፈልግ ለዘወትር የሚቀመጥበት ቤት ለመሥራት አንድ ቦታ አለ ዋጋ ይሰጠዋል።

፲፪ኛ። የሸዋ መንግሥት በኢጣሊያኖች መካከል ገብቶ በነገራቸው ለመፍረድ አይችልም። የኢጣሊያኖችም ነገር ሁሉ በቆንሲላቸው ወይም በተከታዩ /ወኪሉ/ ይፈረዳሉ። እንደዚሁም የኢጣሊያ ቆንሲል በሸዋ መንግሥት መካከል ገብቶ ዳኛ ሆኖ አይችልም። የሸዋ ሰው ሁሉ ነገሩ ባገሩ ገዥ ይፈረዳል።

ደግሞ በሸዋ ሰውና በኢጣሊያ ሰው መካከል አንድ የጠብ ነገር ቢደረግ በሸዋ አገር ባለው የኢጣሊያ ቆንሲል ወይም በወኪል ይፈረዳል። ነገር ግን ያገሩ ገዥ ፍርዱ በሚፈረድበት ጊዜ በፍርዱ ሸንጐ ተቀምጦ ነገሩን እየጠበቀ ያስፈርዳል።

በኢጣሊያ ሰውና ባንድ በሌላ በውጭ አገር ሰው መካከል አንድ ጠብ ቢደረግ በኢጣሊያ ቆንሲል ይፈረዳል። ተከሳሹም ቆንሲል ያለው እንደ ሆነ ግን በቆንሲሉ ይፈረዳል። ቆንሲልም ከሌለው በጭራሽ በኢጣሊያ ቆንሲል ይፈረዳል።

፲፫ኛ። የሸዋ መንግሥት ከኢጣሊያ መንግሥት በአሰብ ላይ ከተሾመው ገዥ ፈቃድ ጠይቆ ወደ አውሮጳ ነገሥታት መተዋወቅና አንዳንድ ዕቃ ማስመጣት ደብዳቤውም መጻጻፍ ይችላል። እንደዚህም መሆኑ በአስብ ለተሾመው የኢጣሊያ ገዥ አስታውቆ የጻፈ እንደ ሆነ የሸዋ መንግሥት የላከው ደብዳቤ በዓለም ባሉ ነገሥታት ሁሉ የታወቀና የታመነ እንዲሆን ነው።

ደግሞ በኢጣሊያ መንግሥት ጥግነት ተመሥርቶ በሥልጣኑና በፈቃዱ የተስማማ እንደ ሆነ የተስማማው ነገር እርግጠኛ ሆኖ ይገኛል።

የሸዋ ሕዝብም አንድ ነገር ወደ አውሮጳ ለመላክና ከአውሮጳ ለማስመጣት ቢፈልጉ እንደ መንግሥታቸው አስቀድመው ከኢጣሊያ ቆንሲል ፈቃድ ጠይቀ በሥልጣኑና በጥገኝነቱ ለመላክና ለማስመጣት ይችላሉ። ራሳቸውም በሄዱ በየሄዱበት አገር በኢጣሊያ ሥልጣን ይጠበቃሉ።

፲፬ኛ። ሁለቱ አገሮች በንግድ እየተመላለሱ በመልዕክትም እየተስማሙ ያገር ልማትና ፍቅር ያደርጋሉ። ከዚያም በኋላ ከሁለቱ አንዲቱን አገር መንግሥትን የሚጠቅም አንዳንድ የበለጠና የተከበረ ዕቃ ላንዲቱ አገር ትሰጣለች። ደግሞ መሣሪያና ሌላም እንደዚሁ የመሰለ የተከለከለ የንግድና ሌላም የሚጠቅም ዕቃ ሁሉ ያለ ችግር ያለ ጭንቅ፣ ያለ ፍርሃት ካንዲቱ አገር ወደ አንዲቱ ለመተላለፍ ይችላል።

፲፭ኛ። የኢጣሊያን መንግሥትና የሸዋን መንግሥት የሚያጣላ አንድ በመካከላቸው የተገኘ እንደ ሆነ በወንድሞቻቸው /ባልንጀሮቻቸው/ ነጋዴዎች ይገላገላሉ። የማይቻል የሆነ እንደሆነ ግን በሥርዓት ወደ መካከለኛ ዳኛ ይቀርባል። እርሱም መካከለኛ ሆኖ ሁለቱንም በትክክል ያስታርቃቸዋል። በዚህም የማይስማሙ ቢሆኑ በሁለቱም ወገን ወደ ታመነና ወደ ታወቀ ባለሥልጣን ትልቅ ዳኛ ቀርበው እርሱ በፈረደው ፍርድ ነገሩ ይጨረሳል።

፲፮ኛ። ይህ ውል በአማርኛና በኢጣሊያ ቋንቋ ተጽፎ ይኖራል። ሁለቱም መዝገብ በሁለቱ ቤተ መንግሥቶች ይቀመጣል።

የሁለቱም አገር መኳንንቶች ይህንኑ መዝገብ ይዘው በሆነው ነገር ሁሉ በፍጹም እየተማሙ በትክክል ነገሩን በሰላም ለመቋቋም ይችላሉ።

፲፯ኛ። ይህ ውል ከተጻፈበት ጀምሮ አሥር ዓመት ድረስ የጸና ይሆናል። ከአሥር ዓመት በኋላም ከሁለቱ መንግሥት አንዱ ለማደስ ቢፈልግ ካንድ ዓመት በፊት የፈለገውን ነገር ገልጦ ላንዱ መንግሥት ያስታውቃል። ዓመቱም ሲጨረስ ሁለቱ ባንድነት ሆነው ነገሩን መርምረው ለማደስ ይችላሉ።

፲፰ኛ። ይህ ውል በሸዋ ታውቋል። እንደዚሁ ደግሞ ወደ ሮማ በቶሎ እናስታውቃለን።

በሆነውም ነገር እስከ ፤ ወር ሳይታወቅ እንዳይቆይ እናደርጋለን። ለዚሁም ለ፲፰ቱ ክፍል ውል ንጉሥ ምኒልክና ፔዬትሮ ኮንት አንትኔሊ በግንቦት ፲፬ ፲፰፻፸፫ ዓመተ ምሕረት በአንኮበር ላይ ተፈራርመዋል። ኮንት አንቶሊኔም በኢጣሊያ መንግሥት ስም ሆን የንግድና የወዳጅነት አስመስሎ በሸዋ መንግሥት ላይ ትልቅ ጉዳት የሚያወጣውን ይህን ውል ከተፈራረመ በኋላ በልጥ ማረፊያ ቦታ ሶስት ወር ያህል ቆይቶ በመጣበት በአውሳ (በአፋር) መንገድ ወደ ኢጣሊያ ተመለሰ።

አጼ ዮሐንስም ንጉሥ ምኒልክና ኮንት አንቶኔሊ አንድ ውል መዋዋላቸውን በሰሙ ጊዜ እጅግ አድርገው አዘኑ። ከማዘናቸውም የተነሣ «ከኢጣሊያ መንግሥት ጋራ መዋዋላቸው እኔን የጐዱ መስሏቸው ይሆናል። እኔ ግን የምታመነው በእግዚአብሔርና

በእምነ ጽዮን ስለ ሆነ የነሱ መዋዋል ምንም አይጐዳኝም። ዳሩ ግን የጫሩት እሳት የኋላ ኋላ ንጉሥ ምኒልክን ሳይፈጃቸው አይቀርም» የሚል እንደ ትንቢት የመስለ ቃል ተናገሩ ይባላል።

ቢሆንም ሰው ሆኖ የማያስብና የማይሰጋ የለምና «የንጉሥ ምኒልክ አሳብ በእኔ ላይ እንደዚህ ከሆነ በእንግሊዝ መንግሥት አማካይነት ከምስሮች ጋራ ተዋውዬ ንጉሥ ምኒልክ እንዲቀኑና እንዲያዝኑ አደርጋለሁ» ብለው በሰኔ ፳፫ ቀን ፲፻፸፱ ዓመተ ምሕረት ከምስሮች ጋር የንግድና የወዳጅነት ውል ተጻጽፈው በአድዋ ከተማ ተፈራረሙ።

በዚያን ዘመን የደርቡሽ ጦር ቱርኮችን ስለ አስጨነቃቸው ከመተማ እየወጡ ወደ ምጥዋ ሲሄዱ አጼ ዮሐንስ እርዳታ እንዲያደርጉላቸው በእንግሊዝ አማካይነት ምስሮች ስለለመኗቸው የሚቻላቸውን ሁሉ እያደረጉ በመርዳታቸው ምስሮች በአጼ ዮሐንስ ወዳጅነት ለጊዜው በታም ደስ ብሏቸው ነበር።

# ምዕራፍ ፴፫

## ስለ አፄ ዮሐንስና ስለ ምስሮች /ስለ ግብፆች/ ጦርነት።

የኢትዮጵያ የምስር /የግብጽ/ ነገሥታት ከቀድሞ ከፈርዖኖች ዘመናት ጀምሮ በአገር መፋለም እየተጣሉ ጦርነት ያደርጉ ነበር። በዚህም በሚያደርጉት ጦርነት አንዳንድ ጊዜ ኢትዮጵያውያን እያሸነፉ የላይኛውን ምስርን ሁሉ ይገዙ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ምስሮቹ ኢትዮጵያን እያሸነፉ እስከ ደጋው ኢትዮጵያ ድረስ ይገዙ ነበር።

ከአፄ ዮሐንስም ዘመን አስቀድሞ ምስሮች ከምጥዋ ጀምሮ የባሕሩን ዳር ሁሉ እስከ ሐረርጌ ድረስ ይዘውት ነበር። ዋና አሳባቸው በነጭ ዓባይ በኩል ብዙ ወታደሮች ካሰናዱ በኋላ በትግሬም (የትግራይም) በሐረርም በኩል ኢትዮጵያን ከበው ወደ መኻል ኢትዮጵያ ለመግባትና ወደ ምስር እስከሚወርደው እስከ ዓባይ ምንጭ ለመድረስ ነበር ይባላል።

በምጥዋም ያለው የምሥራቅ ሱዳን ገዥ አድርገውት የነበረው የስዊዘርላንድ ሰው ዊነር ሙሲንጀር /ሙዚንገር/ የሚባለው ቦጐስ የሚባለው አገር እንዲይዙ ስለ መከራቸው ከምጥዋ መጥተው ይዘውት ነበር። ይህንንም ማድረግ ሳይበቃቸው ስለቀረ ምናልባት ቦጐስን የለቀቅን እንደሆነ እንዳያገኘን ሐማሴንንም መያዝ ያስፈልገናል ብለው ለመያዝ ገና ሲሰናዱ አጼ ዮሐንስ ሰምተው በኅዳር ወር በሺ፲፻፷፯ ዓመተ ምሕረት

ዘመቱባቸው። የቦጐስ ገዥ ልጅ የነበሩት ራስ ወልደ ሚካኤልም ለአጼ ዮሐንስ ረዳት ሆነው ነበርና በመረብ አጠገብ ጉንዳጉንዲ በሚባል ሥፍራ ጦርነት ገጥመው ለወሬ ነጋሪ አንድ እንኳ ሳያመልጥ ሁሉንም ፈጅተው ወደ አድዋ ተመለሱ።

የምስርም ከደዊ (ኬዲቭ) ወታደሮቹ ድል ሆነው ማለቃቸውን በሰማ ጊዜ ብድር ለመመለስ ብሎ ባመቱ ከፊተኛው የሚበልጡ ፲፬ ሺ ወታደሮች አሰናድቶ ሰደደ።

አጼ ዮሐንስም የምስር ከደዊ (ኬዲቭ) ሌሎች ወታደሮች አሰናድቶ መሰደዱን ሰምተው ተጠንቅቀው ይጠብቁት ነበርና በመጋቢት ፲፯ ቀን በሺ፰፻፷፰ ዓመተ ምሕረት ጉራዕ ላይ ሲደርስ አደጋ ጥለው ድል አድርገው ፈጁት። የጦር አለቃ የነበረው ሐሰንና ሌሎች ሹማምንቶች ተማረኩ።

ከዚህም በኋላ አጼ ዮሐንስ ልብስ መንግሥት ለብሰው በመንበረ መንግሥት ተቀምጠው የምስሮች ምርኮኞች ሁሉ እየታሰሩ በፊታቸው ሲያልፉ ሐሰንና ባዩ ጊዜ ወደዚህ አቅርበው ብለው በእጁ ላይ የመስቀል ምልክት አስነቀሱበት።

አጼ ዮሐንስም ለክርስቲያ ሃይማኖት ቀናዒ በመሆናቸው ለጊዜው በአሳባቸው ይህን አደረጉ እንጂ እርሱ ግን ወደ ሀገሩ ሲመለስ የመስቀሉን ንቅሳት ባንድ ምክንያት ሳያጠፋው አይቀርም።

በዚህም ጦርነት ፵ መድፍና ፳ ሺህ ጠመንጃ ከብዙ ጥይት ጋራ ተማርኮ ነበር። ነገር ግን ምስሮች ድል ሆነው ቦጐስን በጭራሽ ለቀቁት ተብሎ ቢወራ ውርደቱን ስለ ፈራ እንደ ገና አጼ ዮሐስን ተለማምጠው «በያመቱ ስምንት ሺህ ብር ግብር እየተሰጠን እንደ ገባር ሆነን እንቀመጥ ይፍቀዱልን» ብለው ስለ ለመኑ ለጊዜው ተፈቀደላቸው።

ደግሞ ያው ዊነር ሙሲንጀር /ሙዚንገር/ የሚባለው ምስሮች በታጁራ በኩል ወደ ወሎ እንዲሄዱና በዚያ አውራጃ ያለውን የእላሙን አገር እንዲይዙ ስለ መከራቸው ፬፻ የሚሆኑ የሱዳን ወታደሮችን ስንቅ ጨምረው ሰጡትና አለቃ ብሩ የሚባለውን ከአጼ ዮሐንስ አስከድቶ የግራዝማች ዮሴፍን ወንድም ገብረ ሥላሴ ንጉሤ የሚባለውን አስተርጓሚ አድርጎ በባሕሩ ዳር እየተጓዘ ሲሄድ ከመሐመድ አንፋሪ አገር በደረሰ ጊዜ መሐመድ አንፋሪ የንጉሥ ምኒልክ ወዳጅ መሆኑን ያውቅ ነበርና መድፍና ጠማንጃ ይዘን ወደ ንጉሥ ምኒልክ እንሄዳለን እያለ በአለቃ ብሩ አፍ ያስወራ ጀመር።

መሐመድ አንፋሪም ይህን ነገር በሰማ ጊዜ «እንደዚህማ ከሆነ ንጉሥ ምኒልክ አስቀድመው ሳይልኩብኝ መቼ ይቀሩ ነበር? ስለዚህ ወደ ንጉሥ ምኒልክ እንሄዳለን ማለታችሁ በሐሰት ነው። እንዲያውም ሰላዮች ትመስላላችሁ» ብሎ ዊነርን ሙስንጀርንና /ሙዚንገርንና/ አለቃ ብሩን ከነተከታዮቻቸው በጩቤ እየቆራረጠ ገደላቸው። ገብረ

ሥላሴ ንጉሤ ግን እንደ ምን እንዳመለጠ ሳይታወቅ ወደ ታጁራ ሄዶ ላገኘው ሰው ሁሉ የሆነውን ነገር ተናገረ።

አንዳንድ ሰዎች አለቃ ብሩን ከአጼ ዮሐንስ አስከድተው ሙሲንጀር /ሙዚንገር/ ባሻን ይዞ ወደ ሸዋ እንዲመጣ ያደረጉ ንጉሥ ምኒልክ ነበሩ። ነገር ግን ባለ መጠንቀቅ ለመሐመድ አንፋሪ ሳያስታውቁት ስለ ቀሩ ይህ ሁሉ አደጋ ደረሰባቸው እያሉ ይናገራሉ የዚህንም እውነቱን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ እውነት ወይም ሐሰት ነው ብለን ለመፍረድ አንችልም።

ከዚህም በኋላ የእንግሊዝ መንግሥት በምስሮችና በአጼ ዮሐንስ መካከል ሆኖ ለማስታረቅና ጠቡን ለማብረድ ስለ አሰበ ጐርዶን ባሻ የሚባለውን የሱዳንን ዋና ገዥ ወደ አጼ ዮሐንስም ልኮ ሰደደው።

ጐርዶን ባሻም ወደ አጼ ዮሐንስ ቀርቦ የእርርቁን ነገር ቢያነጋግራቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ግዴታ እንዲገቡላቸው ጠየቁ።

፩ኛ። ምስክሮች የምጥዋን በር በሙሉ እንዲለቁላቸው ጠየቁት።

፪ኛ። የምጥዋን በር በሙሉ ለመልቀቅ የማይቻል ከሆነ እንደ ሆነ ግን ለዕቃ መውጫና መግቢያ ከምጥዋ በር አንድ ክፍል እንዲሰጡዋቸው።

፫ኛ። ቀድሞ የኢትዮጵያን ግዛት የነበረውን ኋላ በአጼ ቴዎድሮስ ዘመን ቱርኮች የወሰዱትን የኢትዮጵያን መሬት እንዲመልሱ።

፬ኛ። በጉንዳጉንዴና በጉራዕ ስለ ተደረገው ጦርነት ምስሮችን ካሣ እንዴከፍሉ ነው።

ይህም አራቱ ነገር የሚፈጸም የሆነ እንደ ሆነ ዕርቁን እታረቃለሁ የሚል ምላሽ ቢሰጡት ይቅርና የተላኩትንም ጉዳይ ጨርሶ ሳይነጋገር በቁጣ ተነስቶ ወደ ሀገሩ ተመለሰ።

# ምዕራፍ ፴፯

## በአፄ ዮሐንስና በእስላሞች መካከል ስለ ተነሣው ሁከት።

በሺ፰፻ ዓመተ ምሕረት ከተነሣው ከግራኝ መሐመድ ጦርነት ጀምሮ በኢትዮጵያ የእስላም ሃይማኖት እየበዛና እየሰፋ ሄዶ ነበር። ይልቁንም በወሎ አውራጃና በትግሬ

/በትግራይ/ ዙሪያ ባሉት አገሮች የሚኖሩ እስላሞች በሃይማኖታቸው የጸኑ ፋናቲኮች ነበሩ።

ንጉሥ ምኒልክ በሀገራቸው የሃይማኖት ሁከት እንዲነሣ አያስቡም ነበርና በወሎ ግዛታቸው ውስጥ የሚኖረውን እስላም እንደ ሃይማኖቱ ጠብቀው ያኖሩት ነበር። አጼ ዮሐንስ ግን በ፲፰፻፸ ዓመተ ምሕረት ሸዋ መጥተው ሲመለሱ ስለ ሁለት ልደትና ስለ ሃይማኖት በወሎ አውራጃ በቦሩ ሜዳ ላይ ክርክር ካደረጉ የዚህ ነገር ከተጨረሰ በኋላ እስላምን ምን ማድረግ ይሻላል? ብለው ላንዳንድ ያልተማሩ መነኮሳት አሳባቸውን በገለጡላቸው ጊዜ እያስተማርን እብፈቃዱ ወደ ክርስቲያን ሃይማኖት እንዲመለስ እናደርገዋለን በማለት ፈንታ ወደ ክርስቲያን ሃይማኖት ገብተው ያልተጠመቅህና ያልቆረብህ እስላም ሁሉ ትቀጣለህ የሚል አዋጅ ይንገሩ ብለው ስለ መከርዋቸው በዚህ ነገር እግዚአብሔርን ደስ የሚለው መስሏቸው የመነኮሳቱን ምክር ተከትለው ባገሬ በኢትዮጵያ የምትኖር እስላም ሁሉ ወደ ክርስቲያን ሃይማኖት እየተመለስህ ሳትጠመቅና ሳትቆርብ የቀረህ እንደ ሆነ ትቀጣለህ የሚል አዋጅ በ፲፰፻፸ ዓመተ ምሕረት አስነገሩ።

መከራውን የፈሩት እስላሞች በልባቸው ሳያምኑ ባፋቸው ብቻ አምነናል እያሉ ተጠመቁ። ሥጋ ወደሙም ከተቀበሉ በኋላ በስውር ካፋቸው እያወጡ እስከ መጣል ደረሱ። መከራውን ያልፈሩ እስላሞች ግን ክርስቲያን ከመሆን ሞት ይሻለናል እያሉ እኩሉ በሞት፣ እኩሉም በእሥራት እኩልም በመወረስ እኩሉም ካገር እየወጡ በመሰደድ ተቀጡ። ከነዚሁም ጉልበት ያላቸው ወደ ምስር ወደ መተማ ደርቡሽ ወደ ዓረብ አገርና ወደ ሌላውም ወሬው ለአጼ ዮሐንስ ወደ ማይሰማበት አገር ተበተኑ። በየተበተኑበትም አገር ሆነው ለአጼ ዮሐንስ ጠላት የሚሆን ይፈልጉ ጀመር።

ወደ ምስርም የወረዱት ወደ ከደዊ /ኬዲቭ/ እየገቡ ግፋቸውንና ችግራቸውን ሁሉ በነገሩት ጊዜ የእስክንድርያውን ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስን አስጠርተው በቀድሞ ዘመን አይሁድና ክርስቲያኖች ባንድነት ሆነው በዓረብ አገር የሚኖሩትን እስላሞች ባስጨንቋቸው ጊዜ እስላሞቹ እየተሰደዱ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ነበርና በዚያ ዘመን የነበረው የኢትዮጵያ ንጉሥ በመልካም አቀባበል ተቀብሎ የማረፊያ ሥፍራ እየሰጠ በደስታ እንዲኖሩ ማድረጉን በታሪክ እንሰማ ነበር። ያሁኑ የኢትዮጵያ ንጉሥ አጼ ዮሐንስ ግን ባገሩ ውስጥ በሚኖሩ እስላሞች ላይ ልዩ ልዩ መከራ እያመጣ ስለ አስጨነቃቸው እርዳታ ለምነውልኛልና የአደራ ደብዳቤ ጽፈው ይላኩበት» ብሎ ቢነግራቸው ገዥያቸው ነውና ፈርተው «እባክህ ልጄ ሆይ! ልባገርህ ውስጥ የሚኖሩት እስላሞች በወደዱት ሃይማኖት እንዲኖሩ አድርግልኝ» የሚል ደዳቤ ጽፈው ወደ አጼ ዮሐንስ ላኩ። አጼ ዮሐንስም ደብዳቤውን ካዩ በኋላ ለንጉሥ ምኒልክ ለማስታወቅ ሲሉ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል በደብዳቤ ጻፉላቸው።

«መልእክት ዘሥዩመ እግዚአብሔር ቀጥሎ ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ይድረስ ከንጉሠ ነገሥት ምኒልክ በአማን እስራኤላዊ ዘአልቦ ጽልሁት ሰላም ለከ ወሰላመ እግዚአብሔር የሃሉ ምስሌከ። እኔ በእግዚአብሔር ቸርነት በእምነ ጽዮን አማላጅነት አምላክ ቅዱሳን ይክበር ይመስገን ደህና ነኝ። ምሕረቱ ለዘላለም ነውናና»

«ይህ እስላም ኃይል ቢያጣ ነው እንጂ ተንኮሉን አልተወንም። ይህም ሊታወቅ የምስሩ ከደዊ /ገዥ/ ሊቀ ጳጳሳቱን ጠርቶ ምነው የእናንተ ልጆች እስላሙን ሃይማኖትህን ትተህ በእኛ ሃይማኖት ግባ እያሉ ካለ ፈቃዱ ያስቸግሩታል?» ብሎ ነግሮአቸው ኑሮ ሊቀ ጳጳሳቱ «ምነው ልጄ ብትተውልኝና በየወደደው ሃይማኖት ቢኖር። ከዚህ ያለነው አባቶችህ እንዳንቸገር» ብለው ላኩብኝ። እንደዚህም ማለታቸው የወዲያኞቹን እስላሞች ነገር ፈርተው ነው እንጂ እስላሙ ወደ ክርስትና ቢመለስ ጠልተው አይደለም።

እኛም እንግዴህ ይህ ስለሆነ የተመለሰውም እንዲጸና ያልተመለሰውም እንዴመለስ በረቂቅ እያደረግን ሥራችንን እንዳንፈታ ይሁን። ተጽሕፈ በአስመራ ከተማ አመ. ፱ ለሚያዝያ በ፲ወ፰፻ወ፭ ዓ.ም።»

አጼ ዮሐንስ የእስላም ሃይማኖት እንዲጠፋ አስበው የተነሡበት ጉዳይ ስለሆነ ባንድ ወገን የአቡነ ቄርሎስ ልመና እንዳይቀርባቸው በሁለተኛው ወገን እስላም ሳይማር በግድ እንዲያምንና እንዲጠመቅ የነገሩት አዋጅ እያፈርስባቸው በረቂቅ እያደረግን ሥራችንን እንዳንፈታ ይሁን የሚል ደብዳቤ ለንጉሥ ምኒልክ ጻፉላቸው።

የዚህም ትርጓሜ ወደ ክርስቲያን ሃይማኖት የማይመለሰውን እስላም ላይ ላዩን በሌላ ምክንያት እያስመለስን ውስጥ ውስጡን ግን ስለ ሃይማኖት እያደረግን እስላሙን ማስጨነቃችን እንዳይቀር ይሁን ማለት ነው።

አጼ ዮሐንስ የአቡነ ቄርሎስ የልመና ደብዳቤ በመጣባቸው ጊዜ ለማድረግ የሚገባቸው ልመናቸውን ተቀብለው እስላሙ ሁሉ በየሃይማኖቱ በነፃ እንዲኖር ማድረግ ወይም የአዋጃቸውን ቃል አጽንተው አልጠመቅም ያለውን መቅጣት ነበር እንጂ በረቂቅ እያደረግን ሥራችንን እንሥራ ማለትና በሌላ ምክንያት እያስመሰሉ እስላሙን መቅጣት ትክክለኛ የንጉሥ ሥራ ነው ማለት አይቻልም።

ደርቡሾችም ባንድ ወገን አጼ ዮሐንስ ለእንግሊዞችና ለምስሮች ረድተው ቱርኮችን በመቀበላቸውና ባገራቸውም በኢትዮጵያ እያሳለፉ ወደ ምጥዋ ስለ መስደዳቸው በሁለተኛውም ወገን የሃይማኖት ወንድሞቻቸውን በኢትዮጵያ የሚኖሩትን እስላሞች ስለ ማስጨነቃቸው የከፋት ብድር ለመመለስ ሲሉ ከመተማ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት እየወጡ አገር ማጥፋት ቤተ ክርስቲያን ማቃጠል ጀመሩ።

አጼ ዮሐንስ እስላሞችን ወደ ክርስቲያን ሃይማኖት ለመመለስ ትቀጣለህ ብለው አዋጅ መንገራቸውና መቅጣታቸው ቀርቶ በትምህርትና በፍቅር አድርገውት በነበረ ትምህርትና ፍቅር የማይሰበው የለምና በፈቃዳቸው እያመኑ ይጠቁሙ ነበር። በመንግስታቸውና በራሳቸው ላይ ጠላትና ባላጋራ አይነሣባቸውም ነበር።

# ምዕራፍ ፴፪

## ንጉሥ ምኒልክ እንደ ገና ወደ ወሎ ስለመሄዳቸው።

ንጉሥ ምኒልክ በ፲፰፻፸፪ ዓመተ ምሕረት ከዋያት በመለስ ያለውን ሠራዊታቸውን ሰብስበው የእንጦጦን ከተማ ሲያድሱ ቆይተው ወደ ደብረ ብርሃን ወጥተው ነበርና በዚያ ምታ ነጋሪት! ይከተት ሠራዊት! ብለው አዋጅ አስነግረው በግንቦት ፲ ቀን ተነሥተው ወደ ወሎ ተጓዙ።

ምክንያቱም በዚሁ ዘመን የእንግሊዝ ንግሥት የግርማዊት ቪክቶሪያ መላክተኛ አድሚራል ሰር ውሌም /ዊሊያም/ ሂወት የሚባል መጣ ስለ ተባለ አጼ ዮሐንስ ከደርበ ታቦር ወደ ትግሬ /ትግራይ/ ሲወርዱ ምናልባት የእንግሊዝ ንግሥት መላክተኛ በስተኋላ ጦር አስከትሎ መጥቶ ይሆናል በማለት ስለሠጉ መመጣቱን ለንጉሥ ምኒልክ ደብዳቤ አስታውቀዋቸው ነበርና ጦርነት የተደረገ እንደ ሆነ ለአጼ ዮሐንስ ለመርዳት ነበር። በስተኋላው ጦር አለማስከተሉ ከታወቀ በኋላ ግን የትግሬ /የትግራይ/ አገር ለሁላችን ስንቅና ለከብት ሣር ለመስጠት አይችልምና የንጉሥ መከረሚያ ወሎ ላይ ቢሆን ይሻላል የሚል የአጼ ዮሐስንስ ደብዳቤ ስለ መጣ ንጉሥ ምኒልክ ወሎ ቦሩ ሜዳ ላይ ለመከረም ቁርጥ አሳብ አደረጉ።

አድሚራል ሰር ውሌም /ዊሊያም/ ሂወትም አመጣጡ አማካይ ሆኖ አጼ ዮሐንስንና ምስሮችን ለማስታረቅ ነበርና እርሱ ስለ እንግሊዝ ንግሥት ስለ ግርማዊት ቪክቶሪያ፣ ማሰን ቢ ስለ ምስር ከደዊ /ኬዲቭ/ ስለ መሐመድ ቶውፊቅ ሆኖ ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ በራሳቸው ስም ሆነው ፍሬ ነገሩ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ውል ተዋዋሉ።

፩ኛ። በምጥዋ በር ወደ ኢትዮጵያ የሚገባውና ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር የሚወጣው ማናቸውም ዕቃ ጠመንጃና ጥይትም በነፃ ይተላለፋል።

፪ኛ። ምስሮች የቦጐስን አገር በጭራሽ ለቀው በዚያውም ያለውን ዕቃና የጦር መሣሪያ ሁሉ ለንጉሠ ነገሥት ያስረክባሉ።

፫ኛ። በከሰላ ያሉት የምስር ወታደሮች በኢትዮጵያ ግዛት ያለ ችግር ወደ ምጥዋ እንዲያልፉ ጃንሆይ ንጉሠ ነገሥት ፈቅደዋል።

፬ኛ። ጃንሆይ ንጉሠ ነገሥት ከምስር አገር ጳጳስ ሲያስመጡ የምስር ከደዊ (ኬዲቭ) ምንም ችግር እንዳያደርግ ውል ገብቷል።

፭ኛ። ወንጀል የሠሩ ሰዎች እየሸሹ ካንዱ ግዛት ወደ አንዱ ግዛት የገቡ እንደ ሆነ ሁለቱም ወገኖች እጃቸውን እየያዙ ለመስጠት ተስማምተዋል።

፮ኛ። ይህን ውል ከተዋዋሉ በኋላ በመካከላቸው የሚነሳው ተብ ሁሉ በእንግሊዝ መንግሥት አማካይነት ይጨረሳል።

፯ኛ። ይህን ውል ግርማዊት የእንግሊዝ ንግሥትና ልዑል የምስር ከደዊ (ኬዲቭ) መቀበላቸውን አድዋ ላይ እናረጋግጣለን።

አሁንም ለጊዜው ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ አትመውበታል። አድሚራል ሰር ውሌም /ዊሊያም/ ሂወትና ማሰን ቢ ፈርመውበታል። ግንቦት ፳፯ ፲፰፻፸፮ ዓመተ ምሕረት /በአውሮጳውያን ሰኔ ፫ ፲፰፻፹፬።/

ይህንም የወዳጅነት ውል ተዋውሎ ሲጨርስ በኢትዮጵያ የባርነት ነገር እንዲቀር ነገሩን ሁሉ ለአጼ ዮሐንስ አስረድቶ ሁለተኛ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ውል ተዋዋለ።

ቪክቶሪያ በጸጋ እግዚአብሔር የታላቋ ብሪታኒያና የአየርላንድ ንግሥት የህንደኬ ቄሣርይት፣ ሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ወኩሉ አድያሚሃ በእንግሊዝ ቤተ መንግሥትና በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት የባርያ ንግድ እንዲቀር። ባርያ እንዳይሸጥ በፈቃዳችን ተዋደን ውል አድርገናል። ለዘላለም በኢትዮጵያና በእንግሊዝ መንግሥት ለነገሠ ይሁን። ነገር ግን ሲጨርስ የመጣ ምስለኔያቸው ሪየር አድሚራል ሰር ውሌም /ዊሊያም/ ሂወት የሕንደኬ የጦር መርከብ ደምሳሽ ነው። ከትልቅ ብሪታንያና ከአየር ላንድ ንግሥት የሕንደኪኤ ቄሣርይት የተላከ።

፩ኛ። ጃንሆይ በግዛትዎ ባሪያ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ሊከለክሉ።

፪ኛ። ጃንሆይ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ባርያ ከሌላ አገርም መጥቶ ከአገርዎም ግዛትዎም እንዳይሸጥ ወደ ሌላ አገር ወጥቶም እንዳይሸጥ ወደው ይህን ውል አድርገናል።

፫ኛ። ጃንሆይ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ነስጻ የወጣውን ባሪያ ማንም ወደ ባርነቱ እመልሰዋለሁ ብሎ የያዘው እንደ ሆነ በብርቱ ቅጣት ሊቀጣ ፈቅደዋል።

፬ኛ። የብሪታንያ ንግሥት ከሌሎች ነገሥታት ጋራ ሁሉ ባሪያ እንዳይሸጥ ቀድሞ ውል አድርጋለች። ስለዚህም በባሕር ያሉ ሹማምንቶችዋን ጠብቁ ብላ አዛለች። በመርከብ ሲሄዱ ባርያ ቢያዝ ወደ ንጉሠ ነገሥት ወደ አገሩ ይመለስ ብላ ንግሥት አዛለች።

፭ኛ። ይህ የዕርቅ ውል ቶሎ ብሎ ታትሞ አድዋ ድረስ ይመጣል። ደግሞ ስለ ምስክርነት ሪየር አድሚራል ስር ውሌም /ዊሊያም/ ሂወት የብሪታኒያ ንግሥት የሕንደኬ ቄሳርት ምስለኔና ሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ነገሥት ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለዚህ ውል ሁለቱም በገዛ እጃቸው ማኅተማቸውን አትመዋል። ተጽሕፈ በአድዋ ከተማ አመ ሣልሱ ልጁን በ፲ወ፰፻፹፬ ዓመተ ምሕረት በእንግሊዝ ቁጥር /በ፲ወ፰፻፸፮ ዓመተ ምሕረት አመ ፳ወ፯ ለሰኔ በኢትዮጵያ ቁጥር።/

ይህንንም ከተዋዋለና ከተፈራረመ በኋላ ተሰነባብቶ ወደ ሀገሩ ተመለሰ። አበጋዝ ሆነው ወረይሉ ላይ ሠፍረው እንዲጠባበቁ ታዘው ነበርና ከራስ ሚካኤል ሰዎች ጋራ በአምባ ጓሮ ተጣልተው ሁለት ሰዎች ቢሞቱባቸው በዚህ የተነሳ ለገሎራንና ለገ ሂዳን አሊ ቤትን እስከ ልጓት ወራሪ ሰደው አገሩን ስለ አጠፉት ንጉሥ ምኒልክ በዚህ ነገር ተቆጥተው ሳይገናኙ ወደ ሸዋ መለሷቸው። እርሳቸው ግን ክረምቱን በወሎ ከርመው እስከ ታህሣሥ ወር ቆይተው ለልደት በዓል እንጦጦ ከተማ ገቡ።

በ፲፰፻፸፰ ዓመተ ምሕረት በኅዳር ወር ራስ ጐበና ከሌቃ መጥተው ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ተገናኝተው ብዙ ግብርና ገፀ በረከት አቀረቡ። በዳር አገር ያሉት ባላባቶች ሁሉ ከጌራ ንግሥት በቀር አንድ ሳይቀር ራስ ጐበናን ተከትለው መጥተው ከንጉሥ ምኒልክ ጋራ ተገናኙ። የጌራ ንግሥትም ያልመጣችበት ምክንያት ልጅዋ ገና ሕፃን ስለ ሆነባት ነበር።

ከዚህም በኋላ ንጉሥ ምኒልክ በአማራውና በሸዋ አገር ብቻ ፲፪ ዓመት ሙሉ ተሠሪ ሆኖ የኖረውን ጐንደሬ ነፍጠኛ የሚባለውን ጭፍራ ለየመኳንንቱ አካፍለው ራስ ጐበና በአቀኑት በዳር አገር ሁሉ ከዚህ እንደሚከተለው ሹም ሽር አደረጉበት።

ለደጃች ወልዴ አሻግሬ ሶዶን አጨበርን ጉራጌን።

ለፊታውራሪ ተክለ ማርያም /ጉልላቴ/ ሜጫን።

ለደጃዝማች ኃይለ ማርያም ወልደ ሚካኤል ቶኬን ቦተርን እስከ ጊቤ ማዶ።

ለደጃች ደስታ ዳርጌ ጨልያን።

ለደጃች በሻህ አቦዬ ጌራን ጉማን።

ለደጃች ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ ሊሙን።

ለደጃች ተሰማ ናደው ጉማን ይሉባቦርን።

የእነዚህም ሁሉ ሰበርና የበላይነት ለራስ ጐበና ሰጡ። ከዚህም በኋላ ራስ ጐበና ወደ ሌቃ ተመልሰው ወርደው ከዚያ ደግሞ በደጃች ጆቴ መሪነት ወደ ዐረብ ሻንቅላ /ቤንሻንጉል/ አገር ዘመቱ።

# ምዕራፍ ፴፫

## አጼ ዮሐንስ ወደ ወሎ ስለ መምጣታቸውና ንጉሥ ምኒልክም ለመገናኘት ወደ ወሎ ስለ መሄዳቸው።

ንጉሥ ምኒልክ ራስ ጐበና ባቀኑት በምዕራብ አገር ሹም ሽር ካደረጉበት በኋላ ፊታቸውን ወደ ደቡብ አገር ወደ አሩሲ ለማዞር አስበው ሳሉ አጼ ዮሐንስ ከትግሬ /ከትግራይ/ ወደ ወሎ መምጣታቸው ስለ ተሰማ ሌላውን አሳባቸውን ሁሉ ትተው ወደ ወሎ ለመሄድ ቁርጥ አሳብ አደረጉ።

አጼ ዮሐንስም ወደ ወሎ የመጡበት ምክንያት የወሎ ገዥ ራስ አርአያ ነበሩና የትግሬ /የትግራይ/ ወታደሮች በየምክንያቱ ባላገሩን እየዘረፉ እስለቅሰውት ነበር። ይልቁንም በክርስትና ምክንያት ካልተጠመቅህ ካልቆረብህ እያሉ ገንዘቡን በግፍ እየወረሱ ግብሩንም ባገሩ ያልተለመደውንና ያልተወሰነውን በግድ አምጣ እያሉ ጥቃትና ውርደት አብዝተውበት ነበር። በዚህም ላይ ደግሞ የተኹለደሬውን ባላባት አመዴ ሰዲቅን በግድ አሰገዱለት። ከሁሉም የባሰ ነገር ንጉሥ ምኒልክ ከአጼ ዮሐንስ ከድተዋል እያሉ ያስወሩ ነበርና በዚህ ሁሉ ምክንያት የወሎ አገር ተናጠ። ስለዚህም አጼ ዮሐንስ ወደ ወሎ ዘምተው እስከ ጨሉና እስከ ኤፍራታ ወረራ ሰደው አስጠፉት። ወደ ሸዋም ለመምጣት ማሰባቸውን ንጉሥ ምኒልክ በሰሙ ጊዜ በጦር ኃይል እመልሳቸዋለሁ እንዳይሉ ሠራዊታቸውን በሹም ሽር ምክንያት በየዳር አገሩ በትነውት ነበርና በቅርብ የተገኘውን ጥቂቱን ሠራዊታቸውን አስከትለው ብዙ ግብርና ገጸ በረከት ይዘው በጥር ወር በ፲፰፻፸፫ ዓመተ ምሕረት ወደ ወሎ ገሰገሱና ኮምቦልቻ ላይ ከአጼ ዮሐንስ ጋራ ተገናኙ።

ንጉሥ ምኒልክም ከአቀረቡት ግብርና ገጸ በረከት የሚበዛው ሡንጋ /የሥጋ ከብት/ ነበርና የትግሬ /የትግራይ/ ወታደር ከንጉሥ ምኒልክ ሠፈር ሡንጋውን እየዘረፈ ወስዶ በየድንኳኑ ያርዱ ጀመር።

አጼ ዮሐንስም ወታደራቸውን ሠንጋ እየዘረፈ ማረዱን በሰሙ ጊዜ በታም ስለ ተቆጡ ሁለት አፍ ግንጥል ጠመንጃቸውን ይዘው በፈረስ ተቀምጠው በሠፈሩ መካከል እየጋለቡና እየተኮሱ ብዙ ሰዎች ገደሉ። ምክንያቱም ለግብር የመጣውን ሠንጋ በኃይል እየወሰዱ ስለማረዳቸው ነው። ሁለተኛውም የሁዳዴ ጾም ገብቶ ነበርና በጾም ለምን ሠንጋ አረዳችሁ ብለው ነው።

ከዚህም በኋላ አጼ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ በነገረ ሠሪ በመካከላቸው የተነሣውን ሁሉ ተገላልጠውና ተነጋግረው ስሕተቱንም አርመው ሲጨርሱ አጼ ዮሐንስ ወደ ዞብል ሄዱ። ምኒልክ ግን በሚያዝያ ወር ለፋሲካ በዓል ወደ እንጦጦ ተመለሱ።

ወዲያውም ተጀምሮ የቆየውን ሹም ሽር ለመጨረስ ለልዑል ራስ ዳርጌ አሩሲን፣ ለደጃዝማች ወልደ ገብርኤል ይቱን /ጨርጨርን/ ሰጥተው የአሩሲ ጋላ /ኦሮሞ/ እጅግ ኃይለኛ መሆኑን ያውቃሉና ራስ ዳርጌን እንዳያቸግራቸው ብለው ባንድነት ዘመቱ። ጋላም /ኦሮሞ/ ምንም እየመላለሰ አደጋ ቢጥል ለማሸነፍ አልቻለምና ለራስ ዳርጌ ከተማ የሚሆን ለጋላ /ኦሮሞ/ ጦር መጠባበቂያ የሚመች አዙሊ የሚባል ሥፍራ መርተው በሰኔ ወር መጨረሻ ወደ እንጦጦ ተመለሱ።

# ምዕራፍ ፴፱

## በአጼ ዮሐንስና በኢጣልያኖች መካከል ጠብ ስለ መጀመሩ

ከኢጣሊያኖች አስቀድሞ ፈረንሳዮች በምጥዋ ቆንሲል አስቀምጠው ነበርና ቆንሲሉ ቢሆንለት የምጥዋን በር ባይሆንለትም በዚያው አጠገብ ያለውን የዙላን በር ለማግኘት ከአጼ ዮሐንስ ጋራ በመላላክ ቃል ለቃልም በመነጋገር የወዳጅነት ሥራ ጀምሮ ነበር። አጼ ዮሐንስ ግን ከቀረበላቸው የውል አሳብ አንድናአዱን ካለመቀበላቸው የተነሣ ማናቸውንም ውል ሳያትሙለትና አሳቡን ሳይፈጽሙለት ቆይተው ነበር።

ንጉሥ ምኒልክም ወደ አጼ ዮሐንስ የተጠጋውን ሁሉ በወዳጅነት እየሳቡ ወገን ለማድረግ ይጣጣሩ ነበርና ከአጼ ዮሐንስ ጋር ወዳጅነት ለጀመረው ለፈረንሳዊ ቆንሲል ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጽፈው ላኩለት።

«የተላከ ከንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ዘኢትዮጵያ። ይድረስ ከቆንሲል ፈረንሳዊ ደርዘክ። እጅጉን እንዴት አሉ? በዝና እኔንም ደህንነት ቢጠይቁ እግዚአብሔር ይመስገን ከነሠራዊቴ ደህና ነኝ። ከዚህም ሰላምታ በኋላ ደብዳቤ ልሰድልዎ አሰብሁኝ። የፍቅር ምልክት። የእርስዎንም ደግነት ርእሰ መማክርት ጊዮርጊስ ነገረኝ። ስለዚህም ነገር

ፍቅርዎን ፈለግሁኝ። ከኤውሮጳ ነገሥታት ሁሉ እንዲያፋቅሩኝ። ብርሃን በኢትዮጵያ እንድትገባ እንዲጥሩልኝ። እኔም በችሎቴ ምክርዎን እሰማማለሁኝ። በክርስቲያን ሥራት ይርዱኝ። በተቻለዎት ሁሉ ደብዳቤዎ አይለየኝ። ነጋዶችንም ሠራተኞችንም በርስዎ ደብዳቤ ሁሉ የመጣውን እቀበላለሁኝ።

ደግሞም ቢሆንልዎ ቤተ መንግሥትን የሚያጠና ተግባር ይፈልጉልኝ። እኔም ወረታዎን እመልሳለሁ። ወደ ፓሪስ የሚሄደውን ወረቀት አይተው ቃሉን አስተርጉመው ያድርሱልኝ። ሌላ አይወቀው። ምላሹ ቶሎ ይምጣልኝ። እግዚአብሔር ለመገናኘት ያብቃን።

በ፲ወ፰፻፸ወ፮ ዓመተ ምሕረት በጥር ፳፬ ቀን ወሎ ሀገረ ምሻ ተጻፈ።»

ንጉሥ ምኒልክ አጼ ቴዎድሮስ ከሞቱበት ከሺ፰፻፷ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ አጼ ዮሐንስ ወደ ሸዋ እስከ መጡበት እስከ ሺ፰፻፸ ዓመተ ምሕረት ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት እያሉ ይጽፉ ነበርና አጼ ዮሐንስ ወደ ሸዋ ከመጡ በኋላ ንጉሠ ነገሥት እያሉ እንዳይስፉ ስለከለከሏቸው ንጉሥ ምኒልክ የዲፕሎማቲክ ዕውቀት ነበራቸውና በምጥዋ ላለው ለፈረንሳዊ ቆንሲል ሲጽፉ የተላከ ከንጉሠ ነገሥቱ ምኒልክ ዘኢትዮጵያ ብለው ጻፉለት እንጂ ምኒልክ ሸዋ ብለው አልጻፉም።

እንግዲህ ወደ መጀመሪያው አሳባችን እንመለሳለን። አጼ ዮሐንስንና የፈረንሳዊ ቆንሲል ባንድነት ቃል ሳይሰማው ቀርተው አንድ ውል እንኳ ሳይጻጻፉና ሳይቀባበሉ በመካከሉ የእንግሊዝ መንግሥት ከምስር መንግሥት ጋር ሁሉ ደርቡሽን ከሱዳን አገር ለማስወጣት ስለ አሰበ፣ በዓባይ ወንዝና በአትባራ ወንዝ ዳር ዳር ብዙ ወታደሮች አስቀምጦ ነበርና ለዚሁ ሥራው ረዳት የሚሆነውን ከፈረንሳዊ ይልቅ ኢጣሊያን መርጦ እኛ በከሰላ በኩል ወደ ምሥራቃዊ ሱዳን መግባታችን ነውና እናንተም ፈረንሳአው ሳይዘው የምጥዋን በር በቶሎ ብትይዙ ይሻላል ብዬ ለኢጣሊያኖች ቢያስታቃቸው ኢጣሊያኖች ከአሰብ በቶሎ አልፈው ቤይሉል የሚባለውን የባሕር ጠረፍ ያዙ።

ከዚህም በኋላ በጥር ፳፰ ቀን ፲፰፻፸፰ ዓመተ ምሕረት የምጥዋን በር ይዘው ወዲያው ምጥዋን የያዝነው በእንግሊዝና በምስር መንግሥት በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ፈቃድ ነው የሚል አዋጅ አስነገሩ። ቀጥለውም ከኢጣሊያ አገር ብዙ ወታደር እንዳመጣና እንዲጨምርላቸው አደረጉ።

በዚያ ዘመን በእንግሊዝና በፈረንሳዊ መንግሥት መካከል የነበረውን ፖለቲካ ለማወቅ አልቻልንምና የእንግሊዝ መንግሥት የምጥዋን በር ከፈረንሳይ ይልቅ ኢጣሊያ እንዲይዘው የወደደበትን ገልጠን ለማስረዳት ባለመቻላችን እናዝናለን።

አጼ ዮሐንስም ኢጣሊያኖች የምጥዋን በር መያዛቸውን በሰሙ ጊዜ እጅግ አዘኑ። ንጉሥ ምኒልክም ኢጣሊያኖች ምጥዋን ይይዛሉ ብለው አላሰቡም ነበርና በጣም ደነገጡ። ይልቁንም በአጼ ላይ ከምስር መንግሥት ጋር የሚላላኩት በምጥዋ በር ነበርና ምጥዋ በኢጣሊያኖች እጅ ከሆነ ከምስር መንግሥት ጋራ ለመላላክ የማይመች መሆኑን ስለ ተረዱትም ነው።

# ምዕራፍ ፵

## ንጉሥ ምኒልክ ወደ ሐረርጌ ስለ መዘመታቸው

ቱርኮች ምስርን ሁሉ ከያዙ በኋላ በኤርትራ ባሕር ዳር ያሉትን አገሮች ሁሉ ሲይዙ ሐረርንም ይዘውት ይኖሩ ነበርና አጼ ዮሐንስ ከቱርኮች ጋራ እየተዋጉ በኢትዮጵያ ሰሜን ያለውን አገር ማስለቀቅ በጀመሩ ጊዜ ንጉሥ ምኒልክም በስተ ምሥራቅ ያለውን ሐረርን ከቱርኮች እጅ እንዲያስለቅቁ አስታውቀዋቸው ነበር።

ንጉሥ ምኒልክም ወደ ሐረር ለመዝመት ባሰቡ ጊዜ በሐረርጌ ያለው የቱርኮቹ እንደ ራሴ አሚር አብዱላሂ የዘመቻውን ወሬ እንዳይሰማና ለጦርነት እንዳይሰናዳ ብለው ዘመቻውን ወደ አሩሲ አስመስለው በኅዳር ፬ ቀን ፲፰፻፸፱ ዓመተ ምሕረት ከእንጦጦ ከተማ ተነሡ። በእየሩሳሌም ዞረው በጨርጨር አድርገው ሲጓዙ በታኅሣሥ ፳፫ ቀን ጨለንቆ ላይ ሠፈሩ።



የሐረር ከተማ



# አሚር አብዱላሂ የሐረር ገዥ

አሚር አብዱላሂም ንጉሥ ምኒልክ ለጦርነት መምጣታቸውን ሰምተው ሠራዊቱን ሰብስቦ የጦር መሣሪያውን አሰናድሮ ይጠብቅ ነበረና በዓለ ልደት እንደ ቀረበ አውቆ ልደት የክርስቲያኖች ትልቅ በዓል ሠንጋ እያረዱና እየበሉ ይበሉ ይጠጡ የሚውሉበት ቀን ነውና ቢሆንም ባይሆንም በልደት በዓላቸው ጦርነት ብገጥማቸው ይሻለኛል ብሎ በታኅሣሥ ፳፱ ቀን ፰ ሰዓት ሲሆን አደጋ ጥሎ ጦርነት ተጀመረ። ጥቂት ሰዓትም እንደ ተዋጋ ብዙ ሠራዊት አስለቀበትና ድል ሆነ። እርሱ ግን በፈረስ ሸሽቶ ወደ ሐረር ገባና ከዚያ ደግሞ ሚስቶቹንና ልጆቹን ይዞ በሌሊት ወጥቶ ሄደ።

ንጉሥ ምኒልክም ከጨለንቆ ተከታትለው ሄደው አቦከር ላይ ሠፍረው ነበርና በማግሥቱ የአሚር አብዱላሂ አጐት አሊ አቡበከርና ዩሱፍ ቦርከሊ፣ ቃዳ አብደላና ሌሎችም ብዙ ሽማግሎች ወደ ንጉሥ ምኒልክ መጥተው አሚር አብዱላሂ በሌሊት ወጥተው ሄደዋልና ግንቡን /ከተማውን/ ይረከቡን እንጂ ሕዝቡን በከንቱ እንዳያጠፉት

እንለምናለን ብለው ተናገሩ። ንጉሡም ይህን በሰሙ ግዚኤ ለዕቃውና ለከተማው መረከብ በጅሮንድ አጥናፌን፣ የከተማውን በር ለመጠበቅ የሻቃ ተክሌን ባላምባራስ ዳምጠውን የሻቃ አድጐን የሻቃ ገበየሁን አዘው በ፫ቱ በር ሁሉ የኢትዮጵያ ባንዲራ እንዲቆምበት አደረጉ።

በ፫ኛውም ቀን ልብሰ መንግሥት ለብሰው ሠራዊታቸውን አሰልፈው የመድፍና የጠመንጃ ግባት እየተተኮሰ ወደ ሐረር ከተማ ገቡ። የከተማውም ሕዝብ ገንዘብ እንዳይዘረፍበት የሚጠብቁ ዘበኞች አዝዘው ነበር።

## ስለ ሐረር ከተማ ጥንታዊነት

የሐረር ከተማ በሺ፩፻ ዓመተ ምሕረት ከተነሣው ከግራኝ መሐመድ አስቀድሞ የተሠራ ነው። ምንም እንኳ ሥፍራው ጐድጓዳ ቢሆንም በቀኝና በግራ ፈሳሽ ውሃ ስላለበትና በዙሪያውም ላይን የሚታየው ሥፍራ ሁሉ ለምለም አታክልት ስለሆነ ደስ ያሰኛል። ለጤናም የተስማማ ነው።

ንጉሥ ምኒልክም የሐረርን ከተማና ግዛቱንም ሁሉ እጅ ካደረጉ በኋላ ወደ ሸዋ ለመመለስ ባሰቡ ጊዜ በሐረርጌ ተሾሞ ለመቅረት መኳንንቱን ደስ እንዳይላቸው ስለ ጠረጠሩ በተዘዋዋሪ እያደረጉ ቢያስታውቋቸው በግድ ካልሆነብን በዚህ በእስላም አገር ላይ ተሾመን ለመቅረት ፈቃድ የለንም እያሉ ተናገሩ ይባላል።

በኋላ ግን ንጉሡ ባላምባራስ መኮንን ለብቻ አድርገው «እዚህ ሾሜ በተውህ ይከፋሃል ወይ?» በልው ቢጠይቋቸው «የጌታዬ ፈቃድ ከሆነ ደስ ይለኛል እንጂ ለምን ይከፋኛል?» ቢሏቸው በእምነት ለማገልገል የቆረጡ መሆናቸውን ስለ ተረዱ በጥር ፳ ቀን ፲፰፻፹፱ ዓመተ ምሕረት ነጋሪት አስወጥተው «ሐረርጌን ለልጅ ለወዳጄ ለደጃዝማች መኮንን ሰጥቸዋለሁ» ብለው አዋጅ ነገሩላቸው።

ከዚህም በኋላ በሐረርጌ ከተማ ዙሪያ እየተዘዋወሩ አንድ ወር ያህል ቆይተው የአሚር አብዱላሂ የነበሩትን ሁለት ትልልቅ መድፎችና ሁለት ሚልዮን የሲናድር ጥይት አስጭነው በየካቲት አንድ ቀን ተነስተው ወደ ሸዋ ተጉዘው በየካቲት ፳፰ ቀን እንጦጦ ከተማ ገቡ።

# ምዕራፍ ፵፭

## ራስ አሉላ ከኢጣልያኖች ጋራ ተዋግተው ድል ስለ ማድረጋቸው

ኢጣሊያኖች ምጥዋን ስለ መያዛቸው አጼ ዮሐንስ በጣም ተናደው ነበርና ራስ አሉላ የእናታቸው የኢትዮጵያና የጌታቸው የአጼ ዮሐንስ ፍቅር ስለ አደረባቸው በምጥዋ ላለው ማርኮፖሎ ቤይ ለሚባለው ለቱርኮች እንደራሴ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጻፉለት።

## የተላከ ከራስ አሉላ ዝውእቱ ቱርክ ባሻ።

«ይድረስ ከክቡር ማርኮፖሎ ቤይ። ኢጣሊያኖች መጥተው ምጥዋ ሲገቡ ለምን ዝም አላችኋቸው? ይህም አመጣጣቸው በምስር ከደዊ (ኬዲቭ) ፈቃድ እንዳልሆነ በኢትዮጵያና በምጥዋ መካከል ያለውን መንገድ እኔ እዘጋዋለሁ። እናንተስ ለምን ፈቃድ ሰጣችኋቸው? ባገሩ ዋና ሰው የለበትምና ወደ ፊት ለመያዝ እንዳይመቻቸው አባሩዋቸው! ይህችም ሥፍራ የኢትዮጵያ ግዛት መሆኑና ኢጣሊያኖችም እንዲቀመጡባት አለፈቀደኡን በስመ ነገሥት ዮሐንስ አስታውቃችኋለሁና ወደ ሀገራቸው ይመለሱ። ሐምሌ ፫ ቀን ፲፰፻፸፰ ዓመተ ምሕረት።»

ራስ አሉላ በእግንሊዝ መንግሥት አማካይነት ቱርክና ኢጣሊያ መስማማታቸውን ዘንግተው ለቱርኮች እንደራሴ ለማኮአፖሎ ቤይ ይህን ደብዳቤ ጻፉለት እንጂ ኢጣሊያኖችስ ምጥዋን መልቀቃቸው ይቅርና እድነ ገና ከኢጣልያ አገር ብዙ ወታደሮች መጥተው እንዲጨመሩላቸው አደረጉ።

ራስ አሉላም በዚህ ነገር እጅግ ስለ ተናደዱ አገራችንን ልቀቁ የሚል ደብዳቤ ጽፈው በቀጥታ ጄኔራል ጄኔ ለሚባለው በምጥዋ ላለው ለኢጣሊያ ሹም ቢልኩለት ምጥዋን ለቀን ለመሄድ ከመንግሥታችን አልታዘዝንም» የሚል ምላሽ ጻፈላቸውና ወዲያው በፍጥነት ወደ ሰሐጢ ወጥቶ እርድ ይሠራ ጀመር።



ራስ አሉላ አባነጋ የዶጋዓሊው ባለድል

ራስ አሉላም ጄኔራል ጄኔ የጻፈላቸውን ደብዳቤ አይተው «እኛ ከኢጣሊያኖች ጋራ ጠብ ለማንሣትና ለመዋጋት አላሰብንም ነበር። እነሱ ፈለገውና ጠብ አንሥተው ከመጡ ለምን ዝም ብለን እንጠብቃለን» ብለው ሠራዊታቸውን በአዋጅ እንዲሰብሰብ

አደረጉ። ከዚህም በኋላ ወደ ሰሐጢ ወርደው በጥር ወር በ፲፰፻፸፱ ዓመተ ምሕረት ዶጋዓሊ በሚባል ሥፍራ ላይ በኢጣሊያኖች ላይ አደጋ ጥለው ፈጁአቸው።

አጼ ዮሐንስም ራስ አሉላ ከኢጣሊያኖች ጋራ ተዋግተው ድል ማድረጋቸወን በሰሙ ጊዜ «ይህ ጦርነት የተደረገው በራስ አሉላ መቸኮል ነውና ወደ ፊት በመካከላችን ፍቅርና ሰላም እንዲሆን አደርጋለሁ» የሚል ቃል ወደ ኢጣልያኖች ቢልኩባቸው «ይህ ንግግር የፖለቲካ ንግግር ነው እንጂ ይህን የሚያህል ትልቅ ጦርነት ምንም ቢሆን ንጉሠ ነገሥቱ ሳይሰሙለትና ሳይፈቅዱ አይደእግም።» በማለት ነገራቸውን ሳይቀበሏቸው ቀሩ። እንዲያውም እንደ ገና ወታደር ሰብስበው ወደ ፊኢት እየገፉ ሰሐጢን መያዛቸው ስለ ተሰማ አጼ ዮሐንስ ለጦርነት ይሰናዱ ጀመር።

ኢጣሊያኖች ንጉሥ ምኒልክ ከእርሳቸው ጋራ ሆነው አጼ ዮሐንስን በሚወጉበት ጊዜ ንጉሥ ምኒልክ ይረዱናል በማለት ተስፋ ነበራቸውና አሁን ከአጼ ዮሐንስ ጋራ ሆነው ኢጣሊያኖችን ለመውጋት ተማምለዋል የሚል ወሬ በመስማታአቸው እጅግ አዘኑ። ንጉሥ ምኒልክ ግን በዲፕሎማቲክ መንገድና ዕውቀት እኔ አስታርቃችኋለሁ እያሉ ወደ ኢጣሊያኖች ይልኩ ነበር።

# ምዕራፍ ፵፪

## የእንግሊዝ መላክተኛ ሰር ፖርታል የሚባለው ወደ አጼ ዮሐንስ ስለ መምጣቱ

ራስ አሉላ በሰሐጢ አጠገብ ቱዳዓሊ በሚባል ሥፍራ ፫፻ በሚሆኑ ኢጣሊያኖች ላይ አደጋ ጥለው ስለ ፈጅዋቸው የኢጣሊያ መንግሥት ሰሐጢንና ዊዓ የሚባለውን አገር በጦርነት ለመያዝ እንደ ገና መሰናዳት ሰለ ጀመረ አጼ ዮሐንስ በበኩላቸው ለጦርነት መሰናዳት ጀመሩ።

ስለዚህም የእንግሊዝ መንግሥት ላይ ላዩን በአጼ ዮሐንስና በምስሮች መካከል ስላለው ነገር አስመስሎ ውስጡን ግን በአጼ ዮሐንስና በኢጣሊያኖች መካከል የታሰበውን ጦርነት ለማስቀረት ሲል ሰር ፖርታል የሚባለውን ዋና መላክተኛ አድርጐ ወደ አጼ ዮሐንስ ላከው። ይህንንም የሚያስረዳው ነገር በንግሥት ቪክቶሪያ ማኅተምና ፊርማ የመጣው ደብዳቤ በአጼ ዮሐንስና በምስሮች መካከል ያለውን ገዥ የሚናገር ነው። በማስታወሻ የቀረበው መልእክት ግን ስለ ኢጣሊያኖች ጉዳይ የሚናገር ነበር።

በማኅተምና በፊርማ የመጣው የንግሥት ቪክቶሪያ ደብዳቤ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

ቪክቶሪያ በእግዚአብሔር ጸጋ በታላቂቱ ብሪታንያ ዩናይትድ ኪንግደምና የአየርላንድ ንግሥት። የህንድ ንግሥተ ነገሥት የሃይማኖት ጠባቂ።

ለወዳጃችን ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ግርማዊነትዎ በጤና እንዳለ ተስፋ እናደርጋለን። እኛ በእግዚአብሔር ቸርነት ደህና ነን።

ከሁለት ወር በፊት ሰላማችንን ለግርማዊነትዎ በደብዳቤ ልከን ነበረ። ለግርማዊነትዎ ደህንነትና ለመንግሥትዎ ሰላም ልማት ከልብ የሆነ ምኞታችንን በዚሁ ደብዳቤ ገልጸን ነበር።

የግርማዊነትዎ ግዛት አዋሳኝ በሆኑትና በልዑል ከደዊ (ኬዲቭ) መንግሥት በሚገዙት ባንዳንድ አውራጃዎች ምክንያት አንዳንድ ነገር ስለ ተነሣ ከግርማዊነትዎ ጋራ በዝርዝር ለመነጋገር የሚያስፈልግ ሆነ።

ስለዚህ ነዋሪነቱ በካይሮ ሌጋሲዮኖችን የሆነ የታመነ ሽም ሚስተር ዤራልድ ፖርታል ይህን ደብዳቤ ይዞ ወደ ግርማዊነትዎ እንዲመጣ የሚያስፈልግ መስሎ ታየን።

ሙሉ እምነታችንን በእርሱ ላይ አድርገን ከዚህ በላይ የተመለከተውን ጉዳይና በየጊዜው በግርማዊነትዎና በእኛ መካከል በተላኩት ደብዳቤዎችም የተመለከተውን ሌላውን ነገር ሁሉ ከግርማዊነትዎ ሚኒስትሮች ጋራ እንዲነጋገር ሥልጣን ሰጥተነዋል።

ይህንንም የታመነና የተከበረ መላክተኛችንን እንዲጠብቀውና ደስ እንዲያሰኘው ግርማዊነትዎን አደራ እንላለን።

ለግርማዊነትዎ ጤናና ደስታ ለግዛትዎ ልማት እንዲሆን የማያቋርጥ ምኞታችንን እንገልጽልዎታለን ፡

ጥቅምት ፲፪ ቀን ፲፰፻፹ ዓመተ ምሕረት። በነገሥን በ፶፩ ዓመት በባልሞራል ቤተ መንግሥታችን ተሰጠ /ተጻፈ/

የግርማዊት ንግስት ቪክቶሪያ ፊርማና ማኅተም። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሚኒስትር ሳልሰበሪ ፊርማ።



ሰር ዤራልድ ሔርበርት ፓርታል

የእንግሊዝ መንግሥት መልክተኛ

[Gerald Portal - Wikipedia]

ስለ ኢጣሊያኖች ጉዳይ በማስታወሻ አድርጐ በራሱ ፊርማ ፈርሞ ያቀርበው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

ባለፈው ጥር ወር ራስ አሉላ ባስገደሏቸው አራት መቶ አምሳ ኢጣሊያኖች ሞት ግርማዊት ንግሥት ቪክቶሪያ እጅግ አዝነዋል።

ደግሞ ወዳጃቸው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ከኢጣሊያ ንጉሥ ጋር ጦርነት ለማድረግ በመታሰቡ በጣም ተጨንቀዋል።

ይህም የታሰበው ጦርነት በኢትዮጵያ እንዳይደረግ ለማስቀረት ሲሉ ለትልቅ ጦርነት መሰናዳት ይቅርና በመካከላችሁ ሰላምና ወዳጅነት ቢሆን መልካም ነው ብለው የኢጣሊያን መንግሥት ቢጠይቁ የኢጣሊያ ንጉሥ ከኢትዮጵያ ንጉሥ ጋር በሰላምና በወዳጅነት ንግድን በማስፋት ለመኖር ፈቃዴ ነውና ለጦርነት መሰናዳታችን የሚቀረው ንጉሥ ዮሐንስ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የውል አሳብ መሰናዳታችን የሚቀረው ንጉሥ ዮሐንስ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

፩ኛ። በአሳውርታና በሀሳብ የሚኖሩ የዓረብ ነገዶች የኢጣሊያ ጥገኞች ሆነው መኖራቸው የታወቀ ይሆናል ፡

፪ኛ። ሰሐጢና ዊዓ በዙሪያቸውም እስከ ፫ ቀን መንገድ ያሉት አገሮች ሁሉ የኢጣሊያ ግዛት ይሆናል።

፫ኛ። ወደ ፊትም በወሰን ነገር ጠብ እንዳይነሣ ወሰኑ ሁሉ በግምብ ዓምድ ይመለከታል። የወሰኑንም ፀጥታ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚጠብቅ በእንግሊዝ አማካይነት ኢጣሊያና ኢትዮጵያ ተስማምተው ይጨርሳሉ። ጊንዳ ግን የኢትዮጵያ የወሰን ከተማ ሆኖ ይኖራል።

፬ኛ። ሲንሂት በኢጣሊያኖች እጅ ይሆናል።

፭ኛ። ወደ ፊት በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መካከል የሰላምና የወዳጅነት የንግድም መስፋፋት ውል ይዋዋላሉ የሚልና ሌላም ይህን የመሰለ አንዳንድ እንገር ያለበት ነው።

ራስ አሉላም የሚስተር ፖርታልን መምጣት በሰሙ ጊዜ የመጡበትን ምክንያቱን የሚጠይቁና ወዲያውም የደጃች ደብብን ነገር በደብዳቤ የሚያመለክቱ መኳንንቶች ልከው ሰደዱ።

የደብዳቤውም ቃል ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

መልእክተ ዘራስ አሉላ ዝውእቱ ቱርክ ባሻ።

«ይድረስ ከዤራልድ ፖርታል የእንግልትራ ንግሥት መላክተኛ። እንዴት ሰነበትህ። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። የቀድሞውን ዕርቃችንን ታውቀዋለህ። ከእናንተም ወደ ኢትዮጵያ አለፈቃዳችሁ ሰዋችሁ ሲመጣ አስረን ልንሰት። እናንተም ከእኛ አለፈቃዳችን ከኢትዮጵያ ወደ እናንተ ሰዎችን ሴምታ አስራችሁ ልትሰዱልን ይህ ነው ዕርርቃችን።

አሁንም ከሁለታችንም ቤተ መንግሥት መካከል ጠብ የለንም፣ እይምንጣላበትና ነጋዴም የተከለከለበት በዚህ ደብብ የሚባል ሽፍታ ነው እንጂ በሁለታችን ሌላ ጠብ የለንም። አሁንም ደብብ ያለው በምጥዋ ውስጥ ነውና እንደ እርቃችን እንደ ፍቅራችን ደብብን እንድትይዝ ይሁን። ከኢጣሊያኖች ጋርም ያጣላን ደብብ ነው።

ይህንም ማለቴ ቤተ መንግሥት መካከል ያእል አመጠኛ ቢጠፋ የቤተ መንግሥት ፍቅር ይጠናል። ነጋዴም እንደ ወትሮው ይነግዳል ብዬ ነው። ግን ይህን ማለቴ ፍቅራችንን አይቼ ነው እኒ የትእዛዝ አይደለም። ተጽሕፈ አመ ፳ወ፫ ለጥቅምት ፲፰፻፹ ዓመተ ምህረት።»

ደጃች ደብብ የትልቁ የራስ አርአያ ልጅ ነው። በአምባጓሮ አንድ ሰው ስለ ገደለ አጼ ዮሐንስ ፈርቶ በሽፍንት ሲዞር በኋላ ግን ኢጣልያኖች ገብቶ በምጥዋ ተቀምጦ ነበርና እርሱን እንድትይዝ ይሁን ያሉበት ምክንያቱ ስለዚህ ነው። እርሱ ግን በኋላ ለኢትዮጵያ የሠራውን ትልቅ ሥራ ከሥፍራው ስንደርስ እንጽፈዋለን።

ራስ አሉላ በዚህ ደብዳቤያቸው ቀድሞ አጼ ዮሐንስና የእንግሊዝ መንግሥት የምሥርም ከደዊ (ኬዲቭ) የተዋዋሉትን ውል ጠቅሰው መጻፋቸው ኢጣሊያኖች ምጥዋን መያዛቸውን አለመቀበላቸውን ለማስረዳት ይመስላል።

ሚስተር ፐርታልም ወደ አሥመራ ከደረሰ በኋላ ወደ አጼ ዮሐንስ ለመሄድ ቢያስብ ራስ አሉላ ልዩ ልዩ ምክንያት እያደረጉ በወታደር እያስከበቡ ብዙ ቀን አቆዩት። በኋላ ግን አጼ ዮሕጀንስ ፈቅጀለታለሁና ይምጣ የሚል ደብዳቤ ስለላኩባቸው ሂድ ብለው አሰናበቱት። ቢሆንም «ወደ ንጉሠ ነገሥቱ የተጻፈውን የእንግሊዝን ንግሥት ደብዳቤ ሳታሳየኝ አልሰህም» ስላሉት ደብዳቤውን አሳይቶ ተሰናበተ።

ወደ አጼ ዮሐንስም በደረሰ ጊዜ በታላቁ ማዕርግና ክብር ተቀበሉትና ከግርማዊት ንግሥት ቪክቶሪያ ያመጣውን ደብዳቤና ማስታወሻውን አስረከበ።

አፄ ዮሐንስም ስለ ኢጣሊያኖች ጉዳይ ሚስተር ፖርታል ባማርኛ ቋንቋ አስተርጉሞ ያቀረበላቸውን የውል ማስታወሻ አስነብበው ከሰሙ በኋላ በነገሩ እጅግ አዝነው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል መለሱለት።

«ጦርነት ማድረግ መልካም ነገር አይደለም። ይልቁንም ክርስትቲያን ከክርስቲያን መዋጋት የማይገባ ነገር መሆኑን አውቃለሁና እርቅና ሰላም ለማድረግ ፈቃዴ ነው። ለኢጣሊያኖች አገር ይስጧቸው ስለማለትህ ግን አገር መስጠቴ ይቅርና አንድ ስንዝርም መሬት አልሰጣቸውም። አሁንም ያሉበት ምጥዋ እንኳ የሚገባው ለእኔ ነው። ኃይልና ድል ማድረግ በኢየሱስ ክርስቶስ ነውና ኢጣሊያኖች የምፈራበት ነገር የለኝም» የሚል ቁርጥ የሆነ ቃል ገሩትና አሳቡ ሳይፈጸምለት በመቅረቱ እጅግ አዘነ።

ነገር ግን የመጣበትን ነገር ከአጼ ዮሐንስ ተነጋግሮ ስያጨርስ ኢጣሊያኖች ወደ ሰሐጢ ወጥተው አገሩን መያዛቸው ስለ ተሰማ አጼ ዮሐንስ ቁጣቸው እየበረታ ሄደና ለጦርነት ወደ ሰሐጢ ለመውረድ ቁርጥ አሳብ አደረጉ። ስለዚህም ለእንግሊዝ ንግሥት ለግርማዊት ቪክቶሪያ መላክተኛ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ጽፈው ሰጡት።

«በስመ እግዚአብሔር ወኢየሱስ ክርስቶስ። እስመ ለዓለም ምሕረቱ። ከሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ለወዳጃችን ለትልቂቱና ለደገኛይቱ ንግሥት ቪክቶሪያ። በእግዚአብሔር ጸጋ የታላቋ ብሪታንያና የአይርላንድ ንግሥት የህንድ ንግሥተ ነገሥት። የሃይማኖት ጠባቂ። ከጻፍሁልዎ ወዲህ እንደ ምነዎ? እኔ ራሴና መንግሥቴም በእግዚአብሔር ቸርነትና በእምነ ጽዮን አማላጅነት አምላክ ቅዱሳን ይክበር ይመስገን ደህና ነን። ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።

በጥቅምት ፲፪ ቀንና ደግሞ ከኢጣሊያኖች ጋራ ታረቁ የሚል በኅዳር ፲፮ የተጻፉት ደብዳቤዎች ደርሰውኛል። በእርስዎም ላይ በቱርኮችም /በምስሮች/ ላይ ምንም አለማድረጌንና ክፉ ሥራ አለመሥራቴን በእውነት ገልቸ እነግሮታለሁ። እኔንና በእንግሊዝ በምስርም መካካል የተደረገው ውል እኔ ስላፈቅድ አንድ እንኳ መሣሪያ በምጽዋ በኩል እንዳይወጣ ነበር። እነርሱ ግን ውሉን አፍርሰው መሣርያ አምጥተው ለሼሆ /ሆሳ/ ሸጠዋል። ሼሆም ጉሣ ባገሬ ላይ ትልቅ ሁከት አስነሥቷል።

ኢጣሊያኖች ተበድለናል ስለማታቸው ግን ጥፋቱ የነሱ ነው እንጂ፣ የእኛ አይደለም። የኢትዮጵያን ነጋዴዎች በመከልከላቸውና ሰሐጢንና ዊዓን በመያዛቸው ጠብ የጀመሩ እነሱ ናቸው። ንግዱን ስለምን ከለከሉ? ወደ ሀገሬስ ስለምን ገቡ? እኔም በንግሥት ቪክቶሪያ ፈቃድ መጥታችሁ እንደሆነ ማኀተም አሳዩኝ አለዚያ አገሬን ልቀቅ ብዬ ጻፍሁላቸው። እነሱ ግን እምቢ ስላሉ በዚህ ምክንያት ከራስ አሉላ ጋራ ጦርነት ገጥመው ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰዎች ሞቱ። እርስዎ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠኝን አገር እንደምን ለኢጣሊያኖች ልቀቅ ይሉኛል? ልቀቅ እንኳ ቢሉኝ ያልተገባ ነገር ነው።

የእርስዎ አሳብ በመካከላችን እርቅ ለማድረግ እንደ ሆነ ይህ እርቅ የሚሆነው እነሱም ባገራቸው እኔም ባገሬ ሆነን ነው። አሁን ግን በሁለታችንም ወገን ፈረስ

ተጭኗል፤ ጐራዴም ተመዟል፣ ቁጥሩም እንደ አሸዋ የሆነ ወታደሬ ለጦርነት ተዘጋጅቷል። ኢጣሊያኖችም ጦርነት ማድረግ ፈልገዋል።

ቢሆንም ኃይል የኢየሱስ ክርስቶስ ነውና የፈቃዳቸውን ያድርጉ። እኔ ግን በሕይወተ ሥጋ እስካለሁ ድረስ እነሱን ፈርቼ በጉድጓድ ውስጥ ተደብቄ ለመኖር አልችልም።

በኅዳር ፳፬ ቀን ፲፰፻፹። በአሸንጌ ከተማ ተጻፈ።

ደግሞ ግርማዊት ንግሥት ቪክቶሪያ በዚሁ በሚስተር ፖርታል እጅ አንድ ጐራዴና አንድ ትልቅ መነጽር እንደ ገጸ በረከት አድርገው ልከውላቸው ነበርና ስለዚህም የምስጋና ቃል ለብቻው በሌላ ደብዳቤ ጽፈው ከሰጡት በኋላ እስከ መቀሌ ተከትሎ ሔዶ የደጃዝማች ማዕርግ ሽልማት ሸልመው አሰናበቱት።

# ምዕራፍ ፵፫

## ንጉሥ ምኒልክ በአጼ ዮሐንስ ፈቃድ ወደ ወሎ ስለ መሔዳቸው።

ንጉሥ ምኒልክ በመስከረም ፳፩ ፲፰፻፹ ዓመተ ምሕረት በእንጦጦ በተሠራው ቤተ ክርስቲያን ታቦተ ማርያም እንዲገባበት ስለ አደረጉ ልብሰ መንግሥት ለብሰው ዘውድ ጭነው ታላቅ በዓል ካደረጉ በኋላ ሦስት ቀን ሙሉ ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ለወታደሩና ለካህናት ግብር አብልተው ነበርና በዚሁ ሰሞን አጼ ዮሐንስ ከኢጣሊያኖች ጋራ ጦርነት ለማድረግ ወደ ሰሐጢ መውረዴ ስለሆነ በፍጥነት እንዲመጡ ይሁን የሚል በደብረ ታቦር ከተማ የተጻፈው ደብዳቤ ለአቡነ ማቴዎስ ደረሰላቸው። ለንጉሥ ምኒልክ ግን የቃልም የደብዳቤም መልዕክት አልተላከም ነበርና ለንጉሥ ምኒልክ ትልቅ ሥጋት ሆኖባቸው ነበር።

ይህንንም እጅግ የከበደ ወሬ ሰምተው ዝም ብለው ለመቀመት የማይቻላቸው ስለሆነ ብዙ ግብርና ገጸ በረከት አሰናድተው «ጃንሆይ ወደ ሰሐጢ ለመውረድ ማሰብዎን ሰምቻለሁና እኔም ለጦርነቱ እርዳታ እንድመጣ ይፍቀዱልኝ።» የሚል ደብዳቤ ጽፈው በአቡነ ማቴዎስና በደጃች መሸሻ ወርቄ በበጅሮንድ አጥናፌ እጅ ላኩ። እንደዚህም ማለታቸው ጃንሆይ አጼ ዮሐንስ የሚመልሱላቸውን ለማወቅ ነበር እንጂ ከአጼ ዮሐንስ ጋራ ወደ ሰሐጢ ለመዝመት አሳብ እንዳልነበራቸው በብዙ ሰዎች አፍ ሲነገር ሰምተናል።

መላከተኞንቹም ዋድላ ላይ ከአጼ ዮሐንስ ጋራ ተገናኝተው ግብሩንና ገጸ በረከቱን ከደብዳቤው ጋራ አስረከቡ። ነገር ግን አጼ ዮሐንስ ከአቡነ ማቴዎስ በቀር ሁለቱን

መኳንንቶች እንደ ሰላይ እንጂ እንደ መላከተኞች በመልካም ዓይን አላዩዋቸውምና በደስታ ሳያነጋግሩዋቸው ቀሩ።

ከዚህም በኋላ አቡነ ማቴዎስን ከርሳቸው ጋር ወደ ትግሬ /ትግራይ/ እንዲሄዱ አድርገው ሁለቱን መኳንንቶች አሰናብተው መለሷቸው። አቡነ ማቴዎስንም የወሰዱበት ምክንያት ሰው እግዚአብሔር ፈቅዶ የሚያደርገውን ለማስቀረት አለ መቻሉን ምንም ልቡ ቢያውቅበትም ማሰቡና መሞከሩ አይቀርምና ወደ ሰሐጢ ወርደው ከኢጣሊያኖች ጋራ ተዋግተው ድል የሆኑ እንደ ሆነ ልጃቸው ራስ አርአያ በአልጋቸው ሲቀመጥ ንጉሥ ምኒልክ በጳጳሱ በአቡነ ማቴዎስ እጅ ተቀብተው ንጉሠ ነገሥቱን እንዳይወስዱበት ለማድረግ አስበው ነው ይባላል።

ለጦርነቱ እርዳታ ልምታ ብለው ስለ ጻፉት ደብዳቤ ግን «ለኢጣሊያ ጦርነት እኔ አልሰንፍምና ደርቡሽ ከመተማ ወጥቶ ጐንደርን እንዳያጠቃ ለመጠባበቅ ለመላላክም እንዲቀርበን ወደ ቦሩ ሜዳ ብቅ ብሎ መቆየት ይሻላል። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም በቤጌምድር ተቀምጠህ ጠብቅ ብየዋለሁ!» የሚል ምላሽ ጽፈው ልከውላቸው ነበር።

ንጉሥ ምኒልክ ግን ደብዳቤውን አይተው «ጃንሆይ ለጦርነቱ እርዳታ አትምጣ ማለታቸው ከኢጣሊያኖች ጋራ ምክር አለው በማለት ቢጠረጥሩ ይሆናል እንጂ ሌላ ምክንያት ያለው አይመስለኝም። ነገር ግን ለማናቸውም ቢሆን ወደ ወሎ ብቅ ማለቴ መልካም ሳይሆን አይቀርም» በማለት ሠራዊታቸውን በአዋጅ ሰብስበው በታኅሣሥ ፲፰ ቀን ፲፰፻፹ ዓመተ ምሕረት ከእንጦጦ ከተማ ተነሥተው በጥር ፳፪ ወሎ ገቡ። የተከተላቸውም ሠራዊት እጅግ ብዙ ነበርና ሠፈሩ ካርዲቦ ባሕር እስከ ሐይቅ ባሕር ደረሰ።

# ምዕራፍ ፵፬

## አጼ ዮሐንስ ከኢጣሊያኖች ጋራ ለመዋጋት ወደ ሰሐጢ ስለ መውረዳቸው

አጼ ዮሐንስ የእንግሊዝን ንግሥት መላከተኛ ሚስተር ፖርታልን አሰናብተው በመቀሌ ሳሉ ኢጣሊያኖች ወደ ፊት እየገፉ የመምጣታቸው ወሬ እርግጥ በተሰማ ጊዜ መኳንንቱና ከሕዝቡም ትልልቆቹ ወደ አጼ ዮሐንስ ገብተው ጃንሆይ ሁላችንም እስከ ምጥዋ ወርደን ኢጣሊያኖች ከእናታችን ከኢትዮጵያ ምድር እንድናስወጣቸው ይፍቀዱልን ቡሏቸው፣ በመኳንንቶቻቸው የጀግንነት ንግግር ደስ ስለ አላቸው ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ።

መኳንንቶቼ ልጆቼና ሕዝቦቼ ሆይ! እኔም ስለ እናቴ ስለ ኢትዮጵያ ሕይወቴን ልሰዋላት ሙሉ ፈቃድ» አለኝ። ደግሞ በእኔ ልብ ያለው አሳብ በትክክል በእናንተም ልብ ስለመታሰቡ በጣም ደስ ብሎኛል።

እንግዲህ አሳባችን አንድ ከሆነ ጠንክሩ እንጂ አትፍሩ። ለዘመቻውም አዋጅ እነገራለሁና አይዟችሁ በርቱ እያሉ የወንድነት ቃል ከነገርዋቸው በኋላ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን አዋጅ ተነገረ።

«ሀገሬ ሆይ ስሚ! መኳንንቶቼ ወታደሮቼ ሕዝቦቼ ስሙ! በመጋቢት ፳፫ ቀን በምጥዋ መንገድ አቅንተህ ለጦርነት እንድትገሰግስ የኢትዮጵያ መንግሥት በጽኑ ያዝሃል። ወደ ፊት ገስግስ እንጂ ወደ ኋላ አትቅር።

የኢትዮጵያ ልጅ ሆይ ልብ አድርገህ ተመልከት! «ኢትዮጵያ የተባለችው አንደኛ እናትህ ናት! ሁለተኛ ዘውድህ ናት! ሦስተኛ ሚስትህ ናት! አራተኛም ልጅህ ናት! አምስተኛም መቃብርህ ናት! እንግዲህ የእናት ፍቅ። የዘውድ ክብር። የሚስት ደግነት። የልጅ ደስታ። የመቃብር ከባቲነት እንደዚህ መሆኑ አውቀኸው ተነሣ።»

ይህንንም አዋጅ ካስነገሩ በኋላ በመጋቢት ፳፫ ቀን ፲፰፻፹፩ ዓመተ ምሕረት ወደ ሰሐጢ ተጓዙ።

የጦር ፊታውራሪውም ኢጣሊያኖች ወደ አሉበት ሥፍራ በደረሰ ጊዜ ኢጣሊያኖች ለማስፈራራትስ ሲሉ በአየር ላይ የሚወረወር የኤሌክትሪክ መብራት እየወረወሩ ሲያሳዩት በዚያን ዘመን የኤሌክትሪክ ብርሃን እንደ ዛሬ በሀገሪቱ አልተለመደም ነበርና በሰማይ መብረቅ የወደቀበት እየመሰለው ሠራዊቱ ሁሉ ወደ ኋላው መሸሽ ጀመረ። ስለሆነም አጼ ዮሐንስ ይህን ፈርተው ለመመለስ አላሰቡም ነበር። ነገር ግን ኢጣሊያኖች ከእርዳታቸው (ከምሽጋቸው) ውጥ ወጥተው ጦርነት የማይገጥሟቸው መሆኑን ስለተርዱት በእርዱም ውስጥ ገብተው እንዳይዋጉ ሠራዊታቸው በመድፍና በመትረየስ የሚያልቅ መሆኑን ስለ አወቁ ምናልባት ከእርዳቸው ወጥተው ጦርነት ይገጥሙኝ ይሆናል በማለት አንድ ወር ሙሉ ተቀመጡ። ሠራዊታቸውም ቁጥሩ ብዙ ነበርና አገሩ በረሃ ስለሆነ በእህልም በሣርም ችግር ሆኖ ነበር።

ለዚህም በቀር እጅግ የሚያሳዝን ሁለት ወሬ አጼ ዮሐንስ ሰለ ደረሰላቸው ከኢጣሊያኖች ጋራ ጦርነት ማድረጋቸውን ትተው ለመመለስ ቁርጥ ሀሳብ አደረጉ።

፩ኛው ወሬ። ደርቡሽ ወደ ቤጌምድር መላከተኞች ልኮ በአዘዞ ላይ ከንጉሥ ምኒልክ ጋር በምሥጢር ስለተነጋገረ በጦርነት ወጥቶ ቤጌምድርን ሊያጠፋው ይሰናዳል የሚል ነው።

፩ኛው ወሬ። ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከጃንሆይ ሊከዱ ወደ ኢጣሊያም ሊላልኩ ተማምለው ተለያዩ የሚል ወሬ ነው።

በዚህም ሁሉ ምክንያት ከኢጣሊያኖች ጋር ሰነፍ እርቅ አድርገው ወደ መቀሌ ተመሱ። ሰነፍ እርቅ ማለት ጸንቶ የሚቆይ ለጊዜ ብቻ ጠብን የሚያበርድ ማለት ነው።

መቀሊኤም እንደ ገቡ ልዑል ራስ አርአያ ሥላሴ ስለ ሞቱ በሙሉ ትግሬ /ትግራይ/ ትልቅ ኀዘን ተደረገ። ይልቁንም አጼ ዮሐንስ ሌላ ልጅ አልነበራቸውምና አልጋዬን ለመውረስ በሥፍራዬ ለመቆም ደረሰልኝ እያሉ ደስ ሲላቸው ይህን የመሰለ ትልቅ አደጋ ስለ ደረሰባቸው ጽኑ ኀዘን አዘኑ።

# ምዕራፍ ፵፫

## ንጉሥ ምኒልክ ከወሎ ቤጌምድር ሄደው በጐጃም አድርገው ወደ ሸዋ ስለ መመለሳቸው

አጼ ዮሐንስ በ፲፰፻፹ ዓመተ ምሕረት ከኢጣሊያኖች ጋራ ጦርነት ለማድረግ ወደ ሰሐጢ ሲወርዱ የደርቡሽ አኳኋን አስግቷቸው ነበርና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ወደ ቤጌምድር ብቅ ብለህ እኔ እስትመለስ የደርቡሽን አኳኋን እየተጠባበቅህ እንድትቆይ ይሁን ብለው አዘዋቸው ነበር። ስለዚህም ወደ በጌምድር ተሻግረው በሰቀልት ላይ ሠፍረው ሲጠባበቁ ደርቡሽ በዚህ ዓመት በጥር ፲ ቀን ከብዙ ሠራዊት ጋራ መጥቶ በደምቢያ አጠገብ ሣር ውሀ በሚባል ሥፍራ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋራ ጦርነት ተጋጥመው ሲዋጉ ለጊዜው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ድል ያደረጉ መስሎ ነበር። በኋላ ግን ድሉ ለደርቡሽ ሆነና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ድል ያደረጉ መስሎ ነበር። በኋላ ግን ድሉ ለደርቡሽ ሆነና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከልጃቸው ከራስ በዛብህ ጋራ በፈረስ ሸሽተው በደንገል በር አድርገው ጐጃም ገቡ። ሁለተኛውም ልጃቸው ደጃዝማች በለው ጳጳሱን አቡነ ሉቃስን ይዞ በፎገራ መንገድ ሸሽቶ ወደ ጐጃም ገባ። ሴቱቱ ልጃቸው ወይዘሮ ምንትዋብ ግን ተማረከች። ከሠራዊታቸውም ብዙዎቹ በሰይፍ እየታረዱ እኩሉ ደርቡሽ ሲያባርራቸው ወደ ጣና ባሕር እየተወረወሩ አለቁ።

ደርቡሽም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ድል ካደረጉ በኋላ ወደ ጐንደር ወጥቶ አብያተ ክርስቲያናቱና ከተማውን አቃጥሎ ሸሽተው ካመለጡት በቀር ሕዝበ ክርስቲያኑና አርዶ ሴቶችንና ሕፃናቱን ለባርነት ማርኮ ወደ ሀገሩ ተመለሰ።

ንጉሥ ምኒልክ በወሎ ሳሉ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከደርቡሽ ጋራ ተዋግተው ድል ሆነው ወደ ጐጃም መመለሳቸውን በሰሙ ጊዜ ደርቡሽ እንደ ገና ገስግሶ ወጥቶ ጐንደርን ሁለተኛ እንዳያጠፋው ለመጠበበቅ ሲሉ ከቦሩ ሜዳ በየካቲት ፯ ቀን ተነሥተው በመጋቢት ፩ ቀን ደብረ ታቦት ከተማ ገቡ። በዚያም ጥቂት ቀን ቆይተው ወደ ጐንደር ተጓዙና በሚያዝያ ፲፩ ቀን በአዘዞ ትልቅ ሰልፍ አድርገው ግባት ሲያስተኩሱ ዋሉ። ራሳቸውም በፈረስ ተቀምጠው በመሰለፋቸው መኳንንቱም ወታደሩም እጅግ አደነቀ። ንጉሥ ምኒልክ ከነገሡ ጀምሮ ይህን የመሰለ ትልቅ ሰልፍ አላደረጉም ነበር ይባላል።

የደርቡሽም መላክተኞች መጥተው ነበርና የሰልፉን አኳኋን የሠራዊቱን ብዛት አይተው ትልቅ ፍርሃት አደረባቸው። ከዚህም ወደ አምባጫራ ወርደው የደርቡሽን አኳኋን እያዳመጡ ተቀመጡ። ደርቡሽም የንጉሥ ምኒልክን ሠራዊት ብዛት ከመላክተኞቹ አፍ ስለ ሰማ በዚያው በመተማ ምሽጉን እየመሸገ ተቀመጠ እንጂ ወደ ጐንደር ለመውጣትና አገር ለማጥፋት አልደፈረም።

አጼ ዮሐንስም ከሰሐጢ ተመልሰው መቀሌ ገብተው ነብርና የደርቡሽ መላክተኞች ወደ ቤጌምድር መጥተው ከንጉሥ ምኒልክ ጋራ ተገናኝተው የምሥጢር ነገር መነጋገራቸውን በሰሙ ጊዜ «በእኔ ላይ ከኢጣሊይያኖች ጋራ መዋዋል አልበቃ ብሎ ደግሞ ከደርቡሽ ጋራ መመሣጠር ከተጀመረ የንጉሥ ምኒልክ አሳብ ከእኔ ጋራ ለመጣላት ሳይሆን አይቀርም» ብለው «ከእንግዲኢህ ወዲህ በመጣችሁበት መንገድ ወደ ሀገራችሁ ተመለሱ» የሚል ደብዳቤ ወደ ንጉሥ ምኒልክ ላኩባቸው።

ንጉሥ ምኒልክ ግን የተላከባቸውን ደብዳቤ አይተው አጼ ዮሐንስ ለጠብ እንደፈለጓቸው ተረዱትና በብርቱ ካሰቡበት በኋላ «በመጣሁበት መንገድ ስመለስ ገስግሰው መጥተው ቢቆዩኝሳ? ዳግመኛ እጅ ልነሣ? ያውም ለወቀሳ ለክስ ይህስ የማይሆን ነገር ነው ብለው እባክዎ ጃንሆይ በጐጃም አድርጌ ወደ ሸዋ እንድመለስ ይፍቀዱልኝ» የሚል ደብዳቤ ጽፈው በግስጋሴ ላከ። አጼ ዮሐንስም ከመኳንንቶቻቸው ጋራ መክረው «ንጉሥ ምኒልክ በጐጃም አድርገው ወደ ሸዋ ለመመለስ ቁርጥ አሳብ አድርገው እንደ ሆነ በመጡበት ይመለሱ ብንላቸው አይመለሱልንም። ብንገሰግስም አንደርስባቸውም ወዲያውም ሠራዊታችን በሰሐሕጢ ዘመቻ ተጐድቷልና አንችላቸውም። ስለዚህ በጐጃም እንዲሄዱ ቢፈቀድላቸው ይሻላል» ተባለና ይሂዱ የሚል ፈቃድ መጣላቸው። ወደ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ለንጉሥ ምኒልክ መንገድ አትከልክል ስንቅም ስጥ የሚል ትእዛዝ ስጥ የሚል ትእዛዝ አለፈላቸው።

ንጉሥ ምኒልክም ከአምባጫራ ተነሥተው ዓባይን ተሻግረው ጐጃም ሲደርሱ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንደ መጠርጠር ብለው መሸሽ ጀምረው ነበር። በኋላ ግን

በፍቅር ምልክት ስለ ተላከባቸው ተመልሰው በደስታና በፍቅር ተቀበሏቸው። ቢሆንም ሲገናኙ እንደ ወንድም ተገናኙ እንጂ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ታጥቀው እጅ አልነሱም ነበር። በሚቀመጡበትም ጊዜ ሦስት ዙፋን እየተዘረጋ አንደኛው ለንጉሥ ምኒልክ ሁለተኛ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሆነ። መካከለኛው ግን አምሮ ተነጥፎ የንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ዙፋን ነው ይባል ነበር።

ንጉሥ ምኒልክ በጐጃም በሚዘዋወሩበትና በሚያድሩበት ሥፍራ ሁሉ በየመንገዱም ሕዝቡ በደስታና በክብር ተቀበላቸው። ካህናቱም በወረብ ንጉሥ ምኒልክ አጼ የሚባሉበት ጊዜ ደረሰ ለማለት «ናሁ በጽሐ ጊዜሁ ለሣህለ ማርያም» እያሉ ሴቶችም በዘፈን እያሞገሱ ትንቢት ይናገሩላቸው ነበር።

ከዚህ በኋላ ሁለቱ ነገሥታት በአጼ ዮሐንስ ላይ ለማድርግ ያሰቡትን በምሥጢር ተነጋግረው ሲጨርሱ ከደርቡሽ ጋራ ስትዋጋ የጦር መሣሪያህ ተማርኮብሃልና ስለ እርጥባን ነው ብለው ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሁለት መድፍና ሁለት መቶ አምሳ ጠመንጃ ሰጧቸው።

እንደዚህም በተድላና በደስታ ሰንብተ በሚለያዩበት ጊዜ በመካከላቸው የሚዘረጋውን የአጼ ዮሐንስ ዙፋን የሚበላውን አስቀርተው ሁለት ዙፋን ብቻ እንዲዘረጋ በማድረጋቸው የጐጃምና የሸዋ ሰው ሲያደንቅ ሰነበተ። ጉዳያቸውንም ከጨረሱ በኋላ ተሰነባብተው ንጉሥ ምኒልክ በግንቦት ወር በሰላሌ አድርገው እንጦጦ ተመለሱ።

ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከእምባቦ ጦርነት ጀምረው በምስጢር መስማማታቸወ እርግጥ ነው። ነገር ግን አሁን አጼ ዮሐንስን ለመክዳት ቁርጥ አሳብ ማድረጋቸው በሁሉ ዘንድ ግልጥ ሆኖ ይወራ ነበር።

ንጉሥ ምኒልክ ወደ ሸዋም ከገቡ በኋላ የልዑል ራስ አርአያ ሥላሴን ሞት ተረዱና ትልቅ ኀዘን ተደረገ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም «ያረገዘች ታስታው፣ ከደረቷ ትታጠቅ» እንደሚባለው እህሉንና ማሩን ቅቤውንና ይህንንም የመሰለውን ሁሉ እየሰበሰቡ ወደ ተራ አምባ ያስገቡ ጀመር።

# ምዕራፍ ፵፯

## አጼ ዮሐንስ ጐጃምን ስለ ማጥፋታቸው

አጼ ዮሐንስም ስለ ልጃቸው ስለ ራስ አርአያ ሥላሴ ሞት መዋዕለ ኀዘናቸው ከተፈጸመ በኋላ ወደ ቤጌምድር ገሰገሱ። የገሰገሱበትም ምክንያቱ ወሬውን ገና ሰሐጢ ሳሉ እንደ ሰሙት ደርቡሽ በዚህ ዓመት በሰኔ ፲፮ ወጥቶ ሠፈሩን በተከል ሜዳ አድርጎ አገር ማጥፋቱን ቤተ ክርስቲያን ማቃጠሉንና ሕዝበ ክርስቲያኑን ማረዱን ስለ ሰሙ ነው።

ደርቡሽም አጼ ዮሐንስ በግስጋሴ መምጣታቸውን በሰማ ጊዜ በፍጠንት ድንኳኑን ነቅሎ በሽሽት ወደ መተማ ወረደ።

ከዚህም በኋላ አጼ ዮሐንስ በቤጌምድር አውራጃ አሞራ ገደል ከሚባለው ሲደርሱ ከመኳንንቶቻቸው ጋራ ምክር አድርገው «ደርቡሽ ወደ ጐንደር ለመውጣት የመሰናዳቱን እርግጠኝነት አግኝተንዋል። ቢሆንም በመጀመሪያ ወደ ጐጃም ሄደን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ወግተን ደርቡሽ ጊዜ የሚሰጠን ሲሆን ንጉሥ ምኒልክን ለመውጋት ወደ ሸዋ እንዘምታለን። ጊዜ የማይሰጠን የሆነ እንደ ሆነ ከጐጃም ወደ መተማ ወርደን ደርቡሽን መውጋት ይሻለናል» በማለት ምክሩ ተቆረጠና ከቤጌምድር ወደ ጐጃም ተጓዙ።

የልዑል ራስ አርአያ ሥላሴ ሚስት የነበሩት ልዕልት ዘውዲቱም ወደ ሸዋ ለመመለስ ከአጼ ዮሐንስ ጋራ ይጓዙ ነበር። ስለዚም የትግሬ /የትግራይ/ መኳንንት ባንድነት ሆነው «ንጉሥ ምኒልክ ከእኛ መከዳታቸው እርግጥ ከሆነ ልጃቸው ልዕልት ዘውዲቱ እንደ መያዣ ይሆኑናልና ወደ ሸዋ እንዳይመለሱ ብናቆያቸው ይሻላል» ብለው መክረው ነበር። አጼ ዮሐንስ ግን «በአባቷ በደል እርስዋን አልቀጣምና ምንም ቢሆን ይህን ምክራችሁን አልቀበልም» አሏቸው።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የአጼ ዮሐንስን መምጣጥ በሰሙ ጊዜ ሙተራ ወደ ሚባለው አምባ ወጥተው ተቀመጡ። አፄ ዮሐንስም የሙተራን አምባ በመድፍ ለማፍረስ ቢሞከሩ በዚያን ዘመን የነበረው መድፍ እንደ ዛሬው ዘመን መድፍ በሩቅ ሄዶ ሥራ አይሠራም ነበርና አምባውን ለማፍረስ የማይችሉ ሆኑ። በዚህም ነገር እጅግ ስለ ተናደዱ አገሩን ጐጃምን ያጠፉት ጀመር። በሌላው ሥፍራ ይቅርና ጐጃሜው ከመከራው የሚድን እየመሰለው ገንዘቡን እየያዘ በየቤተ ክርስቲያኑ እየተማጠነ ሲገባ የትግሬው /ትግራዩ/ ወታደር በኃይል እየገባ ገንዘቡን እየቀማ እምቢ ያለውንም እየገደለው ይወጣ ነበር።

ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አጼ ዮሐንስን ለመከዳት ሲማማሉ አጼ ዮሐንስ ወደ ጐጃም የሄዱ እንደ ሆነ ንጉሥ ምኒልክ በስተጀርባ በወሎ ዞረው ቤጌምድር ላይ ሆነው ሊረዱ፣ ወደ ሸዋም የመጡ እንደ ሆነ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በቤጌምድር ዞረው በስተጀርባ መጥተው ሊረዱ ነበር።

ነገር ግን አጼ ዮሐንስ ጐጃም ገብተው አገሩን እየዞሩ ሲያጠፉ ንጉሥ ምኒልክ ሠራዊታቸውን በአዋጅ ሰብስበው ከደራ እስከ ወለጋ በዓባይ ዳር ዳር አሠልፈው እርሳቸው በእንጦጦ ከተማ ሆነው ይጠባበቁ ነበር እንጂ በወሎ ዞረው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ለመርዳት አላሰቡም ነበር።

ቢሆንም ንጉሥ ምኒልክ የዲፕሎማቲክ ዕውቀት ያላቸው ነበርና «ጃንሆይ አገርዎ ጐጃምን ለምን ያጠፉታል? ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም በድሎ ተገኝቶ እንደ ሆነ ይማሩት። ለዚሁም ነገር እኔ እንዳስታርቃችሁ ይፍቀዱልኝ» እያሉ ይጽፉ ነበር።

አጼ ዮሐንስ ግን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ያስከዱ ንጉሥ ምኒልክ መሆናቸውን ያውቁ ነበርና የሚልኩባቸውን ነገር ሁሉ አምነው አይቀበሏቸውም ነበር።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አጼ ዮሐንስ ጐጃምን እንዳጠፉት ንጉሥ ምኒልክም ለእዳታ እንዳመጡላቸው አይተው ከመታረቅ በቀር ሌላ የሚሻል ነገር አላገኝም ብለው እንዳያስሩአቸው ቃል ኪዳን አስገብተው ከሙተራ አምባ ወርደው በዕርቅ ገቡ።

# ምዕራፍ ፵፺

## አጼ ዮሐንስ በንጉሥ ምኒልክ ስለ መቀየማቸውና ወደ ልዑል ራስ ዳርጌ የወቀሳ ቃል ስለ መላካቸው።

ሳይጠፉኝ ይህን ሁሉ እየሰማሁ ዝም ብል በመጨረሻው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን አባብላችሁ አስከዳችሁት። ስለ ከዳ ግን አገሩ ጠፋበት፣ ተጐዳ እንጂ አሁን እግዚአብሔር ምህረት አውርዶ ታርቆ ገባ። ደግሞ እኔ እግዚአብሔር የትህትና ደካማ ነኝ እንጂ የሰው ደካማ አይደለሁም። የኔን ነገር የሚገዛው የለም።



ራስ ዳርጌ ሣህለሥላሴ

ይህን ሁሉ እያደረገ እናንተንና እኔን ሰይጣን ሆኖ የሚያፋጀውን መንግሥት ሊያፈርስ የሚጥር የዓለምን ሁሉ ቋንቋ ሲያጠና የሚኖር ነፍስ አባት አይሉት የሰው አገር ሰው ቤጌምድሬ መሸሻ ወርቁ የሚሉ መካር አበጅታችሁ ተንኮሉ ሁሉ ምንጭ እርሱ ነው እንጂ፣ የንጉሡም የእናንተም ይህን ያህክ እንደሌለ አውቃለሁ። አሁንም እኔ ግድ የለኝም አስተውላችሁ ብትመክሩበት ይሻላል። ደብዳቤውንም እርስዎ አይተው ወደ ልጅዎ ወደ

ንጉሥ ይስደዱት። ተጽህፈ በዳሞት ሠፈር አመ ፲ወ፰ ለኅዳር በ፲ወ፰፻፸፮ ዓመተ ምሕረት።

ልዑል ራስ ዳርጌም የአጼ ዮሐንስ ደብዳቤ ባዩ ጊዜ በነገሩ እጅግ ስለ ደነገጡ በቶሎ ወደ ንጉሥ ምኒልክ ላኩባቸው።

ንጉሥ ምኒልክም ሳያስቡት ይህ እጅግ የበረታ የወቀሳ ቃል ወደ ራስ ዳርጌ ስለ መጣ አጼ ዮሐንስ ቃላቸውን የሚያምኑላቸው ስለ መሰላቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጽፈው በልዑል ራስ ዳርጌ በኩል ወደ አጼ ዮሐንስ ላኩ።

«ይድረስ ከሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የተላከ ከንጉሥ ምኒልክ። ወደ ራስ ዳርጌ የመጣው የጃንሆይ ደብዳቤ ደረሰልኝ። ሰይጣናት ብሰው አድረው በእኔና በጃንሆይ መካከል ነቅዕ ስለአገቡብን ደብዳቤውን አይቼ አዘንሁ።

እኔም ከመሥጋቴ በቀር ከያዝሁት መንግሥት ፈልጌ እንደ ሆነ ጃንሆይንም ጠልቼ የጃንሆይ መንግሥት እንዲናወጥ አድርጌ እንደሆነ እግዚአብሔር ምስክሬ ነው። ደግሞ እስካሁን በጃንሆይ ትዕግሥት በጃንሆይ ልበ ጥሩነት ነው እንጂ ሠራዊቱማ የሚያወራብኝ ብዙ ነው። ፊት ደርቡሽን አመጡ ተብዬ ነበር። ኋላም ኢጣልያ ቢመጣ ይህንኑ አለኝ። እኔ ግን ይህ ሁሉ ቢወራ ግድ የለም ከጦርነቱና ከሞቱ የተለየሁ እንደ ሆነ ያን ጊዜ ሁሉም ይታወቃል ብዬ ሠራዊቱን አስከትቼ ብመጣ ጃንሆይ ወደ ድርቡሽ አዘዙኝ።

እኔም ደስ ብሎኝ እግዚአብሔር ኃይል ቢሰጠኝ የክርስቲያንን ደም እመልሳለሁ፣ ብሞትም ሰማዕትነት እቀበላለሁ፣ ብዬ ሄድሁ። በእግዚአብሔር ቸርነት በጃንሆይ ሀብት ጠላታችን ሸሽቶ ቢሄድ ታርቀው ሄዱ እያለ ያወራል አሉ።

ዳግመኛ ጃንሆይ ባዘዙልኝ ቃል ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መልካም አድርጎ ቢቀበልኝ ደስ ብሎኝ ክርስቲያን ወንድም ለወንድሙ መርጠብ ይገባል መስሎኝ ሁለት መድፍና ፪፻፶ ጠመንጃ ረጥቤው መጣሁ። ይህ ነውር ሆኖብኝ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ያስከዱ ጐጃምን ያስጠፉ ንጉሥ ምኒልክ ናቸው ይለኛል አሉ።

ደግሞ የጃንሆይ ደብዳቤ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን አባብላችሁ አስከዳችሁት ይላል።

ከእንግዲህ ወዲህ የዚህን ነገር ብናገር ሀሰት እንጂ እውነት አይመስልም። ካልጠፋ መንገድ በጐጃም መምጣቴ ነው የሚያሳዝነኝ።

ነገሩንም እግዚአብሔር ባወቀ ይግለጸው። «እኔማ ወይሰበክ ወንጌለ መንግሥተ ሰማያት ውስተ ኩሉ ዓለም። ከመ ይኩን ስምዓ ላዕለ ኩሉ አሕዛብ» ያለው በጃንሆይ ጊዜ ደርሶ ሊፈፀም ነው ብዬ ሳለሁ የኛን አንድነት ሰይጣናት አፍርሰው የመሐመድ ቁራን በኢትዮጵያ ሊነገርበት ይሆን ብዬ አዝኜ ነበርሁ። አሁንም የፈራሁበትን ነገር ከምሕረትዎ ጋራ ላባታችን ለአቡነ ማቴዎስ ነግሬአለሁ። ለራስ ዳርጌም ጽፌአለሁ። በታኅሣሥ በ፲፫ ቀን በ፲፰፻፹፩ ዓመተ ምሕረት በእንጦጦ ከተማ ተጻፈ።»

ልዑል ራስ ዳርጌም አጼ ዮሐንስ ለጻፉላቸው የወቀሳ ቃል ምላሽ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጽፈው ከንጉሥ ምኒልክ ደብዳቤ ጋራ ባንድነት አድርገው ለአጼ ዮሐንስ ላኩላቸው።

«ይድረስ ከሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥስት ዘኢትዮጵያ»

«ወደ እኔ የተላከው የጃንሆይ ደብዳቤ ደረሰልኝ። እኔን ሽማግሌ አድርገው አስበው ስለላኩብኝ እግዚአብሔር በምሕረት ልቡናው ያስብዎ። ደብዳቤውንም እኔ ዓይቼ ወደ ንጉሥ ምኒልክ ሰደድሁት።

ሰይጣን ባልሆነ ሰዎች አድሮ ነገር ሲያበላሽ እያዩ ምነው ዝም ይላሉ ብለው የላኩብኝንም ነገሩን ማወቁ ጃንሆይ ጐጃምን ከረገጡ ወዲህ ነው እንጂ ከዚዒያ በፊት የሰማሁት ነገር አልነበረም።

ነገር ግን የጃንሆ ልብ ጥሩ ነውና ይህን ደብዳቤ ስለላኩብኝ እጅግ ደስ አለኝ። ከንጉሥ ምኒልክ የመጣልኝን ማኅተም ነገሩ የተንኮል የክፋት እንዳልሆነ ባየው ከንጉሥ ሳላስፈቅድ ጃንሆይ እንዲያዩት ብዬ ይኸው ሰድጄዋለሁ።

አሁንም ደግነትና ምሕረት ልማድዎ ነውና ከልብዎ ይማሩት። ማግባቱን ግን ሥጋት ከሆነበት ጃንሆይ የሰይጣናትን ክንፍ ይስበሩ። ኋላም ነገሩ እየተመረመረ እንደዚህ ቀደሙ ፍቅርዎ ስቦት ቶሎ እንዲገባ አውቃለሁ።

እግዚአብሔር ምክሩንና ጥበቡን ይግለጽልዎ።

የተላከ ከራስ ዳርጌ። ክርስቶስ ጤና ይስጥልኝ ብዬ እጅ እነሣለሁ።

በታኅሣሥ ፲፫ ቀን በ፲፰፻፹፩ ዓመተ ምሕረት ተጻፈ።»

አጼ ዮሐንስም የንጉሥ ምኒልክንና የልዑል ራስ ዳርጌን ደብዳቤዎች ካነበቡ በኋላ በምላሹ እንደ ፊተኛው ለልዑል ራስ ዳርጌ ጻፉላቸው እንጂ ለንጉሥ ምኒልክ ምንም አልጻፉም። ምክንያቱም በነገሩ በጣም ስለ አዘኑበትና ንጉሥ ምኒልክንም ስለ አለማመናቸው ይመስላል።

መልዕክት ዘሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ይድረስ ከራስ ዳርጌ እንዴት ሰነበቱ? እኔ ከሠራዊቴ ጋራ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። አመ ፲ወ፫ ለታኅሣሥ የተጻፈውም ደብዳቤዎ ደረሰልኝ። ኢጣልያ የመምጣቴ ወሬ የመጣልኝ በሐረርጌ በደጃዝማች መኮንን በኩል ነው። ኢጣሊያንን ንጉሥ ምኒሊልክ አመጡት እያሉ በደጅ ይጫወቱ እንደ ሆነ እንጂ ፊቴ ደፍሮ እንዲህ ያለ የሚናገር የለም። ከዚያ በኋላም መምጣቱ ከታወቀ ወዲያ ጃንሆይ የጦሩ ዕለት እንዳልለይ ያድርጉልኝ የሚል የንጉሥ ቃል በአቡነ ማቴዎስ መጣልኝ። እሺ ብዬ ወደ ንጉሥ ላክሁኝ። ከዚያ ወዲያ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ድል ሆኖ ነበርና ዳግመኛ ክርስቲያኑን ደርቡሽ ወጥቶ ይፈጀዋል ብዬ ቢያሳዝነኝ በእግዚአብሔር ፈቃድ ለኢጣሊያው እኛ እንበቃዋለን አምባጫራ ላይ ሆኖ እርሱን መጠበቅ ይሻላል ብዬ ወደ ንጉሥ ላክሁኝ። ይህም ሆነ አልቀረም። በምጥዋም በመተማም ያለውን ጠላታችንን እግዚአብሔር አሳፈረው።

ንጉሥ ምኒሊልክ ከደርቡሽ ጋራ ተላልከዋል ብለው የደምቢያና የቤጌምድር ሰዎች ይጫወቱ እንደ ሆነ እንጂ ከእኔ መኳንንቶች አፍ እንዲህ ያለ ነገር አይወጣም። እኔም መቅደላ እከርማለሁ ብዬ ሳለሁ ደርቡሽ ወጣ ቢሉኝ ክርስቲያኑን ይፈጀዋል ብዬ ወደ ቤጌምድር ወርጄ አሞራ ገደል ሠፍሬ ሳለሁ ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አሲረው ከድተዋል። ተማምለዋል። ወደ ኢጣሊያም እኛና እናንተ አንድ ነን ብለው ጽፈው አትመው ሰደዋል። ጃንሆይም ነገሥታቱ ከድተዋቸዋል። በወዲያውም ደርቡሽ መጥቶባቸዋል እንግዴህ ምን ኃይል አላቸው እያሉ ኢጣሊያኖች ይሳለቁብዎታል የሚሉ ወሬ ሰውማሁ። በዚህ ምክንያት ጐጃም የተነሳ ነው።

የመተማመኑ ነገር ግን እኔ አልከዳሁ፣ መሃላ አላፈረስሁ አፍርሼ እንደሆንሁ ክርስቲያን አልባልም። ዳግመኛስ የምንተመመነው የፊቱን ማን አፍርሶት ነው። በእኔም በንጉሥም ፈርሶ እንደ ሆነ ከዚህ ከእኔ ጋራ ብዙ መኳንንት በወዲያም ብዙ መኳንንት አሉና በያሉበት ሆነው መርምረው እገሌ ከድቷል እገሌ መሃላውን አፍርሷል ይበሉነ። ከዚያ ወዲያም ወደ ቁም ነገራችን እንሄዳለን።

ተጽሕፈ በዳሞት ሠፈር። አመ ፭ወ፮ ለታኅሣሥ በ፲ወ፰፻፹፩ ዓመተ ምሕረት።»

ልዑል ራስ ዳርጌም ይህን ደብዳቤ ካነበቡ በኋላ ለንጉሥ ምኒልክ ልከውላቸው ነበርና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በመካከላቸው የነበረውን ምሥጢር ለአጼ ዮሐንስ በማውጣታቸው ንጉሥ ምኒልክ ስለ ተሰናዱ እርሳቸውም በበኩላቸው የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ምሥጢር እያወጡ ጽፈው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ለአጼ ዮሐንስ ላኩላቸው።

ይድረስ ከሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን፣ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። የተላከ ከንጉሥ ምኒልክ።

«ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን እውነት ልትከዱኝ ተማምላችሁ ኑርዋልን? ወደ ኢጣሊያስ ልካችሁ ኑርዋልን? ብዬ ብጠይቀው ከጃንሆይ ጋራ አልዋጋም ብያለሁ እንጂ መሃላውንስ ተማምያለሁ አለኝ የሚል አገኘሁ። መከዳቱን ከድቻለሁ መዋጋት ግን አልዋጋም ማለት ይህ ስንፍና ነው እንጂ መቼ ትሕትና ነው? ነገሩም ሐሰት መሆኑ በዚህ ይታወቃል።

መሃላ ተማምለን ነበር ወደ ኢጣሊያም ተላልከን ነበር፣ ያለውን ግን አሁን እኔ ብናገር እውነት አይመስልም። ነገር ግን «አልቦ ክዱን ዘኢያስተርኢ። ወአልቦ ኅቡዕ ዘኢይትከሠት» እንዳለ እግዚአብሔር ይግለጠው። እኔ ግን የማልሁት መሃላ እንደዚህ ብዬ ነው።

ካምባጫራ ተነሥቼ ፎገራ ስደርስ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፫ መነኮሳት ላከብኝ። የመጣችሁበት ነገሩ ምንድነው ብዬ ብጠይቃቸው «ባገሬ ላይ ሊመጡብኝ ነውና ንጉሥን አስታምኑልኝ» ብለዋል ብለው ቢነግሩኝ ቀድሞ «ጃንሆይ አማምለውና አገዛዝተው አስታርቀውናል። አሁን ደግሞ ከጠረጠረኝ መጥቶ አይገናኝ እንጂ ቢሻው አምባው ይግባ አለዚያም ከፈቀደው ቦታ ይቀመጥ።

እኔ ጃንሆይ ባዘዙኝ መንገዴ እሄዳለሁ ብዬ ለጊዜው ተቆጣሁ። በኋላ ግን ነገሩ ይህ አይደለም የማጫውትዎ ብርቱ ምሥጢር አለኝ። ይህነን ለሰው እንዳያስወጡብኝ አስታምኑልኝ ያሉት ስለዚህ ነው ቢሉኝ ለዚህማ ምን ከፋኝ ብዬ ታመንሁ። ወዲያው ጐጃም ገባሁ።

ከርሱ ከተገናኘን በኋላ ምን ጠርጥረኸኝ ነው ማል ተገዘት ብለህ መነኮሳት የላክህብኝ? ብዬ ጠየቅሁት። ራስ አርአያ ሥላሴ ደጃች ሥዩምን ይዞ እንደ ሰጠ እኔንም ጃንሆይ ይያዙት ብለዎ እንደ ሆነ ነው የሰጋሁት አለኝ።

በምን ምክንያት ምን አጠፋህና እንደዚህ ያለ ነገር ይደረጋል? ይህስ እውነት አይመስለኝም አልሁት።

እርስዎም ኢጣሊያን አመጡ ተብሎ ታምተዋል።

እኔንም የኢጣሊያ መንግሥትና የጐጃም መንግሥት አንድ ነው ብለህ ጽፈሃል ብለው ጠልተውኛል። ከገባንም ሁለታችንንም አይተውንም ይይዙናል አለኝ።

ይህ በምን ይታወቃል ብለው አሁን መጥተው ጐጃም ይከርማሉ። እኔም ከዚያ ከድንጋዬ ገብቼ እሞታለሁ እንጂ አልገባም አለኝ። ሰይጣናት በፍቅር ይቀናሉ የኛን አንድነት ለመለየት ነው እንጂ ጃንሆስ እንዲህ ያለ ነገር አያደርጉም። አሁንም ወደ ጐጃም የመጡ እንደ ሆነ ነገሩ ተገልጦ እንዲምሩህ እንድትታረቅ ወደ ጃንሆይ ደብዳቤ እልክልሃለሁ ብዬው መጣሁ።

ወዲያው ደግሞ ንጉሥ ምኒልክ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መድፍና ብዙ ነፍጥ ሰጥተው ተማምለው መጡ ተብሎ ይህን ጃንሆይ ሰምተው ራስ አሉላ በሰሜን በኩል ተጓዙ ጃንሆይ መምጣታቸው ነውና ይጠንቀቁ ብሎ እዚያ ያለ ወዳጄ ላከብኝ።

ወዲያው ደግሞ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከዳኝ ወደ ጐጃም ተሻገርኩ የሚል የጃንሆይ ደብዳቤ መጣልኝ።

እኔም ፊት እንደላክሁት ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ለኔም ነግሮኛል ጃንሆይ ተናደው አገርዎን እንዳያጠፉት ብዬ ወደ ጃንሆይ ላክሁ። ተናደው የአገርዎን እንዳያጠፉት ብዬ ወደ ጃንሆይ ላክሁ።

የዚህም ምላሽ ይልቅስ በእኛ በሁለታችን ሰይጣን አይግባብነ፣ እግዚአብሔር እንደሞቱትና እንዳሉት አድርጎ አይለያየነ፣ ባገሩም ጥፋት እግዚአብሔር በፈረደው ይፍረድ የሚል ደብዳቤ መጣልኝ።

እንዲህ መታረቁ ላይቀር ሰይጣን አበርዳለሁ አስታርቃለሁ ብዬ ብልክ የኔ ቃል ሳይሰላልኝ ቀረ። ከዚያ ወዲያ ግን የሆነ ያልሆነውን ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጻፍሁለት በታኅሣሥ ፳ ቀን በ፲፰፻፹፩ ዓመተ ምሕረት በእንጦጦ ከተማ ተጻፈ።

ንጉሥ ምኒልክ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በአጼ ዮሐንስ ላይ የሠሩት ሥራ ምንም ለየራሳቸው ጥቅም ቢሆንም በመካከላቸው ጽኑ መሃላ መደረጉን ሁለቱም ወገኖች መስክረዋል።

ይልቁንም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የማጫውትዎ ብርቱ ምሥጢር አለኝና ይህን ለሰው እንዳያወጡብኝ ይታመኑልኝ ብሎ ሦስት መነኮሳት ቢልክብኝ እሺ ብዬ ታመንሁለት ብለው ንጉሥ ምኒልክ በደብዳቤያቸው መስክረዋል።

ስለዚህ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ንጉሥ ምኒልክም በመካከላቸው የተደረገውን መተማመን አፍርሰው ምስጢራቸውን ለአጼ ዮሐንስ መናገራቸው የማይገባ መሆኑ አእምሮ ያለው ሰው ሁሉ ሊያስተውለው ይችላል።

ስለሆነም አጼ ዮሐንስ በዚህ ወራት ንጉሥ ምኒልክ ለሚጽፉላቸው ደብዳቤ ምላሽ በቀጥታ ለመጻፍ ስለ አልፈቀዱ ምላሹን የሚልኩት ወደ ልዑል ራስ ዳርጌ ነበር። ራስ ዳርጌም ምንም አድራሻው ወደ እርሳቸው እየሆነ ቢጻፍም ምላሹ ለንጉሥ ምኒልክ መሆኑን ያውቁ ነበርና አጼ ዮሐንስ በታኅሣሥ ፳፯ ቀን በ፲፰፻፸፩ ዓመተ ምሕረት የጻፉላቸውን ደብዳቤ ለንጉሥ ምኒልክ ስለ ላኩላቸው ንጉሥ ምኒልክ እንደ ገና ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጽፈው ልከው ነበር።

ይድረስ ለሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የተላከ ከንጉሥ ምኒልክ።

«ዳግመኛ የማይተማመን የፊቱን ማን አፍርሶ ነው? በኔም በንጉሥም ፈርሶ እንደሆነ ከዚህም ከእኔ ጋር ብዙ መኳንንት ከወዲያም ከሸዋ ብዙ መኳንንት አሉ።

በያሉበት ሆነው መርምረው እገሌ ከድቷል እገሌ አፍርሷል ይበሉና የሚል ቃል አገኘሁ። ነገር ግን መጀመሪያ የተማመነን ጊዜ ካልተገናኘን ወሎን እወስዳለሁ የተገናኘን እንደ ሆነ ግን ለሌላ ሰው አልሰጥም አሉኝ። እኔም ከጃንሆይ የምገባ ነኝ ብዬ ለሰዎቼ ባማከራቸው ከገባንም ከበሽሎ ወዲህ ላለው አገራችን አሳምነን እንግባ ቢሉኝ ለእጄ ብቻ ይታመኑልኝ እንጂ ከገባሁስ አጼ ቴዎድሮስ ሳይሞቱ ጀምሮ ያቀናሁትን አገሬን ወሎን ይነሱኛል ብዬ አልጠረጠርኩም፣ አላምንም ብዬ ገባሁ።

ጃንሆይም በተናገሩት ቃል ከበሽሎ ወዲህ ሰጥቼሃለሁ ብለው አዋጅ ነግረውልኝ ደስ ብሎኝ ተቀምጬ ሳለሁ ወዲያው ደግሞ ራስ ሚካኤል ከፋኝ አሉ። ወረሂመኑን ልቀቅለት አሉኝ። ለቀቅሁ።

ደግሞ የሚኖርበት ሥፍራ ሳላጣ ጃንሆይን በማመኔ ደጃች መሸሻን ሳይንት ላይ ባሥር ፈትተው ወሰዱብኝ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አገሬ ላይ መጥቶ ቢወጋኝ እግዚአብሔር ረድቶኝ እርሱንም መኳንንቱንም ይዤ ብገባ ነፍጡን መልስለት አሉኝ፣ እሺ ብዬ መለስሁ። ደግሞ ወዲያው ወሎን ለኔ አደርገዋለሁ ሐዋርያ እሆንበታለሁና ልቀቅልኝ ቢሉኝ ለራስ ሚካኤል የሰጡብኝ እንደ ሆነ ይከፋኛል እንጂ ላጃንሆይ ከሆነ እሺ ብዬ ለቀቅሁ።

ኋላ ግን ለራስ አርአያ ሥላሴ ቢሰጡት ጥጃ ጠባ፣ ከሆድ ገባ እንዲሉ ለልጄ ከሆነ ብዬ ደስ አለኝ። ወዲያው አይስጡብኝ ላልሁት ለራስ ሚካኤል መልሰው ቢሰጡት እየኖረ ፍቅር እየጨመረ ይሄዳል እንጂ ይጐድላልን ብዬ በዚህ ከፋኝ።

እምነትና ፍቅር ፈረሰብኝ አላልሁም። ባገሬማ እኔ ባልገባ ተማምዬበት አልቆ ነበር። ኋላ ግን ፍቅር እጨምራለሁ ወሎንም አገኛለሁ ብዬ ገባሁ። አሁን ግን ቢቀርብን በቀደመው ውሌ አለሁ ማለቴ ሰለዚህ ነው።

እኔስ ለጃንሆይ ሽማግሌ ምን አስፈልጎኝ? ይህን ደብዳቤ በብሩህ ልብናዎ ተመልከተው ይህ ያስከፋዋል፣ ይህ አያስከፋውም ብለው ጃንሆይ ይፍረዱት።

ደግሞ ይህንን ሁሉ መጻፌ የመድፈሬ አይደለም ጃንሆይ ከፈቀዱልኝ ብዬ ነው እንጂ።

«በጥር ፲ ቀን ፲፰፻፹፩ ዓመተ ምሕረት እንጦጦ ከተማ ተጻፈ።»

አጼ ዮሐንስም ከ ፲፰፻፹፩ አስቀድሞ በየጊዜው ወደ ንጉሥ ምኒልክ የጻፉላቸውን ደብዳቤዎች ስንመለከት የፍቅርና የወዳጅንት የመተማመንና የትሕትና ቃሎች አኝተንባቸዋል። በሐምሌ ፪ ቀን በ፲፰፻፸፬ ዓመተ ምሕረትና በኅዳር ፲፰ ቀን ፲፰፻፹፩ አመተ ምሕረት በተጻፉ ደብዳቤዎች ውስጥ ግን እግጅ የረቀቁና የሚያስገርሙ ሦስት የፖለቲካ ቃሎ ተጽፈው መገኘታቸው ለታሪክ አንባቢዎች በጣም ሳይደንቃቸው አይቀርም።

፩ኛው ቃል ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እምባቦ ላይ በተዋጉ ጊዜ አጼ ዮሐንስ ደብረ ታቦር ላይ ነበሩና የሁለቱ ነገሥታት ወሬ ቢጠፋባቸው ወደ ሸዋ ለመምጣት በቁጣ ተነሥተው ወረይሉ ሲደርሱ የንጉሥ ምኒልክ መላክተኛ ፊታውራሪ ናደው ደርሶ ንጉሥ ምኒልክ ድል ማድረጋቸውን ቢነግራቸው አፍረው ወደ ቤጌምድር ለመመለስ ክረምቱ ተጭኗልና ሠራዊቴ በውሀ ሙላትና በጭቃ ያለቀው አልቆ የተረፈውን ይዤ መመለስ ይሻለኛል ያሉት ነው።

፪ኛው ቃል ንጉሥ ምኒልክ ዒጣሊያን አምጥቷል እየተባልኩ እታማለሁ ብለው ቢጽፉላቸው ኢጣሊያን ንጉሥ ምኒልክ አመጡት እያለ በደጅ ይጫወ እንደሆነ ነው እንጂ በፊቴ ደፍሮ እንደዚህ ያለ ነገር የሚናገር የለም ያሉት ነው።

፫ኛው ቃል ንጉሥ ምኒልክ ከደርቡሽ ጋር ተላልከዋል እየተባልኩ እታማለሁ። ብለው ቢጽፉላቸው ንጉሥ ምኒልክ ከደርቡሽ ጋር ተላልከዋል እያሉ የደምቢያና የቤጌምድር ሰዎች ይጫወቱ እንደ ሆነ እንጂ ከእኔ መኳንንት አፍ ይህን የመሰለ ነገር አይወጣም ያሉት ነው።

አጼ ዮሐንስ በጐጃም ንጉሥ ምኒልክ በእንጦጦ ሆነው ጉዳያቸውን ሁሉ በደብዳቤ ሲላላኩ ልዕልት ዘውዲቱ በዚያው በአጼ ዮሐንስ ሰፈር ነበሩና አባታቸው ታርቀው ለመግባት ፈቃድ እንደሌላቸው በሰሙ ጊዜ «ባሌ ራስ አርአያ ባልሞቱ ጃንሆይና አባቴ

ሳይታረቁ አይቀሩም ነበር» የሚል እጅግ የሚያሳዝን ቃል ስለ ተናገሩ አጼ ዮሐንስ ይህን ሰምተው ራስ አርአያ እንደሞቱበት ቀን መኳንንቱ ሁሉ ተሰብስቦ ትልቅ ልቅሶ ተደረገ ይባላል።

ከዚህም በኋላ በማዕርግና በክብር አድርገው የሚሸኙ መኳንንቶች ጨምረው በሰላሌ በኩል ስለሰደዷቸው መኳንንቱ ወደ እንጦጦ አድርሰው ለአባታቸው ለንጉሥ ምኒልክ አስረከቧቸው።

የሸዋ መኳንንት ግን አጼ ዮሐንስ ልዕልት ዘውዲቱን ለንጉሥ ምኒልክ መያዣና ማስፈራሪያ አድርገው የሚያስቀሩዋቸው ይመስላቸው ነበርና ሁሉም አጼ ዮሐንስን አመሰገኑ።

# ምዕራፍ ፶፫

## ስለ አጼ ዮሐንስ ዕረፍት

ንጉሥ ምኒልክና ተክለ ሃይማኖት በአጼ ዮሐንስ ላይ ተማምለው ስለ ከዱ አጼ ዮሐንስ ጐጃምን ካጠፉት በኋላ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ታርቀው ገቡ። ንጉሥ ምኒልክ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሳይረዱ ወይም ወደ አጼ ዮሐንስ ሳይገቡ ሠራዊታቸውን በአዋጅ ሰብስበው በዓባይ ወንዝ ዳር ለዳር በሰላሌ በግንደ በረትና በጉድሩ ላዩንም ከደራ ጀምሮ እስከ ሳይንት ድረስ አሰልፈው የዲፕሎማቲክ /የማታለል/ ቃል እየጻፉ ወደ አጼ ዮሐንስ እየላኩ በእንጦጦና በአዲስ አበባ ከተማ እየተመላለሱ ወደ ፊት የሚሆነውን ነገር ይጠባበቁ ነበር።

አጼ ዮሐንስም ምንም እንኳ በንጉሥ ምኒልክ ሥራ ቢናደዱም ደርቡሽ ወደ ኢትዮጵያ ወሰን ሊመጣ ይሰናዳል ማለትን ሰምተው ነበርና እርሱ ሳይወጣ እርሳቸው ወደ መተማ ወርደው ለመዋጋት ሲሉ ፊታቸውንው እደ መተማ አዞሩ።

ንጉሥ ምኒልክም አጼ ዮሐንስ ፊታቸውን ወደ መተማ ማዞራቸውን እርግጡን ካገኙት በኋላ በአዋጅ የተሰበሰበው ሠራዊት ሁሉ ወደ እንጦጦ እንዲመለስ አዘዙ።

አጼ ዮሐንስም ፊታቸውን ወደ መተማ ስለማዞራቸው አንዳንድ ሰዎች አጼ ዮሐንስ ሸዋ መጥተው ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ለመዋጋትና ሸዋን እንደ ጐጃም ለማጥፋት ካሰቡ በኋላ የንጉሥ ምኒልክን ሠራዊት ብዛት ቢሰሙ ፈርተው ተመለሱ እያሉ ይናገራሉ።

አንዳንዱ ደግሞ አጼ ዮሐንስ ወደ ሸዋል ለመምጣት ሲነሡ በምሥጢሪ ከንጉሥ ምኒልክ የተላኩ መነኮሳት መጥተው «ወደ ሸዋ የሄድህ እንደሆነ ንጉሥ ምኒልክን ድል ታደርጋለህ፤ በነፍስህ ግን ትጐዳለህ። ወደ መተማ የሔድህ እንደ ሆነ ግን በሰማዕትነት ትሞታለህ፣ በነፍስህ ትጠቅማለህ፣ ቢሏቸው በሥጋዬ ተጠቅሜ በነፍሴ ከምጐዳ ሞት ይሻለኛል ብለው ወደ መተማ ሄዱ» እያሉ ይናገራሉ።

አንዳንዱ ደግሞ ደርቡሽ ለጦርነት መሰናዳቱን ሰምተው ነበርና አሁን ወደ ሸዋ የሂድሁ እንደ ሆነ ደርቡሽ በፍጥነት ወጥቶ የቤጌምድርን አገር ያጠፋዋል ሕዝበ ክርስቲያኑን ያርደዋል ቤተ ክርስቲያኑንም ያቃጥለዋልና እግዚአብሔር ቢረዳኝ በፊት ደርቡሽን ወግቼ ድል ካደረግሁ በኋላ ወደ ሸዋ እዘምታለሁ ብለው መተማ ተጓዙ እያሉ ይናገራሉ።

ስለዚህ ይህን ከዚህ በላይ የተጻፈውን በእውነተኛ ልብ ስንመረምረው ይህ ሦስተኛው የተነገረው ቃል እውነት ነገር ይመስለል።

ከዚህም በኋላ አጼ ዮሐንስ ከጐጃም ተነሥተው በአገው ምድር አልፈው ወደ ደምቢያ ወርደው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና ደርቡሽ ወደ ተዋጉበት ሣር ውሀ ወደሚባለው ሥፍራ ሲደርሱ በጦርነት ውስጥ የሞቱትን የሕዝበ ክርስቲያን አጥንት ብዛቱን አይተው እጅግ አዘኑ። ልባቸውም እንደ እሳት ተቃጠለ።

ከሞትም የተረፉት የጐንደር ሊቃውንት ከዳዊት መዝሙር ፸፰ኛውን ጠቅሰው «እግዚኦ ቦኡ አሕዛብ ውስተ ርስትከ። ወርአኲሱ ጽርሐ መቅደስከ። ወረሰይዋ ለጐንደር ከመ ልገተ ዐቃቤ ቀምሕ። ወረስዩ አብድንቲሆሙ ለአግብርቲከ መብልዓ ለአዕዋፈ ሰማይ። ወሥጋሆሙኒ ለጻድቃኒከ ለአራዊተ ገዳም። ወከዓው ደሞሙ ከመ ማይ ዐውዳ ለሀገረ ደምቢያ። ወኀጥኡ ዘይቀብሮሙ» ብለው ጽፈውላቸው ነበርና ይህን በማንበባቸው የተነሣ ልባቸው በኀዘን እሳት ተቃጠለ።

ከዚያም ወደ መተማ ገሠገሠ። አሳባቸውም በፊት መተማን አጥፍተው ቢመቻቸው ወደ ትልቁ ከተማ ወደ አምዱርማን ለመሄድ ነበር። ከአጼ ዮሐንስም ጋራ የዘመቱ መኳንንቶች ትልቁ ራስ አርአያ ቢትወደድ ገብረ መስቀል ራስ ሚካኤል ራስ ኃይለ ማርያም፣ ራስ አሉላ፣ ራስ መንገሻ፣ ራስ ሀጐስ ነበሩ። የዘመተውም ሠራዊት ሁሉ ቁጥሩ ፻፶ሺ ነበር።

ከዚሁም ከ፻፶ሺ ፳ውሺ ፈረሰኛ ነው። ይህም ወሬ በመተማና በአምዱርማን በተሰማ ጊዜ ሽብርና ድብልቅልቅ ሆነ። የደርቡሽ የጦር አበጋዝ ጀግናው አቡ አንጋ ከሞተ ቦኋላ ዘኪ ከማል የሚባል ሰው የጦር አበጋዝ ሆኖ ተሾሞ ነብርና እርሱ የወታደር

አለቆቹን ሁሉ ሰብስቦ «ጠላቶቻችንን እንዴት ሆነን እንቆያቸው? በውጭ ወይስ በቅጥር ውስጥ?» ብሎ ምክር ቢጠይቅ ቃዲ አህመድ የሚባለው «በሜዳ ተሰልፈን እንቆያቸው እንደሆነ ሐበሾች ፈረሰኞች ናቸውና በፈረስ አጎዳ ይጥሱናል። ስለዚህ እዚሁ አጥራችን ውስጥ ተሰልፈን ብንቆያቸው ይሻለናል» ብሎ መከረ። ዜኬም ሠራዊቱን ቢያስቆጥረው ፹፫ሺ ሆነ። ይህን አጥር ውስት አሠለፈው። በተረፈ በየገበያውና በየመንደሩ ዋጅ ነጋሪ እየሰደደ ነጋዴውን ከንግዱ ላይ ገበሬውን ከእርሻው እያስነሳ የጦር መሣሪያ እያስያዘ አሠለፈው። ወደ ከሊፋም መልክት ልኮ «እዘንልኝ፤ ረዳትም ስደድልኝ ወደ ሀበሾችም ሰላይ ልኬ ነበርና ብዛታቸው እንደ ሰማይ ኮከብ እንደ ባሕር አሸዋ ነው። ሲጓዙም ከብዛታቸው የተነሳ ምድሩ ትቢያ እንደ ደመና ሆኖ ፀሐይን ይከልላታል ብሎ ካርቱም ድረስ ይመጣሉ ፈረሶቻቸውም እስከ እምቢያቸው ድረስ በሰው ደም እየተነከሩ በነጭ አባይ ዳር በበቀለው ዛፍ ይታሠራሉ የሚባል ንግር አለና ይኸ ሁሉ ያስፈራኛል» ብሎ ላከበት። ከዚያም አጼ ዮሐንስ የየካቲ ወር ሲያልቅ መተማ ደረሱ። ለጦሩ አበጋዝ ለዘኬም «መጣሁብህ ተዘጋጅተህ ቆየኝ። እንደ ሌባ በድንገት መጣብኝ እንዳትለኝ መመጣቴም የክርስቲያንን ደም ለመበቀል ነው» ብለው ላኩበት።

በመጋቢት ፩ ቀን ፲፰፻፹፩ ዓመተ ምሕረት ቅዳሜ ጦርነት ተጋጠሙ። ከሠራዊቱም ብዛት የተነሣ ትቢያው እንደ ደመና እየሆነ ሰውና ሰው ፍጽሱም አይተያይም ነበር።

በዚያን ጊዜ በከተማው ውስጥ ያሉት የሴቶቹ፣ የሕፃናቱ፣ የሽማግሌው፣ የባልቴቱ ጩኸትና ልቅሶ ጀግናው ሲፎክርና ሲያቅራራ ድምጡ እየተደባለቀ የክረምት ነጐድጓድ ይመስል ነበር ይባላል። በብርቱ ጦርነት ውስጥ ያለ ሰው ሁሉ እየሸሸ እንዲወጣ ብለው ቤቱንና ቅጥሩን አቃጥሉት። ባንድ ወገንም ዘልቀው ግምጃ ቤቱን ያዙት። ያቡ አንጋንም አጽም ለማቃጠል ቤቱን ሁሉ ይቀሰቅሱ ጀመር። ይህንንም ያሰቡት ምክንያት አቡ አንጋ ጐንደርን አጥፍቶ ሊቃውንቱን ሁሉ በእሳት አቃጥሏቸው ነበርና የዚያን ብድር ለመመለስ ነበር። ነገር ግን አጼ ዮሐንስ ምንም ጠንክረው ቢዋጉ ድል ማድረጋቸው ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አይሆንምና ድል ለማድረግ ጥቂት ሲቀራቸው አጼ ዮሐንስም በጠመንጃ ቆሰሉና ወሬው ያንጊዜውን በየሠልፉ ውስጥ ተሰማ። መኳንንቱም ወታደሩም ከቅጥሩ ውስጥ እየወጡ መሸሽ ጀመሩ።

አጼ ዮሐንስም ከመቁሰላቸው የተነሣ ሰውነታቸው መድከሙን ስለ ተረዱ የወንድማቸውን የደጃች ጉግሣን ልጅ ራስ ኃይለ ማርያምን አልጋ ወራሽ ለማድረግ አስበው ጳጳሱንና እጨጌውን ለጊዜውም ባጠገባቸው የተገኙትን ትልልቆች መኳንንቶች ሰብስበው «ራስ ኃይለ ማርያምን ጥሩት!» ቢሉ በጦርነቱ ስለ ቆሰሉ ለመምጣት አይችሉም አሏቸው። እርሳቸው ግን አይችልም ያሉኝ ቢሞት ነው ብለው በጣም አዘኑ።

ቀጥሎውም ወንድሙ ራስ መንገሻ ነውና ለርሱ ተገዙ ብለው የኑዛዜ ቃል ተናገሩ በማግሥቱ አረፉ።

ያጼ ዮሐንስ ሬሣ በሣጥን ውስጥ አግብተው ይዘው ወደ አትባራ ወንዝ ፊታቸውን መልሰው ሸሹ። ጳጳሱ አቡነ ጴጥሮስና እጨጌ ቴዎፍሎስም ከመኳንንቱ ጋር አብረው ሸሽተው አመለጡ። ንጉሡና ወታደሮቹ ስለ ሃይማኖታቸው እየፎከሩ በሠልፍ ውስጥ እየገቡ ሲሞቱ ጳጳሱና እጨጌው ሞት ፈርተው በመሸሻቸው እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያ ሰው ሁሉ ይገርመዋል።

ደርቡሾችም በጦርነት ውስጥ የሞቱትን የኢትዮጵያ መኳንንቶች ሁሉ ራሳቸውን እየቆረጡ ኦምዱርማን ድረስ ለከሊፋ አብደላ ላኩለት። በማግስቱም ሐበሾች እንደ ገና ተመልሰው አደጋ ይጥሉብናል እያሉ ሰፈሩ አደሩ። ነገር ግን ሰላይ ልከው ነበርና ሰላዩ ተመልሰው ፊታቸውን ወደ አትባራ ወንዝ አድርገው ይሸሻሉ እንጂ አንድ መኮንን እንኳ ተዳፍሮ ወደ እኛ ወገን ፊቱን ያዞረ የለም ብሎ ተናገረና በዚያ ጊዜ የጦር አበጋዙ ዛኪከማል ሠራዊቱን ሁሉስ ሰብስቦ በድንጉላ ፈረስና በግመል ጠያር እየሆነ እግር ለእግር ተከታተላቸው።

በመጋቢት ፫ ቀን የአጼ ዮሐንስ ሬሳ ይዘው የሚጓዙትም መኳንንቶች በአትባራ ወንዝ ዳር ሠፍረው ደረሰባቸውና አደጋ ጥሎ ተዋጋቸው።


የአጼ ዮሐንስ አሽከሮችና መኳንንቶች ግን በድንኳን ዙሪያ ተሠልፈው እርስ በርሳቸው እየተፏከሩ ተዋጉ። የጌታችንን ሬሳ ሳንሞት አናስማርክም ብለው በዚያው በድንኳኑ በር በሬሳው ላይ የሞቱት ሰዎች ትልቁ ራስ አርአያ ቢትወደድ ገብረ መስቀል የዘበኞች አለቃ ደጃች ተድላ ብላታ ገብረ ማርያም አዛዥ ወንድምሁነኝ አዛዥ ላዕኩ ድራግ - ማሰሬ ዘሚካኤል መምህር ወልደ አረጋዊ መምህር ክንፈ ኪሩብ ቄስ ገበዝ ሰላማ ናቸው።

ከዚህ በኋላ ደርቡሾቹ በድንኳን ውስጥ አንድ ትልቅ ሣጥን አገኙ። ሣጥንኑም በሰም ተመርጐ ነበር። በመጀመሪያ ገንዘብ ያለበት መስሏቸው ነበር። ቢከፍቱት ግን የሰው ሬሣ ሆኖ አገኙት ወዲያው ከምርኮኞቹ አንዱን ሰው አቅርበው ቢጠይቁት የአጼ ዮሐንስ ሬሳ ነው አሏቸው። በሳጥኑም አጠገብ ከሬሳው ጋራ በብራና የተጻፈ ገብታው በባህር ዓረብና በወርቅ የተለበጠ አርባዕቱ ወንጌል፣ የዕለት የሳምንት የወር የዓእምት ቁጥር የሚቆጠር የወርቅ ሰዓት። ትልቅ መነጥር ከንግሥት ቪክቶሪያ የመጣላቸው የሰላምታ ደብዳቤና አንድ ባለ ፈርጥ መስቀል ተገኘ። ደርቦሾችም የአጼ ዮሐንስ ሬሳ መሆኑን ከተረዱ በኋላ ራሳቸውን ቆርጠው ለከሊፋ አብዱላሂ ወደ ኦምዱርማን ሰደዱለት። ከሊፋ አብዱላሂም ያንን ባየ ጊዜ ይህንን በመስማት ደስ አለው። ከሦስት ቀን በኋላ የአጼ

ዮሐንስ በእንጨት ላይ ሰክቶ በግመል ጀርባ ላይ አድርጐ ገበያ ለገበያ መንደር ለመንደር እያዞረ ለትልቅ ለትንሹ ለሴት ለወንዱ ስያሳየው ዋለው ይባላል።

ከሁለቱም ጦርነት እየሸሹ ያመለጡት ጳጳሱ አቡነ ጴጥሮስና እጨጌ ቴዎፍሎስ ከመኳንንቱም ብዙዎቹ በሠፈር ወገን እየለዩ ይጓዙ ነበር። ምክንያቱም አጼ ዮሐንስ ከልዑል ራስ አርአያ ሥላሴ በቀር ሌላ ልጅ አልነበራቸውም። የወንድሞቻቸውን ልጆች የደጃች ጉግሣ ምርጫ ልጅ ራስ መንገሻ የደጃች ማሩ ምርጫ ልጅ ደጃች መሸሻ፣ የትልቁ ራስ አርአያ ልጅ ደጃች ቦጋለ አልጋ ወራሽ እንሆናለን በማለት ገና አስቀድሞ እርስ በርሳቸው ይቀናኑ ነበረ።

ነገር ግን አጼ ዮሐንስ ገና ሳይሞቱ አልጋ ወራሼ ራስ መንገሻ ነው ማለታቸውም ከዘመቻው አስቀድሞ የራስነት ማዕርግ ሰጠው በክብር አብልጥው የሚወዷቸው ራስ መንገሻ ጉግሣ መሆናቸውን የሚያውቁ ከመኳንንቱም ከሠራዊቱም ብዙዎቹ ወደ ራስ መንገሻ ወገን ሆነው ነበር። ስለዚህም ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስና እጨጌ ቴዎፍሎስ ራስ አሉና ራስ ሀጐስ ራስ ሚካኤልና ፊታውራሪ ለውጤ እነዚህንም የመሰሉት ሁሉ ባንድነት ተሰብስበው «የእነዚህ የጃንሆይ ዘምዶች አኳኋን እጅግ የሚያሰጋ ነው። ራስ ወልደ ሥላሴ ከልጃቸው ከደጃች ነጋሽ ጋራ በሰሜን ሆነው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በጐጃም ሆነው፣ ንጉሥ ምንልክ በወሎ ሆነው ይጠባበቁናል በዚህ ላይ ደግሞ በመካከላችን ስምምነት ካልተገኘ ወደ ሀገራችን ለመግባት እንኳ መቸገራችን አይቀርምና የአጼ ዮሐንስን የኑዛዜ ቃል ለመኳንንቱም ለሠራዊቱም በአዋጅ ብናስትውቅ ይሻላል» ብለው ምክራችውን ጨረሱ።



ራስ መንገሻ ዮሐንስ

ከዚህም በኋላ መኳንንቱንም ሠራዊቱንም ሰብስበው «ጃንሆይ አልጋ ወራሼ ልጄ ራስ መንገሻ ነውና እኔ ካረፍኩ በኋላ ለርሱ ተገዙ ብለው ተናዝዋል» የሚል የአዋጅ ቃል ተነገረና ከደጃች መሸሻ በቀር ሁሉም አሜን ብሎ ተቀበለ።

ደጃች ቦጋለና ደጃች መሸሻ ግን «ለጃንሆይ ልጅ የላቸውም። በወንድም ልጅነት የሆነ እንደ ሆነ ግን ሁላችንም እኩል ነንና አገራችን ከገባን በኋላ እግዚአብሔር

ለሚሰጠው ይሰጠዋል» እያሉ ልብሳቸውን በአፍንጫቸው ላይ እያደረጉና እያጉረመረሙ ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ ይባላል።

ከብዙ ዘመን በኋላ የአጼ ዮሐንስን ታሪክ ያነበበ አንድ ኢትዮጵያዊ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የምስጢር ግጥም ገጠመላቸው።

አጼ ዮሐንስ ሞኝ ናቸው።

እኛም ሁላችንም ናቅናቸው።

ንጉሥ ቢሏቸው በማኻሉ።

ወሰን ጠባቂ ልሁን አሉ።

አጼ ዮሐንስ ይዋሻሉ።

መጠጥ አልጠጣም ይላሉ።

ሲጠጡ አይተናል በርግጥ።

ራስ የሚያዞር መጠጥ።

# ምዕራፍ ፵፬

## ንጉሥ ምኒልክ ወደ ወሎ ሲሄዱ የአጼ ዮሐንስን ዕረፍት ስለ መስማታቸው

ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ተማምለው ከአጼ ዮሐንስ መክዳታቸው መጀመሪያ ለጐጃም አገር ጥፋት ሆነ። ቀጥሎም ለአጼ ዮሐንስ ሞት ምክንያት በመሆኑ አዕምሮ ያለውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚያሳዝን ሆነ። ቢሆንም ንጉሥ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት የሚገባኝ ከቀዳማዊ ምኒልክ ዘር ለተወለድሁ ለእኔ ነው በማለት ይህንኑ ለማግኘት ነበር። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ግን ይገባኛል የሚሉ አልነበሩምና አጼ ዮሐንስን ለመክዳት የደረሱበት ምክንያቱ ለማንም አልተገለጠም።

ነገር ግን የንጉሥ ምኒልክና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አደራረግ የኢጣሊያና የደርቡሽ ጦርነት ከተጨረሰ በኋላ ተደርጐ የነበረ ለኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች የተመቸ ሆኖ ታሪክ አንባቢዎችን ሁሉ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ይሆን ነበር። ምን ይሆናል። ቀረና።

የኢትዮጵያ አንበሳ አጼ ዮሐንስ ወደ መተማ ወርደው የኢትዮጵያን ጠላት ደርቡሽን ለመውጋት ቁርጥ አሳብ አድርገው ከጐጃም ተነስተው ጉዞ ሲጀምሩ ንጉሥ ምኒልክም

በየካቲት ፲፰ ፲፰፻፹፩ ዓመተ ምሕረት ከእንጦጦ ተነስተው ወደ ወሎ ጉዞ ጀመሩ። ወደ ወሎም ለመሄድ ያሰቡት ምክንያቱን ምን አልባት አጼ ዮሐንስ መተማ ላይ ከደርቡሽ ጋራ ሲዋጉ ድል የሆኑ እንደሆነ ደርቡሽ ተከታትሎ ወጥቶ የቤጌምድርን አገር እንዳያጠፋና ሕዝበ ክርስቲያኑንም እንዳይገልድ በወሎና በቤጌምድር ወሰን ሆነው ለመጠባበቅ ነበር።

ንጉሥ ምኒልክም ወቀት የሚባል አገር ሲደርሱ በመጋቢት ፲፯ ቀን የአጼ ዮሐንስ ሞት ተረድተው ነበርና አራት ቀን ያህል በኀዘን ሰነበቱ።

አጼ ዮሐንስ የሞቱት በመጋቢት ፪ ቀን ነው። ንጉሥ ምኒልክ በመጋቢት ፲፯ ቀን ከተረዱ ከመተማ እስከ ቀወት ወሬው በ፲፭ ቀን መድረሱ ነው።

በዚያን ጊዜ የኢጣሊያ መንግሥት መላክተኛ ኮንት አንቶኔሊ ከንጉሥ ምኒልክ ጋራ ይጓዝ ነበርና ለኢጣሊያ ንጉሥ እንዲልክላቸው በመጋቢት ፲፰ ፲፰፻፹፩ ዓመተ ምሕረት የተጻፈ አንድ ደብዳቤ ሰጡት። በደብዳቤውም ውስጥ የተጻፈው ዋና ዋናው ቃል ቀጥሎ ያለው ነው።

፩ኛ። አንበሳው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ከደርቡሽ ጋራ ሲዋጉ ድል ሆነው አረፉ የሚል።

፪ኛ። ከኢትዮጵያ መንግሥት እየከዱ ከትግሬም /ከትግራይም/ ወጥተው በበረሀ የሚኖሩ እይታጡምና በምጥዋ ያሉት የእርስዎ መኳንንቶች የነዚያን ቃል እንዳይሰሙና እንዳያምኑ የጦር መሣሪያም እንዳይሰጧቸው ያስታውቋቸው የሚል።

፫ኛ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለመሆን የተገባኝ ስለ መሆኔ ከብዙ ዘመን ጀምሮ ምኞቴ ነውና ይህ ምኞቴ ነውና ይህ ምኞቴ በትክክል እንዲፈጸምልኝ ወደ እግዚአብሔር ይለምኑልኝ የሚል ነው። ሌላውም ትንንሹ ነገር በረጅሙ ሆኖ ተጽፎ ሰጡትና በአሳብ በኩል በፍጥነት ላከላቸው።

ከዚህም በኋላ ወደ ወሎ ተጉዘው ከዚያም በዋድላ አውራጃ ቋና ከሚባል አገር ሲደርሱ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ተገናኙ። በዚያውም ትልቅ ሹም ሽር ተደረገና ስለ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በያዙት አገር ላይ ከፋን ጨመሩላቸ። ደጃዝማች ወሌን ራስ ብለው ከጨጨሆ በላይ ያለውን የየጁን ግዛት የቤጌምድርንና የደምቢያን ቆራጭነት፣ ለዋግሹም ብሩ የዋግን ዋግሹምነት ለጃንጥራር አስፋው አምባሰልን፣ ለራስ ወልደ ሥላሴ ሰሜንን ለራስ መሸሻ ቴዎድሮስ ደምቢያን ሰጥተው የቀሩትን የቤጌምድርን መኳንንቶች እንደያዛችሁ ቆዩ አሏቸው።

ራስ መንገሻ ግን መጥቼ ልገናኝ ብለው ሳይልኩ በመቅረታቸው አጼ ምኒልክ እስከ ትግሬ /ትግራይ/ ብቅ ለማለት አስበው ነበር። እንገር ግን ባንድ ወገን በኢትዮጵያ የከብት በሽታ ገብቶ ከብቱ ሁሉ በማለቁ በሁለተኛውም ወገን የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ጭነው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሳይባሉ ወደ ትግሬ /ትግራይ/ መሄድ ደስ ስላላሰኛቸው የትግሬን /የትግራይን/ መንገድ አሳባቸውን ለጊዜው አቆይተው ወደ ሸዋ ለመመለስ ቁርጥ አሳብ አደረጉ።

ቢሆንም አጼ ምኒልክ በጣም የፖለቲካ ዕውቀት ነበራቸውና ራስ መንገሻ ሙሉ ትግሬ /ትግራይ/ መቸውንም የእኔ ግዛት ነው ብለ በኋለኛው ሹም ሽር እንዳያስቸግርዋቸው በሚመጣው ዓመት እመለሳለሁና እስከዝያ ሙሉ ትግሬን /ትግራይን/ እየጠበቅህ ቆይ የሚል ትእዛዝ አሳለፉላቸው።

# ምዕራፍ ፶

## በአጼ ምኒልክና በኢጣሊያ መንግሥት መካከል በውጫሌ ሠፈር ስለ ተደረገው ውል።

ኮንት አንቶኔሊ ንጉሥ ምኒልክ በአጼ ዮሐንስ ላይ እንዲነሱ ለማድረግ ከብዙ ዘመን ጀምሮ ሲጣጣር ነበርና አሁን በአጼ ዮሐንስ ሞት አሳቡ ሁሉ የሚቃናለት ስለመሰለው ንጉሥ ምኒልክ በአምባሰል አውራጃ ውጫሌ በሚባል አገር ሠፍረው ሳሉ አስቀድሞ ያዘጋጀውን የወል አሳብ ይዞ ቀርቦ «እንግዴህ የአጼ ዮሐንስ ነገር ከተጨረሰልን የብዙ ዘመን ጀምሮ ልናደርገው አስበን የቆየነው በሁለቱ መንግሥቶች መካከል ጸንቶ የሚኖር የወዳጅነት ውል እንድንዋዋልና እንድፈራረም ፍቃድዎ ይሁንልኝ» ብሎ ስለ አመለከታቸው በኢጣሊያ ቋንቋ የተጻፈውን ቃል በጥንቃቄ ሳይመረምሩ በኮክንት አንቶኔሊና በአስተርጓሚው በግራዝማች ዮሴፍ ንጉሤ እምነት እሺ ብለው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ውል ተፈራረሙ።

የኢጣሊያ ንጉሥ ዑምቤርቶ በስም መጀመሪያ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ዘኢትዮጵያ መንግሥት ለኢጣሊያ መንግሥት የሚጠቅም ለልጅ ልጅ የሚኖር ሰላምና ዕርቅ ለማድረግ የፍቅርና የንግድ ውል ተዋዋሉ።

የኢጣሊያ ንጉሥ ኮንት አንቶኔሊን በኢጣሊያ መንግሥት ዘውድ ኒሻን ኮማንዳቶሬ ተብሎ የተሾመ፣ በአልዛርና በሞሪስ ኒሻን ካባልዬሬ ተብሎ የተሾመ ተመርጦ እንደራሴ ሆኖ ወደ ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ሙሉ ሥልጣን ተቀብሎ የተላከ፣ የተቀበለውንም ሙሉ

ሥልጣን በንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ፊት በርግጥ የተቀበለ ስለሆነ ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ የኢትዮጵያን አልጋ የወረሱ እርስዎ ስለሆኑ ይኸን ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ውል ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ጋራ ተዋዋልን።

## መጀመሪያ ክፍል

በኢጣሊያ ንጉሥና በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መካከል በወራሾቻቸውና በሕዝቦቻቸውም፤ እነዚህንም በተጠጉ ሕዝብ መካከል ሰላምና ፍቅር ሳይጐድል ለዘወትር ለልጅ ልጅ ይኖራል።

## ፪ተኛ ክፍል።

እነዚህ ሁለቱ አሁን የተዋዋሉት በየሀገራቸው በየምሳለኔዎቻቸው ይነጋገራሉ። አንዱ ካንዱ ቆንሲልም ወኪልም መሾም ይቻላቸዋል። እነዚህም ሹሞች እንደ አውሮፓ ነገሥታት ሥርዓት መታፈርና መከበር አይጎድልባቸውም።

## ፫ተኛ ክፍል።

በነዚህ በ፪ ነገሥታት ወሰን ጠብና ክርክር እንዳይነሣ በዕውቀት የተመረጡ ከ፪ቱ ወገኖች ሁለት ሽማግሌዎች ልከው በማይጠፋ ምልክት የግዛቱን ድምበር ይወስናሉ። ከድምበሩ ወዲህ የሚጨምሩት አገሮች እነዚህ ናቸው። የደጋው አፋፍ ከኢትዮጵያና ከኢጣሊያ መሃል ወሰን ይሆናል። ከራፋሊ ጀምሮ ሐላይና፣ ሰገነይቲ፣ አሥመራ ሦስቱ የኢጣሊያ መንግሥት መንደር ይሆናሉ። ዳግመኛ በቦገስ በኩል አዲ ነፋስና ዓዲ ዋስን በኢጣሊያ ድምበር ውስጥ ይሆናሉ። ከአዲ ዋስን መንደር ጀምሮ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ባቀና ይከፈላል።

## ፬ተኛ ክፍል።

የደብረ ቢዘን ገዳም ከነጉልቱ ከነርስቱ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደ ሆነ ይቀራል። የጦር አምባ መሆን ግን አይቻለውም።

## ፭ተኛ ክፍል።

ከምጥዋ የሚወጣ የንግድ ዕቃ የሚገባም የንግድ ዕቃ ከመቶ ፰ በገቢ ዕቃ እየተገመገመ በገቢ አንድ ጊዜ ይከፈላል።

## ፮ተኛ ክፍል።

የጦር መሣሪያ ንግድ ከምጥዋና በኢትዮጵያ መካከል የሚመላለሰው ለንጉሠ ነገሥት ብቻ ይፈቀድልዎታል። ሲያስመጡም ባለ ማኅተም ደብዳቤውን ለኢጣሊያ ሹማምንት እየላኩ ያስመጣሉ። ነፍጡንም የያዘውን ሠፈር ከምጥዋ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድምበር ድረስ የኢጣሊያ መንግሥት ወታደሮች ዘበኛ ሁነው ይሸኛሉ።

## ፯ተኛ ክፍል።

የነዚህ የ፪ቱ ውል ያደረጉ ነገሥታት ዜጎች የንግድ ዕቃቸውን ይዘው አንዱ ካንዱ አገር መሄድና መምጣት ይቻላቸዋል። በየመንግሥቱና በየወረዳው ባለው ሹም ጥግነት ደስ ብሏቸው ይመላለሳሉ። ነገር ግን ከ፪ቱም ወገኖች የጦር መሣሪያ የያዘ ብዙ ሆኖ ከ፩ዱ ድምበር ወደ አንዱ ድምበር መተላለፍ ተከልክሏል። እንዲሁም ማለት ፩ዱ ያ፩ዱን ከብት እንዳይዘርፍ በሁሉ ነገር እንዳይነካካ ተከልክሏል።

## ፰ተኛ ክፍል።

የኢጣሊያ ሰዎች በኢትዮጵያ። የኢትዮጵያ ሰዎች በኢጣሊኢያ የኢጣሊያ መንግሥት በሚገዛው አገር ቢሆንም እንዳገሩ ልማድ መግዛት መሸጥ መከራየት ይቻላቸዋል።

## ፱ተኛ ክፍል።

የዚህን የ፪ቱ ነገሥታት ዜጎች ፩ዱ ካንዱ አገር ቢሄድ በየሃይማኖታቸው ይኖራሉ

## ፲ኛ ክፍል።

የኢጣሊያ ሰውና የኢጣሊያ ሰው የተካሰሱ እንደሆነ እነዚያ በመረጡት ዳኛ ለዚያውም ተያይዘው ምጥዋ ወርደው ይዳኛሉ። የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ሰው የተጣላ እንደሆነ ግን የኢትዮጵያ መንግሥት ወኪልና የኢጣሊያ የምጥዋ ሹም አንድነት ሁነው ይዳኛሉ።

## ፲፩ኛ ክፍል።

የኢጣሊያ ሰው በኢትዮጵያ የሞተ እንደ ሆነ የኢትዮጵያ ሰው በኢጣሊያ አገርና በኢጣሊያም መንግሥት በሚገዛው አገር የሞተ እንደ ሆነ ከሟቹ መንግሥት ወገን ገንዘቡን የሚቀበል ሰው እስኪመጣ ድረስ የ፪ቱ ነገሥታት ሹማምንት ገንዘቡን ጠብቀው ያስቀምጣሉ።

## ፲፪ኛ ክፍል።

በማናቸውም ኃጢያት ተከሶ የተያዘ የኢጣሊያ ሰው በኢጣሊያ ሹማምንት ይዳኛል። ስለሆነ ግን ታላቅ ኃጢአት ሠርቶ የተገኘውን የኢጣሊያን ሰው ፈጥኖ ይዘው ለምጥዋ ሹማምንት መስጠት ነው። ደግሞ በኢጣሊያ መንግሥት ግዛት የኢትዮጵያ ሰው ታላቅ ኃጢአት ሠርቶ የተገኘ እንደሆነ በኢትዮጵያ ዳኛ ይዳኛሉ።

## ፲፫ተኛ ክፍል።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና የኢጣሊያ ንጉሥ ብርቱ ኃጢአት የሠራ ካንዱ ግዛት ወደ አንዱ ግዛት ሸሽቶ እንደሆነ ሁለቱም እያሠሩ ይልካሉ።

## ፲፬ተኛ ክፍል።

የባሪያ ንግድ በክርስቲያን ሃይማኖት የተከለከለ ስለሆነ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በሚቻላቸው ነገር ሁሉ ባገራቸው ባሪያ እንዳይነገድ ይከለክላሉ።

## ፲፭ተኛ ክፍል።

ይህ አሁን የተጻፈው ውል ለኢትዮጵያ መንግሥት ሁሉ ውል ነው።

## ፲፮ተኛ ክፍል።

ይህ ውል በተደረገ ከ፭ት ዓመት በኋላ ከኹልቱ መንግሥት አንዳቸው ውል ለመጨመር ወይም ለመለወጥ የፈለጋቸው እንደሆነ ከዓመት በፊት አስቀድሞ መናገር ይገባቸዋል። ነገር ግን የንግድ ውል ብቻ ማረም ማስጠንቀቅ ይቻላቸዋል እንጂ፣ ዛሬ የተለየውን የድንበር ወሰን ማፍረስ አይቻላቸውም።

## ፲፯ተኛ ክፍል።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከኤውሮፓ ነገሥታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ በኢጣሊያ መንግሥት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል።



የኢጣሊያ ንጉሥ ቀዳማዊ ዑምቤርቶ

## ፲፯ተኛ ክፍል።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከሌላ መንግሥት ሰዎች ጋራ የጥበብ የንግድ ነገር ለመዋዋል የፈለጉ እንደሆነ ከ፩ቱም ውል አንድ እንደ ሆነ ለኢጣሊኢያ ሰው ይሰጡታል።

## ፲፰ተኛ ክፍል።

ይህ አሁን የተደረገው ውል በአማርኛና በኢጣሊያ ቋንቋ ትክክል ሆኖ ተገልብጦ ስያበቃ የታመነ ምስክር ይሆናል።

## ፳ኛ ክፍል።

ይህ አሁን የተጻፈው ውል ለሮማ ከተማ ፈጥኖ ይጠነቀቃል። ነገር ግን ይህ ውል ኮንት ፒየትሮ አንቶሌሊ በኢጣሊያ ንጉሥ ስም ከንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ጋራ ተዋውለው አትመው ጨርሰዋል። በሚያዝያ በ፳፫ ቀን በ፲፰፻፹፩ ዓመተ ምሕረት በውጫሌ ሠፈር ተጻፈ።

አጼ ምኒልክ በውጫሌ ላይ ከኮንት አንቶኔሊ ጋራ ውሉን ተፈራርመው በቋና ላይ የሹም ሽሩን ነገር ከጨረሱ በኋላ ወደ ሸዋ ተመልሰው በሐምሌ ፱ ቀን እንጦጦ ከተማ ገቡ።

ደርቡሽ ግን አፄ ምኒልክ ወደ ሸዋ መመለሳቸውን ስለሰማ በነሐሴ ወር እንደገና ወደ ጐንደር ወጥቶ ከቀድሞው አደጋ የተረፉትን ሽማግሎችን ሁሉ በሰይፍ ገደላቸው።

ከነዚሁም መካከል የጥቂቶቹን ስም እንጽፋለን። መምሕር ወልደ ሚካኤል የሚባሉት የሐዲስ መጻሕፍት ስመ ጥሩ መምሕር ነበሩና በጉባዔ ተቀምጠው ሲያስተምሩ ደርቡሽ መጣ ሲሉ ቢሰሙ ከእናንተ መካከል የፈራ ቢኖር ወጥቶ ይሽሽ ያልፈራ ግን ከእኔ ጋራ ይቆይ እያሉ ለደቀ መዛሙርቶቻቸው ሲናገሩ ወዲያው ደርቡሽ ሰይፉን መዞ «አላህ ኢለላህ መሐመድ ረሱል አላህ!» እያለ ገብቶ በጉባዔው መካከል ቆመ። መምሕር ወልደ ሚካኤልም ከሰባቱ ደቀ መዛሙቶቻቸው ጋራ «ነአምን በክርስቶስ አምላክነ» እያሉ በሰማዕትነት አረፉ።


ደግሞ አንጣጭ ፈንታ የሚባል ልጅን በክንዱ እንደታቀፈ ደርቡሽ መጣ ቢሉት «ልጄ ሆይ! መቸም ሞት አይቀርልንምና ዛሬውኑ እንደወረደው» እያለ የክርስቶስን ስም እየጠራ በሰማዕትነት አረፈ።



የውጫሌውን ውል የተዋዋለው ፒዬትሮ አንቶኔሊ

ሦስተኛም አዕምሮ የሚባለ ለጐንደር በዓታ መሪ ጌታ በድምጠ መልካምነቱና በዜማው እጅግ ስመ ጥሩ ነበር። ደርቡሽም በመጣ ጊዜ ሸሽቶ ከመለጠ በኋላ «ሚስትህ ተማረከች!» ብለው ቢነግሩት «እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየውም» ብሎ እንደ ገና ተመልሶ ወደ ደርቡሽ ሠፈር ገባ። በዚያም ሚስቱን አግኝቶ ከእርሷ ጋራ ለባርነት ወደ መተማ ወረደ። ነገር ግን ትምህርቱ የዜማ ትምህርት ነበር እንጂ

መጻሕፍትን ተምሮ የእግዚአብሔርን ትዕግሥትና ኃይል አያውቅም ነበርና «እግዚአብሔር እኔን ክርስቲያኑን ለእስላም አሳልፎ መስጠቴ ከክርስቲያን እስለምን ቢወድ አይደለምን?» ብሎ ማተቡን በጥሶ ቁርዓን ተምሮ የእስልምና ሃይማኖት መምሕር ሆኖ ሲኖር በዚያው አረፈ።



የውጫሌውን ውል የተረጐሙት ግራዝማች ዮሴፍ

# ምዕራፍ ፵፩

## ልዑል ደጃዝማች መኮንን በአጼ ምኒልክ ተልከው ወደ ኢጣሊያ አገር ስለ መሄዳቸው

ኮንት አንቶኔሊ ከአጼ ምኒልክ ጋር በኖረበት ዘመን ሁሉ በአጼ ዮሐንስና በንጉሥ ምኒልክ መካከል አንድነትና ፍቅር እንዳይሆን በሚቻለው ሁሉ ይጥር ነበርና አጼ ዮሐንስን በንጉሥ ምኒልክ ላይ ለማስቆጣት ሲል አንድ መላክተኛ ወደ ንጉሥ ምኒልክ ምክሩን ተከትለው መላክተኛ ለመላክ ፈቃዳቸው ሆኖ ሳለ አጼ ዮሐንስ በመሥጋት አሳባቸውን ሳይፈጽሙ ቆይተው ነበር። አሁን ግን የአጼ ዮሐንስ ነገር በሞት ስለ ተጠቃለለና የኢትዮጵያንም መንግሥት አደላድለው የመያዛቸውን እርግጠንት ካወቁት በኋላ ከመሳፍንቶቻችውና ከመኳንንቶቻቸው መከከል ልዑል ደጃዝማች መኮንንን መርጠው ወደ ኢጣሊያ አገር ለመላክ ቁርጥ አሳብ አደረጉ።

በኢትዮጵያ በቀድሞ ነገሥታት ዘመን ወደ ውጭ አገር መላክተኛ ለመላክ የታሰበ እንደ ሆነ በሊቅነቱ የታወቀ ከቤተ ክህነት ወገን አንዳንድ ሰው እየተመረጠ ይላክ ነበር እንጂ ከመሳንፍንቱና ከመኳንንት ወገን አንዳንድ ሰው እየተመረጠ ይላክ ነበር እንጂ ከመሳንፍንትና ከመኳንንት ወገን ተልኮ አያውቅም። ይኸውም በአጼ ያዕቆብ ዘመን ወደ ሮሜ አቡነ ኒቆዲሞስ በአጼ ልብነ ድንልግ ዘመን ወደ ፖርቱጊዝ ጻጋ - ዘአብ እንደ ተላኩት ነው።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ለንግድ ለሌላ ጉዳይም ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ የሚኖሩ የውጭ አገር ሰዎች አይታጡም ነበርና ከነዚያ መካከል በንጉሡ ዘንድ በጣም የታወቀቅና የተለመደው እየተመረጠ ይላክ ነአብር። ይኸውም በአጼ ልብነ ድንግል ዘመን ማቴዎስ የሚባል የአርመን አገር ሰው በአጼ - ሠርፀ ድንግል ዘመን ጴጥሮስ የሚባል የእስፓንያ አገር ሰው እንደ ተላኩት ነው።

አሁን ግን በአጼ ምኒልክ ዘመን ጥቂት የሥልጣኔ ሥራ ስለ ተጀመረ የነጋሢነት ዘር ያላቸውን ያከስታቸውን የልዕልት ተናኘ ወርቅን ልጅ ልዑል ደጃዝማች መኮንንን መርጠው በመላካቸው የኢጣሊያ መንግሥት የአጼ ምኒልክ የወዳጅንት መልዕክት ከፍ አድርጎ ገምቶት ነበር።

ልዑል ደጃዝማች መኮንን የነጋሢ ተወላጅ በመሆናቸው ላይ ድሯ ኢንተርናሽናል የሚባለውን የዓለም መንግሥታት የተስማሙበትን ደንብና ሕግ ከውጭ አገር ሰዎች በመስማት ስለለመዱ በጣም የታወቁ ነበሩና አጼ ምኒልክ ማናቸውንም የውጭ አገር ጉዳይ በልዑል ደጃዝማች መኮንን በኩል እንዲጨረስ ያደርጉ ነበር። ይህም አደራረግ

በዚያ ዘመን በአገራችን ስላልተለመደ ነው እንጂ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንደ ማለት ነው።



ደጃዝማች መኮንንና ተከታዮቻቸው በሮማ

ልዑል ደጃዝማች መኮንን በዲፕሎማቲክና በፖለቲካ ሥራ በጣም የሰለጠኑ በጦርነትም ረገድ ስመ ጥሩ ዐርበኛ በመሆናቸው ላይ ለአጼ ምኒልክ በልዩ ታማኛቸው ነበሩ።

ከኢትዮጵያ ሰዎችም አልፎ በውጭ አገር ዘንድ እጅግ የተመሰገኑ ነበሩ።

የውጭ አገርም ሰዎች የደጃዝማች መኮንን ዕውቀትና ረቂቅ የሆነ ሥራቸውን እያዩ ንጉሥ ምኒልክ ቢሞቱ እንኳን አልጋውን ለመውረስ የሚገባቸው ደጃዝማች መኮንን ናቸው እያሉ ይናገሩላቸው ነበር።

ይህም ሁሉ ሲሆን የነጋሢ ተወላ ወይም የንጉሥ ባለሟል ነኝ በማለት በማንም ላይ ኩራትና ትዕቢት አልነበራቸውም።

ወደ ኢጣሊያም አገር የተላኩት በዚህ ሁሉ ዕውቀታቸውን ታማኝነታቸው ስለ ተመረጡ ነው። ተልከው ሲሄዱ የውጫሌውን ውል የተረጐመው ግራዝማች ዮሴፍ ንጉሤ አስተርጓሚ ሆኖ ሄዶ ነበር። ከመኳንንቶቻቸውም ወገን ተከትለው የሄዱት

ቀኛዝማች ገነሜ፣ ቀኛዝማች ቆለጭ፣ ቀኛዝማች ተገኔ፣ ባላምባራስ አሰግድ፣ መምህር ወልደ ሚካኤል ነበሩ። ደጃዝማች መኮንንም ከሐረሪ ተነስተው ወደ ኢጣሊያ ዋና ከተማ ወደ ሮማ በደረሱ ጊዜ በታላቅ ማዕርግና ክብር ተቀበሏቸው።

አጼ ምኒልክም «ደጃዝማች መኮንን በቃል ልኬዋለሁና ይነግርዎታል» የሚል የሰላምታ ደብዳቤ ብቻ ለግርማዊ የኢጣሊያ ንጉሥ ጽፈው ነበርና ልዑል ደጃዝማች መኮንን የሰላምታውን ደብዳቤ ካስረከቡ በኋላ በንጉሡ ፊት ቆመው በቃል የላኩትን አራቱን ጉዳዮች በግራዝማች ዮሴፍ አስተርጓሚነት ተናገሩ።

፩ኛው ጉዳይ። የኢትዮጵያ መንግሥትና የኢጣሊያ መንግሥት ማናቸውንም ነገር ለመጠያየቅ ፍቅራቸው የተገለጠ እንዲሆን ነው።

፪ኛው ጉዳይ። በኮንት አንቶኔሊ በፊትም በፍቅር የተደረገው ውል እንዲታደስ ነው።

፫ኛው ጉዳይ። የኢትዮጵያና በአሥመራ ያሉት የኢጣሊያ መኳንንቶች ሁኔታ ሰላምና ፍቅር እንዲሆንና በውጫሌም የተደረገውን የድንበር ውል እንዲጠብቁ ነው።

፬ኛው ጉዳይ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከኢጣሊያ መንግሥት ተስማምቶ ላገሩ ጥቅም የሚሆነውን የንግድ ስራ ከማስፋት በቀር ሌላ አሳብ እንደሌለው ለማረጋገጥ ነው።

የኢጣሊያም ንጉሥ ደጃዝማች መኮንን የተናገሩትን ቃል ሰምተው «ምላሹን አስበን ወደ አገርዎ በሚመለሱበት ጊዜ እናስታውቃለን» ብለው ለማረፊያ ወደ ተዘጋጀላቸው ሥፍራ ሰደዷቸው።

በሚመለሱበትም ጊዜ በነገሩ ሁሉ ተስማምተው በውሉም የሚጨመረው ተጨምሮ የሚታደሰው ታድሶ ተፈራርመው ከሮማ ተነሡ።

ነገር ግን ገና ወደ ኢትዮጵያ ሳይደርሱ በአሥመራ ያለው ጀኔራል ባልዴሣራ የሚባለው በውጫሌ በተፈረመው በ፫ኛው ክፍል የተጻፈውን የወሰን ውል አፍርሶ ወደ መረብና ወደ ሙና በሰላም ወጥቶ የኢጣሊያንን ሰደቅ ዓላማ አቆመበት።

ይህንንም ማድረጉ አልበቃውምና አጼ ምኒልክን ለማስቆጣት ሲል ራስ መንገሻ በራስ አሉላ ረዳትነት ከእርስዎ ጋራ ተዋግተው በትግሬ /በትግራይ/ በአባታቸው አልጋ ለመቀመጥ ጦር ያሰናዳሉ እያለ ወደ አጼ ምኒልክ ይልክ ጀመር።

አጼ ምኒልክም ነገሩ እውነት መሆኑን ለመረዳት ሲሉ የራስ መንገሻን አኳኋን አሰልለው የራስ መንገሻ አሳብ ለአጼ ምኒልክ ታዛዥ ሆነው በኢትዮጵያ ጠላት እንዳይገባበት ከመከላከል በቀር አሳብ እንደሌላቸው አውቀው ዝም አሉ።

ጄኔራል ባልዴሣራ ግን ፖለቲካው ሳይዝለት በመቅረቱ እጅግ አዘነ።

ከዚህም በኋላ አጼ ምኒልክ ከቋና ተነስተው በደሴ አድርገው በሐምሌ ፱ ቀን ፲፰፻፹፩ ዓመተ ምሕረት እንጦጦ ከተማ ገቡ።

# ምዕራፍ ፵፱

## አጼ ምኒልክ የንጉሠ ነተሥት ዘውድ ስለ መጫናቸው።

አጼ ምኒልክ ከላይ የቀዳማዊ ምኒልክ ከታችም የልብነ ድንልግ ዘር በመሆናቸው ከብዙ ዘመን ጀምሮ ሲመኙት የነበረውን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት ስለ አገኙ እንደ ሕጉ በሊቀ ጳጳሱ በአቡነ ማቴዎስ እጅ ቅብዓ መንግሥት ለመቀባትና የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ለመጫን ለሥርዓተ ንግሥ የሚያስፈልገው ሁሉ እንዲዘጋጅ አዘዙ። ሥርዓተ ንግሡም የሚፈጸምበት በጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፰፻፹፪ ዓመተ ምሕረት በእንጦጦ መንበረ ፀሐይ በተባለ በእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን እንዲሆን ተወስኖ ነበርና ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ እቴጌ ጣይቱ፣ ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ እጨጌ ገብረ ሥላሴ ሌሎችም መኳንንቱና ወይዛዝሩ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄዱ አደሩ። ሊቃውንቱና መዘምራኑም እንደ ሥርዓቱ ለሥርዓተ ንግሥ የሚገባውን ፀሎት ሲጸልዩ አድረው ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን በሊቀ ጳጳሱ በአቡነ ማቴዎስ እጅ ቅብዓ መንግሥት ተቀብተው የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ጫኑ። ሥርዓተ ንግሡም ከተፈጸመ በኋላ ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ ገባሬ ሰናይ ሆነው ቀድሰው ሥጋ ወደሙ አቀበሏቸው።

ከጧቱ 4፡00 ሰዓት ሲሆን አጼ ምኒልክ ዘውድዎን እንደ ጫኑ ልብሰ መንግሥትዎን እንደ ለበሱ በትረ መንግሥታዎን እንደ ያዙ ራሶች በቀኝና በግራ ሊቀ መኳሶች በፊትና በኋላ ሆነው ካህናቱ «ብሩክ አንተ ንጉሠ እስራኤል» እያሉ አንድ ጊዜ ዑደት ከተደረገ በኋላ ከዚያ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ምንጣፍ ተነጥፎ ዙፋን ተዘግቶ ነበርና በምንጣፉ ላይ ቆመው «አርቶዶክሳዊ ንጉሣችሁ እኔ ነኝ! የሚል ቃል ተናግረው በዙፋኑ ላይ ተቀመጡ።»



አጼ ምኒሊክ በንጉሠ ነገሥትነት ልብስ መንግሥት

በዚያ ጊዜ ትንሹም ትልቁም በአንድ ቃል «ሺህ ዓመት ያንግሥዎ!» እያለ በእልልታና በደስታ ይመርቅ ጀመር።

ቀጥሎም «ዕዳ ያለብህ ነፃ ብየሃለሁ! በዱር በገደልም ያለህ ወንጀለኛ ምሬሃለሁና ግባ» የሚል አዋጅ አስነግረው በወርቅ ኮርቻና በወርቅ ዕቃ ባጌጠች በቅሎ ተቀምጠው ወደ እንጦጦ ቤተ መንግሥት ጉዞ ተጀመረ።

በስተፊትም ነጋሪቱ እየተጐሰመ እምቢልታውና መለከቱ እየተነፋ ሕዝቡ በቀኝ የሰሌን ቅጠል /የዘንባባ ዝንጣፊ/ እየያዙ «ሺህ ዓመት ያንግስዎ!» እያሉ በእልልታና በደስታ ወደ ቤተ መንግሥት ደርሰው በዙፋን ሲቀመጡ ፻፩ ጊዜ መድፍ ተተኮሰ። ከዚያም በኋላ ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ለወታደሩና ለካህናቱ ትልቅ ግብዛ ተደርጎ ዋለ።

# ምዕራፍ ፶፫

## ስለ እቴጌ ጣይቱ ዘውድ መጫን።

በሠለጠነው ዓለም ንጉሥና ንግሥት ዘውድ የሚጭኑበት በቤተ ክርስቲያን በአንድ ቀን ነው። በኢትዮጵያ ግን አሁን አጼ ኃይለ ሥላሲኤ እስቲያደርሱት ድረስ እንደ ልማድ ሆኖ ንጉሥ ቅብዓ መንግሥት በተቀባና ዘውድ በጫነ በ፫ኛው ቀን በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ዘውድ ይጭንላት ነበር።

ምክንያቱንም ስንመረምር የእቴጌይቱ ክብር ከንጉሡ ክብር እንዳይስተካከል ስለ ክብርዋ ማነስ የተደረገ ይመስላል።

በዚህም ልማድ አጼ ምኒልክ ቅብዓ መንግሥት ተቀብለው ዘውድ በጫኑ በሦስተኛው ቀን በዚያው በተሰናዳው በሰፊው ዳስ ውስጥ የንጉሰ ነገሥቱ ዙፋን ተዘርግቶ ነበርና አጼ ምኒልክ በዙፋናቸውው ሲቀመጡ እቴጌ ጣይቱም በስተቀኝ በተዘረጋው አነስተኛ ዙፋን ላይ ተቀመጡ።

በዚያን ጊዜ ሊቀ ጳጳሱ አቡነ አምቴዎስ የእቴጌይቱን ዘውድ ከንጉሠ ነገሥቱ ተቀብለው በራሳቸው ላይ ጫኑላቸው። በዚህም ጊዜ ካህናቱ «አክሊለ ተቀጺላ ታንሶሱ» እያሉ በከበሮና በጸናጽል ሲያመሰግኑ መሳፍንቱና መኳንንቱ እየተነሡ በፊታቸው እየቀረቡ እጅ ነሡ። ቀጥሎም ፶፩ ጊዜ መድፍ ተተኮሰ።


በ፯ኛውም ቀን ለመምሕር ገብረ ሥላሴ የእጨጌነት ሹመት ተደረገላቸውና የንግሥ በዓሉ ተጨረሰ።



እቴጌ ጣይቱ የእቴጌነት ዘውድ ከጫኑ በኋላ



አጼ ምኒልክ የነገሡበት የእንጦጦ ማርያም በመጀመሪያ የተሠራው ቤተክርስቲያን



የእንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን በኋላ የተሠራውና እስከ አሁንም ያልወ።



ሊቀጳጳሳቱ አቡነ ማቴዎስ

# ምዕራፍ ፺

## አጼ ምኒልክ ወደ ትግሬ /ትግራይ/ ስለ መሄዳቸው።

አጼ ምኒልክ የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ጭነው ኢትዮጵያን አደላድለው መያዛቸውን ከተረዱ በኋላ የኢትዮጵያ ባላገር አጼ ዮሐንስን የሚጠላበትን ነገር ሁሉ ያውቁት ነበርና አጼ ዮሐንስ እንኳ ሞቱ! አጼ ምኒልክ እንኳን ነገሡ! የሚባሉበትን ሥራ ሁሉ በአዋጅ አስታወቁ።

፩ኛ። አጼ ዮሐንስ የተጠሉበት ዋናው ነገር ባልተማሩ መነኮሳት ምክር እየተመሩ እስላሙን ፈላሻውን አረመኔውን ሳይመር እንዲያው በግድ ተጠመቅና ክርስቲያን ሁን እያሉ አዋጅ በመንገራቸውና አንጠመቅም! ክርስቲያን አንሆንም! ያሉትን በሞትም በስደትም በእሥራትም በልዩ ልዩ መከራና ስቃይም በመቅጣታቸው ነበር። አጼ ምኒልክ ግን ተምሮ በፈቃዱ ተጠምቆ ክርስቲያን ካልሆነ በቀር እንደ አባቱ ሃይማኖት እንዲኖር እንጂ በግድ እንዳይጠመቅ አደረጉለት።

፪ኛ። አጼ ዮሐንስ የተጠሉበት ሌላው ዋና ነገር ማንም ሰው በመሬቱ ላይ ትንባሆይ እንዳይዘራና እንዳይጠጣ አዋጅ በመናገራቸውና በመሬቱ የዘራ መሬቱን ይነጠቃል። ባፉም የጐረሰ ከንፈሩን ይቆረጥ፣ ሱረትም በአፍንጫው የጠጣ አንጫውን ይፎነን፣ በማለታቸው ነበር።

አጼ ምኒልክ ግን ትምባሆ መጠጣት እንደ ጠላ እንደ ጠጅ ልማድ ነው እንጂ፣ በመጽሐፍ የተከለከለ በነፍስም የሚያስኮንን አለመሆኑ አውቀው በትምባሆ ነገር ሰው ሁሉ እንደ ልማዱ እንዲኖር አደረጉለት።

፫ኛ። አጼ ዮሐንስ የተጠሉበት አንዱ ዋና ነገር ካንዱ አገር ወደ አንዱ አገር ሲዘዋወሩ ለወታደራቸው ሁሉ ነፃነት እየሰጡ በየባላገሩ ቤት ተሠሪ እየሆነ እየገባ የባላገሩን እንጀራውን ወጡን ጠላውን ሥጋውን ይኅንንም የመሰለውን ሁሉ በግድ እንዲወስድበት ስለ አደረጉ ነበር። አንዳንዱም የባላገሩን ሚስት በግድ እየያዘ በበሏ ፊት ያስነውራት ነበር ይባላል። አጼ ምኒልክ ግን «ለኋላው ሁሉንም አስቀርልሃለሁ። አሁን ለጊዜው ግን ባላገር የሆንህ እንደ አቅምህ እህል እያወጣ ለወታደር ቀለብ ስጥ እንጂ ወታደር በቤትህ አይግባብህ» የሚል አዋጅ ነገሩለት። ይህንንም የመሰለውን አንዳንድ የከበደ ሸክም ከባላገሩ ጫንቃ ስለ አወረዱለት ደስ አለው።

ከዚህም በኋላ ትግሬ /ትግራይን/ በሙሉ ጠቅለው ለራስ መንገሻ መስጠት ለኋላ ጉዳት የሚያመጣ መስሎ ስለ ታያቸው በትግሬ /በትግራይ/ ሹም ሽር ለማድረግ ሲሉ

ለንጦጦ ከተማ ጠባቂ ልዑ ራስ ዳርጌን ትተው በታኅሣሥ ፱ ቀን ፲፰፻፹፪ ዓመተ ምሕረት ወደ ትግሬ /ትግራይ/ ተጓዙ።

ሐውዜንም በደረሱ ጊዜ የትግሬን /የትግራይን/ አውራጃ ከሦስት ከፍለው ሹም ሽር አደረጉበት።

፩ኛ በስተ ምሥራቅ ያለውን አጋሜን ሥዩ፣ ፪ኛ በስተ ደቡብ ያለውን ዋናውን ከተማ መቀሌን ጨምረው ለራስ መንገሻ ዮሐስን ፫ኛ በራስ መንገሻና በደጃዝማች ሥዩም ግዛት መካከል ያለውን አድዋን ራስ መንገሻንና ደጃዝማች ሥዩምን ኢጣሊያኖችንም እንዲጠባበቅ ብለው ለደጃች መሸሻ ወርቁ ሰጡት።

ከዚህም በኋላ ከብዙ ዘመን ጀምሮ ወደ ሸዋ መጥቶ አጼ ዮሐንስና አጼ ምኒልክ የሚለያዩበትን ሥራ ሲሠራ የሚኖር ኮንት አንቶኔሊ አጼ ምኒልክ ወደ ትግሬ /ትግራይ/ መሄዳቸውን ስለ ሰማ ተከታትሎ እስከ ሐውዜን ሲመጣ አመጣጡ ለወዳጅነት ጉዳይ አለ መሆኑን አውቀዋልና ፊት ነሥት እንጂ እንደ ጥንቱ በማዕርግና በክብር አልተቀበሉትም። ይልቁንም በውጫሌ ከእርሱ ጋራ ከተዋዋሉት ውል ፲፯ኛው ክፍል የተጻፈው ቃል የኢትዮጵያን ነፃነት የሚነካ መሆኑን ተረድቶ ነበርና በዚህ ሁሉ ነገር ኮንት አንቶኔሊን በመልካም ዓይን አላዩትም ነበር። ቢሆንም ጥቅሙን የሚፈልግ ሰው መታገስ የሚገባው መሆኑ የታወቀ ነውና ኮንት አንቶኔሊ አጼ ምኒልክ እርሱን አለመውደዳቸውን እያወቀ እንደ አላውቀ መስሎ በተጓዙበት ሥፍራ ሁሉ አንድም ጊዜ እንኳ ሳይለይ ይጓ ነበር።

ልዑል ደጃዝማች መኮንንም የተላላኩበትን ጉዳይ ለኢጣሊያ ንጉሥ አድርሰው ከኢጣሊያ ሲመለሱ ከናፖሊ ወደ ኢየሩሳሌም የባሕር ጠረፍ ወደ ያፍ በሚሄድበት መርከብ ተሳፍረው ያፋ ሲደርሱ በምድር ባቡር ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ። በኢየሩሳሌም የሚኖሩ የኢትዮጵያ መነኮሳት በታላቅ ክብር ተቀብለው የተቀደሱትን ሥፍራዎች ሁሉ ካሳዩዋቸው በኋላ አርባዕቱ እንስሳ በሚባለው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥጋ ወደሙ ተቀብለው ወደ ያፋ ተመልሰው ወደ ምጥዋ የሚሄድ መርከብ ተሳፈሩ። ከምጥዋ በግስጋሴ መጥተው መቀሌ ላይ ካጼ ምኒልክ ጋራ ተገናኝተው ለተላኩበት ጉዳይ ከንጉሥ ዑምበርቶ የተላኩንት ምላሽ እያስረዱ ተናገሩ። ከዚህም በኋላ አጼ ምኒልክ ወደ ሸዋ የሚመጡበት ጊዜ ደርሶ ነበርና በወሎ ዋና ከተማ በደሴ ሲደርሱ ለደጃዝማች መኮንን የራስ ወርቅ ሰጥተው በራስነት ማዕርግ ስለ ሾሟቸው «ይገባዋል! ይገባዋል!» ተባለላቸው። አጼ ምኒልክም ከጥቂት ሳምንት በኋላ ወደ እንጦጦ ከተማ ሲገቡ ልዑል ራስ መኮንን ከረምቱን ከርመው በጥቢው ወደ ሐረር ወረዱ።

# ምዕራፍ ፵፫

## በውጫሌ በተደረገው ውል በ፲፯ኛው ክፍል በተጻፈው ቃል በአጼ ምኒልክና በኢጣሊያ መንግሥት መካከል ክርክር ስለ መነሳቱ።

አጼ ምኒልክ በ፲፰፻፹፪ ዓመተ ምሕረት ወደ ትግሬ /ትግራይ/ ደርሰውና ሹም ሽር አድርገው ወደ ሸዋ ከተመለሱ በኋላ በውጫሌ ውል በ፲፯ኛው ክፍል የተጻፈው ቃል ታርሞ እንዲታደስ ቢሆን ይሻላል እያሉ አሳባቸውን ለኮንት አንቶኔሊ ይነግሩ ነበር። እርሱ ግን አሳባቸውን የተቀበለ ለመምሰል የኢጣሊያም መንግሥት ይህ ቃል ታርሞ ቢታደስ ፈቃድ ነው እያለ የማታለል ቃል ከነገራቸው በኋላ ምሥጢሩ ያልተገለጠ አንዳንድ ምክንያት እየፈለገና እየፈጠረም ስለ አቀረበባቸው እጅግ ተናደዱ።

በውጫሌ ላይ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና በኢጣሊያ መንግሥት መካከል የተደረገውን ውል ከኢጣሊያንኛ ወደ አማርኛ ቋንቋ የተረጐመው በፊት በአሥመራ በካቶሊክ ሚሲዮን ቤት እየተማረ ያደገ በኋላ ግን ለአጼ ምኒልክ ሎሌ የሆነ ግራዝማች ዮሴፍ የሚባለው ነበር።

በውሉም በ፲፯ኛው ክፍል በኢጣሊያኖች ቋንቋ የተጻፈው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከሌሎች ነገሥታት የሚፈልጉትን ጉዳይ ሁሉ በኢጣሊያ መንግሥት በኩል ለመላላክ ፈቅደዋል ይል ነበር።

ግራዝማች ዮሴፍ ግን አጼ ምኒልክን በመፍራት ይሁን ወይም የኢጣሊያኖች ቋንቋ አጥርቶ ባለማወቁ ይሁን ምክንያቱ አልታወቀም እንጂ ወደ አማርኛ ቋንቋ ሲተረጐም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከሌሎች ነገሥታት የሚፈልጉትን ጉዳይ ሁሉ በኢጣሊያ መንግሥት አጋዥነት ለመላላክ ይችላሉ ብሎ ተርጉሞት ነበርና አጼ ምኒልክ ለጊዜው ጉዳያቸውን ሁሉ ያውም ግዴታ ሳይኖርባቸው ቢፈቅዱ በኢጣሊያ መንግሥት አጋዥነት ይልካሉ ማለቱ መስሏቸው ነበር እንጂ የኢጣሊያ ጥገኝነት መሆኑ አላወቁም ነበር። በኋላ ግን አንዳንድ የውጭ አገር ወዳጆቻቸው የዚህ ትርጓሜው ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ጥገኛ ነች ማለት ነው እያሉ ስለ ነገርዋቸው ይህ ፲፯ኛው ክፍል እንዲሰረዝ መላልሰው ቢጠይቁ የማይሆንላቸው ሆነ።

ይህም በውሉ በ፲፯ኛው ክፍል የተጻፈው ቃል የኢትዮጵያን ነፃነት የሚነካ ዋና ነገር መሆኑ ከታወቀ በኋላ በውጭ በያደባባዩ በውስጥም በቤተ መንግሥቱም ትልቁም ትንሹም ነገሩን እያነሳ ያነጋገረው ነበርና እቴጌ ጣይቱ ነበገሩ ስለ ተናደዱና ስለ አዘኑ ከኮንት አንቶኔሊ ጋራ ክርክሩ በእልፍኝ በፊታቸው እንዲሆን ከአጼ ምኒልክ አስፈቀዱ።



ራስ መኮንን ወልደሚካኤል የራስ ወርቅ አድርገው በራስነት ማዕረግ

ኮንት አንቶኔሊም ወደ እልፍኝ ድረስ እየተጠራ እየገባ ብዙ ክርክር ከተደረገ በኋላ ለ፲፯ኛው የውሉ ክፍል ለውጥ የሚሆን ሌላ የውል አሳብ እንዲያቀርብ ተስማምተው ተለያዩ።

በማግሥቱም ከዚህ ቀጥልኮ ያለውን የውል አሳብ ጽፎ ቀረበ።

ይኸው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከመሬቱ አንድ ክፍል ወይም በ፲፯ኛው የውል ክፍል የተባለውን ጥገኝነት ለሌላ ለውጭ አገር መንግሥት እንዳይሰጥ ግዴታ የገባ እንደ ሆነ ፲፯ኛውን ክፍል ለመለወጥ ይቻላል የሚል ነበር።

በዚያንም ጊዜ አጼ ምኒልክና ልዑል ራስ መኮንን ጥንት አንቶኔሊ ያቀረበው የውል አሳብ መልካም መስሎ ታይቷቸው ነበርና፣ በዚሁ ለመስማማት ፈለጉ። እቴጌ ጣይቱ ግን «እኛ ባለፈው ውል ስንፀፀት አሁን እንደ ገና ከመሬታችን ክፍል ወይም ጥገኝነት ለሌላ ለውጭ አገር መንግሥት ለመስጠት ፈቃድ የለንም። ነገር ግን ብንሰጥም ባንሰጥም በእኛው ፈቃድ ብቻ ይሆናል እንጂ ኮንት አንቶኔሊ ሊጠይቀን አይገባውም። እኛም ለዚህ ነገር ግዴታ መግባት አያስፈልገንምና ይህ ቃል በውሉ ውስጥ ሲገባ አይታየኝም» ብለው አሳባቸውን ገልጠው ተናገሩ።

ኮንት አንቶኔሊም እቴጌ ጣይቱ በተናገሩት ነገር እጅግ ስለ ተቆጣ «የውሉን አሳብ እቴጌ ጽፈው ያቅርቡና እናየዋለን» ብሎ የድፍረት ቃል ተናገራቸው።

እቴጌም «እሺ መልካም ነው። እኛም እንጽፋለን አንተም ሌላ ጻፍና አምጣ» ብለው ተለያዩ።

በማግሥቱም እቴጌ ጣይቱ በውጫሌ ውል በ፲፯ኛው የውሉ ክፍል የተጻፈው ቃል በጭራሽ ተፍቆ ቀርቷል የሚል ቃል ብቻ ጽፈው ያቀርቡለት በ፲፯ኛው ክፍል ውስጥ ለኢጣሊያ መንግሥት ጥቅም የሚሆን ሌላ ቃል ካልተጨምረበት የፊተኛው ውል እንደ ጸና ይቆያል እንጂ አይለወጥም ብሎ ተቆጥቶ ወጣ።

ወደ ቤቱም ከገባ በኋላ «አጼ ምኒልክ ሥልጣናቸውን ሁሉ ለሴት ለቀው ያላግጡብናል» እያለ ለባልጀሮቹ ነገራቸው። ወደ ሮማ ከተመለሰ በኋላ ግን የእቴጌ ጣይቱን ብርታትና ዕውቀት እያመሰገነ «እቴጌ ጣይቱ ባይኖሩ አጼ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ለመሆን ብዙ ችግር ሳያገኛቸው አይቀርም» እያለ ለየወዳጆቹ ሲናእር ነበር ይባላል።




ግርማዊት እቴጌ ጣይቱ

በዚያን ጊዜ ለአጼ ምኒልክና ለልዑል ራስ መኮንን የታያቸው በዚህ ምክንያት ጦርነት እንዳይደረግና የክርስቲያን ደም እንዳይፈስ ጥገኝነቱ ከቀረልን ለሌላ መንግሥት አንሰጥም ብለን ብንዋዋል ጉዳት አይደለም ማለት ነበር።

ለእቴጌ ጣይቱ የታያቸው ኮንት አንቶኔሊ እንዳቀረበው አሳብ ብንዋዋል ባገራችን የፈቀድነውን ካልሠራን ያው ነፃነትን ማጣት ነው ማለት ነበር።

በማናቸውም ቢሆን ስምምነት ሳይደረግ ኮንት አንቶኔሊ ወደ ኢጣሊያ አገር ተመልሶ ሄደ።

# ምዕራፍ ፵፮

## ስለ ራስ መንገሻና ስለ ኢጣሊያኖች የወዳጅነት ውል።

ኢጣሊያኖች በፊት በአጼ ዮሐንስና በንጉሥ ምኒልክ መካከል ጠብ እንዲነሳና እንዲዋጉ ለማድረግ በብዙ ይጥሩ ነበር።

ንጉሥ ምኒልክም ለጊዜው የታያቸው በጦርነትም በማናቸውም አደራረግ በሆን የጼኢ ዮሐንስን ኃይል አድክመው እርሳቸው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለመባል ብቻ ነበርና የጦር መሣሪያ ለማግኘት ሲሉ ኢጣሊያኖች ጋራ ያላቸውን ወዳጅነት ለማጽናት በብዙ ይጥሩ ነበር።

ኢጣሊያኖች የጦር መሣሪያ በመስጠት ለንጉሥ ምኒልክ የረዱትን እርዳታ ያውቃሉና ንጉሥ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሲሆኑ ከኢትዮጵያ የሚፈልጉትን ጥምቅ ሁሉ የሚሰጧቸው ስለ መሰላቸው እስከዚህ ጊዜ ድረስ ከራስ መንገሻ ጋራ ለመላላክና የወዳጅነት ሥራ ለመጀመር አላሰቡም ነበር።

በኋላ ግን አጼ ምኒልክ በውጫሌው ውል በ፲፯ኛው ክፍል የተጻፈው ቃል ባለ መታረሙና ባለ መሰረዙ ምክንያት መቀየማቸውን ስለ አወቁት ፖለቲካው ሁሉ እንደፈረሰባቸው ተረድተው በፊት በአጼ ዮሐንስና በአጼ ምኒልክ መካከል እንዳደረጉት አሁንም በአጼ ምኒልክና በራስ መንገሻ መካከል ገብተው ለማጣላትና ለማለያየት ሲሉ ከራስ መንገሻ ጋራ የወዳጅነት ሥራ ለመጀመር ቁርጥ አሳብ አደረጉ።

ከዚህም በኋላ ከኢጣሊያ መንግሥት አንድ ነገር ቢፈልጉ በምጥዋ ወደሚኖረው አገረ ገዥ እየጻፉ ቢያስታውቁ ለማግኘት ይችላሉ የሚል ደብዳቤ ከኢጣሊያ ንጉሥ ከግርማዊ ዑምቤርቶ ለራስ መንገሻ መጣላቸው። ራስ መንገሻም ደብዳቤውን አይተው ለጊዜው ከወዳጅነት በቀር ከኢጣሊያ የምፈልገው ነገር የለኝም። ስለ አሳባቸው ግን እግዚአብሐር ይስጥልኝ የሚል ምላሽ ጽፈው ነበር። በኋላ ግን ከኢጣሊያ መንግሥት ጋራ የፍቅርና የወዳጅነት ብቻ ለመዋዋል ፈቃዴ ነው ብለው አስታወቋቸው።

የአሥመራ ገዥ ጀኔራል ጋንዶልፊ የሚባእልው ይህን ነገር በሰማ ጊዜ ከአሥመራ በቶሎ ወደ መረብ ወጥቶ ራስ መንገሻም እስከ መረብ ሄደው ተገናኙና ቃል ለቃል ከተነጋገሩ በኋላ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ውል ተጻጽፈው ተፈራረሙ።

፩ኛ ውል። ለኢጣሊያ መንግሥት ራስ መንገሻን የሚጠላ ጠላቱ ነው፣ ራስ መንገሻን የሚወድ ወዳጁ ነው፤ ራስ መንገሻን ይወደዋልና የከብረዋልና። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ልጅ እንደ መሆኑ ሁሉ ያውቅቀዋል። ራስ መንገሻን የሚያሳዝን ትንሽ ነገር ስንኳ ምንም እንዳያደርግ ምሏል።

፪ኛ ውል። ራስ መንገሻ የኢጣሊያን መንግሥት የሚጠላ ጠላቱ ነው፣ የኢጣሊያ መንግሥት የሚወድ ወዳጁ ነው፤ የኢጣሊያ መንግሥት ይወደዋልና ያከብረዋልና። የኢጣሊያ መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደ መሆኑ ያውቀዋል። ደግሞ በሐማሴን የሚቀመጥ እንደራሴ ጕቤርኔር እንደ መሆኑ ያውቀዋል። የኢጣሊያን መንግሥት የሚያሳዝን ምንም ትንሽ ነገር ስንኳ እንዳይያደርግ ምሏል።

፫ኛ ውል። ራስ መንገሻና ጀኔራል ጋልዶልፊ በዚህ ውል ተስማምተው ሁለት እጃቸውን በአንድነት ዘርግተው በመስቀልና በወንጌል ላይ ጭነው ተማምለዋል።

፬ኛ ውል። ከእግንዲህ ወዲህ በትግሬ ሰዎችና በኢጣሊያ ሰዎች መካከል ሰላምና ፍቅር ሆኖዋል። ከዚህም በቀር ሌላ የሚዋዋሉበት ነገር የለም። መረብ ላይ ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፰፻፹፬ ዓመተ ምሕረት።

በዚያንም ወራት አጼ ምኒልክ የቀኙንም የግራውንም ለማዳመጥ ደሴ ላይ ቆይተው ነበርና በዚያው ሳሉ ራስ መንገሻ ከኢጣሊያኖች ጋራ ይላላካሉ ማለትን ቢሰሙ እርግጡን ለማወቅ ሲሉ «እስከ ደሴ መጥተህ ማናቸውንም ጉዳይ ተነጋግረን ትመለሳለህ» በልው ቢልኩባቸው ለጊዜ ያልህ እሺ እመጣለሁ የሚል ምላሽ ሰጠው ነበርና ከትግሬ /ከትግራይ/ የሚነሱበትና ደሴ የሚገቡበት ቀን የተቆጠረ ይጠበቅ ነበር። ለራስ መንገሻና ለትግሬ /ለትግራይ/ መኳንንቶችም የሚሆነው ልዩ ልዩ ሽልማት በብዙ ይሰናዳ ነበር።

ኢጣሊያኖች አጼ ምኒልክ ልጃቸውን ወይዘሮ ሸዋረጋን ለራስ መንገሻ ሊድሩላቸው ነው እያሉ ያስውሩ ነበር። ባንድ ወገንም ደግሞ አሁን ከእኛ ጋራ የወዳጅነት ውል መዋዋልም የታወቀ እንደ ሆነ ወደ ደሴ ሲደርሱ መታሰርዎ አይቀርም እያሉ ያስፈራርዋቸው ነበርና ይህን ምክንያት አድርገው ወደ ደሴ ሳይመጡ ቀሩ።

አጼ ምኒልክም ራስ መንገሻ በእርግጥ ከኢጣሊያኖች ጋራ የወዳጅነት ውል ተዋውለዋል ማለትን ሰምተ ነበርና ደሴ ሳይመጡ በመቅረታቸው እርግጡን ስለ አገኙት እርሳቸው ከኢጣሊያኖች ጋራ ሆነው በአጼ ዮሐንስ ላይ የሡሩትን ሥራ ሁሉ ያውቃሉና ራስ መንገሻም ብድር ለመመለስ ሲል ከኢጣሊያኖች ጋር ሆኖ ሳያስቸግረኝ አይቀርም በማለት በጣም አዘኑ።



በመረብ ከራስ መንገሻ ጋር የተዋዋለው ጄኔራል ጋንዶልፊ

ከዚህም በኋላ ልጃቸውን ወይዘሮ ሸዋረጋን ለራስ ሚካኤል ድረው ለትግሬ /ለትግራይ/ መኳንንት የተሰናዳውን ሽልማት ለወሎ መኳንንት ሸልመው ወደ ሸዋ ተመለሱ።

በዚህም ወራት የቤጌምድሩ ገዥ ራስ ዘውዴ ስለ ሸፈተ ራስ ወሬ ታዘው ሄደው ድል አድርገው ይዘውት ነበርና አጼ ምኒልክ ደስ ላይ ሰንብተው ያገኙት ደስታ ይህ ብቻ ነበር።

ወደ ሸዋም ስለተመለሱ በዚያ ዘመን በሁለትና በሦስት ቀን ብቻ የሚገድል የነፋስ ደዌ /ኮሌራ/ የሚባል በሽታ ተነስቶ ነበርና አጼ ምኒልክ አዲስ አበባን ለቀው ወደ እንጦጦ ከዚያም ወደ አንኮበር ሸሽተው ቢሄዱም በሽታውም እየተከታተለ ብዙ ሰዎች ሞቱባቸው። ነገር ግን ሰው ሁሉ ካንዱ ሥፍራ ወደ አንዱ ሥፍራ እንዳይተላለፍ አስከልክለው ነበርና በሽታው እየበረደ ይሄድ ጀመር። ከዚህም በኋላ ክረምቱን በዚያው በአንኮበር ከርመው በመስከረም ፲፩ ቀን ፲፰፻፹፫ ዓመተ ምሕረት ከአንኮበር ተነስተው በመስከረም ፳፫ ቀን እንጦጦ ከተማ ገቡ።

ቢሆንም የነፋስ ደዌ በረደ ሲባል ሌላ የነገር ደዌ ተነስቶ ደጃዝማች መሸሻ ወርቄና አለቃ አድማሱ ሌሎችም መኳንንቶችና የእልፍኝ አሽከሮች በአንድነት አጼ ምኒልክን ገድለው የመርድ አዝማች ኃይሌን ልጅ ፊታውራሪ ጉልላቴን /ተክለ ማርያምን/ ለማንገስ ሲያሴሩ ተገኝተው ነበርና እየተያዙ ቢመረምሩ «አዎን ለመግደል መክረናል» እያሉ በቃላቸው ስለ አመኑ የሞት ፍርዱን በእስራት ለውጠውላቸው ፊታውራሪ ጉልላቴ ወደ ልዑል ራስ ዳርጌ፣ ደጃች መሸሻ ወርቄ ወደ ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስ፣ አለቃ አድማሱ ወደ ደጃች ወልዴ እየሄዱ በግዞት ቤት ተቀመጡ። አጼ ምኒልክን ከደርብ ላይ ገብቶ ለመጣልና ለመግደል ተዘጋጅቶ የነበረው የልፍኝ አሽከራቸው ልጅ አበበ ግን እጅና እግሩ ተቆረጠ።

# ምዕራፍ ፶፯

## ራስ መንገሻ ባለፈው ሥራቸው ተጸጽተው ከአጼ ምኒልክ ጋራ ስለ መታረቃቸው

ራስ መንገሻ ወደ መረብ ሄደ ከኢጣሊያኖች ጋራ የወዳጅነት ውል ሲዋዋሉ ራስ አሉላ አልሄዱም ነበር። ምክንያቱም በዶጋዓሊ በተደረገው ጦርነት ከኢጣሊያኖች ጋራ ፍቅር ስለአልነበራቸው ነው። ቢሆንም አጼ ምኒልክ በአጼ ዮሐንስ ዘመን ከኢጣሊያኖች ጋራ ወዳጅ ሆነው አጼ ዮሐንስን በማስቀናታቸው ሲያዝኑ ይኖሩ ነበርና ራስ መንገሻ ከአጼ ምኒልክ ቢሸፍቱ ደስታቸው ስለሆነ ራስ መንገሻ አነግሳለሁ እያሉ የትግሬን ሕዝብ ይሰብኩት ጀመር።

ራስ መንገሻም ለጊዜው ነገሩ የሚፈሰምና የሚነግሱ ስለመሰላቸው የራስ አሉላን ምክር ተቀብለው ነበር። ስለዚህም በ፲፰፻፹፫ ዓመተ ምሕረት የትግሬን ሕዝብ በሐውዜን ላይ ሰብሰበው ከአጼ ምኒልክ መከዳታቸውንና ለመንገሥ ማሰባቸውን አስታወቁ። ሕዝቡም እውነት እንው ብሎ እንዲቀበላቸው እንደ ንጉሥ ቀይ ጥላ ይዘው ታዩለት። ወዲያው ባለ አንበሳ ማኅተም አሠርተው በደብዳቤያቸው መጀመሪያ ያትሙ ጀመር።

የአጋሜው ገዢ ደጃዝማች ስብሐት ግን ከዚህ አስቀድሞ ከራስ መንገሻ ጋራ አይዋደዱም ነበርና ራስ መንገሻን የጐዱ መስሏቸው የትግሬንና /የትግራይንና/ የራስ መንገሻን ወሬ ለኢጣሊያኖች እያቀበሉ ወዳጅ ሆነው ነበር። ራስ መንገሻም ደጃዝማች ስብሐትን በጦርነት ለመያዝ ካሰቡ በኋላ የማይመቻችወ ሆኖ ቆይቶ ነበር። ከራስ አሉላ ጋር ግን የልብ ወዳጅነት ነበራቸውና የወንድማቸውን የባሻ ገብረ ማርያምን ልጅ ድረውላቸው ነበር። ቢሆንም ፍቅራቸውን ራስ መንገሻ እንዲያውቁባቸው ሁለቱም የተጣሉ እየመሰሉ ካንገት በላይ ብቻ ይናገሩ ነበር።

አሁን የራስ መንገሻ መንገሥ በታሰበ ጊዜ የደጃዝማች ስብሐት በራስ አሉላ ፍቅር ተስበው ከአጋሜ ወደ ሐውዜን መጥተው ለራስ መንገሻ ታጥቀው ገቡላችው። እርሳቸውም በነገሩ ደስ ስላላችው ወዲያው የራስነት ማዕረግ ሰጥተው ራስ ስብሐት አሰኟችወ።

አንዳንድ ሰዎች ራስ መንገሻ መረብ ላይ ከኢጣሊያኖች ጋራ የወዳጅነት ውል በመዋዋላቸው እታሠራለሁ ብለው ስለ ፈሩ ወደ አጼ ምኒልክ አልመጣም አሉ እንጂ መንግሥት ፈልገው አይደለም እያሉ ይናገራሉ። ነገር ግን በማን ዘመን? በየትኛውስ ጊዜ? ራሱ ራስ ሆኖ ሌላውን ራስ ብሎ ይሾማል? ቀይ ጥላ መያዝና ባለ አንበሳ ማኅተም ላንድ ራስ በማን ዘመን ተፈቅዶ ያውቃል? አጼ ዮሐንስ ሲሞቱ አልጋ ወራሹ ራስ መንገሻ ነው ብለው አስታውቀውላቸው ነበርና ለመንገሥ አስበው ሳለ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስላልሆነላቸው ቀረባቸው ተብሎ ቢነገር ይሻል ነበረ እንጂ ለመንገሥ አላሰቡም ብሎ የሐሰት ነገር መናገር አያስፈልግም ነበር።

በኋላ ግን ራስ መንገሻ በመረብ ላይ ከኢጣሊያኖች ጋር መዋዋላቸው ኢትዮጵያን ለመከዳት አጼ ምኒልክን ለማሳዘን የአጼ ዮሐንስና የትግሬን /የትግራይን/ ሕዝብ ስም ለማስጠፋት ነው ተብሎ እንደ ተተረጐመባቸው ባወቁ ጊዜ ባለፈው ሥራቸው ሁሉ ስለ ተጸጸቱ በ፲፰፻፹፯ ዓመተ ምሕረት ይማሩኝና ልግባ የሚል ደብዳቤ ጽፈው በሹም አጋሜ ተስፋዬ እጅ ወደ አጼ ምኒልክ ላኩ።



ራስ መንገሻ ዮሐንስ

በዚህ ዓለም አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔርንና ንጉሥን የማይበድል ሰው አይገኝም። ነገር ግን በደለኛ መሆንን አውቆ በሥጋውና በነፍሱ ከእግዚአብሔር ምሕረት የሚለምን ሰው እንደ ዋና በደለኛ አይቆጠርምና የለመነውን ያገኛል።

አጼ ምኒልክም ራስ መንገሻ ባለፈው ሥራቸው ተጸጽተው ምሕረት ለመለመን ሹም ጋሜ ተስፋዬን መላካቸውን አይተው »ቀድሞውንም ቢሆን የኢትዮጵያ ጠላቶች

አስመስለው ቢነግሩት ይሆናል እንጂ እርሱ ከልቡ አንቅቶ ይህን ሥራ እንዳልሠራው አውቄዋለሁ፤ ብለው ባለፈው ጥፋትህ ሁሉ ምሬሃለሁና ወደ አዲስ አበባ እንድትመጣ ይሁን» የሚል ምላሽ ላኩባቸው።

ራስ አሉላ ግን በአጼ ምኒልክ ላይ ያሰቡት ክፉ አሳብ እንዳልተፈፀመላቸው ባዩ ጊዜ ከራስ መንገሻ ተለይተው ባንድ ሥፍራ ስለ ተቀመጡ ሸፍተዋል እየተባለ ተወራባቸውና በነገሩ ደንግጠው «ከመረብ መለስ ያለውን የወሰኑን አገር ይሹሙኝ ብዬ ሳይሾሙኝ ቢቀሩ አኩርፌ ነው እንጂ ጌታዬን ራስ መንገሻን አጼ ምኒልክንም አልከዳሁምና አስታርቁኝ» ብለው አማላጅ ልከው ታረቁ።

ራስ ስብሐትም ከራስ አሉላ ጋራአ ለመሸፈት መክረዋል ተብለው ስለ ተጠረጠሩ ነገሩን ለመነጣጠር ነው ወደ መቀሌ ተጠርተው ነበርና መቀሌ ሲደርሱ መሣሪያቸውን ሁሉ ተቀብለው ከነልጆቻቸው ይዘው በአምባ ሰላማ አሠርዋቸው።

ከዚህም በኋላ ራስ መንገሻ በሚያዝያ ወር በ፲፰፻፹፯ ዓመተ ምሕረት ከትግሬ /ከትግራይ/ ተነሥተው በግንቦት ወር ወደ አዲስ አበባ ገብተው እጅግ ደስ የሚያሰኝ የክብር አቀበባል ተደረገላቸው። ከርሳቸውም ጋራ የመጡት ትልልቅ መኳንንቶች ራስ አሉላ ራስ ሀጐስ ሹም አጋሜ ተስፋዬ ነበሩ።

በአዲስ አበባ አንድ ወር ያህል ቆይተው ወደ ትግሬ /ትግራይ/ በሚመለሱበት ጊዜ ከዘውድ በቀር ለንጉሥ የሚገባ ሽልማት ተሸለመው ከተሰናበቱ በኋላ በሰኔ ፮ ቀን ከአዲስ አበባ ወደ ትግሬ /ትግራይ/ ተመለሱ። ራስ አሉላ ግን እዚሁ ቀሩ።

በዚሁም ዓመት ከራስ መንገሻ አስቀድሞ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ዋግሹም ብሩ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ነበርና በቤተ መንግሥቱ ታላቅ ደስታ ተደርጐ ነበር።

# ምዕራፍ ፶፫

## አጼ ምኒልክ በኢትዮጵያ ያሉት ኢጣሊያኖች እየወጡ ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ስለ ማዘዛቸው።

አጼ ምኒልክ በውጫሌ ውል በ፲፯ኛው ክፍል የተጻፈው የጥገኝነቱ ነገር ተፍቆ ሌላ ቃል እንዲጻፍበት ወይም በጭራሽ እንዲቀር ለማድረግ ራሳቸው ከኮንት አንቶኔሊና ከዶክቶር ትራቬርሲ ጋራ ተነጋግረው ወደ ሮማ ተላልከው እንዳልሆነላቸው ከተረዱት በኋላ በኢትዮጵያና በራሳቸው ላይ ትልቅ ጉዳት የሚያመጣ ይህን የመሰለ ውል

በውጫሌ ስለ መዋዋላቸው አጥበቀ ተጸጸቱ። ይልቁንም በዚያ ወራት ደግሞ ወደ አውሮጳ ነገሥታት ደብዳቤ ልከው ነበርና የእንግሊዝ የጀርመን፣ የፈረንሣዊ፣ የመስኮብ፣ የአውስትርያ /የነምሳ/ ነገሥታት የኢትዮጵያ ንጉሥ በውጫሌ ውል የኢትዮጵያ ጥገኛ ሆኗልና በኢጣሊያ በኩል ካልመጣልን የምኒልክን ንጉሠ ነገሥትነት አናውቅም ብለዋል እየተባለ በአውሮጳ ጋዜጦች እየታተመ መውጣቱን ሰል ሰሙ እጅግ አዘኑ።

በዚህም ሁሉ ነገር ቁጣቸው እንደ እሳት ስለ ተቃጠለ ከእንግዲህ ወዲህ በሀገሬ በኢትዮጵያ የሚኖር ኢጣሊያኖች ሁሉ እየወጡ ይሂዱ ብለው ለየመኳንንቶቻቸው አስታወቁ።

የሸዋም የኢጣሊያ መንግሥት ተላላኪ ሆኖ የተቀመጠውን ዶክቶር ትራቬርሲን ወደ ሀገርህ ሂድ ብለው አሰናበቱት።

የኢጣሊያም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ግን አጼ ምኒልክ ኢጣሊያኖች ከሀገሬ ይውጡልኝ ወደ ፊትም አይምጡብኝ ብለው የጻፉትን ደብዳቤ ተመልክቶ ምክንያቱ በውጫሌ የተደረገው ውል በ፲፯ኛው ክፍል ባለ መታረሙ መሆኑን ስለ ተረዳው ከዶክቶር ትራቬርሲ በቀር ነገሩን የሚያውቀው ሌላ መልክተኛ አናገኝምና የውጫሌውን ውል ስለ ማረምና ስለ መለወጥ እንዲነጋገር እንደ ገና እርሱን ለመላክ ግድ ሆነብን ብሎ ሁለት ሚሊዮን ጥይት ገጸ በረከት ጨምሮ መልሶ ወደ ሸዋ ሰደደው።

አጼ ምኒልክም ከዶክቶር ትራቬርሲ ጋር በተገናኙ ጊዜ «እኔ በማናቸውም ቢሆን ከኢጣሊያ መንግሥት ጋር የጀመርሁትን ወዳጅነት ለመተው አሳብ አልነበረኝም። እናንተ ግን አሳባሁ ሁሉ ለጠብ እንጂ ለፍቅር አለመሆኑን ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሥራችሁ ይመስክራል።

***መጀመሪያ*** ስለ ወሰን ሰገድ ነገር በውጫሌ ውል በ፫ኛው ክፍል የተጻፈውን ከኮንት አንቶኔሊ ጋራ ተስማምተን ካደስነው በኋላ የታደሰውን ውል አፍርሳችሁ እስከ መረብና እስከ ሙና እስከ በለሳም ወጥታችሁ ሰንደቅ አላማችሁን አቆማችሁ።

***ሁለተኛም*** በዚያው በውጫሌ ውል በ፲፯ኛው ክፍል የተጻፈውን እንለውጣለን ካላችሁ በኋላ ምክንያት እያበዛችሁ ነገ ከነገ ወዲያ እያላችሁ እስካሁን አቆያችሁት።

***ሦስተኛም*** ከሁሉ የሚብስና የሚከፋ ነገር አሁን በቅርቡ ጄኔራል ጋንዶልፌኔን እኔን ለማሳዘን ሲል ወደ መረብ መጥቶ እኔ ሳልሰማ ከራስ መንገሻ ጋራ የወዳጅነት ውል ተዋዋለ።

«ይህም የጠላትነት እንጂ የወዳጅነት ሥራ አለመሆኑ የታወቀ ነው» እያሉ ነገሩን እየገለጡ ነገሩት። ነገር ግን አጼ ምኒልክ አዋቂና የዲፕሎማቲክ ሰው ስለ ነበሩ

ያመጣላቸውን ሁሉ ሚሊዮን ጥይት አልቀበልም ብለው ቢመልሱለት እርሳቸው ተብ ፈላጊ ይባሉ ነበርና ከኢጣሊያ አገር ድረስ ያመኸውን ጥይት አልቀበልም ብዬ ብመልሰው ግርማዊ የኢጣሊያ ንጉሥ ወዳጅነታቸውን የጠላሁ መስሏቸው እንዳያዝኑብኝ ስል ተቀብያለ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ ብለው ተሰማበቱት።

# ምዕራፍ ፶፱

## ጄነራል ባራቴሪ አድዋ መጥቶ በወታደር ከተከበበ በኋላ በእጨጌ ቴዎፍሎስ ስለ ማምለጡ

ዶክቶር ትራቬርሲ ከኢጣሊያ አገር ተልኮ የመጣበትን ጉዳይ ከአጼ ምኒልክ ጋር ተነጋግሮ ሳይቃናለት ስለ ተመለሰ ኢጣሊያኖች በአጼ ምኒልክ በኩል እናገኛለን ብለው ሲያስቡት የኖሩትን ተስፋቸውን ቆረጡና ከራስ መንገሻ ጋራ የጀመሩትን ወዳጅነት ለማስፋትና በአጼ ምኒልክ ላይ እንዲሠሩ ለማድረግ ይጣጣሩ ጀመር። ራስ መንገሻ ግን «በመረብ ከእናንተ ጋር የወዳጅነት ውል መዋዋሌ ጐረቤት ስለሆንን ከጠብ ፍቅር ይሻላል ብዬ ነው እንጂ አገሬን ኢትዮጵያንና ንጉሤን አጼ ምኒልክን ከድቼ ከእናንተ ጋራ ለመሆን የተዋዋልሁት ውል የለኝም» ብለው እምቢ ቢሏቸው።

አንዳንድ የኢትዮጵያ ጠላቶችም እርስዎ የአጼ ዮሐንስ ልጅ ሆነው ለአጼ ምኒልክ መገዛት ትልቅ ውርደት ነው እያሉ ራስ መንገሻን ይመክሩ ጀመር።

ራስ መንገሻ ግን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ይዘው ከውጭ ጠላት ጋራ ለመዋጋት ከማሰብ በቀር በአጼ ምኒልክና በኢትዮጵያ ላይ ጉዳት የሚሆን ሥራ ለመሥራት ለጊዜው ምንም አሳብ አልነበራቸውምና ምክራቸውን አልተቀበሏቸውም።

ከዚህም በኋላ ደርቡሽ ከኢጣሊያኖች ጋራ ጦርነት ለማድረግ በከሰላ በኩል መጣ የሚባል ወሬ ስለ ተሰማ ራስ መንገሻ ደስ አላቸውና በወሰን ላይ ሆነው ከሐማሴንና ከሡራዬ ከያውራጃውም ሁሉ ኢጣሊያኖችን እየከዳ የሚመጣውን ሠራዊት በደስታ እየተቀበሉ ተቀመጡ። ደጃች ሐጐስ ተፈሪ የሚባለው ግን ራስ መንገሻንና ሹም አጋሜ ተስፋዬን የጐዳ መስሎት ከኢትዮጵያ መንግሥት ከድቶ ወደ ጄኔራል ባራቴሪ ገባና በኢጣሊያኖችም ወገን ታላቅ ደስታ ሆነ። ከዚያም በፊት ራስ መንገሻ ራስ ስብሐትን አሥረው በአምባ ላይ አስቀምጠዋቸው ነበርና ጄኔራል ባራቴሪ ከራስ መንገሻ ጋራ ተዋግቼ ራስ ስብሐትን ከእስር ቤት አወጣቸዋለሁ እያለ የራስ ስብሐት ቤተ ዘመዶችን ይስብክላቸው ጀመር።

ወዲያው ራስ መንገሻ እንዳይጠረጥሩና እንዳይዘጋጁ ለማድረግ ሲል «እኔ ራሴ ወደ አድዋ መጥቼ መረብ ላይ በተደረገው ውል ተዋቅሰን ብንታረቅ ይሻላል እንጂ እንዲያው በከንቱ የሰው ደም ቢፈስ ምን ጥቅም አለው?» የሚል ቃል ጽፎ ላከላቸው።

ከእነርሱም ጋራ ያለው የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ ሰው ሁሉ እንዳይከዳው «እኔ ዛሬ ወደ አድዋ መሔዴ ከዚህ ቀድሞ በመረብ ላይ ከራስ መንገሻ ጋራ ያደረግነውን የወዳጅነት ውል ለማደስና ለማጽናት ነው እንጂ ለጦርነት እንዳመስላችሁ» እያለ የማታለል ስብከት ከሰበከላቸው በኋላ በታኅሣሥ ፲፱ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓመተ ምሕረት ከሠራዬ ተነሥቶ ትቂቶች ወታደሮች ይዞ ወደ አድዋ ገሥገሠ። ወደ አድዋም በደረሰ ጊዜ የአድዋ ካህናት በፍቅር የመጣ መስሏቸው ልብስ ተክህኖ ለብሰው መስቀል ይዘው ተቀበሉት። እርሱም ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ወዳጅ ለመምሰል እንደ ሀገሩ ልማድ ከፈረስ ወርዶ መስቀሉን ተሳለመ።

በዚያንም ጊዜ የጄኔራል ባራቴሪ ዋና ሐሳቡ ራስ ስብሐት ወደ ታሠሩበት ሥፍራ ሄዶ በድንገት አደጋ ጥሎ ወዳጁን ራስ ስብሐትን ፈትቶ ለመውሰድ ነበር። ነገር ግን እንዳይጠረጥርና እንዳያውቅበት ፊታውራሪውን ወደ አኩስም አቅንቶ እንዲሄድ ትእዛዝ አሳልፎ እርሱ ገና ከአድዋ ሳይነሣ የራስ መንገሻ ሠራዊት በድንገት ወደ አድዋ ደርሶ ስለ ከበበው እጅግ ተጨነቀ።

ስለዚ ወዲያው በፍጥነት በፈረስ ሆኖ እነዚያን ጥቂቶች ሠራዊቱኡን ያሠልፍ ጀመር። ቢሆንም የጦር አለቃ የሆነው ሰው ዝም ብሎ መሞት አይገባውምና ነው እንጂ በዚያ ጊዜ ተዋግቼ አሸንፋለሁ የማለት አሳብ አልነበረውምና በፍጥነት ወደ አድዋ ካህናትና ቄሶች ቀርቦ እኔ የመጣሁት ለፍቅና ለዕርቅ ነው እንጂ ለጦርነት አይደለምና ቢሆን ከራስ መንገሻ ጋራ አስታርቁኝ ለዕርቁም ፈቃዳቸው ባይሆን ለቀውኝ አስመራ እንድሄድ አማልዱኝ እያለ ይለምናቸው ጀመር።

በመካከላቸው እጨጌ ቴዎፍሎስ ነበርና «እርሱ እንደዚህ እያለ በፍቅር ነገር ሲአንገር አንተ ለምን ጠብ ትፈልጋላችሁ? እያሉ በቁጣ ቃል ስለ ተናገሩ መቼም ቢሆን የኢትዮጵያ መኳንንት የካህናት ቃል ያከብራሉና «አሁን በቶሎ አገራችንን ለቆ ካልሄደ እሺ እንደ አባታችን ቃል እናደርጋለን» ብለው ለቀቁትና ወደ ቀኝም ወደ ግራም ሳይል በቀጥታ ወደ አዲኳላ ተመለሱ። የአድዋ ቀሳውስትና ካህናት እንደዚህ ማለታቸው የመጣሁት ለዕርቅና ለሰላም ነው ስላላቸው በሞኝነታቸው እውነት መስሏቸው ነበር።

እጨጌ ቴዎፍሎስ ግን እጅግ ተከብረውን ተፈርተው የኖሩበት የአጼ ዮሐንስ መንግሥት ወደ ምኒልክ በማለፉ ደስ አላላቸውም ነበርና የማታልፈውን ኢትዮጵያን ሳያስቡ አጼ ምኒልክ ብቻ የሚጎዱ ስለ መሰላቸው የራስ መንገሻን መኳንንት አማልደው

ጄኔራል ባራቴሪን አዳኑት እንጂ የእርሱ አመጣጥ ለእርቅና ለሰላም አለመሆኑን ፈጽመው ያውቁ ነበር ይባላል።

ከዚህም አስቀድሞ ዋጋው እጅግ ብዙ የሆነ ባለ ወርቅ ጥልፍ ካባ ከአስመራ ላኮላቸው እንደ ነበረና ወዳጅነትም ጀምረው እንደ ነበረ የአክሱም ካህናትና በከተማው የሚኖሩ ትልልቅ ሰዎች ሁሉ ያውቃሉ።

# ምዕራፍ ፳

## <u>ስለ ራስ መንገሻና ስለ ኢጣሊያኖች ጦርነት</u>

ጄኔራል ባራቴሪ በእጨጌ ቴዎፍሎስ እርዳታ የራስ መንገሻን መኳንንቶች አታሎ ከአድዋ ወደ አዲኳላ ከተመልሰ በኋላ እንደ ገና ብዙ ወታደሮች አዘጋጅቶ ወደ ኮዓቲት ሰደደ። በአድዋም ያለው የራስ መንገሻ ሠራዊት ጄኔራል ባራቴሪ እንደ ገና ጦር መስደዱን በሰማ ጊዜ በእጨጌና በካህናት እርዳታ ተለማምጦ ሄዶ አሁን ተመልሶ እንደዚህ ማድረጉ እጅግ ያሳዝናል እያለ እጨጌ ቴዎፍሎስንም እያማረረ ይናገር ጀመር።

ራስ መንገሻም መኳንንቶቻቸውንና ወታደሮቻቸውን ሰብስበው «ስለ ሀገራችን ነፃነት ተዋግተን ቢሆን ድል እናደርጋለን ባዮን ደማችንንር ረግጦ ይገባል እንጂ እንዲያው አይገምና አይዟችሁ አትፍሩ። የዮሐንስና የምኒልክ አምላክ ይረዳናል» እያሉ ያሚያጽናና ቃል ስለ ተናገሩ ሁሉ በፊታቸው ይፉክሩ ጀመር። ከዚህም በኋላ እያለ ወደ ኮዓቲት ጉዞ ጀመሩ። ኮዓቲት በተፈጥሮ ምሽግ የሆነ ተራራና ዱር ነው። ስለዚህ ራስ መንገሻ ኢጣሊያኖች ሳይዙት አስቀድመው ገስግሰው ኮዓቲትን ያዙት።

ጄኔራል ባራቴሪም በበኩሉ ራስ መንገሻ የኮዓቲትን ተራራ የያዘብን እንደ ሆነ ማስቸገር አይቀርምና በግሥጋሴ ሂዱ ብሎ ሠራዊቱን አዝዞ ነበር። ነገር ግን ራስ መንገሻ ቀድመው ስለ ያዙት አሳቡ አልተፈጸምለትም።

የኢጣሊያኖች ጦር አመጣጡ በብዙ ሠራዊት ነበር። ማጆር ኪዳልጎ ደጀን፤ ማጆር ቶዞሊ ፊታውራሪ ማጆር ሳሌቤ በቀኝ ቲኒንቲ ሳፍሮቴን በግራ ሆነው ጦርነት ተጀመረ።

ራስ መንገሻም ሠራዊታቸውን ማኻል ለማኻል አሠልፈው እርሳቸው ደጀን ሆነው ያዋጉ ነበር። ምንም ኮዓቲት ጫካና ዱር ቢሆንም እንኳ የራስ መንገሻ ሠራዊት እንደ ወፍ በየዱሩ ውስጥ እየተባረረ ወደ ኢጣሊያኖች ሠልፍ እየገባ በጐራዴ እየመታ ይገድል ጀመር። ኢጣሊያኖችም ድል ሆነው መሸሽ ሲጀምሩና የራስ መንገሻ ሠራዊት በስተጀርባ ዞረው ለመክበብ ሲዘጋጅ ጄኔራል አሪሞንዲ ብዙ ሠራዊት ይዞ በሩቅ ይጠባበቅ ነበርና

የኢጣሊያ ጦር ድል ሆኖ መሸሹ በመነጥር ዐይቶ በፍጥነት ደረሰና ተጋጠማቸው። ቢሆንም ጊዜ መሽቶ ነእብርና ድሉ ለሁለቱም ወገን ሳይሆን አደረ።

በማግሥቱም እንደዚሁ ብርቱ ጦርነት ሆኖ ውሎ ነበር። በሦስተኛው ቀን ግን አንድ ፈሪና መዓት አውሪ የሆነ ሰው ለኢጣሊያኖች ስንቅ አቀባይ ብዙ አጋሰስ ተጭኖ ሲመጣ አይቶ ነገሩ ሳይረጋገጥ ለኢጣሊያኖች የመጣላቸው ረዳት ቁጥሩ አንበጣ ነው ብሎ ስለ አወራ የራስ መንገሻ ሠራዊት በፍጥነት ኮዓቲትን ለቀው ወደ ሰንዓፌ ጉዞ ጀመሩ። ደግሞም እንደ አጋጣሚ ከኢጣሊያኖች የተማረከ አንድ ምርኮኛ አምልጦ ወደ ኢጣሊያኖች ሠፈር ገብቶ ነበርና ራስ መንገሻ ወደ ሰንዓፌ መሸሻቸውን በተናገረ ጊዜ ጄኔራል አሪሞንዲ እንደ ገና ጥሩምባ አስነፍቶ ከርሱ ጋር ያለውን ወታደር ሁሉ አስከትሎ ወደ ሰንዓፌ ገሰገሰ።

ራስ መንገሻም በሰንዓፌ ሜዳ ድንኳን አስተከለው ግብር ሲያበሉ ኢጣሊያኖች በአምባ ታሪክ ላይ ሆነው በድንገት የመድፍ ሩምታ ለቀቁባቸው። የራስ መንገሻም ሠራዊት የድንገት አደጋ ስለሆነባቸ ድንኳናቸውን ሳይነቅሉ እየሸሹ ሄዱ።

ኢጣሊያኖችም ከአምባ ታሪክ ወደ ራስ መንገሻ ሠፈር ወርደው ነጋሪቱን መለከቱን ጥቂትም ጠመንጃና ጥይት ስንቅና ልብስ ይህንንም የመሳሰለ የዘመቻ ዕቃ ዘርፈው በጄኔራል አሪሞንዲ ፊት እየፎከሩ አለፉ።

ከሁሉም ይልቅ አጼ ምኒልክና ራስ መንገሻ፣ ራስ መንገሻና የሐማሴን መኳንንቶች በጣሊያኖች ላይ ሲላላኳቸው የነበሩ ብዙ ደብዳቤዎች ባገልግል ውስጥ ሆነው በራስ መንገሻ ድንኳን ስለ ተገኙ ከድሉ ይልቅ በደብዳቤያዎቹ መገኘት ትልቅ ደስታ አደረጉ ይባላል።

የራስ መንገሻ ሠራዊት ፲፬ ሺህ ባለ ጠመንጃ። ፬ ሺህ ባለ ጦርና ባለ ጋሻ። በድምሩ ፲፰ ሺህ ነበር። በኮዓቲትና በሰንዓፌ ጦርነት ስለ ሀገራቸው ደማቸውን አፍስሰው የሞቱ ፩ሺህ፰ ከነዚሁም ትልልቁ ደጃዝማች ተድላ፣ ደጃዝማች በየነ፣ ደጃዝማች ካሳ፣ ቀኛዝማች አንዳርጋቸው ናቸው።

የቆሰሉም ሁለት ሽህ ይሆናሉ። ከነዚሁም ዋንው ሹም አጋሜ ተስፋይ ነው።

# ምዕራፍ ፳፭

## አጼ ምኒልክ ኢጣሊያኖች የውጫሌን ውል ፲ኛውን ክፍል አንፍቅም ካሏቸው በኋላ ውሉን ለማፍረስ ቁርጥ አሳብ ስለ ማድረጋቸው።

አጼ ምኒልክ ከላይ የቀዳማዊ ምኒልክ ከታች የአጼ ልብነ ድንልግ ዘር የአቤቶ ያዕቆብ ተወላጅ ስለ መሆናቸው የቀዳማዊኢ ምኒልክ ዙፋንና ዘውድ ከሌሎቹ ይልቅ የሚገባቸው ለእርሳቸው መሆኑን ከማወቃቸው የተነሣ የሚገባቸውን ለማግኘት በብዙ ይጥሩ ነበር። በአጼ ዮሐንስም ላይ ከኢጣሊያኖች ጋር የተስማሙባቸው ይህንኑ የሚጌባቸውን ዙፋንና ዘውድ ለማግኘት ኃይል የሚያገኙበትን የጦር መሣሪያ ለማምጣት ነበር እንጂ እውነት አገራቸውን ኢትዮጵያን አሳልፈው ለኢጣሊያኖች ለመስጠት ምንም አሳብ አልነበራቸውምና ውሉን ለማፍረስ ማሰባቸው ስለዚህ ነው።

ምናልባት አንዳንድ ሰዎች በአጼ ዮሐንስ ዘመን በንጉሥ ምኒልክና በኢጣሊያኖች መካከል የነበረውን የስምምነትና የወዳጅነት ነገር ሲያስብ በአጼ ምኒልክ ያዝኑ ይሆናል። ነገር ግን በዚያን ጊዜ የነበረው የአጼ ምኒልክ አሳብ በቅን ልቡና ቢመረመር አጼ ዮሐንስ በኃይል የወሰዱትን የአባታቸውን ዙፋንና ዘውድ ለማግኘት ብቻ መጣጣራቸውን ያስረዳል እንጂ ሌላ ነገር ነበረበት ለማለት አይቻልም።

ይህንንም የመሰለው አሳብ የሙሉ ኢትዮጵያ ሕዝብ አሳብ ነው እንጂ የነገሥታቱ ብቻ አይደለም።

ውሻና ውሻ በሥጋና ባጥንት ተጣልተው ሲናከሱ በመካከላቸው አንድ ጅብ የመጣ እንደ ሆነ የራሳቸውን ጠብ ትተው ባንድነት ሆነው ጅቡን ያባርራሉ እንደሚባለው የኢትዮጵያ ዐርበኞች እንደዚሁ ናቸው።

ይህንንም ለመረዳት አሁን በቅርቡ ዘመን የነበሩትንን የደጃዝማች ደብብንና የደጃዝማች ባሕታን የራስ ስብሐትንና የደጃዝማች ሀጐስን ብቻ ማንበብ ይበቃል።

## ስለ ደጃዝማች ደብብ።

ደጃዝማች ደብብ የታላቁ ራስ አርአያ ልጅ ነው። እርሱም ከአጼ ዮሐንስ ከድቶ በምጥዋ አጠገብ አገመዳ የሚባል በረሃ ተቀምጦ ሳለ «እኔ ከአጼ ዮሐንስ ከድቼ መጥቻለሁና የኢጣሊያ ሎሌ ለመሆን እፈልጋለሁ። ነገር ግን የጦር መሣሪያ የለኝም በቶሎ ላክልኝ» ብሎ በምጥዋ ወደ አለው ወደ ጄኔራል ማርዛኖ ቢልክ ሁለት ሺህ ያህል መሣሪያና ገንዘብ ጨምሮ ላከለት።

ከዚህም በኋላ ኢጣሊያኖች ወደ ደጋው አገር ወደ አሥመራ ለመውጣት አገር ለመያዝ አስበው ከማርዛኖ ጋራ ተቀላቅለው እንድትወጣ ብለው ቢልኩበት አሽከሮቹን

ሰብስቦ «እንዲዚህ የሚል መላክት መጣብኝ እንደምን እናድርግ» ብሎ ምክር ቢጠይቋቸው ባንድ ቃል ሆነው ቃል «አገራችንን አሳልፈን ከመስጠት ደማችንን በላይዋ አፍስሰን ረግጠው ቢወዱት ይሻላል» ብለው ተናገሩና ደጃዝማች ደብብ ምክራቸውን በደስታ ተቀብሎ በፍጥነት ወደ ሰገነይቲ ወጥቶ አሽከሮቹን አሰልፎ ምቹ ሥፍራ ይዞ ይጠባበቃቸው ጀመር።

ኢጣሊያኖችም ይህን ሰምተው ፮፻ ወታደሮች በካፒቴን ከርናንኪያ አዛዥነት አድርገው ደጃች ደብብን ውጉና ያዙ ብለው ቢልኩ ደጃች ደብብ በየመንገዱ ሰላይ አስቀምጦ ነበርና ኢጣሊያኖቹ የሰገነይቲን መንገድ ይዘው ሲጓዙ ለአሽከሮቹ ምልክት በሰጣቸው ጊዜ በሩምታ ተኩሰው ፈጁዋቸው።

## ስለ ደጃዝማች ባሕታ

ደጃዝማች ባሕታ ልጅ አምባየ የሚባለውን የታላቁን ራስ አርአያ ልጅ በአምባጓሮ ስለ ገደለ ሽፍታ ሆኖ በምጥዋና በሀባብ በረሃ እየተመላለሰ ይኖር ነበርና አጼ ዮሐንስ መሞታቸውን ቢሰማ ኢጣሊያኖችን እየመራ አምትቶ ወደ ሰገነይቲ አገባቸ። ፳ ዓመትም ያህል በኢጣሊያኖች ዘንድ እንደ አንድ መኮንን ተቆጥሮ በክብር ተቀመጠ። በኋላ ግን ኢጣሊያኖች የኢትዮጵያ ሰው ሲያዋርዱትና እያስተኙም ሲገርፉት ስለ አዘነ «የሀገሬ ሰው እንደዚህ እየተዋረደ ከማየው ሞት ይሻለኝ ነበር» እያለ በግልጥ መናገር ጀመረ።

ቀጥሎም የኢጣሊያ አሳብ ወሰን እየገፉ ለመሄድና አገር ለመያዝ መሆኑን ስለ ተረዳው «አገሬ ትግሬ /ትግራይ/ በኢጣሊያ እጅ ገብታ ከማይ አስቀድሞ አምላኬ ያጥፋኝ /ልሙት/» እያለ ለአሽከሮቹ ይነግር ጀመር።

ኢጣሊያኖችም የደጃዝማች ባሕታን አሳብ ስለ አወቁ «ከዚህ ቀድሞ ደጃዝማች ደብብ የእናንተ ሎሌ ነኝ ብሎ አታሎ መሣሪያ ተቀብሎ በገዛ መሣሪያችን ወግቶ ፖለቲካችንን አሰናከለብን። አሁን ደግሞ ደጃች ባሕታ እንደዚህ ያለ ሀሳብ እንዳለው ተረድተነዋል፣ ሳይጠረጥር በድንገት ይዘን ወደ አሰብ ብንሰደው ይሻላል» ብለው መከሩበት።

ደጃች ባሕታም በሽፍትነት ምክንያት ወደ ምጥዋ ከሄደ በኋላ በካቶሊካውያን ክፉ ምክር ስለ ሰማው ሳይቀድሙኝ ልቅደማቸው ብሎ አንዱን ኢጣሊያ ሹም ይዞ በሠንሰለት አድርጐ ለራስ መንገሻ ላከላቸው። ወዲያውም በቶሎ ይድረሱልኝ ብሎ አስታውቆ እርሱ በዚያ ያለውን ስልክ በጣጥሶ ዕቃውንም ሁሉ ሰባብሮ ያገሬ ሰው እርዳኝ ብሎ አዋጅ ቢነግር ባንድ ሰሞን ሺ፫፻ ባለ ጠመንጃ ወታደሮች ገቡለት። እነዚህንም ይዞ

በሰገነይቲ ሆኖ ራስ መንገሻን ሲጠብቅ አሥመራ ያለው ማጆር ቶዞሊ የተደረገውን ሁሉ ሰምቶ በግሥገሣ ተነሥቶ በሰገነይቲ አጠገብ ማዕረባ በሚባል አገር ደረሰባቸው።

ደጃች ባሕታም ማጆር ቶዞሊ መምጣቱን ራስ መንገሻ መቅረታቸውን አይቶ እጅግ ተጨነቀና ከዚያ ሸሽቶ ወደ ኃይላይ ወጣ። በኃይላም የነበረውን የኢጣሊያ ካፒቴን እገድላለሁ ብሎ አስቦ ሳለ በዚያ ያልቱ አንተም በእጅህ ያለውን መሣሪያና ዕቃ አስረክብ ብለው የእርቅ ነገር ቢጀምሩ ካፒቴኑ ማጆር ቶዞሊ እስኪደርስለት ሰዓቱ እየደረሰ ባየ ጊዜ በእጁ ያለውን መሣሪያና ዕቃ ከወታደሮቹ ጀግና ጀግናውን መርጦ ሰደደና ካፒቴኑ ሁሉንም እየያዘ ሠንሠለት አገባቸው። ወዲያው ማጆር ቶዜሊ ወታደሮቹን አሰልፎ በደጃች ባሕታ ላይ አደጋ ጣለበት።

ደጃች ባሕታም ምንም እንኳ ለመዋጋት ባይችልም ኢትዮጵያዊ ሆኜ ፊቴን አዞሬ አልሸሽም ብሎ ባንድ ሥፍራ ቆሞ እየተታኮሰ ፲፩ ሰው ያህል ገደለና ፳ ሰው ያህል ካቆሰለ በኋላ በ፫ ጥይት መቱትና ሞተ።

## ስለ ራስ ስብሐት

ራስ መንገሻ ስብሐትን አሥረው አግዘዋቸው አጋሜን ያጼ ዮሐንስ የእልፍኝ አሽከር ለነበረ ለደጃች ተስፋይ ሰጡ። ከዚያም በኋላ ኢጣሊያኖች ከራስ መንገሻ መኳንንት ጋራ በአላጌ ተዋግተው ድል ካደረጉዋቸው በኋላ ራስ ስብሐትን ከታሰሩበት ፈትተው ወስደው በታላቅ ክብር ያኖሩዋቸው ጀመር። ወዲያውም የራስ መንገሻ ጠላት መሆናቸውን ያወቁ ነበርና በራስ መንገድ ላይ የሚናገሩትን ሁሉ በእምነት ይቀበሏቸው ነበር። የእንደርታንና የሁለት አውላሎንም ግዛት ሰጥተዋቸው ነበር።

በኋላ ግን በየካቲት ወር በ፲፰፻፹፰ ዓመተ ምሕረት አጼ ምኒልክ ከኢጣሊያኖች ጋራ ለመዋጋት በተቃረቡ ጊዜ እነዚህ ሁለቱ ክርስቲያን ዐርበኞች ሁለቱ ክርስቲያን ዐርበኞች ከባዕድ ጋራ ሆነን ንጉሣችንን አጼ ምኒልክን ከምንወጋውና አገራችንን ትግሬን /ትግራይን/ በኢጣሊያን እጅ ገብታ ከምናያት ከአጼ ምኒልክ ጋራ ሆነን ስለ ሀገራችን ደማችንን ማፍሰስ ይሻለናልና ብለው ከኢጣሊያኖች እየከዱ ወጥተው ባይናቸው ያዩትን የኢጣሊያኖችን ምሥጢር ሁሉ ለአጼ ምኒልክ ተናግረው ወዲያውም እኛ ባወቅነው ባገራችን ባጋሜ ዙረን በስተኋላ እንገጥማቸዋለን ብለው እንደ ቃላቸው ባጋሜ ዙረው ስልኩን ቆራርጠው ስንቅ አቀባዩን ሁሉ በመፍጀታቸው ለንጉሣቸውና ለኢትዮጵያ አገራቸው ለልጅ ልጅ የማይረሳ ትልቅ ሥራ ሠርተዋል።

## ስለ ራስ መንገሻ

አፄ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ አፄ ምኒልክ ወደ ትግሬ /ትግራይ/ ሄደው ራስ መንገሻን በትግሬ /በትግራይ/ ሾመው ተመልሰው ነበር። ነገር ግን በ፲፰፻፹፬ ዓመተ ምሕረት ኢጣሊያኖች ከአጼ ምኒልክ ሳያስፈቅዱ አታለው የወዳጅነት ውል ተዋውለዋቸው ነበርና በኋላ ግን የኢጣሊያኖች አሳብ ትግሬን /ትግራይን/ ለመውሰድ መሆኑን ስለተረዱ «አሳባችሁ እንደዚህ ከሆነስ እኔ የዮሐንስ ልጅ ነኝና ከናንተ ጋራ ሆኜ አጼ ምኒልክን ከመውጋት አገሬንም በእናንተ እጅ ሆና ከማያት ሞት ይሻለኛል» በለው የተዋዋሉትንም ውል አፍርሰው አጼ ምኒልክ ከሸዋ እስቲደርሱ ድረስ ከኢጣሊያኖች ጋራ ብዙ ጦርነት አድርገዋል።

አጼ ምኒልክም በውጫሌ ውል በ፲፯ኛው ክፍል የተጻፈውን የጥገኛነቱን ነገር ለመፋቅ ኢጣሊያኖች እምቢ ማለታቸውን ከተረዱት በኋላ መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው ከእንግዲህ ወዲህ ከኢጣሊያኖች ጋራ የነበረኝን ወዳጅነት ትቻለሁ። የውጫሌንም ውል አፍርሻለሁ። ለጦርነት ግን እነርሱ እየገፉ ወሰን እያለፉ ካልመጡብኝ እኔ ገፍቼ ሄጄ ለመዋጋት አሳብ የለኝም ብለው አስታወቀው ወደ ፊት ኢጣሊያኖች ለማድረግ የሚያስቡትን እየተጠባበቁ ተቀመጡ።

# ምዕራፍ ፷፪

## ኢጣሊያኖች ወሰን አልፈው ወደ አጋሜ ስለ መግባታቸው።

ጄኔራል ባራቴሪ ራስ መንገሻን በሰንዓፌ ድል ካደረጉ በኋላ ላገር ጥበቃ ማጆር ጋሊያኖን በሰንዓፌ ደጃች ሐጐስ ተፈሪን በአጋሜ ትቶ እርሱ ወደ አሥመራ ተመለሰ። ከዚያም ወደ ምጥዋ ወርዶ በወታደር ሠልፍና በካህናት ቅዳሴ የድሉን በዓል አከበረ። ከዚህም በኋላ ክረምቱን ሲዘጋጅ ከርሞ በመስከረም ፳፩ ፲፰፻፹፯ ዓመተ ምሕረት ከአሥመራ ተነሥቶ ወደ አጋሜ ከተማ ወደ አዲግራት ገብቶ ተቀመጠ። ከዚያም ወደ መቀሌ መጥቶ እንደገና ከራስ መንገሻ ጋራ ጦርነት ሊገጥም ነው እየተባለ ይወራ ነበርና ራስ መንገሻ በቶሎ ወደ አዲስ አበባ ልከው ለአጼ ምኒልክ አስታወቁ።

አጼ ምኒልክም በዚሁ ዓመት በኅዳር ወር ወላሞ /ወላይታ/ ዘምተው በጥር ወር ተመልሰው ነበርና ሦስት ወር ያህል ቆይተው በግንቦት ወር ወደ ወሎ ጉዞ ጀመሩ። ምክንያቱም ራስ መንገሻ ራስ ኢጣሊያኖች እየገፉ ወደ ማኻል ትግሬ ለመምጣት ማሰባቸውን ልከውባቸው ነበርና ወደ ወሎ ብቅ ብለው ኢጣሊያኖች እየገፉ መምጣታቸው በእርግጥ ቢሆን ወደ ትግሬ /ትግራይን/ ለመዝለቅ ይህም ባይሆን የግሼንን ቤተ ክርስቲያን ስራ አይተው ለመመለስ ነበር።

ኢጣሊያኖች አጼ ምኒልክ ወደ ወሎ ብቅ ማለታቸውን በሰሙ ጊዜ ወደ ፊት መግፋታቸውን ትተው በዚያው በአዲግራት ቆይተው ነበርና ራስ መንገሻ ይህንኑ ወደ አጼ ምኒልክ ልከው ስለ አስታወቁ ቢሆንም ባይሆንም ክረምቱን አዲስ አበባ ላይ ሆኖ ማዳመጥ ይሻላል ተባለና ነገሩ በዚሁ ተቆረጠ።

የኢጣሊያኖችም ዋና አሳባቸው የኢትዮጵያን መኳንንት ከአጼ ምኒልክ እያስከዱ ኃይላቸውን ለማድከም ነበርና ወደ ዋግሹም ብሩ ይላላኩ ማለትን አጼ ምኒልክ ስለሰሙ ዋግንና ላስታን ለልጃቸው ለደጃች ዳንኁል ሰጥተው ዋግሹም ብሩ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ተደረገ።

አጼ ምኒልክም ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ቁርጥ አሳብ ባደረጉ ጊዜ ምናልባት ኢጣሊያኖች በክረምት አደጋ ጥለው ራስ መንገሻን ብቻውን እንዳይወጉ በለው ከትግሬ /ከትግራይ/ መጥተው በዳር አገር ተቀምጠው ይኖሩ የነበሩትን ፊታውራሪ ንጉሤን ቀኛዝማች ኃይለ ማርያምን፣ ባላምባራስ በየነን ጠርተው ወደ ሀገራቸው ወደ ትግሬ /ትግራይ/ ሄዳችሁ ከራስ መንገሻ ጋራ ሆናችሁ ኢጣሊያኖችን ስትጠባበቁ ክረሙ ብለው አሰናብተው ሰደዷቸው። ከዚህም በኋላ በሰኔ ፳፱ ቀን አዲስ አበባ ገብተው ክረምቱን የጦርነት ምክር ሲያስመክሩ ክረሙ።

# ምዕራፍ ፰፫

## የመስኮብ መላክተኞች ወደ ኢትዮጵያ ስለ መምጣታቸውና የኢትዮጵያም መላክተኞች ወደ መስኮብ ስለ መሔዳቸው

መስኮቦች ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ መቀራረብና መገናኘት ስለ ፈለጉ በሺ፰፻፸፫ ዓመተ ምሕረት ኒኮላይ ኢባንክሊች አብኖፍ የሚባል መላክተኛ ካንድ ቄስ ጋር ወደ አጼ ዮሐስን መጥቶ ነበር። ቄሱም መስኮቦች በሃይማኖት ኦርቶዶክሳውያን መሆናቸውን ለአጼ ዮሐንስ በነበራቸው ጊዜ ደስ አላቸውና በአድዋ አጠገብ ገዳምና ቤተ ክርስቲያን የሚሠራበት አንድ ቦታ ሰጡት። ዋናው መላክተኛ ኒኮላይ ኢባንክሊች አብኖፍንም በጣም አከበሩት። የመስኮብንም መንግሥት ትልቅነት የሕዝቡን ብዛት ሲነግራቸው በደስታ ያደንቁ ነበር።

በመስኮብም አገር የጦር መሣሪያ ፋብሪካ መኖሩን በነገራቸ ጊዜ ብዙ ወታደሮች አሉኝና ለነዚሁ የሚሆነኝ አምሳ ሺ ጠመጃና ዓርባ መድፍ አምስት ሺ ሺጉጥ፣ ለዚሁ የሚበቃ ጥይት ደግሞ አምሳ ሺ ጐራዴ ጨምረህ ከመስኮብ አገር እንድታመጣልኝ ውል

አንዋዋል ብለው ተዋውለውት ነበር። ነገር ግን በዚያው ዓመት ኢጣሊያኖች የምጥዋን በር ስለ ያዙት የውሉ አሳብ ሳይፈጸም ቀረ።

መስኮቦች በምጥዋ ወደ ትግሬ /ትግራይ/ ወጥተው ከአጼ ዮሐንስ ጋራ የጀመሩት ጉዳይ በኢጣሊያኖች ምክንያት ስለ ተከናወነላቸው አሳባቸውን ወደ ሸዋ አዙረው ከንጉሥ ምኒልክ ጋራ መላላክ ጀመሩና የወዳጅነት መሠረት ተመሠረተ። ይህንኑም በመላላክ የተጀመረውን ወዳጅነት ለማስፋትና ለማጽናት ስለ አሰቡ በ፲፰፻፹፯ ዓመተ ምሕረት ሊዎንቴፍ የሚባል መላክተኛ በጅዎግራፊያ ማኅበር ስም ተልኮ ወደ ሸዋ መጣ።

ጂቡቲም መድረሱ በተሰማ ጊዜ ከጅቡቲ ጀምሮ እስከ አዲስ አበባ ያለ ችግር እንዲመጣ አጼ ምኒኢልክ ወደ ልዑል መኮንን ትእዛዝ አሳልፈው ነበርና ራስ መኮነን በክብር ተቀብለው ወደ አዲስ አበባ ሰደዱት። ከሊዎንቴፍም ጋራ አንድ ሐኪምና አንድ የመድፈኞ አለቃ አንድ ቄስ ነበሩ። በአዲስ አበባም የተደረገላቸው የክብር አቀባበል እጅግ ያማረ ነበር። ሙሴ ሊዎንቴፍም ከጓደኞቹ ጋራ የሚያርፍበት እንደ ዘመኑ የተሠራ መልካም ቤት ተዘጋጅቶለት ነበርና በአዲስ አበባ የቆየባቸውን ቀኖች ሁሉ በታላቅ ደስታ አሳለፋቸው።

ወደ ሀገሩም በሚመለስበት ጊዜ አጼ ምኒልክም በበኩላቸው የመስኮንምን ክሳር /ንጉሠ ነገሥት/ ደስ ለማሰኘት ሲሉ ፊታውራሪ ዳምጠውን ዋና መላክተኛ አድርገው፣ ቀኛዝማች ገነሜንና መምሕር ገብረ እግዚአብሔርን ጨምረው ከሙሴ ሌዎንቴፍ ጋራ ወደ መስኮብ እንዲሄዱ አደረጉ።

ለንጉሠ ነገሥት ኒኮላና ለእቴጌይቱ ለአሌክሳንድራ በያይነቱ የተላከው ገጸ በረከት እጅግ ደስ የሚያሰኝና ያማረ ነበር።

መላክተኞቹም ወደ መስኮብ አገር በደረሱ ጊዜ ፊታውራሪ ዳምጠውን በወርቅ ሠረገላ አስቀምጠው ወደ ቤተ መንግሥት ሲወስዷቸው የተደረገላቸውን የክብር አቀባበል ጽፈው በፖስታ ለአጼ ምኒልክ ልከው በአዲስ አበባ የሰማው ሰው ሁሉ በመስኮብ መንግሥት ወዳጅነት በጣም ደስ አለው። መላክተኞቹም በሰኔ ወር ከመስኮብ አገር ተነሥተው በሐምሌ ወር ጂቡቲ ገብተው ሐረር ላይ ከልዑል ራስ መኮነን ጋራ ተገናኝተው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

# ምዕራፍ ፳፬

## ራስ መንገሻ መቀሌን ለቀው ወደ ሕንጣሎና ወደ ደብረ ኃይላ ስለ መሄዳቸው

አጼ ምኒልክ ከወሎ ወደ አዲስ አበባ ከተመለሱ በኋላ ኢጣሊያኖች ከአዲግራት ተነሥተው ወደ መቀሌ መጥተው ራስ መንገሻን ለመውጋት ቁርጥ አሳብ ማድረጋቸው በተሰማ ጊዜ ራስ መንገሻ ባንድ ወገን ከአጼ ምኒልክ ሳይስፈቅዱ ከኢጣሊያኖች ጋራ ሲዋጉ እንደ ሰንዓፌ ጦርነት ድል የሆኑ እንደ ሆነ ለክብራቸው ትልቅ ውርደት የሚያመጣ መሆኑን ስለ ተረዱት ከመቀሌ ወጥተው ወደ ሕንጣሎ ተጓዙ። ኢጣሊያኖች ራስ መንገሻ ከመቀሌ መሄዳቸውን በሰሙ ጊዜ ከአዲግራት መጥተው ያላንድ ችግር መቀሌን ይዘው ምሽግ እየመሸጉ ተቀመጡ። ጄኔራል አሪሞንዲና ማጆር ቶዞሊ የሚባሉት ግን ራስ መንገሻን እየተከታተሉ እንዲወጉ ታዘው ነበርና አውራውን መንገድ ትተው የባላገሮች መሪ ይዘው ባቋራጭ መንገድ ወደ ሕንጣሎ ገሰገሱ። ራስ መንገሻም የኢጣሊያ ወታደሮች እንደተከታተሏቸው በሰሙ ጊዜ በፍጠንት ከሕንጣሎ ተነሥተው ወደ ደብረ ኃይላ ተጓዙ። በደብረ ኃይላም ከራስ መንገሻ ጋራ የነበሩ መኳንንቶች ምክር አድርገው «ከእንግዲህ ወዲህ ለእኛ መሸሽ አይገባንምና ለኢትዮጵያ እንሞታለን። ነገር ግን ራስ መንገሻ ቢማረኩም ቢሞቱም ለስማቸውና ለሀገራቸው ውርደት ለኢጣሊያኖች ትልቅ ደስታ ይሆናልና ከሸዋ ጦር እስቲመጣ ወደ ራስ ወሌ ግዛት ተጠግተው ቢቆዩ ይሻላል» ተባለና ከደብረ ኃይላ ወጥተው ወደ ስልዋ ሄዱ።

ማጆር ኢማሊዮ የሚባለው ግን ብዙ ወታደሮች ይዞ ሲገሰግስ ደብረ ኃይላ በደረሰ ጊዜ ራስ መንገሻን ሳያገኝ ቀረና በደብረ ኃይላ ከቀሩት መኳንንቶቻቸው ጋር ጦርነት ገጥሞ ድል አደረገ። ከነዚሁም መካከል ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም የሚባለው ቆስሎ ስለ ተማረከ ትልቅ ኃዘን ተደረገ። የቀሩት መኳንንቶች ግን እየተታኮሱ አምልጠው ከራስ መንገሻ ጋራ ተቀላቀሉ።

ቀኛዝማች ኃይለ ማርያምም እጅግ ስመ ጥሩ ጅግና ስለ መሆኑ የኢጣሊያኖቹ የጦር አለቃ ከወደቀበት አስነሥቶ በመልካም ሥፍራ አስተኝቶ በሐኪም እያሳከመ ካዳነው በኋላ ወደ አሥመራ ሰደደው።

ከደብረ ኃይላም ገስግሰው አምባ አላጌ ሲደርሱ ራስ መንገሻን አላገኙዋቸውም ነበርና በጣም አዘኑ። ስለሆነም የቀድሞው ራስ ስብሐት ከነልጆቻቸው የታሠሩት በዚያው በአምባ አላጌ ነበርና እርሳቸውን በማግኘታቸውና በመፍታታቸው ትልቅ ደስታ አደረጉ። ራስ ስብሐትም ወደ ጄኔራል ባራቴሪ ሄደው በተገናኙ ጊዜ የእንደርታን ግዛት ሰጥቶ ደስ አሰኛቸው።


# ምዕራፍ ፳፫

## አጼ ምኒልክ ከኢጣሊያኖች ጋራ ለመዋጋት ቁርጥ አሳብ ካደረጉ በኋላ አዋጅ ስለ መንገራቸው።

አጼ ምኒልክ ኢጣሊያኖች እስከ ደብረ ኃይላና እስከ አምባ አላጌ መጥተው አገር መያዛቸውን በሰሙ ጊዜ «እንደዚህማ እየገፉ ከመጡ በእግዚአብሔር ኃይል ሄጄ እዋጋለሁ እንጂ አዲስ አበባ ከተማዬ እስቲገቡ ዝም እላለሁን?» ብለው ለዘመቻው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን አዋጅ ነገሩ።

«ያገሬ ኢትዮጵያ ሰው ሁሉ ስማ!»

እግዚአብሔር በቸነቱ እስካሁን ድረስ ጠላት አጥፍቶ አገር አስፍቶ አኖረን። እኔም እስካሁን ገዛሁ። ከእንግዲህ ወዲህ ግን ስለ ሀገሬ ስለ ኢትዮጵያ ብሞትም ሞት የሁሉ ነውና አላዝንም። ደግሞ እግዚአብሔር እስካሁን በጠላት ፊት አሳፍሮኝ አያውቅምና ወደፊትም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም።



## የአጼ ምኒልክ ሠራዊት ጉዞ ወዳ አድዋ

አሁንም እግዚአብሔር በባሕር ወስኖ የሰጠንን አገር የሚያጠፉ፣ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት መጥቶብናልና ስንቅህን እያሰናዳህ ተከተለኝ። ያገሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! እስካሁን የበደልሁህ በደል ያለ አይመስለኝም።

ስለዚህ ለሀገርህ ለሚስትህ ለልጅህ ለሃይማኖትህ ስትል ጉልበት ያለህ በጉልበትህ፣ ገንዘብ ያለህ በገንዘብህ፣ ጉልበትም ገንዘብም የሌለህ ግን በኀዘንህ እርዳኝ። ይህን አዋጅ ከሰማህ በኋላ ወስልተህ ከዘመቻው ብትቀር ትቀጣለህ።«እኔም በጥቅምት ወር ከአዲስ አበባ እነሳለሁና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ወረይሉ ግባ። የጐጃም የቤጌምድር የደንቢያ የቋራ፣ የጨጨሆ በላይ ያለህ አሸንጌ ላይ የሰሜን የወልቃይት የጠገዴ ሰው መቀሌ ላይ ላግኝህ» የሚል ነበር።

ከዚህም በኋላ የሐረርና ያውራጃዎቿ ሁሉ ገዥ ልዑል ራስ መኮንን በመስከረም ፲፫ ቀን አዲስ አበባ ገቡ። ከጊቤ በታችም ያለው የዳር አገሩ ጦር በወለጋው ገዥ በፊታውራሪ ተክሌ ጠቅላይነት ገባ። ራስ ወልደ ጊዮርጊስና ደጃዝማች ተሰማ ብቻ የግዛታቸው አገር ሩቅ ስለሆነና ወዲያውም በክረምቱ ምክንያት ወንዙ ሁሉ ስለሞላ ወደ ኋላ ቆይተው ነበር።

ደግሞ በዚያን ዘመን የዳር አገር ሁሉ አዲስ የሚቀና ነበርና ምናልባት አረማዊ ሕዝብ የንጉሡን መዝመት ሰምቶ ከዘመቻ የቀረውን ሽማግሌውን ሴቱንና ሕፃናቱን እንዳይገድል ተብሎ ወደ ሸዋ እየተመለሱ እንዲቆዩ አዋጅ ስለ ተደረገ ካህናቱ ከነታቦቱ ሽማግሌው ከነሕፃናቱ ወደ ሸዋ እየተመለሰ በየርስቱና በየዘመዱ እየተጠጋ ተቀመጠ።

አጼ ምኒልክም ይህን ሁሉ ድርጅት ከጨረሱ በኋላ ለአዲስ አበባ ከተማና ለሀገሩም ሁሉ ጠባቂ ልዑል ራስ ዳርጌን አድርገው ረዳቶችም ደጃዝማች ኃይለ ማርያምንና ወህኒ አዛዥ ወልደ ጻድቅን ጨምረው በጥቅምት ፪ ቀን ሺ፰፻፹፰ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ተነሡ።

እቴጌ ጣይቱም ከኮንት አንቶኔሊ ጀምሮ ኢጣሊያኖች የኢትዮጵያን ነፃነት ለማጥፋት መጣጣራቸውን እያዩ በነገሩ ሲናደዱ ይኖሩ ነበርና ምንም ቢሆን ከዘመቻው አልቀርም ብለው የግል ሠራዊታቸውን በአዛዥ ዛማኔል አስከትተው ከጃንሆይ ጋራ ባንድነት ተነሡ።

በጥቅምት ፯ ቀን ጊዳ ላይ ሠፍረው ሳለ ከጧቱ በ፬ ሰዓት ያህል በየአሩ ላይ እንደ ቀስተ ደመና ኅብር ያለው በስተምዕራብ በኩል ታየና ወዲያው ድምጡ እንደ መብረቅ ሲጮህ በሙሉ ኢትዮጵያ ተሰማ። ጢሱም አረንጓዴ መስሎ አሥር ደቂቃ ያህል እየታየ ቆየና በጥቂት እያለ ጠፋ። ምክንያቱም ግን ምን እንደ ሆነ በእርግጥ አልታወቀም። አንዳንድ ሰዎች ኢጣሊያኖች የአጼ ምኒልክን ሠራዊት ለማስደንገጥ ወደ አየር የወረወሩት የአርቲፊሻል ርችት ነው ይሉ ነበር። አንዳንዱም ከመሬት መዞር የተነሣ በማግኔት የተሳበ ማዕድን ፈንድቶ ነው ይሉ ነበር። አንዳንዱ ደግሞ አጼ ምኒልክ ድል ለማድረጋቸው

እግዚአብሔር ያደረገው የታምራት ምልክት ነው ይሉ ነበር። ስለዚህ የዚህን ዕውቀት ለእግዚአብሔር ብቻ ትተነው ብናልፍ ይሻላል።

አጼ ምኒልክም ከጊዳ ተጉዘው በጥቅምት ፲፯ ቀን ወረይሉ ገብተው የዘመቻውን ነገር ሲያደራጁ ሰነበቱ። የድርጅቱም ነገር ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

፩ኛ። ግርማዊነታቸው መኻል ሠፋር የሚባለውን ጭፍራ ብቻ አስቀርተው በወሎ አውራጃ ሆነው እየተጠባበቁ እንዲቆዩ ነው።

፪ኛ። ልዑል ራስ መኮንን የጦር አበጋዝ አድርገው ራስ ሚካኤልን ራስ ወሌን፣ ራስ መንገሻን አቲከምን፣ ራስ አሉላን ደጃዝማች ወልዴን፣ ፊታውራሪ ገበየሁን ፊታውራሪ ተክሌን፣ ሊቀ መኳስ አድነውን፣ ቀኛዝማች ታፈሰን ወደ ፊት እንዲሰዱት ነው።

፫ኛ። ልዑል ራስ መኮንን የሚቻል ቢሆን ከኢጣሊያኖች ጋራ የዕርቅ ነገር እንዲጀመር የማይቻል ቢሆን ግን የጦር አበጋዝ ሆነ እንዲያዋጉ ነው።

፬ኛ። ልዑል ራስ መኮንን የኢጣሊያኖችን አኳኋን መርምረው ምናልባት እጅግ ብዙ መሆናቸውን የተረዱት እንደሆነ ወደ አጼ ምኒልክ እንዲልኩና እስቲደርስላቸው ጦርነት እንዳይጀምሩ ነበር።

የዳር አገርም ባላባቶች የጅማ ባላባት አባ ጅፋር፣ የወላሞ /ወላይታ/ ባላባት ካዎ ጦና፣ የወለጋ ባላባት ደጃች ጆቴ የሌቃ ባላባት ደጃች ገብረ እግዚአብሔር እስከ ወረይሉ ተከትለው ሄደው ነበርና እየተመለሳችሁ አገር ጠብቁ ብለው አራቱንም አሰናበቷቸው።

ልዑል ራስ መኮንንና የቀሩትም ራሶች ከጃንሆይ እየተሰናበቱ ወደ ፊት ከተጓዙ በኋላ አጼ ምኒልክም ከወረይሉ ተነሥተው ወደ ደሴ ተጓዙ።

ኢጣሊያኖች መሐመድ አንፋሪን አስከደውታል እየተባለ ገና አስቀድሞ ተወርቶ ነበር። አጼ ምኒልክ ግን እርግጡ እስቲታወቅ በማለት ጦር ሳይሰዱበት ቆይተው ነበርና አሁን ከደሴ ተጉዘው ውጫሌ ሲደርሱ የመሐመድ አንፋሪን መክዳት እርግጡን ስለ አገኙት በክረምቱ ምክንያት ወደ ኋላ ለቆዩት ለራስ ወልደ ጊዮርጊስና ለደጃዝማች ተሰማ ወደ እኛ መምጣታችሁ ቀርቶ በዚያው በአንኮበር አድርጋችሁ ወደ አውሳ ዘምታችሁ መሐመድ ቀርቶ በዚያው ትእዛዝ አድርጋችሁ ወደ አውሳ ዘምታችሁ መሐመድ አንፋሪን መክዳት እርግጡን ስለ አገኙት በክረምቱ ምክንያት ወደ ኋላ ለቆዩት ለራስ ወልደ ጊዮርስጊስና ለደጃዝማች ተሰማ ወደ እኛ መምጣታችሁ ቀርቶ በዚያው በአንኮበር አድርጋችሁ ወደ አውሳ ዘምታችሁ መሐመድ አንፋሪን ውጉ የሚል ትእዛዝ ወደ ፊት ይጓዙ ጀመር።

መሐመድ አንፋሪ የአውሳና የአዳል /የአፋር/ አገር ባላባት ነው። እርሱም ከብዙ ዘመን ጀምሮ ለሸዋ ንጉሥ እየገበረና እያገለገለ በእምነት የሚኖር ነበር። በአጼ ዮሐንስ ዘመን አለቃ ብሩ የሚባለው ያመጣውን ባሻ ምስንጅርን /ሙዚንገርን/ ከነተከታዮቹ በገደለ ጊዜ ከእርሱ የማረከውን የጦር መሣሪያ ሁሉ ወደ ሸዋል ልኮ ከነተከታዮቹ በገደለ ጊዜ ከእርሱ የማረከውን የጦር መሣሪያ ሁሉ ወደ ሸዋ ልኮ ለንጉሥ ምኒልክ አስረክቦ ነበር። በኋላ አጼ ዮሐንስ ወደ ጕራሴ /ጉራሌ/ በዘመቱ ጊዜ አውሳን /አፋርን/ ለመውጋትና አገሩን ለማጥፋት ቢያስቡ ለጊዜው ንጉሥ ምኒልክ በዚያው ነበሩና ከፈቃዳችን ወጥቶ የማያውቅ ዜጋችን ነው ብለው አስረድተው አገሩን ከጥፋት ድነውለት ነበር።

በኋላ ግን አብድርሁማን የሚባል አማች ነበረውና ኮንት አንቶኔሊ በአሰብ እየመጣ በአውሳ /በአፋር/ ሲመላለስ ከአብድርሁማን ጋራ ተዋውቆ ገንዘብና የጦር መሣሪያ እየሰጠ ልቡን ስለሳበው፣ እርሱም መሐመድ አንፋሪን እያታለለ የኢጣሊያኖች ወገን ስለ አደረገው ባሁኑ ዘመቻ ጊዜ ከአጼ ምኒልክ መከዳቱ የተገለጠ ሆነ። ስለዚህም ራስ ወልደ ጊዮርጊስና ደጃዝማች ተሰማ ሄደ እንዲወጉት ታዘዙ። ለሁለቱም የጦር አበጋዝ የሆኑት የወህኒ አዛዥ ወልደ ጻድቅ ነበሩ። ምክንያቱም ሁለቱ ትልልቅ መኳንንቶች በጦር አበጋዝነቱ እንዳይቀናኑ ሥራቸውንም በፍቅር እንዲሠሩ ለማድረግ ነበር። አጼ ምኒልክም ከውጫሌ ተጉዘው በየጁ አውራጃ መርሳ ከሚባለው አገር ሲደርሱ ደጃዝማች ጓንጉል ዘገየ ከበረሃ መጥቶ ይማሩኝ ብሎ ገባላቸው።

ወደ በረሃም የገባበት ምክንያቱ በየጁ ተወላጅነቱ የራስ ወሌ ተወዳዳሪ ስለሆነ እቴጌ ጣይቱ አይወዱትም ነበር። በዚህም መካከል የአጼ ምኒልክን ልጅ ልዕልት ዘውዲቱን ላገባ ነው እያለ አስወርቶ ነበርና እንኳን የጃንሆይን ልጅ አግብቶ እንዲያውም ቢሆን በራስ ወሌ ላይ ክፉ ነገር ያስባልና ይታሠርልኝ እያሉ እቴጌ ለአጼ ምኒልክ ያመለክቱ ነበር። ደጃዝማች ጓንጉልም እቴጌ ጣይቱ በጠላትነት እንደተነሡበትና እንደሚያሸንፉትም ስለ አወቀ ተይዤ ከመታሠር በበረሃ መኖር ይሻለኛል ብሎ ከአዲስ አበባ ገግሶ በየጁ በረሃ ገብቶ ተቀምጦ ነበር።

ነገር ግን የኢትዮጵያ ሰዎች ምንም አንዳንድ ጊዜ እርስ በርሳቸው ቢጣሉም ያገራቸውን ነፃነት የንጉሣቸውን ክብር የሚጐዳ ነገር በመጣ ጊዜ ደማቸውን ለማፍሰስ ቆራጦች ናቸውና ኢጣሊያ አላጌ ድረስ መጥቶ አጼ ምኒልክ ከአዲስ አበባ ድረስ መጥተው በሚዋጉበት ጊዜ በጌታዬ ፊት ቢሆን እገድላለሁ ባይሆንም እሞታለሁ እንጂ ተለይቼ አልቀርም በማለት ከበረሃ ወጥቶ ገባላቸው። በዚያንም ጊዜ በአጼ ምኒልክና በመኳንንቱም ሁሉ ልብ የተደረገውን ደስታ ማንም ሊናገረው አይችልም ነበር።

# ምዕራፍ ፷፮

## ልዑል ራስ መኮንን በጦር አበጋዝነታቸው አላጌ ላይ ከኢጣሊያኖች ጋር ስለ መዋጋታቸው

ልዑል ራስ መኮንን የጦር አበጋዝ ስለሆኑ እንደ ሥርዓቱና እንደ ልማዱ እርሳቸው ከራስ ሚካኤል ጋራ ደጀን ሆነው ራስ መንገሻንና ራስ አሉላን በቀኝ፣ ራስ ወሌን በግራ ፊታውራሪ ገበየሁን በግምባር አድርገው ሲጓዙ አሸንጌን ካለፉ በኋላ ጦርነት ሳይደረግ ኢጣሊያኖች የአላጌን አምባ በእርቅ እንዲለቁ ለማድረግ አስበው ለኢጣሊያ የጦር አለቃ ለማጆር ቶዞሊ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ላኩበት። «ምንም ለጦርነት ታዝዤ ብመጣ የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ እርቅ ማድረግ ይሻላል ብዬ ወደ ጠቅላዩ የጦ አለቃ ወደ ጄኔራል ባራቴሪ የወዳጅነት ቃል ልኬ ነበር። ነገር ግን እስካሁን ምላሽ ስላልመጣልኝ ወደ ፊት ለመጓዝና ጦርነት ለማድረግ ግድ ይሆንብኛል። ንጉሠ ነገሥቱም አሸንጌን አልፈው ወደዚህ መጥተዋልና ከዚህ ለመቆየት የማይቻል ነው። ኅዳር ፳፪ ቀን ፲፰፻፹፰ ዓመተ ምሕረት።»

ማጆር ቶዞሊም ከዚህ የሚከተለውን ቃል መለሰላቸው። «እጅግ ክቡር ራስ መኮንን ሆይ! ወደ ጄኔራል ባራቴሪ የጻፉትን ደብዳቤ በዚሁ ወር አሳልፌሎታለሁ። ነገር ግን ይህን ከጻፉ በኋላ ወደ ፊት መገስገስዎ ጦርነት እንጂ ርቅ አለመፈልግዎን ያስረዳል። ሰው እንደዚህ አደርጋለሁ ብሎ ያስባል እንጂ ፍጻሜው በእግዚአብሔር እጅ ነውና በጦርነት የሚያመጣውን ጉዳት ማንም ሊያውቀው አይችልም»እያለ የማስፈራራት ቃል ጨምሮ ላከባቸው።

ልዑል ራስ መኮንንም የማጆር ቶዞሊን ደብዳቤ ከተቀበሉ በኋላ በደባቤው ውስጥ ለእርቅ የሚበቃ ምልክት ባይገኙበትም በግስጋሴ ሄደው በኅዳር ፳፫ ቀን አላጌ ደረሱ። ፊታውራሪ ገበየሁም በግምባር እየተጓዘ ሠፈሩም ከደጀኑ እየራቀ ነበርና በኅዳር ፳፫ ቀን ሌሊቱን በ፲፩ ሰዓት ከማጆር ቶዞሊ ዘበኞች ጋራ ተገናኝተው ተኩስ በተጀመረ ጊዜ የራስ መንገሻ ሎሌ ሹም አጋሜ ተስፋይ በፍጥነት ወደ ልዑል ራስ መኮንን ሄዶ ይህ አሁን ያለንበት ሥፍራ ከአምባ አላጌ ለሚተኮሰው መድፍ የተመቸ ነውና በዚህ ሥፍራ ጦርነት መግጠማችን ቀርቶ በሌላ ወገን ዞረን ብንገጥም ይሽላል ብሎ አመለከተ። ነገር ግን ፊታውራሪ ተክሌና ቀኛዝማች ታፈሰ የተኩሱን ብዛት እየሰሙ ገና ሳይታዘዙ ወደ ፊታውራሪ ገበየሁ ስለተቀላቀሉ ጦርነቱን ለማገድ የማይቻል ሆኖ ነበርና ልዑል ራስ መኮንን የቀሩትን ራሶች በቀኝና በግራ አሠልፈው እርሳቸው በማኻል ሆነው ወደ አምባው ቀርበው ተጋጠሙት። አንድ ሰዓት ያህል እንደ ተዋጉ በግራ የተሰለፉት ራስ

ወሌ በግምባር የገጠማቸውን ድል ስለ አደረጉት እየሸሸ ላይኛው አምባ ገብቶ መድፍ ይተኩስባቸው ጀመር።

የራስ መኮንና የራስ ሚካኤልም ሠራዊት መኻል ለመኻል ገብተው በጐራዴ ስለ ተጋጠሙት ራስ መንገሻና ራስ አሉላም በስተጀርባ ዞረው ስለገቡበት ወደ ኋላው ለመሸሽ ከአምባው መውረድ ጀመረ። ማጆር ቶዞሊ ግን ስመ ጥሩ ጀግና ነበረና ምንም ቢሆን አልማረክም ብሎ በብርቱ ሲዋጋ በሠልፉ ላይ ሞተ።

የጦርነትም ነገር ዋናው ከወደቀ መፈታቱና መፍረሱ አይቀርምና የኢጣሊያ ሠራዊት በቀኝም በግራም ሲሸሹ ከብቱና ሰውም ስለተደበላለቀና መንገዱ ስለ ጠበበ ርዝመቱ ፬፻ ሜትር በሚያህል ገደል እየተወረወሩ አለቁ። በጠመንጃም ከሞቱት በጐራዴም ከሞቱት እየተመቱ የሞቱት ይበዛሉ። ከጦር አለቆቹም እኩሉ በሠልፉ ውስጥ ሞቱ፣ እኩሉም ተማረኩ እኩሉም እየሸሹ አመለጡ። በአላጌ ጦርነት ያለቁት የኢጣሊያ ሠራዊት ነጮ ጥቁሮም ባንድነት ሆነው ፪ሺ፱፻፷ ይሆናሉ። ከኢትዮጵያም ሠራዊት ወገን ከሺ የሚበልጡ ሞተዋል።

ፊታውራሪ ገበየሁም በጉዞው ላይ ትቂት ታሞ ሰንብቶ ነበር። ቢሆንም ጦርነቱን የጀመረ እሱ ለመሆኑ ላገሩና ለንጉሡ ለስሙም ክብር ሲል ጠመንጃህን ትተህ በጐራዴ በለው እያለ በጀግነንት ሲዋጋ ስለ ዋለ እንኳን በኢትዮጵያ ሠራዊት ፊት በኢጣሊያም ሠራዊት ፊት እጅግ የተመሰገነ ሆነ። ካሁን ዘመቻ አስቀድሞ ጐበዝ አየሁ የሚባል አዲስ ነፍጥ ወጥቶ ነበርና፤ «ከነፍጥ ጐበዝ አየሁ ከአሽከር ገበየሁ!» እየተባለ ተዘፈነለት።

የኢጣሊያም ሠራዊት የሞተው ሞቶ የሸሸው ሸሽቶ የተማረከው ተማርኮ ድሉ ለልዑል ራስ መኮንን ከሆነ በኋላ ሠራዊቱ በየሠፈሩ ገብቶ ለሞተው ወንድሙና ዘመዱ ለባልንጀራውም ያለቅስ ጀመር።



ራስ መኰንን ወልደሚካኤል በዋና የጦር አበጋዝነት አለባበስ

ልዑል ራስ መኮንንም የሠራዊቱን ልቅሶ በሰሙ ጊዜ በመኳንንቱና በሠራዊቱ መካከል ቆመው «ወንድሞቼ ሆይ! ዛሬ ስለ ሀገራችን ነፃነትና ስለ ንጉሣችን ክብር ብንሞት ለእኛ ደስታና ክብራችን ነው እንጂ ኦት አይባልምና ግዳይ ጣሉ እንጂ አታልቅሱ!» ብለው

ስለ ተናገሩ እንደ ሀገሩ ልማድ እኩሉ በፈረስ እኩሉም በእግር እየሆነ የሠራውን ጀብዱ እየተናገረ በፊታቸው ይፎክር ጀመር።

ከዚህም በኋላ እንደ ሠለጠነው ዓለም ጦርነት አደራረግ ይህ የኢትዮጵያ ነው ይህ የኢጣሊያ ነው ሳይሉ የሞተውን ሁሉ እያነሡ ያስቀብሩ ጀመር። የቆሰለውንም በየባላገሩ ቤት እያስመሩ እንዲታመም ምርኮኛውም ሳይጉላላ በክብር እንዲቀመጥ አደረጉ። የማጆር ቶዞሊንና የጦር አለቆቹንም ሬሳ አስነሥተው በማዕርግ በታላቅ ሠልፍና አጀብ ወስደው እርሳቸውም በዚያው ቆመው አስቀበሩዋቸው።

ልዑል ራስ መኮንን ድሯ ኢንተርናሲዮናልን /የዓለም መንግሥታት ሕግ/ አውቀው ከጠላት ወገን የሞቱትን በማስቀበራቸው የቆሰሉትን በማስታመማቸው የተማረኩትንም ባለማጉላላታቸው በኢጣሊያ አገር እንኳ ሲመሰገኑ ይኖሩ ነበር።

ደግሞ ምንም ድሉ ለኢትዮጵያ ቢሆንም መጀመሪያ ፊታውራሪ ገበየሁ ቀጥሎም ቀኛዝማች ታፈሰ ሳይታዘዙና ስያስፈቅዱ ከኢጣሊያ ጋር ጦርነት መግጠማቸው በወታደር ደንብና ሕግ ያልተፈቀደ ስለሆነ ነገሩን ለአጼ ምኒልክ እስቲያሳውቁ ይለቀቁ የሚል ትእዛዝ እስቲመጣላቸው የቁም እሥር እያደረጉ አስቀመጧቸው። ከዚህም በኋላ በአላጌ የተማረከውን መድፉን ጠመንጃውን ጥይቱን ሌላውንም የጦርነት ዕቃ ሁሉ አስነሥተው የሚቻለውን ይዘው የማይቻላቸውን በዚያው በአላጌ ዙሪያ ባለው በየባላገሩ ቤት ትተው ወደ አጼ ምኒልክም የጦርነቱን አኳኋንና የድሉን የምሥራች ጽፈው ወደ መቀሌ ጉዞ ጀመሩ።

አጼ ምኒልክም በአላማጣ ጥግ ሠፍረው ሳሉ የድሉ የምሥራች ደረሰላቸውና ትልቅ ደስታ ሆነ።

የኢጣሊያ ጠቅላይ የጦር አለቃ ጄኔራል ባራቴሪ ግን በልዑል ራስ መኮንን አበጋዝነት የመጣውን ሠራዊት ብዛት አጼ ምኒልክም ከወደ ኋላ እየገሰገሱ መምጣታቸውን ስለ ሰማ ጄኔራል አሪሞንዲ የሚባለውን ዋና አድርጎ ማጆር ኤማሊዮ፣ ማጆር ካቴ፣ ማጆር ጋልያኖ ለሚባሉ የጦር አለቆች ፰ ሺ ወታደሮች ጨምሮ በአላጌ ማጆር ቶዞሊን እርዱ ብሎ ልኮ ነእብርና ገና አላጌ ሳይደርሱ የድሉን ወሬ ስለሰሙ ወደ መቀሌ የመመለሳቸውን ነገር ሲመካከሩ ከድሉ በኋላ ፊት ለፊት የሚጓዘው የሸዋና የወሎ የየጁም ወታደር ደረሰባቸውና ተኩስ ተጀመረ። ከኢጣሊያኖች ወገን ፲፫ ያህል እንደሞቱ የጄኔራል አሪሞንዲ ፈርሱ ቆሰለና ወደቀ። እርሱ ግን በሌላ ፈረስ ተዛውሮ የቀሩትም የጦር አለቆች ባንድነት ሆነው ወደ መቀሌ አመለጡ።

መቀሌም በደረሱ ጊዜ ጄኔራል አሪሞንዲ በመቀሌ ምሽግ ከመቆየት ወይም ምሽጉን አፍርሶ ትቶ ከመሄድ የሚሻለውን ምክር ቢጠይቃቸው ከጦር አለቆቹ አንዳንዱ የመቀሌን ምሽግ አፍርሰን ወደ አዲግራት ሄደን ኃይላችንን አበርትተን ብንጠባበቅ ይሻላል እያሉ ተናገሩ።

ማጆር ጋልያኖ የሚባለው ግን «የመቀሌን ምሽግ አፍርሰን መድፋችንንና ወታደራችንን ይዘን መሄድ ለኢጣሊያ ሰንደ ዓላማ ውርደት ነውና ምሽጉን ባናፈርሰው ይሻላል። እንዲያውም እኔ ራሴ በዚሁ ዋና የጦር አለቃ ሆኜ ለመቅረት ፈቃዴ ነው» ብሎ የጀግንነት ቃል ስለ ተናገረ ሁሉም በዚሁ ተስማምተው ማጆር ጋልያኖ ከወታደሮቹ ጋራ ቀረና ጄኔራል አሪሞንዲ የቀሩትን የጦር አለቆች ይዞ ወደ አዲግራት ተጓዘ። አዲግራት ማለት የአጋሜ ዋና ከተማ ነው። ለጊዜው ብርቱ ምሽግ ስለመሸጉበት በቀኝም በግራም በፊትም በኋላም ላለው ለኢጣሊያ ሠራዊት መሰብሰቢያና መገኛ አድርገውት ነበር።

አጼ ምኒልክም ከአሸንጌ ተጉዘው መኻን - ሕዝባ ከሚባለው አገር ሲደርሱ ውሎ አድርገው ነበርና ላዩን  በቤጌምድር አድርገው ሲጓዙ የነበሩት የጐጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መጥተው ተገናኙ። ከዚያም ተጉዘው ጨለቆት ሲደሱ ራስ መኮንንና በርሳቸው አበጋዝነት ቀድመው በአላጌ ተዋግተው ድል ያደረጉት ራሶች ሁሉ በታኅሣሥ ፳፯ ቀን ከአጼ ምኒልክ ጋራ ተገናኙ። በአላጌም ከተማረከው መድፍ ማለፊያ ማለፊያውን ይዘውት ይጓዙ ነበርና አቅርበው ካሳዩ በኋላ ለዛሬው ጦርነት የእኛ መድፎች ይበቁናል ተብሎ የተማረኩት መድፎች ወደ ሸዋ እንዲላኩ ተደረገ።

በዚያም ዘመን ልደት በ፳፰ ቀን ውሎ ነበርና በዓለ ልደትን በጨለንቆት አክብረው በ፳፱ ቀን መቀሌ ገቡ።

# ምዕራፍ ፳፺

## ስለ መቀሌ ጦርነት

መቀሌ የእንደርታ ዋና ከተማ ነው። ኢጣሊያኖች ራስ መንገሻን በሰንዓፌ ድል ካደረጉ በኋላ እየተከታተሉ መጥተው አድዋንም መቀሌንም ይዘውት ነበር። በከተማውም አጠገብ በጉብታው ላይ ከተሠራው ከእንዳ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ታቦቱን አስወጥተው ብርቱ ምሽግ ጀምረው ሳሉ ራስ መንገሻ ወደ ኋላ እያፈገፈጉ ስለ ሄዱባቸው የምሽጉን ሥራ ሳይጨርሱ ወደ ደብረ ኃይላና ወደ አላጌ ገስግሰው ነበር።

አሁን ግን በአላጌ የነበረው የኢጣሊያ የጦር አለቃ ማጆር ቶዞሊ ተዋግቶ ድል ከሆነና ከሞተ በኋላ ጄኔራል አሪሞንዲ ለእርዳታ መጥቶ ነበርና ከአላጌ ጦርነት እየሸሹ ያመለጡት ሁሉ ከጄኔራል አሪሞንዲ ጋራ ተቀላቅለው ወደ መቀሌ ተጉዘው በምሽጉ ውስጥ ገቡ። በመቀሌም ዙሪያ ካለው አገሩን ኢትዮጵያን እየከዳ ለኢጣሊያኖች በገንዘብ እየተቀጠረ የገባው ሰው ሁሉ እየፈራ ሚስቱን ልጆቹን ከብቱንም እየያዘ ወደ ምሽጉ ስለ ገባ ምሽጉ ጠባቸው ነበር። ሳይጨረስም የቀየውን የምሽጉን ሥራ እጅ በእጅ ብለው ጨረሱት።

ከአላጌ የመጣውን ቁስለኛ ግን አንድ እንኳ ሳይቀር ወደ አዲግራት ሰደዱት። ምክንያቱም በመቀሌ /በእንዳ ኢየሱስ/ ምሽግ ያለው ወታደር ቁስለኞቹን እያየ ፍርሃት እንዳያድርበት ነው።

ልዑል ራስ መኮንንና የቀሩትም ራሶች ከአላጌ እየተከታተሉ ሄደው መቀሌ ሲደርሱ የመቀሌን /የእንዳ ኢየሱስ/ ምሽግ ከበው ተቀመጡ። ከአላጌ እስከ መቀሌ ርቅቀቱ ፳ ኪሎ ሜትር ነው።

ልዑል ራስ መኮንን በማናቸውም ቢሆን ጦርነቱ ቀርቶ ነገሩ ሁሉበስምምነትና በወዳጅነት እንዲጨረስ ያስቡ ነበርና ይህንኑ አሳባቸውን በደብዳቤ አድርገው ለጠቅላይ የጦር አለቃው ጄኔራል ባራቴሪ ወደ አለበት ወደ አዲግራት ልከው የዚያን ምላሽ ሲጠባበቁ ለዚሁ ጉዳይ ሌተናንት ፓርቲኒ የተባለ አንድ የወታደር አለቃ ይመጣል ስለ ተባለ ለእርሱ ተቀባይ ብላታ እንግዳ ተሰማ የተባለ ወደ ምሽጉ ተልኮ ሄደ። ልየተናንት ፓርቲኒም በመጣ ጊዜ ልዑል ራስ መኮንን ከቀሩት ራሶች ጋር ባንድነት ሆነው በወዳጅነት ተቀብለው የዕርቁን ሀሳብ ነግረው አሰናበቱት።

አጼ ምኒልክም ከጨለቆት ተነሥተው ወደ መቀሌ በገቡ ጊዜ ከምሽጉ ራቅ ያለ ሥፍራ ላይ ሠፈር አድርገው ወዲያው ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋራ ከፍ ባለ ሥፍራ ላይ ተቀምጠው የእንዳ ኢየሱስን ምሽግ በመነጽር ሲያዩ አመሹ።

ምሽጉ በጣም የጠነከረ ነበር። ዙሪያውን በረድፍ በረድፍ እየሆነ በግምብና በካብ ተሠርቷል። በስተ ውጭም ፈረሰኛና እግረኛ ጥሶ እንዳይገባ በሽቦ ታሮጥሮአል። በካቡም ጥግ አፈርና አሸዋ በጆንያ /በከረጢት/ እየተመላ ተደርድሮበታል። ከዚህም በቀር የሚያሠጋው ሥፍራ ዲናሚትና ባሩድ ሌላም ይህን የመሰለ የሚፈነዳ ነገር ቀብረውበት ነበር። አጼ ምኒልክም የምሽጉን መጠንከር የዲናሚቱን መቀበር በሰላይና በወሬ ሰምተውት ስለ ነበረ ወታደሮች ወሸ ምሽጉ እንዳይቀርቡና እንዳይዋጉ አስለፍፈው ነበር። ዋና አሳባቸውም በዚህ በመቀሌ ምሽግ ሠራዊታቸውን ከማድከም ወደ አጋሜ አልፈው በዚያው በኩል ወደ አሥመራ ሄደው ዋናውን ጦርነት በአሥመራ ላይ ለማድረግ ነበር።

ነገር ግን አሳብን የሚጨርሰው ጊዜ ነው እንጂ ሰው ብቻ አይደለምና አንድ ወታደር ስንቁንና ዕቃውን በአጋሠሡ ጭኖ ወደ ሠፈር ገብቶ አጋሠሡን ሲያራግፍ በቅሎው ደነበረችና በሠፈር መካከል ፈርጥጣ ስትሄድ በሠፈሩ ያሉት ሌሎችም በቅሎዎች እየደነበሩና እየፈረጠጡ የኢጣሊያኖቹ ከብቶች ወደ ተሰማሩበት አቅንተው ስለሄዱ ወታደሮቹ በቅሎዎቻቸውን ለመመለስ እየተከታተሉ በሮጡ ጊዜ በምሽጉ ውስጥ ያሉ ኢጣሊያኖች የአጼ ምኒልክ ወታደሮች ለጦርነት የመጡ መስሎዋቸው መድፍ መተኮስ ጀመሩ።

አጼ ምኒልክ በፍጥነት ሊቀ መኳስ አባተንና በጅሮንድ ባልቻን አስጠርተው መድፍና መትረየስ እየጠመዳችሁ ተኩሱ ብለው ሊቀ መኳስ አባተን በቀኝ በጅሮንድ ባልቻን በግራ ሰደዱዋቸው ሲተኩሱ አመሹ።

ከዚህም በኋላ ልዑል ራስ መኮንንና የቀሩትንም ራሶች አስጠርተው የኔ አሳብ ወደ አዲግራት ወደ አሥመራ ሄደን ጦርነቱን በዚያ ለማድረግ ነበር። አሁን ግን በዚህ በምሽጉ ውስጥ ያሉ ኢጣሊያኖች መድፍ እየተኮሱ ጦርነት ከጀመሩ እንዲህ ማድረጋቸውን ባይኔ እያየሁ ጠላቴን በስተኋላዬ አድርጌ ወደ ፊት አልሄድምና ካብ ካባችሁን አፈር ደልድላችሁ ጠንክራችሁ ተዋጉ። ለመድፉና ለመትረየሱም አባተ ባልቻ ዋና ይሁኑ ብለው አዘዙና ወዲያው ማታውኑ ጀምሮ ሌሊቱን ሁሉ ለመድፍ ለመትረየሱ መታኮሻ የሚበቃ ካብ ተክቦ አደረና ከጠዋቱ ጀምረው ቀኑን ሁሉ ሲታኮሱ ዋሉ።

ደግሞ በእንዳ ኢየሱስ ምሽግ ውስጥ የሚበቃ ውሃ እንደሌለና የውሃው ትልቅ ምንጭ ያለው ከምሽጉ ውጭ መሆኑን አጼ ምኒልክ ሰምተው ነበረና የውሀውን ምንጭ ከመያዝና በውሀ ጥም ከማስጨነቅ የሚሻል ሌላ ነገር አይገኝም ብለው ብዙ ብዙ ጭፍራ ያሏቸውን የእልፍኝ አሽከሮቻቸውን እነ ልጅ ገብረ ጊዮርጊስን እነ ድልነሴን እነ ሽዋየን ሌሎችንም ሁሉ በሌሊት ሄዳችሁ የውሃውን ምንጭ ይዛችሁ ጠብቁ ብለው አዘዙዋቸው።

ከእቴጌ ጣይቱም የጦር ሠራዊት ክፍል በየደንቡ እየታዘዘ ተጨምረውላቸው ነበር። ለውሀው መጠበቅ የታዘዙት ሰዎች ስለ ሀገራቸውና ስለ ንጉሣቸው ፍቅር ምንም ሳይፈሩ በድፍረት እየሄዱ በዚያው በምንጩ ዙሪያ የመታኮሻ ካብ እየካቡ ጠንክረው ይጠብቁ ጀመር። ኢጣሊያኖችም የውሀ ምንጭ ይይዝብናል ብለው አላሰቡም ነበርና በሦስት ሰዓት ተሰልፈው መጥተው እስከ ፺ ሰዓት ጦርነት ገጠሙዋቸውና የማይችሉ ስለ ሆኑ ተመልሰው ወደ ምሽጋቸው ገቡ። ስለሆነም ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰዎች መሞታቸው አልቀረም። በነጋም ጊዜ ሊቀ መኳስ አባተ መድፉን እያነጣጠረ ቢተኩስ የዕቃ

ቤታቸውንና የመኻል ቤታቸውን ያፈርስባቸው ጀመር። በጅሮንድ ባልቻም በበኩሉ በመነጽር ኣይየ በመተኮስና በመምታቱ ኢጣሊያኖቹ በታም ደንግጠው ነበር።

እንደዚህም አድርገው አሥር ቀን ሙሉ ውሀውን ይዘው ስለ አስጨነቁአቸው እርቅ አስመስለው ለመውጣት ይማከሩ ጀመር። ይህም ሁሉ ሲሆን ራሶቹ ተራ ገብተው ማታ ማታ ወታደሮቻቸውን እየላኩ ዘብ ሲያስጠብቁ ያድሩ ነበርና በጥር ፫ ቀን የዘቡ ተራ የልዑል ራስ መኮንን ስለሆነ መኳንንቶቻቸውና ወታደሮቻቸው ለዘብ ጥበቃ ሄደው ሳሉ «እስከ መቼ ከዚህ ስንጠባበቅ እንኖራለን? ቢሆንም ባይሆንም ባንድ ልብ ባንድ ጉልበት ሆነን እንግባበትና ይለይለት» ተባብለው እየተፎካከሩ ሄደው የውጭውን የሽቦውን አጥር ቆራርጠው ወደ ካቡ ተጠጉ። ሌሊቱንም ሁሉ መሰላል ሲሠሩ አድረው ሲነጋ በ፲ ሰዓት ጀምረው በመሰላሉ እየተንጠላጠሉ እጅ ለእጅ እየተያያዙ መውጣት ስለ ጀመሩ ኢጣሊያኖቹ የተመቸ ሥፍራ ይዘው ነበርና እየተታኮሱ ከመሰላሉ ላይ እየገነጠሉ ይጥሏቸው ጀመር።

ይህንን የመሰለውን ጦርነት በጦር በጐራዴ በሚዋጉበት በቀድሞ ዘመን ነበረ እንጂ በጠመንጃ በሚዋጉበት በዛሬው ዘመን ጦርነት የሚሆን አልነበረምና የልዑል ራስ መኮንን ሠራዊት የስሕተትና የድፍረት ሥራ በመሥራታቸው ትልቅ ጉዳት ደረሰባቸው። ምንም እንኳ ብዙ ኢጣሊያኖች ቢገድሉም ከነርሱም ወገን ከመኳንንቱም ከወታደሩም ወገን የሞቱት ከ፮፻ ይበልጣሉ።

በዚያውም ያለ የኢጣሊያ የጦር አለቃ ማጆር ጋልያኖ ምንም እንኳ ምሽጉ የማይደፈር መሆኑን ቢያውቅም ውሀው ስለተያዘበት በዚያ ብዙ ቀን ለመቆየት እንደማይቻል ተረድቶት ነበረና ከርሱ ጋራ ያለውን ሙሴ ፌልተር የሚባለውን ወደ ልዑል ራስ መኮንን ልኮ ሰደደው። ለዚያም መልዕክት ሙሴ ፌልተር የተመረጠበት ምክንያቱ እርሱ ከዚህ ዘመቻ አስቀድሞ የኢጣሊያ መንግስት ሰው መሆኑ ሳይገለጥ በሐረር ከተማ እንደ ነጋዴና እንደ ተራ ሰው መስሎ ከልዑል ራስ መኮንን ጋራ ተላምዶ ነበርና ነገሩን አቃንቶ ሳይመለስ አይቀርም በማለት ነው።

ሙሴ ፌልተርም ወደ ልዑል ራስ መኮንን ቀርቦ «የእንናተ ሠራዊት ወደ ምሽጉ እየቀረበ ለምን ያልቃል? የኛስ ሠራዊት ለምን በውሀ ጥም ይሞታል? ነገሩ በፍቅር ከሆነ እንኳን መቀሌን አዲግራትንም ለቀን እንሄዳለን» እያለ የማታለል ቃል ተናገረ።

ልዑል ራስ መኮንንም «የእርቁን ነገር ወደ ፊት እንነጋገራለን እኔም ገና መቀሌ እንደደረስሁ ይህንኑ የእርቁን ነገር ወደ ጄኔራል ባራቴሪ ልኬ ነበር። አሁን ግን ትናንት የሞቱትን የመኳንንቶቼንና የወታደሮቼን ሬሳ እንዳስቀብር ለማጆር ጋሊያኖ ንገርልኝ» ብለው ሰደዱት።

ማጆር ጋሊኖም ይህን በሰማ ጊዜ «በዚህ በምሽጉ አጠገብ በምጩ ዳር ያለው ወታደር ሁሉ ወደ ሠፈሩ የተመለሰ እንደ ሆነ የሞቱትን ሰዎች ሬሳ ለመውሰድ ትችላላችሁ» የሚል ምላሽ ሰጥቶ ሙሴ ፌልተርን መልሶ ሰደደው። ራስ መኮንን ግን እንደ ጦርነቱ ሕግ የሁለቱንም ወገን ሬሳ እስቲቀበር የእኛ ወታደሮች እንኳ ጠመንጃ እንዳይተኩሱ አድርጌ ጦርነቱን ለማቆም እፈቅዳለሁ እንጂ በምሽጉ አጠገብ ያለው ወታደር ወደ ሠፈር እንዲመለስ አላደርግም በማለት አሳባቸውን ስለ አጠነከሩ የነገሩ ስምምነት በዚሁ ተጨረሰና ሁለቱም ወገኖች የሞቱትን ሰዎች ሁሉ እየወሰዱ አስቀበሩ።

በዚያም ቀን ማታ ኢጣሊያኖች በአጼ ዮሐንስ ጊዜ በሰሐጢ እንዳደረጉት የሸዋን ሠራዊት ለማስደንገጥ አስበው በምሽጉ ውስጥ ሆነው ወደ ሰማይ እየተወረወረ የሚተኮስ የኤሌክትሪክ አርቲፊሴል መብራት ወደ ሰማይ እየወረወሩ ሲያሳዩ አመሹ። ተወርውሮም ሲፈነዳ ልዩ ልዩ ቀለም እየመሰለ ይታይ ነበር። ነገር ግን የትግሬ /የትግራይ/ ሠራዊት በአጼ ዮሐንስ ጊዜ ሰሐጢ ላይ በዓይኑ ስላየው የሸዋና የሌላውም አገር ሠራዊት የሚጐዳ ነገር አለመሆኑ በወሬ ስለሰማው አንድም የደነገጠ ሰው አልነበረም።

ከዚህም በኋላ ልዑል ራስ መኮንን ሙሴ ፌልተር ያቀረበውን የዕርቅ አሳብ ለአጼ ምኒልክ ባስታወቁዋቸው ጊዜ ኢጣሊያኖች በእውነት እርቅ ከፈለጉ እኔም ፈቃዲኤ ነው ብለው ስለ ተናገሩ ይህንኑ በጽሕፈት አድርገው ለፌልተር ሰጡትና ጄኔራል ባራቴሪ ወደ አለበት ወደ አዲግራት በግሥጋሤ ሄደ። በመቀሌ በእንዳ ኢየሱስ ምሽግ ውስጥ ያሉት ኢጣሊያኖች የውሀው ምንጭ ስለ ተያዝባቸው በውሀ ጥም ለማለት መቅረባቸውን አስረድቶ የእርቁን ነገር ወደ ፊት እንጨርሳለን አሁን የመቀሌን ምሽግ ለቃችሁና አስረክባችሁ ውጡ የሚል ወደ ማጆር ጋሊያኖም የተጻፈ ደብዳቤ ይዞ ተመለሰ።

ውሀውንም የሚጠብቁ የአጼ ምኒልክ ዘበኞች በምሽጉ ውስጥ ያሉት ኢጣሊያኖች ምናልባት እንኳ ኃይል አግኝተው ውሀ ለመቅዳት ቢመጡ እንዳያገኙ በለው ምንጩን በአፈርና በድንጋይ እየጠእብቁ ደፍነውት ነበር። ኢጣሊያኖችም በውሃ ጥም ከመጨነቃቸው የተነሣ በቀን ላንድ ሰው የሚሰጡት ውሀ የጠርሙስ እኩሌታ ያውም ድፍርስና መጥፎ ሽታ ያለው ነበር።

ማጆር ጋሊያኖ ግን «ምንም የመቀሌን ምሽግ ለመልቀቅ ብታዘዝ ለዕቃችንና ለመሣሪያችን ለአወጣጣችንም በጽሕፈት የሆነ ውል መቀበል ያስፈልገኛል ብሎ ስለ ተናገረ፣ ሙሴ ፌልተር በጄኔራል ባራቴሪ ፈቃድ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የዕርቅ ውል አቀረበ።

፩ኛ ኢጣሊያኖች ምሽጉን በሙሉ ለቀው አጼ ምኒልክ ለሚያዙት ሰው አስረክበው እንዲወጡ።

፪ኛ አጼ ምኒልክም ዕቃቸውንና መሣሪያቸውን እንዳይወስዱባቸው ወደ አዲግራትም ሲሄዱ ለመኳንንቶቹ /መኮንኖቹ/ መቀመጫ በቅሎዎች ለዕቃቸው መጫኛ አጋሰሶች እንዲሰጡዋቸው።

፫ኛ እስከ አዲግራት የሚሸኙ መኳንንቶች እንዲያዙላቸው ነው።

ይህ ስምምነት ከተደረገ በኋላ በጥር ፲፪ ቀን ወደ ማታ በ፲ ሰዓት በምሽጉ ውስጥ ያሉት የኢጣሊያ ወታደሮች መውጣት ጀመሩ። የጦሩ አለቃ ማጆር ጋሊያኖ ግን ከማታው በ፩ ሰዓት ላይ ወጣ። ወታደሮቹም በውሀ ጥም ከመሞት ስለዳኑ ሙዚቃ እየነፉ የደስታ ድምጣቸውን እያሰሙ ወጥተው ለሠፈርም በተፈቀደላቸው በመቀሌ ሜዳ ሠፍረው ነበር።

ይህም ከሆነ በኋላ ኢጣሊያኖች ምናልባት ወደ አዲግራ ከደረሱና ከጄኔራል ባራቴሪ ከተቀላቀሉ በኋላ የዕርቁን ነገር ያፈርሱ ይሆናል በማለትና በመጠራጠር በእናንተ ወገን አሥር መኳንንቶች ስለመያዣ ሆነው ከእኛ ጋራ ይቆያሉና የቀሩት መኳንንትና ወታደሮች ይዘህ ሂድ ብለው ለማጆር ጋሊያኖ ቢያስታውቁት እነዚህማ ከሩቅ እንደምን አድርጌ እሄዳለሁ። እገሌም ሐኪማችን ነው፤ እገሌም ሠራተኛችን ነው እያለ ልዩ ልዩ ምክንያት ያቀርብ ጀመር።

አጼ ምኒልክ ግን የዕርቁን ነገር እርሳቸው ያፈረሱ እንዳይመስሉ ነበር እንጂ እነዚያን አሥሩን መኳንንቶች ይዤ አስፈራራለሁ ለማለት አሳብ አልነበራቸውምና ራስ መኮንን ተነጋግረው እንዲጨርሱ ፈቃድ ሰጡዋቸው። ራስ መኮንንም እንደ ኢንተርናሲዎናል ደንብ ተነጋግረው ሁሉንም ይዞ እንዲሄድ አደረጉለት። ለማጆር ጋሊያኖም ባለ መደገፊያ ኮርቻ የተጫነች ማለፊያ በቅሎ ሰጡት። ለመኳንንቱም እንደየማዕርጋቸው አንዳንድ በቅሎ ሰጡዋቸው። ለዕቃቸውም ማንሻ ፺፱ ያህል ግመሎች ከእንደርታ ዙሪያ በኪራይ አስፈልገው ሰጡዋቸውና ኢጣሊያኖች ዕቃቸውንም መሣሪያቸውንም እየጫኑ በጥር ፲፰ ቀን ከመቀሌ ተነሥተው ከልዑል ራስ መኮንን የሚሸኙ መኳንንቶችና ወታደሮች ተቀብለው ወደ አዲግራት ተጓዙ። ከመቀሌ በዕዳጋ ሐሙስ አድርጎ ወደ አዲግራት የመንገዱ ርዝመት ፻፳ ኪሎ ሜትር ይሆናል።

ማጆር ጋሊያኖም ወደ አዲግራት በቀረበ ጊዜ ጄኔራል ባራቴሪ ያንድ ሰዓት መንገድ መጥቶ አንገቱን አቅፎ እየሳመ በክብር ተቀበለው።

አጼ ምኒልክም ከመቀሌ ተነሥተው ወደ ፊት እየገፉ ይሔዱ ጀመር። ምክንያቱም ፌልተር የዕርቁን ነገር ከጄኔራል ባራቴሪ ተነጋግሬ እመለሳለሁ ብሎ ከሄደ በኋላ ሳይመለስ ስለ ዘገየ ነው በጥር ፳፩ ቀን ሐውዜን ላይ ሠፍረው ሳሉ ሙሴ ፌልተር መጥቶ

ተገናኘ። ሐውዜን የሐራማት ዋና ከተማ ነው። የተቆረቆረው በደጃዝማች ውቤ ዘመን ነበር።

ሙሴ ፌልተርም የመጣበትን ምክንያት በተጠየቀ ጊዜ ከመቀሌ የወጡት ኢጣሊያኖች ወደ አዲግራት እስቲገቡ ድረስ የዕርቁን ነገር ለመጨረስ አይቻልም ለማለት ነው ብሎ መለሰ።

አጼ ምኒልክም ይህን በሰሙ ጊዜ «በመቀሌ የነበሩትን ኢጣሊያኖች ከነዕቃቸውና ከነመሣሪያቸው መስድዴ የዕርቁን ነገር ፈቃዴ መሆኑን ይመሰክራል አሁንም የዕርቁን ነገር ብትጨርሱ መልካም ነው። ጦርነትም ብትፈልጉ ኃይል የእግዚአብሔር ነውና እንደ አማጣጣችሁ እቀበላችኋላሁ» ብለው ቢመልሱለት፣ «የዕርቁስ ነገር ፈቃድዎ ከሆነ እኔም አዲግራት ተመልሼ ከጄኔራል ባራቴሪ ምላሽ ተቀብዬ እስክመጣ ድረስ ከዚህ ከሠፈሩበት ከሐውዜን ተነሥተው ወደ ፊት እንዳይጓዙ ቃልዎን ይስጡኝ» አላቸው።

አጼ ምኒልክ ግን ሙሴ ፌልተር እንደዚህ ማለቱ ጄኔራል ባራቴሪ ጦርነት የሚያደርግበትን ሥፍራ እስኪመርጥና እስኪያዘጋጅ ቀኑን ለማስረዘም እንጂ ለዕርቅ አለመሆኑን ልባቸው ስለ ተረዳው በሐውዜን ላኩበት የሚበቃ ሣርና ውሀ የለምና ሣርና ውሀ በሚገኝበት ቦታ ሆኜ ብጠብቃችሁ ይሻላል ብለው አሰናብተው ሰደዱት።

ከሐውዜንም ተነሥተው በወርዕ አልፈው በፈረስ ማይ አድርገው ዛታ ከሚባለው አገር ሲደርሱ ማጆር ሳልሣ አንድ የጦር አለቃ ከጄኔራል ባራቴሪ ተልኬአለሁ ብሎ መጣ። ለርሱም በርጅሮንድ ባልቻን ባልደረባ ሰጥተው በዚያው ድንኳን አስተክለው በክብር አስቀመጡት። በማግሥቱም ልዑል ራስ መኮንን ከአጼ ምኒልክ እንደ ታዘዙት ከራስ ቢትወደድ መንገሻና ከአቶ ሀብተ ጊዮርጊስ ጋራ ሆነው ማጆር ሳልሣ ተልኮ የመጣበትን ጉዳይ ቢጠይቁት የዕርቁን ነገር ተነጋግሬ ለመጨረስ ከጄኔራል ባራቴሪ ታዝዤአለሁ። የዕርቁም አሳብ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

፩ኛ እስካሁን ድረስ ወታደራችን የደረሰበትና ሰንድቅ ዓላማችን የተተከለበት እስከ አላጌ ያለው አገር በኢጣሊያ ጥግ ሆኖ ለመኖር እንዲፈቀድልን።

፪ኛ አጼ ምኒልክ በትግሬ /በትግራይ/ መቆየታቸው ቀርቶ በቶሎ ወደ ሸዋ ተመልሰው እንዲሄዱ ውሉም ለ፫ ዓመት እንዲጸና የሚል ነው።

ልዑል ራስ መኮንንም ይህን እጅግ የሚያሳዝን ቃል ሰምተው ከራስ ቢትወደድ መንገሻና ከአቶ ሀብተ ጊዮርጊስ ጋራ ሆነው ለአጼ ምኒልክ ባስታወቁዋቸው ጊዜ «መቼም ቢሆን ኢጣሊያኖች ዕርቅና ሰላም ፈላጊዮች እየመሰሉ እኛን ለማታለልና ቢቻላቸውም አደጋ ለመጣል ነው እንጂ ዕርቅ አለማሰባቸውን ተረድቼዋለሁ። አሁንም እኔ ራሴ ወደ

ዘመቻው የመጣሁት ወሰን አልፋችሁ መጥታችሁ የተከላችሁን ሰደቅ ዓላማ አስነቅዬ ወደ መጣችሁበት እንድትመለሱ ለማድረግ ነው እንጂ ባገሬ በኢትዮጵያ የኢጣሊያ ሰንደቅ ዓላማ እንዲተከልባት ለመፍቀድ አይደለምና እንታረቅ ያላችሁ እንደ ሆነ አዲግራትን ለቃችሁ መረብን ተሻግራችሁ ለነጋዴ መሥፈሪያ ብዬ በሰጠኋችሁ ባሥመራ ተቀመጡ።»

«የውጫሌንም ውል ፲፯ኛውን ክፍል ሰርዙልኝ። ይህን የኔን አንቀበልም ብትሉ ግን ዕርቁ ይቀር እንጂ ሌላ ነገር ለማድረግ አልችልም ብለዋል ብላችሁ ንገሩትና ተመልሶ ይሒድ» አሉዋቸው። ከጦርነቱ በኋላ ግን ወሰኑ ያው መረብ ሆነ። ማጆር ሳልሣም የአጼ ምኒልክን የውል አሳብ በሰማ ጊዜ አሳቡ ባለመፈጸሙ እያዘነ ወደ አዲግራት ተመለሰ።

ጄኔራል ባርቴሪም የአዲግራትንም ምሽግ መገናኛና መሰብሰቢያ አድርጐ የጦርነቱን ሥፍራ ለመምረጥ ወታደሮቹን እያሠለፈ መድፉን መትረየሱን እየጫነ ወደ አንኪጨው ጉዞ ጀመረ።

# ምዕራፍ ፳፫

## <u>ራስ ስብሐትና ደጃች ሐጐስ ተፈሪ ከኢጣሊያኖች እየከዱ ወደ አጼ ምኒልክ ስለ መግባታቸው</u>

ራስ ስብሐት የአጋሜ ባላባት የሰባጋዲስ የልጅ ልጅ ናቸው። ራስ አሉላ ከራስ መንገሻ በተኮራረፉ ጊዜ ራስ ስብሐትም በሤራው ውስጥ አሉበት ተብለው ተጠርጥረው ነበር። ባንድ ወገንም ለኢጣሊያኖች የትግሬንና /የትግራይንና/ የራስ መንገሻን ወሬ ያቀብላሉ እየተባሉ ይታሙ ነበርና በዚህ ሁሉ ምክንያት ራስ መንገሻ ከነልጆቻቸው አሥረው በአምባ ሰላማ አስቀምጠዋቸው ነበር። ነገር ግን በኮዓቲት ጦርነት ጊዜ ኢጣሊያኖች ፈትተው እንዳይወስዱዋቸው ካምባ ሰላማ ወደ አላጌ ሄደው እንዲታሰሩ አደረጉ።

ከዚህም በኋላ ጄኔራል አሪሞንዲና ማጆር ቶዞሊ ራስ መንገሻን እያባረሩ አላጌ በደረሱ ጊዜ ስብሐትን ከነልጆቻቸው ፈትተው ከአላጌ አወረዱዋቸው። ወዲያውም ወደ ጄኔራል ባራቴሪ ሄደው በተገናኙ ጊዜ የእንደርታን ግዛት ሾሜሃለሁ ብሎ ደስ አሰኛቸው። ፊትም በኮዓቲት ጦርነት አጋሜን ለደጃች ሐጐስ ተፈሪ ሰጥቶት ነበር። ይህም መደረጉ የትግሬ መኳንንት እንደነ ራስ ስብሐት እንሾምሃለን እያሉ ከራስ መንገሻ እየከዱ

እንዲገቡለት ለማድረግ ይሆናል እንጂ እንደርታ የራስ ስብሐት አጋሜ የደጃች ሐጐስ ግዛት ሆኖ እንዲቀር አልነበረም።

ልዑል ራስ መኮንንም ከቀሩት ራሶች ጋር በግሥጋሤ ወደ አላጌ መምጣታቸው በተሰማ ጊዜ ጄኔራል ባራቴሪ ራስ ስብሐትን የፋኖ ወታደር ሁሉ አለቃ አድርጐ ወደ አላጌ ሰዷቸው ነበርና ከማጆር ቶዞሊ ጋራ ሆነው በአላጌ ሲዋጉ ውለው ድል ሆነው ቶዞሊ ሲሞት እርሳቸው ሸሽተው አመለጡ። እነዚህም ሆነው ከኢጣሊያኖች ጋራ ቆይተው ሳሉ ከመቀሌ ጦርነት ጀምሮ በአጼ ምኒልክና በኢጣሊያኖች መካከል የታሰበው ጦርነት ቀርቶ ሰላምና ዕርቅ ሊሆን ነው እየተባለ ሲወራ ነበርና አሁን የዕርቁን ነገር ቀርቶ ሁለቱም ወገኖች ለጦርነት መሰናዳታቸው ቁርጡ በታወቀ ጊዜ ራስ ስብሐትና ደጃች ሐጐስ ባንድነት ተማክረው «እኛ ወደ ኢጣሊያኖች መግባታችን ራስ መንገሻ ቢያስቀይሙን እርሳቸውን ብቻ የጐዳን መስሎን ነበር እንጂ ያገራችንን የኢትዮጵያን ነፃነት የሚያጠፋ የንጉሣችንን ክብር የሚያዋርድ ጠላትማ ሲመጣ ከጠላት ጋራ ሆነን እንደምን ንጉሣችንን እንወጋለን? እናታችንን ኢትዮጵያንስ እንደምን እንከዳለን? እንደዚህማ ብናደርግ እግዚአብሔርስ በነፍስና በሥጋችን ይፈርድብን የለምን? ተባብለው ከኢጣሊያኖች የተቀበሉትን የጦር መሣሪያ እንደ ያዙ የአካለ ጉዛይን ሰዎች አስከድተው ወደ ማታ በ፲ ሰዓት ከሠፈር ተነሥተው እምቢልታ እያስነፉ በልግፕ ይጓዙ ጀመር። የኢጣሊያም የጦር አለቆችና ወታደሮች ለመናፈስ ለሽርሽር የሚሄዱ እንጂ በግልጥ እምብኒልታ እያስነፉ ከድተው ይሄዳሉ ብለው አልጠረጠሩዋቸውም ነበርና የአጀቡን ማማረና የሚሄዱበትን መንገድ በመነጽር እያዩ ዝም አሉዋቸው። ወዲያውም ቀኑ እየመሸና ሰዓቱ እየጨለመ ሲሄድ ያለ ሥጋት ይጓዝ ጀመር።

ሌሊቱንም ሲጓዙ አድረው ጠዋት ሲነጋ አሌቋ ባለው በኢጣሊያ ሠራዊት ላይ አደጋ ጥለው አንድ ሰው እንኳ ሳያመልጥ ሁሉንም ገደሉዋቸው።

ይህም ወሬ በተሰማ ጊዜ ማጆር ባሊ የሚባለው ከንኪጨው ሄዶ እንዲረዳ ታዘዘና በግሥጋሤ ቢሄድ በአሌቋ ያሉት ኢጣሊያኖችና ባሽባዙቆች አልቀው እነራስ ስብሐትም አምልጠው ከሄዱ በኋላ ስለደረሰ በጣም አዘነ።

ነገር ግን እንደ አጋጣሚ ከነገር ያልገቡ ከጦርነቱም ያልነበሩ ሐያ ሰባት የሚሆኑ ባላገሮች በዚያው ዙሪያ ስለ ተገኙ እነዚያን አስይዞ የፊጥኝ እያሠረ በሆዳቸው እያስተኛ በጠመንጃ ሳንጃ ጀርባ ጀርባቸውን እያስወጋ አስገድሎ ቁጭቱን ተወጣአብቸው። ከዚህም በኋላ የሞቱትን ሰዎች ሬሳ አስቀብሮ ሲጨርስ ወደ አንኪጨው ተመለሰ።

እነራስ ስብሐት ግን ከአሌቋ አልፈው ሳግሬን የሚባል ሥፍራ ላይ ያሉትን ኢጣሊያኖች ፈጅተው ወደ ደብረ ተኅሦ ሲደርሱ ኮሎኔል ክርስቶፎር ከሚባለው ጋራ ጦርነት ቢገጥሙ ድል አድርገው መለሳቸው።

ከዚህም በኋላ ወደ አጼ ምኒልክ ተላልከው እንዲመጡ ከተፈቀደላቸው በኋላ መጥተው ተገናኝተው ከኢጣሊያኖች ጋራ ሆነው በሠሩት ባለፈው ሥራቸው መጸጸታቸውን እየገለጡ ተናግረው የጦርነቱንም አኳኋን ተናግረው ሲጨርሱ የማዕርግ ልብስና መሣሪያ ተሸልመው ወደ አጋሜ ተመልሰው ሄዱ።

አጋሜም የኖሩበትና መውጫ መግቢያውን ያውቁት አገራቸው ስለ ሆነ ካንዱ ወዳንዱ እየተዘዋወሩ ከአዲግራት ወደ አንኪጨው በሚመላለሰው ጓዝ ላይ አደጋ ጥለው ብዙ ሰዎች ፈጅተው ስንቅ የተጫኑ ፺፱ ያህል ግመሎችና አጋሰሶች ቢያገኙ ሁሉንም በጐራዴ ቋንጃቸውን እየመቱ ጣሉዋቸው።

የተጫነውንም ዕቃ ሁሉ ባላገር እየተዛረፈ ወሰደው። ከዚህም በኋላ በአጋሜ ጀርባ ዞረው ከአሥመራ ከምጥዋ ጋራ የሚያገናኘውን ስልክ ሁሉ እየቆራረጡና እየበጣጠሱ ጨረሱት።

ኢጣሊያኖች ይህን የመሰለ ትልቅ ጉዳት ስለ አገኛቸው እነራስ ስብሐትን እየፈለጉ ለመያዝ ምንም እንኳ በብዙ ቢጥሩ ሳይሆንላቸው ቀረ።

አጼ ምኒልክም ከየሃ ተነሥተው ገንደብታ ላይ ሠፍረው ሳሉ ኢጣሊያኖች ከእንጨው ምሽጋቸው መጥተው አደጋ ይጥላሉ እየተባለ ይወራ ነበርና ስመ ጥሩ ዐርበኛ አሽከራቸውን ቀኛዝማች ታፈሰን «ወደ አንድ ተራራ ዘልቀህ የኢጣሊያኖችን ሠፈር በመነጽር ዓይተህ ተመለስ» ብለው ልከውት ነበርና እርሱ ወደ ረጅም ተራራ ወጦ ሲመለከት ብዙ የኢጣሊያ ወታደሮች ከምሽጋቸው ወጥተው እርሱ ወደቆመበት ተራራ እግር ሲመጡ ቢያይ ከእርሱ ጋር መቶ ያህል ወታደሮች ነበሩና እነዚያኑ ይዞ ወርዶ መታኮስ ሲጀምር እየሸሹ ወደ ምሽጋቸው ተመለሱ።

ቀኛዝማች ታፈሰም ተመልሶ መጥቶ ያየውንና የሠራውን ሁሉ ቢነግራቸው መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው የኢጣሊያኖች አሳብ በጉድባና በምሽግ እየሆኑ እኛን ብዙ ቀን ለማስቸገር ነው እንጂ በሜዳ ወጥተው ጦርነት ለማድረግ አይመስለኝምና ወደ ሐማሴን አቅንተን ብንሔድ ይሻላል በማለት ምክንያታቸውን ቆረጡና ከገንደብታ ተጉዘው አሣይ በሚባለው ከአባ ገሪማ ጉልት አልፈው በየካቲ ፲፬ ቀን አድዋ ከተማ ገቡ። በዚያም ተሠልፈው ቢጠብቋቸው ኢጣሊያኖቹ ከምሽጋቸው ሳይንቀሳቀሱ ቀሩ። በማግሥቱም ልዑል ራስ መኮንንና ራስ መንገሻ ዮሐንስ ራስ ቢትወደድ መንገሻ

ፊታውራሪ ተክሌ፣ ፊታውራሪ ገበየሁ፣ ሊቀ መኳስ አድነው፣ ወደፊት እስከ መረብ ብቅ ብለው እንዲጠብቁ ታዘው ነበርና መንገድ ከጀመሩ በኋላ ወንዞች ሁሉ በመድረቃቸው ምክንያት ውሀ ስለ ተቸገሩ ግድ ሆነባቸውና ተመለሱ።

በየካቲት ፲፯ ቀን የኢጣሊያ ወታደሮች እየተሰለፉ ከምሽጋቸው መውጣት ጀምረዋል ተባለና ደጃች በሻህ አቦዬና ደጃች ወልዴ ወዲያው ተጠግተው ዘብ ሲጠብቁ እንዲያድሩ ታዘዙና ሄዱ። በማግሥቱም አጼ ምኒልክ የፊቱን በፊት የኋላአውን በኋላ፣ የቀኙን በቀኝ፣ የግራውን በግራ አሠልፈው እሳቸው በመካከል ሆነው ቢወጡ ኢጣሊያኖችም ተመልሰው ወደ ምሽጋቸው ገብተዋል ተባለና በዚህ ነገር እጅግ ተናደዱ። መኳንንቱ ግን ዛሬ በዚህ አድረን ነገ ጥዋት ወደ ሽምጉ በኃይል ገብተን እንዋጋለን በማለት ምክር ከጨረሱ በኋላ የትግሬው /የትግራዩ/ ገዥ ራስ መንገሻ ይህን ቢሰሙ «ጃንሆይ ጉዳብ ጉድቦና ምሽግ መሽጎ በተቀመጠ ጠላት ላይ በኃይል ከገባን ሠራዊታችንን ከማስጨረስ በቀር ምንም ጥቅም አናገኝም ይህ ነገር እንዳይደረግ ጃንሆይን አስምላለሁ» እያሉ ስለ ተናገሩ መልካም ምክር ነው ተባለና ወደ ሠፈር ተመለሱ።

ከዚያም ቀድሞ የመሐመድ አንፋሪን መከዳት የራስ ወልደ ጊዮርጊስን የደጃች ተሰማንና የአዛዥ ወልደ ጻድቅን ወደ አውሳ /አፋር/ መዝመት በቀደምት ገጽ ፈን ነበረና እዚያ ከመሐመድ አንፋሪ ጋር ተዋግተው ብዙ ሺህ ሰዎች ገድለው ድል አድርገው ኖሮ የምሥራቹን የያዙ መልእክተኞች በየካቲት ፳፪ ቀን አድዋ ገብተው ለአጼ ምኒልክ ስለ ተናገሩ በሠፈሩ ሁሉ ትልቅ ደስታ ሆነ። ወዲያው ገዱ ያማረ ነውና እኛም ይቀናናል እየተባለ በየሰው አፍ እንደ ትንቢት ሲነገር አመሸ።

# ምዕራፍ ፷፱

## <u>ስለ አድዋ ጦርነት</u>

አጼ ምኒልክ ከመቀሌ ጀምሮ የተጀመረው የዕርቁ ንግግር የሚፈጸመው ነገሩ ሁሉ በወዳጅነት ተጨርሶ ወደ ሸዋ የሚመለሱ መስሎዋቸው ነበር። ጄኔራል ባራቴሪ ግን ለነገሩ ወዝ እየሰጠ የተመቸ ቀንና ሥፍራ ፈልጐ አደጋ ለመጣል ነበር እንጂ፣ የእርቁ ነገር እንዲፈጸም አለማሰቡን ስለ ተረዱት ወደ ፊት እየገፉ ይሄዱ ጀመር። ቢሆንም ለዘመቻው ከተነሡ ፭ኛ ወር ያህል በመሆኑ ለሠራዊታቸው የሚበቃ ስንቅ አልተገኘም ነበር። አድዋም ከገቡ በኋላ ጦርነቱ በመኻሉ የሚጀመር ስለ መሰላቸው ሁለት ቀን ያህል እየተሠለፉ ቢወጡ ኢጣሊያኖች ከምሽጋቸው የማይወጡ ሆኑ። በአዲግራትና በአንኪጨው ወደ ተሠራው ምሽግና ጉድባ ገብተው እንዳይዋጉ በጣም ጠንካራ መሆኑን

ሰምተው ነበር። ስለዚህ ከአጼ ምኒልክ ሠራዊት ከሶቱ አንዱ ስንቅ ለመፈለግ ወደ ሽሬ ወደ ተንቤን እስከ ጠለምት ድረስ ተበታተነ። አንዳንዱም የአክሱም ፅዮንን ቤተ ክርስቲያን እንሳለማለን እያለ ወደ አክሱም ሄዶ ነበር።

ይህ እንኳን መደረጉ የጦር አለቆቹ ሳይጠነቀቁ በመቅረታቸው ነው እንጂ በጦርነት ጊዜ አንድ ልብ ሆኖ በየታዘዘበት ስፍራ ጸንቶ ጠላትን መጠባበቅ ነበር እንጂ ቤተ ክርስቲያን እሳለማለሁ ገዳምና ደብር አያለሁ ብሎ ያለ ፈቃድ ከሠፈር መሄድ የማይገባ መሆኑ በጦርንት ሕግ የታወቀ ነው።

ቢሆንም የእግዚአብሔር ፈቃድና ረድኤት ሲጨመርበት የከበደው ሁሉ ይቀላልና ኢጣሊያኖች በእንኪጨው ሠፍረው ሳሉ ገብረ እግዚአብሔርና አውአሎም የሚባሉ ሰላዮች አበጅተው ነበርና እነዚያ ወደ አድዋ እየመጡ በአጼ ምኒልክ ሠፈር ያዩትንና የሰሙትን ሁሉ እየወሰዱ ለጄኔራል ባራቲሪ ይነግሩ ነበር። ስለሆነም በትውልዱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሰው ሁሉ ላገሩ ነፃነት ለንጉሡ ክብር ተቆርቋሪ ነውና ምንም ከኢጣሊያኖች ገንዝብ ቢቀበሉም በልባቸው እናታቸውን ኢትዮጵያን ንጉሣቸውን አጼ ምኒልክን አልከዱም ነበርና ከኢጣሊያኖችም ያዩትንና የሰሙትን እያመጡ ለአጼ ምኒልክ መንገር ጀምረው ነበር።

እነዚህም ሁለት ሰላዮች ወደ ጄኔራል ባራቴሪ ሄደው የአጼ ምኒልክ ሠራዊት ስንቅ ስላለቀበት በሽሬ በተምቤን በጠለምት በአክሱም ተበትኖ ከአጼ ምኒልክ ጋር ያለው ሠራዊት እጅግ ጥቂት ነውና ዛሬ ወይም ነገ ጦርነት ብትገጥሙ ባንድ አፍታ ድል ታደርጋላችሁ!» ብለው ነግረው ባንድ ወገን ደግሞ ወደ አጼ ምኒልክ ልከው «ለጄኔራል ባራቴሪ ረዳቱ ወይም ጠቅላይ የጦር አለቃው መሆኑ ያልታወቀ ጄኔራል ባልዲሠራ የሚባል ከብዙ ሠራዊት ጋራ ከኢጣሊያ አገር መጥቶ ምጥዋ ገብቱዋል እየተባለ ይወራልና ዛሬ ወይም ነገ ጦርነት ካልገጠሙ ነገሩ ሁሉ የሚያስፈራ መሆኑን ይወቁት። ለጄኔራል ባራቴሪ የአጼ ምኒልክ ሠራዊታቸው ሁሉ ስንቅ ለመፈለግ ተበትኖ ብቻቸውን ናቸውና ዛሬ ወይም ነገ ጦርነት ብትጀምር ይሻላል ብለን ነግረነዋልና እንዲጠነቀቁበት ይሁን» ብለው ልከው ነበር።

ጄኔራል ባራቴሪም በየካቲት ፳፪ ቀን ፲፰፻፹፰ ዓመተ ምሕረት ማታ በ፲፪ ሰዓት ሠራዊቱን አሠልፎ ከእንኪጨው ተነሥቶ ሌሊቱን ሲጓዝ አድሮ ፲ ሰዓት እንዳአባ ገሪማ ደረሰና ጄኔራሎቹን በደንብና በሥርዓት አሰልፎ ጦርነት እንዲጀመር አደረገ።

የኢጣሊያኖች አሰላለፍ እንደሚከተለው ነበር። ጦርነት እንዲደረግበት የተቆረጠው አምባ በሰማያታ ተራራና በሰሎዳ ተራራ መካከል ያለው ተዳፋት ቦታ ነበር።

በስተግራ ጄኔራል አልቤርቶኒ የሚያዛቸው መድፈኞችና ወታደሮች ተሠልፈው ነበር።

በስተቀኝ ጄኔራል ዳቦርሚዳ የሚያዝዛቸው መድፈኞችና ወታደሮች ተሠልፈው ነበር።

በመካከል ጄኔራል አሪሞንዲ የሚያዝዛቸው መድፈኞችና ወታደሮች ተሠልፈው ነበር።

በደጀን ጄኔራል ኤሌና የሚያዝዛቸው መድፈኞችና ወታደሮች ተሠልፈው ነበር።

ከነዚህም በቀር በየተራራው ላይ እየሆኑ የጦርነቱን አኳኋን እያዩ ለእገሌ ረዳት ጦር ይሂድለት፣ እገሌ፣ ወደ ፊት ይግፋ እገሌ ወደ ኋላ ያፈግፍግ እያሉ ትዕዛዝ የሚሰጡ የጦር አለቆች ነበሩ። ትዕዛዝም የሚያቀባብሉ ፈረሰኞች በየሥፍራቸው እየቆሙ ይጠባበቁ ነበር። የጦር አለቆችም ሲቆስሉ በቶሎ እየወሰዱ የሚያክሙ ሐኪሞች የተለየ ሥፍራ ተደርጐላቸው ነበር።



እቴጌ ጣይቱ ብጡል

ይህም ሁሉ ከተሰናዳ በኋላ ጄኔራል አልቢርቶኒ በተሠለፈበት የራስ መንገሻ ዮሐንስ ዘበኞች ባሉበት በኩል ከሌሊቱ በ፲፩ ሰዓት ተኩስ ተጀመረና ሲዋጉ ሁለት ባሽ ባዙቆች ስለተማረኩ ወሬ ቢጠይቋቸው ጄኔራል ባራቴሪ ከእንኪጨው ያሉትን ጄኔራሎችና የጦር ሠራዊቱን በሙሉ ይዞ መጥተዋል ብለው ተናገሩ።

አጼ ምኒልክም ትልቁን ዐርበኛ አሽከራቸውን ቀኛዝማች ታፈሰን አዝዘው ከማታው ጀምሮ በሠፈሩ ዙሪያ እየሄደ የዘበኞቹን ትጋት የጠላቶቹንም ወሬ ሲጠይቅ አድሮ ነበር። በራስ መንገሻ ሠፈር በኩል ተኩስ መጀመሩን ሰምቶ ወዲያው በፍጥነት መጥቶ ለአጼ ምኒልክ አስታወቀ።

አጼ ምኒልክም በጅሮንድ ከተማ ንና የፈረስ ዘበኛውን አለቃ በፍጥነት ሄዳችሁ ራስ መንገሻን እርዱ ብለው ላኩና ወዲያው ታጠቅ! እያሉ በየሠፈሩ አስለፈፉ።

፲፪ ሰዓትም በሆነ ጊዜ የጦርነት ልብሳቸውን ለብሰው ከድንኳን ብቅ ባሉ ጊዜ በቀኝና በግራ በፊትና በኋላ ያለው ሠራዊታቸው ባንድ አፍታ የጦርነት ልብሱን እየለበሰ ከቀፎ እንደ ወጣ መስሎ እየተፋዋከረ ጦርነት ወደ ተጀመረበት ሥፍራ ይሮጥ ጀመር።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ወታደሩ ባላገሩና ነጋዴውም ካህናቱ ሳይቀሩ ስለ አገራቸው ነፃነት ስለ ንጉሣቸው ክብር ሲሉ ሞታቸውን የማያፈሩ ጀግኖችና ቆራጦች ናቸውና የመድፉን የጠመጃናውን ተኩስ ሳይፈሩ በሠልፉ ውስጥ ገቡበት።

የፊተኛው ሲወድቅ የኋለኛው ወደፊት ከመገሥገሥ በቀር የወደቀውን ላንሣ ደከሞኛልና ልረፍ አይልም ነበር።

እቴጌ ጣይቱም በክፍላቸው ፪ሺ ወታደር ነበራቸውና ምንም ሴት ብሆን በዛሬ ቀን በድንኳን ውስጥ ተቀምጩ አልውልም ብለው በሠልፉ መካከል ሁነው «አይዞህ በርታ!» እያሉ ይሰዱት ነበር።

ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስም ከየደብሩ አለቆችና ከድንባሮ ማርያም ካህናት ጋር ባንድ አፍታ ሥፍራ ቆመው ወደ ጦርነቱ የሚገባውን ወታደር «እግዚአብሔር ይፍታህ!» እያሉ ያናዝዙ ነበር።

የጦርነቱ አኳኋን አለቃውም ጭፍራውም ፍየል እንድ አየ ነብር በየፊቱ ከመሮጥና ከመግደል በቀር ባንድነት ቆሞ ለመዋጋት አያስብም ነበር። እንኳን የጭፍራ አለቆች ደጃዝማችና ራሶቹም ቢሆኑ በፈረስ እየሆኑ አንደኛውን እየጋለቡ ይገድሉ ነበር። በጠመንጃ መግደልንም ከጉብዝና ስላልቆጠሩት በጐራዴ ለመግደል ይሽቀዳደሙ ነበር። ይልቁንም ተራ ወታደር ከመደል ይልቅ የጦር አለቆችን መግደል ጀግንነት ነው እያሉ

ተራውን ወታደር እያለፉ በቆቡና በልብሱ የወርቅ ምልክት ያለበትን የጦር አለቃ ይፈልጉ ነበር።


## በአድዋ ጦርነት የኢጣሊያንን ሠራዊት የመሩት አዛዦች



የተማረከው ጄኔራል ማቴዎስ አልቤርቶኒ



በዓድዋ ጦርነት የኢጣልያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ጄኔራል ባራቲዬሪ




በዓድዋ ጦርነት ላይ የሞተው ጄኔራል ዳቦርሚዳ



በዓድዋ የሞተው ጄነራል አሪሞንዲ

# በአድዋ ጦርነት የኢትዮጵያ ሠራዊት አዛዦች ዋና ዋናወቹ



ራስ መንገሻ ዮሐንስ



ራስ (በኋላ ንጉሥ) ሚካኤል አሊ



ሊቀመኳስ (በኋላ ራስ) አባተ ቧ ያለው



ራስ ወሌ ብጡል



በጅሮንድ (በኋላ ደጃዝማች) ባልቻ ሳፎ



በአድዋ ጦርነት የሞቱት ተዋጊዎች አፅም

ይህንንም በመሰለ በጀግንነት አኳኋን ፮ ሰዓት ያህል እንደ ተዋጉ የኢጣሊያ ጦር ድል መሆንና መሸሽ ጀመረ። የአጼ ምኒልክም ሠራዊት እየተከታተለና እየቀደመው የተራራውን ጫፍ ያዘ። ጄኔራል ባራቴሪና ጄኔራል አሪሞንዲ ሌሎችም የጦር አለቆች ሽጉጥ እያጐረሱ ጐራዴ እየመዘዙ የኢጣሊያን ሠራዊት አትሸሽ! እያሉ ለማስፈራራት ቢሞክሩም እምቢ ብሎ እየጣሳቸው ሸሸ።

እቴጌ ጣይቱ በማናቸውም ቢሆን ለእርዳታ ይፋጠኑ ነበርና ባንድ ሥፍራ ትልቅ ከጅባር ድንኳን አሰካክለውና ተቀምጠው ከእርሳቸው ጋራ ያሉትን ዘበኛቸውንና ገረዶቻቸውን ሁሉ ወይዛዝሩ ሳይቀሩ በገንቦ በእርኮት ይህንንም በመሰለው ሁሉ ውሀ እያስቀዱ ቁስለኛውን ሁሉ እያስነሡና እያስመጡ ውሀ ያጠጡት ነበር። በዚህም በርኅራኄ ሥራቸው የኢጣሊያ ቁስለኞችን እንኳ እያነሡ ውሀ ያጠጡዋቸው ነበርና ትልቅ ምሥጋና አገኙ። ፱ ሰዓትም በሆነ ጊዜ የአጼ ምኒልክ ጀግኖች ቁስለኛቸውንና ከኢጣሊያ የማረኩዋቸውን ምርኮኞቻቸውን እየያዙ ወደ ሠፈር መመለስ ጀምረው ነበርና እቴጌ ጣይቱ ይህነን አይተው ከእኔ ድንኳን እያሳረፍህ ተመለስ፣ ምርኮኛህንም እኔ ዘበኛ አስጠብቅልሃለሁ እያሉ ያሰለፍፉ ነበር።

በስተግራም በኩል ያሉት የኢጣሊያ ወታደሮች በርትተው ሲታኮሱ ነበርና አጼ ምኒልክም በዚያ በኩል ያለው የኢጣሊያ ወታደር ድል እስቲሆን አልመለስም ብለው በ፲፪ ሰዓት ለጊዜው ተኩሱ ተግ ማለቱን አይተው ከማታው በ፩ ሰዓት ወደ ሠፈር ተመለሱ። ቢሆንም ከሌሊቱ እስከ ፫ ሰዓት ተኩሱ አላቆመም ነበር። ሠራዊቱም ከወገኑ የቆሰለውን በከብት፥ የሞተውንም በቃሬዛ እየያዘ ወደ ሠፈር ሲገባ አደረ።

ነገር ግን ምንም ድሉ የኢትዮጵያና የአጼ ምኒልክ ቢሆንም ከሚወዱዋቸው መኳንንቶቻቸውና አሽከሮቻቸው ብዙ ስለ ሞቱባቸው በሠፈራቸው ትልቅ ኀዘን ተደርጎ ነበር። የሞቱትም መኳንንቶች ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

ደጃዝማች በሻህ አቦዬ

ደጃዝማች ጫጫ /የጐላው ሻለቃ/

ፊታውራሪ ገበየሁ /የጦር ፊታውራሪ/

ስለዚህ የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፍ ደራሲ ስለ ብላቴ ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ከዓለም ዙሪያ ልዩ ልዩ ሰዎች የሰጡት አስተያየት ከዚህ ቀጥሎ በተጨማሪነት የመጽሐፉ አካል ሆኖ ቀርቧል። ይህም ከየሰዎች የተሰጠው አስተያየት በሁለት ክፍል ሆኖ ይታያል።

1ኛው/ በክቡር ቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት ተዘጋጅቶ የቀረበውና የታላቁን ኢትዮጵያዊ ደራሲ የድርሰት ልዩ ችሎታ የሚያሳይ ሲሆን የተለያዩ ሰዎችም ስለ ደራሲው የሰጡትን ምስክርነት የሚያመለክት ጭምር ነው።

2ኛው/ ብላቴ ጌታ ኅሩይ ከኢጣሊያ የኢትዮጵያ ወረራ አስቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በነበሩበትና ለመጀመሪያ ጊዜ ጃፓንን በጐበኙበት ወቅት የተደረገላቸው አቀባበልና መስተንግዶ የሚገልጽ ጥናታዊ ጽሑፍ ነው። ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ለአይ.ኤስ.ደቡብ (ለኢንተርናሽናል እስተዲስ ደቡብ) መድረክ ክላርክ ጄ. ካልቪት 3ኛ በተባሉ ምሁር የቀረበ ሲሆን ኢትዮጵያ ለዘመናዊ የሥልጣኔ እርምጃዋ የጃፓንን ዓይነት የልማትና የእድገት ጐዳና እንድትከተል ያቀዱት ብላቴን ጌታ ኅሩይ መሆናቸውን ለማሳየት የቀረበ ጥናት ነው።

እነዚህ ሁለት ጽሑፎች የመጽሐፉ አካል ሆነው ታትመው በመቅረታቸው አንባቢያን ጽሑፎችን ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር ምንስ ያያይዛቸዋል? ምንም ግንኙነት የላቸውም። ነገር ግን ይህን የኢትዮጵያ ታሪክ የደረሱት ብላቴን ጌታ ኅሩይ በውጭ ተመልካቾችና ጥናተኞች ዘንድ ምን ዓይነት ሰው ሆነው ይታዩ እንደ ነበር ለማሳየት የተደረገ ሙከራ ነው እንጂ።

የመጽሐፉ ዝግጅት ክፍል።



ከክቡር ቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት የቀረበ

ስለ ቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት

ክቡር ቢየትወደድ ገብረ ሕይወት ከልጅነት አንስተው እስከ ሕይወት ፍጻሜያቸው ድረስ ለኢትዮያ ሀገራቸው ካበረከቱት ቅን አገልግሎት መካከል በጣም ጐልተው የታወቁባቸው በተለያዩ አገሮችና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ /አምባሳደር/ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ፣ የአገር ግዛት ሚኒስትር የሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሆነው ማገልገላቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው። የክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴን የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፍ ለማሳተም እቅድ መኖሩን ሰምተው ይህን ስለ ብላቴ ጌታ ኅሩይ ልዩ ልዩ ሰዎች አስተያየት አጭር ማስታወሻ አዘጋጅተው የመጽሐፉ አካል እንዲሆን በማለት ለአሳታሚዎ ሰጡ። ከዚያም ምንም ያህል ጊዜ ሳይቆዩ የካቲት ፺ ቀን በ፲፱፻፺፩ ዓመተ ምሕረት ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

## <u>ከ፪ኛው የኢጣሊያ ወረራ በፊትና በወረራውም ጊዜ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስለ ነበሩት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ልዩ ልዩ ሰዎች የሰጡት አስተያየት።</u>

## ቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት እንዳቀረቡት

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በሃያኛው መቶ ዓመተ ምሕረት መጀመሪያ ላይ በየጥሪአቸው ለአገር አገልግሎት በማበርከት ላይ ይገኙ ከነበሩት የኢትዮጵያ ሊቃውንት አንዱ ናቸው። ከዚህም በላይ ብላቴን ጌታ ኅሩይን ሌሎች የሞያ ጓደኞች ለይቶ የሚያሳያቸው የውጭውን ዓለም ሊቃውንት የአስተሳሰብ መንገድ የማወቅ ፍላጎታቸው ነው። በዚሁ ፍላጎታቸው በመነሳሳት በሚያስደንቅ ትጋት በጥቂት ጊዜ ውስጥ የፈረንሳይና የእንግሊዝ ቋንቋዎችን አጥንተው የቋንቋዎቹ ባለቤት ከሆኑ በኋላ መጻሕፍትን በማንበብ፣ በውጭ ተልዕኮ በተመዛዘነ አስተሳሰብ የተሰናዳ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ደራሲ ለመሆን የበቁ ስማቸው እንደሚያመለክተው ከምርጦች መካከል «ምርጥ» ኢትዮጵያዊ ሊቅ ናቸው። እኒህን ስመጥር ደራሲ ሥራዎች ለኅትመት የበቁት ቁጥራቸው ከሃያ በላይ ይሆናል። ከነዚሁ የመጀመሪያዎቹ መጻሕፍት ያለፉትን ነገሥታት

ሥራዎች ቁጥራቸው መልካቸው በማቅረብ የተወሰኑ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ለሕዝቡ የአዲስ ዘመን ንጋት በማብሰር በማንቃትና በማሰናዳት ላይ ያተኮሩ ነበሩ። ይህንንም በቴአትር መልኩ በማቅረብ የትግሉን ዓይነትና ታጋዮቹን እንዲሁም ቦታውንም ለማሳየት መሞከሩ «ወዳጄ ልቤን» እና የ «ጽዮን ሞገሳን ጋብቻ» ሌሎችንም በምሳሌነት መጥቀስ ይበቃል።

እዚህ ላይ ሊታወቅ የሚገባ ሌላ አንድ እውነት አለ። ከባለታሪኩ ብሩኅ መስተኃልይ የፈለቁት በደራሲነት ሞያቸው ያበረከቱዋቸው ነዋሪ ሥራዎቻቸው ሁሉ የተከናወኑት በትርፍ ጊዜያቸው መሆኑ ነው።

እኒህን በምር አሳቢና ብልህ ሰው በየጊዜው ለከፍተኛ የኃላፊነት ቦታና ምርጥ ለሆነ የማዕርግ ስም ባለቤት ለመሆኑ ያበቃቸው ትጋታቸውንና ሥራቸውን የሚያቀርቡበትን ጊዜና ቦታ ለይቶ የማወቅ ችሎታቸው መሆኑን ማየት ይቻላል። ከሁሉም በላይ ሰውን የሚወዱ፥ የጊዜን ዋጋና የሥራን ክቡርነት የሚያውቁ በምሳሌነታቸውም ላላወቁ የሚያሳውቁ የኢትዮጵያ ውድ ልጅ ናቸው።

ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በ፲፱፻፴፫ ዓመተ ምሕረት በድል አድራጊነት ከስደት ተመልሰው ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴን አጽም ከነበረበት ከለንደን አስመጥተው በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል መካነ መቃብር በክብር እንዲያርፍ ስላደርጉ ቃላቸውን ፈጽመዋል። ይህ ታሪክ በታሪክነቱ ከአንድ ቤተሰብ አልፎ በጠቅላላው ኢትዮጵያዊ ኅብረተሰብ ከተከታታዩ ለትውልድ መተላለፍ ያለበት መሆኑን በዚህ ወቅት እንደ ገና ማሳሰቡ ተገቢና የኢትዮጵያዊነት ግዴታ ነው እንላለን።

## <u>የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴን በሚያውቋቸው የውጭ አገር ሰዎች የቀረበ አስተያየት</u>

1. በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ ከአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች መካከል የቅርብ ተመልካች የነበሩ የውጭ አገር ሰዎች የሰጡትን ምስክርነት ተከትሎ ጐርዶን ማክላን የተባለ ፀሐፊ «የመጨረሻዋ አፍሪካ» በሚል ርዕስ ባቀረበው ውዳሴ እንደ ዘገበው ብላቴን ጌታ ኅሩይ በሥራቸው አፈጻጸም የውጭ አገር ሰዎችን በጨዋነትና በትህትና በመቀበል ጉዳያቸውን ይፈጽሙላቸው እንደ ነበር በሰፊው አሳይቶ በበኩሉ አድናቆቱን በምስጋና ገልጿል።
2. ቻርስል ሬይ የሚባል ጸሐፊ በበኩሉ «ያልተሸነፈች የአበሻ አገር» በሚል ድርሰቱ የባላቴን ጌታ ኅሩይን ድርሻ፣ ተግባር አፈጻጸምና የደራሲነት ችሎታ በአድናቆት አስታውሶ፣ የውጭ አገር ሰዎች ቆንሲላቸው ሳይኖር በማይዳኙበት በዚያ ጊዜ በልዩ ፍርድ ቤት በዳኝነት ሥራ ስለአበረከቱት ድርሻ አድናቆቱን ሲገልጽ በሰፊው ሊታወቅ ይገባል ብሏል።

3. የታወቁት የሰብአዊ መብትና የፍትሕ ጠበቃ፣ የኢትዮጵያ የክፉ ቀን ወዳጅና የሁልጊዜ ረዳት ሚስስ ሲልቪያ ፓንኸርስት ባቀረቡት ውዳሴ ስለ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የደራሲነት አስተዋጽኦ ብዙ የሚሉት ነገር አላቸው። በተለይም ያደነቁት ከ፲፱፻፲፪ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ የደረሷቸው መጻሕፍት የኢትዮጵያን ትምህርት ቤቶች ፍላጎት ያሟሉ መሆናቸውን ነው።
4. 4. ሌላው ተመልካች ጆውራይ አርምስዎርዝ የተባለ የእንግሊዝ ደራሲ «አበሻ በአደጋ ፊት» በሚል ድርሰቱ የታላቁን የኢትዮጵያን ሊቅ የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴን የድርሰት ችሎታ ካወሳ በኋላ በተለይ በዚያን ጊዜ ባቀረቡት የኢትዮጵያ ነገሥታት የሕይወት ታሪክ፣ የፖለቲካ አስተሳሰባቸውን የሚያንጸባርቅ በመሆኑ በዚህና በሌላውም የሕይወት መስከ ጠቃሚ የሥነ ጽሑፍ አዝመራ ትተውልና ሲል አሞግሷቸዋል። ይኸው ጸሐፊ ሌላ ጓደኛውን አስተያየትም ሲያስተጋባ፡-

   «አንድ አሜሪካዊ የሰው ዘር ጥናት ተመራማሪ /አንትሮፖሎጂስት/ ወደ ፍልስጥኤም ሲጓዝ እግረ መንገዱን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ድሬዳዋ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ኅሩይን አገኛቸው። ስሙም ክሪልቶን ይባላል። ስለ እርሳቸውም «በተፈትሮአቸው እጅግ በጣም የላቀ የዕውቀት ማኅደር የሆኑና ሰው ወዳድ የነበሩ» ሲል ለአንባቢያን የራሱን አስተያየት ሲገልጽ «ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በኢትዮጵያ ውስጥ በጣም ታዋቂና ዝነኛ ሰው ነበሩ። መኖሪያ ቤታቸውና የቤት ዕቃቸውም በዘመናዊ መልክ የተዘጋጁ ሲሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ የአሮፓውያንን ምግብ የተመገብንበት ጊዜ የእርሳቸው ብቻ ነበር» ብሏል።

5. ሮበርት ሙለት የተባለው ደግሞ ስለ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ሲመሰክር «ኅሩይ ሀሳባቸውን ያለ ምንም ማመንታት በግልጽ ከመናገር ወደ ኋላ የማይሉ ትዕቢት የሌለባቸው በፍቅረ ንዋይ ያልተሸነፉ ናቸው። እንደ ዋና ግዴታቸውም የሚቆጥሩት አገራቸውንና ኢትዮጵያዊ ወገናቸውን መርዳቱን ብቻ ነበር» ይልና ተጨማሪ ምስክርነቱን ሲሰጥ «ብዙ ሰዎችን የረዱና ሥራ ያስያዙ ቢሆኑም ለውለታቸው ምንም ዓይነት አጸፋ እንዲከፈላቸው አይጠብቁም ነበር» በማለት አስተያየቱን ገልጿል።

«አበሻ በአደጋ ፊት» በሚለው ርዕስ በተሰናዳው ጽሁፍ ውስጥ እንደተጠቀሰው ለብላቴን ጌታ ኅሩይ ወቅታዊ ጥያቄ ቀርቦላቸው ሲመልሱም ትንሽ ከተከዙ በኋላ «ምስኪኖቹ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን አልጋቸው ላይ እንደ ተኙ በቦምብና በመርዝ ጋዝ እንዳያልቁ የምንችለውን ሁሉ ከማድርግ አናፍርም። ነገር ግን ለሰላም ስንል ልንከፍለ የሚገባን ዋጋ ምን ይሆን!? «የሰላም ምልክት የሆነውን ነጭ ሰንደቅ ዓላማ

እያውለበለብን የቀረውን ሕይወታችንን በባርነት ውስጥ ከመጣል ይልቅ ለነፃነታችንና ለመብታችን ቆመን እየተዋጋን መሞቱ ይመረጣል» ካሉ በኋላ በዚያ ጊዜ ይሰበክ የነበረውን የአሠልጣኝነት ተልዕኮ አውስተው «በእውነት ኢጣሊያ ከጐናችን ቁማ በእኩልነት ለመሥራት የምትሻ ይመስላችኋልን?» የሙሶሊኒን የመጨረሻ ንግግሮቹን አንብባችኋልን? ኢጣሊያ ከተሽከርካሪዎች ከሐኪሞች፣ ከሆስፒታሎች የተሻሉ ሌሎች የምትሰጠን ነገሮች አሏትን? የኢጣሊያን ፖለቲካ ሃይማኖት፣ ታሪክና ግብረ ገብነት ፈጽሞ አንሻውም። ባለፉት ሺ ዓመታት የራሳችን በቅቶን አልኖርንም!? ሲሉ ጥያቄውን በጥያቄ መልሰዋል።

«ሙሶሊኒ ኢትዮጵያን ድል ቢያደርጋትስ?» ብዬ ለጠየቅሁዋቸው ሲመልሱም፣ መሣሪያ ለማንሳት አቅሙ የሚፈቅድለት የኢትዮጵያ ወንድና ሴት ጎልማሶች በሀገሪቱ ውስጥ እስካሉ ድረስ ሙሶሊኒ ኢትዮጵያን ድል አያደርጋትም። ምናልባትም ኢጣሊያ በገንዘብ ሆነ በሕይወት ጉዳዩ ከአቅሟ በላይ ይሆንባታል። ሙሶሊኒም አንድ ቀን ከእንቅልፉ ይነቃና ሕልሙ እንደጠበቀው የማይሳካለት መሆኑን ይገነዘባል» አሉ። «ዛሬ በምንኖርባት ዓለም ይህ ጦርነት በነጭና በጥቁር መካከል እንደሚካሄድ ጦርነት አድርገው የሚናገሩ እኩያን አሉ።» በማለት ላቀረቡላቸው ተጨማሪ ጥያቄ ደግሞ ሲመልሱ፣ የሽማግሌው ዓይኖች ቦግ ብለው የቸበጡ እጆቻቸውን ከጠረጴዛው ላይ አሳረፉና «በእኔ እምነት ጦርነት የሚካሄደው በግፈኞችና በተበደሉ ወገኖች መካከል ነው። በዓለማችን ላይ የሚገኙ ሕዝቦች በተለይ በመንግሥታት ማኅበሩ ውስጥ የሚገኙት ወዳጆቻችን የኛን ጦርነት እንዲዋጉልን አንሻም፤ ጠላቶቻችንንም አንፈራም፤ ምንም ከእኛ የተሻለ የታጠቁ እና የተደራጁ ቢሆኑም ጦርነቱም እስካልቀረ ጠላታችንን ብቻችንን እንቋቋመዋለን። የመጨረሻው አስቸጋሪ ነገር ከመጣም በዓለም ላይ የሚገኙት የሠለጠኑ ሕዝቦ ሁሉ ጦርነቱን በግብረ ገብነትና በፍትሕ አንፃር በማየት ግፈኛው የትኛው ወገን እንደ ይፈርዳሉ፤ የሚል እምነት አለን» ሲሉ መልሳቸውን ደመደሙ።

## ከአገር ውስጥ ሊቃውንት ሊቀ ማዕምራን /ፕሮፌሰር/ ታምራት አማኑኤል ስለ ብላቴን ጌታ ኅሩይ የሰጡት አስተያየት /እንዳለ የተወሰደ/

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ሽዌ /1931 -1939/ በኢጣሊያን ወረራ ወቅት በባዝ ከተማ በእንግሊዝ አገር የነበሩ በኢትዮጵያ ከፍተኛውን ትምህርት ፈጽመው በቤተ ክህነት ሲያገለግሉ ኑረው ሠላሳ ዓመት ያህል በቤተ መንግሥት ልዩ ልዩና ከፍ ያለ ሹመት ተቀብለው ከባድ የሆነ ኃላፊነት ሥራ የፈጸሙ ሰው ናቸው። የአሁኑ ማስታወሻ ስለ ደራሲነታቸው ብቻ የሚናገር በመሆኑ በሹመታቸው ስላስኬዱት ትላልቅ ሥራ ከዚህ ማንሳት የለብንም። ከድርስት ሥራዎቻቸውም ዋናዎቹ ሆነው የሚታዩት «ወዳጄ ልቤ»

«ጐጎ ጽባሕ» እና «ሀገረ ጃፓን» በመሆናቸው የቀሩት መጻሕፍቶቻቸው ግን ለኢትዮጵያዊ ሕዝብ ስንኳ በብዙው ቢጠቅሙትም አሳባቸውንና ደራሲነታቸውን ግን በሦስቱ መጻሕፍት ማግኘት ስለ ተቻለ ስለ እነርሱ ደራሲነታቸውን ግን በሦስቱ መጻሕፍት ማግኘት ሰለ ተቻለ ስለ እነርሱ ብቻ በአጭሩ እናመለክታለን። ብላቴን ጌታ ኅሩይ በጻፉት ሁሉ ዋና አሳባቸው፣

1. በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረ ሰው ሁሉ በፈጣሪውና በመንግሥት ዘንድ እኩል መሆኑን ነው። የእውነትም ነው። ሲፈጠር ብልህና ሞኝ ሁነዋል። በሥራ ዕውቀትና ዕድለኛ በመሆን ከሰው የተሠራ አስፈላጊ የሆነ የማዕርግ ከፍተኝነትና ዝቅተኝነት ይህንንም የመሰለ ብዙ ልዩነት አለ። ነገር ግን በምንፈርድለትና በምንፈርበት ጊዜ መሠረት ልናደርገው የሚገባን ሁሉም ትክክል መሆኑን ነው።
2. በዘርና በሃይማኖት የመጣውን ልዩነት እርስ በርሳችን ተቻችለን እንደሌለ ሁሉ መቁጠር ይገባናል።
3. የክርስቲያን ሃይማኖት በዓለም ከታወቁት ሃይማኖቶች ለመንፈሳዊና ለሥጋዊ ኑሮ የሚስማማ ነው።
4. ሰው በማናቸውም ሰዓት ሞት እንደሚመጣበት ማሰብ ይገባዋል።
5. ሰው የልማድ ባርያ ሳይሆን በነፃነት ሕጉንና ሥርዓቱን እያሻሻለ መሄድ አለበት የሚል ሆኖ እናገኘዋለን።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ከጻፍዋቸው መጻሕፍቶች ሕዝቡ ዕድለኛ ሆኖ አንብቦ የማይጠግበው ከሁሉም ይልቅ «ወዳጄ ልቤን» ነው እንዲህ ያለውን መጽሐፍ የሚጽፍ የእንግሊዙን ደራሲ የዮሐንስ ቡንያን መጽሐፍ ያነበበ ሰው ብቻ መሆኑን የምንረዳው፣ የዚህኑ ደራሲ «የክርስቲያን መንገድ» የተባለውን መጽሐፉን ስናነብ ነው። ብላቴን ጌታ ኅሩይ ግን ንድፉን /ፕላኑን/ ስንኳ ከእንግሊዙ ደራሲ ቢቀበሉ የጽሑፋቸውን ሕንፃ፣ መልክና ጠባይ በፍጹም ኢትዮጵያዊ ያውም የሚያምር ኢትዮጵያዊ አድርገውታል።

በሀሳባቸውም የፈጠሩት «ወዳጄ ልቤ» የተባለው ሰው የርሳቸው የራሳቸው ወይም ክርስቲያን ሁኖ የክርቲያንን ሕግ ለመጠበቅ የሚታገል ሰው ምሳሌ ነው። ወዳጄ ልቤ ለብቻው ሆኖ የእግዚአብሔርን ህላዊና የሕዝበ - አዳምን ዕጣ ፈንታ በተለይም የነፍስን ሁኔታ በሚያስብበት ጊዜ ወይም እግር ጥሎት ከልዩ ልዩ ሰዎች ጋር ተገናኝቶ ከፋታቸውንና በጐነታቸውን በሚገልጥበት ጊዜ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ በተለይም በክርስቲያን ላይ የሚመጣበትን መከራ ሲያስታውስ ተስፋ ሲቆርጥ ሲቃጣና በርትቶም ሲታገል፣ ከባልንጀሮቹ ጋርና ለብቻው መሰንቆውን ይዞ ሲያንጐራጉር በሠርግ አስመስሎ ስለ ክርስቲያን ሃይማኖት አጀማመርና ድል እየነሣ በሄደበት ዘመን ሁሉ ያለበትን መከራ ሲተርክ ፍጹም ክርስቲያናዊ ነው።

ወዳጄ ልቤ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ካመነ በኋላ ከኃጢአት ላይ ላለመውደቅ ምን ቢሠራ ይሻላል? ብሎ የሚጠይቅ ወይም የዚህን አሳብ የሚያሳድር ሆኖ ይታያል። አንባቢው ቁልፉን ወይም መልሱን አገኘሁ፣ መጽሐፉ ሊነገረኝ ነው ብሎ ሲጓጓ «ብፁአን እለ ተኃድገ ሎሙ ኃጢአቶሙ» /ኃጢአታቸው የተሠረየላቸው ምስጉን ናቸው።/ ብሎ ያሰናብተዋል።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ስለ ሃይማኖትና ስለ ፖለቲካ ስለ ልዩ ልዩ ጉዳይም ያሰቡትን ሁሉ ካንድ ላይ ሰብስበው ጽፈው ያወጡትን መጽሐፍ «ጐኅ ጽባሕ» ብለው ሰይመውታል። ጐኅ ጽባሕ ስለ ሃይማኖት የሚገልጠው አሳብ ንግግሩ ልዩ ቢሆንም ከወዳጄ ልቤ ጋር ይቀራረባል። ሕግንና ልማድን ማሻሻል ብላቴን ጌታ ኅሩይ ሥራዬ ብለው የቆሙለት ዋና አሳብ በመሆኑ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር፣ ስለምንኩስናና ስለ ጋብቻ ሥርዓት ስለ ጸሎትና ስለ ንስሐ ከጻፉት ክፍል የኢትዮጵያ የሃይማኖት ሥርዓት እየተሻሻለ የሚሄድበትን መንገድ መሠረት ባለው አካሄድ አስረድተዋል።

ከቤተ ክህነት ቤተ መንግሥትን መምራት ይገባኛል እያለ በመንፈሳዊና በሥጋዊው ጉዳይ ላይ የበላይ አስተዳዳሪ ልሁን የሚል እንደማይጠፉ ስለተረዱት፣ የሁለቱንም ሥልጣን ወስነው ሁሉም በየክፍሉ በየሥራው ኃላፊነት እንዳለበት፣ የሁሉ በላይ ግን መንግሥት መሆኑን አደላድለው ወስነዋል። ወገን ለሌለው በዘር በሃይማኖት የተለየ ሰውና ለእንስሳ ርኅራኄ እንዲገባ በብዙ ሰብከዋል። ለዛሬው ትውልድ ኢትዮጵያዊ እያንዳንዱ ስንኳ የዚህ ዓይነት ምክር ባያስፈልገውም ከአገራችን ሕዝብ ላብዛኛው አዲስ ነገር ሁኖ ሳይታየው የማይቀር ነውና መጽሐፉ ለእነዚህ ያለው ክፍል ብርቱ አሳብ የሚያሳድርበትና ጥቅም ያለውን ክርክር የሚያስነሳ ነው።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ የመንግሥት መልዕክተኛ ሁነው ገና ወደ ጃፓን አገር ሳይሄዱና ከዚህም በኋላ በኢትዮጵያ ውጭ ስላዩዋቸው አገሮች ሁኔታ የጻፉዋቸው መጻሕፍት አሉ። በተስተካከለ አማርኛና ያላዩትን አገርና ሕዝብ እንደ አዩት ሆኖ የሚያስቆጥር አነጋገር የመንገዳቸውን አኳኋን የገለጡበት መጽሐፍ ግን፣ «ማኅደረ ብርሃን» /ሀገረ ጃፓን/ ብለው የሰየሙት ነው። መጽሐፉ ከማያስፈልግና ከሚያታክት ዝርዝር ሳይገባ በወሬ የምናውቀው የጃፓን አገርና ሕዝቡ፣ ሃይማኖቱ የአገሩ ልማድ፣ ሥልጣኔውና አስተዳደሩ ምን እንደ ሆነ ነግሮ የሚያጠግብ ነው።

ደራሲው የተላኩበት ሥራ ከሕዝብና ከትላልቅ ሰዎች ከንጉሠ ነገሥቱና ከንግሥቲቱ ጋራ የሚያገናኝ በመሆኑ የሆቴሉንና የባላገሩን፣ የሚኒስትሮችንና የቤተ መንግሥቱን እልፍኝ ከአዳራሽ ወጉንና ሥርዓቱን አይተዋል። ያዩትንም ላላየነው ካየነው እንድንቆጥረው አድርገው ጽፈዋል። ከዚህም ሁሉ ጋር ጃፓን አገርና ሕዝብ መሆን

ከጀመረበት ዘመን አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ያለውን ታሪኩን እንድናውቀው ከሌላ ባለ ታሪክ እየጠቀሱ በአጭሩ ተርከውልናል። የባሕሩንና የመሬቱን፣ የጫካውንና የአትክልቱን ሁኔታ የሚነግረው ክፍል ደህና ሥዕል ሣይ በሚስማማ ቀለም ነድፎ ያቀረበው ሠሌዳ ይመስላል።

ክርስቲያኑ ኅሩይ ክርስቲያን ያይደሉትን ወገኖች አምልኮና ባሕል የሚያዩት እጅግ ከፍ ባለ አስተያየት ነው። የጃፓን አምልኮም እንደ ሌላው አምልኮ፤ የእግዚአብሔርን ምስጢር ለማግኘት የሚጣጣር ሁኖ ስለታያቸው ያገራችን ሕዝብ ባይቀበለውም ግን በሰፊው እንዲመለከተው አድርገው ገልጠውታል።

ከዚያን በፊት ልዩ ልዩ መጻሕፍትን በመጻፍ ብዙ ትግል ደርሶበት ያየው የብላቴን ጌታ አዕምሮ አማርኛ ሀገረ ጃፓንን በጻፈበት ጊዜ ድርጅቱ ከፍ ካለ ደረጃ የደረሰ ሁኖ ይታያል።

አማርኛ ማሠሪያ አንቀጹን አርቆ፣ ከማኸሉ ልዩ ልዩ አሳብ ጣልቃ ማስገባት የተፈጥሮ ጠባዩ ነው። ብላቴን ጌታ ኅሩይ ግን አብዛኛውን ጊዜ ይህን ሳይከተሉ ንግግሩን በአጭር በአጭሩ ማሰር ልዩ ባሕርያቸው ነው። ከአማርኛው መርማሮች አንዳንድ ሰው ብላቴን ጌታ ኅሩይ አማርኛቸውን የውጭ አገር /በአሮጳ/ ንግግር ዓየንት እንጂ በተፈጥሮ ጠባዩ አያስኬዱትም ብሎ ጽፎባቸዋል። ነገሩም እውነት ይሆናል ግን ደግሞ ደራሲ መከተልና ማሻሻል የሚገባው የሚጽፍበትን ቋንቋ ጠባይ ነው ስለ ተባለ ይኸው ደራሲ የሚጽፈው ነገር የንግግር ጣዕም ያለውና በፍጥነት የሚያስተውሉት ከሆነ ከተራው ሕዝብ ተለይቶ ልዩና ማዕርግ ያለው ደራሲ ነው መባልን አያግደውም።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ አዕምሮን ለዋጭና ለሕፃናት የሚሆኑ ልዩ ልዩ መጻሕፍት ትተውልናል። እንዲያውም ከመጻሕፍት ዓይነት በጽሕፈት ለመግለጥ ያልሞከሩት ጥቂት ነው ለማለት ይቻላል። በሥራ የተፈተነው የተፈጥሮ ባሕርያቸው ትእግሥተኛ ሲሆን፣ ጽሕፈት ሲልዋቸው ፍጥነታቸው የመኪና ያህል ስለ ነበረ፣ ከአማርኛቸው በቀር ለወጣቱ ኢትዮጵያዊ ለአንዳንዱ የጻፉት ታሪክና ልብ ወለድ ታሪክ ሌላውም ሁሉ አብዛኛውን ጊዜ ውዝፍ ሆኖ ይታየዋል። ምክንያቱም በቤተ መንግሥት የነበረባቸው ከአብድ ሥራ ለሚጽፉት መጽሐፍ የተገባውን ምርመራ ለማጥለቅና ለማስፋፋት ፍታ አስልሰጣቸው ስላለና ለአገራቸው ሕዝብ በነበራቸው ፍቅር እርሳቸው ካወቁት ከብዙው ጥቂቱን ሳያስታውቁት ቢቀሩ «ዘደፈነ ወርቅ እግዚኡ» የጌታውን ወርቅ እንደ ሸሸገ /እንደ ቀበረ/ አገልጋይ እንዳይሆኑ ሲሉ ይሆናል።

የሂሣብ የፍልስፍና የሕክምናና፣ የሥነ ፍጥረት ይህንንም የመሰለውን ልዩ ልዩ ዕውቀት የተማረ ሰው ካልሆነ በቀር በሌላ ዕውቀትም ሊቅ ሊሆን ሰው አያስተውለውም።

አንዳንድ ሰዎች ግን፣ በድርሰት ችሎታቸው እንኳንና የተማረ ሰው ተራውም ሕዝብ ሳይቀር በሚያስተውለው ንግግር ልዩ ዕውቀታቸውን ለመጻፍ ተችሏቸዋል። ቃለ እግዚአብሔር የሚያስተምሩና የሃይማኖትን መጻሕፍት የሚተረጉሙ ስለ ሃይማኖትም የሚጽፉት ሊቃውንት ምስጢሩ ግን እያላቸው ንግግራችወ ወይም አጻጻፋቸው አማርኛው ተለውጦ ለግል ውሎ የማይደፈር ሁኖ ይኖራል። ደግሞም ትምህርት ሲባል ከጥንት እስከ ዛሬ፣ የአገርና፣ የመንግሥት ወሰን የማያግደው አገርና መንግሥቱም ቢለያዩ እንኳ ሰንደቅ ዓላማው ወይም ወገኑ አንድ የሆነ ነው። ለጊዜው ያገራችን ሊቃውንት ግን ከኢትዮጵያ ውጭ ያለው ትምህርትና እውቀት ባዕድ ሆኖባቸዋል።

ቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት

## ኢትዮጵያ ምዕራባዊነትን ለማላበስ ምዕራባዊ ያልሆነው የኢትዮጵያ ዓይነተኛ (ሞዴል) ሙከራ፡- የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኅሩይ ወደ ጃፓንም ያደረጉት የተልዕኮ ጉዞ ፲፱፻፪ ዓመተ ምሕረት

ለአይ ኤስ ደቡብ የቀረበ ሰነድ


ጄ ካልቪት ክላርክ 3

ጃክሰንቪል ዩኒቨርሲቲ

ጃክስንቪል ዩኒቨርሲቲ (USA)


### የጽሑፉ ረቂቅ

እ.ኤ.አ 1920ዎቹ ዓመታት ውስጥ አብዛኛዎቹን የምዕራባውያን ኃይሎች በጣም ባስበረገገና ባስደነገጠ መልኩ ጃፓናውያን ጐብኚዎች በጃፓንና በኢትዮጵያ መካከል በተከታታይ ንግድን ለማስፋፋት የፈለጉበት ሁኔታ ታይቷል። ጃፓናውያኑ ተወካዮች በ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት በአጼ ኃይለ ሥላሴ የንግሥት በዓል ላይ የተገኙ ሲሆን ወደዚያውም ከኢትዮጵያ ጋር የወዳጅነትና የንግድ ስምምነት ተፈራርመዋል። በተከታዩም ዓመት ኢትዮጵያውያን ቀደም ሲል እ.ኤ.አ 1889 ዓ.ም ከወጣውና የጃፓን የሜይጂ ሕገ መንግሥት ጋር በጣም ተመሳሳይነት ያለውን ዓይነት ሕገ መንግሥት አወጁ። ይኸንንም ቅርበትና ልባዊ ግንኙነት ይበልጥ የተሻለ እንዲሆን በማሰብ ኢትዮጵያን ልክ እንደ ጃፓን ለማድረግ ያሰቡትና ጥሩ ተሰሚነትም የነበራቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ እ.ኤ.አ 1931 ዓ.ም መጨረሻ ጃፓንን ጐበኙ። ኅሩይ የንግድና የፖለቲካ ትስስሮችንና ወታደራዊ እርዳታን ለማግኘት ፈልገው የነበረበትና ከፍተኛም አክብሮት የተመላበት መስተንግዶ ለማግኘት ሲሆን ኅሩይና አብረዋቸው የሄዱት ኢትዮጵያውያን አብዛኛዎቹ የጃፓንን የታወቁ የኢንዱስትሪና የወታደራዊ ተቋማትን እየተዘዋወሩ በመጐብኘት ደህና አድርገው መርምረው አይተዋል። የብሔርተኛነት ስሚዔት ያየለባቸው የጃፓን መሪዎች በነጮች ቅኝ አገዛዝ እና በኢምፔሪያሊዝም ላይ በሚደረገው «የቀለም ሕዝቦች» ትግል በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈላጊውን አጋር ለማግኘት ተስፋ በማድረጋቸው ለኅሩይና ለተከታዮቻቸው ከፍተኛ ጉጉት የተመላበትን ሰላምታ አቀረቡላቸው። የኅሩይም ጉብኝት ከፍተኛ የትብብር ደረጃን የመላከተ ጉዳይ ነበር። የዓለምን ኃያላን መንግሥታት ቁጣ በመጋፈጥ ረገድ የጃፓን መንግሥት ፈቃደኛነት ግን ከጃፓናውያን ብሔርተኞች ፍላጐት ያነሰ ነበር። ይህ ሰነድ በእንግሊዝ በፈረንሣይ፣ በኢጣሊያ፣ እና በጃፓን በዋና ዋናዎቹና በሁለተኛም ደረጃ ምንጮች ላይ ተመስርቶ በሚገባ በሰፊው ስለተነገረለት የታወቀው ጉብኝት አነሳሽ ምክንያቶቹንና ተከታይ ውጤቶቹን ዘርዝሮ ይገልጻል። በተጨማሪም በሰፊ ዲፕሎማሲያዊ አድምታው ይህንን የግሎባላይዜሽንና የምዕራባዊነትን ምሳሌ ምዕራባዊ ባልሆነ አገር አማካይነት ይወክልልኛል በማለት በሰፊው ተንትኖ አስቀምጦታል።

ፍፁም የተዋጣላቸውና ተራማጅ አስተሳሰብም ያላቸው ኅሩይ ታሪኢኮችና ማኅበራዊ ፍልስፍናዎች ያሉዋቸውን ወደ ሃያ ስምንት ያህል የሚሆኑ መሳሕፍትን በአማርኛ ደርሰዋል። ልዩ የቋንቋ ችሎታ ያላቸውና እ.ኤ.አ 1930 ዓ.ም በኋላ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሆኑት ኅሩይ ወደ ፓሪስ ወደ ጀኔቫ ወደ ጃፓንና ወደ አሜሪካ የዲፕሎማቲክ መልእክተኛ በመሆን አገልግለዋል። አጼ ኃይለ ሥላሴና ኅሩይ የጃፓንን የልማትና ዕድገት መንገድ ከመፈለጋቸውም በላይ የጃፓናውያን አስተማሪዎችና አለማማጆች በመሆን አውሮፓውያን የጃፓንን ፈጣን የለውጥ እርምጃ ያመጡ ቀስቃሾች መሆናቸውን ተገንዝበዋል። በኢትዮጵያ ከነበሩት የፈረንሣይ ጉዳይ ፈጻሚ ጋር

ሲነጋገሩም ጎሩይ የጃፓንን የለውጥ እርምጃ በማሞገስ «ከጃፓን ይልቅ እዚህ በኢትዮጵያ ከዚህ በፊት ያልተደረጉ ዓይነት ልዩ እርምጃዎችን ያያሉ» ሲሉ አረጋግጠዋል።

ከጃፓን ጋር የተደረጉትም ቅርርቦች የዲፕሎማቲኢክ ጠቀሜታዎችን የያዙ ነበሩ። እ.ኤ.አ 1930ዎቹ ዓመታት መጀመሪያዎች ላይ የኢትዮጵያ ፖሊሲ በኢትዮጵያ ላይ የአጭር ጊዜ የጥቅም ፍላጐቶች ለሌላቸው ለምሳሌ እንደ አሜሪካ ጀርመን ጥቂት የኤሮፓ ትናንሽ አገሮችና ጃፓንን ለመሳሰሉ አገሮች ዋና ዋና የንግድ ሥራዎችን ለመስጠት የታሰበበት ትልም ነበር። በኢንተርናሽናል የፖለቲካ ፉክክርም ቢሆን ጃፓን ባላት ጂዎግራፊያዊ አቀማመጧ ምክንያት ጃፓናውያን የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ሊያሠጉ እንደማይችሉ ጎሩይ በሚገባ ተረድተውት ነበር። ከዚህም በላይ አንድ አውሮፓዊ ሃህይል ኢትዮጵያን የሚያሠጋት ቢሆን ጃፓን በኢትዮጵያ የሚኖራት የኢኮኖሚ ጥቅም ኢትዮጵያን እንድትደግፍ ያስገድዳታል የሚል አስተሳሰብም ነበር። በመጨረሻም በኢትዮጵያ የጃፓን መገኘትና የጃፓናውያን በብዛትም መግባት የኢትዮጵያን ጐረቤት ቅኝ አገሮች የያዙትን እንግሊዝንና ፈረንሣይን ያዳከማቸው ይሆናል።

የፈረንሣይ ዲፕሎማቶች ጎሩይ ሥራቸውን እንደ ጀመሩ ገና ከጠዋቱ ስለ ጎሩይ በመጀመሪያ መልካም አስተሳሰብ ነበራቸው። እ.ኤ.አ 1919 ዓ.ም ጎሩይ ወደ ኤውሮፓ በሄዱ ጊዜ የኢትዮጵያን የምሁራን ወገን የሚመሩ ዓይነት ሰው አድርገው ተመልክተዋቸውም ነበር። በፈረንሣይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር (ኳይዶርሲ) ጥያቄ ጎሩይ የሕዝብ መምሕር (አስተማሪ) የሚል የሽልማት ዓርማ ተሰጣቸው። እ.ኤ.አ 1922 ዓ.ም በአዲስ አበባ የተቋቋመውና የሀገሬው ዜጐች ያልሆኑትን ሰዎች የሚዳኝ ልዩ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ሆነው በመሾማቸው የውጭ አገሮች ዲፕሎማቶች ስለ ሹመቱ እርካታ ተሰምቷቸው ነበር። እ.ኤ.አ 1917 ዓ.ም እስከ 1923 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ የነበረው የፈረንሣይ ለጋሲዮን ሚኒኢስትር ጎሩይ ትክክለኛ ብልህና የልዩኡ ፍርድ ቤቱ መልካም አሠራር ሳይናጋ እንዲቀጥል የሚያደርጉ ሰው ናቸው የሚልና በኢትዮጵያ የሚገኙ አውሮፓውያን ሁሉ እንደሚተማመኑባቸው ፈረንሣዊ ዲፕሎማት ማመልከታቸው ተረጋግጦአል። እ.ኤ.አ 1924 ዓ.ም ጎሩይ ተፈሪ እምኮንን ይባሉ ከነበሩት የወደፊት ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ከሚሆኑት ጋር በሌላ ጉዞ ወደ ኤውሮፓ አብረው ሄዱ በዚያን ጊዜ የፈረንሣይ ለጋሲዮን ሌላው ሚኒስትር፡-

«ትልቅ ግምት የሚሰጣቸውና ምናልባትም ልዑሉ ዙፋኑን ከያዙ በኋላ ከዋነኞቹ ታላላቅ ሚኒስትሮች አንዱ መሆናቸው የማይቀርላቸው ጎሩይ ራሳቸውን ለራስ ተፈሪ ፍፁም ታማኝ ያደረጉ ሚዛናዊ አመለካከትና ግልጽ አዕምሮ ያላቸው ሰው ናቸው። ዘመናዊ አስተሳሰቦችን የሚያውቁና ሀገራቸውም እነዚህን ዘመናዊ አስተሳሰቦችን ማወቋ

አስፈላጊ መሆኑን የተገነዘቡ ከመንግሥት ዋንዎቹ ኃላፊዎች አንዱም ናቸው» በማለት መስክረውላቸዋል።

ይሁንና ግን ይህ ስለ ኅሩይ የተመሰከረለው በጎ አስያየት ትንሽ በትንሽ እየተለወጠ ሄደና አዲስ አበባ የሚገኘው የፈረንሣይ ለጋሲዮን ጉዳይ ፈጻሚ እ.ኤ.አ ሐምሌ 25 1931 ዓ.ም ባስተላለፈው መልእክት ኅሩይ ብልህነት የጐደላቸውና ሥራቸውንም ለይስሙላ ያህል ላይ ላዩን ብቻ በማስመሰል እንደሚሰሩ ዓይነት ገለፀ። ይሁንና ግን የኢትዮጵያ መንግሥት ኅሩይን ሳያማክር የሚወስደው ውሳኔ አልነበረም። ኅሩይ በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ የነበራቸው ተደማጭነት እጅግ ተፈላጊና ጠቃሚም ሆኖ በመቆየቱ አንድ የፈረንሣይ መንግሥት ተወካይ የኢትዮጵያው ራስፑቲን ብሎ ሲሰይማቸው ሌላው ደግሞ ኅሩይ ኃይለ ሥላሴ በተባለ ርእሰ አንቀጽ ጽፎባቸዋል። ሌላው ተረበኛ ደግሞ ኅሩይን ምትሀተኛው ጠንቋይ ሲል ገልጿቸዋል።

ለመሆኑ የኅሩይ ዝና በፈረንሣይ ዲፕሎማቶች ዘንድ ለምን እንደዚህ ከፉኛ ሊያሽቆለቁል ቻለ? ምንም እንኳን ፈረንሣይን የሚጠሉ ባይሆኑም በጠቅላላው አውሮፓውያንን የማያምኑና ወደ እንግሊዝና ወደ ስዊድናውያን መቀራረብን የሚፈልጉ ነበሩ። እንደዚሁም ደግሞ ኢትዮጵያን ከሌሎች እያገለለ የሄደውን የኅሩይን ያልተለሳለሱ አክራሪ ፖሊሲዎችን ፈረንሣዮችን ጨምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ጃፓን ስላደረገችው የመቀራረብ እርምጃ ኅሩይን ይወቅሱ ነበር።

## የኅሩይ ጉብኝት

የኅሩይ ጉብኝት ሀሳቡ የተፀነሰው ጃፓን በቱርክ የነበረው እምባሳደሯ እ.ኤ.አ 1930 በኅዳር ወር በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የንግሥ በዓል ላይ በልዩ መልክተኛነት እንዲገኝ ከማድረጓ አንድ ዓመት አስቀድሞ ነበር። አምባሳደር ዮሺዳ ኢሳብሮ በኢትዮጵያ በነበሩበት ጊዜ አዲስ የወዳጅነትና የንግድ ስምምነት ውል የተፈራረሙ ሲሆን ይህንንም ስምምነት ሁለቱም

አገሮች ከሁለት ዓመት በኋላ አስድቀዋል። ኢትዮጵያ የጃፓናውያንን መስመር ተከትላ ዘመናዊነት ከጃፓን በሞዴልነት መቅሰም ትችል እንደሆነ ለማየት ካደረባቸው ጉጉት የተነሣ ኅሩይ ግንኙነቶቹን ለማሻሻል አንድ የኢትዮጵያ የልዑካን ቡድን ወደ ጃፓን ለመላክ እ.ኤ.አ ኅዳር 19 ቀን አሳሰቡ። ለዚህም ማሳሰቢያ መልካም ምላሽ በመገኘቱ የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት ጃፓን የኢትዮጵያን ባለሙሉ ሥልጣን መልክተኛ እንድትቀበል በማለት በይፋ ጠየቁ። የጃፓን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤትም አምባሳደር ዮሺዳ ስለቀረበው ጥያቄ በዝርዝር እንዲነጋገሩበት መመሪያ ሰጣቸው። ኅሩይም በመጀመሪያ ያቀዱት በግንቦት ወር ለመሄድ ነበርና ከጃፓን ጉብኝታቸውም

በኋላ ወደ አሜርካ ከዚያም ከአልጋወራሹ ጋር ለመገናኘት ወደ ፈረንሣይ ለመሄድ አቅደውም ነበር። በዚህ ጊዜ ግን ኢትዮጵያውያን ወደ ኤውሮፓ የሚደረገውን የአልጋ ወራሹን የጉብኝት ጉዞ ላልተወሰነ ጊዜ ስላስተላለፉት ኅሩይ ከጃፓን በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ወሰኑ። ከጃፓንም ወደ አሜሪካ እንዲሄዱ ንጉሠ ነገሥቱ ለኅሩይ ትእዛዝ የመስጠታቸው ነገር እምብዛም ዕድል አልነበረም። ለማናቸውም ቢሆን ኅሩይ በአዲስ አበባ በሚጠብቃቸው ሥራ ምክንያት ከሦስት ወር በኋላ ለመመለስ አቀዱ።

የንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ልዩ መልዕክተኛ የሆኑት ኅሩይ ስለ እቅዶቻቸው ለኢጣሊያ መንግሥት ከገለጹ በኋላ እ.ኤ.አ 30 ቀን ከአዲስ አበባ ተነሡ። ከእርሳቸውም ጋር በጅቡቲ የኢትዮጵያ ቆንሲል የነበሩት ተፈሪ ገብረ ማርያም አርአያ አበባና፣ ዳባ ብሩ አብረዋቸው ነበሩ። ሁላቸውም እ.ኤ.አ 5 1931 ዓመተ ምሕረት ከጅቡቲ በመርከብ ተሳፍረው ወደ ጃፓን ተጓዙ። የወደፊቱንም ጊዜ ገጹን ለማመልከት ከመንገደኞቹ አንደኛው አርአያ አበበ የተባሉት ኩሮዲ ማሳኮ ከተባለች አንዲት ጃፓናዊት ጋር በጋብቻ ለመተጫጨት ያሰቡ ሲሆን ዳባ ብሩ ደግሞ በኢጣሊያና ኢትዮጵያ ጦርነት ወቅት እ.ኤ.አ 1935 ዓመተ ምሕረት እንደ ገና ወደ ጃፓን ተመልሰው የሚኈበኙ ሆነው ነበር።

ኅሩይ ከጅቡቲ ወደ ጃፓን በሄዱበት በዚያው ቀን በአዲስ አበባ የአሜሪካው መንግሥት ተጠሪ ኤዲሰን ሳውዛርድ የተባሉት ወደ ዋሽንግተን አንድ ረጅም መልእክት አስተላለፉ። በመልክቱም ኅሩይ ወደ ጃፓን የሄዱት መዋነኛነት በቅርቡ ጃፓናውያን መልእክተኞች በኢትዮጵያ ለአደረጉት ጉብኘተ መልካም ምላሹን ለማድረግ፣ ለጋሲዮን ለመክፈት የንግድና የወዳጅነት ውል ለመዋዋልና በጃፓን ንጉሥ ሥርዓተ ንግሥ አከባበር ላይ ለመገኘት መሆኑን እንደ ገለፁላቸው አስረድተዋል። ጃፓናውያን እንዲያውም ካሁኑ በኢትዮጵያ ውስጥ በተወዳዳሪነት ያየሉበትን የጥጥ ሥራ ሸቀጣ ሸቀጦችን ገበያ በብቸኝነት (በሞኖፖል) ለመያዝ የሚያስችላቸውን ዓይነት ስምምነት ለማድረግ ማሳሰባቸውን ሳውዛርድ የመኑበት መሆኑንም በሪፖርታቸው አመልክተዋል። ሳውዛርድ ተረድቼዋለሁ እንደሚሉት ለዚህ በጋራ ስምምነት የዋጋ ድርድር ያደረገው አንዱ ጃፓናዊ ድርጅት «ኒሲሺን ቦሴኪ ካቡስኪኪ ካይሻ ሶሳይቴ አኖኒም የፊላቱር ደኮቶን ቶኪዮ ጃፓን» የተባለው ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ከርዳዳ ዓይነተኞችን የጥጥ ሥራ ምርቶች ለማስመረት ይፈልጉ ስለ ነበረ ጃፓናውያን የዚህ ዓይነቱን ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲያቋቁሙ ኅሩይ ሀሳቡን እንደሚያቀርቡ ሁሉ ሳውዛርድ ያስቡ ነበር።

ለብዙ ዓመታት ሳውዛርድ ካደረጉዋቸው ውይይቶች ንጉሠ ነገሥት ጃፓንን በጣም እንደሚያደንቁና ጃፓናውያን በዓለም የታወቀውን ተደናቂ አቋማቸውን ለማግኘት የበቁት የውጭ አገር ተወላጆች የሆኑ አማካሪዎችን በመጠቀም መሆኑን

እንደሚያምኑበት ማወቃቸውን አረጋግጠዋል። ኢትዮጵያም በዚሁ ዓይነት በውጭ አማካሪዎቿ አማካይነት ተመሳሳይ የሆኑ አስደናቂ ክንውኖችን ለማድረግ የምትጠበቅ መሆኗ ተገቢውም እንደ ሆነ ኃይለ ሥላሴ ማሰባቸውን ጠቁመዋል። በኢትዮጵያና በጃፓን አገሮችና በሕዝቦቻቸው መካከል ያሉትን ሰፊ ልዩነቶችን ችሎታዎቻቸውንና ሀብቶቻቸውን እንዲሁም ኢትዮጵያ ካለችበትና መቼም ቢሆን ተስፋ ከምታደርገው በላቀ ሁኔታ ጃፓንን ቀዳሚ ሥፍራ በሰጣት ሁኔታ ላይ ንጉሠ ነገሥት በእርግጥም ምንም ግንዛቤ እንዳልነበራቸው ሳውዛርድ በጥርጣሬ ዓይነት ጨምረው ገልጸውታል። ሳውዛርድ ለአሜሪካ ወደ ውጭ ጉዳይ አገልግሎት ከመግባታቸው በፊት በሩቅ ምሥራቅ ውስጥ በርካታ ዓመታትን ያሳለፉ በመሆናቸው ጃፓንን ደህና አድርገው ያውቃሉ። ይሁን እንጂ ግን በሁለቱ አገሮችና በሕዝቦቻቸውም መካከል ያለውን ትልቅ ልዩነት ገልጸው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትን ለማሳመን ምናልባትም የማይቻልና ከቶም የማይሞከር አስቸጋሪ ተግባር መሆኑን ከቶም አላሰቡም ካሉ በኋላ ነገር ግን ከጃፓን ጉብኝታቸው በተጨባጭ መልኩ ሁኔታዎችን እንዲያነፃፅሩ በማለት ለጎሩይ ኦፊሲየላዊ ባልሆነና ብልህነት በተዋሀደው ዘዴ ሳውዛርድ አሳስበዋል።

አንድሬ ሬቦን በተባለ መርከብ ተሳፍረው ኅሩይና ተከታዮቻቸው በምዕራብ ጃፕና ኮቤ በተባለው ወደብ ጥቅምት 26 ቀን (እ.ኤ.አ ኖቨምበር 5) ከጠዋቱ ልክ 3 ሰዓት ላይ ደረሱ። ከፍተኛ የጃፓን መንግሥት ባለሥልጣኖች የአንድ ክፍለ ግዛት አገረ ገዥ ከንቲባውና ከሁለት ሺህ እስከ ሦስት ሺህ የሚገመቱ ጃፓናውያን ዜጎች፣ የወጣቶች ማኅበር አባላትና ቦይስካውቶችንና ተማሪዎችን ጨምሮ እንግዶቹን እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት አቀባበል አደረጉላቸው። የእንግዶቹም መሪ ለተቀበላቸው ሕዝብ ስለሁለቱ አገሮች የጋራ ብልፅግና የተቀራረበ ወዳጅነትና የንግድ ትስስር የሚታዩዋቸውን ተስፋዎች ገለፁ። ከዚያም፡-

> «በቅርቡ በተደረገው የጃፓንና አቢሲኒያ የንግድ ስምምነት ተደስቼአለሁ። ከ3000 ዓመታት በፊት የተመሠረተው የአቢሲኒያ መንግሥት ግዛት ከጃፓን ንጉሠ ነገሥት ነገሥታዊ ግዛት ጋር የሚያመሳስሉት በርካታ የጋራ ነገሮች አሉት። በንግሥተ ሳባ ሥልጣን የሰሎሞን ልጅ መንግሥቱን የመሠረተ ሲሆን የአሁኑም የኢትዮጵያ ንጉሥ ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው ዘር 127ኛው ነጋሢ ናቸው። ባለፉት የ3000 ዓመታት ታሪክ ውስጥ በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮችና በመሐመዳውያን (ሙዝሊሞች) መካከል የሀገሪቱን የባህል ዕድገት በጣም የጐዱ ግጭቶች አጋጥመዋል። አቢሲኒያ በባህልና በሌሎችም እንቅስቃሴዎች ዘግይታም ቢሆን ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፈጣን ዕድገትን

አሳይታለች። ለምሳሌም ያህል ዋና ከተማው አዲስ አበባ በአሁኑ ወቅት የባቡር መስመር አላት» ብለዋል።

በኋላም ኅሩይ በጉብኝታቸው የገጠማቸውን ሲገልፁ «ጃፓን በደረስን ጊዜ የሰዎችን የደስታ ጩኸት ሰማን። ብዙ ጃፓናውያን ዜጎች የኢትዮጵያንና የጃፓንን ሰንደቅ ዓላማዎች እያውለበለቡ ከወደቡ ላይ ጠበቁን። በየሄድንበት ሁሉ ተመሳሳይ ሁኔታ ነበር» ብለዋል። ጃፓናውያን በቅርቡ ከሊግ ኦፍ ኔሽንስ (ከመንግሥታት ማኅበር) ስለ ወጡ ከአፍሪካ የመጣውን በኅሩይ የተመራውን የወዳጅነት ተልእኮ ቡድን እንኳን ደህና መጣችሁ ብለው ለመቀበል በተለይም ተደስተው ነበር። ከምሳም በኋላ የእግንዶቹ ቡድን ወደ ሮኮ ተራራውን ወደ ታካራዙካ በመጓዝ በዙይሆጊ ቤተ መቅደስ በተደረገው የሻይ ግብዣም ላይ ተገኝቷል።

በዚያኑ ዕለት ምሽት ልክ በ3 ሰዓት ላይ የኅሩይ ቡድን ወደ ቶኪዮ በሚሄደው ልዩ ባቡር ተሳፍሮ በመጓዝ በማግሥቱ ጠዋት ቶኪዮ ሲደርስ የንጉሣዊው ቤተሰብ (የቤተ መንግሥት) ሚኒስትሩ ኢቺኪ ኩቶኩሮ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሺዴሃራ ኪጁሮ እና ሌሎችም ከፍተኛ ባለሥልጣናትና ይጋዜጠኞች ቡድን በሚያስደስት ሁኔታ ተቀበሉት። ወታደራዊው የቶያማ ባንድ (የሙዚቀኞች ቡድን) ትርዒቱን እያሳየ ሳለ ኢትዮጵያዊው መልእክተኛና ተከታዮቻቸው ለአጭር ጊዜ ዕረፍት በጣቢያው ወደሚገኘው የታዋቂ ልዩ እንግዶች ማረፊያ ክፍል ገቡ።

ከዚያም እንግዶቹ በንጉሠ ነገሥታዊው የክብር ዘበኞች ታጅበውና በክብረ በዓሉ ዋና አዛዥ ዋታናቢ አስተናጋጅነት ወደ ንጉሣዊው ሆቴል ተጓዙ። እንደገናም ደግሞ የክብር ዘበኞችና በሞተር ቢስክሌተኞች ታጅበው ከቤተ መንግሥት በተላከላቸው ልዩ ሠረገላ በመሆን ከረፋዱ በ4 ሰዓት ከ20 ደቂቃ ከሆቴሉ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቤተ መንግሥት ሄዱ። በቤተ መንግሥቱም የፌኒክስ አዳራሽ በንጉሠ ነገሥቱ በግርማዊ ሒሮሒቶ ፊት ኅሩይ በአማርኛ ቋንቋ የከበረ ሰላምታ ከገለፁ በኋላ የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት ደብዳቤ አቅርበው በኢትዮጵያ ግዛት ከፍተኛ ክብር ያለውን ባለ ጳውሎዊና አበባ ያለበትን የሰሎሞንን ኮርዶን ኒሻን አበረከቱ። በምላሹም ከጃፓን ንጉሠ ነገሥት ተገቢው አንደኛ ደረጃ ሽልማትና የማለዳው የፀሐይ ጀምበር አወጣጥ የተሰኘውን ታላቅ ኮርዶን ኒሻን ተሸለሙ። ከዚያም ኅሩይ ኢትዮጵያ ለዘመናዊነት እርምጃዋ የጃፓንን ምሳሌ (ሞዴል) እንደምትመርጥ በማረጋገጥ ሲናገሩ «ንጉሠ ነገሥታችን የኢትዮጵያ መሪ በጃፓን ውስጥ ባለፉት ስድሣ ዓመታት የተደረገውን አስደናቂና ታላቅ ዕድገት በታም አድንቀዋል። የጃፓን ንጉሠ ነገሥት ግዛት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲህ ዓይነቱን ትልቅ ተግባር አሳክታ በማከናወኗ የኛ ንጉሠ ነገሥት በጣም በመገረም ስለተመሰጡበት የጃፓን ግዛት ለኢትዮጵያ እጅግ መልካም ምሳሌ (ሞዴል) እንድትሆን በዚህ አቅጣጫ

ለማነቃቃት ወስነዋል።› በማለት ገልፀው የጃፓኑ ንጉሥ ነገሥት ባለፈው የፀደይ ወራት በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የንግሥ በዓል ላይ በወኪላቸው አማካይነት ተካፋይ በመሆናቸውና ራሳቸውን ጎሩይንም የጃፓን እንግዳ በማድረግ እየሰጧቸው ስላለው ክብር ምስጋናቸውን አቅርበውላቸዋል። የጃፓኑ ንጉሥ ነገሥትም በበኩላቸው ሲናገሩ ስለ ተሰጣቸው የኒሻን ሽልማትና ከሩቅ አገርም መጥተው ጃፓንን ስለጐበኙላቸው የተሰማቸውን ደስታና ምስጋና ገልፀዋል። ከዚያም ጎሩይ በእቴጌይቱ ዘንድ አቀባበል ስለ ተደረገላቸው የኢትዮጵያን ታላቁን ኮርዶን ኒሻን ለእቴጌዋ አበርክተዋል። ከዚያም ጎሩይና ተከታዮቻቸው ከረፋዱ 5 ሰዓት በኋላ ከንጉሣዊው ቤተ መንግሥት ወደ ሆቴላቸው ተመልሰዋል። ጎሩይም ከተከዮቻቸው ጋር በመሆን በ6 ሰዓት ተኩል ላይ እንደ ገና ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመልሰው በሆሜይደን አዳራሽ ለእንግዶቹ ክብር በተዘጋጀላቸው ንጉሣዊ እይምሻ ግብዣ ላይ ተገኝተው ነበር። በዚያም ወቅት ጃፓናዊው ንጉሥ ነገሥት እቴጌይቱ ልዑሉና ልዕልቲቱ በምሳ ግብዣው ላይ ተገናኝተዋል። እንግዶቹም ከእኩለ ቀን በኋላ ከ8 ሰዓት ቀደም ብለው ከቤተ መንግሥት እንደ ወጡ የጃፓኑ ንጉሥ ነገሥትም ለጉብኝቱ ምላሽ ከቤተ መንግሥት እንደ ወጡ የጃፓኑ ንጉሥ ነገሥትም ለጉብኝቱ ምላሽ እንዲደረግ ለክብረ በዓሉ ዋና አዛዥ ሃያሺ መልእክት አስተላለፉ።

ጎሩይ ጋይሙሾ በመባል በታወቀው የጃፓን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት መደበኛውን የአክብሮት ሰላምታ ለመግለጽ ኅዳር 7 ቀን ከጠዋቱ 4 ሰዓት ጀምሮ ጉብኝት አድርገዋል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሺዴሃራም በጉብኝጡ ጊዜ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ባደረጉት ንግግር፦

«የኢትዮጵያው ንጉሥ ነገሥት ባለፈው ዓመት በተከበረው የንግሥ ክብረ በዓል ላይ የጃፓን ተወካዮች እንዲገኙ ጋብዘው ስለ ነበር እኛም ለዚህ ታላቅ ተልእኮ ጥልቅ በሆነ ስሜት ሚኒስትር ዮሺዳን ልከናል። አሁን ደግሞ በኢትዮጵያው ርእሰ ብሔር ወደ ጃፓኑ ንጉሥ ነገሥት ከተላኩት ከክቡርነትዎ ጋር በመገናኘት ደስታችን ከፍ ያለ ነው። በመሆኑም ለኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት ግዛት ብልጽግና ለሁለቱ አገሮች ዘለዓለማዊ ወዳጅነት መልካም ምኞቴን እየገለጽሁ ለኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት በጃፓንኛ ባንዛይ! እላለሁ ብለዋል።

ጎሩይም በተዘጋጀላቸው ፕሮግራም መሠረት እንቅስቃሴያቸውን እንደ ቀጠሉ ነበር። ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሺዴሃራ ጋር ከተገናኙ በኋላ የተቀደሰው ሜይዢ በተባለው ሥፍራ ተገኝተው አክብሮታቸውን ገልፀዋል። ከእኩለ ቀን በኋላም እንግዶቹ የዩኤኖን የእንስሳትና የመናፈሻ ሥፍራና በቶኪዮ ክፍለ ግዛት መስተዳደር «የቴይተንን» የሥነ ጥበብ ሙዚየም ኤግዚቢሽን ጐብኝተዋል። በምሽቱም ወቅት ጃፓናውያኑ

ጐብኚዎቹን በካብኪዛ ቴአትር አስተናግድዋቸዋል። በማግሥቱም ኅዳር 9 ቀን ጠዋት ኅሩይ ኒኮ ከደረሱ በኋላ በካናያ ሆቴል አድረዋል። ከዚያም የቶሾጉን ቤተ መቅደስ ከጐበኙ በኋላ ኅዳር 10 ቀን ወደ ሌላ ቦታ ሄደዋል። ኅዳር 11 ቀን ከረፋዱ 4 ሰዓት ጀምሮ በጃፓን የንጉሡ ነገሥቱ ቤተ መንግሥት አስተዳደር በሃማ ገለልተኛ ቤተ መንግሥት ለኅሩይ የዱር ዝይ (ዳኬ) አደንና የምሳ ግብዣ አድርጐላቸዋል።

በኅሩይም ጥያቄ መሠረት የጃፓን የጦር ሚኒስቴር ቢሮ በጃፓን ንጉሠ ነገሥት የክብር ዘበኛ ክፍለ ጦርና በዑፁኖሚያ 14ኛው ክፍለ ጦር መካከል በቶቺጋ ክፍለ ግዛት የተካሄደውን የምር ያልሆነውን የውጊያ ግጥሚያ እንዲመለከቱ አስፈላጊውን ዝግጅት አድርጐላቸዋል። ይህም የውጊያ ትርኢት በየክፍለ ጦሮች መካከል የሚደረግ መካከል የሚደረግ ከሦስት ቀን ውጊያ ግጥሚያ አንዱ ክፍል ነበር። የኅሩይ ልዑካን በኅዳር 14 ቀን ቅዳሜ ዕለት ጠዋት ከቶኪዮ ተነስተው በመጓዝ በኦምሊያና በካታኩሩ የምድር ባቡር ፋብሪካውን በዚያው ዕለት ጠዋት ጐብኝቷል። የምር ያልሆነ የጦርነት ትርኢቱ የተካሄደው በአሞይ ወንዝ ዳር ከእኩለ ቀን በኋላ 8 ሰዓት ጀምሮ ነበር። በዚያን ቀን ሌሊትም ቡድኑ አዳሩን በሳኖ አደረገ። ኅዳር 15 ቀን ኅሩይና ተከታዮቻቸው ከጠዋቱ በ5 ሰዓት በቶቺን አካባቢ የተጀመረውን የውጊያ ግጥሚያ ተመልክተዋል።

ከዚያም በናጐያ የሰነበቱት ኅሩይና ተከታዮቻቸው ኅዳር 18 ቀን ጠዋት በ2 ሰዓት ተኩል ከናጐያ ሆቴል ተነስተው የሀቶራን የዶሮ እርባታ እርሻ የጃፓንን የምድር ባቡር ፉርጐ ፋብሪካና የሚትስቡሺን የአውሮፕላን ፋብሪካ ለመጐብኘት ተጓዙ። ከቀኑ 6 ሰዓት ተኩል ኢትዮጵያኑ እንግዶች ከንቲባ አይዋ በፁሩማይ መናፈሻ በቡቴንካኩ ሬስቶራንት ባዘጋጁት የምሳ ግብዣ ላይ ተገኝተዋል። ከዚያም በኋላ እንግዶቹ የናጐያን ቤተ መንግሥት የሰገነት ማማ ተመልክተዋል። በዚያን ቀን ምሽትም ቡድኑ በአይቺ ክፍለ ግዛት፣ በናጐያ ከተማና በናጐያ የንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት በጋራ በተዘጋጀላቸው የራት ግብዣ ላይ የክብር እንግዶች በመሆኑን ተገኝተዋል። በናጐያ ክፍለ ግዛት አገረ ገዥ በናጐያ ከተማ ከንቲባና በሌሎችም ጭምር አሸኛኘት የተደረገላት ኅሩይና ተከታዮቻቸው ኅዳር 19 ቀን ከጠዋቱ በ3 ሰዓት ከ52 ደቂቃ በናጐያ ባቡር ጣቢያ ተነሥተው ወደ ኪዮቶ ተጓዙ። ኅዳር 24 ቀን ከሰዓት በኋላ ኅሩይና ተከታዮቻቸው ከናራ ተነስተው ኦሳካ ገቡ። በዚህንም ጊዜ ቀድሞ በፖርት ሳይድ ምክትል ቆንሲል የነበሩት ባሁኑ ጊዜ ግን በሳይጐን ቆንሲል የሆኑት ኩሮኪ ቶኪጂሮ ከኅሩይ ቡድን ጋር ተቀላቀሉ። ኩሮሊ ጃፓንና ኢትዮጵያ በመጀመሪያ ባደረጉት የመቀራረብ ሙከራ ዋነኛው ሰው ነበሩ። ኅሩይም ከመጓጓዣው ከወረዱ በኋላ «አሁን እያደረግን ባለው የጉብኝት ጉዞ ጃፓን ከማንም የበለጠች እንግዳን ተቀባይ መሆኗን ተገንዝቤአለሁ። በሄድኩበት ሥፍራ ሁሉ ልባዊ አቀባበልና ደማቅ መስተንግዶ ስለተደረገልኝ ምንጊዜም አልረሳውም።

በተለይም ጃፓን ይህን በመሰለ ከፍተኛ ሁኔታ ማደጓ አስደንቆኛል» ብለዋል። የክፍለ ግዛቱ በርካታ ከፍተኛ ባለሥልጣኖችና አስተዳዳሪዎች እንዲሁም የንግድ ሥራ ኃላፊዎች ለጎሩይ አቀባበል አድርገውላቸዋል። መልእክተኛውም ከባቡር ጣቢያው ተነስተው በተጓዙ ጊዜ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ተማሪዎችና የከፍተኛ ትምህርት ቤት ሴቶች ከጣቢያው ፊት ለፊት የነበሩት ሁሉ የባንዛይ ጩኸት እያሰሙ ትናንሽ የወረቀት ባንዲራዎችን ውለብልበዋል። ከዚያም ቡድኑ ወደ አሳሂ ተጉዞ የጋዜጣውን ፕሬዝዳንትና አዘጋጆችን ወደ አገኘበት አሶካ ማይቺኒ በመሄድ እየተዘዋወረ ጐብኝቷል። በተለይም የጋዜጣውን የብሬይል ዝግጅት ጎሩይ አስደሳች ሆኖ አግኝተውታል። ከዚያም የጐብኚዎቹ ቡድን በአሳካ ሆቴል ተመዘገበ። ረቡዕ ጠዋት በ3 ሰዓት ከሆቴል ተነስተው በመሄድ የአሶካን ቤተ መንግሥት ሕንፃ የአሳካን ክፍለ ግዛት አስተዳደር መሥሪያ ቤት የአሳካን ማዘጋጃ ቤትና የአሳካን የንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ጐብኝተዋል። ከቀኑ 6 ሰዓት እስከ 8 ሰዓት ድረስ ጃፓናውያኑ ስለ ጎሩይና ተከታዮቻቸው ክብር በአሳካ ክበብ በጋራ ባዘጋጁላቸው የምሳ ግብዣ አስተናግደዋቸዋል። ከዚያም በኋላ እንግዶቹ ከአሳካን የጦር መሣሪኢያ ግምጃ ቤት ጐበኙ። ከሰዓት በኋላ ወደ አመሻሹ መቃረቢያ ላይ ጎሩይ በቡንራኩዛ ቴያትር ቤት የአሻንጉሊት ቴአትር ትርኢት ተመልክተዋል። በምሽቱም ጊዜ የኮቶን (የጥጥ) ልብስ ላኪዎች ማኅበር ለጎሩይ የራት ግብዛ አድርገውላቸዋል።



# ብላቴን ጌታ ኅሩይና ኢትዮጵያውያን መልእክተኞች በጃፓን ጉብኝታቸው

እ.ኤ.አ ኅዳር 26 ቀን ጐብኚዎቹ በካኔቦ ወደ ሚገኘው ወደ ካኔጋፋቺ የሽመና ኩባንያና የቶዮ የጨርቃ ጨርቅ ሽመና ኩባንያ ሄደው ከጐበኙ በኋላ ምሳ እዚያው ተጋብዘዋል። ከዚያም በኋላ የሱሚቶሞን የመዳብ ሥራዎችና የአዙሚን የተባይ ዱቄት መድኃኒት ፋብሪካን ጐበኙ። በዚያም ማታ ወደ አፍሪካ የሽቀጣ ሸቀጥ ላኪዎች ማኅበር የራት ግብዣ ከማድረጉም በላይ በጌይሻ (ቆንጃጅት ወንዶችን በሚያዝናኑበት) ጊዜ ጋበዙዋቸው።

እ.ኤ.አ ኅዳር 27 ቀን ከኦሳካ በመኪና መጥተው ከእኩለ ቀን በኋላ በ9 ሰዓት ለደረሱት ለኢትዮጵያውያኑ መልእክተኞች የኮቤ ከተማ ልባዊ አቀባበል አድርጋላቸዋለች። የልዑካኑንም ጉብኝት «በሁለቱ ሀገሮች መካከል ንግድን የሚያጐለብት የአዲስ ዘመን መጀመር ክስተት ነው» በማለት የክፍለ ግዛቱ አገረ ገዥ ተናግረዋል። የአገረ ገዥውም ጸሐፊ የጐብኚዎቹ እንግዶች ባልደረባ በመሆን አጅበው ህዮጐ ወደሚገኘው የናይጋይ የላስቲክ ሥራ ፋብሪካ በመውሰድ አስጐብኝተዋቸዋል። በኋላም ቁጥራቸው ከሃምሳ በላይ የሆኑ በግምባር ቀደምትነት የታወቁ የንግድ ሥራ ሰዎችና የከተማዋ ባለሥልጣኖች በተገኙበት በንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ሕንፃ ስለ እንግዶቹ ክብር የሪሴፕሽን ግብዣ ተደርጐላቸዋል። በዚያን ቀን ምሽትም በአገረ ገዥው በከተማዋ ከንቲባና በንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት በኒሽቶኪዋ በጋራ በተዘጋጀው የራት ግብዛ ላይ መልእክተኞቹ የክብር እንግዶች ነበሩ።

የጃፓንን በጥሩ ስነ ሥርዓት የሠለጠኑ ወታደሮችን በማድነቅ ኅሩይ የኢትዮጵያን ወታደሮች የጃፓን ዓይነት ወታደራዊ የደንብ ልብስ በማልበስ «ልክ እንደ ጃፓን» ለማድረግ ስለወሰኑ ኦሳካ ከነእብረው ቅርንጫፍ ከሆነው የጃፓን ጦር ሠራዊት የልስብ ግምጃ ቤትና ከሌላም ሥፍራ ጭምር የቀረቧልቸውን ናሙናዎች ካዩና ከመረመሩ በኋላ ለኢትዮጵያ ሠራዊት የደንብ ልብስ እንዲያቀርቡ በማለት ኅሩይ ከቶዮና ከካኔጋፋቺ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ጋር ኦፊሲዬል ያልሆኑ ውሎችን ተዋውለውም ነበር። የወታደር ልብስ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሰፋ ለማድረግ ኅሩይ ጃፓናውያን ልብስ ሰፊዎችን ወደ አገር ቤት ለማምጣት ፈልገው ነበር። ለዚህም እንዲረዷቸው ኅሩይ ኩሮኪን ቢጠይቁም ኩሮኪ የመንግሥት ባለሥልጣን በመሆናቸው ልብስ ሰፊዎችን ለመምረጥ እንደማይችሉ ገለፁላቸው። ከዚያም በኋላ ከኦሳካ የንግድና የኢንዱስትሪ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ጋር መነጋገር ጀመሩ። ኅሩይ ወደ አገራቸው ከተመለሱ በኋላ ኢትዮጵያውያን የጨርቃ ጨርቅ ሸቀጦች ከጃፓን እንዲላኳልቸው ትእዛዝ ያስተላልፋሉ

የሚል ሀሳብ በቶሎ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ፕሬዝዳንት ዘንድ ነበር። ኩሮኪም በዚህ ረገድ መልካም ተስፋ አድሮባቸዋል።

ጎሩይ ወደ ጃፓን በመምጣታቸው የጃፓን ነጋዴዎች በተለይም በኦሳካ የሚገኙት ገበያን ለማስፋፋት በኢትዮጵያ ብሩህ የወደፊት ዕድል እንደሚኖር ግምት ነበራቸው። መሥሪያ ቤቱን በኦሳካ ያደረገው የጃፓን ብሔራዊ የጥጥ ጨርቃ ጨርቅ ላኪዎች ማኅበር ምንም ስንኳ በኢትዮጵያ ገበያ ውስጥ ከሚገኘው የጥጥ ጨርቃ ጨርቅ ከመቶ ሰማንያው (80%) በላይ የጃፓን

ምርት ቢሆንም ቀሪውን መቶኛ መጠን ከኢትዮጵያ ገበያ ውድድር ፍፁም ለማስወትት ከጃፓን ወደ ኢትዮጵያ ተጨማሪ የጥጥ ጨርቃ ጨርቅ እንዲላክ የሚያበረታታ ድርጅት ነበር። በተጨማሪም ጃፓናውያን በሴሉሎይድ ዕቃዎች ምርት በወባ ትንኝ ማጣበቂያ መድኃኒቶችና በተባይ ማጥፊያ የዱቄት መድኃኒት ሥራ፣ በላስቲክ ቦቶችና ጫማዎች በአሉሚኒየም በባርኔጣዎችና ቆቦች ረገድ የሚኖረውን የገበያ ዕድገት ከማንም ቀድመን ተገንዝበነዋል። ከዚያን በፊት ወደ ኢትዮጵያ ገበያ ያልተላኩ እንደ ሳሙና ፎጣዎችና የሱፍ ብርድ ልብሶች የመስታወትና ብርጭቆ ምርቶችና ሌሎችም ሸቀጣ ሸቀጦች ሁሉ በኢትዮጵያ ውስጥ አዳዲስ ገበያዎችን እንደሚያገኙ ተስፋ ተደርጎባቸው ነበር። በኦሳካ በቆዩባቸው ሦስት ቀኖች ውስጥ ጎሩይ የሺማዲን የመስታወት ፋብሪኢካ ጨምሮ ብዙ ልዩ ልዩ ፋብሪካዎችን ጐብኝተዋል። በዕቃዎቹ ዋጋና በጥራታቸውም ዓይነት በመደሰታቸው እንግዳው 1500 የጃፓን ዬን ዋጋ ያላቸውን የተቆረጡ መስታወቶችን ሳሙናና ሌሎችም ሸቀጣ ሸቀጦች ለናሙና ያህል ብለው ማኅበር አንድ ባለሥልጣን ኢትዮጵያውያን የጃፓንን ዕቃዎች ጥራት እንደማያደንቁና ዋጋቸው ውድ በሆኑ የሌሎች አገሮች ምርቶች ላይ እንደሚያተኩሩ በመግለጽ ቅሬታን ያሰሙ ቢሆንም ቅሉ «አሁን በጃፓን በጉብኝት ላይ ያለው የመልእክተኞች ቡድን ግን የጃፓንን ዕቃዎች ጥራት የተረዳ ስለሚመስል ለተለያዩ የንግድ ልውውጦች የሚደረጉት ድርድሮች በጃፓናውያን አምራቾችና ከኢትዮጵያም በመጡት ወኪሎች መካከል መልካም አቅጣቻን የያዙ ይመስላሉ» የሚል ተስፋ ያለውን አስተያየት ጨምረው ገልፀዋል።

ጎሩይ በጃፓን እያሉ አጼ ኃይለ ሥላሴ ለጃፓኑ ንጉሠ ነገሥት ሁለት አንበሶችን ልከውላቸዋል። እነዚህም አንበሶች እ.ኤ.አ ታህሣሥ 2 ቀን ዮኮሃማ ወደብ የደረሱት የሎይድ ትሪስቲኖ ንብረት በሆነችው ቬኒሲያ 1ኛ በተባለች መርከብ ነበር። በመጀመሪያም አንበሶቹ እንዲታዩ ሲባል የተወሰዱት ወደ ጃፓን ንጉሠ ነገሥት ቤተ መንግሥት ሲሆን ከነዚህም ቀጥሎ ወደ ኡኤኖ አራዊት መጠበቂያ ተወስደው ነብሩ ከሚገኙበት አጠገብ ካለው የብረት አጥር ውስጥ እንዲኖሩ ተደርገዋል።

በታካሃማ በጊዜያዊ ቆይታ የነበሩት ኅሩይ ሙራሳኪ ማሩ በተባለች የኦ.ኢስ.ኬ መርከብ እ.ኤ.አ 3 ቀን ኮቤ የገቡ ሲሆን ከዚያም ቡድኑ ወዲያውኑ በመኪና ወደ ኦሳካ ሄዷል።

እ.ኤ.አ ታኅሣሥ 12 ቀን 1931 ዓመተ ምሕረት ኢኑካይ ፀዮሺ የጃፓን አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር በሆኑ ጊዜ ኅሩይ ከእርሳቸው ጋር ለመገናኘት ጥያቄ በማቅረባቸው ከሦስት ቀናት በኋላ ከአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር ለመገናኘት ችለዋል። ይህም የኅሩይ የመጨረሻውና ታላቁም ግንኙነት ነበር። እ.ኤ.አ ታኅሣሥ 28 ቀን 1931 ዓመተ ምሕረት የኅሩይ ቡድን ጉብኝቱን ፈጽሞ ከጃፓን ወጥቶ ሄዷል። ቡድኑ በጃፓን ውስጥ አርባ ቀኖች ያህክ አሳልፏል። እ.ኤ.አ በታኅሣሥ 15 እና 28 መካከል ምንስ ተደረገ?

# የኅሩይ ጉብኝት ውጤቶች

ጉዞው ኅሩይና ከእርሳቸውም ጋር የተጓዙትን ስሜታቸውን መንካቱ ግልጽ ነበር። ጃፓን እስኪደርሱ አንድ ወር የፈጀው ረጅም የባህር ላይ ጉዞ በህንድ፣ በሲንጋፖር፣ በኢንዶቻይናና በሻንጋይ መርከባቸው እየቆመች የተጓዙበት ሁኔታ ነበር። በጉዞዋቸው በየደረሱባቸው ሥፍራዎች ሁሉ እስያውን በነጮች ቅኝ ገዥዎች ሥር የሚገዙ መሆናቸውን አዩ። በንጽጽር ጃፓን ግን ወዳጅነት ዘመናዊነት ብሩህነት የተመላባት ጠንካራና ነፃ ሆና የታያቸው አገር ናት። በተለይም ለኢትዮጵያውያኑ አስደናቂ የሆነባቸው በወቅቱ ከተወሰኑ ጥቂት ሰዎች በስተቀር ማንም ከማያገኛቸውና ልክ እንደ ጣዖት ዓይነት ከሚቆትሩትና ከሚመለኩትም የጃፓኑ ንጉሠ ነገሥት ጋራ አብረው የሙብላትና የመጠጣጣቸው ጉዳይ ነበር። ኅሩይም በየዕለቱ የሚሰማቸውን ስሜት ሁሉ በጽሑፍ እንዲከትቡላቸው ለአርአያ አበበ በቃል እየነገሩ ስለሚያጽፉዋቸው እነዚህን ማስታወሻዎቻቸውን በመጠቀም እ.ኤ.አ 1932 ዓመተ ምሕረት ማኅደረ ብርሃን - ሀገረ ጃፓን በሚል ርዕስ አንድ መጽሐፍ በአማርኛ ደርሰዋል። በ58 ባለ ቀለም ፎቶግራፎች የታተመውን የዚህን መጽሐፍ እትም የጉቢ ሴባህ ማተሚያ ቤት እያንዳንዱን ኮፒ በ3 ተኩል ማሪያቴሬዛ ብር ሲሸጥ በቀለም ያላጌጠውን ደግሞ አንዱን ኮፒ በ2 ተኩል ማሪያቴሬዛ ብር ሸጦአል። ይህም መጽሐፍ ጃፓንን በቁም ነገር ለአፍሪካውያን ለማስተዋወቅ በአፍሪካዊ ተወላጅ የተሞከረበት የመጀመሪያው መጽሐፍ ነበር። የጃፓኑ የቀድሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሺዴሃራ ኪጁሮ እ.ኤ.አ በ1934 ዓመተ ምሕረት በቶኪዮ ውስጥ ለታተመው «ታላቋ ጃፓን» ለተሰኘው የዚህ መጽሐፍ የጃፓንኛው ትርጉም መጽሐፍ የመግቢያ መልዕክቱን የጻፉለት ሲሆን ጃፓናውያን የመጽሐፉ አንባቢዎችም ታሪኩን ያነበቡት በከፍተኛ ጉጉትም ነበር። የኅሩይ የጉብኝታቸው ጉዞና

ተከታትሎም የታተመው መጽሐፋቸው ኢትዮጵያ ወደ ዘመናዊነት ለመለወጥ በምታቅደው እርምጃ የጃፓንን አርአያ ትከተል ይሆናል የሚለውን የምዕራባውያን መንግሥታትን ሥጋት አባብሶትም ነበር።

ኅሩይ የጃፓን ተልዕኮአቸውን ፈጽመው ወደ ኢትዮጵያ በተመለሱ ጊዜ ሁለት ጃፓናውያን አብረዋቸው መጥተዋል። የመጀመሪያው አንድ ታዳ የተባለ ልብስ ሰፊነት ለ3 ወራት ጊዜ ብቻ ኅሩይ ዘንድ የቆየ ሲሆን ሁለተኛውም ሰው ዶክተር ያማውቺ ማሶኦ ግን ጠቃሚነታቸውን ይበልጥ ሊያስመክሩ የቻሉ ናቸው። እርሳቸውም የኢሚግሬሽን ሚኒስቴር ወኪል በመሆን ከሰሩ በኋላ የኦሳካ ማይኒቺ ጋዜጣ ልዩ ጋዜጠኛ ሆነዋል። በሁለቱም የሥራ ምድቦቻቸው በቆዩባቸው ጊዜ ሁሉ አንዳንድ የአማርኛ ቃላትን ለማወቅ ምንም ያህል ጊዜ ያልወሰደባቸው ሲሆን በጃፓንና በኢትዮጵያ መካከል የመቀራረብን ግንኙነቶች ያዳበሩ ሰው ናቸው። በኤውሮፓውያን ዘንድ ብዙ ድንጋጤን የፈጠረውን በኢትዮጵያ የጃፓንን የንግድ እንቅስቃሴ በግንባር ቀዳሚነት ያበረታቱም ናቸው። ለማኡቺም ታታሪነት «ለችሎታቸውና ለአለመታከታቸውም» አድናቆታቸውን የገለፁትን የእንግሊዙን ሚኒስትር ያስገረመ ሁኔታ ነበር። እንግሊዛዊው ሚኒስትርም «የጃፓናውን ተወዳዳሪነት የሚያማርሩት» የኤውሮፓ ነጋዴዎች እንደ ጃፓናውያን ብርቱዎቹና ተግባራውያን ያልሆኑ ናቸው» በማለት የተሰማቸውን የቅሬታ ስሜት ገልፀዋል።

የጃፓናውያን አቀራረብና ግንኙነት በተለይም ኢጣሊያውያንን ሊያስጨንቃቸው የበቃ ጉዳይ ነበር። እ.ኤ.አ 1906 ዓመተ ምሕረት የተደረገው የፈረንሳይና የኢትዮጵያ ስምምነትና እ.ኤአ. 1928 ዓመተ ምሕረት በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል የተፈረመው ውል ሁለቱም በኢትዮጵያ ውስጥ የኢጣሊያ አቋም ያፀኑና ማንም ሊነካው የማይችል የተቀደሰ መብት ያደርጉታል በማለት ሮማ ተናግራለች። ሆኖም ግን በማንኛውም ወገን በተለይ በአሜሪካውያንና በጃፓናውያን የሚደረግ ጣልቃ ገብነት ኢጣሊያን በፍርሃትና በድንጋጤ እንድትጨነቅ አድርጓታል። በዝያንም ወቅት በሮም ውስጥ ሆነው ሪፖርቶችን ከሚያነቡት ይልቅ በቶኪዮ የነበሩት የኢጣሊያ ወኪሎች ይበልጥ በተረጋጋ ሁኔታ በጃፓን ይፈፀም የነበረውን የኅሩይን ተልዕኮ ዕድገትና መሻሻል በቅርብ ሆነው ኃላፊዎቻቸው ይልቅ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት የኢጣሊያ ወኪሎች በደመኛነት መልክ ብዙ ጊዜ የጃፓንን ጥረቶች ውጤቶችና ስኬቶችንም ሲያቃልሉ ነበር። የኅሩይ የጃፓን ጉብኝት ለጃፓናውያን በብዛት ቁጥር ወደ ኢትዮጵያ መግባት (ፍልሰት) በሩን የሚከፍት ቁልፍ ሊሰጣቸው ይችላል ከሚለው ፍርሃት አኳያ ቢሆንም በኢትዮጵያ የነበሩት የኢጣሊያ ወኪሎች እ.ኤ.አ 1932 ዓመተ ምሕረት መጀመሪያ ገደማ የኢትዮጵያ ንጉሠ

ነገሥት ቤተ መንግሥት ሁለት ጃፓናውያን ብቻ እነዚህም አንድ ባልና ሚስት ባልዬውን በወጥ ቤትነት ሴቲቱን በቤት ሠራተኝነት የቀጠረ መሆኑን አስታውቀው ነበር።

የጎሩይ የጃፓን ጉብኝትም ለጃፓን በጠቀመ መልኩ ሲታይ የጃፓንንና የኢትዮጵያን ግንኙነቶች በጉልህ ሁኔታዎች እጅግ በጣም ከፍተኛ ወደ ሆነ ደረጃ ያደረሰና ከጥቂት ዓመታትም በኋላ በኢትዮጵያ ላይ የደረሰውን የኢጣሊያን ወረራ አስመልክቶ በጃፓን የሕዝቡ ድጋፍ ለኢትዮጵያ ለማስጠት ያበረታታ ሁኔታ ነበር። በተጨማሪም ደግሞ የጎሩይ የጃፓን ጉዞ የተጉዢን የወደፊት ዘመነ ሕይወት ሙያ የሚያመለክትና የእርሳቸውም የጃፓንን ዕድገት መንገድ አርአያነቱን ማድነቃቸው በአፍሪካ ምድር ሁለተኛዋን ሌላ ጃፓን ለማየት የማይፈልጉትን ምዕራባውያን ኃይሎችን ያስደነገጠ ሁኔታ ነበር።

ከጎሩይ ጉዞ ሁለት ያክል ዓመታት በኋላ ተዘዋዋሪው ጋዜጠኛ ላዲስላስ ፋራጐ የጎሩይን ጉብኝትና ያስከተለውንም ሁኔታ አስመልክቶ «ከቡርነትዎ ወደ ጃፓን ስለሚያደርጉት ጉብኝት ሲናገሩ ነበር። ጉዳዩ በወቅቱ ትልቅ ሁከት የፈጠረና በርካታ ሀሜቶችንም ያነሳሳ ነገር ነበር። ለመሆኑ ወደ ጃፓን ለምን ሄዱ?» ሲል ጠየቃቸው። በሰጡትም መልስ፡-

> «ይህ ጥያቄ ሁልጊዜ የሚጠየቅ ጥያቄ በመሆኑ እኔም እጠብቀው ነበር። ደግሞም ዲፕሎማቲክ ሳልሆንና በግልፅም እወንቱን መናገር ለኔ አስቸጋሪ አይሆንብኝም። እኛ አንዳችም ዓይነት ድብቅ ዓላማ ስለሌለን የፈለግነው ነገር መስጢራዊ አይደለም። ጃፓን ከታላላቆቹ ኃያላን አገሮች አንዷ በመሆን እያደገች በመምጣት ላይ እንደመገኘቷ ሌሎች ታላላቅ አገሮችና ሕዝቦች በአዲስ አበባ ወኪሎቻቸው እንደሚገኙ ሁሉ ጃፓን ግን በግርማዊነታቸው ቤተ መንግሥት በክብር ቆንሲል እምብዛም አልተወከለችም ነበር። ከጃፓን ጋር ዲፕሎማቲክ ግንኙነት መጀመር ለኛ ትልቅ ነገር በመሆኑ ዋነኛው የጉዞዬ ምክንያት ይህ ነው። ሁለተኛው ምክንያት ሙሉ በሙሉ ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ነው። ሕዝባችን ደሀ እንደ መሆኑ ሁሉ ወደ ውጭ የምንልከውም ወጪ ንግዳችን በኢኮኖሚ ማሽቆልቆል (ሪሴሽን) በዓለም በሚታየው ችግር ምክንያት መጠኑ እጅግ ቀንሷል። የዕለት መጠቀሚያ ዕቃዎችን በርካሽ ዋጋ የምናገኝበትን ምንጭ መፈለግ የነበረብን ሲሆን ዕቃዎችን በተለይም ሀገራችን ባሁኑ ወቅት በብዙ መጠን የምታስገባውን የጥጥ ጨርቃ ጨርቅና ምርት በርካሽ ዋጋ በመሸጥ ጃፓን በዓለም የታወቀች ሀገር ናት። የምንፈልገውን አብዛኛውን የጥጥ ጨርቃ ጨርቅና ምርት እናገኝ የነበረው ከአሜሪካ ነበር። ነገር ግን ጃፓን ይህንኑ የጥጥ ምርት ሰማንያ በመቶ እጅ (80%) በቅናሽ በርካሽ ዋጋ ማቅረብ ስለምትችል የምንፈልገውን ከእርሷ እንገዛለን። ወደ ሀገር ውስጥ

ከምናስገባቸው ዕቃዎች ግማሹን የጥጥ ምርትና ጨርቃ ጨርቅ በመያዙ «የጃፓን ወረራ» የሚለው የተለመደ አባባል በዚህ ሀገር ውስጥ እውነተኛ ትርጉም አለው። » በማለት መልሰውለታል።

ኅሩይም ከሚፈልጉት በላይ ዲፕሎማሲያዊ ነበሩ። ከጃፓን መንግሥትም የጦር እምሣሪያና ጥይቶችን ለማግኘት ጠይቀው ነበር። ይሁንና ግን ቶኪዮ በዚያን ጊዜ የማንቹሪያን ግጭት እየተጋፈጠች ስለ ነበረ ለኢትዮጵያ የጦር መሣሪያዎችንና ጥይቶችን ከማቅረብ አልፎም ሌሎች የተለዩ ሥጋቶችም ነበሩባት።

ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመውጋት በተዘጋጀችባቸው በርካታ ዓመታት ወቅት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኅሩይ የኢትዮጵያን ነፃነት ለመጠበቅ በቂ የሆኑ የቃል ኪዳን ወዳጅ አገሮችን (የጦር ጓደኞችን) ወይም የጦር መሣሪያዎችን ለማግኘት አልቻሉም ነበር። ምንጊዜም የኃይለ ሥላሴ ታማኝ አማካሪ የነበሩት ኅሩይ በኢጣሊያ ከተደረገው ጥቃትም በኋላ እ.ኤ.አ 1936 ዓመተ ምሕረት ከነገሥቱ ጋር በስደት ሄደው በእንግሊዝ ሀገር ሞቱ።

## <u>የዚህ ጽሑፍ ሁለት ተጨማሪ መረጃዎች (ፖስትስክሪፕትስ)፦ የጋብቻ ዕቅድ የጦር መሣሪያዎችን ለማግኘት ዳባ ብሩ ያደረጉት ተስፋ አስቆራጭ ፍለጋ።</u>

ኅሩይ ወደ ጃፓን ካደረጉት ጉብኝት ሁለት አስደሳች ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴዎች ተፈጥረዋል። የመጀመሪያው እንቅስቃሴ አርአያ አበበን የሚመለከት ጉዳይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የኅሩይ አስተርጓሚ የነበሩትን ዳባ ብሩን የሚመለከት ነበር።

የአጼ ኃይለ ሥላሴ የሥጋ ዘመድ የሆኑት አርአያ አበበ ኢትዮጵያን ጃፓናዊ በማድረጉ እንቅስቃሴ ውስጥ የነበራቸው ሚና አነስተኛ ነበር። በነበሯት ግንኙነቶች ጠቃሚ ሚና የነበራቸውና የኢጣሊያና የኢትዮጵያ ጦርነት እስከተጀመረበት ጊዜ ድረስ በሁሉም ረገድ ትላልቅ ነገሮችን ለማከናወን የተዘጋጁ ሰው ነበሩ። አርአያም የጃፓንን አርአያነት ለማስፈን ያቀዱትን ወገኖች የራዕይ ምኞተኞች አድርገው ከመመልከት ባለማለፍ እኚህ ሰው በዛሬው ጊዜ የሚታወሱበትም ነገር ቢኖር ትልቅ ደስታን ባስከተለውና በብዙ አውሮፓውያን ታዛቢዎችም ዘንድ ትልቅ ፍርሃትን ስለፈጠረው ከጃፓናዊቷ ኩሮዳ ማሳኮ ጋር ለመጋባት እያደር እያደገ የመጣው ዕቅድ ሁኔታ ነበር። እ.ኤ.አ 1931 ዓመተ ምሕረት ከግል ወዳጃቸውና ጃፓናዊት ሴት ለማግባት የነበራቸውን ፍላጎት አርአያ ገልፀው ነበር። ይህም የአርአያ ሀሳብ በውስጣቸው የነበራቸውን

ጃፓናዊነትን የመላበስ ሁኔታና በባህላዊ መልኩም ታዛዥ ነበር። የአርአያን ፍላጎት የተገነዘቡት ኅሩይም የታቀደው የጋብቻ ሀሳብ በኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያደርጋል። እንዲሁም እርሳቸው ወደ ጃፓን በሚያደርጉት ተልእኮ ውስጥ ጣልቃ ይገባል በሚል ፍራቻ ገና ከጅምሩ ሀሳቡን ቀጩት።


ጃፓን በፖለቲካ በንግድና በወታደራዊ መስኮች በኢትዮጵያ ውስጥ ጣልቃ የመግባቷ ሁኔታ በለንደን በፓሪስ፣ በሞስኮና በሌላም ሥፍራ ሁሉ ለነበሩ የመንግሥታት መሪዎች ሥጋት ስለሆነባቸው እ.ኤ.አ 1934 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ የወረራ ዝግጅት ለማድረጓ ተገቢው ምክንያት እንደሆነም መስሎ ታያቸው። እ.ኤ.አ 1933 እና 1934 ዓመተ ምሕረት የታቀደው የአርአያ ጋብቻም በሚያናድድ መልኩ ጭምር ለነዚህ ጣልቃ ገብነቶች ተገቢ ምክንያት ሆኗል።

አንድ የተጋነነ ታሪክም ስለሁኔታው በክርክር መልክ ሲገልጽ «ቁጥራቸው 2000 በሚሆኑ ብቁ ጃፓናውያንና በአቢሲኒያ ተወላጅ ሴቶች መካከል ቅይጥ ጋብቻዎችን ለማስፈጸም እቅዶች ተዘጋጅተዋል። በማለት ይህም በነጮች ዘር ላይ የተባበሩ ክልስ ሕዝቦችን አመፅ የሚመቱ አዲስ የመሪዎችን ዘር ለማስገኘት የታቀደ ግልጽ ፖሊስ የጃፓናዊው ልዑል ኩራዶ (ኩሮዳ) ሴት ልጅ የሆነችው ልዕልት ማሳኮ ከኢትዮጵያዊው ልዑል ከልጅ አየለ (አርአያ) ጋር በሚደረግ ጋብቻ ሊመረቅ ነበር» ብሏል።

ይህንንም ጋብቻ ንጉሣዊኢ ሠርግ ይሆናል በማለት አውሮፓውያን በስሕተት በማመናቸው የታቀደው ጋብቻ ኢትዮጵያ ለዘመናዊነት እርምጃዋ ጃፓንን ሞዴሏ ለማድረግና ለኢትዮጵያ ካላት የስሜታዊነት ራዕይ የተፈጠረ ጉዳይ አድርገው ተመልክተውታል።

ይህም ሁኔታ አርአያና ኩሮዳ ዝግጅት በተደረገበት ጋብቻ ለመጣመር ያላቸውን አነሳሽ ምክንያት የሚገልጽ ሲሆን ሌሎች ግለሰቦችም በጉዳዩ እንደተሳተፉበት ታውቋል። ከነዚህም መካከል እጅግ የታወቁት በጃፓንና በኢትዮጵያ መካከል በሚደረጉ የንግድ ልውውጦች ለራሳቸው ጥቅምን ለማግኘት ሲሉ የጋብቻውን እቅድ ወደ ከፍተኛና ግልጽ ደረጃ በማድረስ ያስተዋውቁ የነበሩ አያሌ ያፓን ኤሽያን ናሽናሊስት ጃፓናውያን ሲሆኑ ከነርሱም አንዱ ያማኡቺ ነበሩ። በቶኪዮም ሆነ ወይም በአዲስ አበባ የነበረ ማንኛውም መንግሥት የጋብቻውን ሀሳብ አለመደገፉ የሚያስገርም እንደ መሆኑ የጋብቻው ጉዳይ እ.ኤ.አ 1934 ዓመተ ምሕረት በከሰመም ጊዜ ማንኛውም ወገን ኀዘኑን አልገለፀም ነበር። በዚህ የጋብቻ እቅድ ምክንያትም ሁለት መንግሥታት ዓለም አቀፋዊ ችግር ደርሶባቸውም ነበር።

የታቀደውም የጋብቻ ጥምረት ከቀረ በኋላና ከተቋረጠም ረጅም ቢያልፍም ነገሩ ኢጣሊያኖች ክፉኛ ሲከነክናቸው ነበር። ጉዳዩ የተፈራው የተሠጋበትን የፖሊሲ አቅጣጫ እንዳልያዘና በተግባርም እንዳልተፈፀመ ካወቁበት ጊዜ በኋላ ስለ ጉዳዩ መጻፋቸውን ቀጥለውም ነበር። ለምሳሌም ያህል እ.ኤ.አ 1936 ዓመተ ምሕረት የታተመ አንድ የኮሚኒስት መጽሐፍ «ጃፓኖች የአቢሲኒያ ልዑል የጃፓን ባላባት በማግባት በኩል በኢትዮጵያ ውስጥ አስፈላጊ የአየር ማረፊያዎችን በማቅረብ እና የጥጥ ምርት የጋራ ስምምነት ለማግኘት ችለው ነበር።» ብሎ የብዙዎችን ጭንቀት እና አሳብ ባስተጋባበት ጊዜ ገልጿል። በእርግጥም የእነዚህ መግለጫዎች ስህተትነት ለሞስኮውም ሆነ ለሌሎች በርካታ ሀገራት እና ወገኖች ከባድ ፀረ - ጃፓን እና ፀረ - ኢትዮጵያ ክርክሮችንና ተቃርኖዎችን ለማግኘት ከነበራቸው ፍላጐት ይልቅ ጠቀሜታው አነስተኛ እንደ ነበር ታይቷል።



ብላቴን ጌታ ኅሩይና ተከታዮቻቸው በጃፓን አገር ጉብኝታቸው

ሁለተኛው ዲፕሎማሲያዊ የመረጃ ጽሑፍ የኅሩይን አስተርጓሚ ዳባ ብሩን የሚመለከት ነበር። ኢጣሊያ በምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ጦርነት ለመክፈት እየተጣደፈች

በነበረበት እ.ኤ.አ 1930ዎቹ የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ኢትዮጵያ የኢጣሊያን ታላቅ ኃይል ከእርሷ አቅም ጋር ለማመጣጠን የውጭ ፖለቲካ የወታደራዊ እና የኢኮኖሚ እርዳታ ፈልጋ ነበር። ይሁን እንጂ ኢጣሊያኖችን እና በጃፓን መንግሥት ውስጥ የነበሩ ብዙዎቹን በጣም ባበሳጨ ሁኔታ ከጃፓን ፓን - ኤሽያን ብሔርተኞች ይበልጥ ማንም ተስማሚ ምላሽ አልሰጠም። በመሆኑም እ.ኤ.አ 1935 የበጋ ወራት ላይ ጦርነቱ እየቀረበ ሲመጣ ኢትዮጵያ በጠረፍ ላይ የነበረው ሠራዊቷ በየዕለቱ ምንም ላያገኙ መሣሪያ እናገኛለን በማለት ወደ አዲስ አበባ በመጉረፋቸው የኢትዮጵያ ስንቅ እና ትጥቅ አቅርቦት ከመቼውም ይበልጥ ለማግኘት ሆነ። ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ የጦር መሣሪያ እና ጥይቶችን ለማግኘት ፈልገው ተስፋ አቆራጭ በሆነ መልኩ ዳባን ወደ ጃፓን ለመላክ እና የታዋቂ ጃፓናውያንን ስሜት ለመሳብ በዕድሉ ለመጠቀም ወሰኑ። ለማስመስያነትም ዳባ በኦሳካ የሚገኘው የኢትዮጵያ የክብር ቆንስላ የመጀመሪያ ጸሐፊ ሊሆን ነበር። ስለሆነም ፓን - ኤሽያን ብሔረተኛና ለኦሳካ ማይኒቺ ቃል አቀባይ የሆኑት ሾጂ ዩኒሱኬ የተከተሏቸው ሲሆን የእርሳቸውም ጋዜጣ የጉዞውን ወጪ በመሸፈን ስፖንሰር አድርጓል። ሶጂ አርአያ ከኩሮዳ ጋር የነበራቸውን የጋብቻ ዕቅድ ንቃት በተሞላችበት ሁኔታ ያበረታቱ እና ያስተዋወቁ ነበር።

ዳባ እባ ሾጂ እ.ኤ.አ 13 ቀን ጃፓን የደረሱ ሲሆን ኢጣሊያ ደግሞ ከሦስት ሣምንታት በኋላ ኢትዮጵያን በማጥቃት ወረረቻት። ምንም እንኳ በርካታ የጃፓን ብሔረተኞች ለዳባ ጥልቅ ስሜት ያለበትን አቀባበል ያሳዩአቸው ቢሆንም በቶኪዮ ያለው መንግሥት ግን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ኢጣሊያ ለመቃወም ፈቃደኛ አለመሆኑን አረጋገጠ። በሩቅ ሀገር በሚካሄድ የጦርነት ቴአትር ውስጥ ተጋፍጦ እንዳይወጣም የጃፓን መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት ጥቅሞቹ እጅግ አነስተኛውም መልኩ ጃፓን ዓለም ዓቀፍ ግንኙነቶችን ያስቀደመች ሲሆን በማንኛውም መልኩ ለምሥራቅ አፍሪካ የምትሰጣቸው እርዳታዎች ጥቂት ነበሩ። የሕዝብ ስሜት በፖሊሲ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር እንደሌለበት የጃፓን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እና የጃፓን ጦር ሠራዊት የተስማሙበት ሲሆን መንግሥቱም ገለልተኝነትን አጥብቆ የሚይዝ እና የምሥራቅ አፍሪካን ግጭት በእርጋታ እንደሚመለከት እንዲሁም የሊግ ኦፍ ኔሽንስን ፖሊሲ ሙሉ በሙሉ ችላ እንደሚል በግልፅ አስታወቀ። ጃፓኖች ምንም ዓይነት ብድር የጦር መሣሪያ ጥይት፣ የበጐ ፈቃድ ሠራተኞች ወይም ወታደራዊ ልዑካን በማናቸውም መልኩ ወሮታውን መክፈል ለማትችለው ለኢትዮጵያ እንደማይልኩ ለዳባ ሳይሆን ለኢጣሊያኖች ነግረው ነበር። በመሆኑም ቶኪዮ እ.ኤ.አ በጥር 1936 በአዲስ አበባ ከተማ የጃፓንን አዲስ ለጋሲዮን የሚከፍተውን ሚኒስቴርን በጊዜያዊነት ለመሾም በዝግጅት ላይ ባለችበት እ.ኤ.አ በታኅሣሥ 4 ቀን ባወታቸው መመሪያ በኩል የዳባን ጥያቄዎች ውድቅ አደረገች። እ.ኤ.አ ጥር 23 1936 ኀሩይ አነስተኛ መጠን ያላቸው ቀላል

መሣሪያዎችን ከጃፓን ለማዘዝ በአዲስ አበባ ውስጥ አዲስ የተከፈተውን የጃፓን ሌጋሲዮን የጐበኙ ቢሆንም፣ ዳባ ካከናወኑት የተሻለ ነገር አላደረጉም።

ከጃፓን ብሔረተኞች አንዱ እ.ኤ.አ 1931 በተደረገው የጎሩይ ጉብኝት፣ በአርአያ የጋብቻ እቅድ ውስጥ በንቃት የተሳተፉ ሲሆን አሁን ደግሞ በዳባ ጉብኝት በደጋፊነት የታዩት ሱማዮካ ቶሚዮሺ ነበሩ። እ.ኤ.አ በመጋቢት ወር መጨረሻ ላይ ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በተላከ ደብዳቤ በልበ ሙሉው ንጉሠ ነገሥት የሚታዘዘው ጀግናው የኢትዮጵያ ሠራዊት ጠላቶቹን እንደማያሸንፍ ተንብየው ነበር። ደብዳቤውም የዳባን ተግባራት እንደሚከተለው በማድነቅ እና ተንብየው ነበር። ደብዳቤውም የዳባን ተግባራት እንደሚከተለው በማድነቅ እና በማሞገሱ የቀጠለ ሲሆን «ዳባ በጃፓን ውስጥ ለ6 ወራር ያህል በቆዩበት ጊዜ ሁሌ ክብር እና ዝና ያገኙ ነበር። እንዲሁም በማናቸውም። ጊዜ ቢሆን የአቢሲኒያ ክብር በእርሳቸው እጅ ችግር አልደረሰበትም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሄሮታ በግል ጉባኤያቸው /ኮንፈረንስ/ ውስጥ ሁለት ጊዜ ዳባን የተቀበሏቸው ሲሆን በተሰናበቱበትም ወቅት እስከ በሩ ድረስ በአካል ሸኝተዋቸዋል» ይላል።

«የጃፓን ሕዝብ ለአቢሲኒያ ያላቸው በጐ ፈቃድ ዳባ፣ ኮቤ ላይ በደረሱ ጊዜ እና ቶኪዮ ጣቢያ በደረሱ ወቅት በተደረገላቸው የሞቀ አቀባበል እንዲሁም ድርጅቶች እና ግለሰቦች የአቢስኒያን ሕዝብ ለመርዳት የሕክምና መሣሪያዎች ገንዘብ እና ሌሎች ዕቃዎችን ለመላክ ባደረጉት ጠንካራ እንቅስቃሴ በግልፅ የታየ ነው» በማለት ደብዳቤው ገልጿል።

የሱሚዮካ መግለጫ አውቆም ሆነ ተሳስቶ ሕጋዊ /ኦፊሴላዊ/ በሚመስለው የዳባ ጉብኝት ላይ በግልፅ ትኩረት ሰጥቷል። እንዲሁም ሱሚዮካ ስለ ዳባ ጉብኝት የሥራ ስኬት ውጤቶች የዘረዘረው፣ ማለትም ዳባ ሁለት ጊዜ ሂሮታን እንደጐበኙ እና በሚኒስትሩም እስከ በር ድረስ እንደ ተሸኙ፣ ዝርዝር መግለጫዎች ባይኖሩም በመርህ ደረጃ ስምምነት ላይ መድረሳቸውን በርካታ ጃፓኖች በጥቅል ጉጉት እና ስሜት የተቀበሏቸውም መሆኑ አንዳንድ ጥቂት ቡድኖች ጥቂት የሕክምና መሣሪያዎችን መላካቸውን እና ዳባም ራሳቸውን አለማሳፈራቸውን በመግለጽ የሠፈረው ሀተታ፣ የዳባ ጉብኝት ያገኘው ወይም ሊያገኘው ይችል የነበረው ስኬት ምን ያህል አነስተኛ እንደ ነበር በቀላሉ የሚያንፀባርቅ እንደ ነበር። በቶኪዮ የነበረው የኢጣሊያ አምባሳደር የተሰማማበት ጉዳይ ነበር። እንዲሁም የዳባን ተግባሮች እና ሙከራዎች የተከታተለው ያለ ዕቅድ ነበር። በመጋቢት ወር መጨረሻ ላይ ዳባ ከቶኪዮ መነሳታቸውን አስመልክቶ ለሮም ባቀረበው የሪፖርት ዝርዝር ላይ ዳባን በጣቢያው ተገኝተው የሸኙትን 200 የሚያህሉ ኋላ ቀርና አድኃሪ የብሔረተኛ ማህበራት አባላት እንደ ነበሩ ገልጿል። ለዳባ የሰጡት ስንቅ እና ትጥቆች ጥራታቸው አነስተኛ የሆኑ ጥቂት ናሙናዎች ብቻ እንደ ነበሩ

እና የለማቋረጥ የጠየቁት ዓይነት ጠመንጃ አንድ እንኳ እንዳልተካተተ ከጦር ሚኒስቴር ማረጋገጫ ማግኘቱንም ያመለከተ ሪፖርት ነው።

ዳባ በጃፓን ውስጥ 7 ወራት ከቆዩ በኋላ እ.ኤ.አ የካቲት 2 ቀን ወደ እናት ሀገራቸው በመርከብ ተመለሱ። ዳባ ምንም እንኳ በቀኝ ክንፍ ድርጅቶች በተዘጋጀው የመሸኛ ግብዣ ላይ ላለመገኘት ቢወስኑም፣ ከመሄዳቸው በፊት ከኦሳካ ማይኒቺ ጋዜጣ ጋር ባደረጓቸው ቃለ ምልልስ ወቅት ፊታቸው ያልተፈታ ነበር። እ.ኤ.አ የካቲት 17 ቀን በተካሄደው ፕሬስ ኮንፈረንስ የጃፓኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ሲናገሩ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን አሸንፋ ካስከበረች ጃፓን በዚያ ክልል ውስጥ ያሏትን መብት እና ጥቅሞች ለማስጠበቅ ራሷን ችላ ተግባሯን እድነምትፈጽም የገለፀች ሲሆን ጃፓን ከኢትዮጵያ ጋር የወዳጅነት እና የንግድ ስምምነት እንዳላት እና በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው የንግድ ልውውጥም እየጨመረ እንደነበር አመልክተዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኢትዮጵያ ሠራዊት በብቃት አልታጠቀም፣ አልሰለጠነም ወይም የኢጣሊያንን ወረራ ለረጅም ጊዜ ተቋቁሞ እንዲመክት በስኬታማነት አልተመራም። ስለዚህም የኢጣሊያ ሠራዊት እ.ኤ.አ በግንቦት ወር 1936 በታኅሣሥ 12 ቀን ለኢጣሊያ ባለሥልጣን እጃቸውን በመስጠት ፓስፖርት ተቀበሉ።

ቶኪዮም ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ግዛት ላይ ካገኘችው የወረራ ድል ጋር ራሷን አስማማች። በመሆኑም እ.ኤ.አ ታህሣሥ 1936 በተደረገው የዕውቅናቸው መለዋወጥ ሁኔታ፣ ማለትም ጃፓን ማንቹኮን በወረራ ድል መንሳቷ እና ኢጣሊያም ኢትዮጵያን በወረራ መያዟ በቶኪዮ እና በሮም መካከል ለሰፈነው ዕርቅ እና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት እያደር ለተከሰተው ኅብረታቸው መንገድ ጠራጊ ሆነላቸው።

እርግጥ ቶኪዮ ኢትዮጵያ በዳባ ተልእኮ አማካይነት እጅግ በጣም ፈልጋው የነበረውን የጦር መሣሪያ ዝውውር እና ሥልጠና አለመስጠቷን ጠቅሳ ለንጽሕናዋ ያቀረበቻቸውን በርካታ መግለጫዎች ኢጣሊያኖች ባያምኑ ኖሮ ሮም እና ቶኪዮ እንዲህ ዓይነት ፈጣን የአስተሳሰብ ለውጥ አይኖራቸውም ነበር። ምንአልባትም ጭራሽ ባልነበራቸውም ነበር። ነገር ግን ይህ ዓይነቱ የአስተሳሰብ ለውጥ ነበራቸውም ወይም አልነበራቸውም። እ.ኤ.አ 1935 ሙሉን ዓመት በ1936 አብዛኛውን ወቅት በተለይ በለንደን፣ በፓሪስ፣ እና በሞስኮ ውስጥ ለመጪው የኢጣሊያ ድል እና ገድል ከፍተኛ ዓለም አቀፍ ተቃዋሚን በተሳካ ሁኔታ ትጥቅ ለማስፈታት ጃፓኖች በኢትዮጵያ ውስጥ ድንተገኛ ወረራ እንዳደረጉ ጭምጭምታ እና ሃሜቶችን በሚገባ ተጠቅመውባቸው ነበር። እንደ እውነቱ የዳባ ጉብኝት በሾጂ እና ኦሳካ የሕዝብ ትኩረት በአደባባይ

ለማግኘት ከተመቻቸው ሁኔታ ሌላ ስኬትን ለማግኘት ምንም ዓይነት እውነተኛ ድል አልገጠመውም።

# ዋቢ መጽሐፍት

## ቀዳሚ ምንጮች

ኢጣሊያ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የዲፕሎማቲክ ሰነዶች ኅትመት ኮሚሽን፣ /የኢጣሊያ የዲፕሎማቲክ ሰነዶች/ 7ተኛ ተከታታይ እትም እ.ኤ.አ 1922 – 1935 ሮም ኢጣሊያ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የፖለቲካ ጉዳዮች ዋና ጽ/ቤት ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ 1930 - 1945 ሮም ኤፒ ኢትዮጵያ - ጉኤራ ተብሎ የተጠቀሰ

ጃፓን ጋይሙሾ፣ ጋይኮ፣ ካን /ቶኪዮ/.... የሪኮርድ መ/ቤት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር.... ጂኤስኬ ሆኖ የተጠቀሰ

ዩናይትድ ስቴትስ ብሔራዊ ቤተ መዛግብት /ኮሌጅ ፓርክ፣ ሜሪላንድ/ የሪኮርድ ቡድን 59 የዲፓርትመንት ኦፍ ስቴት ጠቅላላ ሪኮርዶች ዴሲማል ፋይሎች። ኤንኤአርኤ ሆኖ የተጠቀሰ

ከአምዴ አርአያ /የአርአያ አበበ ልጅ/ እና ከአርአያ አበበ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፣ ፌይር ፋክስ ሌክስ ፓክ፣ ቨርጂኒያ እና የአርአያ አበበ አፓርትመንት አሌክሳንድርያ፣ ቨርጂኒያ፣ እ.ኤ.አ 7/2001 1,45 – 6,30 ፒ.ኤም.

## ጋዜጦች

ጃፓን አድቨርታይዘር

ጃፓን ታይምስ

ሳካ ማይኒቺ ኤንድ ቶኪዮ ኒቺ ኒቺ /ኦኤም ኤንድ ቲኤንኤን የተጠቀሰ

## ተከታታይ ምንጮች

አኪ ሱሚዮ ኤንድ ኩሪሞቶ ኢሴ፡- ጃፓኒዝ ኢንተረስት ኢን ኢትዮጵያ /1868 - 1940 እ.ኤ.አ/ ክሮኖሎጂ ኤንድ ቢቢሲዮግራፊ፡- ኢን ኢትዮጵያ ኢን ብሮደር ፔሪስፔቲክቭ፡- ፔፐርስ ኦፍ ዘ 13ዝ ኢንተርናሽናል ኮንፈረንስ ኦፍ ኢትዮጵያ እስተዲስ፡- ኬኢ ኤንድ ኤም. ሺጌታ ኢዲሽን 3 ቮልዩምስ ኪዮቶ ቮካዶ ቡክሌለርስ 1977 713 -28 ኦይኪ ሱማዮ. ዘ ቮየጅ ኦፍ ኢትዮጵያን ሚኒስቴርስ ኦፍ ፎሪይን አፌይርስ ቱ ጃፓን ኤንድ ሪሌሽን ቢትዊን ጃፓን ኤንድ ኢትዮጵያ ጌካን አፍሪካ 37/1977/ 31 -34

ባሕሩ ዘውዴ፡- ዘኮንሴፐት ኦፍ ጃፓናይዜሽን ኢን ዘ ኢንተሌክችዋል ሂስትሪ ኦፍ ሞደርን ኢትዮጵያ.... በባህሩ ዘውዴ፣ ፕሮሲኢዲኢንግስ ኦፍ ፊቭዝ ሴሚናር ኦፍ ዘ ዲፓርትመንት ኦፍ ሂስትሪ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲቲ እ.ኤ.አ 1990 ብራዲሾው ሪቻርድ - ጃፓን ኤንድ ኢሮፒያን ኮሎኒያሊዝም ኢን አፍሪካ እ.ኤ.አ 1880 - 1937 ፒኤችዲ ዲስርቴሽን ኦሃዮ ዩኒቨርስቲ እ.ኤ.አ 1992

ክላርክ ጄ. ካልቪት 3ኛ ... ዳሽድ ሆፐስ ፎር ስፐርት ዳባ ብሩስ ኤንድ ሾጂ ዮኑሱኬ ስ ፐሪፐ ቱ ጃፓን 1935.... ሴሌክትድ አንዋል ፕሮሲዲንግ ኦፍ ዘ ፍሎሪዳ ኮንፍረንስ ኦፍ ሂስቶሪያንስ 11/ፌብሯሪ 2004/ 135 -51

ክላርክ፣ ጄ. ካልቪት 3ኛ፡- ማሪየጅ አሊያንስ፡- ዘ ዩኒየን ኦፍ ቱ ኢንፔሪየምስ ጃፓን ኤንድ ኢትዮጵያ? ሴሌክትድ አንዋል ፕሮሲዲንግስ ኦፍ ዘ ኮንፈረንስ ኦፍ ሄስቶሪያንስ 7/ዲሴምበር 1999/ 105 -16

ክላርክ፣ ጄ. ካልቪት 3ኛ፡- ሚውችዩወል ኢንተረስት፡- ጃፓን ኤንድ ኢትዮጵያ ቢፎር ዘ ኢታሎ - ኢትዮጵያ ዎር፣ 1935 -1936 ሴሌክትድ አንዋል ፕሪሲዲንግስ ኦፍ ዘ ፍሎሪዳ ኮንፈረንስ ኦፍ ሂስቶሪያንስ 9/ፌብሯሪ 2002/ 83 -97

ክላርክ ጄ ካልቪት 3ኛ፡- ፔሪፈሪ ኤንድ ክሮስሮድስ፡- ኢትዮጵያ ኤንድ ወርልድ ዲፕሎማሲ፣ 1934 – 1936 ኢን ኢትዮጵያ ኢን ብሮደር ፔሪስፔክቲቭ፡- ፔፐርስ ኦፍ ዘ 13ዝ ኢንተርናሽናል ኮንፈረንስ ኦፍ ኢትዮጵያን ስተዲስ ቮልዩምስ ኪ.ኤ ኤንድ ኤም. ሺጌታ ኢዲሺን ኪዮቶ፣ ሾካዶ ቡክሴለርስ 1997 እ.ኤ.አ 1፡699-712

ክላርክ ጄ. ካልቪት 3ኛ ሲኪንግ ኤ ሞዴል ፎር ሞደርናዜሽን ኢትዮጵያንስ ጃፓናይዘርስ ሴሌክትድ አንዋል ፕሮሲዲንግስ ኦፍ ዘ ፍሎሪዳ ኮንፈረንስ ኦፍ ሂስቶሪያንስ 10/ ፌብሯሪ 2004/፣ 7 -22

ፋኤርበር - አሺሃራ፣ ሂደኮ «ጎሩይ ሌ ጃፓን ኤትሌስ ጃፓኒሳንትስ» ኢን አላይን ሮውድ

ፋኤርበር - ኢሺሃራ፣ ሂደኮ። ሌስ ፕሬሚየርስ ኮንታክትስ ኢንትሪ ኢትዮፒ ኤት ሌ ጃፓን። ፓሪስ አርሴይ 1998

ፋራጎ፣ ላዲስላስ። አቢሲኒያ ኦን ዘ ኢቭ። ኒውዮርክ ጂ.ፒ ፑትናምስ ሰንስ፣ 1935

ፋሩካዋ ቴሱሺ። «ጃፓኒዝ - ኢትዮጵያን ሪሌሽን ኢን ዘ/1920 - 30ዎቹ/ ዘራይዝ ኤንድ ፎል ኦፍ - ሴንቲሜንታል - ሪሌሽንስ» በአፍሪካ መካነ ጥናት ማኅበር 34ኛ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ የቀረበ ሰነድ፣ ሴንት ሉዊስ፣ ኤምኦ፣ እ.ኤ.አ 1991

ፉሩካዋ ቴትሱሺ። «ጃፓንስ ፖለቲካል ሪሌሽን ዊዝ ኢትዮጵያ፣ በ1920ዎቹ - 1960ዎቹ ኤ ሂስቶሪካል አቨርቪው» በአፍሪካ መካነ ጥንት ማኅበር 35ኛ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ የቀረበ ያልታተመ ሰነድ፣ ሲአትል ዋሽንግተን እ.ኤ.አ ኅዳር 20 – 23 1991

ጎሩይ ወልደ ሥላሴ። የጃፓን ብርሃን። በኦርስቴ ቫካሪ የተተረጐመ። በባሮን ሺዲሃራ ኪጁሮ የመግቢያ ቃል የሠፈረበት። ቶኪዮ ኢቡንፖ - ትስሮን ሾጂ፣ 1933

ሞክለር፣ አንቶኒ። የኃይለ ሥላሴ ጦርነት የኢጣሊያና - የኢትዮጵያ ውጊያ 1935 – 1941 ኒውዮርክ ራንደምሃው 1984

አካቡራ ፓካሺ ኤንድ ኪታጋዋ ካትሱፒኮ /የጃፓን - አፍሪካ ግንኙነት ታሪክ፣ ከሜይገ ጊዜ አንስቶ እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ክፍለ ጊዜ ድረስ/ ቶኪዮ ዶቡን - ካን 1993

ፕሮቻዘዛ፣ ሮማን። አቢሲኒያ ዘ ፓውደር ባረል የብሪቲሽ ዓለም ዓቀፍ ዜና ወኪል 1936

ፕራውቲ ክሪስ ኤንድ ኢውጊን ሮዘን ፌልድ የኢትዮጵያ ታሪካዊ መዝገበ ቃላት። መኢቱሰን ኤንጄ፣ ዘ ስካሬክሮው ፕሬስ 1981

ሾጂ ዩኖሱኬ። ዋት ዊል ሃፐን ቱ ዘ ኢትዮጵያ ማሪየጅ ኢሹ ካንስሌሽን? ኦር ኖት!! አይ ረኩዌስት ዘ ሪ - ሪኮግኒሽን ኦፍ ዘ ጃፓኒዝ ኔሽን ባይ ናሬቲንግ ዘ ትሩዝ ኦፍ ኢትዮጵያ ዊዚዝ ዘ ማሪየጅ ኢሹ አዝ ዘ ሴንትራል ቲኢይም/ ቶኪዮ ሴይኮ 1934

ታኒን አ. ኤንድ ኢ. ዮሃን ሆየን ጃፓን ጐስ ቱ ዋር። ኒውዮርክ ኢንተርናሽናል ፐብሊሸር 1936

ታውራ ማሳኖሪ፡ ኤ ፊኤዝ ኦፍ ዘ1930 ኮሜርሺያል ዲፕሎማሲ ኢን ዘ ጃፓኒዝ - ኢትዮጵያ ሪሌሽንስ/ ከሰይፉ ለሚንካን/ መንግሥት እና ሲቪሎች/ ዓመታዊ ሪፖርት የዘመናዊቷ ጃፓን ጥማት /17 /1997/፡ 141 – 70

ሁኖ ዮሼሮ። ጃፓን እና ሁለተኛው የኢጣሊያ - ኢትዮጵያ ጦርነት። የፖለቲካ እና ግል መጽሔት /ኒጋታ ዩኒቨርሲቲ ጃፓን/ 16፣ 2 /1982/፡ 188 – 240

ይልማ አሰፋ። ኃይለ ሥላሴ፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የወቅቱን ትግል እና የሀገሪቱን እና የሕዝቧን ዝርዝር መግለጫ ጨምሮ የኢትዮጵያ ታሪክ ጭምር መግለጫ። ለንደን ሳምፕሰን ሎው ማርስተን ኤንድ ካምፓኒ 1936

ዜርቮስ፣ አድሪየን። ለአምፒር ደለ ኢትዮፒ ሌ ሚሮይር ደ ለ ኢትዮፒ. ሞዴርን 1906 – 1935 አሌክሳንድሪያ ግብፅ

ይህን መጽሐፍ እንዲታተም እንድንጀምርና እንድንፈጽም ለፈቀደልን ለእግዚአብሔር አምላክ ክብር ምስጋና ይሁን

. . . እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ አሜን!

# የሰውና የሥፍራ ስሞች ማገናዘቢያ - INDEX


### ሀ

ሀሪስ /ካፒቴን/ ፸፮ ፹

ህዮጎ ፪፻፩

ሀገረ ጃፓን ፪፳፩ - ፪፳፱

ሂሮታ ፪፺፯

ሂወትዊሌም /ዊሊያም/ አድሚራልሰር ፩፶፱ -፶፮

ሃማ ቤተ መንግሥት ፪፻፩

ሆሜይደን አዳራሻ ፫፻፹

ሆሮ ፩፻፳፫

### ሐ

ሐመረ እሸቴ /ወይዘሮ/ 14

ሐማሴን ፩፻፸፮ - ፪፻፳

ሐሰን ፩፻፸፮

ሐሰኢቱ /አለቃ/ ፩፻፲፫

ሐረርጌ ፺፬ ፩፻፶፩ ፩፻፶፱

ሐራማት ፪፻፸፫

ሐርአምባ ፶፩

ሐሮ ፩፻፳፱

ሐውዜን ፪፻፲ - ፪፻፲፱ - ፪፻፸፫ - ፪፻፸፱

ሐይቅገዳም ፺፪

ሐጐስ /ራስ/ ፩፻፹፫ - ፩፻፹፮

ሐጐስ ተፈሪ /ደጃች/ ፪፻፳፬ - ፪፻፴፩ - ፪፻፶

ሒሮሒቶ /ግርማዊ የጃፓን ን. ነ/ ፪፻፸፱

ሔጃዝ ፷

ሕንድ ፩

ሕንደኬ ንግሥት ፲፩

ሕንጣሎ ፪፻፴፫

### ኀ

ኂሩት ፩፻፴፩

ኃይለ መለኮት /ንጉሥ/ ፹፫ - ፩፻፴፮

ኃይለ ማርያም ወልደ ሚካኤል /ደጃች/ ፩፻፶፫ - ፩፻፴፮

ኃይለ ማርያም ፩፻፴፫

ኃይለ ማርያም /ራስ/ ፩፻፹፫ - ፩፻፹፮

ኃይለ ማርያም /ቀኛ/ ፪፻፴፩ - ፪፻፴፬

ኃይሉ /አቶ/ ፸፩

ኃይሌ /ኃይለ ሚካኤል/ መርዕድ አዝማች ፺፪ ፺፫ ፺፬ ፩፻፫

ኃይለ ሥላሴ /ንጉሠ ነገሥት/ 8 12 21 ፪፻፸፫ - ፪፻፸፬ - ፪፻፹፮

ኀኑይ ወልደ ሥላሴ /ብላቴን ጌታ/ 1 4 5 6 9 10 16 17 – 23 26 ፪፻፳፩ - ፪፻፳፫ ፪፻፸፪ - ፪፻፸፫ -፪፻፸፫ - ፪፻፺

### ለ

ለንደን 19

ለገሂዳ ፩፻፶፪

ለገጐራ ፩፻፶፪

ለውጤ /በጅሮንድ/ ፩፻፲፫

ለዚህ ዓለም /አቶ/ ፳፫

ሉክሰንበርግ 19

ሉቃስ /አቡነ/ ጳጳስ ፩፻፪ - ፩፻፸

ሉዊፊሊፕ /ንጉሥ/ ፸፱ - ፹

ሊሙ ፩፻፶

ሊቃኖስ /አባ/ ፷

ሊዎንቴፍ ፪፻፴፪

ሊግኦፍኔሽንስ ፪፻፸፱

ላሊበላ /ንጉሥ/ ፴

ላሊበሎች ፳፱

ላምዋሻ ፳፺

ላስታ ፳፺

ልብነድንግል /አጼ/ 1 ፵ - ፵፩ ፩፻፳፪

ልቼ ፺፱ ፩፻፳ ፩፻፲፺ - ፩፻፴፳

ልጥማገሬፊያ ፩፻፸፫

ልጓት ፩፻፶፪

ሎሬንሶ መብራህቱ ታእዛዝ /ብላቴንጌታ/ 22

### መ

መሐመድ አሊ /ይማሙ/ ፩፻፫ ፩፻፳፺

መስቀላ አምባው ፩፻፫

መስተዋት /ወይዘሮ/ ፩፻፫ ፩፻፳፺

መሶበ ወርቅ /ወ/ሮ/ ፴

መስኮብ ፩፻፳፪ ፩፻፴፪
መራተክለሃይማኖት ፷፫
መርሐቤቴ ፷፫ ፷፯
መርሶ ፩፻፴፫
መረብ ፩፻፫ ፩፻፲፮ ፩፻፲፯ ፩፻፳፫
መሮፔዎስ ፲፫
መሸሻ ሠይፉ /አቤቶ/ደጃች/ ፩፻፱ ፩፻፲፫
መሸሻ ማሩ /ደጃች/ ፩፻፴፱
መሸሻ ወርቄ /ደጃች/ ፩፻፸፮ ፩፻፲ ፩፻፲፫
መቀሌ ፩፻፸ ፩፻፴፩ ፩፻፴፩ ፩፻፵፫ ፩፻፵፭ ፩፻፺፱
መቅደላ ፩፻፫ ፩፻፭
መቅዶንዮስ ፩፻፲፱
መተኮ ፷፫ ፸፫’
መተማ ፩፻፳፩ ፩፻፹፩ ፩፻፹፱
መንዝ አቲከም /ራስ ቢትወደድ/ ፩፻፲፮ ፩፻፴፯ ፩፻፶፪
መንገሻ ዮሐንስ /ራስ/ ፩፻፹፫ ፩፻፲ ፩፻፲፱ ፩፻፳፩ ፩፻፳፪ ፩፻፳፫ ፩፻፳፭ ፩፻፴ ፩፻፶፪ ፩፻፶፱
መኮንን /ራስ/ ፩፻፶፱ ፩፻፷ ፩፻፲ ፩፻፲፩ ፩፻፲፪ ፩፻፴፯ ፩፻፴፱ ፩፻፵፩ ፩፻፵፪ ፩፻፵፫ ፩፻፶፪
መኻን ሕዝባ ፩፻፵፫
ሙለር ሮበርት ፩፻፷፭
ሙሶሊኒ ቢኒቶ ፩፻፷፩
ሙቅ ምድር ፷፩
ሙተራ አምባ ፩፻፸፫
ሙዚንገር /ፓሻ/ ፩፻፵፮ ፩፻፵፯
ሙና ፩፻፫ ፩፻፳፫
ሚካኤል /ራስ/ ፩፻፷፬ ፩፻፲፫ ፩፻፴፯ ፩፻፵ ፩፻፺፱
ሚጣቅ ፩፻፱
ማስያስ /አባ/ ፩፻፲፩ ፩፻፲፪ ፩፻፲፬
ማሳኮ /ልዕልት/ ፩፻፺፫
ማሩ /ደጃች/ ፻፲፯
ማርት /ወ/ሮ/ ፩፻፴፫
ማርኮፖሎቤይ ፩፻፶፱
ማቴዎስ ጳጳስ /አቡነ/ ፩፻፫ ፩፻፷ ፩፲፶፮
ማክላን ጐርዶን ፩፻፷፫
ማይበላ ፬
ማዳጋስካር ፩
ሜጫ ፪ ፩፻፴፮
ሜይገዢ ፩፻፹፩
ምላት /አለቃ/ ፩፻፲፬
ምስር ፩ ፩፻፵፮
ምኒልክ /ቀዳማዊ/ ፬ ፮ ፯ ፲፩ ፴፭ ፴፬
ምኒልክ /ዳግማዊ አጼ/ 2 ፷፪ ፹፱ ፺፭ ፩፻፳፩ ፩፻፳፫ ፩፻፵፮ ፩፻፱ ፩፻፶፱
ምንትዋብ /ወ/ሮ/ ፩፻፸
ምንጃር ፶፪ ፶፫ ፷፫ ፺፭
ሞረት ፷፯
ሞዓኢየሱስ /አባ/ ፴፭
ሞጣ ፩፻፯
ሞፈርውሃ ፵፭

## ሠ

ሠራዬ ፩፻፳፭
ሠራዊቱ /አቶ/ ፩፻
ሠናይት ተክለ ማርያም /ወይዘሮ/ 3 8 27
ሠይፉ መሸሻ /አቤቶ/ ፹፭ ፹፫ ፺፫ ፺፭
ሣህለ ሥላሴ /ንጉሥ ሸዋ/ ፷፪ ፷፬ ፷፮ ፹፪ ፹፬
ሣልሣ /ማጆር/ ፩፻፵፱
ሣርውሃ ፩፻፪ ፩፻፹፬
ሣኮ ፹፮
ሥላሴ ፸፱
ሥዩም ፩፻፲

## ሰ

ሰሐጢ ፩፻፲፮ - ፩፻፲፱
ሰላሌ ፺፪
ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ፲፮
ሰላማጳጳስ /አቡነ/ ፺፪
ሰላማ ቄስገበዝ ፩፻፹፯
ሰላድንጋይ ፷፬
ሰልዋ ፩፻፴፫
ሰሎሞን /ንጉሥ እስራኤል/ ፪ ፫ ፬ ፮ ፯
ሰማያታ ተራራ ፩፻፶፭
ሰሜን ፩፻፴፮
ሰባጋዲስ ፩፻፶
ሰቀልት ፩፻፸
ሰንአፌ ፩፻፳፮
ስሙንጉሥ /አቶ/ ፺፬ - ፩፻፲

ሰዲቅ አህመድ ፩፻፵፬
ሱሚቶም ፪፻፹፬
ሱስንዮስ /አጼ/ ፩፻፲፱ - ፩፻፴፰
ሱዳን ፩
ሲናዲር ፩፻፲፮
ሲንሂት ፩፻፷፬
ሲዳሞ ፪፻፷፪
ሲድራኮስ ፲፭
ሳሊቤ /ማጆር/ ፪፻፳፮
ሳባ ነገሥት ፩ ፫ ፬ ፭ ፮ ፯
ሳሙኤል ፮
ሳምሶን ፮
ሳይንት ፩፻፴፪ - ፩፻፴፫
ሳግሬን ፪፻፵፩
ሳውዛርድ ኤዲሰን ፪፻፸፯ - ፪፻፸፰
ሳፎኔቲ /ቲኒንቲ/ ፪፻፳፮
ሴሴ ወንዝ ፩፻፳፰
ሴንትራል ማተሚያ ቤት 27
ስብሐት /ራስ/ ፪፻፲፱ ፪፻፳፬ ፪፻፳ ፪፻፶
ሶሎዳ ተራራ ፪፻፵፬
ሶዶ ፷፯ ፩፻፵፫

## ሸ

ሸምቡ /አቶ/ ፸፩
ሸዋ ፳፰ ፴፬ ፵፩ ፷፭ ፸፰ ፺፩ ፩፻፲፮ ፩፻፳፪ ፩፻፳፬ ፩፻፵፫
ሸዋረጋ /ወይዘሮ/ ፪፻፲፰ ፪፻፴፮
ሸዋዬ /ልጅ/ ፪፻፳፭
ሺማዲኢ ፪፻፹፮
ሽሬ ፪፻፵፫
ሽሽጉ /አቶ/ ፺፩

## ረ

ረመሸት 10
ሩባቲኖ ኩባንያ ፩፻፳
ራጉኤል 3
ሬይ /ቻርልስ/ ፪፻፷፫
ርቄ ፵፱
ሮሐ ገዳም ፴፪
ሮም /ግሪክ ሮም/ ፰
ሮሼ ዴሬኩር ፸፱ - ፹
ሮኮ ተራራ ፪፻፸፱

## ቀ

ቀረጥ አምባ ፶
ቀቤና ፩፻፳፮
ቀይ አፈር ፷፯
ቀይ መስቀል 12
ቀይ ጥላ ፪፻፲፱
ቀያ ፷፯
ቀወት ፵፱ - ፩፻፺
ቀዲዳ /ፊታ/ ፩፻፳ - ፩፻፴
ቀጸላ /አቶ/ ፳፯
ቀሮገደል ፷፭
ቁንዲ ፷፪ - ፷፭
ቋረኛው ፷፮
ቁራ ፪፴፮
ቃሲም /የጁ/ ፩፻፮
ቃሮዳ ፩፻፲፯
ቄርሎስ ጳጳስ ፹፫ ፩፻፳፱ - ፩፻፷፫
ቄርሎስ ፩፻፴፰
ቅብዓት /ሃይማኖት/ ፩፻፳፩
ቅዱስት ሥላሴ ካቴድራል - 21 - ፪፻፷፫
ቆስጠንጢኖስ /ን.ነ/ ፲፯ ፩፻፲፱
ቆለጭ /ቀኛ/ ፪፻፪

## በ

በሁበቱ /አቶ/ ፺፩
በሬሳ /ወንዝ/ ፵፫
በሻህ አቦዬ /ደጃ/ ፩፻፲፮ ፩፻፵፫ ፪፻፫
በረከት ፺፩ ፺፭ ፺፰
በለጥሻቸው /ወይዘሮ/ ፷፱
በርበሬ ፩፻፯
በለሳ ፪፻፫ ፪፻፳፫
በለው /ደጃ/ ፩፻፸
በሽሎ ወንዝ ፩፻፲፪ ፩፻፲፭
በኩሩ /አቤቶ/ ፷፭
በዛብህ /አቶ/ ፺፩ ፺፬ ፺፭ ፺፮
በዛብሽ /ወይዘሮ/ ፷፱ ፹ ፹፫ ፹፰

ባቡ /አቶ/ ፩፻፮
በየነ /ባላም/ ፪፻፴፩
ባዩ /ግራዝማች/ ፩፻፸
በድሉ /አቶ/ ፺፩
በዳኔ /አፈ ንጉሥ/ ፩፻፰ ፩፻፱
ቡልጋ ፹፯
ቡንያን /ዮሐንስ/ ፪፻፹፯
ቡንራኩዛ ፪፻፳፬
ቡኔ /አቶ/ ፸፩
ቡግና ፵፮
ቪክቶሪያ /ባህር/ ፩
ቪክቶሪያ /ንግሥት/ ፸፭ ፩፻፹፪ ፩፻፹፮
ባሕሩ ዘውዴ /ፕሮፌሰር/ 26
ባሕታ /ደጃች/ ፩፻፵፰ ፩፻፵፱
ባሊ /ማጆር/ ፪፻፷፩
ባልቻ አባ ነፍሶ /በጅሮንድ/ ፪፻፶፪ ፪፻፶፱ ፪፻፶፱
ባልዲሰራ /ጄኔራል/ ፪፻፫
ባራቲዬሪ /ጄኔራል/ ፪፻፵፫ ፪፻፶ ፪፻፶፪ ፪፻፶፮ ፪፻፶፰ ፪፻፶፱ ፪፻፷፫ ፪፻፷፬ ፫፻፷፯
ባርቅ ፮
ባሸባዙቆች ፪፻፷፮
ባሺን ፩ ፲ ፲፭
ባዝ /ከተማ/ 19
ባፈና /ወይዘሮ/ 10 ፩፻፭ ፩፻፯ ፩፻፰ ፩፻፶
ቤርሳቤህ ፯
ቤጌምድር ፺፭ ፩፻፰ ፩፻፴፫ ፩፻፴፮
ቤተ ክህነት ፪፻፹፱
ብላታ 13
ብላቴን ጌታ 1 4 5 6 9 10 14
ብሩ /ዋግሽም/ ፩፻፺፮ - ፩፻፵፪
ብሩ /አለቃ/ ፩፻፶፯
ብሪታንያ ፸፮ ፸፰
ብርቄ /አቶ/ ፸፬
ቦሩሜዳ ፩፻፲፯ - ፩፻፴፰ - ፩፻፸፮
ቦርጃ ፲፫ - ፸፫ - ፸፭
ቦተር ፩፻፷፫
ቦጋለ /ደጃች/ ፩፻፳፱
ቦጉስ ፩፻፶፮ - ፩፻፷፩

## ተ

ተምቤን ፪፻፷፫
ተሰማ ናደው /ደጃዝ/ ፩፻፷፫ ፪፻፷፫
ተስፋ ኢየሱስ ፴፬
ተስፋዬ /ሹም አጋሜ/ ፪፻፵፬ - ፪፻፶
ተንጐዳጓጅ /ባሻ/ ፩፻፲፮
ተንከል ሜዳ ፩፻፸፪
ተናኘ ወርቅ /ልዕልት/ ፪፻
ተስፉ ፩፻፶፰
ተክለ ሃይማኖት /አባ/ ፴፬ ፴፭ ፴፮ ፴፯ ፴፰
ተክለ ሃይማኖት /ንጉሥ/ ፩፻፵፩ ፩፻፵፰ ፩፻፴ ፩፻፸፫
ተክለ ማርያም ፩፻፷፫
ተክሌ /ፊታ/ ፪፻፴፮ ፪፻፴፯ ፪፻፶ ፪፻፷፪
ተክለ ጊዮርጊስ /አጼ/ ፩፻፫ ፩፻፶
ተገኔ /ቀኛ/ ፪፻፪
ተጉለት ፴፭ ፴፱ ፹፯
ቱርክ ፩፻፮ ፩፻፸፭
ቱኒዝያ ፲፭
ተድላ /ደጃች/ ፪፻፵፮
ተድላ ደጃች የዘበኞች አለቃ ፩፻፳፯
ተፈሪ መኮንን /ልዑል ራስ/ 12
ተፈሪ ገብረ ማርያም ፪፻፸፮
ታምራት አማኑኤል /ፕሮፌሰር/ ፪፻፹፮
ታካራዙካ ፪፻፸፱
ታፈሰ /ቀኛ/ ፪፻፴፯ - ፪፻፶፩ - ፪፻፷፪
ቴይቴን ፪፻፳፩
ቴዎድሮስ /ን.ነ/ 1 ፳፮ ፳፯ ፳፰ ፳፱ ፺ ፱-፩ ፺፪ ፺፫ ፺፬ ፺፭ ፺፮
ቴዎፍሎስ /እጨጌ/ ፩፻፲፮ - ፩፻፳፩ - ፪፻፵፫ - ፪፻፵፭
ትግሬ /ትግራይ/ 25 ፩ - ፩፻፵፬ - ፩፻፷፫ - ፪፻፲ - ፪፻፴፩ - ፪፻፶፮
ትሪፖሊ ፲፭
ትሁን /ወይዘሮ/ ፷፬
ትራቬርሲ /ዶክተር/ ፩፻፵፪ - ፩፻፵፫
ትርዳእ ጐበዝ ፵፰
ቶሾጉ ፪፻፳፩
ቶኬ ፩፻፷፫

ቶዮ ፪፻፹፭
ትዞሊ /ማጆር/ ፪፻፳፱ - ፪፻፵ - ፪፻፶

## ቸ

ቸሀ ፩፻፮

## ነ

ነአኩቶለአብ /አጼ/ ፴፭ ፴፮ ፴፰
ነጋሲ /አቤቶ/ ፵፩ ፵፪ ፵፫
ነጋሽ ወሬኛ ፩፻፯
ነጭ ዓባይ ፩፻፹፭
ኒኮ ፫፻፹፮
ኒቆዲሞስ ፪፻
ኒያንዛ ፩
ናይጋይ ፪፻፹፬
ናደው /አቶ/ ፺፩ ፩፻፭ ፩፻፲፭ ፩፻፲፰
ናጐያ ፪፻፹፪
ናፒየር /ሎርድ/ ፩፻፪
ናፖሊ ፪፻፲
ንስጥሮስ ፩፻፲፱
ንጉሠ ነገሥቱ ፪፻፵ ፪፻፸፯
ንጉሤ /ፊታ/ ፪፻፴፩
ንግዶ /የሻቃ/ ፶፱

## አ

አህመድ /ቃዲ/ ፩፻፹፭
አህየዋ /ንግሥት/ ፲፭
አህያ ፈጅ ፳፰ ፷፯
አሉላ /ልጅ/ ፩፻፴፰
አሉላ /ራስ/ ፪፻፲፱ ፪፻፴፯ ፪፻፵
አሊበር /መቅደላ/ ፺፯
አሊ አቡበከር ፩፻፶፰
አመዴ ሰዲቅ ፩፻፶፬
አሌቃ ፪፻፶፬
አልቤርቶኒ /ጄኔራል/ ፪፻፶፬ - ፪፻፶፯
አልአሚዳ /ንጉሠ ነገሥት/ ፰
አልጄሪያ ፲፭
አልፎንስ /አባ/ ፩፻፲፱
አመንሸዋ ፩፻፺፯
አሚር ፺፬
አማራ ፷፭ - ፸፮ - ፺፮
አሜሪካ 3
አምባሰላማ
አምባሳደር ፪፻፪
አምባታሪክ ፪፻፳፮
አምባላጌ ፪፻፴፬ - ፪፻፴፰ - ፪፻፵ - ፪፻፵፩ - ፪፻፵፪
አምባ ጫራ ፩፻፳፪ - ፩፻፳፬
አሞይ ፪፻፹፪
አሣይ ፪፻፶፪
አሥመራ ፩፻፵፱ - ፪፻፲፮ - ፪፻፴፩ ፪፻፵፬ - ፪፻፵፱
አሥራት /አለቃ/ ፺፭
አስቴር ፳፮
አስቴር ዘሙይ 27
አሰግድ /ባላም/ ፪፻፪
አስፋወሰን ፶፫ - ፶፭ - ፶፮ - ፷፩
አስፋው /ጃንጥራር/ ፩፻፺፩
አረጋዊ /አቡነ/ ፳፭
አረርቲ ፺፩
አርባዕቱ እንስሳ ፪፻፲፩
አርኤያ አበበ /ልጅ/ ፪፻፸፮ - ፪፻፹፯ -፪፻፺፩ - ፪፻፺፪
አርኤያ ሥላሴ /ራስ/ ፩፻፴፮
አርኤያ ትልቁ /ራስ/ ፩፻፹፭ - ፩፻፹፯
አርምስወርዝ ጀውራይ ፪፻፷፬
አርዮስ ፲፯
አርጐባ ፩፻፳፩
አሸብር /አቶ/ ፳፰
አሸንጌ ከተማ ፩፻፷፩ - ፪፻፴፮ - ፪፻፵ ፪፻፵፫
አበበ አረጋይ /ራስ/ 21
አበበ /ልጅ/ ፪፻፲፰
አቡአንጋ ፩፻፹፭
አብደላ አማን ፺፮
አብዱላሂ /አሚር/ ፩፻፶፯ - ፩፻፶፰
አብኖፍ ኒኮላይ ፪፻፴፪
አብቹ ፷፪
አብዩ /መርዕድ አዝማች/ ፶ - ፶፩
አባተ ቧ ያለው /ሊቀ መኳስ/ ፪፻፵፬ ፪፻፵፱ ፪፻፶፱
አብርሃ /ንጉሥ ፲፭ - ፳፯

አባሞቴ ፺፱

አባውርጂ /አቶ/ ፺፩

አባኢሬ /አቶ/ ፺፩

አባዋጠው /ይማሙ/ ፩፻፳፰

አባገሪማ /ጉልት/ ፪፻፶፪

አባይነህ /አቶ/ ፺፩

አባዳማ ፷፫

አባጂፋር ፩፻፴፯

አባጆቢር /የጉማው/ ፩፻፳፬

አቦከር ፩፻፶፮

አቦዬ /አቶ/ ፺፩

አትባራ /ወንዝ/ ፩፻፶፰ - ፩፻፳፭

አትናቴዎስ /ሊቀጳጳስ/ ፲፯ - ፩፻፫

አትሞችሆዋ /ወይዘሮ/ ፶፬

አንበረም ፲፮

አንበሳውድም ፳፯

አንትሮፖሎጂስት ፪፻፷፬

አንኮበር ፳፪ ፺፪

አንተይስጠኝ /አቶ/ ፺፩

አንቶኔሊ.ፒዬትሮ /ኮንት/ ፩፻፵፪ ፩፻፵፭

አካለወልድ /መምሕር/ ፩፻፳፩

አኩስም ፲፭ ፳፰ ፳፮

አንዳርጋቸው /አቶ/ ፺፩

አንዳርጋቸው /ቀኛ/ ፪፻፳፯

አንጋቻ ፩፻፵፮

አንጾኪያ ፶፯

አንጐለላ ፳፪

አንፋሬ መሐመድ ፩፻፵፯ ፪፻፴፯ ፪፻፶፪

አንድሬ ሬቦን /መርከብ/ ፪፻፸፮

አዕምሮ ፩፻፺፮

አይራራ /ወንዝ/ ፺፩

አውስትርያ ፪፻፳፪

አውሳ ፪፻፴፯

አውዓሎም /ሰላይ/ ፪፻፶፫

አውሮፓ 3 12 ፪፻፳፪

አዋሽ ወንዝ ፺፩

አዙ /ዋሻ/ ፺፰

አዙሊ ፩፻፶፬

አዜብ ፯

አዲስ አበባ 12 ፪፻፺፭

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 26

አዲግራት ፩፻፬ ፩፻፵፬ ፩፻፵፰ ፩፻፵፮ ፩፻፵፱ ፩፻፶፫

አዳል /አፋር/ 25

አዳል /ራስ/ ፩፻፰ ፩፻፳፪ ፩፻፳፫ ፩፻፳፬

አድማሱ /አለቃ/ ፪፻፲፮

አድነው /ሊቀ መኳስ/ ፪፻፴፯ ፪፻፶፪

አድዋ ፩፻፳፩ ፪፻፳፩ ፪፻፳፬ ፪፻፴፭ ፪፻፵፫ ፪፻፶፪ ፪፻፷

አድጎ /ሻለቃ/ ፩፻፶፮

አገኘው እንግዳ /ሠዓሊ/ ፫

ኢጋቦስ ፯

አጥናፌ /በጅሮንድ/ ፩፻፶፮

አፈወርቅ ተክሌ /ሜትር አርቲስት የዓለም ሎሪየት/ ፪ ፲፪

አፍቀራ አምባው ፺፰ ፩፻፬

አፍቀራ ጐሌ /የመንዝ ባላባት/ ፷፪

አሳቡሮ ዮሺዳ ፪፻፸፪

ኢብነሐኪም ፬

ኢብነመለክ ፬

ኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ማዕከል 26

ኢየሱስ ክርስቶስ ፩፻፲፮ ፪፻፳፮

ኢየሩሳሌም ፯ ፪፻፲፪

ኢያሱ ሚካኤል /አቤቶ/ 3

ኢየሱ አድያም ሰገድ /አጼ/ ፵፫

ኢዝንበርግ /አይዝንበርግ/ ፸፭ ፸፱

ኢጣሊያ ፩፻፳፪ ፩፻፵፰ ፩፻፵፭ ፪፻፲፭ ፪፻፷፩ ፪፻፹፬

ኤሌና /ጄኔራል/ ፪፻፵፬ ፪፻፶፯

ኤሎስ ፩፻፴፮

ኤሚሊዮ /ማጆር/ ፩፻፶፪

ኤራቅሊስ ፩፻፴፮

ኤፍራታ ፶፯ ፷፯ ፩፻፶፬

እልእስክንድሮስ ፲፯

እስክንድርያ ፲፭ - ፲፯

እርመጃቸው /ወይዘሮ/ ፩፻፯

እሸቱ /አለቃ/ ፩፻፲፭

እምባቦ ፩፻፴

እምነጽዮን ፩፻፺፪ ፩፻፺፱

እነዋሪ ፩፻፯ ፩፻፱

እንሳሮ ፴፮

እንኪጨው ፪፻፷፱ ፪፻፵፰

እንግሊዝ 2. 4 ፪፻፺፪

እንግዳ /ራስ/ ፳፩

እንግዳ /ዋልድቤ/ ፲፻፲፮ - ፩፻፲፮

እንግዳ /ብላታ/ ፪፻፷፪ ፪፻፷፭

እንደርታ ፪፻፷፰

እንዳ አባ ገሪማ ፪፻፵፬

እንዳ ኢየሱስ ፪፻፶፰

እጅግ አየሁ /ወይዘሮ/ ፴፫

እግርበር ፩፻፮

እንጦጦ 3. 11 ፩፻፺፬ - ፩፻፶፩

ኦምዱርማን ፩፻፹፭

ኦሳካ - ኦሳሂ ፩፻፹፭

ኦሳካ ፪፻፹፬

## ዐ

ዐረብ ፩

ዐረብ ሻንቅላ /ቤንሻንጉል/ ፩፻፵፰

ዑምቤርቶ /ንጉሥ/ ፩፻፷፯ - ፩፻፳፪ - ፩፻፲፯

ዑፁኖሚያ ፩፻፹፩

ዓይኔ ከተማ ፵

ዓባይ ወንዝ ፩፻፺፫ - ፩፻፺፱ - ፩፻፶ - ፩፻፵፯

ዔሊ ፮

## ከ

ከሊፋ አብዱላሂ ፩፻፹፮

ከሰላ ፪፻፺፬

ከተማ /አቶ/ ፳፩

ከተማ /በጅሮንድ/ ፪፻፵፭

ከደዊ /ኬዲቭ/ ፩፻፷፯

ከፋ /ከፊቾ/ ፩፻፺፬ - ፩፻፺፯

ኩሮኪ ቶኪጂሮ ፪፻፹፪ - ፪፻፹፭

ኩሮዳ /ልዑል ፪፻፳፰

ኩቱኩሮ ኢቺኪ ፪፻፸፱

ኪዳልጎ /ማጆር/ ፪፻፺፯

ኪዳነ ወልድ ፩፻፲፯

ኪጁሮ ሺዴሃራ ፪፻፸፱

ክሣ /ልዑል ራስ/ 12

ካሣ /ደጃዝማች/ አባታጠቅ

ካሣ /ደጃዝማች/ አባበዝብዝ ፩፻፷

ካልቪት ክላርክ 3ኛ ፪፻፴፩

ካሌብ /አጼ/ ፺

ካቴ /ማጆር/ ፪፻፷፪

ካቶሊክ ሃይማኖት ፩፻፲፱ - ፩፻፺፫ - ፩፻፺፱

ካራመገን ፵፪

ካርቱም ፩

ክረጽፍ /ዶክተር/ ፸፭ - ፸፱

ክብረነገሥት ፩`፩

ክብረት ፳፬

ክርስቶፎር /ኩሎኔል/ ፩፻፵፱

ክርስቲያን ሃይማኖት ፩፻፲፯

ክነፈኪሩብ መምሕር ፩፻፴፮

ኮራ ታቦተ ማርያም ፩፻፲፰

ኮሌራ ፩፻፲፫

ኮአቲት ፪፻፺፯

ኮቤ ወደብና ከተማ ፪፻፸፫ - ፪፻፴፬ - ፪፻፳፮

ኮምቦልቻ ፩፻፵፬

## ወ

ወላስማ መሐመድ ፷፫

ወላሞ /ወላይታ/ ፪፻፶፮

ወሌ /ደጃዝማች/ ፩፻፯ ፩፻፶፫ ፩፻፳፩ ፪፻፶፪ ፪፻፷

ወልደ አረጋዊ /መምሕር/ ፩፻፹፮

ወልደ አረጋይ አባይቱ ፴፰

ወለጋ ፪፻፸፰

ወልደ ማርያም /ራስ/ ፩፻፯

ወልደ ሚካኤል /መምሕር/ ሰማዕተ ጐንደር ፩፻፳

ወልደ ሚካኤል /መምሕር/ ፪፻፪

ወልደ ሚካኤል /ደጃዝማች/ ፩፻፲፫

ወልደ ሚካኤል /ራስ/ ፩፻፷፯

ወልደ ሥላሴ /አቶ/ ፩፻፲

ወልደ ሥላሴ /ራስ/ ፩፻፳፩

ወልደ ሥላሴ /አለቃ/ ፳፭

ወልደ ሩፋኤል /ደጃዝማች/ ፩፻፶፫

ወልዴ /ደጃዝማች/ ፪፻፲፰

ወልደ ገብርኤል /አቶ/ ፺፩

ወልደ ጊዮርጊስ አባ ፩፻፴

ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ /ደጃዝማች/ራስ/ ፩፻፶፫ ፪፻፲፰ ፪፻፴፯ ፪፻፴፰

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ /ጸሐፊ ትእዛዝ/ 22

ወልደ ጻድቅ /አቶ/ ፺፩

ወልደ ጻድቅ /አዛዥ/ ፩፻፰

ወሎ ፩፻፴፪ ፩፻፶፫ ፪፻፴፩ ፹፮ ፺፰

ወሰን ሰገድ /መርዕድ አዝማች/ ፷፪

ወረሂሙኑ ፺፰

ወርቂት /ወይዘሮ/ ፹፯ ፩፻፭

ወርዕ ፪፻፵፱

ወደራ ፶፬ ፩፻፲፭ ፩፻፲፮ ፩፻፲፯

ወዳጄ ልቤ መጽሐፍ ፪፻፷፪ ፪፻፷፮

ወዳጆ ግርሜ ፸፫ - ፸፬

ወዳጆ /ራስ/ ፶፩ ፶፪

ወንጌል ፩ - ፲፭

ውጫሌ ፩፻፺፪ - ፩፻፺፮ - ፪፻፴፯

ዋህድ /ደጃዝማች/ ፩፻፲፮

ዋቆዲቦ ፹፮

ዋዜማ 1

ዘ

ዘሚካኤል /አባ/ ፰

ዘሚካኤል /ዘሜ/ መርዕድ አዝማች/ ፵፪

ዘሚካኤል /ጽግራ ማሠሬ/ ፩፻፹፯

ዘቢጥ ፩፻፮

ዘርዐያዕቆብ /አጼ/ ፵፩

ዘነበወርቅ /ወይዘሮ/ ፷፪

ዘውዴ /ራስ/ ፪፻፲፰

ዘውዴ ገብረ ሕይወት ቢትወደድ ፩፻፷፩ - ፩፻፷፪

ዘውዴ ገብረ ሥላሴ /ዶክተር ደጃዝማች/ 4 26

ዘውዲቱ /ወይዘሮ/ ንግሥተ ነገሥታት/ ፩፻፴፬ - ፩፻፴፯

ዛማኔል ፪፻፴፮

ዛታ ፪፻፵፱

ዛጉዌ 1. ፲፩

ዜና ማርቆስ ገዳም /አቡነ/ ፩፻፲፫

ዜጋመል ፷፪

ዜኪ ከማል ፩፻፹፭

ዞብል ፩፻፶፬

የ

የመን ፫

የካ ፩፻፲፫

የጁ ፷፮

የውብዳር ፩፻፴፰

የውልዩ ፶፪

ዩኖሱኬ ፪፻፺፭

ያሬድ /ማኅሌታይ ቅዱስ/ ፳፩

ያሬድ አማረ /ዶክተር/ 26

ያዕቆብ /አቤቶ/ ፵፩ - ፵፪

ያፉ ፪፻፲

ይመር /ፊታ/ ፩፻፳፰

ይምዓታ /አባ/ ፰

ይቱ ፩፻፶፬

ይፋት ፶፫ - ፷፯

ዮሐንስ ፬ኛ /ንጉሥ ነገሥት/ ፩፻፫ ፩፻፳፭ ፩፻፳፱ ፩፻፴፩ ፩፻፴፪ ፩፻፴፫ ፩፻፴፬ ፩፻፵፩ ፩፻፵፮ ፩፻፶፩ ፩፻፶፪ ፩፻፶፬ ፩፻፹፬ ፩፻፹፮ ፩፻፹፯ ፪፻፱

ዮሐኒ /አባ/ ፴፬

ዮሴፍ /ግራዝማች/ ፩፻፺፪ ፩፻፺፱ ፪፻፪ ፪፻፲፩

ደ

ደራ ፹፮ ፩፻፲፯ ፩፻፸፫

ደምቢያ ፩፻፹፭ ፪፻፴፮

ደስታ ብጡል ፩፻፴፰

ደስታ ተድላ /ራስ/ ፩፻፮

ደሳርዛከ ፩፻፶፭

ደረሶ /ራስ/ ፩፻፳፬ ፩፻፳፯ ፩፻፳፰

ደርቡሽ ፩፻፷፱ - ፩፻፸፩

ደብረ ኃይላ ፪፻፴፫ ፪፻፳፬

ደብረ ሊባኖስ ፵፫ ፷፫ ፷፭ ፩፻፮

ደብረ በግዕ ፹፱

ደብረ ብርሃን ፷፭ ፹፯

ደብረ ታቦር ፩፻፳፬ ፩፻፴፪ ፩፻፸፩

ደብረ ተጎሥሥ ፪፻፶፩

ደምቢያ ፩፻፹፮

ደንገል በር ፩፻፪
ዲናሚት ፪፻፵፬
ዳማ ፸፩
ዳምጠው /ፊታ/ ፪፻፴፫
ዳርጌ /ራስ/ ፹፬ ፹፯ ፺፫ ፩፻፳፬ ፩፻፸፬ ፩፻፹፫ ፪፻፲፰
ዳን ፯
ዳዊት ዘውዴ /ዶክተር/ 27
ድልነድዓ 1. ፲፩ ፳፬ ፳፰
ድልነሴ /ልጅ/ ፪፻፵፭
ድሬዳዋ ፪፻፷፬
ዶባ ፳፰ ፷፯
ዶቃቂት ፶
ዶጋዓሊ ፪፻፲፱

## ገ

ገሆር /መንዝ/ ፵፩
ገላን ፷፯
ገሪማ /አባ/ ፰
ገርማሚ /አቶ/ ደጃዝማች/ ፺፩ ፻፯ ፩፻፱
ገበየሁ /ፊታ/ ፪፻፴፯ ፪፻፵ ፪፻፵፩ ፪፻፶፪ ፪፻፶፰
ገበያነሽ /ወ/ሮ/ ፺፫ ፺፭
ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ፩፻፳
ገብረ መስቀል 10.
ገብረ መስቀል አጼ ፳፪ ፳፫
ገብረ መስቀል /ቢትወደድ/ ፩፻፴፬ ፩፻፹፭
ገብሬ ፩፻፴፰
ገብረ ማርያም /አዛዥ/ ፩፻፹፯
ገብረ ሥላሴ ጸሐፌ ትእዛዝ 11.
ገብረ ሥላሴ /እጨጌ/ ፪፻፫
ገበር ኪዳን /ራስ/ ፩፻፴፬ ፩፻፹፭
ገብረ እግዚአብሔር /መምሕር/ ፪፻፴፫
ገብረ እግዚአብሔር /ደጃዝማች/ ፪፻፶፫
ገብሩ ፷፰
ገነሜ /ቀኛ/ ፪፻፪ ፪፻፴፫
ገነት ኀሩይ ወ/ሥላሴ /ወ/ሮ/ 10.
ገነት ኀሩይ ተክለ ማርያም /ወ/ሮ/ 27.
ጉለሌ ፩፻፲፫
ጉልላቴ /ፊታ/ ፩፻፲፰
ጉማ ፩፻፳፬ ፩፻፶፫
ጉባ /አባ/ ፰
ጉራጌ ፶፯ ፷፭ ፩፻፶፫
ጉራዕ ፩፻፵፰
ጉንዳጉንዲ ፩፻፵፰
ጉግሣ ራስ ፷፫
ጉግሣ /ራስ/ ፩፻፴፰
ጉዲት ፳፰
ጉድሩ ፩፻፳፱
ጊቤ ፩፻፶፫ ፪፻፴፮
ጊዮርጊስ /አባ/ ዘጋስጫ ፵
ጊዳ ፪፻፴፮
ጋሊያኖ /ማጆር/ ፪፻፴፩ ፪፻፵፪ ፪፻፵፮ ፪፻፵፯ ፪፻፵፰
ጋላ /ኦሮሞ/ ፷፭
ጋንዶልፌ /ጄኔራል/ ፪፻፲፮ ፪፻፲፯
ጋዛ ፲፩ ፲፪ ፲፬
ጋዲሎ ፺፰
ጌስ ፷፪
ጌዴዎን /መስፍነ እስራኤል/ ፮
ጌዴዎን /ዘፈላሻ/ ፳፮
ጌራ ፩፻፶፫
ግሎባላይዜሽን ፪፻፸፫
ግሸን ፪፻፴፩
ግሼ ፶፯ ፷፯
ግብጽ 2. ፯ ፴ ፴፩
ግራኝ መሐመድ ፵ ፵፩
ግርማ ሥላሴ /መምሕር/ ፩፻፲፮
ግርማዊነታቸው ፪፻፴፯
ግዛው ፩፻፯
ግፋወሰን /ሻቃ/ ፸፪
ጎኅጽባሕ /መጽሐፍ/ ፪፻፷፮ ፪፻፷፰
ጎሜ ጎሹ ፶፫
ጎረቤላ ፷፩
ጎርዶን ፓሻ ፩፻፵፪
ጎበና ዳጪ /ራስ/ ፺፮ ፩፻፲፮ ፩፻፳፬ ፩፻፳፮ ፩፻፳፯ ፩፻፪፶፪ ፩፻፶፫
ጎበዜ /ደጃዝማች/ ፩፻፵
ጎበዝአየሁ ፪፻፵፩

ጉንች ፩፻፮

ጉንጂ ፶፱

ጉንደሬ ጦር ፩፻፭

ጓንጉል ብሩ /ደጃዝማች/ ፪፻፴፩

ጓንጉል ዘገየ /ደጃዝማች/ ፪፻፴፯

### ጀ

ጀር ገዳም ፩፻፲፫

ጀርመን ፪፻፷፪ - ፪፻፸፫

ጂሎ /አቶ/ ፸፩

ጂማ ፩፻፷፩ ፩፻፷፱

ጂቡቲ ፪፻፴፫

ጃራ ፳፱

ጃርሶ ፺፪

ጃፓን 3. ፪፻፳፩ ፪፻፸፪ ፪፻፸፫ ፪፻፸፬ ፪፻፸፮ ፪፻፸፯ ፪፻፸፱ ፪፻፹

ጃንሆይ ፺፰ ፪፻፴፰

ጄኔቫ 12. ፪፻፸፫

ጄኔ /ጄኔራል/ ፩፻፶፱

ጄዝዊት ፩፻፲፱ ፩፻፷

ጆቴ /ደጃዝማች/ ፩፻፶፫ ፪፻፴፰

ጅጅጋ /የሸዋው/ ፩፻፲፰

ጅፋ ፩፻፲፪

### ጠ

ጠለምት ፪፻፶፫

ጠምቄ ፹፮

ጠንቀኛ /አቶ/ ፸፪

እገዴ ፪፻፴፩

ጢሮስ ፲፭

ጣርማበር ፶፰

ጣይቱ /ወ/ሮ/ ፳፪ ፳፬

ጣይቱ /እቴጌ/ ፩፻፴፯ ፪፻፫ ፪፻፭ ፪፻፮ ፪፻፲፫ ፪፻፲፬ ፪፻፴፮ ፪፻፵፭ ፪፻፶፮ ፪፻፶፯

ጦና /ካዎ/ ፪፻፴፰

### ጨ

ጨለቆት ፪፻፵፫

ጨለንቆ ፩፻፶፯

ጨሉ ፩፻፶፬

ጨሊያ ፩፻፷፱ ፩፻፶፫

ጨንፐ ፶፰

ጨርጨር ፩፻፶፯

ጨጨሆ ፩፻፺፮ ፪፻፴፮

ጫጫ /ደጃዝማች/ ፪፻፶፯

ጫጫ /ቦታ/ ፶፯

ጭሬደን /ወንዝ/ ፩፻፲፮

ጭኒ ፩፻፷፮

### ጰ

ጳውሎናዊ /አበባ/ ፪፻፹

ጴንጤሊውን /አባ/ ፳

ጴጥሮስ /ጳጳስ/ አቡነ ፩፻፹፮

### ጸ

ጸጋዘአብ ፪፻

ጽሕማ /አባ/ ፳

ጽዮንሞገሳ ፪፻፳፪

### ፈ

ፈላሾች ፷፮ ፶፪

ፈረስማይ ፪፻፵፱

ፈረንሲስ /ፈረንሣይ/ ፸፱ ፹ ፹፩ ፪፻፸፫ ፪፻፸፬ ፪፻፸፭

ፈንታ /አንጣጭ/ ፩፻፺፯

ፈንግል /በሽታ/ ፺፪

ፊሊጶስ ፲፩ ፲፪ ፲፬

ፊንፊኔ ፳፰

ፋሲል /አጼ/ ፩፻፷

ፋሺስቶች 1. 2. 9

ፋኖ ፪፻፶

ፌልተር /ሙሴ/ ፪፻፵፮ ፪፻፵፯

ፌንክስ አዳራሽ ፪፻፸፱

ፍሎርንጻ /ፍሎሬንስ/ ፵

ፍሬምናጦስ ፲፭

ፍራንሼ ደስፐሬይ /ማርሻል/ 20.

ፍቅሬ ግንብ ፩፻፯

ፍቼ ፻፲፰

ፎገራ ፩፻፸

### ፐ

ፓሪስ ፪፻፸፫

ፓንክኽርስት ሲልቪያ ፪፻፳፫


ፓንክኽርስት ሪቻርድ /ፕሮፌሰር/ 26.

ፓርቲኒ /ሌየተናንት/ ፪፻፵፬

ፖርቱጊዝ ፵፪ ፪፻

ፖርታል ሰር ሔርበርት ፭፻፳፭ - ፭፻፳፯

ፖቲ ፭፻፳



## ስለደራሲው በጥቂቱ

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በመኻል ኢትዮጵያ በሰሜን ሸዋ በመርሐቤቴ አውራጃ በታች ቤት ወረዳ ረመሸት ቀበሌ ደን አቦ ገዳም በ፲፰፻፸፮ ዓ.ም ተወለዱ። ሲወለዱ የተሰጣቸው ስም ገብረመስቀል ነው። ትምህርታቸውን በደን አቦ ገዳም ጀምረው ሰላሌ ስሬ መድኃኔዓለም የዜማ ትምህርት አጠናቀዋል ከዚያም ወደ እንጦጦ ራጉኤል ሄደው በአጭር ጊዜ በቅኔ ትምህርት በከፍተኛ ማዕርግ ተመረቁ። አዕምሮአቸው ከማንም የበለጠ ብሩህ ነበርና መምሕራቸው ገብረመስቀል የተባለውን ስማቸውን ለውጠውላቸው ኅሩይ በማለት ስለሰየሟቸው ስማቸው ኅሩይ ሆነ። ይህም በግዕዝ ምርጥ ማለት ነው።

በ፳፫. ዓመት ዕድሜያቸው ወ/ሮ ሐመረ እሸቴን በቤተክርስቲያን ደንብና ሥርዓት አገቡ። ከጋብቻው አራት ሴቶችና ሁለት ወንዶች ልጆችን አግኝተዋል፡-- በ፲፱፻፫- ዓም በእንግሊዙ ንጉሥ ጆርጅ ፭ኛ ሥርዓተ ንግሥ ላይ በዚያን ጊዜ ደጃዝማች (በኋላም ልዑል ራስ) ካሣ መሪነት በተጓዘው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን አባል ሆነው ወደ ሎንዶን ሄደዋል። በእንግሊዝ አገር በበዓለ ንግሡ ከተገኙ በኋላ አክስፎርድ ዩኒቨርስቲን፣ ፓሪስን፣ ሮምን፣እስከንድርያን ካይሮንና ኢየሩሳሌምን በመጐብኘታቸው ጉብኝቱ የአመለካከት አድማሳቸውን ይበልጥ በማስፋቱ ስለትምህርት፣ ስለምርምርና ስለዘመናዊ ሥልጣኔና ጥበብ ያደረባቸው ግንዛቤ በዘመኑ- በሀገራችን ከነበሩት ሰዎች ልዩና ድንቅ እንዲሆኑ አብቅቷቸዋል። በዚህም ወቀት ነበሮ ከአለቃ ታዬ ገ/ማርያም ጋሮ ቀደም ሲል የጀመሩትን መጽሐፍ ቅዱስን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አማርኛ ቋንቋ የመተርጐሙን ሥራ አለቃ ታዬ በሌላ ሥራ ምክንያት በማቋረጣቸው ብላቴን ጌታ ኅሩይ የተጀመረውን ትርጉም ጨርሰውት የመጀመሪያው የአማርኛ "መፅሐፍ ቅዱስ ሊታተም ችሏል።

፲፱፻፯ ዓ.ም. ለኣዲስ አበባ ከተማ አስቶተዳደር ዲሬክተር ሆነው ተሾሙ። በዚህ ጊዜ በኢትዮጵያ ለከተማ አስዳደር ሥርዓት ማዘጋጃ ቤት የሚለውን ስያሜ በመጀመሪያ ያወጡለት እርሳቸው ናቸው። የከንቲባውን ጽ/ቤት በአዲስ መልክ አደራጁ። የከተማውን የቦታ ካርታ የቀረጥና የግብር አሰባሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ ለከተሜው ነዋሪ የፈጠሩለት እሳቸው ናቸው። በ፲፱፻፲ ዓ.ም. ብላታ ተብለው በልዩ ለተቋቋመውና የውጭ አገር

ሰዎችን በሚመለከተው የዳኝነት ጉዳይ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆነው ተሾሙ። ከ፲፱፻፲፪ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፲፱ ዓ.ም. የመንግሥት አማካሪ ሆኑ። በዚያንም ጊዜ ከኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ከልዑል ራስ ተፈሪ መኩንን ጋር ሆነው አውሮፓን ጎበኙ በ፲፱፻፲፱ ዓም ብላቴን ጌታ ተብለው እስከ ሚያዝያ ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዲሬክተር ሆኑ ከ፲፱፻፳፪ ዓ.ም አስከ ዐረፉበት መስከረም ፪ቀን ፲፱፻፴፩ዓም. ድረስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በመሆን አገልግለዋል። ስለመንግሥት ሥራም በየጊዜው ወደአውሮፓና አሜሪካ አገሮች እየተላኩ በመሄድ የተላኩባቸውን ጉዳዮች በጥሩ አከናውነዋል። ከውጭ አገር ጉብኝታቸው የመጨረሻውና እጅግ ደማቅና ውጤታማ የሆነው የጃፓን ጉብኝታቸው ነበር። በዚህም ላይ በተጨማሪ አዲስ ለተቋቋመው የኢትዮጵያ ቀይመስቀል ማኅበር የመጀመሪያው ሊቀመንበር ሆነው የኢጣሊያ ፋሺስቶች ወረራ ከመጀመሩ በፊት በጥድፊያ ብዙ ዝግጅት እንዲደረግና በየጦር ግምባሩ ሁሉ የቀይ መስቃል እንዲሰማራ ብዙ ደክመውበታል።

ይህ ሁሉ ከባድ ሥራና ኃላፊነት እንዲሁም የጉዞና የጉብኝት አድካሚ እና ተደራራቢ ጫና' ቢኖርባቸውም ከቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ ባገኙት ጥቂት ትርፍ ጊዜ ሌሎች የውጭ አገር መጻሕፍትን በማንበብና ይበልጡኑም ደግሞ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን እራሳቸው በማዘጋጀት ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲዳረስ አድርገዋል። ዕውቀት እንዲስፋፋም ብዙ ጥረዋል ከሁሉም በላይ ግምባር ቀደም የዕውቀት ዐርበኛ ናቸው በመሆናቸውም ከሃያአንድ ያላነሱ ልዩልዩ መጻሕፍትን ደርሰዋል። ይህ “ኢትዮጵያ ታሪክ ከንግሥተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል" የተባለው የመጨረሻው ድርሰታቸው ነው። የደራሲውን የአጻጻፍ ስልት በጥሞና እና በትኩረት ለሚመረምር አንባቢ በዐረፍተ ነገሮቹ አጫጭርነት፣ በቃላቱ ሁኔታን ገላጭነት፣ ለኹነቱ ምክንያትና ማስረጃን በማቅረብ ረገድ የአንባቢን ስሜት በታሪኩ ማርኮ እየሳበ የሚወስድ እንጂ ለአዕምሮ የቸከና አሰልቺ ያለመሆኑን በተጨማሪ ወደዚያውም ስለሚገልጥለት ወደሚቀጥለው ታሪክ እንዲያልፍ ይገፋፋዋል እንጂ አይገታውም።

## የደራሲው ሥራዎች

1. ከንግሥተ ሳባ እስከ ታላቁ ዐድዋ ዘመቻ (**ታሪክ**)
2. ኢትዮጵያና መተማ (**ታሪክ**)
3. ዳግማዊ ቴዎድሮስ (**ታሪክ**)
4. ደስታና ክብር (**ታሪክ**)
5. የሕይወት ታሪክ (**ትምህርት**)
6. ዋዜማ (**ታሪክ**)
7. ማኅደረ ብርሃን ሀገረ ጃፓን (**ታሪክ**)

8. በዕድሜ መሰንበት ሁሉን ለማየት (**ታሪክ**)
9. መጽሐፈ ቅኔ (**ግጥምና ቅኔ**)
10. ወዳጄ ልቤ (**ልብወለድ**)
11. የልብ ሐሳብ (**ልብወለድ**)
12. ዐዲስ አለም (**ልብወለድ**)
13. ጎሐ ጽባሕ (**መልክ፥ ገድልና: ነገረ መለኮት**)
14. ጥሩ ምንጭ (**መልክ፥ ገድልና ነገረ መለኮት**)
15. ስኳርና ወተት (**ተረቶችና ቀልዶች**)
16. ለልጅ ምክር ላባት መታሰቢያ (**ትምህርት**

በሴንትራል ማተሚያ ቤት ታተመ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY